# በዓሉ ግርማ

# ኦሮማይ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
አዲስ አበባ · ኢትዮጵያ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

ኰ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
**Kuraz Publishing Agency**
✆ 11 27 19 • ☐ 30933
አዲስ አበባ · ኢትዮጵያ
***Addis Ababa · Ethiopia***

መጀመሪያ በ፲፱፻፸፭ ዓ.ም. ታተመ ።
በድጋሚ በ፲፱፻፹፪ ዓ.ም. ታተመ ።

የሽፋን ስዕል ፡ ጥበበ ተርፋ

በሌ ማተሚያ ቤት ታተመ

# ማስታወሻ

ሐቀን ለማሳወቀ ራሱን ለሳልፎ ለመታሠር ፥ ለመሰቃየት ፤ ለሞት የበቃ - ልጆቼን ፥ ቤተሰቤን ሳይል ታፍኖ ወጥቶ የቀረውን ተወዳጅ ደራሲ ባለቤቴን በጣም አከብረዋለሁ ፥ አደንቀዋለሁም ።

በሚወዳቸው ልጆቹና በእኔም በባለቤቱ ላይ ከፍተኛ ሀዘንና ጭንቀት ቢደርስብንም አንማረርበትም ፤ ለእውነት መቆምን በተግባር ያስተማረን ነውና ።

ዘጠኝ ዓመት ያስቀጠረ ቢሆንም እውነት ጊዜዋን ጠብቃ እነሆ ዛሬ የህይወት መለዋዕት የተከፈለበት ይህ መጽሐፍ ለመታተም በቀቷል ።

እኔም ሆንኩ ልጆቼ እያስታወስነው ፥ እያከበርነው እንኖራለን ፤ ከሱ የሚበልጥብን የለንምና ። ፍርዱን ግን ለሰፊው ሕዝብ እተወዋለሁ ።

ለልማዝ ለበራ
ነሐሴ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም.

# ገጽ አንድ

ይህ የጸጋዬ ኃይለማርያም ቁንጽል ታሪክ ነው ። ጸጋዬ ኃይለማርያም ማነው? አትችኩል ። በዚህ ዓለም ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ? ባይቸኩሉም ሕይወት ራሷ አጭር ናት ። ታሪኩን ራስህ ትደርስበታለህ ። በራሱ ቋንቋና አስተሳሰብ ፣ ስሜትና እይታ ፣ ድርጊትና ዝምታ ጸጋዬ ራሱ ታሪኩን ይገልጽልሀል ።

እሺ እሱስ ይሁን ፣ ይህን የምነግራችሁ እኔ ማነኝ? ግድ የለም ። የተለየ ስምና መልክ ፣ ጊዜና ሥፍራ የለኝም ። እኔ ነኝ ማለት ይበቃል ። ነበርኩ ፣ አለሁ ፣ እኖራለሁ ። ጸጋዬ ውሱን ተራ ሟች ስለሆነ በሁሉም ጊዜና ቦታ የመገኘት ችሎታ የለውም ። ስለዚህ እሱ በማይገኝበት ጊዜና ሥፍራ አንዳንዴ ብቅ እላለሁ ። ማን ይሆን? ብለህ አትመራመር ። ጠቃሚ አይደለም ። ግን የሰው ሞኝነት ማየት አልወድምና ከምትጨነቅ ልንገርህ ። ደራሲው ነኝ ።

ጸጋዬን ከራሱ ይበልጥ አውቀዋለሁ ። የእግዜር በግ ነው ። በሕይወት የሚያየውን ነገር ሁሉ ይወዳል ። ውዴታው ብዙውን ጊዜ ከአቅሙ በላይ ይሆንበታል ። በዓለም ላይ ለሚያየው ውበት ሁሉ ልቡ በቂ ቦታ ስለሌለው የሚጨነቅ ፣ ግን ተራ ሟች የሆነ ፍጡር ነው ። እንዲያውም በቅርብ ካወቁት ሞኝ ነው ። ግን ማነው ሞኝ ያልሆነ! እንዳልኩት ያየውን ነገር ሁሉ ይወዳል ፣ እና ሁሉንም ያጣል ።

ጸጋዬ ራሱ ቢናገር ይሻላል ። የት ቢጀምረው ይሻል ይሆን? ችግሩ ምንድነው? የሕይወት ሂደት የሚጀመርበትንና የሚፈጸምበትን በውል የሚያውቅ ማን አለ? ቁንጽል ታሪኩን የትም ሊጀምረው ይችላል ። ጸጋዬ ይኸውላችሁ፡-

አ ሮ ማ ይ

# ማ ለ ዳ ማ ለ ዳ
# ጀ ግ ና ሰ ው ማ ለ ዳ

## ምዕራፍ አንድ

ሰኞ ማለዳ ። ታኅሣሥ 19 ቀን 1974 ብርዳማና ጭጋጋም ጧት ። ያው እንደ ፈረደብኝ ዘግይቼ ነበር የነቃሁት ። ከጧቱ ልክ በአሥራ ሁለት ሰዓት ቦሌ ዓለምአቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ መገኘት ነበረብኝ ። የቀረኝ ጊዜ ሀያ ደቂቃ ብቻ ። የእጅ ቦርሳየን ብቻ አንጠልጥየ ተነሳሁ ። ደግነቱ ሻንጣየን ባለፈው ቀን አይሮፕላን ማረፊያ ወስጄ አስረክቤ ነበር ። የጧት እንቅልፍ የሚያስጥለኝ ጠበል ይኖር ይሆን? ሮማን እንደኔ አይደለችም ። የማለዳ ወፍ ናት ።

«ትንሽ ነገር አፍህ ብታደርግ» አለችኝ ሮማን ።

«እረ በፈጠረሽ! ምነው አያወቅሽ? ይልቅ እንሂድ» አልኳት የእጅ ሰዓቴን እያየሁ ። ጧት እህል አይዋጥልኝም ።

«የሞትክ እንቅልፋም!» አለችኝ ሰስ ፣ ውብ ከንፈሮችዋን አጣብቃ በመልቀቅ አጮሀ ። እንዲህ ስታደርግ ራሱዋን የምትስም ትመስለኛለች ሁልጊዜ ። አንዳንዴ ሲላት ጡቷን ወጣ አድርጋ ትስማለች ። ጉድ ናት ፣ ራሷን የምትወድ ትመስለኛለች ። እና ቢሆንስ ። ቆንጆ ናት ። ታዲያ ያኮረፈች መስላ ታየችኝ ። ስታኮርፍ ደስ ትላለች ። ያኮረፈችበትን ምክንያት አላጣሁትም ። ለሦስት ወር ያህል ተለይቻት ወደ ሰሜናዊ የኢትዮጵያ ክፍል ፣ ወደ አሥመራ በምሄድበት ቀን ለመሰነባበቻ ፍቅር እድል አልሰጠኋትም ። ጧት መቸም ጥሎብኝ የለየልኝ ሰነፍ ነኝ ። መጥፎ እድል ፣ ጉዞዬን ባጣፈጠ ፍቅር ብጀምረው

ምን ነበረበት፤ ጉንጭዋን ሳም አደረኩ ። ፈገግ አለች ። ጥርሷ ትኩስ የተፈለቀቀ ለጋ የመስና በቆሎ እሸት ይመስላል ።

«ገላህን አልታጠብክ ። ምን ቢያደርጉህ ይሻልሀል?» አለችኝ ።

«አንቺ አንቺን ነው የምሸተው ። ቫኔል ቱይቭ» አልኳት ።

እውነትም እሷ እሷን ነበር ሁለመናዬ የሚሸተው ። ከትዳሜ ማታ ጀምሮ ካልጋ ውስጥ አልወጣንም ። ቅዳሜና እሑድን አልጋ ላይ መዋል የቆየ ልማዳችን ነው ።

«ለሦስት ወር ገላህን እንዳትታጠብ ገዝቼሀለሁ ። በዛሬው ገብርኤል ይዠሀለሁ ። ግን ምን ያደርጋል ውለህ ሳታድር የሴላ ሴት ጠረን ትወስዳለህ ። አንተ በሄድክበት የምትለምድ ፍጡር ነህ ።» አለች ።

የቤቱን ቁልፍ በሙሉ ለሮማን ከሰጠኋት በኋላ ተያይዘን ወጣን ። ደግነው ፣ መኪናየ እንደ ልማዷ ግፉኝ አላለችም ። ሆኖም እንደ ልቤ ለመብረር አልቻልኩም ። መንገዱ ሁሉ ስፍር ቁጥር በሌለው ሰው ተጣቧል ። አብዛኛዎቹ ሴቶች ነበሩ ። ካቅም በላይ ሰው የጫኑ ታክሲዎች ይርመሰመሳሉ ። አመል ሆኖባቸው ሰው ታክሲ ባለ ቁጥር ባገኙበት ቦታ ፍሬን ይይዛሉ ። ከመጠን በላይ ሰው የጫኑ የቤት መኪናዎችም በብዛት መንገድ ላይ ይታዩ ነበር ። ሁሉም የሚጎዘው ወደ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ነበር ። የታኅሣሥ ገብርኤል ። አልፎ አልፎ ግጭትና አደጋ ይደርሳል ። መንገዱ ይዘጋል ። ጊዜው ደግሞ ይሮጣል ፣ ይከንፋል ፣ እኔም ካንድም ሁለት ጊዜ የግጭት አደጋ ሊደርስብኝ ነበር ። የማልራገመው ርግማንና የማልሳደበው ስድብ አልነበረም ፣ ከሰማይ በታች ። ሰው ሲቸኩል ለምን እንከን እንደማያጣው አይገባኝም ።

«እረ በፈጠረህ ቀስ በል» አለችኝ ሮማን ሰውነቷ በፍርሀት እየተኮማተረ ።

መቾም ለነፍሷ በጣም ስሱ ናት ፣ ሮማን ኀለተመርቅ ። አያስደንቅም ። እንከዋን እሷ እኔም እሳሳላታለሁ ። ያያት ሁሉ ይሳሳላታል ። ከእግር ጥፍሯ እስከ ራስ ጠጉሯ በዓይናቸው እንደ ሽንኩርት ላጥ ያደርጓታል ። ባዩዋት ቁጥር ። ይቀኑባ ታል ። «እድሉ ሆኖ ሴቶች አይወዱኝም» ትላለች ። እሷም ሴቶ ችን እንደጦር ነው የምትፈራው ፣ ምናምን ያቀምሱኛል በማ ለት ። ያለ ሴት ጠላት የለኝም ትላለች ። አፈር የሚነካው ገላ ያላት አትመስልም ። እግዜር እጁን ታጥቦ ያለ የሌለ ጥበ ቡን የጨረሰበት ገላ! ምነው አያሳሳ! ባይኔ ሙሉ ተመልክቼ ኳት ፣ እንደ አዲስ ሰው ። ጡቶቿ ጥቁር ሹራቧን ወጥረው ይዘዋል ።

«አይሮፕላኑ ቂም እኔን የሚጠብቀኝ መሰለሽ!» አልኳትና ፍጥነት ጨመርኩ ።

«ሬሳህ እንዳይደርስ ብቻ ፣ ፍሬን.........»

«መቃብሬ ላይ ቂጣ የምታለቅስ እንዳቺ ያለች ውብ እጮኛ ካለኝ ሞት ለምኔ? አጥንቴ ይለመልማል» አልኳት ። «ገናን ውላ ችሁ ብትሄዱ አሁን ምን ነበረበት?» አለች ።

«የኤርትራን ትንሣኤ እንዴት አድርገን?»

«አምና ገናን የት እንዳሳለፍን ትዝ ይልሀል?» አለችኝ ።

«አሊጋ ውስጥ ይሆን?»

ሰካራም ። ራስ ሆቴል ነበር.... እና እውነትም ሰክረህ ነበር ።»

«ውበትሽ ይሆናል ያሰከረኝ.........»

«ኤጭ እቴ!» አለች ፣ «ለሁሉም ነገር ቸኩሎ መሞት እቴ! ነጋ ጠባ ዘመቻ ። እድገት በኅብረት ብሎ ዘመቻ ። ለጦርነት ዘመቻ ። የኢኮኖሚ ግንባታ ዘመቻ ። ማይምነትን ለማጥፋት ዘመቻ ። የቁጥጥር ዘመቻ ። አሁን ደግሞ የኤርትራን ችግር ለመፍታት ዘመቻ ። የዘመቻ ባህል ፈጥረናል ። ያለ ዘመቻ ኖረን የምንሞትበት ቀን መቼ ይመጣ ይሆን?» አለች ፣ እየተነጫነጨች ። ሲላት መቾም ተናጋሪ ነች ።

«ጉዞአችን ረጅም ፤ ተስፋችን ሩቅ ፤ ችግራችን ብዙ ፤ ምን ይደረግ ብለሽ ነው?» አልኳት የእቧን አነጋገር ለማስመሰል እየሞከርኩ ።

«ኤጭ እቴ! አንተ ታሾፋለህ» በሚለት ንግግሯን ቀጠለችና፣ «አም እቴ በናንተ ቤት የኢትዮጵያ ችግር ሁሉ ባዋጅና በዘመቻ እንደ በጋ ጉም በኖ የሚጠፋ ይመስላችሁዋል ? ድንቄም! እንዲህም አድርጎ የለም ። መሠረታዊ ችግራችን ያይምሮ ድኀነት መሆኑ ቢገባን ጥሩ ነበር ። ኋላ ቀርነት ሌላ ትርጉም የለውም ። ያዋጅ ፣ የማጠናከሪያ ያዋጅ ጋጋታ ፤ በመቻ ብሎ ሚጫታ ፤ ምን ፋይዳ ይሠራል ብለህ ነው? ትርምስ ፣ መተራመስ ፣ ተተራምሶ መሞት እቴ ። መጥኔ» አለች ።

«ሩጫ ላይ ያለች አገር ናት ። ቢከፋም ቢለማም ድርጊት ፤ አዲሱ ትውልድ የድርጊት ትውልድ ነው ። ጊዜ ያጥረናል ። ጊዜ የለንም ። ችኩል ትውልድ ነን ። ያበደ ትውልድ ። እብዶች ነን እውነት ። ያሮጌው ትውልድ መጣጭ ያዲሱ ትውልድ የበኩር ልጅ ያንዱ መጨረሻ ፣ የሌላው መጀመሪያ መሆን እብደት ነው ። ያሮጣል » አልኳት ።

«የት ለመድረስ?» ብላ ዝም አለች ።

ነገሩ አልጣማትም ። ያለ ፍቅር የሚጥማት ነገር የለም ። የንጋት ኮከብ የሚመስሉት ዓይኖቿ እንባ አቅርረዋል ።

የመኪናዋ ፍጥነት በሰዓት ወደ መቶ ኪሎ ሜትር ደርሶአል ። ከአብዮት አደባባይ በኋላ ወደ ቦሌ የሚወስደው መንገድ ደኅና ነበር ።

«አይዞአችን ሮሚዬ» አልኳዋት በቀኝ እጄ ትከሻዋን መታ መታ አድርጌ ፤ «ሦስት ወር ከድል በኋላ ስመለስ እንጋባለን ጉሮ ወሸባዬ እንዲያ እንዲያ ሲል ነው ግዳዬ እያልሽ እንድትቀበይኝ ብቻ ። ደሞ አንድ ነገር እንዳትረሺ ። እሑድ እሑድ ለዘማቹ ጓዴ ለጸጋዬ ኃይለማርያም እያልሽ ዘፈን እንድትመርጭልኝ ፣ እሺ?» አልኳት ፣ እየቀለድኩ ።

ደረቁ ቀልዶ አሳሳቃትም ። ይተናነቃት የነበረው እንባ ኮለል ብሎ ወረደ ፣ የማለዳ ጤዛ መስሎ የማለዳ ጸሐይ የሚመስሉትን ጉንጮቿን እያቋረጠ ። ሙሉ ጨረቃ ከሚመስለው ከብ ፊቷ ላይ ከንብል ያለው ረጅም ጥቁር ጠጉርዋን ወደ ላይ መታ አድርጋ ፣ «ይህ ዘመቻ በኔ ላይ ነው የመጣው ። ባይሆን ኖሮ.....» አለችና መሀረብ ከቦርሳዋ አውጥታ እንባዋን ጠረገች ። ቦርሳዋ ሲከፈት የገነት በር እንደተከፈተ ያህል ጥሩ መዓዛው መጥቶ አፍንጫ እውድ ያደርጋል ።

ጥር አጋማሽ ላይ ልንጋባ አቅደን ነበር ። ዝግጅቱን ከጀመርን ቆይተናል ። ሁለታችንም የሥርጋችንን ዕለት በታላቅ ጉጉትና ናፍቆት ነበር የምንጠባበቀው ። ከተጫጩን ድፍን ሁለት ዓመት ሆኖአል ። ሮማን ኅለተወርቅን እስካገኘሁ ድረስ አገባለሁ የሚል አሳብ አልነበረኝም ። ጋብቻ የሚሉት ጣጣ በሳቤ መጥቶ አያውቅም ነበር ። ድንገት ተገናኘንና ጋብቻ የሚሉት ተላላፊ በሽታ ያዘኝ ። ከዚህ በፊት ለብዙ ጊዜ እንተዋወቅ ነበር ። እን ዲያውም የጥሩ ጓደኛዬ እህት ነበረች ። ኋላ ወንድሟ ሞጆ ላይ በመኪና አደጋ ሞተ ። መኪና ሲነዳ እብድ ነበር ። ፍጥነት ይወዳል ። የመኪናው ድምጽ ከሩቅ ሲሰማ የመንደሩ ሰዎች ያ እብድ መጣ ልጆቻችሁን ያዙ! ይባባሉ ነበር ። አቧራ ይቦናል ። ዶሮዎች እያስካኩ በየአቅጣጫው ይበራሉ ። ያዲስ አበባን ሴይቼንቶ ነጂዎች ሽብር የሚለቅባቸው እሽከርካሪ ቢኖር እሱ ብቻ ነበር ። ሮማን ከእሱ መኪና ላይ ወጥታ አታውቅም ። ፍጥነት ሕይወት ነው የሚል ፈሊጥ ነበረው ። የሚወደው ነገር ገደለው ። የጋብቻ በሽታ የለከፈኝ ምሽት ፣ እሷ ፣ ወንድሟና አንድ ጓደኛዋ ራስ ሆቴል ነበሩ ። ራስ ባንድ ይጫወት ነበር ። ያው እንደ ልማዴ ብቻዬን ስንጠለጠል ነበር የመጣሁት ። ማታ ብቻዬን ስዞር ጀብደኛነት ይሰማኛል ። ምሽቱ እንደ ቆማር ጨዋታ ይሆንብኛል ። አንዳንድ ምሽት ይቀናል ። ሰው ብቻውን ወጥቶ ከቆንጆ ቤት ጋር ሲመለስ ፣ ከዚህ የበለጠ ትርፍ ምናለ! አንዳንድ ምሽት ደግሞ ያላሰቡትን ኪሣራ አስከትሎ ባዶ እጅ ወደ ቤት ይመልሳል ። ሕይወት ነው ፣ መገናኘት ፣ መለያየት ። ወንድሟ ጋበዘኝ ። ጓደኛዋ ደስ አላለውም ። ሞቅ ብሎኛል ። ዳንስ እስክን ሳኋት ። ጠጋ አለችኝ ። ጡቶቿ ገፈተሩኝ ። ሽቶዋ ሳበኝ ። ከሙዚቃው ጋር የተፈጠረች ትመስላለች ፣ ስትረገረግ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ውበቷ ማረከኝ ። በፊት ውበቷ አይታየኝም ነበር ።

ለምን እንደሆነ እንጃ በፊት ሳያት እሸሻት ነበር ። ሁል ጊዜ ከእጅዋ የማይጠፋው መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን አይቀርም ባየኋት ቁጥር ከሩቅ የሚያባርረኝ ። ሠይጣን ሆኘ አይደለም ። ሀይማኖት አይስበኝም ። የኔ ሀይማኖት ሕይወት ነው ። መጽሐፍ ቅዱስን የማነብበት ምክንያት ቢኖር በሊትሬቸርነቱ ነው ። ግሩም ሊትሬቸር ነው ። ቡተለይ ፣ መክብብና መኃልየ መኃልይን ማንበብ ደስ ይለኛል ። አንድ ቀን ፣ «ፍቅር በተግባር እንጂ በጸሎት አይሆንም ። የቅርቡን ቁተሽ ከሩቁ ላይ ምን እንጠለጠልሽ? ገነትን እዚሁ ምድራችን ላይ ልንፈጥራት እንችላለን ባካፋና በዶማ ። ጊዜሽን በከንቱ አታባክኚ» ካልኳት ወዲህ ተጠግቻት አላውቅም ። እሷም አትጠጋኝም ። ቀንድ የሌለው ሠይጣን አድርጋ ነበር የምታየኝ ።

እንደሰማሁት አልም ያለች ጴንጤ የሆነችው ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር በሚመታበት ሰሞን ነበር ። ምጽአት መጣ! ንስሐ ግቡ! እያለ ሴቶችንና በተለይም ወጣቶችን የሚያጠምድ አንድ ሰው ጐረቤቷ ይኖር ነበር ። እንደበቱ ይጣፍጣል ፣ ቃላቱ ቅስም ይሠብራሉ ። ቁመናውም ቢሆን ለከቶ አይሰጥም ። ሀብት በእግር ስተት ብላ ቤቱ የገባች ሰው ኘው ። ምናለበትን በማለት ከሰውዬው ጋር ወደ መሠረተ ክርስቶስ ፣ ወደ መካነ ሕይወት ፣ ራጉኤል ትሔድ ጀመር ። ሽባው ሲነሳ ፣ ዲዳው ሲናገር ፣ እውሩ ዓይኑ ሲበራ ፣ በሽተኛው ሲፈወስ...... ጸሎት የሚሠራውን ተአምር አየች ። አማኝ ሆነች ። በዓለም ተስፋ ቆረጠች ። ቀለቧ ጸሎት ብቻ ሆነ ፣ ትራሷም መጽሐፍ ቅዱስ ። አዲስ አማኝ ከጳጳሱ ይበልጥ ተቆርቋሪና ተሟጋች ይሆናል እንዲሉ ፣ እሷም በተራዋ የለየላት ሰባኪ ሆነች ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ወሬ አልነበራትም። ያገኘችውን ሰው ሁሉ «የእግዜር ቃል እንስማ» ሳትለው አትለቀውም ።

አማኝ መሆኗ ከተረጋገጠ በኋላ ሰውዬው ቤት እየተገኘች ሌሎች ወንድሞችና እህቶችን በቅርብ እንድትተዋወቅ ተደረገች። እዚያው ዘወትር ማምሽት መጣ ። ከጥቂት ምሽቶች በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ቀርቶ ፖለቲካዊ ውይይት እየጠፈ ፣ ጸሎት ቀርቶ ሙዚቃ እየደራ በለስላሳ መጠጥ ፈንታ ቢራና ውስኪ እየተደ ረደረ ይሔድ ጀመር ። እዚያ ቤት በየምሽቱ የሚሰበሰቡት እህቶ

ችና ወንድሞች ምንነትና ማንነት ቀስ በቀስ እየገባት ሔደ ። ሁሉም ባይሆኑ አብዛኛዎቹ በሀይማኖት ሽፋን ጸረ አብዮት አቋም የሚያራምዱ የፖለቲካ ሰዎች መሆናቸው ገባት ። ተሰፋ የቆረጠ ችው በየጸሎት ቤቱ ድንናል ብለው እንባ እየረጩ የሚመሰከሩት አንዳንድ ሰዎች አስመሳዮች መሆናቸውን በውል በተገነዘበች ጊዜ ነበር ። እምዬ ማርያም ማሪኝ እያለች አዚያ ቤት በገባችበት እግር ተመልሳ ወጣች.....

ሙዚቃው እጅግ በጣም ደምቋል ። ጠጋ አልኳት ፤ በሕይ ወት ሙዚቃ ስልት የምትረገረግ ትመስላለች ።

«መጽሐፍ ቅዱሱን የት ጣልሺውን »አልኳት ።
«ጡቴ ሥር ነው ።»

«ከሰው ልብ የበሰጠ መጽሐፍ ቅዱስ የለም ። እና ደግሞ ከሕይወት የተሻለ ምን ሀይማኖት አለ?» ስላት ነገሬን ቀበል አደረገችና ፤

«እንዴት ተገለጸልህ «ጃል!» ብላ አሾፈችብኝ ።
«ዛሬ ተገለጸልኝ በቃ.....»
«እኮ እንዴት?»

«ውብ ፊትሽ ላይ አየሁት ።»
«ዛሬ ገና ነው ቆንጆ መሆኔ የተገለጸልህ?»
«እንደ እውነቱ ከሆነ አዎን በእውነት እውር ነበርኩ መሰ ለኝ!» አልኳትና ሙዚቃው ሊያበቃ ሲል ፤ «ሌላ ቦታ እንሂድ» በማለት አሳብ አቀረብኩላት ።
«ትእዛዝ ነው ወይስ ጥያቄ ?»
«ጥያቄ ነው ...»
«በቃ?»
«ልመናም ነው ከፈለግሽ ።»
ወንድሟንና ጓደኛውን አሉበት ጥለን ተያይዘን ጠፋን ። ያዲስ አበባ ምሽት ዋጠን ። ይህ የሆነው ከሁለት ዓመት በፊት ነበር ። ከስንት ቀን በኋላ እንደሆነ አላቅም ያ የማይቀረው አርእስቱ ነገር ተነሳ ። ስለ ጋብቻ መነጋገር ጀመርን ። ሴቶች ሲባሉ መቸም አንድን ወንድ የግላቸው እቃ ሳያደርጉ አይተውም ። ሳይጋቡ

ተፋቅሮ መኖር ለምን እንደማይቻል አይገባኝም ። መቸም ፥ ለብዙ ተራ ሟች ሰዎች ጋብቻ እንደ ሞት የማይቀር እዳ ነውና እሺ ብዬ ነጻነቴን ሸጥኩት ። ብቻዬንም መዞር እርም ብዬ ተውኩት ። ልማድ መቸም መጥፎ ነገር ነውና ያለ «ሮሚ» እንዴት መሽቶ ሊነጋልኝ! ሱስ ሆነችብኝ ። እንዲኔ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ተጋብተን ነበር ። ግን እንዴት ተብሎ! ይሆን እናሟላ ፥ ያንን እናድርግ ስትል ይኸውና ስለጎጆ ሳስብ ፥ (አስቤ የማላውቀውን) ሁለት ዓመት አልፎኛል ። ቆኔና የእሷ ብቻ የሆነች ትንሽ ጎጆ ትመኛለች ። ያች ትንሽ ጎጆ ደግሞ በመንግሥት ሠራተኛ ደሞዝ ባንድ ማግስት የምትፈጠር ሆና አልተገኘችም ። ከሁለት ዓመት ትግል በኋላ ያችን የምንመኛትን ትንሽ ጎጆ ልንፈጥር ትንሽ ቀርቶን ነበር ። የቀይ ኮከብ ዘመቻ መጣ ። ግንኙነታችን የሶስት ወር እድሜ ጨመረች ። ወይም ግን ያውቃል? ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል ። ሁሉም ነገር እንዳሰቡት አይሳካም ። ሕይወት እንዲ ዚህ ናት ።..........

መኪናየን ወስጄ ሀንጋሩ መግቢያ ላይ አቆምኩ ። ወታደሩ ፥ ሲሸሉ ይተራመሳል ። ወታደራዊ ማርሽ ከሩቅ ይሰማል ። አምስት ደቂቃ ያህል ዘግይቻለሁ ።

«ሦስት ወር ምናላት ብለሽ ነው? ነገ ናት ። ይልቅ ደስ እን ዲለኝ በፈገግታ ሸኚኝ ፥ እሺ? » በዬ አገጯዋን ይገቱ ወደላይ ቀና አደረኳት ። ልቤ ክፉኛ ተንጠልጥሎአል ።

በግድ ከንፈሮቿን አላቃ ፈገግ አለች ። ፈገግታዋ አላረካኝም ። በኃይል እንድትስቅ በማለት ብብትዋ ውስጥ ገብቼ ኮረኮርኳት ። መኮርኮር አትወድም።ከኮረኮሯት ያሏትን ታደርጋለች።

«በሞቴ ጸግዬ! » ብላ ሳቀች ። ሳቋዋ እንደ ጥኡም ሙዚቃ ደስ ይላል ። ለው እንዳያየን ገልመጥ ፥ ገልመጥ ብዬ የስርቆት ያህል ከንፈሩዋን ከሳምኩ በኋላ የመኪናውን ቁልፍ ሰጥቻት ልወርድ ስል ፥ እጄን ያዝ አድርጋ ፥

«ጸግዬ ፥ ልቤ ፈራ እኔ እንጃልኝ» አለችኝ ።

«የዘማች እጮኛ ቆራጥ መሆን አለባት ። አይዞአችን ። ፈገግ በይ...........»

«ኢኢ እንደሱ ማለቴ አይደለም ።........»

«ታዲያ ምንን»

«አንተ የደረስክበት ሁሉ ቤትህ ነው ። ትለምዳለህ ። ፍቅሬን ብሌላ እንዳትሰጥብኝ ፈራሁ ። ያሥመራ ሹርቤዎች ካይን የቀደሙ ጨልፊዎች ናቸው አሉ.........»

«አንቺን የምታስንቅ ከተገኘች ግን በጨረታ አልገዳ ድም ። ግን አይመስለኝም ። ስጋት አይግባሽ ቻው ። በነገራችን ላይ ይህን የሞተ መኪና ጋራዥ አስገቢልኝ ። እንደደረስኩ እደውልልሻለሁ ።» ብያት እንባዋን ላለማየት ጥያት ሮጥኩ ።

እኔንም ሆዴን ባር ባር ብሉኝ ነበር ። ለሚሞደዱ ሰዎች ሳጥር ጊዜም ይሁን መለያየት መቸም ስቃይ ነው ። ምናልባት የግዜና የቦታ ርቀት የፍቅር ሌቦች ሳይሆኑ ይቀራሉ? እንጃ ። ፍተሻ መናፋን በመዘንጋት እንደሮጥኩ ሄጄ ወደ አይሮፕላኑ ልገባ ስል ደረጃው ላይ ተያዝኩ ። ፍተሻው ጊዜ አልፈጀም ። አንድ ወታደር ዳሰስ ፣ ዳበስ ፣ ቸብ ፣ ቸብ ፣ አድርጎ ለቀቀኝ ። ሊቀ መንበሩ ወደ አይሮፕላኑ በመምጣት ላይ ነበሩ ። ተጉዋዡ ሁሉ ስፍራ ስፍራውን ቀደም ብሉ ይዞአል ። የፕሮቶኮል ሹሙ አፈጠጠብኝ ። ሰው ሁሉ ቀደም ብሉ ስፍራውን ካልያዘ ይጨነቃል ። እድሉን ያግርራል ። ይራገማል ። ይነጫነጫል ። በያዘው ሊቡት መሠረት አሥር አሥሬ ይጣራል ። እኔ ብቻ ነበርኩ ወደ ኋላ የቀረሁት ። ገና ሲያየኝ በታላቅ እፎይታ ተነፈሰና ፣

«ምን ነው ጓድ ጸጋዬ!» አለኝ ።

«እዚሁ ነበርኩኮ» አልኩት በውሸት ፈገግ ብዬ ።

«እናንተን የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሰዎች ምን ቢያደርጉዋችሁ ይሻላል? መቸ ይሆን በተፈለጋችሁበት ቦታ በጊዜ ለመድረስ የምትችሉት? የሆድ ቁርጠት የልብ ቃር.....»

«ኩተታችን ስለሚበዛ ነውኮ» .....

«የዞረ ድምር እየያዛችሁ ነው'ይ ። ጅማ ባርና ሐምሌ 19 ቡና ቤት ለናንተ ስንል ስልክ ካላስገባን አልሆነልንም» አለ ፈገግ ብሉ ።

የሚፈለገው ሰው ሁሉ አንድ ላይ ከተገኘለት መሳቅና መቀለድ ይጀምራል ። ውሸቱን ይቆጣል እንጂ መጥፎ ተፈጥሮ የለ

ውም ። ሲስቅ ጥርሱም ፥ አይኑም ፥ ቦርጩም አንድ ላይ ይስታል ። መልክ መልካም ባይሆንም ፥ ሳቁ ፥ ቀልዱና ፥ ጥሩ ተፈጥሮውና ግልጽነቱ ያቆናጇታል ። ሻለቃ ነው ። የፕሮቶኮል ሹም ከሆነ ወዲህ በወታደር መለዮ ታይቶ አያውቅም ። አይ ቁሊባበስ ማንም ዘንድ የለም!

ያዲሳባ ሲቪልና ወታደራዊ ባለሥልጣን አንድም የቀረ አይመስልም ። አይሮፕላኑ ከፍ እስከ ገደፉ ጢም ብሎ በሰው ተሞልቶአል ። ባለ ቅኔዎች ፥ ዶራሲያን ፥ ሰዓሊዎች ፥ የሙዚቃና የመድረክ ሰዎች ፥ ድምጻውያን ፥ ተዋንያን ፥ ታሪክ ጸሐፊዎች ፥ ጋዜጠኞች ፥ ፊልምና ፎቶግራፍ አንሺዎች.... የማይታይ የሙያተኛ አይነት የለም ። መቸ በዚህ ብቻ ፥ የድርጅት ሰዎች ፥ የእርሻ ባለሙያዎች ፥ የውሀ መሐንዲሶች ፥ የኢንዱስትሪና የንግድ ሊቆች ፥ ወዘተ.... ጦሩም አልቀሩም ። ይህች አይሮፕላን ሰማይ ላይ አንድ ነገር የሆነች እንደሆነ እኔ የለሁበትም አልኩ በልቤ ።፥ በምቾት አለጥልጦ የሚያበራ ፥ በመጠጥና በሲጃራ የነበዘ ፥ እንቅልፍ በማጣት የተንሳቀለ ፥ ሙልጭ ፥ ጨጎጎታም ፥ ረዛም ፥ ጢማም ፥ ሆናም እንደ ፋሲካ ቢላዋ የተሳለ ሰለታም ፊት ደግሞም እንደ ጦጣ ብልጣ ብልጥ ፥ የማላውቀው ወይም የማያውቀኝ ሰው አይሮፕላኑ ውስጥ ያለ አልመሰለኝም ። ሁላችንም ከቅርብም ይሁን ከሩቅ እንተዋወቃለን ። በዚህም ሆነ በዚያ የማይተዋወቅ ሰው የለም ። ሁላችንም ያንድ ትውልድ ሰዎች ነን ፥ ወጣት ችኩል ፥ ምናልባትም ሥልጣን ፈላጊ ። እና ሁላችንም ለአብዮታዊት እናት አገር ፥ ለውዲቱ ኢትዮጵያ ሕልውና ፥ ክብር ፥ አንድነት ፥ እድገት ፥ ብልጽግናና ሰላም ቀናኢ! የሚያስደንቅ የወጣት ሀላፊዎችና መሪዎች ስብስብ ። ምናልባት ያገራቸውን እድል በእጃቸው የጨበጡ እንዲህ ያለ የወጣት መሪዎች ኃላፊዎች ስብስብ የትም ታይቶ አይታወቅ ይሆናል ። አብዮት ነው ። የወጣት አፍላ ጉልበት ። የወጣት ምኞት ፥ የሩቅ ቅርብ ሕልም ፥ ይህች መሬት! ይህች አገር! ይህች ኢትዮጵያ! ያባት አገር ዱር ጋሻ! የናት አገር ሸማ! ያባት ጀግንነት በአብዮታዊ ወጣት ትውልድ ወኔ የታደመባት አገር!

«ሆ ብዬ እመጣለሁ ሆ ብዬ በድል
ጥንትም ያባቴ ነው ጠላትን መግደል.......»

ቦታዬን ባይኔ እፈልግ ጀመርኩ....

«ሚስተር ቲቪ!» አለኝ አንዱ የኪነት ሰው ።
«ወዲህ! ወዲህ!» አለኝ የፕሮቶኮሉ ሹም ።

በጥድፊያ ተከተልኩት ። የሊቀመንበሩ መምጫ ሰዓት ሲቃረብ መቁንጥነጥ ያበዛል ። ተካልቦ ሰው ያካልባል ። ወደ አንደኛ ማእረግ ወስዶ ከደርግ ቋሚ ኮሚቴና ከኢሠፓአኮ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባሎችና ከሚኒስትሮች ጋራ አስቀመጠኝ ።

«ጓድ ፣ ፕሮቶኮል ተሳስቶ እንዳይሆን!» አልኩት ።
«አርፈሽ ቁጭ በይ» አለኝ ። አንዳንድ የሚወዳቸውን ሰዎች 'አንቺ' እያለ መጥራት ይወዳል ።
«እውነቱን ነው ኮ...»
«ቦታሽ ነው ።»

ጓድ ተድላ ረጋሳ የፕሮቶኮል አቀማመጥ የሚያሳስት ሰው አይደለም ። ስለ ፕሮቶኮል አቀማመጥ በጣም ተጠቦ ይጨነቃል ። የያንዳንዱን ሰው ፖለቲካዊ ክብደት መዝና የሚያውቅ በመሆኑ «ጓድ የሥልጣን ተዋረድ ሊቅ» ይሉታል አንዳንድ የደርግ አባሎች ። ነገሩ ቀልድ አይደለም ። ከደርግ አባሎች ጀምሮ ብዙ ባለሥልጣኖች የከርሞ ፖለቲካዊ ክብደታቸውን የሚመዝኑት በእሱ ዓይን ነው ። ካገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ጋር ጎን ለጎን መቀመጥ ወይም ትከሻ ለትከሻ መጋፋት ልብ ያሳብጣልና እኔም ትንሽ ክብደት ብጤ ተሰማኝ ።

አንደኛ ማእርግ ውስጥ ያለው ቱባ ፣ ቱባ ባለሥልጣን ሁሉ ዞር እያለ ፣ ጸጋሽ ታዲያስ? ሲለኝማ ሞቅ ይለኝ ጀመር ። መቸም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያላስተዋወቀኝ ሰው የለም ። ግን ጥያቄ ያቸው የቁልምጫ ሳይሆን ፣ እዚህ ምን ታደርጋለህ? የሚል አይነት ጥያቄ ነበር ። ፊታቸው ላይ ጥያቄው ይነበባል... ሸዋ ማን ቀረ? ወይስ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አሥመራ ተዛውሮ ይሆን?... ሸዋ ላይ ዳመነ የተባለው ዘፈን በእዝነ ልቦናዬ ከሩቅ ሳንዳፍታ ተሰማኝ ። ግን ፣ አንደኛ ማእርግ ውስጥ ከከፍተኛ የአገሪቱ ባለሥልጣኖች ጋር እንዲቀመጡ የተደረጉት እንደኔ ያሉ ሌሎችም ታዋቂ ባለሙያዎች ነበሩ ። ኩሉኔል በትሩ ተሰማ ከግራ ጎኔ ተቀምጦአል ። ወፍራም የለጠለጠ ፊቱ ያው የተለመደው ፍጹም እርጋታ ይታይበታል ። በሦስት መንግሥ

ታት የስለላ ቴክኒክ ማለትም በሲ.አይ.ኤ ፣ በሞሳድና በኬጂቢ የአሠራር ሥልቶች በተለይም ፣ ኅቡዕ ጸረ መንግሥት ድርጅቶ ችን በመስበር የታወቀ የሕዝብ ደኅንነት ሰው ከቶ አይመስ ልም ፣ ሲያዩት ። ደህና ቴጃር ነወ የሚመስለው ። ፈገግታ ከፊቱ አይለይም ። በፈገግታ ሰላም ይላል ። በፈገግታ ያነጋግራል ። በፈገግታ ይሸኛል ። ብዙ አይናገርም ፣ ሚስተር ፈገግታ ። የተገንጣይ ድርጅቶችን ቴክኒክና ታክቲክ እንደ እጁ መዳፍ ያውቃል ይባላል ። ለፈገግታው አጸፋውን መለስኩለት...... ክበስ ተቀኝ በኩል የተቀመጠው ሰው መጽሐፈ ዳንኤል ይባላል ። ፊቱ ትንሽ ናት ። መላጣው እናቱን ሰንጥቆ ወደ ሁዋላ ስለሚሄድ ጭንቅላቱ ለሁለት የተሰነጠቀች ትንሽ የዱባ ቅል ትመስላለች ። ሰውነቱ ቀጭን ሆኖ ቦርጩ ብቻ እንደ ቃልቻ ድቤ ተወጥሮ ጉች ብሎ ይታያል ። ኦይ አለባበስ! መልኩን በአለባበስ ለማካካስ የሚጥር ይመስላል ። ታዲያ የታወቀ የኢኮኖሚ ሊቅ ነው ። በካፒታሊስቱ ሆነ በሶሻሊስት የኤኮኖሚ መርሆዎችና ፍልስፍና ተከኖአል ። በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ከእሱ ጋር ያልደረሰንበት አው ራጃና ወረዳ የለም ። የሶማሌ ወራሪዎች በሐረርጌ ያደረሱትን ጥፋት እንዲያጠናና ሪፖርት እንዲያቀርብ የተቋቋመው ልዩ ብሔ ራዊ ኮሚቴ መሪ ሆኖ ሲሠራ በነበረበት ጊዜ ነው በቅርብ የተዋ ወቅነው ። ያው እንደ ልማዱ አንድ ነገር የረሳ ይመስላል ፣ ግር ብሎታል ። ሁልጊዜ ይሲጋል ። ሲለው መጥቶ በግድ ያናግራል ። ሳይለው ደግሞ ቢያናግሩትም መልስ አይሰጥም ። ይዘጋል ። ራሱንም ሆነ ዓለምንና እግዜርን ያኮርፋል ። እና ደግሞ ሁልጊዜ እንደራበው ነው ። ሆዱን ያካል ፣ ወይም ዝም ብሎ በሽታውን ያዳምጣል ። በዓለም ላይ ያለ የሌለ በሽታ ሁሉ ጓዙን ጠቅልሎ በእሱ ላይ ሰፍሮ የሚኖር ነው የሚመስለው ። ጤና ይስጥህ! አልኩ በሆዴ ። ሆዱን ማከክ ጀምሮአል ።

ከፊት ለፊቴ የተቀመጠው 'የኢትዮጵያ ሱስሎቭ' ነበር ። የታወቀ አይዶሎጂስት ነው ። እውነተኛ ስሙ የሺጥላ ማስረሻ ነው ። ከቁስ ዘር ነው ። የሺጥላ መካከለኛ ቁመት ያለው ቀጭን ፣ ቀላ ያለ መልከ መልካም ነው ። ስለታም ፊቱ እንደ ስለት ይቆርጣል ። ፈገግታውም ቢሆን ስለታም ነው ። ነገሩም ያንኑ ያህል እንደ ስለት ይቆርጣል ። የሚጠቀምባቸውም ቃላት ጠጣርና ስለታም ናቸው ። ብን ያለው ስስ እፍሮ ጠጉሩም የተሳለ ይመስላል ። ከሁኔታው ኩራተኛ ግን ከተጠገት ትሁትና

ገራም ፣ ጨዋታውም ለዛ ያለው ነው ። ግን ባህርይው ምሥጢራዊ ነው ።

ከበስተኋላዬ ኮሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ቁጭ ብሎ ይተክዛል ። ውስኪና የደፈጣ ውጊያ ውል ያሉት ፣ በዓይኑ የሚሄዱበት ይመስል ። በጣም ቀጭን ከመሆኑ የተነሳ በወሎ ረሀብ ጊዜ ከሞት ተርፎ መጠለያ ውስጥ በማገገም ላይ ያለ ሰው ነው የሚመስለው ። እቃ ከቆጥ ላይ ለማውረድ በተለይ የተፈጠረ ይመስል ሰውነቱም ፣ ፊቱም ፣ እግሩም ፣ እጁም ረጃጂም ናቸው ። ለረጂም ጊዜ ተስተካክለሉት የማያውቀው ዞማ ጠጉሩ ተቆጣጥሮና ተገማምዶ ይታያል ። ከሳህል በረሀ አዲስ የመጣ ወንበዴ ይመስላል ።

ጂማ አብረን እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ተምረናል ። በልጅነቱ የጦርነት ጨዋታ ይወድ ነበር ። የመንደሩን ልጆች ሁሉ አሰልፎ ሲያዋጋ ይውላል ። በትውልድ ኤርትራዊ ነው ። አባቱ ግራዝማች ወልዳይ ባህታ በፋሽስት ጦርነት ጊዜ እምቢ ላገሬ ፣ እምቢ ለወገኔ በማለት አንድ ሺ ሰማንያ ኪሎ ሜትር በእግር በመጐዋዝ ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር ተቀላቅለው አምስት ዓመት ሙሉ በዱር በገደሉ ሲዋጉ የኖሩ ስመጥሩ አርበኛ ናቸው ። ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ..... እንዲሉ ፣ እሱም የታወቀ ጸረ ወንበዴ ተዋጊ ጀግና ሆኖአል ። ኮሎኔል ታሪኩ በዚህ መጣ ሲባል ፣ የወንበዴ መንጋ ያንድ ቀን መንገድ ፈርጥጦ ድራሽ አባቱ ይጠፋል ይባላል ። ከለውጊያና ከለጥሩ ውስኪ ሌላ አያውቅም ።

«ጋሼ ፣ ጎኔ ቦታ ይገርልሀለሁ» የሚል ድምጽ ሰምቼ ዞር አልኩ ።

ፍሬው ዘርይሁን ነበር ፣ የሬዲዮ ጋዜጠኛ ። ቁጭ ብዬ በቁመት እኩል ልንሆን ምንም አይቀረንም ። አጭር ነው ። ከእንደሱ ያለ አጭር ሰው እንደዚያ ያለ ወፍራም ድምጽ ሲወጣ ይገርመኛል ። አይኑም ፣ ፊቱም ፣ ጥርሱም አንድ ላይ ይስቃሉ ።

«እዚሁ ነው የምሆነው ። ተራርቀናል ጓድ» አልኩት ።
«የመደብ ልዩነት ተፈጠረ እንዴ!» አለኝ ።
«ከያንዳንዱ እንደ ችሎታ ፣ ለያንዳንዱ እንደ ሥራው ጓድ»

«በዲሞክራቲክ አብዮት እንዲህ አርጎም የለ!» ብሎኝ በችኮላ ወደ ቦታው ተመለሰ ።

ሲሄድ ይፈጥናል ። ሲናገር ይፈጥናል ። ሲሰራም እንደዚሁ። እጅግ ሲበዛ ደፋርና ፈጣን የፖሊስ ቆመጥ ነው ። የሰው መውደድ አለው ፤ እድሉ ሆኖ በተለይ የሴቶች ።

የፕሮቶኮል ሹም ፤ «ጓድ ሊቀ መንበር! » አለ ድምጹን ከፍ አድርጎ ።

አይሮፕላኑ ውስጥ የነበረው ጉምጉምታ ፣ ሹክሹክታና ሜሜታ ባንድ ጊዜ ፤ ጸጥ ፣ ለጥ ፣ እረጭ አለ ። መርፌ ብትወድቅ እንኳ ይሰማ ነበር ።

«እንደምን አደራችሁ ጓዶች!»

ተርገብጋቢ ወንዳ ወንድ ድምጽ ። እንደ መብረቅ ተግ የሚል ከልብ የሚመነጭ ፈገግታ ። ቅስም ድንገት የሚሰብር ልባዊ ትህትና ። ሰውዬው! ባማረ ሚሊተሪ ዩኒፎርም ነበሩ ። ሳያቸው የሆነ አለኝታ ፤ በራስ የመተማመን ስሜትና ድፍረት ተሰማኝ ። የአገር መሪዎች እንደማንኛውም ሰው ተራ ሟች መሆናቸው ቢታወቅም ሲያዩዋቸው ፤ የሆነ ፍቅር ፤ አክብሮትና ፍርሀት በራስ የመተማመን ስሜትና ድፍረት ለምን በሰው ልብ እንደሚያሳድሩ ሁልጊዜ ይደንቀኛል ። ከሕይወት በላይ ግዙፍና ህያው ሆነው ይታዩኛል ። ምናልባት ያገርና የሕዝብ ክብርና ኩራት ፤ ህላዌና ፈቃድ ጠባቂ ፤ አስከባሪና ባላአደራ ስለሆኑ ይሆናል ። አላውቅም ። የሆነ ሆኖ ፤ በዚህ ምክንያት ይሁን ወይም በሌላ ባለሥልጣን በጣም ማክበር እወዳለሁ ። ይህን ጠባዬን በማየት የሥራ ጓደኞቼ ፤ 'እየው እንግዲህ ባለሥልጣን ሲያይ ጭራውን ሲቆላ' ይሉኛል ከባስተጀርባዬ ። እግዜር እንዳለ ይይላቸውና! እኔ ግን ጭራዬን የምቆላ ሰው አይደለሁም ። ለእራሴ ብዙ ባላውቅም ፤ ጭራዬን እንደማልቆላ አውቃለሁ ። ቆልቼስ የት ልደርስ? እንጃ ። ተፈጥሮዬ ሆኖ የሥልጣን ሱስ የለብኝም ። ፍላጎት ቢኖረኝ በሰው ዘንድ ያለኝ ፍቅር ፤ ሥልጣንም ሆነ አክብሮት ከሙያዬ ብቃትና ብስለት እንዲመነጭ ብቻ ነው ። ስለ ራሴ ይህንንም አውቃለሁ ። አዎን ፤ ሌላም የማውቀው ነገር

አለ ፣ ስሰራሴ አዎ ፣ በነገር እጠመዳለሁ ። እውነት ነው ። በሕ ይወት ካልተጠመዱ ፣ ሕይወት ምን ትርጉም አለው? ሕይወት መጠመዱ ነው ። ከዳር ቆሞ የሕይወት ሂደት ተመልካች መሆን አይቻልም ። ከሕይወት ጋር ወይም በተቃራኒው በሕይ ወት ላይ መዋኘት ። መስጠም ወይም ከጸሐይ በታች መንሳ ፈፍ ። በኔ ግምት ሌላ አማራጭ ያለ አይመስለኝም ። ሕይ ወት ማለት ይሄው ነው! ግን ታዲያ ያለ ዓላማ አይደለም ። በሙያዬ የምደሰትበት ቦታ ሁሉ ቤቴ ነው ።

«ቶሎ በል! ቶሎ በል» አለኝ የፕሮቶኮሉ ሹም በእጄ እየጋበዘኝ ። መቸም ተጣድፎ ያጣድፋል ፣ ተዋከቦ ያዋከባል ። ቀልብ ያሳጣል ።

«ወደየት?» ከመቀመጫዬ እየተነሳሁ ።

«ሊቀ መንበሩ ናቸው የሚፈልጉህ ። ቶሎ በል እንጂ!» ተከተልኩት ። የባለሥልጣን ዓይን ሁሉ ተከተለኝ ። ያ የተለመደ ሞቅ ያለ ልባዊ ፈገግታ ። ሳይወዱ በግድ ትሑት የሚያደርግ ትሕትና ። ፈገግታቸውና ትሕትናቸው ልብ ይሠርቃሉ ። ከጉድጓ ዳቸው ውስጥ ወዲህና ወዲያ የሚያማትሩት አይኖቻቸው ትከ ብለ ው ሰው አይመለከቱም ። አይናፋር ፣ ገራም ፣ ጥቁር ነብር! አንዳ ንዴ ደግሞ ቆስሎ የተቆጣ ጥቁር ነብር! በጣም የሚያስቆጣቸው ነገር ቢኖር ባለሙያዎች አንዳንዴ የሚያቀርቡት ቅጥፈት ሳይ ሆን አይቀርም ። በመጠኑም ቢሆን ከሩቅ አውቃቸዋለሁ ። ባለ ፉት ስምንት ዓመታት በአገር ውስጥ ወደ ምሥራቅ ፣ ምእራብና ደቡብ ኢትዮጵያ በውጭ አገር ወደ ምሥራቅ ጀርመን ፣ ቼኮዝሎ ቫኪያ ፣ ሁንጋሪያ ፣ ሞስኮና ደቡብ የመን አብሬአቸው ሄጃለሁ ። እና በነዚህ ዓመታት ውስጥ ሰውዬው ፣ ከተፈጥሮ የአእምሮ ንቁ ነት ወደ አረጋዊ ብልህነት ፣ ከጋለ ያገር ፍቅር ስሜት ወደ በሳል አብዮታዊ ምሁርነት ፣ ከቆፍጣና ወታደርነት ወደ አርቆ አስተ ተዋይ ሥራ እየተሰወጡ ሲሄዱ ዓይኔ አይቶአል ። ከኃላፊነት የበለጠ አስተማሪ ይኖር ይሆን? እኔ እንጃ ። ሰውዬውን ባየሁዋ ቸው ቁጥር ፣ ባንጻሩ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ፣ ሙያችንን በብ ባቡ የምንመለከት አብዛኛዎቻችን ምሁራን ነን ባዮች ፣ ባለፉት ስምንት አብዮታዊ ዓመታት ውስጥ ያለ ጥፍርና ያለሽበት ምንም ነገር አለማብቀላችን ወይም አለማማራችን ነው! ከብዙ ዘመን

የክፍል ትምህርት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በየመንገዱ በየፋብሪካው ፣ በየመሥሪያ ቤቱና በየእርሻው ቦታ በተግባር በሚደረገው የመደብ ጦርነት የሚገኘው ልምድ ይበልጥ አእምሮን ያጎለምሳል ያለው ማን ይሆን? ረሳሁት ። ግን እውነት ነው ።»

«ጓድ ጸጋዬ ፣ በማስታወቂያ ሚኒስቴር በኩል ለዘመቻው ከውጭ የታዘዙት የፊልምና የፎቶግራፍ ማንሻ ካሜራዎችና ጥሬ ፊልሞች ደርሰዋል ወይ?»

«ጓድ ሊቀ መንበር ጥሬ ፊልሞቹ ደርሰዋል ። ካሜራዎቹ ገና ናቸው.....»

«እኮ ለምን አልደረሱም? ስምንት መቶ ሺህ ብር ወጭ እንዲሆን ከታዘዘ ሀያ ቀን አልፎታል ። ወይስ የዘመቻው ባሕርይና አጣዳፊነት በሚገባ አልታየም? ከቢሮክራሲያዊ አሠራር ነጻ በሆነ መንገድ መሣሪያዎቹን ባስቸኳይ እንድ ታስመጡ አስፈላጊው ሁሉ ተደርጎ ነበር ። ምን ችግር ገጠማችሁ?»

«ጓድ ሊቀ መንበር ፣ የታዘዙት የፊልም ማንሻ ካሜራዎች ፕሮፌሽናል መሣሪያዎች ስለሆኑ ፣ እንደ ማንኛውም እቃ ገበያ ላይ አይገኙም ። ከታዘዙ በኋላ ነው በየፋብሪካው የሚገጣጠሙት ። ቢሆንም አስፈላጊው ጥረት ሁሉ እየተደረገ ነው.....»

«ጓድ ጸጋዬ ጊዜ የለንም ። እኛ ጊዜን የምንሻማ የድርጊት ሰዎች ነን ። እኛ የምንቸኩለው የታፈረችና የተከበረች ሶሻሊስት ኢትዮጵያን ሕልውና ለማረጋገጥ ነው ። ብሔራዊና አብዮታዊ ተልእኮአችን እጣዳፊና ታሪካዊ ነው ። እያንዳንዱ ድርጊት በሚገባ መቀረጽና መመዝገብ አለበት ። ዛሬ የምንሠራው ሥራ ሁሉ የነገ ታሪክ ነው ። ካሜራዎቹን ለመስራት ብንታደል ፣ ካሉበት ገዝተን መጠቀም እንዴት ያቅተናል?»

«በየቀኑ በቴሌክስና በቴሌግራም እየጎተጎትን ነው ጓድ ሊቀ መንበር ። ይደርሳሉ ....»

«ከጥር 10 ቀን በፊት አሥመራ መድረስ አለባቸው ጥር 10 ቀን....»

«እሺ ፣ ጓድ ሊቀ መንበር » አልኩ ፣ የቀሩትን ቀኖች በአእ ምሮዬ እያሰላሁ ። ሀያ ቀን ። እግዜር አውጣኝ አልኩ በልቤ ።» እጅ ነስቼ ወደ ቦታየ ልመለስ ነበር ።

«እሥመራ ላይ ከፍተኛ የፖሊሲ ንግግርና የመላ ኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፣ የሀይማኖት መሪዎችና የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች አባሎች ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ የሚያደርጉበት አንድ ታሪካዊ ጉባኤ ይደረጋል ። ንግግሩንና የጉባዔውን ሂደት መላ የኢትዮ ጵያ ሕዝብ በጋዜጣ ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ለመከታተል እን ዲችል ካሁኑ አስፈላጊው ዝግጅት ሁሉ መደረግ አለበት ።

«በሰሜናዊው ክፍለ ሀገራችን ያለው ችግር የያንዳንዱን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ጥረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው ። እና እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ዜጋ ዛሬ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚወስደው እቋ ምና....የሚሰጠው ፍርድ ፣ ነገ ወይም ወደፊት ወሳኝና ታሪካዊ ይሆናል ። ዋናው ተግባራችን ካሁን ጀምሮ የምናከናውናቸው ሥራዎች ናቸው ። እና በዚህ ወሳኝ ሥራ ውስጥ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ተግባር ከፍተኛ ሚና አለው ። ዝርዝር መመሪያ ኋላ በገለጻ ወቅት ይሰጠሀል ።

«ሌላም ሥራ አለ ። እሥመራ የሚታተሙት ጋዜጦች ፣ ኅብረትና ኢትዮጵያ ፣ ይዘታቸው ተገምግሞ ከምናካሂደው ቀይ ኮከብ ዘመቻ አንጻር መቀየስ አለባቸው ። ሥርጭታቸውም ከፍ የሚልበት መንገድ መፈለግ ይኖርበታል ። በገንዘብና በሰው ኃይል በኩል ምንም ችግር የለም ። የእሥመራ ሬዲዮ ፕሮግራሞ ችም ባስቸኳይ ተገምግመው የዘመቻውን ዓላማ ፣ ግብና ሂደት እንዲያንጸባርቁ መደረግ አለበት ።.....

«ሌላ አጣዳፊ ሥራ 'የጃሚንግ' ጉዳይ ነው ። የወንበዴዎች ሬዲዮ የሚያሠራጨውን ቅጥፈት የተሞላበት ውዥንብር ተከ ታትላችሁ መዝጋት ያስፈልጋል ። ለእረፍት ወይም ለሽርሽር አይደለም ወደ እሥመራ የምንሄደው ። ቀን ከሌት መስራት አለብን ። ሁሉም ያለ የሌለ ጉልበቱንና እውቀቱን ተጠቅሞ ለዚህ ብሔራዊና አብዮታዊ ዘመቻ ግብ መምታት እንደ አንድ ሰው ሆኖ መረባረብ አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው ። ግልጽ ነኝ?»

እንደገና በልቤ ጸሎት አደረስኩ ። የቁልቢው ገብርኤል እንዴት ያወጣኝ ይሆን አቦ! እዚህ ጣጣ ውስጥ ጠቁሞ የዶለኝን ሠይጣን የእርግማን መዓት እያወረድኩበት ወደ ቦታዬ ተመለስኩ ። የአስተናጋጆዋን ትእዛዝ አልጠበኩም ። መቀመጫዬ ላይ የነበረውን ጠብደል ቀበቶ በማንሳት ወገቤን ጠበቅ አድርጌ አሰርኩት ። ከኔ ኋላ የተጠራው መጽሐፈ ዳንኤል ፣ የኢኮኖሚው ሊቅ ነበር ። ሰጫዬው ካሁኑ ሥራቸውን ጀምረዋል። «እኛ የድርጊት ሰዎች ነን ሲሉ የተናገሩት ቃል ፣ ጆሮዬ ውስጥ ደወለ ። አንዷት ዝርዝር ጉዳይ አታልፋቸውም ። ነገር አይረሱም ። ስም አይዘነጉም ። የማስታወስ ችሎታቸው ግሩም ነው ። አንዳንዴ ሳስበው ከማስደነቅ አልፎ ያስገርመኛል ። እኔ በእሳ ቸው ቦታ ብሆን የሚል አሳብ መጣብኝ ። ደግነቱ አይደለሁም ። ብቸኛ ቦታ ነው...... እዚያ ላይ ።

አይሮፕላኑ ለመነሳት ማኮብኮብ ባይጀምር ኖሮ ፣ ኦጭር የሥራ ዝግጅትና አፈጻጸም ሪፖርት የመስማትና ግልጽ መመሪያ የመስጠቱ ተግባር ይቀጥል ነበር ። ካሁኑ እንዲህ ከሆነ ፣ አሥመራ ስንደርስ ምን እንደምነሆን አሰፈራኝ ። ጊዜ የላቸውም እና ጊዜ አይሰጡም ። መላክ ገብርኤል በተአምሩ ሌላ ምስራች ይዞ ካል ቆየኝ በቀር............

እና በእሳቸው ረዳቶች ስም እንኳን ደህና መጣችሁ እላለሁ.............. ይህ 709 ልዩ በረራ ነው...... የምንበርበት ከፍታ 29 ሺ ጫማ.......... በረራው የሚወስድብን ጊዜ ሀምሳ አምስት ደቂቃ...... ከመቀመጫዎቻችሁ ሥር ያሉትን ቀበቶዎች እንድትታጠቁ ትለመናላችሁ..........

መታጠቅ ይነሰን ! ጠበቅ አደረግነው ። አይሮፕላኑ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አፍንጫውን ወደ ሰሜን ደገነ ። ልዩ በረራ ። ተልእኮው ፣ የአርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ። ታሪካዊ በረራ ። አማተብኩ ።

# አሥመራ ያን ቀን በዘምባባዎች
# ጥላ ሥር
# ንግሆ ወጋሕታ

ናይ ሰሜናዊት ፅብቕቲ ፣ አሥመሪና ። የቀይ ባሕር እንቍ
ሽብ ። እረብ ፣ ክንብል ፣ ዝንፍል ብለው በየመንገዱ ዳር የሚ
ታየው ዘንባባዎችና የሰሜናዊ ቆንጃጅት ሽሩባዎች አንጸራጓ
ውብት ባለቅኔም ባይሆኑ ስሜት ይቀሰቅሳሉ ። ከዘንባባና ከሰ
ሜናዊት ቆንጆዎች ሹሩባ ጥላ ስር ሳንዳፍታ እረፍ፣ ጋደም በማ
ለት እንደ ኩል ከጠራ ሰማይ ላይ የምታበራውን ሰሜናዊ ኮከብ
በጠፍ ጨረቃ በእፎይታ መመልከት ምንኛ ደስ ይል ይሆን?
ሠላም ናፈቀኝ! ጦርነት በሕይወትና በቁስ ላይ የሚያስከትለው
ጥፋት የበለጠ የሚየስጠላኝ ነገር በዚህ ዓለም ያለ አይመስለኝም።
የሰው ልጅ በመካከሉ የሚፈጠሩትን ልዩነቶች በውይይትና
በሠላም የሚፈታበት ቀን መቼ ይመጣ ይሆን? ያ ቀን ናፈቀኝ ።
ለምንድን ነው የሰው ልጅ በሠላም የማይኖረው? ያለጦርነትም
ሕይወት ራሷ አጭር ናት ።

ለማንኛውም ነገር አሥመራ ዮሐንስ ትራተኛ አይሮፕላን
ማረፊያ ከደረስኩበት ደቂቃ ጀምሮ ጊዜ አላጠፋሁም ። የማጠ
ፋው ጊዜ አልነበረኝም ። ብሔራዊና አብዮታዊ ተልእኮአችን
ሁለት ስለት ያለው ነበር ፤ ባንድ ፊት ውጊያ ፣ በሌላ በኩል
ሁለንተናዊ የኢኮኖሚ ግንባታ አንድ ላይ ማካሄድ ፣ በተለይ ፣
የኔ ተልእኮ ደግሞ ከዚህም ትንሽ ላቅ ያለ ነበር ። የኔ ተግባር ሥነ
ልቦናዊ ጦርነት ማካሄድና ማፋፋም ነበር ። እኔ እስከማውቀው
ድረስ መቼም ከሥነ ልቦናዊ ጦርነት የበለጠ ውስብስብና አስቸ
ጋሪ ነገር ያለ አይመስለኝም ። ዓላማው ምን በጎና ሀቀኛ ቢሆን ፣
ምኞቱ ምን ቢልቅ ፣ የሰውን አእምሮና ልብ ባንዴ ለማዘዝ
አይቻልም ። ጊዜ ይወስዳል ። ከፍተኛ ትግል ይጠይቃል ።
የሰውን አእምሮና ልብ በቀላሉ ለማዘዝ ቢቻልማ ኖሮ መቼ
ጦርነት ይኖር ነበር? የሰው ልጅ የወደፊት ጦርነት ድሉና ሽን

ፈቱ እዚህ ላይ መሆን አለበት ፣ በሰው አእምሮ ውስጥ ። አንድ አእምሮ ። አንድ ልብ ። ዘላለማዊ ሠላም ። የት እኮ! ጦርነት የማይካሄድበት የዓለም አካባቢ የዓለም ። ሁሉም ቦታ ጦርነት ። ያለም መገናኛ ዘዴዎች ሁሉ ተባበሩ! ለሰው ልጅ ትብብርና ሠላም ዘብ ቁሙ! ያለ ቅጥፈት የማቀርባችሁ ነገር የለም! የራሴ አሳብ መልስ እኔኑ አሳቀኝ ።

ለሚቀጥሉት ሦስት ወሮች ለማረፊያ ከተዘጋጀልን ፣ ከአሥመራ ቤተ መንግሥት በስተጀርባ ፣ አብዮት ጎዳና ላይ ከሚገኘው ከዶክተር ዮሐንስ ቤት ደርሼ ጊዜያዊ አልጋዬ ላይ ሻንጣዬን ወርውሬ ነበር ወዲያውኑ የወጣሁት ፣ 'የሠላም ዘንባባ' የተሰኘ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለመሥራት ። ለምን እንደሆነ እንጃ የአሥመራን ዘንባባዎች ባየሁ ቁጥር የሠላምና የፍቅር ስሜት ይቀሰቅስብኛል ። ፕሮግራሙም በሠላም ላይ እንዲያተኩር የታቀደ ነበር ። አይሮፕላን ላይ ነበር አሳቡ ብልጭ ያለልኝ ።

ከጸጸራት (ፎርቶ) ፣ ከሐዝሐዝ (የሴቶች እሥር ቤት የሚገኝበት ፣ ከቤተጊዮርጊስ የቴሌቪዥን ትራንስሚተር የቆመበት ከአርባእተ አሥመራ ሴቶች የአሥመራን ከተማ መጀመሪያ የመሰረቱበት) ፣ ከገዛ ብርሀኑና ከአዲስ ዓለም ኮረብታዎችና ከራስ አሉላ ግቢ የአሥመራን ከተማ በቴሌቪዥን ፊልም ማንሻ ቃኘን ። አሥመሪቲ ፣ አሥመሪና ፣ በምሥራቅ በጸሎትና በቤተ ጊዮርጊስ ፣ በምዕራብ በጸጸራት ፣ በሰሜን በአክሪያና በአርባዕተ አሥመራ ፣ በደቡብ በዓዲ ጓዕዳድ ኮረብታዎች ተከባ ፣ በሰርባ ዳው ወለል ላይ ሆጭ ብሎ የፈሰሰ የባህር እንቁ የምትመስል ፣ ከባህር 7,500 ጫማ ከፍታ ላይ የምትገኝ ፣ በሚገባ በተቀየሱ አውራ መንገዶችና መጋቢ መንገዶች ፣ በዘምባባ ዛፎችና ብርቅ በሆኑ አበባዎች ፣ በሐረግ አበባዎች ፣ በሽቶ ዛፎች እንደ ሙሽራ ያጌጠች ውብ ፣ ትንሽ ከተማ ናት ። አሥመሪና ። ሚያ ቤሌሳ ። ናተይ ጽብቐቲ ። አሥመራ ደስ ትለኛለች ። የደስ ደስ አላት ። በፊትም አውቃታለሁ ። ጋዜጠኛ መሆን መቸም ጥሩ እድል ነው ። ከቦታ ቦታ ያሠራል ። ንቅናቄ የሕይወት አንዱ አካል ይሆናል ፣ ጋዜጠኛ ከሆኑ ።

አሥመራ ደስ ትለኛለች ብያለሁ ። ግን የሚያስጠላኝም መልክ አላት ። ትንሽ ከተማ በመሆኗ አፍን ታደርጋለች ። ጠባ

ታስጨንቃለች ። ከመጥበቧና ከማፈኗ የተነሳ ልብ ሊፈነዳ ይደርሳል ። መደበቂያ የላትም ። እንደ አዲስ አበባ ወደ አንድ መንደር ጎራ ብሎ መጥፋት ወይም መሰወር አይቻልም ። ታፍኖ ሳለመፈንዳት ካሥመራ ወጣ ወይም ወደ ምጽዋ ወረድ ማለት ያስፈልጋል ። ቀይ ባሕር አለ ። የባሕሩ ሞገድ ተነስቶ እንደ ዘንግ ቁሞ ተመልሶ ሲወድቅ ማየት ልብ ያነሆልላል ፣ ያላብ አድማስ ያሰፋል ። ባሕር ሕይወት ነው ። የኢትዮጵያም ሕይወት ቀይ ባሕር የሕይወት በር ። በእፎይታ ያስተነፍሳል......

ጸሐይዋ ከደመና ግላጭ ውስጥ ብቅ ብላ ዓይናፋር ሰሚናዊት ሽሩቤ ሙሽራ መስላ ትታያለች ። ቀኑ ይበርዳል ። ቁር ሐማሴን ይነፍስ ነበር ። የዘምባባ ዛፎቹ በሠላም መዝሙር የሚያረግዱ ይመስላሉ..... እንዲህ እያሉ ፤

«ያንድ እናት ልጆች
በዓላማ ተለያይተው
ባመለካከት ተሳስተው ተጣልተው
እስታራቂ ጠፍቶ
የእብድ ገላጋይ በዝቶ..........»

ከኮረብታዎቹ ወርደን ወደ ጠባቢቱ ውብ ከተማ ገባን ። ሰንበል ፣ ጉዳይፍ ፣ ትንሹና ትልቁ ገጀረት ፣ ማይ ወላሎ ፣ቴራ ቪሎሽ ማይ ጭሆት ፣ አዲስ ዓለም (ገዛ ባንዳ) ፣ ዕዳጋ ዓርቢ ፣ ዕዳጋ ሐሙስ ፣ገዛ ብርሀኑ ፣ ገዛ አባ ሻውል ፣ ማይ ተመናይ ፣ አንዱም ሰፈር አልቀረንም ። አካለልነው በቲቪ ካሜራ ።

የአሥመራ መንገዶችና ሕንጻዎች በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማዎች ፣ በቀይ ጨርቆች ፣ በአብዮታዊ መፈክሮችና ፖስተ ሮች ፣ በቀስቶችና ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው መብራቶች አጊጠ ዋል ፣ አሸብርቀዋል ። ዘንባባዎች በመብራት ነደዋል ። ከተማ ይቱ በእርግጥም ነዳለች ፣ አብርታለች ፣ ጠፋለች ፣ ለታላቅ በዓል የተዘጋጀች መስላለች ፣ ወደ ጫጉላ ቤት ልትሄድ የደረሰች የተ ቀበችና የታደመች ውብ ሰሚናዊት ቆንጆ ፣ አይናማ ሹሩቤ ። ያዲስ አበባ አርቲስቶች ፣ ደራስያን ፣ ታሪክ ጸሐፊዎች ፣ ጋዜጠ ኞች ፣ መሐንዲሶችና የኢኮኖሚ ሊቃውንት ከምቢሽታቶን (ብሐራዊ ጎዳና) ሆ ብለው የወረሩ ይመስላሉ ። ገና ከፋብሪካ

የወጡ ቀይ ፣ አረንጓዴ ፣ ብጫ ላዳዎችና ላንድሮቨሮች በወታደሮች የታጀቡ ሠላማዊና ወታደራዊ ባለሥልጣናች ይዘው እንደ ሽማኔ መወርወሪያ ያለማቋረጥ ወዲህና ወዲያ ሽው ፣ ሽው ይላሉ በከተማይቱ ጎዳናዎች ። ነዋሪው ሕዝብ በየደጃፉ ፣ በየቡና ቤትና በየሱቅ ቤት በር ላይ ቁሞ ተገርሞ ፣ ዝም ብሉ ይመለከታል ፣ ምናልባት በልቡ..... «እንታይ መጺኡ?..... እንታይ ኢዩ እዚ ዕግርግር? ሽብድብድ?»፡ የሚል ይመስላል ፣ አስተያየቱ ።

‘ኮምቢሽታቶ ምዝዋር ክሊአሙኒ
ወይ ሞሶሊኒ ካብዚ ‘ዶ ክፍአትኒ’

የተባለው በጣልያን ጊዜ የተዘፈነው ዘፈን ትዝ ያላቸው የሚመስሉም አንዳንድ ወጣቶችና ኮረዳዎች ነበሩ ።

«ሠላም ፣ ሠላም እንደምን ናችሁ
ከሸዋ መጣን ልናያችሁ
ሠላም ፣ ሠላም ፣ ኤርትራ ሠላም.....»

አ ዝ ማ ሪ ና አ ዝ ማ ሪ ና ፤
ሰይቱ ፒዮ ቢላ ረጂና ፤
ሰቲቪዶ ዳ ሎንታና ፤
ካስካ ኩሊሉክኢ ኢን መና ።

አ ሥ መ ራ የ አ ሥ መ ራ የ ፤

ካብ ሐንቲ ንግሥቲ ይበልጽ መልክዕኪ ፤
አማዕድየ ክርእየኪ ከሎኹ ኸአ
አብ ኢደይ ዘሎ ነገር ይወድቕ ።

አ ሥ መ ራ የ አ ሥ መ ራ የ ፤

ከአንዲት ንግሥት ይበልጣል መልክሽ
በሩቅ ሲያይሽ በውበትዋ ስለ ተማረከ
በእጇ ያለ ነገር ሳይታወቀኝ ይወድቃል ። ግሰት ነውትርጉሙ»

1. አንተ አምላክ አንተ ፈጣሪ ፥
   የሰው ልጅ እንዴት በበረሀ ያረጃል ፥
   ከዓይናችን አይንህ ይበልጥ የለም ወይ?

2. አንተዬ እኔን ገረመኝ ፤
   ወደኋላ የምትሄድ መቼ መሰለኝ ።
3. ጥዋት በማለዳ ።
4. ማታ ፤ በሰሜናዊ ኮከብ ጥላ ሥር ።
5. በ «ኮምብሽታቶ» መንሸራሸር ከለከሉኝ ፥
   ሞሶሊኒ ከዚህ የባሰ ምን አደረገኝ ።

«አሁን ወደ ገበያ እንሂድ» አልኩዋቸው ። ፊልም አንሺዎቼ ደከመዋል ። 'ዝሁል'ቢራ ብቻ ነበር የሚታያቸው ።

«አረ ጓድ ጸጋዬ ለዛሬ ይብቃን» አለ አንዱ ከመካከላቸው።
«ገና ምን ተይዞ?» አልኩት ።

ወደ ገበያ ተያይዘን ሄድን ፥ የረሀብ አልቂት የመጣ ይመስል ሁሉ እየተሻማ ያገኘውን እህል ባገኘው ዋጋ ይሸምታል ። ማይክሮፎን ይዤ ወደ አንድ አሮጊት ጠጋ አልኩ ። ሹሩባቸው ከንብንባቸውን ወጥሮ ይዞታል ። ቡችላ ፤ ቡችላ ፤ የሚያካክሉ የወርቅ ጌጦች ጆሮና አንገታቸው ላይ ጉች ጉች ብለው ይታያሉ ። የትግሬ ቤትና ወርቅ መቼም በመሀላ አይተጣጡም ።

«ምንድን ነው የሚሸምቱት እማማ?»
«ዋእ! እህል» አሉኝ ።
«ዋጋው እንዴት ነው?»
«ዋእ! ውድ ። እሳት ሆኖአል ።»
«ለምን?»
«ተወዲኡ.....»
«ለምን እህል ጠፋ?»
«እንዲኢ ። ሁሉም ይሸምታል.....»
«እኮ ለምን? ምን መጣ?»

ለወሬ ያሰፈሰፉ መአት ሰዎች ከበውናል ፥ ወጣት አሮጊት ሽማግሌ ። እንደ ዘምባባ ዛፍ ያለ ሹሩባ ። በቁንዳላ እንደ ድግ

ኩኖን የተወጠረ ክንብንብ ። አንዳንድ በቴሌቪዥን የሚያውቁኝ ወጣቶች ነበሩ ። እሱ ይሆን፣ ወይም አይደለም በማለት የሚወራረዱብኝ መሰለኝ ። መቸም በቴሌቪዥን 'ሣጥን' ውስጥ አምረውና ቆንጅተው በየምሽቱ የሚቀርቡት አንዳንድ የቴሌቪዥን ሰዎች ፣ ውጭ በሕይወት አጭር ፣ ፋንጋ ፣ መላጣ ፣ ገባጣ ፣ ከፈጩበት የቆሉበት መስለው ብቅ ሲሉ ወሽመጥ ይቆርጣሉ ።

— ውይ እሱ ነው እንዴ!
— ውይ እሱዋ ናት እንዴ!
— ይሀ ቲቪ ለካ የሌለ መልክ ነው የማያሳየው ። ኤጭ!
እኔስ ምን መሰዬ ታይቻቸው ይሆን?
«ጸግሽ!» አለ አንዱ ደፋር ።

ስም ያለው መቸም ሞኝ ነውና ዞር አልኩ ። በውርርዱ ሳይረታ አልቀረም ።

አሮጊቷ በመጨረሻ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ መልስ አልሰጡኝም ። በብሩህ ዓይናቸው ዝም ብለው ይመለከቱኝ ነበር ። ምነው ስንተዋወቅ ባንተናነቅ የሚሉ ይመስላሉ ። የሁሉም አፍንጫ የጠርነት ፣ የእልቂት ፣ የረሀብ ና የቸነፈር አየር የሚያሸት ፣ አይናቸው ምጽአት የሚያይ ፣ ጆሮአቸው የጥይት ፉጨትና የሞት ዋይታ የሚሰማ መስሎ ታየኝ ። ነገሩ የተገንጣይ ወንበዴዎች ተንኮል ሳይሆን ይቀራል? የጦፈ ፣ የተጧጧፈ ስነ ልቦናዊ ጦርነት በመካሄድ ላይ መሆኑ ገባኝ ። ተናደድኩኝ ። ደግሞም አዘንኩኝ ። ይሀ የዋሀ ሕዝብ አሳዘነኝ ። የመሸበር ፣ የመደናገጥ ፣ የፍርሀት ደመና ጥላ ፊታቸው ላይ ያንዣብባል ። በሞት ጥላ ግርዶሽ የተዋጡ ይመስላሉ ። የባሰውን ተበሳጨሁ ።

የካሜራችን ዓይን ሸመታው ላይ አተኩሮአል ። ሸማችና ነጋዴ አይከራከሩም ። ነጋዴው ባለው ዋጋ ይሸጣል ። ሸማቹም በተባለው ዋጋ ይገዛል ። የእህል ዘር ፣ የጥሬ ዘር በያይነቱ ፣ ከሰል ፣ የማገዶ እንጨት ፣ ዘይት ፣ ላምባ ፣ በገፍ ይሸጣል ፣ በገፍ ይገዛል ፣ በገፍ ይጫናል ። ሁሉም ይሮጣል ፣ ይጣደፋል ፣ መጪው ክፉ ቀን ሳይቀድመው ለመቅደም ያለ የሌለ ጥሪቱን አፍስሶ ባከማቸው እህል ነፍስና ሥጋውን ይዞ ለማቆየት ባለፈው ጊዜ የተበለጥነው ይበቃል! የሚል ይመስላል ዓይኑን ሳያሽ ገንዘቡን

ሆጭ አድርጎ በእልክ እንደዚያ ሲገበያይ ። አይፈረድበትም ። ጦርነትና እልቂት ሊመጣብህ ነው ሲሉት ሕዝቡ ምን ያድርግ? እፍኝ ጥሬ ጠፍቶ ጦም ተውሎ የታደረበት ፣ ሳጥን ፣ ቁምሳጥን ፣ ወንበር ሳይቀር ተፈልጦ ለማገዶ የዋለበት ፣ ያ የ1969 እና የ1970 ጦርነት ጊዜ የሩቅ ትዝታ አይደለም ። ግን ጦርነት ቢመጣስ አሁን ማን ይሙት ማን ሞቶ ማን ሊቀር! የሰው ነገር ይገርማል ። መቸም እኔ እሞታለሁ የሚል የለም ። ሁልጊዜ የሚሞተው ሌላው ሰው ነው ።

የባለድምጽ ካሜራውን ማይክሮፎን አፌ ላይ ደቅኜ የዘመቻውን ዓላማ አንቆረቆርኩት ፣ እንዲህ ስል ።

«አንተ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ሕዝብ ። ላለፉት ሀያ ዓመታት ሰላም ሲርብህ ! ሲጠማህ ! ሲናፍቅህ ቆይተሀል ። አንተም እንደ ማንኛውም ሕዝብ ሰላም ፈላጊ ነህ ። የሰፊው ሕዝብ ፍላጎትና ምኞት ምን ጊዜም ቢሆን ሰላም ነው ። ሰላምን ትሻለህ ። ግን ሰላም የማይሰጡህ የኢምፔሪያሊዝም አለኝታና ጋሻጃግሬ የሆኑ ፣ ያለ ስምህ ስም ፣ ያለ ታሪክህ ታሪክ ፣ ያለ አላማህ አላማ እየደረቱልህ ፣ አንተ በማታምነውና በማትቀበለው የታሪክ ቡቱቶ ባንተ ስም የሚነግዱ ተገንጣይ ወንበዴዎች አሉ።

«ዛሬም ሊያወናብዱህ ይሞክራሉ ። ጦርነትና እልቂት ሊመጣብህ ነው እያሉ ያሸብሩሀል ። ሠላምን እንጂ ጦርነትን ፍለጋ የመጣ የለም ። ተገንጣይ ወንበዴዎች በሚነዙት ከንቱ አሉባልታ እና አንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች ፣ የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ ፣ ሆን ብለው በሚፈጥሩት ውዥንብር አትሸበር ። ጥሪትህን በከንቱ አታፍስ ። አንተ ላይ የተቃጣ ጦርነትና እልቂት የለም ። ጦርነትና እልቂትን የሚሹት ግን በጦር ሜዳ ያገኙታል ። የምትናፍቀው ሠላም ከእንግዲህ ሩቅ አይደለም ። ተቃርቦአል ። እንዳንተው ሰላምን የሚሹ ፣ ሰላምን የሚናፍቁ ሐቀኛ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ዛሬ በመካከልህ ይገኛሉ ። ተልእኮአቸው ሠላም ነው ። ሠላም የኤርትራ ሕዝብ ። ሠላም ። የሠላም ዘምባባ......»

አርባ ደቂቃ የሚፈጅ ባለድምጽ ፕሮግራም ነበር የሠራሁት ። ፊልሞቹን ይዤ ወደ ሰንበል ፣ አርሚ አቪዬሽን በረርኩ ፣

ቢት እንደደረስኩ ለሥራ በተሰጠችኝ ቀይ ላዳ መኪና ። መኪ
ናዋ አዲስ ስለሆነች መንገዱን ፉት አለችው ። ስትበር መንገ
ዱን እያፈሰች የምትውጥ ትመስል ነበር ።......

አርሚ አቪዬሽን እንደደረስኩ ሻለቃ ታደሰ ቆሪችን አገ
ኘሁት ። ሻለቃ ታደሰ ቆሪች ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ ከአርሚ
አቪዬሽን ሜዳ በውርርድ አይታጣም ። ላለፉት ሰባት ዓመታት ፣
ከከፍተኛ ባለሥልጣን ጀምሮ እስከ ተራ ሰው ያለው ሁሉ የሚያ
ውቀው የታወቀ ተቋም ሆኗል ። የአርሚ አቪዬሽን ትራፊክና
ስምሪት አዛዥ ነው ። በጣም ቁልፍ የሆነ ቦታ ነው የያዘው ።
ያለ እሱ በጎ ፈቃድና ውሳኔ በአርሚ አቪዬሽን ሄሊኮፕተሮችና
አይሮፕላኖች የሚጓጓዘም ሆነ ሰቃ የሚጭን ሰው የለም ። በእዙ
ሥር ያሉት አይሮፕላኖች ሁሉ በየትኛው ደቂቃ የት ቦታ ላይ
ምን በመሥራት ላይ እንዳሉ በቃሉ ያውቃል ።
«እህስ ጽጋሽ?» አለኝ ።

ሞቅ ያለ ፈገግታና በጎ ፈቃድ መችም የማል ገንዘቡ ናቸው ።
ረጂም ፣ ጠይም ፣ ሰውነተ ደንዳና ቆፍጣና ወታደር ነው ።

«ሻለቃዬ ይህን ፊልም ወደ አዲሳባ ልልክ ፈልጌ ነበር ።
ዛሬ ማታ መታየት ያለበት ፕሮግራም ነው» አልኩት ።

«ደህና ደርሰሀል ። በግማሽ ሰዓት ውስጥ ወደ አዲሳባ የሚ
ነሳ ዳሽ አለ» አለኝና ፊልሞቹ የታሸጉበትን ካርቶን ተቀበለኝ ።
«በረራው ምን ያህል ጊዜ ይወስድ ይሆን? » አልኩት ፣
አገር እንዲህ ሲተባበር እንዴት ደስ ይላል እያልኩ በልቤ ።

«ሁለት ሰዓት ያህል»

የእጅ ሰዓቴን ተመለከትኩ ። ከጧቱ አምስት ሰዓት ሆኖ
አል ። ፊልሞቹን እጥቦ 'ኢዲት' ለማድረግ በቂ ጊዜ በመኖሩ ደስ
አለኝ ። ዛሬ ምሽት ፣ 'የሠላም ዘምባባ'። ቀላል ጥረት አይደለም ።
ያሰቡት ነገር ሲሳካ ደስ ይላል ። ሆኖም ራሴን ለማመስገን ጊዜ
አልነበረኝም ።

«አመሰግናለሁ ሻለቃዬ ።» አልኩት ።
«ምንም አይደለም ። ዘመቻው የጋራችን ነው ።» አለኝ ።
«ወደፊትም እንደሚረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ.....»

«ጥረት የሚያደርግ ሰው ምን ጊዜም መረዳት አለበት ። ግን ጠባያችን ሆኖ መኮርኮም ይቀናናል» አለኝ ወገቡ ላይ የሻጠውን ኮልት እያስተካከለ ።

ቦርጭ አውጥቶአል ። ከዚህ በፊት ብሩህ ፊቱ ላይ አይቼው የማላውቀው የምሬት ጥላ ተነበበኝ ።

«ለመሆኑ እዚህ ሜዳ ላይ ስንት ዘመን አሳለፉ?» ብዬ ጠየኩ

«ሰባት ዓመት ። የሰንበል ቁርና ሐሩር እየተፈራረቁብኝ ግን አሁንማ እዚህ መዋሉ ሁለተኛ ተፈጥሮዬ ሆኖአል ። ያይሮፕላን ጩኸት ሳልሰማ ብውል ጤነኛ እሆናለሁ ብለህ ነው!»

«ስለ እርስዎ አንድ ቀን አንድ ፕሮግራም መሥራት አለብኝ፥ አባቴ ይሙት» አልኩት ።

ቀልዴን አልነበረም ። እሱን በማቅረብ ጥሩ ገፀባሕርይ መሳል ይቻላል ። ዓይኖቹ ብዙ አይተዋል ፣ ብዙ ታሪክ መዝግበዋል ። ባለፉት ሰባት ዓመታት ሰንበል ሜዳ ላይ ምን ያላየው ነገር ይኖራል? ሕይወት ፣ ሞት ፣ ድል ፣ ሽንፈት ።

«ጡረታ ከመውጣቴ በፊት ቶሎ ብለህ» አለኝ በረጃሙ ትንፍሶ ።

«ጡረታ ሊወጡ ነው እንዴ?» አልኩት ።

«አዎ ፣ እንግዲህ ምን ቀረኝ? እዚሁ ሜዳ ላይ ደፍ ደፍ ስል ላይታወቀኝ የጡረታዬ ጊዜ ደረሰ ። ንብረት አላፈራሁ ፣ ጥሪት አልቋጠርኩ ። ንብረቴም ጥሪቴም ፣ ሕይወቴም ይሄው ሜዳ ነበር ። ግን ከሁሉም ነገር ቅር የሚለኝ ከአይሮፕላን ጩኸት መለየቴ ነው ። አይሮፕላን ሲነሳ ልቤ አብሮ ይመጥቃል ፣ መጥቶ ሲያርፍ ልቤ አብሮ ያርፋል ። የሰው ነገር ይገርማል ። ልማድ መጥፎ ነው» አለኝ ።

አነጋገሩ ልቤን ነካው ። ቁልፍ ቦታ ላይ ያሉ ከፍተኛ የሥራ ልምድ ያካበቱ ፣ ጤናማ የሆኑና ችሎታ ያላቸው ሰዎች ፣ ዕድሜአቸውም ቢደርስ ፣ ለምን በጡረታ እንደሚገለሉ ብልሀቱ አይገባኝም ። ላገር ጉዳይ ነው ፣ እድሜ የአብዮታዊነት መለኪያ ነው ያለውስ ማን ነው! እኛም ዛሬ በወጣትነታችን የምንኮራው ነገ እናረጃለን ። መቼም ዘላለም ወጣት ሆኖ የሚኖር የለም ። ዘ

ሳለም ወጣት ሆኖ መኖር ቢቻል ምን ነበረበት! እና ልጆቻችን ወግ አጥባቂዎች ብለው ያምጹብን ይሆናል ። ማን ያውቃል? እና ፣ ያብዮታውያን ልጆች ሲያምጹ ምን ይሆናሉ? እስቲኝ ። ትውልዳዊ ግጭት ፣ የማይቀር ታሪካዊ ሂደት.....ሁለት ሚግ 23 ተዋጊ አይሮፕላኖች ተከታትለው ተነሱ ። እንደ ኪውብድ ቀስት ጭልጥ ወዳለው ሰማያዊ ሰማይ ተወረወሩ ። ወደ ናቅፋ ። ሻለቃ ታደሰ በአይሮፕላኖቹ በረራ ተመስጦ ቀርቶ ነበር ።

«እንግዲህ አይራ አይሮፕላኑ አዲሳባ ሲደርስ የቴሌቪዥን ሰዎች ሂደው ፊልሙን እንዲቀበሉ ስልክ እደውላለሁ» ብዬው እኔም መኪናዬን አስነስቼ በረርኩ ። በአምስት ሰዓት ተኩል ከአዲስ አበባ ከኔ ጋር ከመጡ ጋዜጠኞችና ከኤርትራ ክፍለ ሐገር የማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ጋር ቢሮዬ ስብሰባ ነበረኝ ። አሥመራ መንገዶች ላይ ብዙ መኪናዎች አይታዩም ። በመሆኑም ነው መሰለኝ ፣ ነዋሪው ሕዝብ ዳር ይዞ የሚሄዱን ነገር የረሳ ይመስላል ። ቢሆንም ቢሮዬ በጊዜ ደረስኩ ። የቀጠርኳቸው ሰዎች ገና በመምጣት ላይ ነበሩ ። ጓድ ጸጋዬ ኃይለ ማርያም ፣ በሁግአዘ ፖለቲካ መምሪያ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ክፍል ኃላፊ የሚል በወርቅ ቀለም የተጻፈ ምልክት ቢሮዬ በር ላይ ተጽፎ ይታያል ።

«ረዛን..... መጀመሪያ አዲስ አበባ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋር ፣ ስልክ ቁጥር 12 39 74 አገናኝን ። ቀጥሎ ከክፍለ ሀገሩ ቴሌኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ ጋር ። እሺ?» አልኳት ።

«ጥሮንቶ ። እሺ እምባር»

ረዛን ምንጊዜትአብ ጸሐፊዬ ናት ። አይጥ ትመስላለች ። ያለጠጉር ውበት የላትም ። ቆንጆ ፣ ጥቁርሃር የመሰለ ረጅም ጠጉር አላት ። አብዛኞዎቹ የአሥመራ ሴቶች ውበት ጠጉር ፣ ዓይንና ጥርሳቸው ነው ። አብዛኞዎቹ በእግር ቅርጽ የታደሉ አይደሉም ።

«አዲሳባ» አለች ረዛን ። «ሃሎ እ! ጸጋዬ ነኝ ጓድ ። ይዘና ደርሰናል ፣ ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ እንዲሉ ሥራም ጀምረናል ። የደወልኩትም ለዚሁ ነበር ። ፊልም ልኬአለሁ.... ዳሽ «ፋየርቨ» አይሮፕላን ይዞ ይመጣል ። ከሁለት ሰዓት

በኋላ ቦሌ ሰው ልከህ እንዲወስድ አድርግ ፣ ዛሬ ማታ መታየት አለበት ። ቻው እምባር »

ወዲያውኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ጥሪ መጣ ።

«ማን ልበል?..... እሺ ጓድ ። ጸጋዬ ኃይለማርያም እባላለሁ ። ከዚህ ካዲሱ የፖለቲካ መምሪያ ነው የምደውለው..... ደህና..... ደህና መጣን..... ጥሩ ። አሁን የፈለግሁዎት አንድ አስቸኳይ ስብሰባ መኖሩን ልነግርዎት ነበር..... አሁን..... በታው በፊት የሕዝብ ጎንነት የነበረው ሕንጻ ነው ። ከቤተ መንግሥት በስተጀርባ ። የመንግሥት ሠራተኞች ክበብ ፊት ለፊት ። ፖለቲካ መምሪያ ብለው ይምጡ— ጊዜ የለንም..... አሁን ።»

አነጋገሬ ሁሉ የባለሥልጣን አነጋገር ጠባይ መያዙ እኔኑ መልሶ አስገረመኝ ፣ መሆን አለበት ፣ አሁን ። የሚገርመው ነገር ደግሞ ሰው ሥልጣን ሲያሳዩት ይደነግጣል ። የሁገአዘ ፖለቲካ መምሪያ ።

ድንገት የቢሮዬ በር በኃይል ተከፈተ ። ደነገጥኩ ። ሰለሞን በትሬጊዮርጊስ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ አገናኝ መኮንን ነበር ። ከጥቁር ፣ ብሩህ ፊቱ ላይ ሁልጊዜ የማይጠፋው ልባዊ ፈገግታው ባንድ ጊዜ ሰው ይወርራል ። ቁመቱ አጠር ፣ ሰውነቱ ፍርጥም ያለ ፣ ድካም የሚሉት ነገር ፊቱ ላይ የማይታይበት ሰው ነው ።

«ይህን ልሰጥህ ነበር የመጣሁት» አለኝ እየቸኮለ ።"መቼም ይጣደፋል ። ሁልጊዜ ይጣደፋል ። የጊዜን ውድነት ከሁኔታው ለመረዳት ይቻላል ። ሲያዩት ለሩጫ የተዘጋጀ ይመስላል ። የማይገኝበት ቦታ የለም ። ደግሞም የትም ቦታ የለም ። እንቆቅልሽ ።

«ምንድነው ልጇ?» አልኩት የሰጠኝን ጥራዞች በጥድፊያ እገላብጨ እየተመለከትኩ ።

«የሁገአዘ መምሪያዎች ድርጅታዊ መዋቅርና የሥራ መመሪያዎች ናቸው ። ይህን እንኳን ላንተ መንገር የለብኝም..... ግን..... ብቻ በምስጢር መያዝ አለባቸው ። አሁን የቀረን ነገር ዲኖር አላማዎቹን ተግባራዊ ማድረግ ነው ። ድርጊት» አለኝ ።

የወታደራዊ ዘመቻና እቅድ መምሪያ፣የወታደራዊ ፖለቲካ መምሪያ ፣ የኢኮኖሚ ልማት ዘመቻና እቅድ መምሪያ ፣ የሕግ ርና የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ መምሪያ ፣ የኢንስፔክሽን መምሪያ ፣ የገበሬዎች ማደራጃና የግብርና ልማት መምሪያ (ገማግል) የሚሉ ጥራዞች ነበሩ ።

«ከመቸው ነው ይህ ሁሉ የተሠራው ባክህ?» አልኩት ።

«ከኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ጀምሮ ይህንኑ ስንሠራ ነው የከረምነው ። ካንድ ዓመት በላይ ፈጅቶብናል» በማለት መልስ ሰጠኝ ።

«ጥሩ ዝግጅት ነው...... እውነት...»

«አዎ ጥሩ ዝግጅት ተደርጓል ። ግን ምን ያረጋል? ተግባር ላይ ስንደርስ እንዝረከረካለን ። በዕቅድ መሥራት አይሆንል ንም ። ያዘው ጥለፈው ማለት ነው የሚቀናን ። እውነቱን ነው...... እስቲ የልደታችንን ፣ የሠርጋችንን ፣ የሞታችንን የኑሮአችንንና ያመጋገባችንን ሁኔታ አስበው ። ግብታዊነት ይበዛበታል ። በግብታዊ አሠራር እንደኛ 'ጂንየስ' የሆነ ሕዝብ ባለም ላይ ያለ አይመስለኝም ።

«ከግብታዊነት የምንላቀቅበት ጊዜ ነው የሚናፍቀኝ ። የሶሻሊዝም መሠረቱ እቅድ...... ፕላን...... ድርጅታዊና ማዕከላዊ አሠራር ነው ... ያለዚህ ሶሻሊስታዊ ሥርዓትና ግንባታ እንዴት ለማካሄድ እንደምንችል አይገባኝም» አለ ።

«እንማራለን ። ስምንት ዓመት ያንድ ሰው እድሜ አይደ ለም ። እኛ ባይሆንልን ልጆቻችን ይማሩ ይሆናል......»

«ልጆች ካፈሩን» አለ ሰቆ ።

«እንዴት?»

«ዛሬ ለሚስቱ ማን ጊዜ አለው ብለህ ነው? በድናችን ነወ ማታ ቤት የሚደርሰው ። እና ደግሞ ንዝንዛቸው ይባስ ። ደል ቶን፣ጊዜ ተርፎን ፣ ቤት ስናባርር የምንውል ነው የሚመስላቸው። እንደ እናቴ አሳብ ሳይሆን እንደ ሚስቴ አውለኝ ብሎ መነሳት ትልቅ ጸሎት ነው ። ነጋ ጠባ ስብሰባ ። ጠዋት ስብሰባ ። ማታ ስብሰባ ። እኩሌሊት ደክሞህ ቤትህ ስትገባ ከሚስትህ ጋር ስብ

ሰባ ። ሕይወት የማያቋርጥ የስብሰባ ሂደት ሆናለች ። መቼ ጊዜ አግኝተን እንደምናመርት አይገባኝም» በማለት ቀለደና ቀጥሎ ፣

«ምን የጎደለህ ነገር አለ?» ብሎ ጠየቀኝ ።

«ምንም ። ሁሉም ነገር ጥሩ ነው ። ድርጅቱም ፣ ዝግጅቱም እንከን አይወጣለትም» አልኩት ።

ኀንገት በላይ ምስጋና ሳይሆን ካንጀቴ ነበር ። ካዲስ አበባ ለመጣው ሰው ሁሉ እንደ የማዕረጉና እንደየኃላፊነቱ አመች መኖሪያ ቤት ፣ የተሟላ ቢሮ ፣ የግል ተሽከርካሪ ከነነዳጁ ፣ በሰምና በአድራሻ አደራጅቶና አዘጋጅቶ መጠበቅ በእውነት ቀላል ሥራ አይደለም።ሰለሞን ማን ሆነና ። ማለፊያ አሠሪ ነው ። ታዲያ በጅራፍ አይደለም ፣ በፈገግታ ሠርቶ ያሠራል ። አውቀዋለሁ ። ላንድ ሰው የሥራውን ግብ ከፍ ፣ ጊዜውን ደግሞ አጠር አድርገህ ከሰጠኸው የፈለገውን አከናውኖ ይቆይሀል የሚል ፈሊጥ አለው ።

«ይህን ሰሞን እንቅልፍ አልተኛሁም» አለኝ ።
የበቆሎ እሸት የሚመስለው ነጭ ጥርሱ ፣ የደስ ደስ ካለው ጥቁር ፊቱ ጋር ሲነጻጸር ይማርካል ።

«ግን የደከመህ አትመስልም» አልኩት ።
ሲያዩት አርፎ የተነሳ ሰው ነው የሚመስለው ፣ ሁልጊዜ ።

«ጥቁር ሰው ጉዳቱ ፊቱ ላይ ስለማይታይበት ይሆናል» አለኝ ፣ «ምን ባክህ አኩራፊውም በዝቶአል ።»

«ለምን?»
«ያዲሳባ ሰው ሁሉ ዓመሉን በጉያው እንደያዘ መጥቶ ነው እዚህ የተዘረገፈው ። ትንሹም ፣ ትልቁም የግል መኪና ፣ መኝታ፣ ክፍልና ቢሮ ይፈልጋል ። ለዚህ ሁሉ ሰው የግል መኪና ፣ የግል መኝታ ቤትና ቢሮ ከየት ልወልድ ነው? በእውነት ላብድ ትንሽ ነው የቀረኝ ። እየሮጥኩ ነው ውሳኔ የምሰጠው» አለኝ ።

«አይዞአችን»
«ይሄ ዘመቻ አልፎ አይቼ ብቻ ።»

ሥራው የሁግን ፖለቲካ መምሪያ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ፣ የዘመቻውን አጠቃላይ ዝግጅትና መስተንግዶ ፣ የትልቁ ጉባኤ ቅድመ ዝግጅትና የምጽዋ ፌስቲቫል ቅንብር ሁሉ እሱን የሚመለከቱ ነበሩ ። በእሱ ቦታ ባለመሆኔ ዕድሌን አመሰገንኩ ። ገሀነብ ውስጥ የምትራወጥ ነፍስ ይዞ ነበር የሚሮጠው ።

«የማያልፍ ነገር የለም ፣ አይዞህ» አልኩት ።
«ለኮንግሬሱና ለምጽዋ ፌስቲቫል ስንት ሰዎች ከመላ ኢትዮጵያ ተጋብዘው እንደሚመጡ ታውቃለህ?»
«ስንት ናቸው?»
«ወደ2115 ይሆናሉ ፣ አሁን እዚህ የሚገኙት ከ400 አያንሱም ። እየዞሩ እስቲ ይታይሃል?»

«አ ቦይ..» አለኩ ።
አንድ ነገር ሲደንቀኝ አ ቦይ፣ ማለት ይቀናኛል ።

«ኮንግሬሱ ላይ 69 የሚሆኑ የመላ ኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ተወካዮች ፣ የኤርትራ ክፍለ ሀገር የሀይማኖት መሪዎች ፣ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች አባሎች ንግግር ያደርጋሉ ። ይታየሃል? ይህ ሁሉ የኛ ሃላፊነት ነው ።

«በዚህ ላይ ለሕዝብ የሚቀርቡትን ዘፈኖችና መዝሙሮች አስቀድሞ መገምገም ፣ ፖስተሮች ፣ በራሪ ጽሑፎችን ፣ ትንንሽ መጽሔቶችን ፣ ሥነ ጽሁፎችን መፈክሮችን ማዘጋጀት አለ ። ገሀነብ ውስጥ ነው ያለነው ። ቀልድ አይደለም» አለና በረጅሙ ተነፈሰ ።

«እንወጣዋለን» አልኩት ።
«እንዲህ ዓይነቱ መንፈስ ደስ ይለኛል ። ባሁኑ ጊዜ የሚያስጠላኝ ነገር ቢኖር ስለችግር መስማት ነው ። አንገቴ ድረስ ደርሶአል ። በተለይ የግል ችግር መስማት ያቅለሸልሸኛል ። የግል ጉዳያችንን ትተን ለጋራ ዓላማ ብንሮጥ እንዴት ጥሩ ነበር ። ይገረምሀና የዚህ አገር ሰው አንድ አዲስ ድርጅት መጣ ሲሉት ቁርበት የሚያክል ማመልከቻውን ይዞ የሚሮጠው ወደዚያ ነው ። ለማንኛውም ነገር አንተ የፕሮፓጋንዳውንና የቅስቀሳውን ሥራ አጥብቀህ ያዝልኝ ። ሌላው ግድ የለም» አለኝ ።

አእምሮው ውስጥ ብዙ አሳቦች የሚተራመሱበት ይመስ ላል ። የተወሰነ ማስታወሻ ደብተር መያዝ አይወድም ። ባገኘው ቡጭቅጫቂ ወረቀት ላይ ማስታወሻ መጻፍ ያዘወትራል ። ጥሩ ነቱ የያዘውን አይረሳም ።

«የሚቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ» አልኩት ።

«ጥሩ ። እንዳልኩት ቀና አስተሳሰብ ደስ ይለኛል ። የሚያ ያበረታታኝም ይሄው ነው ። ሰው ሁሉ ምን እንደ ነካው አላው ቅም ቀና ሆኖአል ። ሁሉም ላይ ለውጥ ይታያል ። ተአምር ነው ። ይህ ዘመቻ ብዙ ነገር ሳያስተምረን አይቀርም ። በነገራችን ላይ ስለ 'ጃሚንግ'ና ፣ ከዚህ ራዲዮ ለማስተላለፍ ስለምንችልበት ዘዴ አትርሳ ። ጓድ ሊቀ መንበር አጥብቀው ያሰቡበት ጉዳይ ነው......»

«በዚሁ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር አሁን እንሰበሰባለን» አልኩት ።

«ላንበሳ አይመችሩም ፣ ለብልህ አይነግሩም ። ደህና ይዘ ህል ቻው እምባር» ብሎኝ ተፈተለከ ።

አጅሬ ሠርቶልኝ ነበር የሄደው ። ሳይታወቀኝ ያላሽከመኝ ኃላፊነት አልነበረም ። ቢሆንም ኦልከፋኝም ። ከሰለሞን ጋር መሥራት ሁልጊዜ ደስ ይለኛል ። ጥሎብኝ እወደዋለሁ ። ቀናና ግልጽ ነው ። ቶሎ ነገር ይቆርጣል ። እንደ ጳጉሜ ዝናብ እኝኝ አይልም ። ይወስናል ። መቸም ፍርሀት የሚባል ነገር ከመዝገበ ቃላቱ ውስጥ የለም ። አብዮት እያካሄዱ ለነገ ማለት አይቻልም ፣ ልክም ይሁን ስሕተት መወሰን ያስፈልጋል ፣ ፍርዱን ለታሪክ መተው ነው ይላል ።

ታዲያ አንዳንድ ሰዎች ችኩል ነው ይሉታል ። ሌሎች ደግሞ ሥልጣን ይወዳል በማለት እንደ ጦር ይፈሩታል ። ያም ፣ ይሁን ይህ ፣ ወሳኝና ቆራጥ እስከ ሆነ ድረስ እኔ ምን ተዳዬ! እንዳልኩት ወሳኝና ቆራጥ ሰው ጥሎብኝ እወዳለሁ ። ሕይወት የማያቋርጥ የውሳኔና የቆራጥነት ሂደት አይደለች፤ ሰው ድንጋይ ኦይደል ። ወሳኝና ቆራጥ መሆን አለበት ። መወሰን ፣ የሰው ልጅ እጣ ፈንታ ነው...... ።

ስብሰባው ቀጠለ ። ቢሮዬ በሰው ተሞልቶአል ። የተከና
ነቡ ሴቶችም ነበሩ ። ቤትም ሲገባ ከንብንብ የማይነሳበት አገር ።
ጉድ ነው ።

«...የመጣንበት አላማ ግልጽ ነው ። ምንም ድብቅ ነገር
የለውም ። የምንደብቀውም ነገር የለም ። ከሰፊው ሕዝብ የሚ
ደብቅ ነገር መኖር የለበትም ። ታሪክ ሠሪው እሱ ነውና ።

«ይህን ደጋግሜ የምናገረው የዘመቻውን ሕዝባዊ ባሕርይ
ለማስገንዘብ ያህል ነው ። የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ
ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ይባላል ፣ ባጭሩ ሁገአዘ ።

«አላማው ፤ በዚህ ክፍለ ሀገር ላይ ላለፉት ሀያ ዓመታት ፣
እንደ ኮሶ ተጣብተው ፣ ሰፊውን የኤርትራ ሠርቶ አደር ሕዝብ
ሠላም ሲነሱና ደሙን ሲመጡ የኖሩትን ተገንጣይ ወንበዴዎች
ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ደምስሶ ፣ በእነሱ ምክንያት የወደቀውን
ኢኮኖሚ መልሶ መገንባት ነው ።

«ጓዶች ፤ የመጀመሪያው ሥራችን ፣ ከዚች ሰዓት ጀምሮ ፣
የሁገአዘን የግንባታ ተልዕኮ ገጽታ አጉልቶ ማሳየት ይሆናል ።
ምናልባት እንደ ሰማችሁትና እንደምታዩት ፣ ተገንጣይ ወንበዴ
ዎች ፣ ካሁኑ ጦርነትና እልቂት ሊመጣባችሁ ነው በማለት ሠላ
ማዊውን ሕዝብ ማሸበር ጀምረዋል ። በዚህ የተነሳ ገበያው
እየተራቆተ ነው ። ስግብግብ ነጋዴዎችም በሁኔታው ተጠቅመው
ሕዝቡን በመዝረፍና በማራቆት ላይ ይገኛሉ ።

«የተገንጣይ ወገኖች የቅርብ ዓላማ ሕዝቡን ማሸበር ሲሆን፣
የሩቅ ዓላማቸው ፣ ሕዝቡ ሕይወቱንና አብዮቱን አማሮ እንዲ
ሸፍት ለማድረግ ነው ። የ1969 እና የ1970 ታሪክ በምንም ሁኔታ
አይደገምም ። ታሪክ ራሱን አይደግምም ። የቅጥፈት ፕሮፓጋን
ዳቸውን ተቋቁመን በማክሸፍ ሕዝቡን ማረጋጋት አለብን ካሁን
ጀምሮ ። በርዕስ አንቀጾች ፣ በሐተታዎች ፣ በዜና ፤ በራዲዮና
በቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እና የጋዜጦችንም ሆነ የራዲዮ ፕሮ
ግራሞቻችን ይዘት ሁሉ የዘመቻውን ባሕርይ ፤ ይዘትና ቅርጽ
እንዲይዙ ሆነው እንደገና መገምገም አለባቸው ። ሪፖ
ርቱ በሁለት ቀን ውስጥ እንዲደርሰኝ ያስፈልጋል ።
የዘመቻውን ወታደራዊ ባሕርይና ገጽታ ድልድዩን የምን

ሻገረው ስንደርስበት ነው እንደሚባለው ፥ ወደፊት በወቅቱ ተከታትለን እንገልጻለን ። እንዳልኩት ከሕዝቡ የምንደብቀው ነገር የለም ።

«ሳንጃ ባፈሙዝ! ወደፊት! ብእራችንን ማለቴ ነው ። እዚህ ላይ አንድ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን ፤ ውጋው! ግደለው! አባረው! ገረፈው! ከማለት እንቆጠብ ። መቸም እንደምታውቁት የዚህ ክፍለ ሀገር ችግር ውስብስብ ነው ። ባል ፥ ሚስት ፥ ልጅ ፥ እህት ፥ እኅት ፥ አክስት ፥ እናት ፥ አባት በረሀ ያልሄደበት ቤተሰብ የለም ፤ የምናካሂደው ፕሮፓጋንዳ ሁሉንም በወል የሚዉፈጭፍ መሆን የለበትም — የዘመቻውን የመደብ ባሕርይና ገጽታ ሳንዘነጋ ፤ ጥያቄ አላችሁ?» በማለት የዘመቻውን ዓላማና ይዘት ባጭሩ ገለጽኩላቸው ። ቀልዴን ነው ። አጭር ገለጻ አልነበረም ። ብዙ ነገር ነው የተናገርኩት ። መቸም የፖለቲካ ወጣኔዎች ከሚሰጡበት መተላለፊያ ላይ ድንገት መገኘት ፥ ብዙ ስለሚያሳውቅ ነው መሰለኝ ፥ ሳይወዱ ብዙ ያናግራል ። በራሱ ላይ ከፋኛ የመተማመን ስሜት ይፈጥራል ። ውሎ አድሮ እብሪት ማሳደሩ ይቀር ይሆን? በራቤ ላይ ያየሁት ነገር ጥሩ አዝማሚያ የያዘ አልመሰለኝም ። ካሁኑ ሰው ማናገር ሳይሆን ወደታች መናገር የጀመርኩ ኋላ ምን ልሆን? ሆ!ሆ! የሥልጣን አረቄ ራስ ላይ ከወጣ ኋላ አጉል ነው!

አንዱ እጁን አውጥቶ ፥ «ሙዚቃው ሁሉ አሳደው ፥ ግረፈው ፥ ግደለው ነው የሚለው ። ምን ልናረግ እንችላለን?» የሚል ጥያቄ አቀረበልኝ ።

«ጨርሶ የማያዝናጋ ከሆነ የሚያዝናና ሙዚቃ ለማቅረብ እንችላለን» አልኩት ።

«የሚያዝናኑ ዘፈኖች አሉ» አለኝ ።

«ታዲያስ?»

«ግን አብዛኛዎቹ የበረከትና የጺሐይቱ ዘፈኖች ናቸው»

«ከዛሬ ጀምሮ ይለቀቁ ። እነሱ ይዘኑ እንጂ እኛ ምን ቸገረን ። ይለቀቁ» የሚል ትእዛዝ ሰጠሁ ።

ሌላ ጥያቄ አልቀረበልኝም ። የተዘጋጁትን መፈክሮች ጓድ ሰለሞን በትረ ጊዮርጊስ ከሰጠኝ ፋይል ውስጥ አውጥቼ ሰጠኋቸው ። ሐያ መፈክሮች ነበሩ ።

«እሺ ጓዶች ፣ እነዚህን መፈክሮች ከዛሬ ጀምሮ በየሙያው እንጠቀምባቸዋለን ። መሪ ፖስተሮችና መዝሙሮችም ተዘጋጅተዋል ። ኋላ እንዲደርሷችሁ ይደረጋል» አልኳቸውና ቀጥዬም ፣ «የኛ መፈክር ደግሞ ፣ ቀናና ቀጥተኛ አስተሳሰብ ፣ ቀናና ቀጥተኛ ድርጊት መሆን አለበት ። የመጀመሪያ ሰው ቀናና ቀጥተኛ ሰው ነው — ሶሻሊስት ሰው ቀናና ቀጥተኛ አስተሳሰብ ቀናና ቀጥተኛ ጋዜጠኞች ይፈልጋል ። አብዮታዊት ኢትዮጵያ ለ'ሲኒካል' ጋዜጠኞች ከእንግዲህ ቦታ የላትም» አልኳቸው ።

ግብታዊና ስሜታዊ መሆኔ መልሶ እኔን አሳቀኝ ። እኛ ኢትዮጵያውያን እንዲያው ደመ-ትኩስ መሆናችንን በራሴ ላይ አየሁት ።

«ይሄው ነው ጓዶች» አልኩ — «ይህ ታሪካዊ ዘመቻ ከእያንዳንዳችን ያለ የሌለ የፈጠራ ችሎታችንን ይጠይቃል ። መላ የፈጠራ ችሎታችንን ሳንቆጥብ መጠቀም አለብን ።

«ግን ከግላዊነት ፣ ከስሜታዊነትና ከግብታዊነት እንድንርቅ አደራ ። የማዕከላዊ አሠራር መርሆ መጠበቅና መከበር አለበት ፣ እሺ? ቻው ።»

የከፍለ ሀገሩ የማስታወቂና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ፣ የክፍለ ሀገሩ የቴሌኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅና የአሥመራ ራዲዮ ጣቢያ ኃላፊ ወደኋላ እንዲቀሩ አድርጌ ሌሎችን አሰናበትኩ ። ሁሉም ለሥራ የነበረው ስሜትና ጉጉት ያስደስት ነበር ። ቀጥተኛ ሰዎች ፣ ቀጥተኛ ድርጊት ፣ ቀጥተኛ ውስጡ ይስቃል ልበል? ግን ከፍ ያለ ተስፋ አድሮብኝ ነበር ። ምናልባት ተሳስቼ ይሆናል ። ያብዛኛዎቹ አብዮታውያን ስህተት ብዙ ጊዜ የሚመነጨው ፣ የሰው ልጅ ባሕርይ በመሠረቱ ጥሩ ነው — ቀና ነው — ቀጥተኛ ነው ከሚለው አስተሳሰብ ነው ። ምናልባት ይሆናል ። ምናልባትም ላይሆን ይችላል ። አላውቅም ። እስካሁን ነገሩን አላረጋገጥኩም ።

«እሺ ጓዶች — ሦስታችሁ ልዩና አጣዳፊ ሥራ አለባችሁ ። ካሁኑ ደቂቃ ጀምሮ» አልኳቸው ።

የቴሌኮሙኒኬሽኑ ሰውዬ ለምን እንደተጠራ ግራ የገባው ይመስላል ። እንደ ዘሎ ረጅምና ግዙፍ ነው ። የራዲዮው ሰውዬ ደግሞ ባንጻሩ አጭር ፣ ቀይ ፣ ዓይነ ፈጣጣ ነው ። ዓይኑ ወደ ውጭ ስለሚጎለጎል ሲያዩት ሞኝ ይመስላል ። የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤታችን ኃላፊ እንደ ሞኝ ዝም ብሎ ይስቃል ። ሁልጊዜ የሚያስቀው ነገር ምን እንደሆነ አይገባኝም ። ሰው ሁሉ አስቂኝ መስሎ ይታየው ይሆን? ራስ በራና ጉንጫም ነው ።

«ጓድ!» አልኩት የራዲዮውን ሰውዬ — «ዛሬ ከቀትር በኋላ ጀምሮ ፣ ዛሬ ባይቻል ግን ከነገ ጧት ጀምሮ ፣ በምንም ሁኔታ የወንበዴ ራዲዮ ጣቢያ የሚያሠራጨው ፕሮግራም መዘጋት...... አ......ጀም መደረግ አለበት ።»

የሻዕቢያ ራዲዮ ፕሮግራም ሥርጭት ሰዓት ፣ ጣቢያው የሚጠቀምበትን ሞገድና ፍሪኩዌንሲ ከመጣልኝ የሚስጢር ፋይል ውስጥ አውጥቼ ሰጠሁት ።

ወደ ውጭ በሚጎለጎሉት ዓይኖቹ መረጃውን ተመለከተና ፣ «እንዴት?» አለኝ ።

«እንዴት ምን?»

የቴክኒክ ሰዎችን ዝንባሌ በመጠኑም ቢሆን አውቃለሁ ። አመል ሆኖባቸው አስቀድመው ይቻላል የሚሉት ነገር የለም ። ችግር መደርደር ይቀናቸዋል — እንደተቀሩት ሌሎች ፕሮፌሽናሎች ችግር የሚያደሩ ኤክስፐርቶች ።

«በቂ ቴክኒሻኖች የሉንም.....»

«መረባረብ ነው.....»

«ትራንስሚተሩም ሎድ ሲበዛበት ሊቃጠል ይችላል.....»

«እንዳይቃጠል መንከባከብ.....»

«በዚህ ላይ ደሞ በኮምቢሽታቶ ወደ ትራክ ቢ ቴክኒሻኖችን የሚያመላልስ በቂ ሰርቪስ የለም ። ትራክ ቢ ከዚህ ሰባት ኪሎ ሜትር ነው ። ከከተማ ውጭ ስለሆነ ከመሸ በኋላ ወደ ከተማ መግባት አይቻልም ።»

«ጓድ — ስለሰርቪስ ካሌታህ ጋር ተነጋገርበት ። ካስፈለገም እዚያው ማደር ፣ ሌላ አማራጭ የለም ። የሻዕቢያ ራዲዮ ጣቢያ

ቀጣፊ ምላስ መቆረጥ አለበት ። እንዴት እንደምታደርገው የኔ ጉዳይ አይደለም ። ውሳኔውን ተግባራዊ ማድረግ ያንተ ፈንታ ነው ። ኤክስፐርቱ አንተ ነህ ። እኔ አይደለሁም ። ሥራው በምንም ሁኔታ መሠራት አለበት ። ተግባባን ጓድ?» አልኩት ።

ፊጣጣ ዓይኖቹ የዛሰውን ወደ ውጭ ተንሰንሱ ። አብድ ነው ወይስ ጅል? የሚል ይመስላል ። እርግጠኛ ነኝ ። ይህን ነበር በልቡ የሚለው ። ቴክኒሻኖችን እውቃቸዋለሁ ብያለሁ ። በእነሱ ዓይን ሌላው ሁሉ ሰብድና ቂል ነው ። ምናልባት ልክ ሊሆኑ ይችላሉ ። የምናጠልቀው የሙያ መንጽራትን ጉድለት አንዳንዴ ወይም ብዙ ጊዜ እውነቱን አጣሞ ያሳያል — ሙያዊ በሽታ!

ወደ ቴሌ ሥራ አስኪያጅ ዞር ብዬ ፣ «ጓድ ፣ ከሥራ ላይ ስለጠራሁዎት ይቅርታ እለምናለሁ ። ግን ሥራው በጣም አጣዳፊ ስለሆነ ነው» አልኩት ።

የማስታወሻ ደብተሩን እያዘጋጀ ፣ «ምንም አይደለም ። ምን ነበር?» አለኝ

ደንበኛ ቢሮክራት ነው ፡ ወይም መሰለኝ—ግዘፋና ስሜት አልባ እንደቢሮክራሲ ። ማን ነህ አንተ ለመሆኑ? የሚል ይመስላል አፉ አውጥቶ ባይጠይቅም ።

«አዎ ፣ አንድ ትልቅ ጉባዔ እዚህ ይደረጋል ። የጉባዔውን ሂደት ከዚህ በራዲዮ ለመላ ኢትዮጵያ እንድናሰማ ይፈለጋል ...»

«እና?» አለኝ ቅንድቦቹን ከፍ ፣ ዝቅ አድርጎ ።

«እና ቤተ መንግሥት ካለው የትንግሌ አዳራሽና በኛ ስቱዲዮ መካከል 'ኬብልና' ሌላም አስፈላጊ ነገር ሁሉ እንዲዘረጋ ነው .....።

«መቼ?» አለኝ ።

«ባምስት ቀን ውስጥ፣ባብዮት አደባባይና በሳባ ስታዲዮምም ተመሳሳይ ሥራ መሠራት አለበት ።»

እንደገና ቅንድቦቹን ከፍ ፣ ዝቅ አደረገ ። ምጸታዊ ፈገግታ ጥቁር ፣ ረጂም ፊቱ ላይ ይታያል ። ረጂም ፊቱ የባሰ ጦት ረዘመ ።

«ትእዛዙ በጽሁፍ ቢሆን ጥሩ ነበር» አለኝ ።

«አሁን ለቢሮክራሲ ጊዜ የለንም ጓድ ፡፡ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ነው ያለነው» አልኩት በንዴት ፡፡

በዚህ በኩል ክርክሩ አላዋጣ ስላለው ነው መሰለኝ ነገሩን በማዞር ፡ «ሥራው መቻሉም'ኮ ገና በውል የታወቀ አይደለም» አለኝ ፡፡

«መቻል አለበት ፡፡ የማይቻልበት ምክንያት የለም ፡፡ ሂደቱን የተጓጓለጠሽ ማድረግ ነው» ከማለት ሌላ የምለው ነገር አልነበረኝም ፡፡

«እንዴት፣ ያዲሳባ ራዲዮ ጣቢያ ከዚህ የሚተላለፈውን ፕሮግራም ተቀብሎ 'ሪሌይ' እንዲያደርግ ነው እንዴ?» — የማስታወቂያ ሚኒስቴሩ ሰው ነበር ፡፡ እንደ እሱ ድዱን ገልፍጦ እየሳቀ የሚናገር ሰው አላየሁም ፡፡

«አዎ — ጓድ ፡፡ ምናልባት ለሦስትና አራት ቀኖች ከዚህ የሚተላለፈውን ማንኛውንም ነገር እየተቀበለ 'ሪሌይ' እንዲያደርግ ነው የሚፈለገው ፡፡ ቀኑን ሙሉ — ለሦስትና አራት ቀኖች» ካልኩት በኋላ በተጨማሪ ፡ «ከዛሬ ጀምሮ ምናልባት ለጥቂት ወሮች አሥመራ ዋና ከተማችን ሆናለች ፡፡ ዘመቻውን በሚመለከት አሥመራ ናት የውጊያ ማዕከል ተገባባንን በነገራችን ላይ 'የጃሚንግንና' የሪሌይን ሥራ ተከታትለህ ማስፈጸም ያንተ ኃላፊነት ነው ፡፡ የጃሚንጉን ሥራ በነገው ዕለት የሪሌቶን ባምስት ቀን ፡፡ ይኸው ነው ጓዶች» አልኳቸው ጮህ ብዬ ፡፡

ድምጼም የባለሥልጣን ድምጽ ነበር ፡፡ የምጠቀምበትም ዘዴ የለየለት የባለሥልጣን ዘዴ ነበር ፡፡ መቸም ኃላፊነትን ተቆ ብሎ ወደ ታች መወርወር የተለመደ ዘዴ ሆኗል ፡፡ እኔም እየተ ካንኩት ሳይሆን ይቀራል፣ ደግሞ የፍጥነቱ!

ስልኬ ጮኸ ፡፡ ሦስት ስልኮች ተደርድረዋል ፡፡ የትኛውን እንደማነሳ ግር አለኝ ፡ የውስጥ ስልኬ ነበር ፡፡

«ሀሎ?»

«ሰሎሞን ነኝ....»

«እሺ ጓድ....»

«ለምሳ አልሄድክም እንዴ?»

የእጅ ሰዓቱን ተመለከትኩ ። ሰባት ሰዓት አልፎአል ። አልራበኝም ። ለማንኛውም ነገር በተወሰነ ሰዓት የመመገብ ልምድ የለኝም ። የጋዜጠኞች ልምድ ነው እንዳልል አንዳንድ ሆዳሞች አይታጡም ።

«ቀስ በል» ሲል ለራሱ የማይጠቀምበትን ምክር መከረኝና፣ «አሁን የደወልኩት ልክ በስምንት ሰዓት ጠቅላላ ስብሰባ መኖሩን ልነግርህ ነው ።» አለኝ ።

«ምን ነው ቦታው?»

«ቤተ መንግሥት ። ጓድ ሊቀ መንበር ቢሮ ። ልክ በስምንት ሰዓት እ! ቻው.....»

ስልኩን አኖርኩ ።

«ጓድ አንድ ነገር ግልጽ አልሆነልኝም» አለኝ የከፍለ ሀገሩ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሰውዬ ።

«ምን?»

«የዚህ የሁገአዘ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ክፍልና የኛ መሥሪያ ቤት የሥራ ግንኙነት ግልጽ እንዲሆንልኝ ፈልጌ ነው» አለኝ።

በሌላ አነጋገር አንተ ማን ነህ? ነበር ያለኝ ። ልክ ነው ። በእሱ ቤት ማንም ምንም አይደለሁም ። እሱ የክፍለ ሀገሩ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት — መለስተኛ የማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊ ነው ። እኔ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መምሪያ የዋና ክፍል ኃላፊ ነኝ ። እንዴት ብሎ ሽቅብ ይየኝ፣ ግድ የለም ። ነገሩን ከራሴ አንጻር በግል የማየቱን ጉዳይ ወደ ጎን ትቼ፣ «አዎ ጓድ ፣ ጥሩ ጥያቄ ነው ። ከኢሠፓአኮ ፣ ከወታደራዊ ክፍል ፣ ከማስታወቂያ ሚኒስቴርና ከሌሎችም መሥሪያ ቤቶች የተውጣጡ ብዙ ጋዜጠኞች ፣ ፎቶግራፍና ፊልም አንሺዎች እዚህ መጥተዋል ። ሁገአዘ የራሱ ፖለቲካ መምሪያና በዚህ መምሪያ ሥር የሚገኝ የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ክፍል ይኖረዋል ።

«የሁገአዘ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ክፍል ደግሞ በሥሩ የዜና ፣ የሕትመት ፣ የራዲዮና የቴሌቪዥን ንዑስ ክፍሎች ይኖሩታል ። ድርጅታዊ መዋቅሩ — የሥራ መመሪያው ከነጊዜ ቻርቱ ፣ እንዲሁም የሥራው ቅደም ተከተል — ስትራተጂውና ታክቲኩ

በሁለት ፥ ሦስት ቀን ውስጥ ተዘጋጅቶ ይሰጥሀል ። ሁኅአዘን በሚመለከት ስለሚተላለፈው ማንኛውም ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ የሚሰጠው መመሪያ ከዚህ ይሆናል ። ተግባባን ጓድ?» አልኩት።

«ደህና»
«ምን ቅር ያለህ ነገር አለ?»
«ምንም ።»

«ጥሩ ። ግን...... እዎ...... ካዲሳባ የመጣን ሰዎች የናንተን ሥራ ለማገዝ......እ...... ለማጠናከር ነው እንጂ እናንተን ለመተካት ወይም ሥራችሁን ለመሻማት እንዳልሆነ በግልጽ መታወቅ አለበት ። እና ካሁኑ ሥራችንን በቀና መንፈስና ጥሩ ቅን ጅት ካልጀመርነው ኋላ በኃላፊነት ያስጠይቀናል ።» አልኩ ቃላቴን እኝክ እያደረግሁ ። በዚሁ ንግግሩን አላቆምኩም ። ቀጥዬ ፥ «ከመሐል ሀገር ለዚህ ዘመቻ የመጣን ሰዎች ስለ ኤርትራ ክፍለ ሀገር ችግርና መፍትሔ ይበልጥ እናውቃለን ፥ ሳብዮቱ ይበልጥ እንቆረቆራለን ወይም ለተያያዝነው ቀይ ኮከብ ዘመቻ መሳካት የበለጠ እናስባለን የሚል መንፈስ ያለን አይመስለኝም ። ካለ ስህተት ነው ። ካሁኑ መታረም አለበት ። ነገር የሚያበላ ሸውም እንዲህ ዓይነቱ ዝንባሌና አስተሳሰብ ነው ። መፍትሔ እናገኛለን ብለን የባሰ ችግር እንዳንፈጥር መጠንቀቅ ያስፈል ጋል ። ፈረንጆች እንደሚሉት ፥ የመፍትሔ እንጂ የችግር ፈርጅ ለመሆን አልመጣንም ። በቂ ችግር ፈጣሪዎች አሉ ። ተጨማሪ አያስፈልገንም ።

«በነገራችን ላይ...... ሳልረሳው...... የኅብረትና የኢትዮጵያ ጋዜጦች ሥርጭት ቁጥር ከፍ ማለት አለበት ። ስለገንዘብ አት ስጋ ። እና ደግሞ ባማርኛና በትግርኛ የ45 ደቂቃ ፕሮግራሞች ጠዋት ፥ ጠዋት — ካሥራ ሁለት ተኩል እስከ ሁለት — እንጀ ምራለን ። ባምስት ቀን ውስጥ ። የፕሮግራሞቹ ቅርጽና ይዘት እንደሁኔታው የሚያወላዳ ዓይነት ቢሆን ጥሩ ነው ። ይኸም ያንተ ኃላፊነት ነው ። አምስት ቀን ። መልካም ሥራ» በማለት ሸኘኋቸው ።

አምስት ቀኖች ። ደስተኛ ሰዎች አልነበሩም ። እኔም አልነ በርኩም ። ጨካኝ እንኳን አይደለሁም ። ግን ሥራው መሠራት

አለበት ። ምን ምርጫ ይኖራል? ሕይወት የግዴታዎች ሰንሰለ-ናት ። ኃላፊነት ያስጨንቅናል መሰለኝ ። ለማንኛውም ነገር ብዙ ነበር የተናገርኩት ። ንግግር! ንግግር! ንግግር! የጊዜያችን ምልክት ። አንዳንድ ሰዎች ሶሻሊዝምን ከንግግር ጋር ማያያዝ ሳይዮምሩ አልቀሩም ። ብዙ ንግግር ትንሽ ሥራ ። የለም ። ሌሎች ደግሞ ከስብሰባ ጋር ያያይዙታል ። ስብሰባ! ስብሰባ! ስብሰባ! ግምገማ! ግምገማ! ግምገማ! ብዙ ስብሰባ ። ብዙ ግምገማ ትንሽ ውጤት ። ሌሎች ደግሞ ከመፈክሮች ጋር ሳያያይዙት አይቀሩም ። መፈክር ፣ መፈክር ፣ መፈክር ፣ ደግሞ በዚህ ላይ የመጣደፋችን ፣ የመቻኮላችን ፣ የሩጫችን ነገር! አይጣል ነው ። ድርጊት! ለመሞት ጊዜ የለም ። ለማረፍ — ለማፍቀር ጊዜ የለም ። አብዮት! ልጆችዋን ትበላለች አሉ ? ከውጭ የታዘዙት ካሜራዎች ጉዳይ አሳሰበኝ ። ትንሽ ጸሎት በልቤ አደረስኩ ።

ተነስቼ ወደ ስብሰባ አዳራሽ ሮጥኩ.....

# ድኅሬ ቀትሬ

አዳራሹ በሰው ተሞልቷል ። ሁሉም እንደ ፕሮቶኮሉ ነበር የተቀመጠው — በተዋረድ ። ስም ስማችንን የያዘ ካርድ ከፊት ፊታችን ተቀምጧል ። ስሜ የተጻፈበትን ካርድ አይቼ ተቀመጥኩ ። የተያዘልኝ ቦታ የመጨረሻው ወንበር ነበር ። ‘ቀይ ኮከብ’ ዓርማ ያለበት የሁግአዘ ልዩ ማስታወሻ ደብተር ከያንዳንዳችን ፊት ጠረጴዛ ላይ ተደርድሮአል ። የሚያጨስ የለም ። ከረባት ያላሰረ ሰው የለም ። ሁሉም እንደ አቅሙ ታንቋል ። ለውጥ ይታያል ። መጎፈር — ጺም ማስረዘም — አለከራባት ደረት ገልብጦ ሽጉጥ አንገድሮ መጎማለል — አለመበጠር ፣ አለመታጠብ — ፕሮቶኮል አለመጠበቅና አለመከባበር ፣ እጅጉርድ ካኪ ኮት አጥልቆ መንጠልጠል ፣ እንደ አብዮተኛነት የሚታይበት ጊዜ ያከተመ ይመስላል ። ሥነ ሥርዓት ሰፍኗል ። አብዮት ተቀልብሷል የሚል ይጠፉ ይሆን! መቸም ሥርዓት አልበኛነት የሚናፍቃቸው አንዳንድ ሰዎች አይታጡም ።

በትልቁ የተሠራ የሁግአዘ ድርጅታዊ መዋቅር ቻርት ተዘርግቷል ። ሌሎችም ብዙ ቻርቶችና የጊዜ ዕቅዶች ተዘርግተው ይታያሉ ። እውነትም ዝግጅቱ ብዙ ጊዜና ጥረት ሳይጠይቅ አል

ቀረም አልኩ በልቤ ። ዝርዝር ነገሮች ሳይቀሩ የታሰበባቸው ይመስላል ። ወደ ስብሰባው አዳራሽ የሚያስገባው በር ድንገት ተከፈተ ። ጓድ ሊቀ መንበር መጡ ። ሁሉም ከመቀመጫው አንድ ላይ ሲነሳ ትርምስ ተፈጠረ ።

«እንደምን ዋላችሁ ጓዶች ። ቁጭ በሉ ። ቁጭ በሉ» በማለት እንዳንቆም ቶሎ ብለው ተቀመጡ ። ጥቁር ባለሸንትር ልብስ ፣ ውሀ ሰማያዊ ሸሚዝ ፣ መሠረቱ ነጭ ሆኖ ጥቁር ጥለቶች ጣል ጣል ካሉበት ከራባት ጋር ለብሰዋል ። ፈገግታቸው ሞቅ ብሏል ። ደስ ያላቸው ይመስላሉ ። ያለቃህን ፊት አይተህ እደር! የሚሉት ፈሊጥ ትዝ አለኝ ። ሁሉም ፈገግ ብሎአል ። እኔም ፈገግ አልኩ ። በሥልጣን አካባቢ ያሉ ሰዎች አንድ ዓይነት ባሕል ወይም ልምድ ይመሠርታሉ ልበል!

የንስር ዓይኖች የሚመስሉት የሰውዬው ዓይናች ከጉድጓዶቻቸው ውስጥ ወዲህና ወዲያ ማለት ጀመሩ ። ትሕትናቸው አይበገሬ መንፈሳቸውንና ቆራጥነታቸውን ይደብቃል ። ሰውዬው— እሳትና ውሀ ፣ የበግ ግልገልና ጥቁር ነብር ሁሉም አንድ ላይ ። ሲያዩዋቸው በሰው ላይ የሆነ እምነት ያሳድራሉ ።

«ጓድ ሊቀ መንበር ፣ ልንጀምር እንችላለን» የሁገአዘ ዋና ጸሐፊ ነበሩ የተናገሩት ። ክብ ፊታቸው ፣ ጥርሳቸው ፣ ዓይኖቻቸው ከራስ መላጣቸው ጋር የልብና የአእምሮ ንጽሕናና ሐቀኝነት ሳቅ አንድ ላይ የሚሰቁ ይመስላሉ ። ሲናገሩም ያስቃሉ ። ፊደላትን ፣ በተለይም እንደ ሁ ፣ ብ ፣ ጓ እና የመሳሰሉትን አያጠብቁም።'ን' ፊደልን ደግሞ የትም ነው አምጥተው የሚደነቅሯት ። 'ታዕታይ — ላዕላይ — ድኅረ — ማለት ከነ'መራችሁ ወዲህ አማርኛ ሲገባኝ ጀምሮአል» ይላሉ ። መቸም ቀልድ አያጡም ። አንድ ጊዜ የተናገሩት ቀልድ ትዝ ይለኛል «አንድ አዛውንቲ ነበሩ ትርፍ ገዛ...ቤት ፣ ቤት ተወርሶባቸዋል ። በ68 ቀበሌን ሄደው ሲመዘገቡ ስድሳ ዓመቴ ነው ብለው ነበር ። በ74 እንደገና ሲመዘገቡ ዕድሜአቸው ሲጠየቁ ጊዜን አሁንም 60 ዓመት ብለው ተዛረቡ..... ተናገሩ ። የቀባሌውን ሹም ስዮስቱን ዓመት ወዴት አስቀሩት አባቴ? በ68 ሲመዘገቡም 60 ዓመቴ ነው ብለው ነበር ሲላቸውን ጊዜ 'ስድስቱን ዓመት አትቁጠርብኝ ልጄ አልኖርኩትም' አሉ ይበሀል .... ይባላል ።»

ስቃው ማሳት ይወዳሉ ። አይ አለባበስ! አለባበስ መቸም ማንም በንድ የለም ። በወትር ቲቅ እንዳሉ ነው ። ከራስ በነገራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ። ጠጉር እንኳን የላቸውም ። «እግር ከሚበዛበት መንገድ ላይ ሳር አይበቅልም» ይላሉ በራሳቸው ላይ ሲቀልዱ ። በራስ ላይ መቀለድ መቻል ጸጋ ነው ። በጣም ነው ። ብዙዎቻችን እንዲህ ዓይነቱን ጸጋ ከፉ ዕድል ሆኖ አል ታደልንም ። ዕድሜአቸው ይህን ያህል አይደለም ። ግፋ ቢል ከሀምሳ አይበልጡም ። ግን ፣ በመንፈስ ከማንኛውም ወጣት ይበልጥ ወጣት ናቸው ። ወጣትነት በዕድሜ ብቻ መቸ ሆነ የሚለካው? ያለን መንፈስም ከቁጥር ይገባል ። ሁሉንም 'ነትስ' ነው የሚሉት ። ለእሳቸው ሁሉም 'ነትስ!' ነው ። ጣፋጭ ነትስ!

የስብሰባው አጀንዳ ለሁሉም ግድስ ነበር ።

«ጓደኞች ፣ የዛሬው ስብሰባችን ዓላማ ፣ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻችንን አጠቃላይ ቅርጽና ይዘት በሚገባ ተረድተን ስናበቃ በየግንባራችን የተደቀነ ውን ታሪካዊ ሥራ ዛሬ ፣ ነገ ሳንል ለመጀመር እንድንችል ለማ ድረግ ነው» በማለት ንግግራቸውን ጀመሩ ።

'ይህ ቀይ ኮከብ' በሚል ስያሜ ከእንግዲህ የሚታወቀው ታሪካዊ ዘመቻችን የቆምንለት የመደብ ትግል አካል እንደመሆኑ ማኅበራዊ ፣ ባሕላዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ገጽ ታዎችና ይዘቶች አሉት ። ይህ ብሔራዊ እና አብዮታዊ ዘመቻችን ዋናው ባሕርይ ሕዝባዊነቱ ነው ።

«ቀደም ሲል ከታደላችሁት ድርጅታዊ መዋቅርና ሥራ መመሪያ ለመረዳት እንደሚቻለው (ሁላችሁም እንደደረሳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ)» ከትንሽ ቆይታ በኋላ «የዘመቻው ዓላማ ፣ ይህን ሰሜናዊ ክፍለ ሀገራችንንና በዚህ ክፍለ ሀገር የሚገኘውን ሠርቶ አደር ሕዝብ ፣ በዚህ አካባቢ የኢምፔሪያሊዝም አለኝታ ከሆኑት ከታሪክ አተላዎች ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነጻ እያወ ጣን ፣ ከጠመንጃ አፈሙዝ ማብግብ ጎን ለጎን ማኅበራዊ ፣ ባሕላዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንባታ ሥራዎች በማካሄድ ፣ የክፍለ ሀገሩ ሠርቶ አደር ሕዝብ እንደተቀሩት የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች የአብዮታችን ፍሬ ቀማሽና ተቋዳሽ ብቻ ሳይ

ሆን ፣ ራሱም ላብዮት ሂደትና ጥንካሬ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ነው ።

«የቀይ ኮከብ ዘመቻችን ሦስት አበይት ምዕራፎች ይኖሩታል ። አንደኛው ምዕራፍ ለዘመቻው የሚያስፈልጉትን አጠቃላይ ጥናቶችና ዝግጅቶች ማድረግ ነበር ። አጠቃላይ ጥናቱና ዝግጅቱ አልቆ ይኸው ዛሬ እዚህ ደርሰናል ። አሁን የቀረን ሥራ ዘመቻውን ማብሰር ሲሆን ለዚህም አስፈላጊው መድረክ እየተዘጋጀ ነው ። በቅርቡ አንድ ታላቅ ጉባኤ ይደረጋል ። እንዲሁም ከጉባኤው ጋር የተያያዘ አንድ ታላቅ የምጽዋ ፌስቲቫል ። ሁለተኛው ምዕራፍ የጦር ሜዳውን ፍልሚያ መጀመርና የፈረሱትን የኢኮኖሚ አውታሮች መልሶ ማቋቋም ይሆናል ። ሦስተኛው ምዕራፍ ነጻ በሚወጡትና በተቀሩትም ሥፍራዎች ሁሉ የክፍለ ሀገሩን ምዝብር ገበሬዎች ማንቃት ፣ ማደራጀትና ማስታጠቅ ይሆናል ። ወሳኙ ነገር ድርጅት ነው ። እና የመጨረሻ ግባችን ገንጣዮችን ማንበርከክ ብቻ አይደለም ። የሩቅ ግባችን በዚች ምድር ሶሻሊዝምን መገንባት ነው ።

«ጓዶች! ዛሬ በዚች ሰዓትና ሥፍራ የምንገባው ቃል ቀላል አይደለም ። ነገ ፣ ታሪክና የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይጠይቀናል ። ይህን ስል ፣ ሐያ ዓመት ሙሉ ሲደራጅና ሲታጠቅ የቆየውን የወንበዴ መንጋ ከዚች ገጸ ምድር ጨርሶ እናጠፋለን ማለቴ አይደለም ። አከርካሬታቸውን ለመስበር እንደምንችል ግን ጥርጣሬ የለኝም ።

«ዛሬ የአብዮታችን አለኝታ ፣ ጋሻና መከታ የሆነው አብዮታዊ ሠራዊታችን ከምን ጊዜውም ይበልጥ ተደራጅቷል ፣ ታጥቋል ። ብሔራዊና አብዮታዊ ተልዕኮውን ያውቃል ። ቤቱ ፣ ንብረቱ ፣ ምቾቱ ሳይል ፣ በቀበሮ ጉድጓዶች ተሠስኖ በቆራጥነት ይዋጋል ፣ በየደቂቃው ከጠላት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ እየተናነቀ ይዋደቃል ። ይህ በኢትዮጵያ ውድ ወጣት ልጆች የተገነባው ሠራዊታችን የሚጠይቀው ዋጋ ፣ ከአብዮቱና ከብሔራዊ አንድነቱ ሌላ ነገር የለም ። እዚህ በምትቆዩበት ጊዜ ኑሮ አይመቻችሁ ይሆናል ። ግን ማሰብ ያለባችሁ በቀበሮ ጉድጓድ የሚኖረውን አብዮታዊ ሠራዊታችንን ነው ። » በማለት ለጊዜው ንግግራቸውን ገታ አደረጉ ።

ሌሎችን እንጃ እኔን ሬሜት ያዘኝ ። መላ ሰውነቴን ነዘረኝ ። እንባዬም መጥቶ ይተናነቀኝ ጀመር ። በንግግራቸው ከመመሰጤ የተነሳ ማስታወሻ መውሰድ ካቆምኩ ቆይቻለሁ ። ሰውዬው ያለምንም ማስታወሻ በቃል ሲናገሩ ቃላት እንዴት እንደሚፈልቁላቸውና አሳብ እንዴት እንደሚሳካላቸው ሁልጊዜ ይደንቀኛል ። የተጻፈ ንግግር ከማንበብ ምናለ ሁልጊዜ በቃል ቢናገሩ፧ እላለሁ ። ሰውየው በቃላቸው ሲናገሩ ማንነታቸው በሙሉ ይታያል ፤ ይሰባል እና ሰሚን ይቀሰቅሳል ። ምን ዓይነት ግሩም ተሰጥኦ! አንድ ጊዜ በ1969 አንድ ሚኒስትር ፤ «ምናለ እኚህ ሰው የሚያነቡትን ንግግር ትተው በቃል እንዲናገሩ ብታደርጓቸው፧ በቃል ሲናገሩ ችግሩም ሆነ ተስፋው በይበልጥ ይሰማኛል ፤ ይታየኛል ። ጥቁር ዕንቁ ናቸው» ብሎ ሲናገር የሰማሁት ትዝ ይለኛል ። ያ ሚኒስትር አሁን ባገር የለም ።

ጉባዔ ሲመሩ ብዙ ጊዜ አይቻቸዋለሁ ። ሁሉም የሚናገረውን በታላቅ እርጋታና ትእግሥት የማድመጥ ጥሩ ተሰጥኦ አላቸው ። እንደሚመስለኝ በማዳመጥ ነው ብዙ ነገር ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊማሩ የቻሉት ። የሰውን አሳብ መስማት አይሰለቻቸውም ። እና የሚመሩትን ጉባዔ ጠቅላላ ሂደት የማሰባሰብና ለውሳኔ የሚያበቃ አሳብ የማቅረብ ችሎታቸው ብዙውን ጊዜ ያስገርመኛል ። የነገር ብልቶችን ለይቶ የማውጣት ግሩም ተሰጥኦ አላቸው ። አስተሳሰባቸው ሁልጊዜ ቀጥተኛና ግልጽ ነው ።

በሚሰጡት ቀጥተኛና ግልጽ ትንታኔ የኢኮኖሚ ሊቃውንትና ሌሎች ኤክስፐርቶችን ያስንቃሉ ። ወደኋላ የሚሉት ወይም የሚደብቁት ነገር የለም ። ሐቁን ፍርጥ ያደርጋሉ ።

እኔ እንዳየሁት ሌላም ተሰጥኦ አላቸው ። ደከመኝ የሚል ቃል ቋንቋቸው ውስጥ የለም ። ሥራ ያዝናናቸው እንደሆን አላውቅም ፤ ግን ይሠራሉ ። ለትንሹም ለትልቁም ነገር እኩል ዝግጅት ያደርጋሉ ። አንዳንዴ ሳስብ በዝርዝር ጉዳዮች ተውጠው እንዳይቀሩ እሰጋለሁ ። በሶማሌ ጦርነት ጊዜ ጥይት ሲቆጥሩ አይቼ ፤ ደከመኝ የማይል ፤ ካስፈለገ ሀያ አራት ሰዓት ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ እንዲህ ያለ ወጣት መሪ ይዘን ፤ ሁላችንም እንደ እሱ ብንሠራ ይህችን ውብ ፤ ግን አሳዛኝ አገር የትና የት ልናደርሳት በቻልን ነበር የሚል አሳብ አደረብኝ ። ግን ብዙዎቻችን

ሥራ መቾ ሆነ የሚቀናን። ሌላውን ማጋፈጥና ለሚደርሰው ጥፋት ተጠያቂ ማድረግ እንጂ! ያገር ጉዳይ የአንድ ወይም ጥቂት ሰዎች ጉዳይ ሊሆንም አይችልም ።

ሰውየው ንግግራቸውን ቀጠሉ — «ያለ ዕድል ሆኖ ባንድ እጅ ውጊያ ፣ በሌላ እጅ የግንባታ ሥራ ማካሄድ እስካሁን እጣ ፈንታችን ሆኖ ቆይቷል ። ቢሆንም የተነሳንበት ዓላማ በዚች ምድር ሶሻሊስታዊ ሥርዓት ለመገንባት ነውና የተጠየቀውን ማንኛውንም መስዋዕትነት እንከፍላለን ።

«ይህን ዘመቻ ለማቀድና ለማዘጋጀት ካንድ ዓመት በላይ ጊዜ ፈጅቶብናል ። ምናልባትም ከፍተኛ ጊዜና መረባረብ የጠየቀን ዘመቻ ቢኖር ይኸኛው ነው ። ከዚህ ቀደም ካካሄድናቸው ዘመቻዎች ያገኘናቸውን ልምዶች መሠረት አድርገን ነው የተነሳ ነው ። ከዚህኛውም እንማራለን ። አብዮት ለዘላለም የማይዘጋ ትምህርት ቤት ነው ።

አንዳንድ ሰው ማጨብጨብ ልማድ ሆኖበታልና ፣ ከመካከላችን አንዱ ሲጨበጨብ ሁላችንም አጨበጨብን ። አንዳንዱማ ገና «ጓዶች» ሲባል ማጨብጨብ ይጀምራል ። በተገቢ ቦታ ፣ ለተገቢ ጉዳይ ከልብ ማጨብጨብም እኮ ብስለትና ንቃት ሳይጠይቅ ይቀራል! አላዋቂ ሳሚ መሆን ደግ አይደለም ።

ብሩህ ፈገግታ ፣ ያው የተለመደው ትሕትና የተመላበት ጠን ካራ ባሕርዩ — ቀጠሉ ፣ «ይህ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ የታቀደውና የተዘጋጀው የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ የሰሜን ተገንጣይ ወንበዴዎችን በማስመልከት የሰጠውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ነው ። ውሳኔውን እጠቅሳለሁ ።»

ውሳኔውን አነበቡ ። የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ያሳለፈው ውሳኔ ፤

በኤርትራ ክፍለ ሀገር ውስጥ አብዮቱ በፈጠረው አመቺ ሁኔታ ላይ በመመሥረት ልማት እንዳይፋጠንና እንዳይስፋፋ የሚያውኩትን ጸረ አንድነትና ጸረ አብዮት ወንበዴ

ዎችን በመመንጠርና በዚያ በኩል ኢምፔሪያሊዝምን እለ ኝታ በማሳጣት የሰላም ዋስትና እንዲረጋገጥ እንዲደረግ ፤

2. በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከወንበዴዎች ጋር በመሆን ወይም በመተባበር እገራቸውን የበደሉና አሁን ግን ስሕተታቸውን በመገንዘብና በመጸጸት ወደ አብዮቱ ሠፈር የሚመለሱት በሠርቶ አደሩ የእዲስ ኅብረተሰብ ግንባታ ትግል ውስጥ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንዲደረግ ፤

3. የምሥራቅና የደቡብ ኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በአብዮታዊ ሠራዊታችን ጎን በመሰለፍና በከፍተኛ መስዋዕትነት የሶማሊያን ወረራና ፣ ወንበዴዎችን ቡርቦራ በመመከትና በአጭር ጊዜ ውስጥ በድል አድራጊነት በመውጣት ዛሬ በከፍተኛ ወኔ የግንባታውን ትግል እንደተያያዝነው ሁሉ ፤ በኤርትራ ክፍለ ሀገር ውስጥ ያለውም የሰፊው ሕዝብ አካል ለተሟላ ሰላሙ መረጋገጥና ለግንባታው ትግሉ መፋፋም እስካሁን በአርሱም ተሳትፎ በተቀዳጃቸው ድሎች ላይ በመመርኮዝ ከአብዮታዊ ሠራዊታችን ጋር ከንዱን በማስተባበር ሲፈታተኑት ፤ ለወርደት ሲዳርጉትና ሲነግዱበት የኖሩትን ወንበዴዎች ጨርሶ በማስወገድ አኩሪ ታሪኩን እንዲያድስ ‹ኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል» የሚል ነበር ።

ሰውዬው ኢሠፓአኮ የሰጠውን ውሳኔ አንብበው ከጨረሱ በኋላ ፤ «ጓዶች ፤ የዚህ ታሪካዊ ዘመቻ ዓላማና ተግባር በጭሩ ይህን ታሪካዊ ጥሪና ውሳኔ ተግባራዊ ማድረግ ነው ። እሠራራችን ሁሉ ከቢሮክራሲ ነጻ የሆነ አብዮታዊና ወንድማዊ መሆን አለበት ። በተለይም» አሉ — «ግንኙነታችን ወደ ላይም ወደ ጎንም እንዲሆን ያስፈልጋል ። ድርጅታዊ መዋቅራችንም የተዘጋጀው በዚህ መርሆ መሠረት ነው ። ወደ ዝርዝር መግለጫ ከመሄዳችን በፊት እዚህ ላይ ጥያቄ ወይም አስተያየት ካለ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ ውይይት ማካሄድ ይቻላል ።»

ለጊዜው ዝም ፤ ዝም ሆነ ። ሁሉም ይተያይ ጀመር ። አብዛኞዎቻችን መቸም ፤ ኋላ መተቸት ነው እንጂ የሚቀናን በቦታው ላይ ፊት ለፊት የሚሰማንን ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ አሳብ ለመ

ስጡት አይሆንልንም ። እኔ እስከ ማውቀው ድረስ ለምንከተለው ዲሞክራሲያዊ ማዕከልነት ሥርህ ከዚህ ድብቅ ጠባይ የባሰ ጠን ቀኛ ነገር ያለ አይመስለኝም ። ከድክመቶችን የተነሳ ዲሞክራሲያዊነትን እየጠፋን ማዕከላዊነትን ብቻ በማጠናከር ኃላፊነትን ባንድ ሰው ወይም በጥቂት ሰዎች ላይ እንዳንጥል ሁልጊዜ ያሰጋኛል ። ኃላፊነትን የሚያክል ከባድ ነገር ተሸክሞ ወይም ረልጎ ፣ ባንጻሩ ደግሞ አድር ባይ ፈሪ ሆኖ መኖር ላገርም ሆነ ለአብዮት የሚበጅ አይመስለኝም ..... ሆዴ ጮኸ ። ራብኝ መሰለኝ ። ከነጋ እህል አልቀመስኩም ። ሰዓቱ ሄዷል ። አንዱ እጁን አወጣ ።

«እሺ ጓድ ... ግድ የለም ቀጭ ብለህ ።»

«ይህ ዘመቻ..... እ..... አብዮታዊ ዘመቻ....እ.... የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ..... ማለቴ እ..... ባሁኑ ጊዜ የተቀደው.....እ..... ወይም አሁን እንዲሆን የተመረጠበት ምክንያት ምንድን ነው? ጓድ ሊቀ መንበር»

ጥያቄውን የጠየቀው ሰው ከመመንጠሩ የተነሳ የነደደች ከብሪት ስንጥር ይመስላል ። ሰውነቱም ፣ እጁም ከንፈሩም ዩን ቀጠቀጡ ነበር ። አንገቱ ሁሉ ይንቀጠቀጥ ነበር ። ከፊት ለፊቴ ነበር የተቀመጠው ።

ሰጡዬው መቸም ጥሩ ተናጋሪ ብቻ አይደሉም ። ጥሩ አድማጮም ናቸው ። እያንዳንዱ ሰው የሚናገረውን በጥንቃቄ እና በትእግሥት የማይመጥ ልምድ አላቸው — «እሺ ጓድ ፣ ጥሩ ጥያቄ ነው» አሉ ።

እውነትም ጥሩ ጥያቄ ነበር ። የሚሰጡትን መልስ በጥንቃቄ ለማስፈር ተዘጋጀሁ ። ሠሰፋቴ መንጫጫቱን አቁሞ ነበር ። ለምን አሁን?

«እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ትግል ፣ በተለይም በአብዮታዊ ሠራዊታችን ጎላቋረጠ መስዋዕትነት በወዳጅ ሶሻሊስት አገሮች ሁለገብ ድጋፍ ፣ አብዮታችንን ከተከላካይነት ወደ ጥቃትነት አሸጋግረነዋል ።

«ከዚያም እንደ ሁኔታው አስፈላጊውን የትግል ታክቲክና ስትራቴጅ እየቀየስን በተከታታይ በሀገሪቱ መሐል ፣ ምሥራቅ ፣

ደፀቀብና ምዕራብ የተነሱብንን የአብዮቱን የውስጥ ጠላቶች ፣ የውጭ ወራሪዎችና ጣልቃገቦች ሁሉ ያምስሰናል ።

«በአሁኑ ጊዜ ለአብዮታችን እርምጃ ፣ ለሀገራችን አንድነት ፣ ለሕዝባችን ደህንነት በተለይም ለአብዮታዊ ሠራዊታችን ፋታ ማጣትና ለኢኮኖሚያችን መቆርቆዝ ብቸኛና ዓይነተኛ ጠንቅ በመሆን የሚፈታተነን ቢኖር በኤርትራ የመሸገው ተገንጣይ የአድሀሪ ድርጅት ነው ።

«ይህ ቅጥረኛ አድሀሪ ድርጅት የጥፋት ተልዕኮውን ተግ ባራዊ ለማድረግ ከተነሳሳ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለውና እንደ ሌሎች ችግሮች ሁሉ ካለፈው ሥርዓት የተረከብነው ሲሆን የጥፋት ተግባሩን እጅግ ያስፋፋውና በተቋሙም እጅግ የተጠ ናከረው አመቺ ሆኖ ባገኘው አጋጣሚ ከአብዮታችን ፍንዳታ ወዲህ ነው ።

«ይህ አድሀሪ ገንጣይ ድርጅት አብዮቱ በመጣባቸውና የመደብ ትግሉም ጣንገዋለላቸው የውስጥ ጠላቶቻችን ድጋፍና የውጭ ኃይሎች እርዳታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረና በዚያ ውም መጠን የጥፋት ተግባሩን እያስፋፋ መጥቶ ፤

«በተለይ እኛ በተለያዩ ችግሮች ተወጥረን በነበረበትና እሱ ከመላው አድሕሮት ካምፕና ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ከፍተኛ የሞራልና የማቴሪያል እርዳታ አግኝቶ ዓላማውን እስከ ማሳካት ተቃርቦ በነበረበት ወቅት ማለትም ከሦስት ዓመት በፊት ሁለተኛወ ነጻ አውጪ አብዮታዊ የጦር ሠራዊታችን አይቀጡ ቅጣት እየቀጣ ወንበዴው ተንሠራፍቶባቸው በነበሩት የክፍለ ሀገሪቱ ሰባት አውራጃዎች በማስወጣት ከሱዳን ሪፑብ ሊክ ጋር በሚያዋስነን አንድ አውራጃ ማለትም በሳሕል አው ራጃ እንዲሰባሰብ ኦስገድዶታል ።

«ሀገራችን በውስጥም በውጭም እያሉ ችግሮች ተወጥራ አንድነቷና የአብዮቱም ደህንነት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ በወደቀበት ወቅት ከዚህ አደገኛ ሁኔታ በአስቸኳይ ለመውጣት ሲባል በአስቸኳይ የተቋቋመው አብዮታዊ ሠራዊታችን ትምህ ርትነየውጊያ ልምድና በአጠቃላይ ዝግጅቱ የይድረስ ይድረስ ስለ

ነበረና የተጠቀሰውን አያሌ ድሎች የተቀዳጀነውም ከፍ ያለ መስዋዕት በመክፈል ስለነበረ ፣ ላለፉት ሁለት ዓመታት ውጊያውን በመጠኑ ጋብ አድርጎ መልሶ በመቋቋምና ጉድለቶችን በማሟላት ለመጨረሻ ወሳኝና ደምሳሽ ውጊያ እራሱን በማዘጋጀትና ነጻ በወጡ ቀበሌዎች የሚገኙትን ወገኖቹንም እንደዚሁ መልሶ በማቋቋም በማንቃትና በማደራጀት ቆይቷል ።

«የኤርትራን ችግር በሠላም መንገድ ለመፍታት ለተገንጣይ ቡድኖች የማይዋጥላቸው መሆኑ በተደጋጋሚ የተደረገላቸውን የሠላም ጥሪ አለመቀበላቸው የሚያረጋግጥ ስለሆነ ከኃይል በስተቀር የሠላም ቋንቋ ለማይገባቸው ተገንጣይ ወንበዴዎች የሚፈለገውን የኃይል ሚዛን ከማሳየት በስተቀር ሌላ ምርጫ ስለማይኖር የማያዳግም ወታደራዊ ርምጃ ለመውሰድ ተገደናል ። እኛ ጦርነትን ፈልገን አይደለም የምንዋጋው ፣ ተገደን ነው ። እኛ የምንፈልገው ሠላም ነው ፣ ብልጽግና ነው ።

«ወደ ጥያቄው ልመለስ ። ለምን ባሁኑ ጊዜ? የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ አንዱ ክፍለ ሀገሩ በወንበዴ አራዊት ተወሮ ሠላም አለኝ ፣ ወይም ደግሞ ከአካሉ ክፍሎች አንዱ ቆስሎ ጤንነት አለኝ ሊል አይችልምና በዚሁ ክፍለ ሀገር ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆየውን ችግር ማስወገድ የወቅቱ ተቀዳሚ ተግባሩ አድርጎታል ። እንደሚታወቀው በሌሎች ግንባሮች ትንሽ ፋታ አግኝተናል ። ኃይላችን ሰሜናዊው ግንባር ላይ ሊያተኩር የሚችልበት አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮአል ። ዚያድ ባሬ ዛሬ በከፍተኛ ውጥረት ላይ ይገኛል ። የዐረብ ዓለም በካምፕ ዴቪድ ስምምነት የተነሳ በከፍተኛ ፖለቲካዊ ግጭት ተወጥሮአል ። ኢራቅና ኢራን በጦርነት ላይ ይገኛሉ ። ጎረቤታችን የሆነችው ሱዳንም ባሁኑ ጊዜ ፋታ የማይሰጣት የውስጥ ችግር አላት ።

«ተገንጣይ ወንበዴዎች የሞራልና የማቴሪያል ርዳታ እንደልባቸው የማያገኙበት ጊዜ ነው ብለን እንገምታለን ። ተገንጣይ ወንበዴዎች ባካሄዱት የእርስ በእርስ ጦርነት ምስቅልቅላቸው የወጣበትና የተዳከሙበት ጊዜ ነው ። ባንጻሩ ፣ አብዮታችን በውስጥም ሆነ በውጭ ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ የተጠናከረበት ጊዜ ነው ። ዛሬ መላ የሶሻሊስት ካምፕ እና ተራማጅ ድርጅቶች ከአብዮታችን ጎን ተሰልፈው ይገኛሉ ። ተገንጣይ ወንበዴዎች

ተተፍተዋል ። እና ግብአተ መሬታቸውን የምንፈጽምበት አመች ጊዜ አሁን በመሆኑ ነው ። ግልጽ ነኝ?» የሚል ነበር የተሰጠው መልስ ።

«ሌላ ጥያቄ ወይም አስተያየት?»

«እኔ እጄን አወጣሁ። ሲከነክነኝ የቆየ ጥያቄ ነበረኝ ። ወደ አሥመራ ከመምጣቴ በፊት በቪና እና በፓሬት የተጻፈ ፣ የሚል ትንሽ መጽሐፍ አግብቤ ነበር ። ጥያቄዬ ፣ የጎሪላ ውጊያ ስልት ፣ ሲያመች ማጥቃት ፣ ሳያመች መሸሽ ፣ ከቦታ ቦታ እየ ተዘዋወሩ አደጋ በመጣል የመንግሥት ወታደሮች ማስጨነቅና ማበሳጨት ስለሆነ ፣ እንደተባለው እኛ በተደራጀ ወታደራዊ ውጊያ ስልት ስንሄድባቸው ናቅፋ ላይ ተሰባስበው ይቆዩናል ወይ? እልቂታቸውን መጋበዝ አይሆንባቸውም ይሆን?» የሚል ነበር ።

«አዎ ፣ ጓድ ። ጥሩ ጥያቄ ነው ። አንተ የጠቀስከው የጎ ሪላዎችን የመጀመሪያ እድገት ደረጃ ነው ። የጎሪላ ንቅናቄ ለረ ጅም ጊዜ በዚህ ሁናቴ ሊቀጥል አይችልም ። በግድ ወደ ኮንቬ ንሽናል አርሚ ይለወጣል ። ታክቲኩና ስትራተጂውም እንደዚሁ ወደ ኮንቬንሽናል ታክቲክና ስትራተጂ ይለወጣል ። ባጠቃላይ ሰሜናዊ ተገንጣይ ወንበዴዎች አሁን እንዲህ ያለው የዕድገት ደረጃ ላይ ነው የሚገኙት ።

«ወደ መጀመሪያ ደረጃ እንዳይመለሱ ማድረግ የኛን ያላ ሰለሰ ጥረትና ፖለቲካዊ ትግል ይጠይቃል ። ዓሣ ከባሕር ከወጣ ይሞታል ። ተመልሶ እንዳይገባ ለማድረግ ርዕዮተ ዓለማዊ ፣ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ሥራችንን ማጠናከር ያስፈልጋል ። ተሳ ስቼ እንደሆነ ልታረም እችላለሁ ። የሰጠሁት መልስ በቂ ነው ወይስ አይደለም?»

ለኔ የተሰጠው መልስ በቂ ነበር ። ግን ሌላ እጅ ሲወጣ አየሁ ። ኮ/ታሪኩ ወልዳይ ነበር ። በጸረ-ጎሪላ ወጊያ የታወቀ ኤክስፐርት ነው ። ሰውዬው ጀግና ይወዳሉ መሰለኝ ሲያዩት ፈገግ አሉ ። ጆሮዬን አቀናሁ ።

ከወታደራዊ ስላምታ በኋላ ፣ «ጓድ ሊቀመንበር ፣ የማክለው ተጨማሪ አሳብ የለኝ» አለ ። ጥልቀት ያለው ድምጹ ።

«እሺ ጓድ ።»

እንደገና ወታደራዊ ሰላምታ ። በዚያ ቁመቱ ላይ ወደላይ ተንጠራርቶ ሰላምታ ሲሰጥ ፣ የባሰውኑ ተመዘዘ — እንደ ሽምበቆ — «ጓድ ሊቀመንበር በትክክል እንዳስቀመጡት ማንኛውም የኀሪላ ንቅናቄ የራሱ ዲያሌክቲካዊ ሂደትና ዕድገት አለው ።በቡድን ፣ በቡድን ሰራ በታ ላይ የደፈጣ ውጊያ ሲያካሂድ የቆየ የኀሪላ ንቅናቄ ፣ የሠራዊቱ ቁጥር ካደገና ኃይሉ ከተጠናከረ በኋላ በግድ አንድ ላይ ተሰባስቦ ኮንቬንሽናል ጦርነት ለማካሄድ ይገደዳል ። ይህን ካላደረገ ድል ሊቀዳጅ ወይም ሕልውና ሊኖረው አይችልም ።

«በወንበዴዎች መካከል የሆነው ን የእርስ በእርስ ጦርነት ያስከተለው ፣ የሀይማኖት ፣ የጎሣ ፣ የደገኛና የቆለኛ ቅራኔ ብቻ ሳይሆን ፣ የደረሱበት የዕድገት ደረጃም ጭምር ነው ። ሻዕቢያ ጀብሐን ደምስሶ ከሜዳ ያስወጣው ራሱን ብቸኛ ተወካይ ለማድረግና ፖለቲካዊና ወታደራዊ ሞኖፖሊ ለመያዝ ነው ።

«በተገንጣይ ወንበዴዎች መካከል ያለው ቅራኔ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም ። ቅራኔው በአውራጃና በመንደርም ጭምር ነው ። ደገኛው ፣ የሐማሴን የአክለጉዛይ ፣ የሠራዬ ተወላጆች በማለት አይስማማም ። ቆለኛው ፣ የሰምሐር ፣ የማረያ ፣ የሠነሂት ፣ የባርካ ፣ የሣሕል ፣ የደንከል ልጆች በማለት አይጣጣም ። ሻዕቢያ ፣ ጀብሃ ፣ አልዋሕዳ ፣ ዓፈብ የሚባሉት ፖለቲካዊ ቅርጾች የዚሁ ፈለግ ነጸብራቆች ናቸው ። እንደ እውነቱ ከሆነ የነጠረ ወይም የጠራ ፖለቲካዊ ዓላማና ይዘት የላቸውም ። የሚያራምዱት ሕዝባዊ መስመር የላቸውም ። ጎሣዊ ድርጅቶች ናቸው ።

«ወደተነሳሁበት ነገር ልመለስና ፣ ሻዕቢያ ዛሬ ወደ ቋሚ የውጊያ ስልት ታክቲኩንና ስትራቴጂውን ለውጧል ። ሻዕቢያ ባሁኑ ጊዜ ኃይሉን አንድ ላይ አሰባስቦ መደበኛ ጦርነት ከመግጠም ሌላ ምርጫ የለውም ። ይህ ሊሆን የቻለው ባንድ ፊት ከውስጣዊ ድክመቱ የተነሳ ነው ። ጀሌዎቹን አንድ ላይ አሰባስቦ

በጠመንጃ አፈሙዝ እያስገደደ ካላዋጋ በስተቀር ሕልውናው ያከትማል ። ጀሌዎቹ በበጎ ፈቃድ የገቡ አይደሉም ። ከየማሳው በግድ ታፍነው የተወሰዱ የገበሬ ልጆች ናቸው ። ነጻነት ይዘን በድል ባጭር ጊዜ ውስጥ እንመለሳለን በማለት በ1967 የናት ትገር ጥሪ ተቀብለው በጀብደኛነት ወደ በረሀ የወጡትም አያሌ ወጣቶች ዛሬ ተስፋ ቆርጠዋል ። የበረሀ ኑሮ እንገፍግፎአቸዋል። ለመመለስ ይፈልጋሉ ። እነዚሀ ሁሉ አንድ ላይ ታፍነው ካል ተያዙ የሻዕቢያ ሕልውና ያከትማል ።

«አሁን ጥያቄው የሻዕቢያ ድክመትና ጥንካሬ ምንድን ነው? የሚለው ይሆናል ። የኀሪላ ንቅናቄ ድክመትና ጥንካሬ በአሥር ነጥቦች ሊለካ ይችላል ። እነዚህም ፣

— የውጊያ ወረዳ አመችነት (ቴሬን)
— የሠራዊቱ ሞራል
— ፖለቲካዊ ንቃት
— ሎጂስቲክ
— የሠራዊቱ ተዋጊነት ብቃት ወይም ሥልጠና
— የመሣሪያ ዓይነት
— የመሪዎቹ ብቃት
— ዲሲፕሊን
— መጠጊያ አገር ወይም ሥፍራ (ሳንክቹዋሪ)
— እና ሕዝባዊ ድጋፍ ናቸው» በማለት መለኪያ ነጥ ቦቹን ከደረደረ በኋላ ፣ «ለያንዳንዱ አርእስተ ነገር 10 ነጥብ እየሰጠን ከመቶ ብንተምን ፣ ሻዕቢያ ዛሬ ያለበትን ፖለቲካዊና ወታደራዊ ሁኔታ በተጨባጭ ለመገመት ይቻላል ።

«ባጠቃላይ ፣ የሻዕቢያ ሠራዊት ሞራል ወድቋል ። የሚሰጠ ውን ፖለቲካዊ ትምህርት በአድርባይነት ካልሆነ በቀር ከልቡ የሚቀበል ያለ አይመስለኝም ። የሚተዳደረው በጠመንጃ አፈ ሙዝ ዲሲፕሊን ነው ። ሕዝባዊ ድጋፍ የለውም ። ዛሬ የኤርትራ ሠርቶ አደር ሕዝብ ፣ ምንም እንኳን በረሀ ላሉት ልጆቹ ቢያስ ብም ሥጋ ነውና — በሙሉ ልቡ ሠላምን ይፈልጋል ።

«የሻዕቢያ ጀሌዎች ዛሬ ምንም ዓይነት ወታደራዊ ሥልጠና አያገኙም ። እርግጥ ጦር ሜዳ ሙሉ ከመዋጋት የበለጠ የጦር ትምህርት ቤት የለም ። የገበሬ ልጆች እንደ በግ እየተነዱ ነው ለጥይት የሚዳረጉት ። መሪዎቹ የለየላቸው ቅምጥሎችና አምባገነኖች ናቸው ። ጅብደኞች ናቸው ። በመጠኑም በኩል ሻዕቢያ ዛሬ በሱዳን አመች ሁኔታ የለውም ። ጆብሲ ጥቃቱን ለመወጣት ከኋላ እየተዘጋጀለት ነው ። በመግረዩና በሎጂስቲክ ሻዕቢያ ደህና ነው ። ድርጅቱ የሚያስገርም ቅልጥፍናና የፈጠራ ችሎታ አለው ።

«ዋናው ጠንካራ ጎኑ ግን ሻዕቢያ የመረጠው የውጊያ ወረዳ ነው ። ናቅፋ የተፈጥሮ ምሽግ ነው ። የናቅፋ ተራራዎች አይበገሩም ። ሻዕቢያ ደግሞ እንኳን በናረቢት ቀርቶ ባደረበትም ሥፍራ የሰው ቁመት የሚያህል ጉድጓድ ሳይቆፍር አያድርም ። ፍልፈል ነው ። የሻዕቢያ ጀሌዎች እንደ ከምሽግ ከወጡ ቁመው የመዋጋት ልምድ የላቸውም ። ፈርጣጮች ናቸው ። እና ጠያፊት የምንዋጋው ከሻዕቢያ ወኔ ጋር ሳይሆን የተፈጥሮ ምሽግ ከሆኑት ከናቅፋ ተራራዎችና ድንጋዮች ጋር ይሆናል ። እና ወሳኙ ነጥብ የውጊያ ወረዳ ሁኔታ ነው ። የሻዕቢያ ወኔና ጥንካሬ አይደለም ። አመሰግናለሁ» ብሎ ወታደራዊ ሠላምታ ከሰጠ በኋላ ቁጭ አለ ።

መጥፎ ትንተና አልነበረም ። በሙያው ምሁር ነው ። ሰባት ዓመት ሙሉ ወንበዴዎችን ሲዋጉ መቆየት ቀላል ልምድ አይደለም ። የኮ/ታሪኩ ወልዳይ ዝና በወንበዴዎችም ዘንድ የታወቀ ነው ። ሰውዬው እንደልማዳቸው በጥንቃቄ እያዳመጡ አንዳንድ ማስታወሻ ይወስዱ ነበር ። እንዳልኩት ጥሩ አድማጭ ናቸው ። ማንኛውንም ሃሳብ አይንቁም ። ንቀው የሚተውት ነገር የለም ። ሳያቸው ሁልጊዜ ተማሪ ይመስሉኛል ። አዎ ፣ አብዮት ትልቅ የተግባር ዩኒቨርሲቲ ነው ። ትጉህ ተማሪ ይጠይቃል ።

«እናመሰግናለን ጓድ ። በትግላችንና በምንከፍለው መስዋዕትነት ተፈጥሮአዊ መሰናክሎችን ከቁጥጥራችን ሥር እናውላለን ። ሌላ ጥያቄ ወይም አስተያየት...... እሺ ጓድ የሺጥላ ።»

'ሱብሎቭ'— የሺጥላ ማስረሻ ነበር ። በለጋም ፊቱ ደብልጥ ተስሎ ይታያል ። ሲናገር ቀስ ብሎ ቃላቱንና ሀረፍተ ነገሮቹን እየሳለ ነው ። አሳቡም የተሳለ ነው ። አሳቡን ሲሰለው ስለ

ታም ፊቱ ላይ ይታያል — «እኔ ላነሳው የምፈልገው ነጥብ ጸረ—ፕሮፓጋንዳን በሚመለከት ይሆናል» ብሎ ጀመረ ።

«ቅድም በትክክል እንደተገለጸው ፣ ዓሣ ከባሕር ከወጣ ተፈጥሮአዊ ሞት ይሞታል ። በሌላ አነጋገር ወንበዴዎችን ከሕዝብ ነጥሎ መምታት ይሆናል ማለት ነው ። ይህ ቀላል ሥራ አይደለም ። የምናካሂደው ፕሮፓጋንዳ ከጀብደኝነትና ከግብታዊ ነት ፍጹም የራቀ ፣ የተጠና ፣ ቁዕቅድና በፕላን የሚሠራ መሆን ይኖርበታል ።

የዚህን ክፍለ ሀገር ችግር ለመፍታት አሁን ከምናካሂደው ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ሥራ ጎን ለጎን እና ከዚያም ባሻገር ወሳኙ ሥራና ውጊያ የምንቀይሰው የፕሮፓጋንዳ ታክቲክና ስትራተጂ ይሆናል ። ዛሬ እንደ 'ማሌ' ያለ ሣይንሳዊ መሣሪያ ታጥቀናል ። ግን ይህን አሸናፊ መሣሪያ ለማን፤ ለምን፤ እንዴት ነው ልንጠቀምበት የምንችለው፤ የቆምነው ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ ልዕልና ነው — ለእኩልነት ፣ ለሠላም ፣ ለብልጽግና ፣ ለፍትሕ ፣ ለዲሞክራሲ ።

«የምናካሂደው ፕሮፓጋንዳ ይህን በጥሩ ቋንቋ እየተነተነ ማስረዳት ይኖርበታል ። በሌላ በኩል የወንበዴዎችን ፖለቲካዊ ከሥረት — አቋማቸውና ዓላማቸው ጸረ - ሕዝብ መሆኑን ማጋ ለጥ የፕሮፓጋንዳ ሥራ አንዱ ፈርጅ ነው ። የኔ ብዮታዊውን ነጻ አውጭ ሠራዊታችንን ሞራል መገንባት የፕሮፓጋንዳው ክ ፍል ሌላው ተግባር ነው ።

«በዚህ ክፍለ ሀገር ፣ በመላ ኢትዮጵያና በዓለም ዙሪያ የምናስራጨው ፕሮፓጋንዳ ምን እንደሆነ በውል ተለይቶ መታወቅ ይኖርበታል ። የዘመቻው ባሕርይ ብሔራዊና አብዮታዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊም ነው ። ዝግጅት ፣ ፕላን ፣ ዕቅድ ፣ የጊዜ ሠንጠረዥ ያስፈልጋል ። ከግለኛነት ፣ ከጀብደኛነትና ከግብታዊነት አሠራር መራቅ ግዴታ ይመስለኛል ።

«የምናካሂደው ፕሮፓጋንዳ ከብሔራዊ ጠባብነት መንፈስ የራቀ ፣ ከስሜታዊ አስተሳሰብ ይልቅ ትንታኔን ፣ ከመደብ እርቅ ይልቅ የመደብ ጦርነትን በጥራት አጉልቶ የሚያሳይና የሚያስተ

ምር መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ ። እኛ የመጣነው ችግሩን ለማድበስበስና ለመሸፋፈን ሳይሆን ፍርጥርጥ አድርገን በማቅረብ የመጨረሻ መፍትሔ ለመሻት ነው ብዬ እገምታለሁ ።

በቀደም ሲል አንዱ ተናጋሪ ሕዝቡ ሠላም ይፈልጋል ብለዋል ። እኛም የምንፈልገው ሠላም ነው ። ግን ምን ዓይነት ሠላም?

«የመደብ ሠላም ነው የምንፈልገው ። እና ሠርቶ አደሩ ሕዝብ የመደብ ጠላቶቹን አውቆና ማንነውን ለይቶ ካልቆመ በስተቀር ሠላም ሊኖረው አይችልም ። ፕሮፓጋንዳችን ፣ ትግላችን ሁሉ እዚህ ነጥብ ላይ ማተኮር አለበት ብዬ አምናለሁ ። አመሰግናለሁ ።»

እንደ ሳማ የሚለበልብ ፣ እንደ እሾህ የሚወጋ ንግግር ነበር ። ስለ ማስታወቂያ ሚኒስቴር አሠራር ይሆን የተናገረው ግን አሳቡ ትክክል ነበር ። ምናልባት ማንኛውም ነገር በቲዎሪ ቀላል ሆኖ ሊታይ ይችላል ። ተግባር ግን ሌላ ነው ። ያስቸግራል ። ሌላ ጥያቄ ወይም አስተያየት ወይም ማብራሪያ አሳብ አልቀረበም ። ወደ ድርጅታዊ መዋቅሩ ገለጣ ከመሄዳችን በፊት የሁጋአዘ ሕዝብ ደህንነት መምሪያ ኃላፊ አጭር ማስገንዘቢያ እንዲሰጥ ተጠየቀ ። ኮሎኔል በትሩ ተሰማ ነበር ። ሽክ ብሎአል ። ጉንጮቹ ያበራሉ ። ፈገግታው ይሞቃል ። እንዳልኩት የወንዝ ቱጃር ነው የሚመስለው ። ሁሉም ጆሮውን ቀና አደረገ ።

የጥበቃ ነገር ሁሉንም ያሳሰበ ያስመስላል ። አንዳንዶች ለምን አያስጠብቁንም በማለት ከሁኔታ ያኮረፉም ነበሩ ። ለሕይወታቸው ይህን ያህል ስጋት እያደረባቸው ይሆን? ማን የት በምን ምክንያት እንደሚመጣ በደምብ ጥሩ ነበር ። ወይስ መጥፎ? አላውቅም ። ስለሞት አስቤ አላውቅም ። ለምን አስባለሁ? የማይቀር ዕዳ ነው ። ሲመጣ ይመጣል ። አድፍጦ የሚመጣ ሌባ ነው ። ዛሬን ኑሩ! ሰው ስለሞት ለምን እንደሚጨነቅ አይገባኝም ። ግን አሁን የአንዳንዶቹን ጭንቀት ሞት አልመሰለኝም ። ትልቅና ተፈላጊ ሰው ሆኖ የመታየት ፍላጎት እለ አያይል! እንደ እሱ መሰለኝ ትልቅ ሆኖ የመታየት በሽታ!

«ጓዶች ፣ ግንኛውም ድርጊት ተጻራሪ ድርጊት አለው» በማለት ኮሎኔል በትሩ ተሰማ ንግግሩን ከፈተ— «የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ግቡን እንዳይመታ ለማድረግ የሚፈልጉ ኃይሎች በዚህ ከተማ ተምናልባትም በጉያችን ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ ። በጸጥታ ረገድ ያለብን ችግርና ድክመት የሚመነጨውም ከዚሁ ነው ። አንድ ሕዝብ ስለሆነ ጠላትን ከወገን ለይቶ ማየት ያስቸግራል ። አብረን እንውላለን ፣ እንጠጣለን ፣ እንበላለን ፣ አብረን እንመራለን እንማራለን ። ነገሩ ውስብስብ ነው ። ስለሆነም እያንዳንዳችሁ ለዚህ ታሪካዊ ሥራ በጥንቃቄ ተመልምላችሁ የመጣችሁ መሆናችሁን በማወቅ ንቅታችሁ አካባቢያችሁን መቃኘት አለባችሁ ። ጥርጣሬ ከሙያችን ተነጥሎ የማይታይ መሆኑን ለማመልከት ነው ። ‘ያል ጠረጠረ ተመነጠረ’ የሚለውን የቆየ ዘይቤ እንደመፈክር እን ጠቀምበታልን ።

«ለሐቅ ነው የቆምነው ። ግን ለሐቅ ቆመናል በማለት መዘናጋት የለብንም ። መጠራጠር ያስፈልጋል ። ጠላቶች አሉን ። ነቅተን ለዘመቻችን መሳካት በያለንበት ዘብ እንቁም ። ሁሉም ሰላይ መሆን ፣ ዘብ መቆም አለበት — ላብዮቱ ።

«ጠላቶቻችን ካሁኑ ውዥንብር በመፍጠር ሕዝቡን መረበሽ ጀምረዋል ። የገበያው — ኢኮኖሚ እየተናጋ ነው ። ሽብር በመፍጠር ሕዝቡ እንዲሸፍት ለማድረግ ይፈልጋሉ ። እኛ ሐማሴን የሆነ ሁሉ የሻዕቢያ አባል ነው እንልም ። ወገንን ከጠላት ለይተን እናውቃለን ። ሕዝቡን የማረጋጋቱንና የዘመቻችንን ትክክለኛ ዓላማ የማስረዳቱን ጉዳይ ለፖለቲካ መምሪያ ልተወው ። በነገራችን ላይ በሻዕቢያ ውስጥ የሐለዋ ሰውራ ኃላፊና የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረ ፣ ሥዕላይ በራኺ የሚባል ትልቅ ሰው በቅርቡ እጁን ሰጥቷል ። ብዙ የሚያውቅ ሰው ነው ። የሻዕቢያ 4ኛ ብርጌድና የደቡብ ዕዝ አዛዥም ነበር ። ፖለቲካ መምሪያው በጣም ሊጠቀምበት የሚገባ ሰው ነው ።

ጠላቶቻችን የሚመጡበት መንገድና ዘዴ ብዙ ነው ። የያንዳንዳችንን ደካማ ጎን አጥንተው በማወቅ ይጠቀማሉ ። የመሐል አገር ሰው ሴትና ሥጋ ካየ ዓይን የለውም የሚል ፈሊጥ አላቸው..... (ሳቅ) አዎ..... ጓዶች ፣ ከሴትና ከሥጋ መጠንቀቅ.... (ሌላ ሳቅ.....)

«እውነቱን ነው ። ለሰሰኛው ሰው ፣ ለሆዳሙ ሥጋና መጠጥ፣ ፍቅረንዋይ ለሚያጠቃው ገንዘብ — ችግር ላለበት አጥጋቢ ድጎማ በገንዘብ ፣ በንብረት — የያንዳንዱን ሰው ድክመት ተከታትለው በማጥናት ለዓላማቸው ያጠቀሙበታል ። በዚህና በዚያ ብለው ሰውዬውን ማሸነፍ ካልቻሉም ፣ በውንጀላ በዴ ተጠቅመው የዓላማቸው መሣሪያ ከማድረግ አይመለሱም ። የሚጠቀሙበት መንገድ ዘዴ ረቂቅ ነው ። በተለይም ዕድሜው ለጡረታ የደረሰና የገንዘብ ችግር ያለበትን ሰው አሳያው ነው የሚጠቀሙበት ። ጓዶች ፣ ይኸው ነው ። ጠንቀቅ ማለት አለብን ። ስንቃችንን ባህያ ፣ ህመላችንን በጉያ! (ሳቅ.....)»

ከሳቁ በኋላ እርስ በእርሳችን እንተያይ ጀመር ። አንዱ ሌላውን የሚጠይቅ ይመስላል — 'አንተ የትኛው ትሆን?' እያለ ። እነዚህ መሰሪዎች በየትኛው መንገድ ይመጡብኝ ይሆን? አልኩ በልቤ ። ማን ራሱን ያውቃል? አብዛኛዎቻችን በለጠንካራ ጎናችን ነው እንጂ ጉራ የምንነፋው ፣ ስለደካማ ጎናችን አበክረን አናስብም ቅሉ ፣ ስለራሳችን ሐቁን መቀበል ያቅተናል ። የማልሠራው ወይም ያልሠራሁት ኃጢአት ይኖር ይሆን? ይህች ጡብና ግን አጭር ሕይወት የምታበረክተውን ጥሩ ጥሩ ነገር ሁሉ እወዳለሁ ። ማን ነው የማይወደው? በሕይወት ካልተደሰቱ የመኖር ጥቅሙ ከምኑ ላይ ነው? እንጃ!

ሥዕላይ በራሂ ። በማስታወሻ ደብተሬ ላይ ስሙን በትልቅ ጻፍኩ ። በሻዕቢያ ውስጥ ትልቅ ስም ነበር ። በደቡብ ኤርትራ የተዋጋው አብዮታዊ ሠራዊታችን ዝናውን ያውቃል ። ጀግና ተዋጊ ተዋጊና ጥሩ ስትራቴጂስት ነው እየተባለ በሰፊው ይወራለታል ። መቸም ጠላትም ቢሆን ጀግና ይከበራል ። በእውነትም ሻዕቢያ ተፍረከርካለች ፣ አልቆላታል ፣ የእሱ ባሁኑ ጊዜ እጁን መስጠት የውስጥ ደጋፊዎቻቸውን ተስፋ ያስቆርጣል ፣ ቅስማቸውንም ይሰብራል አልኩ ። እንዴት እንደምጠቀምበት ካሁኑ ታየኝ ። ሳይደግስ አይጣላም ። ጥሩ ዕድል! የማቀርብለትን ጥያቄዎች ባሳቤ እደረድር ጀመርኩ......

የድርጅታዊ መዋቅሩ ገለጣ ቀጥሎአል ። የመዋቅር ገለጣ መቸም ያሰለቻል ። በግማሽ ልብ ነበር የማዳምጠው ። ስለሰለ

ቸሁ ብቻ አይደለም ። ደክሞኝ ነበር ። የረጂም ስብሰባ ችግር ይኸው ነው ፣ ያደክማል ። ቀስ ብሎ አእምሮ ያበልዛል ። የመጨረሻ ውጤቱ — እያነሰ የሚሄድ ገቢ ። ደግሞ ርቦኝ ነበር ። አፌ ኩበት ፣ ኩበት ማለት ጀምሮአል ። ደግነቱ ገለጣው ተገባዶአል ። የመጨረሻው ሳይሆን አልቀረም ። የኢኮኖሚ ልማት ዘመቻና ዕቅድ መምሪያ ላይ ነበርን ። በምርት አገልግሎት ሥር ፣ የግብርና ፣ የመንግሥት ርሻ ፣ የእንዱስትሪ ፣ ያገር ውስጥ ንግድ ፣ የኃይል ምንጭና የውሀ ሥራ ግብረ ኃይሎች ፣ በድጋፍ ሰጭ አገልግሎት ሥር የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ፣ የመልሶ ማቋቋም ፣ የጤና ፣ የኮንስትራክሽን ፣ የትራንስፖርትና የከተማ ልማት ግብረ ኃይሎች ። አሥራ ሁለት ግብረ - ኃይል ፣ አሥራ ሁለት ሐዋርያት! የኢኮኖሚ መምሪያውን ኃላፊ ፣ መጽሐፈ ዳንኤልን በዓይኔ ሠረቅ አድርጌ አየሁት ። ስጋት አድሮበት ሆዱን ያክ ነበር ። የሚያስበው ነገር ተሰማኝ ። ምናልባት የተወለደበትን ቀን ነበር የሚረግመው ።

# ም ሽ ት

## አብጽኣል ሰሜናዊ ኮከብ

ጨልሟል — ከስብሰባው ስንወጣ ሁሉም የተኮራረፈ ይመስላል ። እያዛጋ በየአቅጣጫው ተበተን ። ጭንቅላቴ እንዳረጀ ሞተር ሲጮህ ይሰማኛል ። ወደ ማረፊያ ቤቱ ሐጂ በቀዝቃዛ ውሀ ገላዬን ከታጠብኩ በኋላ ጉኔን አልጋ ከማስነካት ሌላ የሚታየኝ ነገር አልነበረም ። ጦረኔ ሁሉ አስጠላኝ ። ሸቷል ሰውነቱ ። ይነፍስ የነበረው ቀዝቃዛ ኡየር ትንሽ መንፈሴን አደሰው ። ጨረቃ የማትታይበት ምሽት ነው ። ሰሜናዊ ኮከብ ከጠራው ሰማይ ላይ ፈርጥ መስላ ትታያለች ። ግዙፍ ጥቁር ጥላዎች መስለው በቆሙት ዘምባባዎች ውስጥ አጮልቄ ነበር ያየኋት ። ወደ መኪናዬ ልገባ ስል ስለሞን በትረጊዮርጊስ ጠራኝ።

«ወዴት ልትሄድ ነው?» አለኝ ።

«ከዚህ ማራቶን ስብሰባ በኋላ ወዴት የምሔድ ይመስልሀል? ቀጥታ ወደ መጠለያ ጣቢያዬ ነው ። ደክሞኛል» አልኩት ።

«አይ እናንተ ጋዜጠኞች!» አለና ሳቀ ።

«ምን አጠፋን?» አልኩት ።

«መጠለያ ጣቢያ እልከው፣ ምግቡን ደግሞ ምን ልትሉት ይሆን?»

«ምግብ ለሥራ»

እንደገና ካንጀቱ ሳቀና ፣ «በል አሁን ቤቱ አብረን እንሂድ» አለኝ ።

«ሴላ ጊዜ አሁን በእውነት ደክሞኛል» አልኩት ።

«ኖ ኖ» አለ — «ይኸ አሁን የመጣውን ወዮ ጋብ እንድትገናኘው ነው ። እኔም ሳገኘው እፈልጋለሁ ። ለሥራችን በጣም ይጠቅማል ። ጥሩ ውስኪም አለኝ ። ጋዜጠኞች መቼም ይችዩቺን አትጠሉም ። ወሬና አረቂ ትወዳላችሁ»

«እዚሁ ላይ ነኑ» አልኩት ። ሳስበው እውነትም ጥሩ መጠጥ አስኝቶኝ ነበር ። ጉሮሮዬ ድርቅ እንደመታው መሬት የተሰነጣጠቀ ያህል ይሰማኛል ። ያንን ዝነኛ ወንበዴ ለማየትም ፈለግሁ ። ድካሙ ባንዴ ለቀቀኝ ።

«ሌላስ ምን ይወዳሉ ይባላል? » ብዬ ጠየኩት ።

«ሴት» ብሎ ሳቀና ቀጠለ «ምግብ ላይ ግን ሰነፎች ናችሁ ይላሉ ። ግን የዜና አቀራረባችሁ ደስ አያሰኝም» አለ ።

«ለምን?»

«ሰው ሰው አይሸትም ። ደረቅ ነው ። ሶሻሊዝም ስለስታቲስቲክ አይደለም ። መነሻውም ሆነ መድረሻው ሰው ነው ። በይህን ያህል ምርት አደገ ፣ ይህን ያህል መሬት ታረሰ ፣ ይህን ያህል ሰዎች ተደራጁ ፣ ይህን ያህል ሰዎች ከማይምነት ተላቀቁ ወዘተ..... አሃዝ ብቻ ነው ። እርግጥ ጋዜጠኞች ሪኮርድ መያዝ ይገባቸዋል ። ግን ሪኮርድ ለማሳየት ስትሉ ሰው ትረሳላችሁ ፣ ደሞ ቀዝቃዛዎች ትሆናላችሁ ። የምታቀርቡት ዜና ሁሉ ሰው ሰው መሸተት አለበት ። ደሞም የምታካሂዱት ቅስቀሳ ሁሉ የአጠቃላይነት ባሕርይ ያጠቃዋል ። አሰልቺ ነው ። ከሐቅ መነሳት አለባችሁ ። ሐቅ ማለት ደግሞ ፋክት ነው ። ግባና እንሂድ» አለኝ ።

«የምናቀርበው ዜና ሁሉ ሰው ሰው እንዲሸት ከተፈለገ በሰው ልጅ ላይ እምነት ያላቸው ፣ በሙያው የሠለጠኑ ጋዜጠኞች በብዛት ያስፈልጉናል» ብዬው ወደ መኪናው ገባሁ ።

ከዓይን የቀደሙ ሁለት ወጣት አንጋቾች ከመኪናው ኋላ ተቀምጠዋል ። ሌሎች አንጋቾች ሞልቶ የያዘ ሌላ አጃቢ መኪና አስነስቶ ከኋላ ይጠብቃል ። ገና ከመግባቱ መኪናዋ በረረች ። ፍጥነት አይጣል ነው ። ትንፋሼን ውጪ ያዝኩ ። በአረንጓዴ ፣ ብጫ ፣ ቀይ መብራቶች ፣ ቀይ ኮከቦችና ቅስቶች ያሸበረቀው «ኮምቢሽታቶ» የቻይና ከተማ መስሏል ። ቀይ መብራቶች እየ ጣስን ነበር የምንበረው ። ከመኪና አደጋ ይሰውረን እንጂ የጠ ላት ጥይትስ አያገኘንም ነበር ፣ በዚያ ፍጥነት ስንበር ። ቀጠ ልኩና «ተጨባጭ ነገር ላይ የተመሠረተ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ እንዲካሔድ ከተፈለገ ያሠራር ቅንብር ያስፈልጋል ። እኛ ጠን ቋይ አንቀልብም ። ኢንፎርሜሽን ሊኖረን ይገባል ። ኢንፎር ሜሽን ሊገኝ የሚችለው ደግሞ ከሕዝብ ደህንነት ፤ ከወታደ ራዊ ክፍሎች ፣ ከውጭ ጉዳይና ከመሳሰሉት ነው ። በቂ መረጃ ሊገኝ የሚችልበት መንገድ ሳይቀየስና የአሠራር ቅንብር ሳይ ፈጠር ፤ አጠቃላይ ቅስቀሳ ነው የምታካሒዱት ማለት ሥራ ውን አያቃናም ። ከሚሠራው ዳር ቆሞ የሚተቸው ክፍል ይበ ዛል» አልኩት ።

«ጥሩ አሳብ ነው ። አሁን እናደርገዋለን .....»

«አሁን ትልደከመሀም?» አልኩት ፤ ገርሞኝ ። አርፎ ውሎ ገና የተነሳ ይመስላል ። የኃይሉ ምንጭ ምን እንደሆነ ምስጢር ይሆንብኛል ሳየው ።

«ምን ይደረግ ብለህ ነው? የኤርትራ ችግር ሁለተኛ ተፈጥ ሮዬ ሆኗል ። ከኤርትራ ችግር ጋር ስኖር ይኸውና አሥር ዓመት አልፎኛል ። ከአብዮቱ በፊት ለሰባት ዓመት ተኩል በዚህ ክፍለ ሀገር የኦፕሬሽን አዛዥ እንደነበርኩ ታውቃለህ?.... አሁን ደግሞ በዚህ ፖለቲካ ሥራ ሦስት ዓመት ሊሆነኝ ነው» በማለት ፣ መኪ ናዋን እንደ አብድ እያበረረ በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ ፣ «አሁን ግን በእውነት ስለኤርትራ ችግርና መፍትሔ ማሰብና መጨነቅ ሰልችቶኛል ። አንገቴ ድረስ ደርሶ እያንገፈገፈኝ ነው» አለኝ ።

ብሔራዊ ጉዳናን አልፈን ፣ በአብዮት አደባባይ ወደ ላይ ከተንዝን በኋላ ፣ አዲስ ዓለም (ገዛ ባንዳ) ማይጃሕጃሕ ደርሰን ነበር ። መንገዱን ቀጠለ፤ ። በኒያላ ሆቴል አድርገን ወደ አይሮፕ

ላን ማረፊያ የሚወስደውን መንገድ ተያያዝነው ። ዛፉም ፣ ቤቱም ፣ መንገዱም እንደ ጥላ ውልብ እያለ ይጠፋል ።

«አይዞህ አሁን የችግሩ መፍትሔ እየቀረበ ነው» አልኩት ።

«ሳይገድለኝ በፊት ቢሆን ጥሩ ነው ። ችግርና መፍትሔ ከማሰላሰል ተገላግዬ እርይ ብዬ የማርፍበት ጊዜ ይናፍቀኛል ። አረ ጆሁ መሰለኝ አርባ ሁለት ዓመት ሆኖኛል ። በዚህ ፈጣን አብዮት አርባ ሁለት ዓመት የሆነው ሰው ልብ እንዲህ ዓይነቱን ሩጫ ይችላል ብለህ ነው !?» አለና ሳቀ ። የምጸት ሳቅ ነበር ።

«እኔም ቢያዚያው ገደማ ነኝ» አልኩት ።
«አግብተ ሃል?»
«እጮኛ አለኝ ።»
«ጥሩ ነዋ ሥርግ ታበላናለህ.....»
«ያለ ዘመቻ ባይመጣ ኖሮ በቅርቡ ላገባ ነበር.....»
«አትስጋ ዘመቻው ቶሎ ያልቃል ። በዘዴና በጥበብ ከያዝ ነው ። ግን ..........»
«ግን ምን?» አልኩት

«ነገሮችን በርጋታና በዘዴ መያዝ አለብን» ብሎ ፣ በመጣበት መንገድ ወደኋላ መመለስ ጀመረ ። ወደ ከሮች ሮሳ (ቀይ መስቀል) ሲኒማ ቤት የሚወስደው መንገድ ከታጠፈ በኋላ ፣ «በዚህ ክፍለ ሀገር ቋሚ ሽብር እንዲኖር የሚፈልጉ ሰዎች አሉ ። በዚህ ሰሜናዊ አካባቢ ላለፉት አራት መቶ ዘመናት ጦርነት ያልተካሔደበት ጊዜ የለም ። እና ይህ ሁኔታ ብዙ ሰዎችን አድርባዮችና ተጠራጣሪዎች አድርጓቸዋል ። አሁንም በዘመቻው ለመጠቀም አሰፍስፈው የሚጠብቁ አይጠፉም ። ለዚህ ነው ረጋ ማለት አለብን የምለው ። የዚህ አገር ችግር ውስብስብ ነው ።

«እና ደግሞ ከመሐል አገር የመጡ አንዳንድ ሰዎች ስልቻ ሙሉ መፍትሔ ይዘው የመጡ ስለሚመስላቸው ፣ የባሰ ችግር በመፍጠር ነገሩን ይበልጥ ውስብስብ ያደርጉታል ። ሌላ ችግር እንዳንፈጥር ነው የምሰጋው ። የታሪክ ሽሚያ ደግ አይደለም ። ቤት ደርሰናል» አለኝ ።

የውጭው በር ክፍት ሆኖ ነበር የሚጠብቀው ። ወታደሮች በሩ ላይ ቆመዋል ። በመጣበት ፍጥነት ሽው ብሎ ገባ ። ትልቅ ግቢ ነው ። በመብራት ነዶ ጸሐይ መስሏል ።

«ዙሪያ ጥምጥም ነው ያመጣሁህ» አለኝ ።

«ረዥም መንገድ ነው»

«ንፋስ እንድንቀበል ብዬ ነው» አለኝ ።

ቀዝቃዛውን አየር ተነፈስኩ ። ግቢው በአበባዎች ተክል ተሞልቶ ይታያል ። በጥሩ እንክብካቤ የተያዘ አትክልት ነው ።

«አበባዎች ትወዳለህ መሰለኝ?»

«አበባ መትከልና መኮትኮት ሆቢዬ ነው ። አንዳንዴ ትንሽ ፋታ አግኝቼ መካከላቸው ቁጭ ስል ደስ ይለኛል» አለኝ ፣ አበባዎቹን እየተመለከተ ።

«ሌላስ?»

«ሌላው ሆቢዬ ይግረምህና ወጥ መሥራት ነው ። አምሽቼ ከሥራ ስመለስ የለሊት ልብሴን ለብሼ ወጥ መሥራት ፣ ለምን እንደሆነ እንጃ ፣ ያዝናናኛል ። ቆይ አንድ ቀን ሠርቼ አበላሃለሁ» አለኝ ።

«ተስፋ አደርጋለሁ ። የዚህ አገር ምግብ ያለ ፓስታ የለም አውን» አልኩት ።

«አዎ ፣ በፓስታ ማን ብሎአቸው! ጉበዝ ናቸው ። ሽሮአቸውም በጣም ጥሩ ነው ። ቀይ ወጥና ዶሮ ወጥ ላይ ግን አይረቡም። ቲማቲም ባናቱ ላይ ይጨምራሉ ። ደግሞ ከቅቤ ዘይት ነው የሚመርጡት ። ዶሮ በዘይት ይታይሃል? በውጥስ እኔ እበልጣቸዋለሁ ። ታያለህ» አለኝ ።

ተያይዘን ወደ ቤት ገባን።ወደ መታጠቢያ ቤት መሄድ ፈልጌ ነበር ። መታጠቢያ ቤቱን አሳየኝ ። ፊቴን ተታጥቤና አፌን ተጉመጥምጬ ስመለስ መጽሐፈ ዳንኤል ፣ ኮሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ፣ ኮሎኔል በትሩ ተሰማና ሌሎች የማላውቃቸው ሦስት ሰዎች እንግዳ ማረፊያ ክፍሉ ውስጥ ተደርድረው ጠበቁኝ ። መጽሐፈ ያስቃቸው ነበር ። ምናልባት ሲለተባበሩት መንግሥታት ስብሰባዎች የሚፈጥረውን ቀልድ እየነገራቸው ይሆናል የሚያስቃቸው ። ሁልጊዜ ስለተባበሩት መንግሥታት ይቀልዳል ።

እንደ በእንደ ሰላም አልኳቸው ፡፡ ሁሉም «ሲኮ» ውስኪ በበረዶ ይዘዋል ፡፡ ጥም አቃጠለኝ እንግዳ ቤቱ መቸም መለስተኛ ቤተ መንግሥት ይመስላል ፡፡ ለመርገጥ የሚያሳዝን ቀይ የፋርስ ምንጣፍ ፣ ትላልቅ ፣ ሰማያዊ 'ክሪስታል' ሻዞች ፣ ከክሪስታል የተሠራ ሻንዲሌር መብራት ፡፡ ግማሽ ብርጭቆ 'ሴኮ' ውስኪ በበረዶ ይዤ ወደ ሰለሞን በትረጊዮርጊስ ጠጋ አልኩና ፣ «እንግዳው የቱ ነው?» አልኩት ፡፡ ካስ ኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ሌላ ወንበዴ የሚመስል ሰው የለም ፡፡

«ይመጣል ፡፡ ወዳጅን ይገፍ ካልመጣሁ ብሎኝ ነው የዘገየው......»

«ወንድ ወይስ ሴት?»

«ሴት ፡፡»

«ካሁኑ ሰላማዊ ኑሮ ጀምሮአል?»

«ሥዕላይ፣ እንደ ሠይጣን ፈጣን ነው ፡፡ ይገርምሀል ፡፡ ደግሞም ደፋር ነው ፡፡ ከድሮ ጀምሮ ነው የማውቀው ፡፡ ከፊሉ የተጣላ ሠይጣን ቢኖር እሱ ነው ፡፡ ቶሎ ይቆጣል» አለኝ ፡፡

«ደህና ሐማሴን ነው በለኛ!»

«አይምሰልህ ሐማሴን የሚባለው ሁሉ ቶሎ የሚቆጣና የሚበርድ ፣ የሚሰማውን ፊት ለፊት የሚናገር ይመስለናል ፡፡ እንደ እሱ አይደለም ፡፡ የብዙዎቹን ልብ ማወቅ ያስቸግራል ፣ በተለይ አሁን ፡፡ ቅድም እንዳልኩህ አብዛኛው ተጠራጣሪ ሆኗል» እንዳለኝ ሦስት ወጣቶች ከውጭ ተከታትለው ገቡ ፡፡

አውቃቸዋለሁ ፤ በቴሌቪዥን 'ኢንተርቪው' አድርጌያቸዋለሁ ፡፡ ቀደም ሲል ከበረሀ የተመለሱ የሻዕቢያና የጀብሐ አባሎች ናቸው ፡፡ መቸ ይሆን 'ኢንተርቪው' ያደረግኋቸው? ከአንድ ዓመት በፊት? አንድ ዓመት ተኩል?...... ቀኑን ረሳሁት ፡፡ ነገር መርሳት ጀምሬአለሁ ፡፡ ነገር መርሳት ለጋዜጠኛ መጥፎ ምልክት ነው ፡፡ ዕድሜ እየጨመረ ሲሄድ ዝርዝር ነገር እየተረሳ አጠቃላዩ ነገር ብቻ እየታወሰ ይሄዳል ልበል! ግን ፣ ደግነቱ ፣ የበረሸኞቹን ስምና ሥራ አልረሳሁም ፡፡ ፍትዊ በርሄ (ወዲ በርሄ) የጀብሐ ሐለዋ ሳውራ ዋና ጸሐፊና የዚሁ ድርጅት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል

ነበር ። ቁመቱ ዘለግ ያለ መልከ መልካም ወጣት ነው ። ዘርዓይ ወዲ ሐለቃም እንደዚሁ የጀብሐ ፖለቲካ ትምህርት ቤት ዲሬክተር ነበር ። መካከለኛ ቁመት ያለው ፣ ጠይም ፣ ቀጭን ወጣት ነው ። ዓይነ አፋር ይመስላል ። ሰው ቀና ብሎ አያይም ። መስፍን ጽሩዕ የተባለው ቀጭን ብልጣ ብልጥ ነው ። ጨዋታና ሳቅ ያበዛል። መስፍን ጽሩዕ የሻዕቢያ ሐለዋ ሳውራ ቀንደኛ አባል ነበር ። ሦስቱም ሙሉ አራዳዎች ነው የሚመስሉት ሲያዩዋቸው ። በረኸኞች የነበሩ አይመስሉም ። ለመሆኑ በረኸኛ ምን ይመስላል? በረኸኞች ከሰዎች የተለዩ ልዩ ፍጡር መስለው በዓይነ ሕሊናዬ ለምን እንደሚታዩኝ አይገባኝም ። እነርሱም አልዘነጉኝም ። ሦስቱንም የእጅ ሠላምታ ሰጠኋቸው ። ተነፋፍቀው እንደ ቆዩ ሰዎች ተቃቀፍን ።

«ትተዋወቃላችሁ ለካ?» አለ ሰለሞን ።

«በጣም እንጂ ፣ በቲቪ ኢንተርቪው አድርጌአቸዋለሁ» አልኩትና ወደ ሦስቱ መለስ ብዬ ፣ «እንዳስቸገርኳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ!» አልኩ ።

«ጥሩ ነበር» አለ ፍትዊ ፣ ፈገግታው ደስ ይላል ።

«ብዙውን የተናገራችሁት እናንተ ነበራችሁ ግን ጥሩ ፕሮግራም ነበር» አልኩ ።

«ዝነኞች አድርገኸናል» አለ ዘርዓይ ወዲ ሐለቃ ።

«አገሩን ነቅንቃችሁት ነበር» አልኳቸው ።

«አሁን ግን የሥዕሳይ ባራኺ ዝና ያጠላብናል ። እኛ ያለፈ ፣ ያረጀ ታሪክ ሆነናል» አለ መስፍን ጽሩዕ ። ሞቅ ብሎታል ። ፍትዊ በርሄም ሞቅ ያለው ይመስላል ። ከመምጣታቸው በፊት ሲቀመቅሙ የነበሩ ይመስላሉ ። ኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይ መጥቶ ተቀላቀላቸው ።

«እህሳ ሚስተር ቲቪ?!» አለኝ መጽሐፈ ዳንኤል ። ከበረኸኞቹና ከኰሎኔል ታሪኩ ጋር መሆን ፈልጌ ነበር ፣ ሲዋጉ የነበሩ ሰዎች ምን እንደሚባባሉ ለመስማት ። ጦርነት መቸም አስቂኝ ነው!» ።

«ታዲያስ ሚስተር ኢኮኖሚ!» አልኩት ።

«ምን ወሬ አለ?» አለኝ ።

የኤሌክትሪክ ብርሀን ያረፈበት መላባው ያብለጨልጫል ። መነጽሩም ብርሀን መልሶ ይፈነጥቃል ። ትናንሽ ዓይኖቹ ይቁለጨለጫሉ ። ተንኮል የሚሠሩና የሚያዩ ይመስላሉ ።

«አብረን ነው የዋልነው ። የኔኑ ያህል ታውቃለህ» አልኩት።

«ከናንተ ጋዜጠኞች እኮ ተራው ሕዝብ ይበልጥ ያውቃል» አለና ምጸታዊ ሳቁን ለቀቀው ። በግድ የሚስቅ ነው የሚመስለው ሲስቅ ። ሲስቅ ሰውነቱ ሁሉ አብሮ ይርገፈገፋል ።

«እንዴት!» አልኩት ።

«ሰው አፍ ላይ ማይክሮፎን ደቅናችሁ ፣ ምን ያስባሉ? የሚያክሉት ተጨማሪ አሳብ አለዎት? ከማለት ሌላ ምን ታውቃላችሁ? እና ደግሞ የሰው አሳብ ቀምታችሁ የራሳችሁ አሳብ አስመስላችሁ ማቅረብ ። የሚሰጧችሁን አሳብ እንኳን በትክክል ብታቀርቡ ጥሩ ነበር ። የነካችሁትን አሳብ ሁሉ ታበላሻላችሁ ። ጀርናሊዝም እንዲህ ከሆነ በሩቅ!» አለ ።

ያው የተለመደ ፣ ብዙ ሰዎች በጋዜጠኞች ላይ የሚሠነዝሩት ሂስ ነበር ። ግምት አልሰጠሁትም ። አንድ ቃል ለምን ተለወጠብኝ በማለት የሚያኮርፉና የሚናደዱ ሰዎች ሞልተዋል ። ግጥም ፣ ስድብም ሆነ ሙገሳ ፣ ተቀብሎ እንደሚያስተጋባ የጠጅ ቤት አዝማሪ ጋዜጠኞችን መመልከት መቸ ይቀር ይሆን! አባቴ ይሙት! አንዳንዴ ሳስበው ጋዜጠኛ መሆኔ ወይም መባሌ ያናድደኛል ። የነገሩትን መልሶ የሚያስተጋባ የገደል ማሚቶ!...... ዋሽ! አድር ባይ! ጠጭ! የማንባለው ነገር የለም።አገልግሎታችን እንደጨው ተፈልጎ ፣ በዚያው ልክ ደግሞ ተጠልቶና ተረግጦ እንዴት ይሆናል! ምን ዓይነት ሕይወት! ምነው አያስጠጣ ፣ ሳይወዱ ያስጉነጫል እንጂ! ከውስኪዬ ተጐነጨሁና ፣

Journalism isn't a desimal
Science like Economics ሚሽን» አልኩት ።

«ተቆጣህ እንዴ!»

«እንዲያውም ።»

«ከናንተ ጋር ተጣልቶ የት ሊደረስ? የጠላችሁትን ሰው አፈር ድቤ ታስግጣላችሁ አሉ......»

«በሆነልን» አልኩት ።

«ኃይለኛ መሣሪያ ይዛችሁ እንዴት አይሆንላችሁም፣ ባታውቁት ነው እንጂኮ ሥልጣን በናንተ እጅ ነው» አለኝ ። መቸም በነገር አገም ጠቀም ማድረግ የተለመደ ጠባዩ ነው ። ቀጠለና ፣ «ስለዛሬው ስብሰባ ምን ታስባለህ?» ብሎ ጠየቀኝ ።

አላመንታሁም «ትምህርታዊ ነበር ። ከፊታችን ላይ የቆደቀነው ችግር አሁን በግልጽ ይታየኛል» አልኩት ።

«እውነት፣ ምነው እንዳንተ ግልጽ ሆኖ በታየኝ፣ ደደብ ነኝ መሰለኝ» አለ ። በዲፕሎማቲኮች ቋንቋ ደደብ ነህ ማለቱ ነው ። በኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለብዙ ጊዜ ሠርቷል ። አይብርጭቆ አያያዝ ያሳምረዋል ። እጅ አነሳሱና አቋቋሙ ሆን ተብሎ የተጠና ነው ። አለባበሱም እንደ አየሩና እንደሁኔታው ይለዋወጣል ። ደመና የታየ እንደሆነ ፣ ካቦርታ ፣ የዝናብ ጫማ ፣ ያንገት ልብስ ፣ ጃንጥላ የማይዘው ነገር የለም ። ቤቱ ደርሼ አላውቅም ። ግን ሰው ቤቱ ሲሔድ በር ላይ ጫማውን ሳያወልቅ ቢሞት አያስገባም ይባላል ። ከአንድ ሁለት ጊዜ ቢሮው እንዳጋጣሚ ሔጃለሁ ። የሆስፒታል ቀዶ ጥገና ክፍል ምስጋና ይግባ! የሲጃራ ዓመድ ወይ ቡና ቢሮው ውስጥ ጠብ ካለ ከጐንና ጐን የቀረችው ጠጉሩ ተነስታ ትቆማለች ። የሥራ ጓደኞቹ ሊያናድዱት ሲፈልጉ ቢሮው ሆን ብለው ሔደው ጠረጴዛው ወይም ምንጣፉ ላይ ሲጃራ ይኮስትራሉ ። ያኔ ጣራ ይመታል ። ሲጮህ ይውላል ። መቸም የሰው ሥራ ሲያብጠለጥል ሳሣር ነው ። አንድ ሥራ እንዲያርም ወይም እንዲያቃና የተሰጠው እንደሆነ ለመጣው ሁሉ ፣ «ይኸውልህ የእገሌን ሥራ ተመልከተው ። እድሌ ሆኖ ሽንፍላ ሳጥብ እኖራለሁ» እያለ ያሳጣል ። ግን ባለሙያ ነው ።

«ላቀረብክልኝ ምስጋና ምስጋናዬ አጥፍ ድርብ ነው ። አንተስ ስለስብሰባው ምን ተሰማህ?» ብዬ ጠየኩት ።

«አየህ ጓድ» አለ ፣ «እኔ መጽሐፌን አድህሪ ነው እንጂ አገር ይሸጣል የሚለኝ የለም ። አድሃሪ ቢሉኝ ደግሞ ግድ የለኝም ።»

«ይህን ምን አመጣው?» አልኩት ።

«ቆይ እንጂ ጓድ ፣ ምነው ጓድ አያልኩህ!» በማለት ምጸታዊ ቀልዱን ጣል አደረገብኝና ፣ ሐያ ዓመት ሥር ሰዶ የኖረ ችግር በዘመቻ አይፈታም ። የኤርትራ ችግር የውስጥ ችግር ብቻ አይደለም ። በውጭ በኩል ያሳሰለሰ ዲፕሎማቲካዊ ጥረት ፣ በውስጥ ደግሞ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ግንባታ ፣ ፖለቲካዊ ሥራና መግባባትን የሚጠይቅ በዘዴና በጥበብ የሚያዝ ሥራ ነው ። ቀልድ አይደለም ። ባንድ ወቅት ፣ ላንድ ሥራ ዘመቻና ርብርብሽ ጥሩ ነው ። ግን ልማድ ሆኖ እንዳይቀር ያሰጋል ። የኤርትራ ችግር ቀላል አይደለም ፣ ውስብስብ ነው ።

«ይህን የቆየ ችግር በዘመቻ እንፈታለን ብለን ስንረባረብ ካሁኑ ሌሎች ችግሮችን እየፈጠርን ነው ። 450 ከባድ የጭነት መኪናዎች ፣ 250 ሼልቶ ፣ 200 ከነተሳቢያቸው ወደ ሰሜን ማዞር ከኤኮኖሚ አንጻር ምን ማለት ነው? ባጭሩ ኢኮኖሚው ተናግቷል ማለት ነው ። ደግሞ አሁን የመኸር ጊዜ መሆኑን አትርሳ ዳቦ ከሰቅ ፣ እህል ከዘበያ ቢጠፋ አይገርመኝም ።

«ያለንን መዋዕለ ንዋይ እዚህ እምጥተን ስናፈስ ምን የሚሆን ይመስልሀል? ባጭሩ የልማት ሥራ ይገታል ። ልማት ቢገታ አሁን ያለው ሥራ አጥ ሠራዊት ቁጥር ይጨምራል ። እና ምን ይሆናል? ሥራ አጥ ሠራዊት ይዞ ሶሻሊዝምን መገንባት እንዴት እንደሚቻል ለኔ ግልጽ አይደለም ። ይህ ዘመቻ የሚነካካው ብዙ ነገር ነው» በማለት ንግግር ብጤ አደረገልኝ ።

ይልቅ አሁን አናደደኝ ፣ «ስብሰባው ላይ ምን ዘጋህ! ቅድም እንዲህ ብለህ አትናገርም ነበር? ማን ከለከለህ? መድረኩ ለማንም ክፍት ነበር ። ለምን ሐቀኛ አንሆንም!» አልኩት ።

«ትቀልዳለህ ልበል!» አለኝ ።

«ኖ! ቀልዴን አይደለም ። የምሬን ነው ። ልክ ነው! ከእንዳንተ ያሉ ምሁራን የሚጠበቅና የሚፈለግ ነገር ቢኖር ግልጽነትና ሐቀኛነት ነው ። ሰውየውም ቢሆኑ አብረዋቸው ከሚሠሯቸው ሰዎች የሚጠብቁት ይኸንኑ ነው ። ግልጽነት ፣ ሐቀኛነት ።

«አብዮትም ይሁን ማንኛውም ሥራ የጥቂት ሰዎች ንቅናቄ ወይም ኃላፊነት አይደለም ። አብዮቱ ወይም አገሬ የሚለው ሁሉ

እኩል ኃላፊነትና ግዴታ አለበት ። ማንም ከሌላው ያነሰ ኢትዮጵያዊ አይደለም እገሬ ፣ አብዮቴ እስካለ ድረስ ። ኖ ኖ...... ስማኝ እንጂ!...... አቀጣጥሎ ወዴት? ይህ የተባበሩት መንግሥታት ሸንጎ አይደለም...... ምሁራን ቀና ብለው ካልተሳተፉ...... እ...... አስተዋጽኦ ካላደረጉ እንዴት ይሆናል! እነማን ናቸው በኃላፊነት ሥራ ላይ ያሉት? ማለት ብቻ አይበቃም ። መሳተፍ ያስፈልጋል ። ባገር ጉዳይ ከዳር ቁጭ ብሎ አያገባኝም በማለት እንደጲላጦስ እጅ መታጠብ አይቻልም...... እና ጓደኛ የኤርትራ ችግር አንተ እንደምታየው አይደለም ። በነገሩ አልተቸኮለበትም ። ስምንት ዓመት ችግሩን ለማስታመም ተሞክሯል ። ያገራችን ኢኮኖሚ በችግሩ ምክንያት እየደማ ነው ። ያገሪቱ ጉሮሮ እየታነቀ ነው ። እስከንሞት አንጠብቅም ። የተከፈለው መስዋእትነት ተከፍሎ መፍትሔው መገኘት አለበት ። ከጦርነት ሌላ ቋንቋ ከማይናገሩ ወንበዴዎች ጋር ከጦርነት ቋንቋ ሌላ መናገር አያስፈልግም...... የሠላም ዋጋ ደም ነው ። ያንን የደም ዋጋ የሚከፍለው ሕዝብ ነው ። የደም ዋጋ ሊከፍሉ የሚችሉ ልጆች ያሉት ብሔር በእውነት እድለኛ ነው ......» እያልኩ ስንጣጣበት ፣ ሰለሞን በትረጊዮርጊስ መጥቶ ፣

«ምንድን ነው የምትጨቃጨቁት ?» ብሎ ጠየቀን ።

የተመካከርን ይመስል ሁለታችንም በአንድነት ፣ «ምንም» አልነው ።

«አይገርማችሁም?» አለ በእጁ ወደ ኰሎኔል ታሪኩና ሦስቱ በረኸኞች እየጠቆመን ። ሞቅ ያለ ጭውውት ይዘዋል ። ሦስቱም ወደ ላይ አንጋጠው ኰሎኔል ታሪኩን ይመለከቱ ነበር ። ለደመራ የቆመ ረጅም አጣና መስሎ ይታያል ። ያስገረመው ነገር ምን እንደሆነ ሁለታችንም አልገባንም ።

«አይገርማችሁም?» አለ እንደገና «ትናንት በጥይት ሲደባደቡ የነበሩ ሰዎች ዛሬ አብረው እየጠጡ ሲጫወቱ ማየት በእውነት ያስገርማል ። ፍትዊ ወዲ በርሄ ከመንደፈራ አሥመራ ድረስ ያለውን አገር ሲያንቀጠቅጥ የነበረ ነው ። በጊዜው ብዙ ሰዎች አስሯል ። ገርፏል ፣ ገድሎአል ። ብዙ አድምቶናል ። ዘርዓይ ወዲ ሐለቃ የጀብሐ ፖለቲካ ትምህርት ቤት ዲሬክተር ሆኖ በሚሰጠው ትንታኔ ብዙ ወጣቶችን ወደ በረሀ ያሸፈተ ሰው ነው ። የጀብሐ ደቡብ አዝ ኮሚሳርም ነበር ፣ መስፍን ጽሩፅ

በኤርባን ጉሪላ ታክቲክ የሠለጠነ የሻዕቢያ ቀንደኛ ፈዳይን ነበር ። ኩሉኔል ታሪኩ ከእነሱ ጋር ያልተዋጋበት ቦታ የለም ።

«እዚህ ከተማ ውስጥ የብርጭቆአችን አባት ታሪኩ ባይኖር ኖሮ ይኸኔ አረቄ በጣሳ እንጠጣ ነበር ነው የሚሉት ። ወንበዴዎች ደቀመሐሪን በያዙበት ጊዜ አሸዋ ጠፍቶ የጠርሙስና የብርጭቆ ፋብሪካ ሥራ ቀጥ ብሎ ነበር ። እሱ ነበር ሁለት መትረየስ ይዞ ግራና ቀኝ እየተታኮሰ አሸዋ የሚያስጭነው ። እሱን ለመግደል ያላደረጉት ሙከራ የለም ። በእውነት ርግጥ አንዳንድ ጥፋት ደርሶአል ቢሆንም ግን እንደኢትዮጵያ አብዮት ሆደ ሰፊ አብዮት ያለ አይመስለኝም ። አንዳንዱ ሳስበው የዋሆች ነን ወይ? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ» ካለ በኋላ ፣ ወደኔ ዞር ብሎ ፣ «ጸጋዬ ፣ በዚህ ላይ ለምን አንድ ጥሩ ፕሮግራም አትሠራም?» አለኝ ።

«ጥሩ አሳብ ነው ። እያችሁን ከሰጣችሁ ፣ ይገርፉዋችኋል ፣ ያሰቃይዋችኋል ፣ ይገድሉዋችኋል እያለች ሻዕቢያ የምትነዛውን ፕሮፓጋንዳ ለመስበር ይረዳል» አልኩት ። አብዮትና ሰፊው ሕዝብ መሐሪ ናቸው የሚል አርእስት ታየኝ ።

«ግን ባይመቻቸው ነው እንጂ እነዚህ ሰዎች የሚተኙልን ይመስልሀል? እኔ አላምናቸውም ። ትናንት ሲወጉንና ሲያደሙን የቆዩ ሰዎች ዛሬ ተመልሰው ላንድነት ቆመናል ፣ ካብዮቱ ጉን ተሰልፈናል ሲሉ አይገባኝም» አለ መጽሐፈ ዳንኤል መላጣውን በመሀረብ እየጠረገ ።

ሰለሞን በሀሣብ ተመስጦ «ከማመን በቀር ሌላ ምን ምርጫ አለ? አናምናቸውም ከሚል አስተሳሰብ ተነስተን መጥፎ ውሳኔ ላይ መድረስ አንችልም ። በግድ ሆደ ሰፊ መሆን ያስፈልጋል ። እርስ በእርሳችን የመተማመን ነገር ጊዜ ይወስዳል ። ግን መሞከር አለብን ። አንድ ቀን ልጆቻችን ተማምነው ለመኖር ይችሉ ይሆናል ። ወደዚያ የሚወስደውን ጥርጊያ መንገድ መክፈት የኛ ፈንታ ነው ። ግን እንዳንተማመን የሚያደርጉን የውጪ ኃይላት ናቸው» ካለ በኋላ ሲያስብ ቆየና «የኤርትራ ችግር እግሩ እዚህ ይሁን እንጂ ጭንቅላቱ ውጭ ነው ። ታሪካዊ አጀማመር ታሪካዊ ፍጻሜ ይኖረዋል» አለ ።

ነገሩ ስላልገባኝ «ምን ማለትህ ነው?» ብዬ ጠየኩት ።

ሰለሞን በትረ ስለ ኤርትራ መናገር አይሰለቸውም ። ጊዜ ካገኘ ስለኤርትራ ሲያወራ ውሎ ያድራል ። «እየህ» ብሎ ጀመረ ፣ «ኤርትራ ለ60 ዓመት በኢጣልያን ቅኝ ግዛት ሥር ቆይ ታለች ። ከዚያ በፊት ባለፉት 400 ዘመናት የጦርነት ዐውድማ ሳትሆን የኖረችበት ዘመን የለም ። ኢጣልያ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ስትሸነፍ ኤርትራ በእንግሊዝ አስተዳደር ሥር ወደቀች ። እና አዲሱ ፖለቲካዊ ድራማ ተጀመረ ። እንግሊዝ እየቆየ የሚ ፈነዳ ቦንብ በኤርትራ ምድር እያተከለ ነው የወጣችው.....» አለ ።

ሁላችንም ጠጋ ፣ ጠጋ አልነው ። ሰለሞን ለመናገር ብሎ የሚናገር ሰው አይደለም ። ከተናገረ ስለሚናገረው ነገር ካንጀቱ ስለሚናገር አድማጭ ይስባል ።

እና ቀጠለ — «ኤርትራን በሚመለከት እንግሊዝ ሁለት ዓላማዎች ነበሯት ። አንደኛው ዓላማዋ ኤርትራን በተቻለ መጠን ከአስተዳደሯ ሥር ማቆየት ሲሆን ፣ ይህ ካልተቻለ ፣ ሁለተኛው ዓላማዋ ሰሜኑንና ምዕራቡን ቆላማ አገር ፣ ምጽዋን ጭምር ፣ ቅኝ ግዛቷ ከሆነችው ከሱዳን ጋር ቀላቅላ መግዛት ነበር ። እነ ዚህን ዓላማዎች መሠረት በማድረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ጀ መረች ። ፖለቲካዊ ስልቶችም ቀየሰች ።

«የመጀመሪያው ፖለቲካዊ ስልት ፣ ኢትዮጵያ ለጊዜው ኤርትራን ፈጽሞ ለማስተዳደር እንደማትችል አድርጋ ለዓለም ማሳየት ነበር ። ይህን ለማድረግ «ታላቋ ኤርትራ» የሚል ፖለቲካዊ ንድፍ አወጣች ። ንድፉ ፣ ትግራይን ከአልውሀ ምላሽ ከኢትዮጵያ በመገንጠል ከኤርትራ ጋር ቀላቅሎ የሚይዝ ነበር ። ይህ ነበር «የታላቋ ኤርትራ» ግንዛቤ ። እንግሊዝ ይህን ዓላማዋን የሚያስፈጽምላት መሣሪያ አላጣችም ። «በሣህለ ሥላሴ ስርወ መንግሥት የተወሰደብኝን ዙፋን ወደ ሳባጋዲስ ስርወ መንግ ሥት» እመልሳለሁ የሚል ምኞት የነበረው ደጃዝማች ተሰማ አስምሮም የተባለ ሰው ነበርና ፣ «ታላቋ ኤርትራ» የተባለውን መፈክር አስነግባ አነሳሳችው ። የወያኔ ጦርነት ተከፈተ ። ዛ ሬም ኢሳይያስ አፈወርቂና ወያኔዎች የማያራምዱት ይህንኑ ዓ ላማ ነው ። ኢትዮጵያ ኤርትራን ለማስተዳደር አትችልም የሚል ጥርጣሬ እየተፈጠረ ስለሔደ እንግሊዝ ያሰበችው ለጊዜው የተሳ ካላት መስሎ ታየ ።

«ይሁን እንጂ ፣ በዚሁ ወቅት ፣ «ኢትዮጵያ ወይም ሞት» የሚል መፈክር ያነሳ ፣ የማኅበር አንድነት ኃይል እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ነበር ። አብዛኛዎቹ የአንድነት ማኅበር መስራቾችና አባሎች ከኤርትራ ደጋማው ክፍል ከመሆናቸውም ሌላ በአብዛኛው ክርስቲያኖች ነበሩ ። እንግሊዝ ግልጹን ነገር አደረገች ። የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች የሆኑትን የቆላማውን አገር ተወላጆች በማሰባሰብ ራቢጣ አል እስላሚያ የተባለ የፖለቲካ ቡድን እንዲመሠረት ከማድረጓም በላይ ፣ በኤርትራ ጣልያንኛ ኦፊሴላዊ ቋንቋ መሆኑ ቀርቶ ከእንግዲህ ትግርኛና ዐረብኛ ብቻ ኦፊሴላዊ ቋንቋ ሆነው እንዲሠራባቸው አደረገች ። የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ መሠረት ያዘ ። ለመጀመሪያ ጊዜ በኤርትራ የፖለቲካ መድረክ ላይ ሦስት የተለያዩ አቋሞች ተከሰቱ ። እነሱም አንደኛ ፣ ታላቋ ኤርትራ የሚለው ወገን ኤርትራ ለኤርትራውያን የሚል አቋም ያዘ ፣ ሁለተኛ ፣ ራቢጣ አል እስላሚያ ኤርትራ በእንግሊዝ አስተዳደር ሥር መቆየት አለባት የሚል አቋም ሲወስድ ፣ ሦስተኛ ማኅበር አንድነት ደግሞ «ኢትዮጵያ ወይም ሞት» በሚለው ዓላማው ጸና ።

«በማይታረቁ የፖለቲካ ፣ የጎሳ ፣ የቋንቋና የሀይማኖት መስመሮች የኤርትራ መገነጣጠል ሁኔታ ተሟላ ። የእንግሊዝ የበኩር ልጅ ተወለደ ። ሁኔታው በኤርትራ ምድር ተወስኖ አልቀረም ። ቀይ ባሕርን «የአረብ ሐይቅ» ለማድረግ የቆየ ዓላማ ያላቸው የአረብ መንግሥታትና ፣ ይህንኑ የዘይትና የሸቀጣ ሸቀጥ መተላለፊያ ስትራተጂካዊ ኬላ የሆነውን ባሕር ለጥቅማቸው ሲሉ ፣ አሁንም ሆነ ወደፊት በቁጥጥራቸው ሥር ለማቆየት የሚፈልጉት ኃያላን መንግሥታት በጉዳዩ ፣ በፀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እጃቸውን ማስገባት ስለጀመሩ ፣ ችግሩ እየሰፋ ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ እየያዘ ሄደ ። የነገሩ ጭራ እዚህ ቀርቶ ጭንቅላቱ ውጭ ወጣ ። የኤርትራ ታሪክ ፣ በተለይም በዐረብ አገሮች ፣ ያልነበረ ቅርጽ ፣ ይዘትና ትርጉም እየሰጠው ፣ በውጭ ኃይሎች እጅ ፖለቲካዊ እንዝርት ይሽከረከር ጀመር ።

«ይሁን እንጂ ነባራዊ ታሪክ ፣ በመጨረሻ ታሪካዊ ፍርዱን ሠጠ ። የአንድነት ማኅበር ዓላማ በአሸናፊነት ወጣ ። ኤርትራ ከእናት አገሯ ጋር በፌዴሬሽን ተዋሀደች ። ሆኖም ፣ ነገሩ በዚህ አላቆመም ። እንግሊዝ ለጥቅሟ ስትል በኤርትራ ምድር ቀብራ

የወጣችው በምብ ቀስ እያለ ይፈነዳ ጀመር ። በሥልጣን ፥ በጥቅምና በሹመት ያኮረፉ አንዳንድ ያገሩ ተወላጆች፥ የፌዴሬሽኑ ሕጋዊ መንፈስ በትክክል ሥራ ላይ አልዋለም በማለት ውስጥ ውስጡን ነገር እየጎነጎኑ ፥ የኤርትራ ጉዳይ እንደገና በተባበሩት መንግሥታት እንዲታይ ጥረት ያደርጉ ጀመር ። ነገሩን እንዲገፉበት የሚገፋፉቸውና የሚያግዛቸው አገሮች አላጡም ። የዐረብ አገሮች ፥ በተለይም ግብጽ ፣ ለዚህ ዝግጁዎች ነበሩ ። ዐባይን ከምንጩ ቀይ ባሕርን ካናቱ ለመቆጣጠር ያላቸውን የቆየ ዓላማ በተግባር ሊተረጉሙ የሚችሉት የኤርትራን ምድርና ሕዝብ የመረማመጃ ድንጋይ በማድረግ እንደሆነ ያውቃሉ ። በጊዜው የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥትም በምኝነቱና በጠባብ አመለካከቱ በራሱና በአገሪቱ ላይ ዱላ ከማቀበል ያነሰ ሚና አልተጫወተም ነበር ። ይባስ ብሎ ፥ «ኢትዮጵያን አግኝታችኋል ፥ ሞትም ያውላችሁ!» የሚሉ ፥ ኤርትራ ለኤርትራውያን በማለት ለጥቅማቸው ሽንጣቸውን ገትረው ይሟገቱ የነበሩትን አንዳንድ ግለሰቦች እየመረጠ ቁልፍ ቦታዎች ላይ ይሾማቸው ጀመር ። የአንድነት ማኅበር አባሎች አንገታቸውን ደፉ ።

«ፌዴሬሽን ፈርሶ ኤርትራ ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሀድ ከተደረገ በኋላ ፥ «ማኅበር ሽውዐቴ» ወይም «ሐረካ» በመባል ውስጥ ውስጡን ይካሄድ የነበረው ንቅናቄ ግልጽ እየሆነ መጣ ። ይህ ንቅናቄ በመሠረቱ በሕግ እንሟገታለን በሚሉ ፥ በሥልጣን እና በጥቅም ሽሚያ ባኮረፉ አንዳንድ ሰዎች የሚመራ ነበር ። ሐረካ ወይም ኤርትራ ሊበሬሽን ሙቭሜንትን የመሠረቱት እንደ ኢብራሒም ሡልጣንና ወልደአብ ወልደማርያም የመሰሉት የቀድሞው ራቢጣ አልእስላሚያ መስራቾች ነበሩ ። እ. ኤ. አ. በ1958 ጀብሐ ወይም ኤርትራ ሊብሬሽን ፍሮንት ተመሠረተ ። በጀብሐና በሐረካ መካከል የሥልጣን ቅራኔ ተነሳ። ሐረካ ተመታ ፥ ሕልውናው ለመጨረሻ ጊዜ አከተመ። የመጀመሪያዋ የአመጽ ጥይት በ1961 በኤድሪስ አዋቴ ተተኮሰች ። በእነ ኢድሪስ ዓደም ፥ ዑስማን ሳልህ ሳቤ ፥ አብዱላ ኢድሪስ ፥ ያናይ ፥ ዑመር አዛዝ ፥ አብዱል ከሪም መሐመድ ፥ ዓሊ ዑማሮና ወልዳይ ካህሣይ የተመሠረተው ጀብሐ በቆላማው አገር የበላይነቱን ከያዘ በኋላ ፥ የኤርትራ ሕዝቦች ብቸኛ ተወካይ እኔ ነኝ ፥ ኤርትራ ዓረባዊት ናት በማለት ፥ ጭራውን እዚህ ፥ ጭንቅላቱን በዓረቦች አገር አድርጎ ፥ ኤርትራን በእምስት ቀጠ

ናዎች በመከፈል ከውስጥና ከውጭ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ማዕበል ይፈጥር ጀመር ። መሐመድ ዴናይ በባርካ ፣ ዑመር አዛዝ በሰምሐር ፣ አብዱል ከሪም መሐመድ በሠንሂት ፣ ዓሊ ዑማሮ በማርያ ቀይሕ እና በማሪያ ጸሊም ፣ ወልዳይ ካህሣይ በደጋማው አገር ተሰለፉ ። ከአሰላለፋቸው ለማየት እንደሚቻ ለው ጀብሐ ዘጠና ፀመቶ የባርካና የአሳውርታ ተወላጆች የበላ ይነት የያዙበት አጻም ሆኖ ይገኛል ። በመሆኑም ጀብሐ ውስ ጣዊ አንድነቱን ይዞ ለመቆየት አልቻለም ።

«ለምን፤ አንዳንድ ታዛቢዎች እንደሚሉት በውስጥ የመከ ፋፈሉን ሁኔታ ያመጣው ርዕዮተ ዓለማዊ ቅራኔ ሳይሆን ፣ የኤር ትራን ሕዝብ የሚወክለው ማነው፤ እስላም ወይስ ክርስቲያን፤ ቆለኛ ወይስ ደገኛ፤ ቆለኛ ከሆነ የትኛው ጎሳ፤ የሚል የሥልጣን ጥያቄ ነበር ። ዘመን ከፍለታት ወይም የመከፋፈል ዘመን ተጀ መረ ። በእንግሊዝ የተተከለው ቦምብ ሥራውን እየሠራ ነበር ።

«በጀብሐ ውስጥ የበላይነትን የያዙት የባርካና የአሳውርታ ተወላጆች የተቀሩትን እያሳደዱ ይመቱ ጀመር ። ሳላህ ሳቤ ከሥልጣን ተባረረ ። በዚህ የተነሳ ሠልፍ ናጺነት የተባለው የጀግኖች ቡድን ፣ ሕዝባዊ ኃይሊ የተባለው የማሪያ ቀይሕ ተወላጆች ቡድንና ዑብል የተባለው የባርካ ተወላጆች አንድ ክንፍ ፣ በሳልህ ሳቤ አማካይነት ሻዕቢያ የተባለውን ግንባር ፈጠረ ። የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አብዮት በ1966 እስከ ፈነዳ ድረስ የጀብሐና የሻዕቢያ እርስ በእርስ ጦርነት በኤርትራ በረሀዎች ሲቀጣጠል ቆየ ።

«በ1966 በረኸኞችን ከመንግሥት ጋር የሚያስታርቁ አንዳንድ ሽማግሌዎች ተመርጠው ተላኩ ። ጀብሐና ሻዕ ቢያ ከአሥመራ 16 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያገኙ ነበር ። የአሥ መራና የአካባቢው ሕዝብ በእርቁ ድርድር እንዲሳተፍ የበኩ ሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ በማለት ሔዶ እንዲመለከት ተፈ ቀደ ። መንግሥትንና በረኸኞችን ለማስታረቅ የሔዱት ሽማግ ሌዎች ጀብሐንና ሻዓቢያን አስታርቀው ተመለሱ ። አንዳንዶ ቹም በዚያው ወደ በረሀ ኮበለሉ ።

«በኢትዮጵያ የተቀጣጠለው አብዮት በምሥራቅና በደቡብ በሶማሊያ ፣ በሰሜን ምዕራብ ፣ የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኅብረት ነን በሚሉ መሳፍንት ፣ በውስጥ እንደ ኢሕአፓ እና ሌሎች አምስተኛ ረድፈኞች ፣ በውጭ ደግሞ በተባበረ የኢምፔሪያሊዝም ኃይል የተወጠረበት ቀውጢ ጊዜ ነበር ። ለአብዮቱ የቀረበለት ጥያቄ ፣ ከአብዮቱ ወይም ከኤርትራ የትኛውን? የሚል አስቸጋሪ ጥያቄ ነበር ። የኢትዮጵያ ሕልውና ታላቅ ፈተና ላይ ወደቀ ። ኢትዮጵያ የምትባለው አገር ከእንግዲህ አከተመች ፣ አለቀላት ይባል ጀመር ። እውነትም ያለቀላት መስሎ ታይቶ ነበር ። አዲሱ የኢትዮጵያ ካርታ ምን እንደሚመስል ለማየት የሚሞክሩ ሰዎች ጥቂት አልነበሩም ። ሁኔታውን በማየት ፣ ጥንቱንም ዐባይን ከምንጩ ፣ ቀይ ባሕርን ከናቱ በመቆጣጠር የተዳከመች ኢትዮጵያን ለማየት የሚፈልጉት አንዳንድ የአረብ መንግሥታት ፣ ሱዳን ጭምር ፣ ከተገንጣዮች ጎን በይፋ ተሰልፈው ፣ እንደ እብድ ገላጋይ ካራ ያቀብሉ ጀመር ። ይህ ሁሉ ተደምሮ ለተገንጣዮች አመች ሁኔታ ፈጠረላቸው ። ወርቃማ ጊዜ መጣላቸው ። ሁኔታውን በመጠቀም ተንቀሳቀሱ ።

«ሳሕል ፣ ከረን ፣ ደቀመሐሪ ፣ በከፊል ምጽዋ ፣ ደንጎሎ ማንዳዕ ፣ ነፋሲት ፣ አምባትካላ ፣ ሠገነይቲ ፣ ናቅፋ ወዘተ በሻዕቢያ እጅ ወደቁ ። ባርካ ፣ መንደፈራ ፣ ዓዲኳላ ፣ አቆርዳት ፣ ተሠነይ ወዘተ በጀብሐ ተያዙ ። አሥመራ ፣ ባሬንቱና በከፊል ምጽዋ ነበሩ በመንግሥት እጅ የቀሩት ። እነዚህም ቢሆኑ የጊዜ ጉዳይ ነበር ። የምጽዋ ሦስት አራተኛው ክፍል ተይዟል ። አሥመራ በሰባት ኪሎ ሜትር ርቀት ተከባለች ። የአሥመራ ጉሮሮ ታንቋል ። ምግብ ፣ ውሀ ፣ መብራት ፣ ማገዶ ፣ የለም ። ረሀብ ገብቷል ። እፍኝ ጥሬ አሮአል ። የቤት ዕቃ እየ ፈለጡ ማንደድ ተጀምሮአል ። ከተኩስ ሌላ የሚሰማ ሙዚቃ የለም ። ተኩሱ ላንዳፍታ ሲቆም ዓለም እንደሙታን መቃብር ጸጥ ይላል ። እና መላክ ሞት መጥቶ በጆሮ ያንሾካሹካል ። እየሩ የሞት ጠረን ይዞ ይመጣል ። ሕጻናት ተርበው ያለቅሳሉ ፣ እናቶች ተጨንቀው ዋይታ ያሰማሉ ፣ ሽማግሌዎች ከደጅ ቁጭ ብለው ይተከዛሉ ። ፋብሪካዎች ጢስ አይታይባቸውም ፣ ማሳዎች ጠም አድረዋል ። ገበያዎች አይቆሙም ፣ ዚቆሙም ባዶ ነበሩ — የቁልቋል ገበያ!

ተገንጣዮች ወይም የውስጥ ደጋፊዎቻቸው እንደሚሉት ተጋደልቲ «ዛሬ ሊገቡ ነው ፣ ነገ ይገባሉ» በማለት ወሬ ስለ ሚያናፍሱ ፣ ቆራጥ ቆራጡ ፣ ይምጡ ምናለ ፣ ሞተን እንጠብቃቸውም! በማለት በሕይወቱ ቆርጦ ሲጠባበቅ ፣ ሌሎቹ ደግሞ የተገንጣዮች ደጋፊ ባይሆኑም ፣ እዚህ ቁጭ ብለን እንዴት እን ጠብቃቸዋለን? ባይሆን ወጣ ብለን ከእነሱ ጋር ከበሮ እየመ ታን ብንገባ ይሻላል በማለት በድል አጥቢያ አርበኝነት ከከተ ማው እየወጡ ይኮበልሉ ነበር ። አምባሻ ጋግረው ፣ ጠላ ጠም ቀውና ቄጤማ ጎዝጉዘው የእነ «ንባተም»ን ወይም «ተጋደልቲ»ን በድል መግባት ይጠባበቁ ነበር ። በኤርትራ ክፍለ ሀገር ታሪክ ውስጥ የበላይነትን ያገኛል ተብሉ የሚገመተውን ኃይል ተቀ ብሉ የማስተናገድ ዝንባሌ አዲስ ነገር አይደለም ። በ400 ዘመን የትግል ታሪክ ውስጥ አንዱ ኃይል ሲሄድና ሌላው ሲመጣ ማየት የተለመደ ነገር ሆኖ ቆይቷልና አድርባይነት ሁለተኛ ተፈጥሮ ሊሆን ምንም አይቀረውም ። መጠራጠር ይበዛል ። የ «ቶማሶች» ቁጥር ቀላል አይደለም ።

«ለማንኛውም ነገር ለተገንጣዮች መጠናከር ምክንያት የሆነው ምን ነበር?

«አንደኛ — በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ከውስጥና ከውጭ የደረሰው ከባድ ውጥረት ምናልባት እንደዋነኛው ምክንያት ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል ። በጊዜው የነበረው ሠራዊት በምሥራቅ ፣ በደቡብ ፣ በሰሜንና በመሐል አገር ፣ በየግንባሩ የተቃጣውን ግፊት ለመቋቋም በቂ ኃይልና ትጥቅ አልነበረውም ። በዚህ ላይ የቆመለትንና የሚዋጋለትን ዓላማ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሠራዊት ካለመሆኑም ሌላ ፣ ሠራዊቱ ያው የማኅበረ ሰቡ አካል እንደመ ሆኑ መጠን ፣ መ.ኢ.ሶ.ን. ኢ.ሕ.አ.ፓ ፣ ወዝሊግ ፣ ኢ.ጭ.አ.ት ፣ ሰደድ ፣ ኢ.ድ.ሕ. ወ.ዘ.ተ. በሚባሉ ፣ ጊዜው በፈጠራቸው የፖለቲካ መስመሮች ውስጥ የተከፋፈለ ፣ የተዳከመና ለጥቃት የተጋለጠ ነበር ።

«ሁለተኛ — በኢትዮጵያ ላይ የቆየ ዓላማ ያላቸው የአካባ ቢው መንግሥታት በአገሪቱ የተፈጠረውን አስጊ ሁኔታ በመ ጠቀምና የቆየ ሕልማቸውን እውን ለማድረግ ከምንጊዜውም ይበልጥ እንደ ጅብ ተጠራርተው በመነሳት ተገንጣዮችን አፍ

ንጫቸው ድረስ ያስታጠቁበት ፣ በሰውር በኢትዮጵያ ምድር ላይ ወታደራዊ ኃይል ያሰለፉበት ጊዜ ነበር ። በጊዜው አብዮቱ የሚተማመንበት የውጭ ኃይል አልነበረውም ። አሜሪካ አዲስ መሣሪያ የመስጠት ጉዳይ ቀርቶ ፣ ቀደም ሲል ለኢትዮጵያ የሸጠችውን መሣሪያ አግዳ ይዛለች ። የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ከሶቪዬት ኅብረት ጭምር ፣ የኢትዮጵያን አብዮት ባሕርይና ይዘት እስኪረዱ ድረስ በታዛቢነት ቆመው የሚመለከቱበት ጊዜ ነበር ። የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከራሱ ሌላ የሚተማመንበት ኃይል አልነበረውም ። መደራጀት የጊዜው አንገብጋቢ ጉዳይ ቢሆንም ፣ ውስጥ ውስጡን ይካሄድ የነበረው የፖለቲካ መስመሮች ሽኩቻ በታኝ ሁኔታ እየፈጠረ ያስቸግር ነበር ። በመሆኑም ፣ አብዮቱ በጊዜው የራሱን ኃይል በአዲስ መዋቅርና መንፈስ ለመገንባት ፋታ ያጣበት ቀውጢ ጊዜ ነበር ።

«ሦስተኛ — በኤርትራ ክፍለ ሀገር ተደራጅተው የሚገኙት ኃይሎች ፣ ጸረ ፊውዳል ፣ ጸረ ኢምፔሪያሊስትና ጸረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም አቋም አላቸው በሚል ግምት ፣ አብዮታዊው መንግሥት ገና ከመመስረቱ የመረጠው የእርቅ ጎዳና ፣ በተገንጣዮች ዘንድ እንደ ድክመት በመታየቱ ፣ አንድም ሞራላቸውን ከፍ አድርጎ ሲያበረታታቸው ፣ ሁለትም ፣ ነጻ ንቅናቄ እንዲያደርጉና ፕሮፓጋንዳ እንዲያካሂዱ ደህና የእድል በር ከፈተላቸው ። በመሆኑም የሚመካበት ኃይል ያጣ የመሰለው ሕዝብ እየኮበለለ ሔዶ የተገንጣዮችን ኃይል ያሳብጥ ጀመር ። በመሆኑም አብዛኛዎቹ የኤርትራ ከተሞች በወንበዴዎች እጅ ወደቁ ።

«በዚህን ቀውጢ ጊዜ ነበር ሁለተኛው ነጻ እውጭ አብዮታዊ ሠራዊት «አብዮታዊት ኢትዮጵያ ወይም ሞት» በማለት በየአቅጣጫው በቆራጥነት ሲተም የመጣው ።

«መሰከረ የኤርትራ ሰፊ ሕዝብ አንድ አካልና አለኝታ በመሆን ። በየጎራው በድል አድራጊነት ይተም ጀመር ።

በልዩ ልዩ ግብረ ኃይሎች ሥር የተሰለፈው ሁለተኛው ነጻ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት በሚያስደንቅ ፍጥነት የጠላትን ምሽግ ድባቅ እየመታ ነበር ወደፊት የሚገሠግሠው ። 501 ግብረ ኃይል ከሰቲት ሁመራ ተነስቶ በአሊ ጊደርና በተሠነይ

በማድረግ ፣ ከእንጥጮ ተነስቶ ፣ መረብን ከላይ በመሻገር በሸም ብቆ አድርጎ ከመጣው ከ502 ግብረ ኃይል ጋር ባሬንቱ ላይ ይገናኛል ። 501 እና 502 ግብረ ኃይሎች እንደገና 508 ግብረ ኃይል ተብለው ፣ ግማሹ ሳዌን ወደ መሣሊት ሲገሥግሥ ፣ ሌላው ደግሞ ወደ ታች ታጥፎ ወደ ከረን ካመራ በኋላ ከአሥመራ አካ ባቢ በመንቃንቅ በለዛ ፣ እምባደርሆ ፣ ዐዲ ገብሩና ኢላበርዕድ ላይ ይገኙ የነበሩትን የጠላት ምሽጐች እየሰባበረ ከመጣው ከ506 ግብረ ኃይል ጋር ከረን ላይ በድል ይገናኛል ። በሀ እና በለ የተከ ፈለው የ503 ግብረ ኃይል ተልእኮ እንደሚከተለው ነበር ። 503 ሀ ግብረ ኃይል የተነሳው ከዓዲግራት ሲሆን ፣ በራማ አድርጎ መረብን ከተሻገረ በኋላ ዓዲ ኳላን ፣ መንደፈራን ፣ ዓረዛን ኩዚ ያምተራእምኒና ድባርዋን በቁጥጥር ሥር በማዋል ሸከቲ ላይ ከ506 ግብረ ኃይል ጋር ይገናኛል ። እንዲሁም ከአድዋ በመነሳት ጾረናን ተሻግሮ የመጣው 503 ለ ግብረ ኃይል በደቀመሐሪ አድ ርጎ ከ503 ሀ እና ከ506 ግብረ ኃይሎች ጋር..... ላይ ይገናኛል ። ከአሰብ በመርከብ ምጽዋ የገባው 505 ግብረ ኃይል የጠላትን እከርካሬ ዕዳጋ ላይ ሰብሮ ፣ የዶጋሊን ፣ የደንጎሎን ፣ የእምባት ካላን ፣ የጊንዳዕንና የነፋሲትን ምሽጎች በመሰበባርና የአሥመራ ምጽዋን መንገድ በመከፈት አሥመራ ይገባል ። በሁሉም አቅ ጣጫ የድል ጉዞ ነበር ።

«ከዛሬ ነገ እንገባለን በማለት በአሥመራ ከተማ ዙሪያ እንደ ጀሬ አሞራዎች አሰፍስፈው የነበሩት ወንበዴዎች ፣ የሁዋሊት ማርሽ አስገብተው ወደ ሣሕል በረሀ ከመፈርጠጥ ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም ።

«አሁን ጀብሐና ሻዕቢያ በሣሕል በረሀ ይፋጠጡ ጀመር ። አንድነታቸው ሳይሆን ልዩነታቸው እየጎላ መጣ ። የሣሕል በረሀ ለሁለቱ ድርጅቶች ጠቦ አይደለም ። አብረው ለመኖር ስለማይችሉ ብቻ ነበር ። እንደገና እንግሊዝ ቀብሮት የሔደው ቦምብ ሥራውን መሥራት ጀመረ ። የኤርትራን ሕዝብ በውስጥም ሆነ በውጭ የሚወክለው ማነው? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ እየጎላ መጥቶ ፣ በሻዕቢያና በጀብሐ መካከል የእርስ በእርስ ጦርነት እንደገና ተከፈተ ። የጀብሐ ኃይል እንዳለ ተመታ ። ሻዕ ቢያ የበላይነቱ ተቀዳጀ ። ቀደም ሲል ሻዕቢያ የሦስት ድርጅ ቶች ግንባር መሆኑ ቀርቶ የደጋው አገር ተወላጆች ብቻ ፖለቲ

ካዊና ወታደራዊ ሥልጣን በሞኖፖል የጨበጡበት ድርጅታዊ መዋቅር ሆኖ ነበር ። ደጎኞችም ቢሆኑ እርስ በርሳቸው ተስማም ተው ሊኖሩ አልቻሉም ። የአከለጉዛይ ፣ የሡራዬ ሴራ እየተባለ የእርስ በእርስ ፍጅት ስለቀጠለ ፣ በመጨረሻ ሻዕቢያ የአንድ አካባቢ ተወላጆች የሥልጣን መድረክ ለመሆን በቃ ።

«ጀብሐና ሻዕቢያ ኤርትራን በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል ቢችሉ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? ብለን እስቲ እናስብ ። ያው የታወቀው ነገር ይሆን ነበር ። ታሪክ በአዲስ ክስተት ወደ ፊት ቢራመድም መሠረቱን አይለቅም ። የእንግሊዝ ፖለቲካዊ ቦምብ በባሰ ሁኔታ በኤርትራ ምድር ይፈነዳ ነበር ። ሌላ የኮንጎ ፣ የናይጀሪያ ፣ የቻድ ፣ ሁኔታዎች በአፍሪካ ምድር ይፈጠር ነበር ። ይከተል የነበረውን ጥፋትና እልቂት ለማሰብ አይቻልም ፣ ቢያስቡትም ይዘገንናል ።

በመጨረሻ ፣ «ከዚህ ሁሉ ምንድነው የምንማረው? የዚህ ክፍለ ሀገር ችግር ባብዛኛው ከውጭ ተጽዕኖ የሚመነጭ መሆኑን ነው ። የኤርትራ ሕዝብ ይህን ማወቅ አለበት ። የውጭ ኃይሎች መሣሪያ በመሆን እስከመቼ ድረስ የገዛ አገራችንን ስንወጋ እንኖራለን? ቅኝ ገዢዎች በመካከላችን ጠምደው የሄዱትን ፣ እየቆየ የሚፈነዳ ቦንብ ነቅለን መጣል አለብን ። ይህን ልናደርግ የምንችለው እርስ በእርሳችን ስንተማመን ነው ። ልባችንን መከ ፈት ስንጀምር ነው ።» ሲል አንድ ወንድና ሴት ተያይዘው መጡ ።

ሥዕላይ በራኺ መሆን አለበት አልኩ ። ግን ዓይኔ ሮጦ ያረፈው ልጅቷ ላይ ነበር ። ንጉሥ ዳዊትን የፈወሰችው ሰሜናዊት ቆንጆ ልብ ስንጥቅ ታደርጋለች ። ረጅም ባለጥልፍ ቀሚስ ለብሳ ፣ ትንሽ ነጠላ ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋለች ። በጥቁር ከፈይ የታ ሠረ ፣ በሰለሞን ኮከብ ቅርጽ የተሠራ ትልቅ ወርቅ ከረጅም አን ገቷ ላይ ጉች ብሎ ይታያል ። ጥቁር ረጅም ጠጉሯ ከትከሻዋ ላይ ወርዶ ዘፍ ብሎአል እና ስትሔድ ይነሰነሳል ። እንደሌሎቹ የአሥመራ ሴቶች ስንጥር መሳይ አይደለችም ። ደረቷ ሙሉ ፣ ዳሌዋ የኮራ ፣ ጠይም ፣ የደም ገንቦ የሚሏት ዓይነት ነች ። ዓይና ቿን ተከተልኩ ። ዓይኖቹ ተወርውረው የሔዱት ወደ ኮሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ነበር ። የተቆጣች ድመት መስላ ነበር የምታ

የው ። እሱም እንደተቆጣ ነብር ሆኖ ይመለከታት ነበር ። ክራ
ንቻና ጥፍር ባይማዘዙም ፥ በዓይኖቻቸው የቁጣ ቃላት የሚለዋ
ወጡ መሰለው ታዩኝ ። ድንገት ሰውነቱ ተቆጣ ፥ ሁኔታው ተለ
ወጠ ። እሷም ደስ አላላትም ። ፈገግታዋ ጨለመ ። በሁለቱ
መካከል የነበረው ስሜት ደስ አላለኝም ። ይሁን እንጂ ስለግን
ኙነታቸው ለማሰብ ውበቷ ጊዜ አልሰጠኝም ። የምታሳስብ
ዓይነት ሴት አይደለችም ። እንዲያው ገና ሲያዩዋት የምትወደድ
ልጅ ናት ። ዳቦ ሳይቆረስ 'ስሜናዊት ቆንጆ' ብዬ ስም አወጣ
ሁላት ።

ሥዕላይ በራኺና ሰለሞን በትረጊዮርጊስ ትክሻ ለትክሻ
ተሳሳሙ ። ሰለሞን እየዞረ ያስተዋውቀው ጀመር ። ከኰሎኔል
ታሪኩ ወልዳይ ጎን ነበር የቆምኩት ። አጠገቡ መቆም ደስ
አይለኝም ። አጭር ባልሆንም እሱ አጠገብ ስቆም ድንክ የሆንኩ
ያህል ይሰማኛል ።

የኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይን ስም ሲሰማ ጆሮውን እንደ
ሚዳቋ አቆመ ። ወደ ላይ አንጋጦ እንደ ድንቅ ሲመለከተው
ከቆየ በኋላ ፥ «ኤይ ሳልሽ ኮኔረ? ከመይ ቀኒኻ?» ብሎት ትክሻውን
አገላብጦ ሳመው ።

ሥዕላይ ጀግና አይመስልም ። ለመሆኑ ጀግና ምን ይመስ
ላል? አላውቅም ። አንዳንድ የማውቃቸው ጀግኖች አጭሮች
ናቸው ። ሌሎቹ ወፍራሞች ናቸው ። የተቀሩት ደግሞ ሰው
ቀና ብለው የማያዩ ዓይነ አፋሮች ናቸው ። ሥዕላይ ቁመቱ ዘለግ
ያለ ፥ ቀጭን ፥ ጉረኛ ቢጤ ነው ። ዓይኖቹ ትናንሽ ናቸው ። ጠጉሩ
ብን ብላ የሳሳች ናት ። ልብስ መርጦ መልበስ የሚያውቅ ይመስ
ላል ። ባለሸንትር ቡላማ ልብስ ከነሰደሪያው ለብሷል ። አሁንም
ዓይኔ ከልጅቷ አልተለየም ። እሷም ፥ የት ነው የማውቀው? በማ
ለት ሳይሆን አይቀርም ፥ አንዳንዴ ውብ ዓይኖቿን ጣል ታደር
ግብኝ ነበር ። በዚያ መከረኛ ቴሌቪዥን አይታኝ ይሆናል ።
አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች በቅርብ የሚያውቁኝ መስሎአ
ቸው ሠላምታ ከሰጡኝ በኋላ ግር ሲላቸው ላይ ያስቁኛል ። ላይ
ላዩን ልሳቅ እንጅ ውስጥ ውስጡን ታዲያ ያናድደኛል ። መልኬን
የሚያስታውስ ሁሉ አያውቀኝም ። ዝና ሙላጭ ነገር ነው ።

«ግን ምን ዓይነት ሠይጣን ነህ!» አለ ሥዕላይ አሁንም በመ ደነቅ ኰሎኔል ታሪኩን እየተመለከተ ።

«አንተም ሠይጣን ነህ» አለው ።

«ሻዕቢያ አንተን ለመግደል ያልሞከረችው ነገር የለም ። ግን ዘጠኝ ነፍስ አለህ መሰለኝ፣ ታስታውሳለህ ፣ አንድ ቀን ደቀመሐሪ ላይ ከበንህ ነበር ። እንደምንም ብለህ አመለጥከን ። ጥይት ለምን እንደማይመታህ አይገባኝም» አለው ።

«ቀጭን ስለሆንኩ ይሆናል ..........»

«በጣም ደፋር ነህ ። ሁለት መትረየስ በግራና በቀኝ እጅህ ይዘህ ደረትክን ገልብጠህ መሐላችን ስትገባ ይገርመኝ ነበር ። እጠላህም ፣ አደንቅህም ፣ አከብርህም ነበር ። ያ ሁሉ አለፈ ። በሕይወት ኖረን ለዚህ መብቃታችን ጥሩ ነው» አለ ሥዕላይ ። ሲናገር ይቸኩላል ንቅናቄው ሁሉ ፍጥነት አለው ።

ኰሎኔል ታሪኩ በዚያ ቁመቱ ላይ እያንዣበበ «አንተንም የምጠላህን ያህል አከብርህ ነበር ። ዓላ ላይ የሠራኸን ሥራ ትዝ ይልሀል፤ እንደዚያ ከበንህ እየተኮስክ ስንጥቀኸን ስትወጣ ዓይኔን ለማመን አቅቶኝ ነበር ። ደቀመሐሪ እንደዚያ ፈራርሳና እንዳልነበረች ሆና ሳያት አንተን ለመግደል ያልጣልኩት መሐላ አልነበረም ። ደቀመሐሪ የተወለድኩባት ከተማ ናት ። መቸም ሕይወት የምትሔድበት መንገድ አይታወቅም» አለ ኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ።

ሥዕላይ ተወራጨና ፣ «ያጠፋሁትን ያህል ለመካስ ዝግጁ ነኝ ። ኃጢአተኛው ተመልሷል ። ከእንግዲህ ወሳኙ ነገር መ ጭው ጊዜ ነው ። ያለፈው አልፎአል» ብሎ ወደኔ መጣ ።

ሰለሞን አስተዋወቀን ። ፎቶግራፍ እንደሚያነሳ ሰው በጣም አተኩሮ ሲመለከተኝ ከቆየ በኋላ በቁጣ ፣ «ለምንድነው ወዶ ገብ እያላችሁ የምትጠሩን፤ እኛ ውሾች አይደለንም ። ሰዎች ነን ፣ በእውነት እኛ ከበረሀ የተመለስን ሰዎች ሁኔታ ያሳዝናል ። የወንበዴዎች የውስጥ ደጋፊዎች በየመንገዱና በየቡና ቤቱ

ሲያዩን ይተቆጡናል ። ወንበዴዎች በራዲዮ ጣቢያቸው ከሐዲ ዎች ፣ ፈሪዎች ፣ ራስ ወዳዶች ይሉናል ። መንግሥት ደግሞ ምንም እንኳ ምኅረት ቢያደርግልንም ፣ ሙሉ እምነት የሚያሳድርብን አይመስለንም ። እናንተ ጋዜጠኞች ይባስ ብላችሁ ወዶገብ የ ሚል የውሻ ስም ትሰጡናላችሁ ። ምንድነው እንዲህ ዓይነት ነገር! እንደ የከዳ ሁልጊዜ ከሐዲ ነው ያለው ማን ነው!» አለኝ ።

«ሌላ ስም እንፈልጋለን» አልኩት ።
«አዎ ፣ ቶሎ ብላችሁ ብትለውጡት ይሻላል» አለ ።

«በረኸኛ» እንዳንላችሁ አውሬ አይደላችሁም «ሠርጐገብ» እንዳንል ደግሞ አይሆንም «በሠላም የተመለሱ» እንዳንል ሠላ ማዊ መሆን በተግባር መታየት አለበት ። መላ ያጣ ነገር ሆኖብን ነው'ኮ» አልኩት ።

ድንገት በጥፊ እንደተመታ ሰው ክው አለ ። ምን እንዳስደ ነገጠው አልገባኝም ። አሳቤን ዘልቆ ለማየት የሚሞክር ነበር የሚመስለው ትክ ብሎ ዓይን ዓይኔን ሲመለከተኝ ።

ቆይቶ ፣ ቆይቶ «ምን አልከ?!» አለኝ ።
«ስቀልድ ነው ምን አጠፋሁ?» አልኩት ።

መልስ አልሰጠኝም ። በትናንሽ ዓይኖቹ እንደ መርፌ ወጋ ቶኝ ወደ ሦስቱ በረኸኞች ሔደ ። ኰሎኔል በትሩ ተሰግ ጀርባዬን ነካ አድርጐ ፣ «ምን ብትለው ነው የተቆጣው?» ብሎ ጠየቀኝ ።

መቸም ፣ ያንን ደስ የሚል ፈገግታውን በምኽት ከሚያበ ራው ፊቱ ላይ ለጥፎ ፣ እያየ እንዳላየ ሆኖ ፣ የሰው ስሜትና ሁኔታ ማጤን ልምዱ ነው ኰሎኔል በትሩ ። የሆነችው ነገር አታመል ጠውም ። አንጐሉ እንደ መዝገበ ቃላት ሁሉን ነገር ይመዘግ ባል ። ከንፈር የማንበብ ችሎታ ሳይኖረው ይቀራል!

«ወዶ ገብ ከማለት ሠርጐ ገብ ማለት ይሻል ይሆን? ስላል ኩት ነው...»
«ለምን እንዲህ አልከው ልጄ?»
«ቀልጄን ነበር..... ምነው ጠየከኝ?»

«እንዲያው ነው ። ይልቅ ከእሱ ጋር የመጣችው ልጅ ዓይኗን ጥላብሀለችና ሒድና አጫውታት» አለኝ ።

«ሴት አትቅረቡ ብለህ የለም እንዴ?»
«ይልቅ ዕድል አያምልጥህ» ብሎኝ ሔደ ።

ምናሰበት አልኩና ወደ ልጅቷ ሔድኩ ። የወንዶችን ወንዳ ወንድ ንግግር መስማት አሰልችቶኝ ነበር ። ለውጥ አይከፋም! «ምነው ብቻሽን ቆምሽ እቱ? ምን ትጠጭያለሽ? ምን ላምጣልሽ?» አልኳት ።

«ቢራ በስፕራይት»

የጥያቄ ፊት አሳየኋት ። 'በቢተር' እሺ ። ቢራ በስፕራይት ሲጠጣ ግን አይቼም ሰምቼም አላውቅም ።

«ጽቡቕ መስተ እዩ» አለች ። ስትናገር ጠጉሯ ይነሰነሳል ። በጠጉሯ የምትናገር ነው የምትመስለው ።

«እው ንጽብቕቲ ቆልዓ» አልኳት ።
«ትግርኛ ትዛረብ ዲኻ»
«እወ ቁሩብ ቁሩብ»
«እስኪ «ሻ» በል»
«ሀ»
«እስኪ «ዐ»በል»
«አ»
«ትግርኛ አትችልም ። አባቴ ይሙት!» አለችኝ እየሳቀች ። እውይ ጥርሶቿ ታይተው አይጠገቡም ። የውበት አምላክ በጥንቃቄ የደረደራቸው የቀይ ባሕር ዕንቁዎች ይመስላሉ ።

«ይኸ ጉሮሮ የሚፍቅ ቋንቋ! መንጉጥ ነው» አልኳት
«እንጥላችሁ ስላልተቆረጠ ይሆናል»
«እስኪ መቶ በይ»
«ምቶ»
«እስኪ አንተ በይ»
«አንቴ»

«አንቺም አማርኛ አትችይም አባቴ ይሙት» አልኳትና መጠጧን ሳመጣላት ሔድኩ ።

መጠጧን ይዤ ስመለስ ሰለሞን በትረጊዮርጊስ መንገድ ላይ ያዘኝ ። የተበሳጨ ይመስላል ።

«ምን ሆንክ?» አልኩት ።

በየደቂቃው ነበር የቴሌፎን ጥሪ የሚደረግለት ። ያሳዝነኛል ። ይበሳጭ እንጂ ድካም ፊቱ ላይ አይታይም ።

«የምጽዋ ፌስቲቫል ኮሚቴ ነው የሚያስቸግረኝ ። ባራት ሰዓት ይጠብቀኛል» አለኝ ።

«ከእንግዲህ? ልብህ እንዳይቆም ብቻ!» አልኩት ።

«ጉርጉሱም ላይ ሁለት ትኩሎች ለመሥራት ፈልገው ፣ ግርና እንጨት አጥተው ተቸግረዋል ። እኔም የሰጠኋቸው ጊዜ በጣም አጭር ነው ። ሐያ አራት ሰዓት እየሠሩ ናቸው» አለ ።

«ታዲያ ሣርና እንጨት ከየት ታመጣለህ? ከጠፋ ለምን አይቀርም......»

«መሠራት አለበት ። ከየትም እንፈልጋለን ። በአይሮፕ ላንም ቢሆን ከየትም እናስጭናለን ።» አለ በጽኑ መንፈስ ።

«በል ብርታቱን ይስጥህ ። ይህን መጠጥ ለዚያች ልጅ ላድርስ» አልኩት ።

«ጋዜጠኛ በደረሰበት የሕዝብ ግንኙነት መኰንን ነው'ኮ ጉሽ አስተናግድልኝ» አለ ።

«ቴሌፎን ይጮህ ነበር»

«ቴሌቪዥን መክፈት ይፈቀዳል?» አልኩት ።

«ምን ፕሮግራም አለ?»

«የኔ»

«ስለምን?»

«ስለአሥመራ»

«መቼ የሠራኸውን?»

«ዛሬ ጠዋት እንደደረስኩ......»

«ከመቸው ደረሰልህ ልጅ? ይቻላል ። እኔም ለማየት እፈል ጋለሁ» ብሎኝ የቴሌፎን ጥሪውን ለመቀበል ሮጠ ። ቤቱም ውስጥ እንደ ሮጠ ነው ።

መጠጡን አመጣሁላትና «ሕራይ ትግርኛ ከትምህርኒ እሺ፡ ሺ እምበእር? ጾጋዬ ኃይለማርያም እባላለሁ» አልኳትና መጠጡን ቀምሼ ሰጠኋት ። እውነትም ጥሩ መጠጥ ነው ።

«በቲሺ አውቅሀለሁ ። አንተም አማርኛ ታስተምረኛለህ» አለች ፣ ጠጉሯን እየነሰነሰች ፈገግታዋ ይናፍቃል ።

«ማን ብዬ ልጥራሽ ስሜናዊት ጽብቐቲ?» ብዬ ስሟን ጠየኳት ሳቀችና ፣ «ፊያሜታ ጊላይ እባላለሁ» ብላ ስሟን ነገረችኝ። ስሟ ደንቆኝ ቅንድቤን ከፍና ዝቅ ሳደርግ አይታኝ፣«ምነው?» አለች ።

«እንግዳ ስም ነው.....»

«የጣሊያን ስም ነው.....»

«ምን ማለት ነው?»

«ትንሽ ነበልባል.....»

«እውነት? እንቺን ከሩቅ መሸሽ ይሻላል» አልኳት ።

«ለምን?» አለችኝ ።

«ስም መላክ ያወጣዋል ይባላል ። እንደ ስምሽ ከሆንሽ አደገኛ ነው ። በትንሽ ነበልባል ተቃጥሎ ማለቅ ደግ አይደለም ። እንደ ስምሽ እንዳልሆንሽ ተስፋ አደርጋለሁ» አልኳት ።

«ነኝ አባቴ ይሙት» አለች ሰቃ ።

«እንዴት?»

«በሕጻንነቴ እሳት ነበርኩ ። እያለቀስኩ ፣ ዕቃ እየሰበርኩ ፣ ከቤት እየጠፋሁ እናትና አባቴን ሳስቸግራቸው ነበር ። ብቻዬን ደግሞ መተኛት አልወድም ነበር ። ብቻዬን ካስተኙኝ ሌቱን በሙሉ ሳለቅስ አድራለሁ ። ከእነሱም ጋር ተኝቼ እነሱ ሲጫወቱ የሰማሁ እንደሆነ አለቅሳለሁ ። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ፊያሜታ የሚል ስም ያወጡልኝ » በማለት አስረዳችኝ ።

«አሁንስ? ብዬ ጠየኳት»

«አሁንም ትልቅ ነበልባል ነኝ ። ለምወደው ግን አይደለሁም ። ለምወደው ሰው ማርና ወተት ነኝ ። ስኳር ነኝ»

«እና የምትወጂው ምን ዓይነት ሰው ይሆን?»

«እንደ ድንጋይ የጠጠረ እንደ ብረት የጋለ ፣ እንደ ስኳር የጣፈጠ ወንድ» ብላ እንደገና ሳቀች ።

«እውነት?»

«ቀልዴን ነው ። ምስጢሬን አሁን አልነግርህም.....»

«ምናለበት?»

«ምስጢር ነው» አለች ።

«እሺ ። ራሴ አንድ ቀን እደርስበት ይሆናል ። ግን ስምሽን ብትለውጪው ጥሩ ነበር.....»

«ለምን?»

«የባዕድ ስም ነው ። የአሥመራ መንገዶች ፣ ሱቆች ፣ ቡና ቤቶች ፣ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች ፋብሪካዎች ሳይቀሩ በባዕዳን ስም ነው የሚጠሩት ። የጣልያን ቅሪት ያው የባዕድ አስተሳሰብና አመለካከት ማስከተሉ አይቀርም ። በዚህ ክፍለ ሀገር ከፍተኛ የባሕል አብዮት ማካሔድ ያስፈልጋል ፣ በእውነት ። አይመስልሽም? አልኳት ።

«ፊያሜታ ካስጠላህ ፋና በለኝ» ብላ ዝም አለች ።

ከአኳኋኗ የውይይቱን አቅጣጫ ለመከተል እንዳልፈለገች ተረዳሁ ። ግን አልተናደደችብኝም ። ማንኛውንም ፖለቲካዊ ውይይት ከሩቁ የምትሸሽ መስላ ታየችኝ ። አልገረመኝም ። የክፍለ ሀገሩ ሰው ሁሉ ከፖለቲካዊ ውይይት የመሸሽ ዝንባሌ አለው ። ምናልባት ሰልችቶ ይሆናል ወይም በፍርሀት ። ግን ወደደም ጠላም ከፖለቲካ ሸሽቶ ለመኖር አይችልም ። አሁንም ይሁን ወይም ኋላ ሚናውን ለይቶ መቆም ይኖርበታል ። በቀይ ኮከብ ዘመቻ ወቅት ሌላ ምን አማራጭ ይኖራል? አንዱ ቢሞት ሌላው ተመልካች ሊሆን አይችልም ። ለማንኛውም ነገር በዚህ አቅጣጫ በነገር ልገፋፋት አልፈለኩም ። አርዕስቱን ለወጥኩ ። እንግዳ ውበት ። እንግዳ ስም ። እንግዳ መጠጥ ። ብርቅዬ ዕድል ፣ አድራሻዋን ጠየኳት ። ያለምንም ማመንታት የቤትና የቢሮዋን ስልክ ቁጥሮች ሰጠችኝና «ፈጣን ነህ አባቴ ይሙት» አለች ።

«ሕይወት ቆማ አትጠብቀንም.....»

«የዚህ እግርግር አባል ነህ?»

እንግዳ ጥያቄ ።

«እግርግር አልሺው!?»

«ታዲያ ምን ይባላል? ከተማው ፍጹም ተረብሿል ። በምን ሥርዓት» ብላ ሌላ ጥያቄ ልታቀርብልኝ ስትል ፣ ሥዕላይ ድም ጹን ከፍ አድርጐ ፣«ፍትዊ ወዲ በርሄ ያደረገኝን ላሳያችሁ!» አለና ኮቱን አወለቀ ። ከራቫቱን ፈታ ። ሰደሪያውንም አውልቆ ጣለ ። ምን ሊያደርግ ይሆን? በማለት ሁላችን ተንጋግተን...... ወደ እሱ ተጠጋን ። ጭቅጭቅ ይዘው ነበር ። የሸሚዙን ቁልፎች ፈትቶ ሲያበቃ ሸሚዙን ወደ ላይ ገለበጠና ጀርባውን አሳየን ። እብድ ያረሰው ማሳ ይ መስላል ። አለንጋው አጥንቱ ድረስ ዘልቆ አርሶታል የእብድ እርሻ ። ሸሚዙን ቆልፎ እያስተካከለ ፣ «ጀር ባዬ ላይ ያያችሁት ጠባሳ የጀብሐ ተራማጅነትና ሰብአዊነት ምልክት ነው! አይደለም ወዲ በርሄ? » ብሎ ሰደሪያውንና ኮቱን ደርቦ ሲያበቃ ከራቫቱን አጥልቆ እያስተካከለ ፣«ቆሞ ያስገረፈኝና የገረፈኝ ወዲ በርሄ ነው ። ለምን ቢባል? ጀብሐ ውስጥ ሠርጐ የገባ የኢትዮጵያና የሲ. አይ. ኤ. ወኪል ነው በማለት ። ባልሆንኩት ነገር እንደዚያ ስገረፍ ፣ ቁስሌ ላይ የፈላ ውሀ ሲፈስ አለቀስኩ? ጮሁኩ? ኖኖ ። ዝም ብየ ሞቴን ነበር የምመኘው ። ለመሞት ብፈ ልግም አልሞትኩም ። ለመሞት እፈልጋለሁ ። አልሞትም ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሞትን አልፈራም ። ሞት ምንም እንዳይደል ጀብሐ አስተምራኛለች» አለ ።

ፍትዊ ወዲ በርሄ ሳቀና ፣ «እኔ ሆኘ ነው እንጂ መግደል ቀላል ነበር» አለው ።

«ለሰብአዊነትህ ከፍ ያለ ምስጋና!» አለው በታላቅ ምጸት ።

ፍትዊ ነገሩን በቀላሉ ለመሸፕት ፈልጐ እየሩን በእጁ ገፋና «ለማንኛውም ነገር ማንነትክን በውድም ሆነ በግድ ማረጋገጥ ነበረብን ። ያንድ ድርጅት ሕልውና ቀልድ አይደለም ። ከሠርጐ ገቦች መጠበቅ አ ለበት ። እና አንተ ደግሞ በጣም አጠራጣሪ ፍጡር ነበርክ....» ሲል ።

ሥዕላይ ተቆጣና ፣ «ማን እኔ ወዲ በራሂ!» አለ ።
«አዎ ወዲ ባራሂ» አለ ፍትዊ ፍርጥም ብሎ ።

«የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣን ነበርክ ወረዳ ገዥ ። የኢሣይያስ አፈወርቂ የቅርብ ጓደኛም ነበርክ ። ይህም ብቻ አይደለም ። በታኘው ጣቢያ ውስጥ ኢሳይያስ አፈወርቂን ሪቻ

ርድ ኮፕላንድ ከተባለው የሲ. አይ. ኤ. ሰላይ ጋር ያገናኘኸው
አንተ ነበርክ ። እነሱን በምታገናኝበት ወቅት እኔ እሥራት
ካሣ ያቋቋሙት የኤርትራ ሠላም ጉባዔ ኮሚቴ አባልም ሆነህ
ስትሠራ ነበር ። ታዲያ ይህን ሁሉ እያወቅን ልባችንን ከፍተንና
እጃችንን ዘርግተን እንድንቀበልህ ፈልገህ ኖሮአል? ዋእ! እስካ
መንበት ድረስ ለአላማ ነበር የቆምነው ። አሁን ያ ሁሉ አልፎአል።
እኔም ሆንኩ አንተ በረሀን ለአድህሪያንና ለብልጦች ትተን መጥ
ተናል ። ከእንግዲህ ላንድ ዓላማ አብረን መሥራት አለብን ።
ጀርባህ ላይ ያለው ጠባሳ ያለፈ ታሪክ ነው ። እርሳው!» አለና
ውስኪውን በንዴት ተጐነጨ ። ቀጠለና ፣ «እና ደግሞ የኢትዮ
ጵያን ሰፊ ሕዝብ አብዮት ተሳስቼ በመውጋቴና በማድማቴ ነው
እንጂ እንተን በመግረፌ ወይም በማስገረፌ የሕሊና ጸጸት አይ
ሰማኝም...... ወዲ ደጃዝማች!» አለው ።

ከዚያ ነገሩ አቅጣጫውን ለውጦ ፣ አንተስ የማን ልጅ ሆን
ክና? በሚል ርዕስ መከራከር ጀመሩ ። አራቱም የደጃዝማቾች
ልጆች ነበሩ ። የሚገርመው ነገር ፣ አባቶቻቸው የአራቱም አባ
ቶች የታወቁ «ዩኒዮኒስቶች» የነበሩ መሆናቸውን ከጭውውታ
ቸው ስረዳ ፣ እነዚህ ያባት እጥንት አስለቃሾች ከምን ላይ በቀሉ?
የሚል ጥያቄ መጣብኝ ። እና ለምን? እንዲያውም «ኢትዮጵያ
ወይም ሞት!» የተባለውን የማኅበር አንድነትን ዘላለማዊ መፈ
ክር በመጀመሪያ ያወጡት የሥዕላይ አባት እንደ ነበሩና ፣ በኋላ
ልጆቻቸው ይህን ክቡር መፈክር ጥለውና ረግጠው ፣ ኤርትራን
ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ወደ በረሀ ሲገቡ ፣ በዚሁ ሁናቴ ተበሳ
ጭተው በልብ ሕመም በድንገት የመሞታቸውን ወሬ በሰማ አዘ
ንኩ ። መጥፎ ኃዘን ተሰማኝ...... የዘሩት ሲጠፋ...... ሳይበቅል
ሲቀር ወይም እንክርዳድ ሲበዛበት...... አይ የገበሬ ድካም...... ኃዘን
ይህች እናት አገር...... የሚያደጓትንና ጡቷን የሚነክሱ ልጆች
የማትወልድበት ጊዜ መቼ ይመጣ ይሆን ፣ ዥጉርጉር የእናት
ሆድ... ሥዕላይ ወደ መስፍን ጽሩዕ ዞሮ ነበር ።

«ከጀብሐ አምልጬ▼ ወደ ሻዕቢያ ስመጣ ማን ተቀበለኝ
መሰላችሁ? ወዲ ጽሩዕ ነበር ። ጀርባዩን ባላየውም አላመነ
ኝም ። በውንብድና ዓለም ውስጥ መተማመን የለም ። የቁም
እሥረኛ ሆኘ ላንድ ወር ያህል ምርመራ ላይ ቆየሁ

«ከዚያ ምን አደረገኝ መሰላችሁ? ወደ ቢሮው ወስዶ ኪስህን አራግፍ አለኝ ። ያለ የሌለኝን ነገር አራገፍኩ ። እና ይህ የማ ፎቶግራፍ ነው?» ብሎ ጠየቀኝ ።

«የናቴ» አልኩ
«ከዛሬ ጀምሮ ያለሻዕቢያ እናት የለህም» ብሎኝ የናቴን ፎቶግራፍ አሬቱ ቀዶ ጣለው

«ይህችስ ማን ናት?»
«ፍቅረኛዬ» አልኩ
«ከዛሬ ጀምሮ ያለሻዕቢያ ሌላ ፍቅረኛ የለህም ብሎ ፎቶግራፏን ቀዶ ጣለው ።

«ያንገቴን ወርቅና የጣት ቀለበቴን ወስዶ ፣ ያለሻዕቢያ ሌላ ጌጥ አያስፈልግም አለኝ ። ከዚያ ማግዬን ልብሴን ወስዶ ለማግ ሸበጥ ለልብስ ጀንያ ብጤ ሰጠኝ ። እንጨት ያበፈልጠኝና ቂጣ ያስጋገረኝ ጀመር ። ገላ መታጠብ ፣ ልብስ መለወጥ የለም ። ማከክና መቅመል ጀመርኩ ። የቁም ሞት መሞት ነው ። ማንም ፣ ምንም የመሆን ስሜት በላያችን ላይ ግዶር ይጀምራል ።

«ካንድ ወር በኋላ ለወታደራዊ ሥልጠና ተወሰድኩ ። ወዲ ጽሩዕ እንደ ጥላዬ ይከተለኛል ። ወታደራዊው ሥልጠና ሞትን ያስመኛል ። የተወሰዱበትን ቀን ያስረግማል ። ያለውሀ ፣ ያለ እህል ከቦታ ቦታ ለማምንት ፣ ለሁለት ሣምንት ዝም ብሎ መጓዝ አለ ። በጸሐይ ፣ በዝናብ ፣ በጭለማ ፣ በቀን መጓዝ መጓዝ ፡፡ እየሄዳችሁ እንቅልፍ ወስዶአችሁ ያውቃል? እንቅልፍ ይዞኝ ብዙ መንገድ ብዙ ቀን የተጓዝኩበት ጊዜ አለ ።

«እና ጓደኞችህ ካጠገብህ ተለይተው ሲወድቁ ታያለህ ። አታነሳቸውም ። ራስክንም መሸከም አትችልም ። ለጅብ ጥለህቸው ትሔዳለህ ። ሞታቸው ያስቀናሃል ። ስለሞት ብቻ ነው የምታስበው ። ግን ነፍስህ አትወጣም ። ትተናንቅሀለች ።

«እና ከዚያ አንድ ቀን እሥረኞች ወደሚረሸኑበት ሥፍራ ትወሰዳለህ ። ራስህ ጉድጓዱን ትቆፍራለህ ። ራስህ ሰውዬውን እንጨት ላይ የፊጥኝ ታስራለህ ። እና ዓይኑን ትክ ብለህ እይ

ትባላለህ ። ታየዋለህ ። ግልግል ነው ሞት ይሻለዋል ትላለህ ። አንተም መሞት ነዋ የምትፈልገው ። ግን አትሞትም ። እና በባንጃ ውጋው ትባላለህ አሠልጣኞችህ ስሜትክን ለማየት ዓይን ዓይን ህን ይመለከቱሀል ። ይመዝኑሀል ። እና ዓይንህ እያየ የፈሞኝ የታ ሰረ ሰው ትገድላለህ ። አፈር ታለብሰዋለህ ። ሞት ምንም አይደለም ። ከዚያ ሰው አትሆንም በቃ! ለመኖር ትገድላለህ ። አይደለም ወዲ ጽሩዕ?» አለ ።

ነገሩን እያጋነነና በንቀናቄ እያስደገፈ ሲገልጽ ልክ የወጣ ለት የመድረክ ተዋናይ ይመስል ነበር ። ሁላችንም አፋችንን ከፍ ተን ነበር የምንሰማው ። ፊያሜታን ረሳኋት ሞት ይርሳኝ !

«ሌላ ቢራ በስፕራይት ላምጣልሽ?»
«ና ና!» አለች ጠጉሯን እየነሰነሰች ።

መጀመሪያ ስትመጣ ውብ ፊቷ ላይ ይታይ የነበረው ጥሩ ስሜት አሁን አይታይም ። የሆነ ሐሳብ የያዛት መሰላ ታየችኝ

ኩሉኔል በትሩ ተሰማ ዝም ብሎ ይስቃል ። የማይሰማ መስሎ ያያል ። ኩሉኔል ታሪኩ አሳብ ጉም ውስጥ ገብቶ የጠፋ ይመስላል ። ሰለሞን በትረ ጊዮርጊስ ጭውውቱ ስለጣመው ሳይሆን አይቀርም የመጣለትን የቴሌፎን ጥሪ ትቶ ዘግቶ ተመ ለሰ ።

«ለምን መጣህ?» ብሎ መጽሐፈ ዳንኤል ስዕላይን ጠየቀው ።

«ዋእ! ጥያቄው ለምን መጣህ? አይደለም ። እንኳን መጣህ ማለት ነበረብህ ። አይመስልህም ወንድም?»

«እንኳን በደህና መጣህ ። ግን ለምን መጣህ?» አለው መልሶ ።

«እንዴት? ለምን መጣህ? ብሎ ጥያቄ አይገባኝም»

«ማለቴ» አለ መጽሐፈ ፡ «የሻዕቢያ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል እና የሐለዋ ሰውራ ዋና ጸሐፊ ነበርክ ። የደቀመሐሪ አስተዳዳሪና የሻዕቢያ ደቡብ ዕዝ ኮሚሳርም ነበርክ ። ትልቅ ቦታ ነበረህ ። በምን ምክንያት ለመመለስ በቃህ? ለማለት ነው ።»

«እንደሱ በለኝ» ብሎ ጀመረ ፣ «እኔ ሻዕቢያን እንደ እናቴ ነበር የምወዳት በዚህ ። የተነሳ በቅንነትና በታማኝነት አገልግያ

ታለሁ ። ደምቼላታለሁ።ግን በመጨረሻ አንድ ነገር ተገነዘቤኩ ። ለአጉል ትምክህት ለጭፍን ዘረኛነት ፣ ለሥልጣንና ለርካሽ ጥቅም ካልሆነ በቀር የምንዋጋለትና የምንሞትለት ዓላማ ፍጹም የለንም ። እኛ ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልዩ ወይም የተሻለ የሚያደርገን አንድም ነገር የለም ። ስድሳ ዘመን በቅኝ ግዛት ሥር መኖራችን ሊያኮራን ወይም በሥልጣኔ የተሻልን ሰዎች ሊያደርገን አይችልም ። ከተሞችን ትተን ገጠሪቱን ኤርትራን ብንመለከት ፣ አርሶ አደሩ ሕዝብ ያው እንደሌላው የኢትዮጵያ አርሶ አደር ማይምና ኋላቀር ነው ። ልዩነታችን የቱ ላይ ነው፣ ታሪካችን? ታሪክን በቅጥፈት መጻፍ አይቻልም ። ኤርትራ ኢትዮጵያዊት አለመሆኗን ማንም ሊያስረዳ አይችልም ።

«እንግዲህ እስካሁን የተዋጋንለትን ዓላማ በምን ልናስረዳ እንችላለን? ጥያቄው እዚህ ላይ ነው ። ኢትዮጵያ ኤርትራን የቅኝ ግዛት አደረገች እንላለን ። ግን ይህን ለማለት ምንም ዓይነት መሠረት የለንም ። ይህን በተጨባጭ ለማስረዳትና ለማሳመን እስካልቻልን ድረስ ዓላማ አለን ማለት ዘበት ነው ።

«ይኸ ሻዕቢያ ናት ተራማጅ ፣ የለም ጀብሐ ነች ተራማጅ የምንለውን ነገር ተወው ። ዋጋ የለውም ። እሱ የማወናበጃና የመለመኛ አቁማዳ ነው ።

«የሻዕቢያና የጀብሐ ግጭት መነሻ አይዲዮሎጂ አይደለም ። ሆኖም አያውቅም ። ይህን በሚገባ አውቃለሁ ። ኖሬበታለሁ ። ሠርቼበታለሁ ። የቅራኔያቸው መነሻ ሀይማኖትና ጐሣ ደገኛና ቆለኛ ከሚል ይመነጫል ። መድረሻውም ይኸው ነው ። የዚህ ቅራኔ ውጤት ምን ነበር? የ1973 የእርስ በርስ አሰቃቂና አሳዛኝ ጦርነትና እልቂት ።

«ጎንደር ላይ ሆናችሁ ዝም ብላችሁ ብትመለከቱን እኮ እርስ በእርሳችን በካራ ስንጨራረስ ታዩ ነበር ። አባቴ ይሙት። የኤርትራ ነጻነት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እያልን የምንጮኸው እንዲያው በከንቱ ነው ። ለየትኛው ብሔረሰብ? ለሡራዬ? ለአከለጉዛይ? ለሐማሴን? ለባርካ? ለሣሕል? ለደንከል ዋጋ ቢስ ነው ።

«አሁን ወዳጄ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው ሰው ወይም እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ላይ የደረሰ ሰው በወንበዴዎች ድርጅት ውስጥ ሊኖር አይችልም ። አሳብህ ሥራህ ላይ ፣ ጠባይህ ላይ ፣ ድርጊትህ ላይ ማንጸባረቅ ይጀምራል ። አደገኛ ሁኔታ ላይ ትደርሳለህ? ልብህ እንዴ ከሸፈተ መሞት ወይም መሔድ ያስፈልጋል ። ግን ስለእግዜር ብላችሁ ወዶ ገባ አትበሉኝ!» አለ ወደኔ እያየ ።

«መቼ ነው'ኢንተርቪው የምትሰጠኝ?» ስል ጠየኩት ።
«ወዶ ገብ ካላልከኝ በፈለከው ጊዜ» አለኝ ።
«ነገ ለምን አይሆንም.....»
«ዝግጁ ነኝ» አለኝ ።

መጽሐፈ ዳንኤል ለጥቆ ፣ «ዓላማ የለንም አትበል ። ዓላማ አላችሁ ። ይኸውም ፣ ቀይ ባሕርን የዐረብ ሐይቅ የማድረግ የቆየ ዓላማ ነው ። የኤርትራ ችግር መንስኤ ይኸው ነው ። ሌላው ደግሞ ይህን የመሀል አገር አድጊ ሁሉ ልንገዛው ካልቻልን ፣ ለምን ከእሱ ተገንጥለን ራሳችንን እንገዛም ነው የምትሉት ። እድጊ! አይደለም የምትሉንን?» በማለት በሥልጣን ተናገረና ፣ «ለምን እንደተመለስክ ነገርከን ። እስቲ ደግሞ መጀመሪያውኑ እንዴት እንደወጣህ እጫውተን» አለው ።

«ሥራዬን ባትሻማኝ አሁን ምናለበት!» አልኩት ።

«ነገ አጣመህ ሳታቀርበው በፊት ከሱ ልስማ ብዬ ነው!» በማለት በነገር ቃሪያ ጥፊ መታች ።

«እኔ የወጣሁት ነፍሴን ለማዳን ወይም በረሀ ገብቼ ባይሆን እየተታኮስኩ ብሞት ይሻላል ብዬ ነው» በማለት ንግግሩን ጀመረ «እንደሌሎቹ የእናት አገር ጥሪ ተቀብሎ ወይም ነጻነት መጥቷል ብዬ ፣ ወይም ግን በተዋጋ ኋላ ግን ይንደላቀቃል በሚለው ቅስቀሳ አልነበረም ። ፍርሀት ነበር ወደ በረሀ ያስወጣኝ ። በዚያን ጊዜ ይካሔድ የነበረው ጭፍን ጭፍጨፋ ወጣት ኤርትራዊ ሁሉ ወንበዴ የሚመስላቸው ሰዎች ነበሩ ። ጓዳ ውስጥ ለምን ልገደል! እናንት ሰዎች እንዳንዴ የራሳችሁ ክፉ ጠላቶች ናችሁ» አለ ።

ስለሞን ነበር ቀጥሎ የተናገረው «አዎ ለጥቅማቸው ሲሉ ይህ አገር ዘላለም እንደደፈረሰ እንዲኖር የሚፈልጉ ሰዎች አይታ

ጡም ። አሁንም ይኖራሉ ። ለዝርፊያ ፣ ለጉቦ ፣ ለሴት ሲሉ ሽብር የሚፈጥሩ ሰዎች ነበሩ ። አሁንም ይኖራሉ ። አንዱ ትግላችን ከእን ደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ጋር ነው ።

«ሰው ያለስጋት አንገቱን ቀና አድርጐ እንዲሔድ ፣ እ..... በእኩልነት ሞላ ሥር ሕግና ፍትሕ አለልኝ ብሎ እንዲያምንና እንዲኖር ከቻልን ለተቀሩት ችግሮች መፍትሔ ማግኘት አያስ ቸግረንም ። እውነቴን ነው ። ዋናው ችግራችን የሰው ችግር ነው» ካለ በኋላ ፣ አንድ ጊዜ ስለደረሰ ችግር አንስቶ ያጫውተን ጀመር እንዲህ ሲል ።

«አንድ ባልና ሚስት ነበሩ ። እዚሁ ከተማ ። ሰውዬው ሀብታም ነጋዴ ነበር ። ሴትየዋ በጣም ቆንጆ ነበረች ። ታዲያ አሁን ስሙን ለመጥራት የማልፈልገው አንድ ባለሥልጣን ሴትዮዋን ይፈልጋ ታል ። እምቢ ትለዋለች ። በሥልጣኑ ተጠቅሞ ሰውዬውን በወ ንጀል ወስዶ ያሳስረዋል ። ከዚያም በኋላ ሴቲቱን ማስቸገር ይጀምራል ። አሁንም እምቢ ትለዋለች ። እንደማይሆንለት ሲያውቅ ፣ 50 ሺ ብር ከሰውዬው ጉቦ ተቀብሎ ይለቀዋል ። ይቆይና ነጋዴው ድንገት ያጋልጠኝ ይሆናል በማለት እንደገና ወስዶ ያሳስረዋል ። ከጥቂት ቀን በኋላ ነጋዴው የደረሰበት ይጠፋል ። ሴቲቱ ባሏን ለመፈለግ ያልደረሰችበት መሀኒ ቤት የለም ። ገንዘብ ስጭንና ባልሽ የት እንዳለ እናሳይሽ በማለት የሚያታልሏት ነበሩ ። ለዚህም ገንዘብ ፣ ለዚያም ገንዘብ ስትል ገንዘቧን ጨረሰች ። ከሰውነትም ወጣች ። አንዴ አጋዴን ግንባር ተልኳል ይሏታል ። ሌላ ጊዜ ደግሞ ሸፍቶ በረሀ ገብቷል ይሏታል ። አዲስ አበባ ዓለም በቃኝ ነው ይሏታል ። ሁሉም ቦታ ሔዳለች ። ባሏ ግን የትም አልነበረም ። በመጨረሻ እኔ ጋ ደረሰች ። ነገሩን አጣራሁና ባልሽ ሙቷል አዝናለሁ አልኳት ። የሚገርማችሁ እልል ብላ ጮኸች ። የደስታ አልነበረም እልል ያለችው ። እውነቱን በማወቋ ነው ። ልቅሶ ኃዘን መቀመጥ እችላለሁ? አለችኝ ። ትች ያልሽ አልኳት ። ተዝካር ላወጣ እችላለሁ? አለችኝ የፈለግሽውን ማድረግ ትችያለሽ አልኳት ። እና የእሷ ዓይነት ችግር ያላቸው ብዙዎች ነበሩ ። በዚህ የተነሳ አብዮቱን ማማረር ይቻላል? አይቻልም ። አንዳንድ ከሐዲዎችና ጥቅም አሳዳጆች በፈጠሩት ችግር አብዮቱን ማማረር ትክክል አይደለም ። ግን » ብሎ ንግግ ሩን ቀጠለና «ሰውም ጥፋተኛ ነው ። ያለምንም ፍርሀት መብቱን

ማስከበር አለበት ። ለፍትሕ መዛባት ፍርሀት መነሻ ነው ። እርግጥ ዛሬ ማንም ያለበቂ ማስረጃ ከቤቱ ተወስዶ አይታሰርም ። አይገደልም ። ያ ጊዜ አልፎአል ። ያኔም ቢሆን አንዳንድ ጥፋት ሊያስከትል የቻለው የእዝ ሰንሰለት መብዛት ነበር ። ዛሬ ኢሠፓእኮ ፣ ምናልባት ነገ ደግሞ የሠርቶ አደሩ ፓርቲ አንድ ወጥ የሆነ ማዕከላዊ አመራር በሚሰጥበት ሁኔታ በውዥንብር ውስጥ የሰው ሕይወትና ንብረት በከንቱ ሊጠፉ ፣ የሰው መብት በግፍ ሊገፈፍ አይችልም» አለ ።

«ተስፋ እናደርጋለን!» አለ መጽሐፈ ዳንኤል ወደኔ መለስ ብሎ

«ይህን ሰውዬ አላምነውም» አለኝ በጆሮዬ ።

«የቱን?»

«ይህን ወዶ ገብ....»

«ለምን?»

«እንጃ ። ግን አላምነውም.....»

«ተጠራጣሪ ተፈጥሮህ ይሆናል እንዲህ የሚያሰኝህ ። ሰውን ቀርቶ ጤንነትክንም ትጠራጠራለህ በነገራችን ላይ የደም ብዛትህ እንዴት ነው?» አልኩት ።

«ምሳ ላይ ሐጂ ተለከፍ ነበር.....»

«እና?»

«ሰማይ ወጥቷል»

«ለምን?»

«ተወኝ ጃል ። አንዳንድ ኩሉኔሎች ይህ አይቻልም ፣ ይኸ ኛው እንኳን በሶስት ቀን በሶስት ማምንትም ሊደርስ አይችልም ሲሏቸው እብድ የሚያክል ሽጉጥ አውጥተው ጠረጴዛ ላይ ራትህ ያደርጉና ፣ ምን አልክ? ይሉሀል ። እና ምን ታደርጋለህ! የደም ብዛትህ ሰማይ ይወጣል ። ይህ ዘመቻ ሳይገድለኝ ይቀራል ብለህ ነው? በቂ ጡረታ እንኳን የለኝም ....»

ሰዓቱ ደርሶ ስለነበር ሐጂ ቴሌቪዥን ከፈትኩ ። ዜና ተሰጠ ። ዜናው ስለጉርሻ አደጋ ፣ ስለአይሮፕላን አደጋና ስለ ልዩ ልዩ ስብሰባች ብቻ ነበር ። ስለ ዘመቻው የተሰጠ ምንም

ዜና አልነበረም ። የኔ ፕሮግራም ቀጠለ ። አንዳንድ አጉል ቦታ ላይ ከመቀራረጡ ሌላ መጥፎ ፕሮግራም አልነበረም ። በቅድሚያ ያመሰገነችኝ ፊያሜታ ጊላይ ነበረች ።

«ወደድሺው?» አልኳት
«እው በሥነ ሥርዓት» አለችኝ። አዎ ስትል ልክ እንደ ድመት 'ሚያው' የምትል ትመስላለች ። በሥነ ሥርዓት የሚል ቃል ከአፏ አይጠፋም ። ሥዕላይ ራት ብሉ ይመለከቱን ነበር ። የቃየል ዓይነት አመለካከቱ ደስ አላለኝም ።

ሰለሞን መጥቶ «ጥሩ ነበር ። የሠላም ዘምባባ ዛሬ የሚፈለገው የኤርትራን ችግር ባዲስ መንፈስ ባዲስ ዓይነት የማየት ጉዳይ ነው…» ብሎ የጀመረውን ንግግር ሳይጨርስ ፍትዊ ወዲ በርሄ ዘጭ ብሎ ሲወድቅ አይተን ወደ እሱ ሔድን ። መጠጡ ላዩ ላይ ፈሷል ። ብርጭቆው እንክሽክሹ ወጥቷል ። አልሞተም ጥምብዝ ብሎ ሰክሮ ነበር ።

መጽሐፈ ወደ ጆርጅ ጠጋ ብሎ «የጥፋተኛ ሕሊና ቅጣት ነው» አለኝ ። እሱም ሞቅ ብሎት ነበር ።

«እባክህ ጃል እንደ እሱ አትበል» አልኩት ።
«ለምን አልልም?»

«እነዚህ ሰዎች ያዩትን መከራና ያሳለፉትን ጭንቀት አንተ አታውቀውም ። ሊገባህም አይችልም ። አትፍረድ ። አንተ የዚህ አገር ተወላጅ ብትሆን ምን ልታደርግ ነበርክ? ጓደኞችህ በረሀ ወርደው እንደ ወንድ ሲሞቱ አንተ እናትህ ጉያ ተሸጉጠህ ወተ ቃግበል ነበር? ጥፋቱ ከዓላማው ላይ ነው» አልኩት ።

እባክህ ተወኝ አቦ! ትናንት ገና ነፍሰ ገዳዮች ነበሩ ። ለምን እንደምናምናቸው አይገባኝም ። በፊትም ቢሆን ተራማጆች ናቸው በማለት ዕድል ሰጥተን እንዲጠናከሩ ባናደርጋቸው ኑሮ እዚህ አይደርሱም ነበር…»

«እባክህ ዝም በል ጥርጣሬና ። ጥላቻ የትም አያደርሰንም ። እምነትና ተስፋ ማሳደር ይሻላል» አልኩት ።

መሽቶ ነበር ። ደክሞኛል ። መጠጡም ራሴ ላይ መውጣት ጀምሮአል ። ረጅም ቀን ነበር ። ስለሞንም ለመሔድ ሳይችኩል አልቀረም ። የምጽዋ ፌስቲቫል ኮሚቴ ይጠብቀዋል ። በመጀመሪያ ሊሔድ የተነሳው ኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ነበር ። ደስ ሳይለው ነበር ያመሸው ። አብዛኛውን ጊዜ መጠጡን ይዞ ሲተክዝ ነበር እንጂ ሲናገር አላየሁትም ። እዚያ እያለ እንዳልነበረ ያሀል ነበር ሁኔታው ። መጥቶ ሊሰናበተኝ ሲል ፥ «ታሪኩ ፥ መቼ እንገናኛለን? አሥመራ ያንተ ከተማ ናት ። አንዳንድ ቦታ እንድ ታሳየኝ እፈልጋለሁ» አልኩት ።

«ነገ መሔዴ ነው» አለኝ ።
«ወዴት?»
«ወደ እፍአበት»
«መች ትመለሳለህ?»
«ካልሞትኩ ፥ ከድል በኋላ» አለኝ ።
«አትሞትም ። ጀግና አይሞትም ። አፍአበት እንገናኝ ይሆናል ። ካንተ ጋር ናቅፋ ሳልደርስ አልመለስም ። ይቅናህ ፥ ቻው» አልኩትና በስሜት ጉንጭና ጉንጩን አገላብጨ ሳምኩት — ተንጠራርቼ ።
«አይዞህ ፥ ድል የኛ ነው ። እናሸንፋለን!» ብሎኝ እሱም እንንብሶ ሳመኝ ። እና ሔደ ።

ፊያሚታን ጠቀስኳት ሰሜናዊ አበባ ። ፈገግታዋ እንደ ጠፍ ጨረቃ ይማርካል ፥ ይጋብዛል ።

«እንደገና እንደምንገናኝ ተስፋ አለኝ» አልኳት ።
«በሥነ ሥርዓት ። አሥመራ ጠባብ ናት» አለችኝ ።
«ትግርኛ ከትምህርቲ ኢ......!»
«እሺ እምባርና ግን በቢላሽ አይደለም»
«የተጠየኩትን ዋጋ እከፍላለሁ.....»
«ደደብ ከሆንክስ?»
«እንዳንቺ ያለች አስተማሪ አግኝቼ አልደድብም» ስላት ሥዕላይ መጣ ።
«ነገ እሺ?» አልኩት ።
«ወዶ ገብ ካላልከኝ እሺ ነገ» አለኝ ።

ነገ ሌላ ረጅም ቀን ። ብዙ ረጅም ቀናት ። ጨረቃዋ ትጋብዘው ነበር ። እግሩ ይቀዘቅዛል ። አብዕላል በሚገናኝ ኮከብ……

ታስታውሰኛለህ? ካላስታወስከኝ ግድ የለም ። በመጀመሪያ ቃል ነበር ። ቃልም ደራሲ ነበር ። ደራሲም ቃል ነበር ። ጸጋዬ ተኝቷል ። ታሪኩ ግን ቀጥሏል ። ሕይወት አንድ ቦታ ላይ አት ቆምም…… ትቀጥላለች ፣ ያንዱን ሕይወት ከሌላው ጋር ድርና ማግ እያደረገች……

# የጎልያድ ንቀት
## የጎልያድ ውድቀት

ሰኞ ታኅሣሥ 19 ቀን 1974 ፋታ ከነሳቸው ግለሰቦች አንዱ ኰሎኔል በትሩ ተሰማ ነበር ። ከሰለሞን በትረ ግብዣ ወጥቶ በቀጥታ የሔደው ወደ ቢሮው ነበር ። አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው በቢሮው ውስጥ ነው ። አንዳንዴም እዚያው ውሎ ያድራል ። ቢሮው መቸም የቢሮ መልክ የለውም ። የሀብታም ሰው ሣሎን ነው የሚመስለው ። ከጥቁር ቆዳ የተሠራው ትልቅ ሶፋ ሁለት ሰዎች በምቾት ያስተኛል ። ኰሎኔል በትሩ ሶፋው ላይ በጀርባው ተንጋሎ ጣራ ጣራውን መመልከት ያዘወትራል — ጣራው ጭራ ሆኖ የጠላትን መምጫና መሔጃ ፣ መግቢያና መውጫ የሚያስነብበው ይመስል ። መታጠቢያ ቤት ገብቶ ጢሙን ሲላጭ የሚታየው በድሎት የሰጠለጠው ወፍራም ፣ ግን ደስ የሚል ፊቱ ሳይሆን አብዛኛውን ጊዜ የጠላት ሶትራተጂና ታክቲክ ነው ። ብዙውን ጊዜ ጢሙን ሲላጭ ፊቱን ይቆርጣል ። እና ይራገማል ። ጥሉበት የኤሌክትሪክ ጢም መላጫ አይወድም ። ተራ የጢም መላጫ መሣሪያና ጂሌት ምላጭ ደስ ይለዋል — ሽልት አድርጎ ስለሚላጭለት ።

ኰሎኔል በትሩ ቢሮው ሲደርስ መለዮ ለባሹም ሆነ ነጭ ለባሹ በተጠንቀቅ ተቀበለው ። መብራት የማይታይበት ወይም የተዘጋ ቢሮ አልነበረም ። እሱ ካላሰናበተ ግን እባቱ ቢሮውን ዘግቶ ይሔዳል! ሁሉም እየተራገመ ፣ እያዛጉ ፣ እያንቀላፉ ፣ ልባቸው እስኪፈርስ ድረስ ቡና እየጠጡ ፣ ሳምባቸው እስኪከስል ድረስ ሲጃራ እያጤሱ ፣ ዓይናቸው እስኪቃጠልና ጭንቅላታቸው እስኪግል ድረስ የዕለቱን ሪፖርት እየጻፉ ይቆዩታል ። ሁሉም ይጠሉታል ። ቀልድ አያውቅም ። ይሠራል ። ያሠራል ። ከሥራ ሌላ ሰው የሚመዝንበት ሌላ መለኪያ የለውም ። የሚሠራው ሰው ሁሉ ጓደኛው ነው።በሥራው መጠን ሰው ያቀርባል ፣ ያርቃል ። ታዲያ ሁሉም ይጥሉት እንጂ የማያከብረው ሰው የለም ። እሱም ቢሆን ከመወደድ ይልቅ መከበርን ይመርጣል ።

ረጂሙን መተላለፊያ (ኮሪደር) አቋርጦ ቢሮውን ከፍቶ ገባ ። መብራት አበራ ። የቢሮው ሽታ ደስ አላለውም ። በሩ ከውስጥ የሚዘጋውና የሚከፈተው በአውቶማቲክ ቁልፍ በመሆኑ ራሱ ተዘጋ ። በሩ ላይ ያለው ልዩ መስተዋት ከውስጥ ወደ ውጭ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ። ከውጭ ወደ ውስጥ ግን ድፍን ነው ። ወደ መታጠቢያ ቤት ሔደ ። ከእብነ በረድ የተሠራ ትልቅ ፣ የተንደላቀቀ መታጠቢያ ቤት ነው ። ሽንቱን ሸና ። ትከሻው አራት ማዕዘን ሆኖ ይታይ ነበር ። ፊቱን ተጣጥቦ ትንሽ አዶኮሎኝ ሲቀባ ሁሉ መስተዋቱ ውስጥ የሚታየው የራሱ መልክ አልነበረም ። ሥዕላይ በራኺ ነበር መስተዋቱ ውስጥ የሚታየው — ትናንሽ ዓይኖቹ — ብልጣ ብልጥ ስለታም ፊቱ — እንደ ስለት የሚቆርጠው ንቁ ጭንቅላቱ ። ኰሎኔል በትሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሱ ሁኔታ ተገረመ ። ከጠላት መልክና ሁኔታ ሌላ የራሱ መልክ በውል አልታይሀም እያለ ማስቸገር ከጀመረው ቆይቷል ። የሚታየው ነገር ሁሉ የጠላት መልክ በቻ ሆኗል — በራሱ መልክ ምትክ ። ምናልባት በዚህ ሥራ ላይ ብዙ ዘመን ስለቆየሁ ይሆናል ብሎ አሰበ ። በሕይወቱ ሌላ ሥራ ይዞ አያውቅም ። በ1949 ከዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በፖለቲካል ሣይንስ በዲግሪ ተመርቆ እንደወጣ የተቀጠረው በጸጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ውስጥ ነበር ። ራሱ ኰሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ነበር የቀጠረው ። ጎንደሬ ከመሆን ሌላ ስለ «ኢንተሊጀንስ» ሥራ ምንም ልምድ ወይም እውቀት አልነበረውም ። ግን ይኸውና በዚሁ ሥራ ላይ ያገኛል ። ሀሣቡ ሐያ አምስት ዘመን ወደኋላ አቋርጦ ጋለበ ። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ባከናወናቸው ቁም ነገሮች ወይም ባገኛቸው ድሎች ልቡ አላበጠም ። ጥልቅ የሆነ ባዶነት ተሰማው ። ባዶ ልብ ። ባዶ ነፍስ ። ባዶ ሕይወት ። አላገባም ። ልጅ አልወለደም — ለስሙ መጠሪያ ። ብቸኛ ፣ ብቸኛ — በዚህ ሠፊ ዓለም ውስጥ ። እና ዕድሜው ገፍቷል ። ከእንግዲህ ምን ሊቀረው— ጡረታና እንደ ቀትር ጥላ የኰበለለው ዕድሜው እናደደው ። በዘመኑ መጣት ባለሥልጣናት ዘንድ ያረጀ ቁና የሚያስመስለው ሽበቱ አስጠላው ። ሽበቱ ለስብእናው የለገሠው ግርማ ሞገስ አልታየውም ። ሽበት የተናቀበት ጊዜ! አለ ።

ባለፉት ሐያ አምስት ዓመታት ውስጥ ያካበተው የሥራ ልምድ የትም አላደረሰውም ። ከሐያ አምስቱ ዓመታት ውስጥ

ኦራቱን ዓመት ያሳለፈው በዓለም ቢታኝ ነበር ። የኰሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ሰው ነው ተብሎ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ተፈረደበት ። ያው እንደ ለመደው ቢሮው ተገኝቶ የመንግሥት ጠላት የህዝብ ጠላት ነው በሚል መርሆ የተለመደውን ሥራ ውን ከመሥራት በቀር በአነ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ውስጥ የተጫወተው ሚና አልነበረም ። ግን አልቀረለትም ። አራት ዓመት ከጠባ በኋላ በምኅረት ተለቆ ወደ ቀድሞ ሥራው እንዲመለስ ተደረገ ። ቢሆንም እምነት የሚጥልበት ባለሥልጣን አልነበረም ። በመሆኑም በሥራው ላይ ዕድገት ወይም ሹመት ሳይሰጠው እንዲሁ የተጣለ ቋና ሆኖ ቆየ ። ከዓመት ዓመት እሱ ሹመት እየታለፈ ፣ እሱ ያመለ ጠናቸው ሰዎች አለቃው እየሆኑ መቆየቱ ይህን ያህል የውስጥ እግር እሳት ሆኖ አያንገበግበውም ነበር ። ይልቅ ፣ ውስጥ ውስ ጡን እንደ ነቀዝ እየበላው በጣም ያንገበገበውና ያበሳጨው የነበረው ነገር እምነት ከማይጥልበት መንግሥት ጎን ተሠልፎ ፣ በሕዝቡም ዘንድ እንደ ሕዝብ ጠላት እየተቆጠረ ያለምንም ምርጫ ሲሠራ መቆየቱ ነበር ። ሥራውን ለመልቀቅ ጥረት ቢያ ደርግም ፣ የሚለቀው ባለሥልጣን አልነበረም ። የመንግሥትን ምስጢር ዐውቆ ወዴት! ኦይለቁት ነገር ምስጢር ያውቃል ፣ አይሾሙት ነገር አይታመንም ። እንዲሁ መታሸት ነበር ዕጣ ፈንታው ። የደም እንጀራ ።

የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ አብዮት ድንገት ከዳር እስከ ዳር እንደችቦ ተቀጣጥሎ ሕሊናወ በእፎይታ የሚተነፍስበት የተሰራ መሰኮት ባይከፍትለት ኖሮ የለየለት ሰካራም ሆኖ በቀረ ነበር ። ከ1966 ጀምሮ እልኮልና ሲጃራ የሚባሉትን ነገሮች ነክቶ ኦያውቅም ። እርም ብሎ ትቷቸዋል ። እንዴት እንደሆነ እሁን በውል ባያውቀውም ፣ ብቻ ፣ የአብዮቱ መቀጣጠልና የሠፊው ሕዝብ ሆ ብሎ መነሳት ካለፉት ወንጀሎቹ ሁሉ ነጻ ያደረገው መስሎ ታየው ። እና አብዮት በኢትዮጵያ ከተቀጣጠለ ወዲህ የሠፊው ሕዝብ ትግል አጋር እንጂ ጠላት ያለመሆን ጠንካራ እምነት ስላደረበት በሥራው ላይ እምነትና ተስፋ እየጣለ ሔደ ። የሠፊው ሕዝብ ጥቅምና ልዕልና ተቃራኒና ተጻራሪ ከሆነ መንግሥት ጎን ቆሞ እንደ ሕዝብ ጠላትና አፋኝ እየተቆጠረ ከመሥራት ራሱን በአልኮል ፣ በዝሙትና በሲጃራ በቀስታ ፣ ግን በእርግጥ ለመግደል ተዘጋጅቶ የነበረው ሰው ድን

ጎት የመንፈስ ተሐድሶ አግኝቶ ልቡ ያንሠራራ ጀመር ። ጠባዩ ፈጽሞ ተለወጠ ። «ለመደብ ጠላት ርኅራሄ ወይም ደግነት ማሳየት አሳፋሪ ድርጊት ነው ወይም እንደ ፍርሀት ተቆጥሮ ሊሳቅበት ይገባል ። ከመደብ ትግል በላይ ወይም ውጭ የሆነ ሕሊና ከቀሳውስት ውዳሴ ቃላት አይሻልም ። የስለላ ተግባር የጥሩ እርበኞች ግዳጅ ነው ። አብዮት ፍርድ ቤት ነው ያለው ማነው? የአብዮት ሠይፍ ምንም እንኳ አንዳንዴ ካንዳንድ ንጹሐን ሰዎች አንገት ላይ ቢወድቅም ፣ ጠላት ድል መመታት ይኖርበታል ። የቀረው ፣ ጠባብ አስተሳሰብ የተጠናወታቸው ምሁራን አጉል መነፋረቅ ይሆናል ። አብዮት የይምሰል ጉዳይ አይደለም ። ይሁን ብለን የምናመጣው ነገር አይደለም ። ራሱ ሲል የሚሆን ሂደት ነው ። ምነው ቢሉ ከኔ መልሱ ግልጽና አጭር ነው ። ምንም ይሰማን ምን ፣ ታሪክ ካፒታሊዝምን ተፍቶታል ። ካፒታሊዝም ጠፊ እንጂ ኗሪ አይደለም ። የሚጠወልግ እንጂ የሚያብብ ኑዩ ደለም ። የታሪክ ፍርድ ነው ። ስለዚህ ሶሻሊዝምን ማግረር ከንቱ ነው» ይላል።ታዲያ ይህ እምነቱ ከንባብ ያገኘው አይደለም፣ ከቀጥታ ልምድ እንጂ ። በመሆኑም ፣ ያለበቂ እውቀትና ልምድ አብዮቱን ለማገልገል በየቦታው የሚያሰፈስፉትንና የሚያደገድጉትን ሰዎች አጥብቆ ይጠላል — «ለአብዮቱ ከሚሰጡት ጥቅም አብዮቱ ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ብዙውን ጊዜ አመዝኖ ይገኛል» በማለት ። በአብዮት ባቡር ለመጓዝ የሚፈልጉ ሰዎች እቤት መብዛታቸው? ግን ስንቶቹ ናቸው አብዮቱን በሐቅ ለማገልገል ባቡሩ ላይ የሚወጡት? በጅምላ ተሳፋሪዎች ምክንያት ስንት ጉዳት ፣ ስንት ጥፋት ደረሰ? ስንት ነገር ተናጋ? ስንት ቤት ፈረሰ? ስንት ሕይወት በከንቱ ጠፋ? በእንደዚህ ያሉ ሰዎች ምክንያት ሶሻሊዝም በብዙ ሰዎች ዘንድ መጠላቱና መወገዙ አሳዘነው ። እና አሁን ደግሞ የቀይ ኮከብ ዘመቻ ። ስንት አወናባጅ ፣ ስንት እሾም እሸለም ባይ ፣ ስንት አትራፊ ነጋዴ መጥቶ ይሆን? የያንዳንዱን ሰው ሕይወት ታሪክ የሚመለከት የመረጃ ሥራ (ባአግራፊካል ኢንተሊጀንስ) ተሟልቶ ያለመኖር ነገር አናደደው ። በሁሉም ነገር የነሲብ ሥራ! አለና የእጅ ሰዓቱን ተመለከተ ። ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኖ ነበር ። ተናዶ ከመታጠቢያ ቤቱ ወጣ ።

አንዱ ግድግዳ ላይ በተርታ ተሰቅለው ከሚታዩት ልዩ ልዩ ካሊቨር ሽጉጦች ውስጥ አንዱን አውርዶ በማይታይ ኢላማ

ላይ እንጣጠረ ። የአእምሮው ዓይን ሥዕላይ በራኺን ይመለከት ነበር ። ረዘም ላለ ጊዜ ዝም ብሎ ሲያንጣጥር ከቆየ በኋላ ሽጉጡን ከነበረበት ቦታ ላይ መልሶ ሰቀለው። ልዩ ልዩ መሣሪያዎች መሰብሰብ ፣ መፍታትና መገጣጠም ፣ ብቻውን ቁጭ ብሎ በሌላ ኢላማ ላይ ማንጣጠር ያዘወትራል ። ያዝናናዋል ። ሌላ የሚዝናናበት ነገር ቢኖር ቢሮው ወይም ቤቱ ብቻውን ቁጭ ብሎ «ሶሊቴር» መጫወት ነበር ። እንደ ናፖሊዮን ቦናፓርት የጀመረውን «የሶሊቴር» ጨዋታ ካልጨረሰ ምን ጦር ቢፈታ ፣ መሬትና ሰማይ ተንዶ ዓለም ምን ቢደበላለቅ ንቅንቅ ወይም ፍንክች አይልም ።

የቅርብ ረዳቶቹ በሩ ላይ ተደርድረው በማየቱ ጠረጴዛው ላይ የነበረውን ቁልፍ በሌባ ጣቱ ጫን አለው ። በሩ ተከፈተ ። አራት ወጣቶች ተከታትለው ገቡ ። የሁሉም ዓይን ቀልቷል ። ሲቆፍሩት የቆዩ ይመስል የሁሉም ጠጉር ተንጨፍርሮ ይታያል ። ፊታቸው በድካም ነብዟል ። ያሰሩት ክራቫት ወዲህና ወዲያ ተጣሟል ። ጠቆር ያለው ወጣት በጣም አጭር ነው ። ሲያዩት በጣም ኩሩ ይመስላል ። ጠይሙ ወጣት አጭርም ረጅምም የሚባል ሰው አይደለም ። ዓይናፋር ብጤ ነው ። የተቀሩት ሁለት ወጣቶች በቁመት ዘለግ ያሉ ሆነው ከዓይን የሚቀድሙ ያራዳ ሎሌዎች ይመስላሉ ። ቀያዮች ናቸው ። አንደኛው ጥቁር የጸሐይ መነጽር አድርጓል ። አራቱም መልከ መልካም ፣ ሸጠ ወጣቶች ናቸው ። ኰሎኔል በትሩ ተሰማ አራቱንም ተራ በተራ አይቶ ፊታቸው ላይ የሚታየውን ድካም ካጤነ በኋላ በልቡ አዘነላቸው ። ለምንድን ነው እነዚህን ልጆች እንደ አህያ የማሠራቸው? በማለት ራሱን ሳይጠይቅ አልቀረም ። መልሱንም አላጣውም ። የተጣለበት የቀይ ኮከብ ዘመቻ የሕዝብ ደህንነትን ጥበቃ ኃላፊነት ምናልባት ከፍተኛውና የመጨረሻው ግዳጁ ከመሆኑም በላይ ላለፉት ሐያ አምስት ዓመታት ያካበተው ልምድና እውቀት እንደ ወርቅ በእሳት ተፈትኖ ጥራቱ የሚታይበት ሥራ መሆኑን ያውቃል ። ለኢዮቤልዩ በዓሉ ለራሱ ያሰበው ልዩ ስጦታ ፣ እና ውድቀትም ሆነ ልማቱ በእነዚህ ልጆች ትከሻ ፣ ጥረትና ትጋት ላይ ያረፈ እንደመሆኑ መጠን ቀንና ሌት እንደ ባሪያ ከማሠራት ሌላ ምርጫ አልነበረውም ። እነዚህን ልጆች እንደ ባሪያ የሚያሠራበት ሌላም ስውር ምክንያት ነበረው ። ዳግመኛ ሲያስብ ፣ ሲያያቸው ያደረበትን ርኅራኄ ከልቡ አውጥቶ፣ ምናባታቸውንስና ይሥሩ! ከሥልጣን ጉጉት በፊት ሥራ መቅደም

እለበት ። እኔ ሐያ አምስት ዓመት አገልግዬ የት ደረስኩ? እህያ የተሟነችውን አትበላም እንዲሉ፣ ዘለዓለሟን ሥራ ተጭኖ ዳገት ከመውጣትና ቁልቁለት ከመውረድ በስተቀር ። የታባታቸው ይሥሩ! ትናንት ከትምህርት ቤት ወጥቶ ዛሬ ሥልጣን ላይ ቂጥ ማለት የለም! በማለት ሲያስብ ቆየና ርኅራኄና ጥላቻ በተቀላቀለ በት ስሜት፣ «የዕለቱን ሪፖርት መስጠት እፈልጋለሁ ። ባጭሩ ። ዝብዝብ አልፈልግም ። ጊዜው መሽቷል» አላቸው ።

«እዎ» አለ ሻለቃ ተኽላይ ዘድንግል ጥቁር መነጽሩን ስልካካ አፍንጫው ላይ እያስተካከለ — «ጊዜው መሽቷል ። ለሰዓት አሳሬ 50 ደቂቃ ብቻ ነው የቀረው ።»

የሥራ ጓደኞቹ ሻለቃ ተክላይ ዘድንግልን ጀምስ ቦንድ እያሉ ነው በቅጽል ስሙ የሚጠሩት ። ቆንጆ ሴቶች፣ ጥሩ መጠጥ፣ ምርጥ ልብስና ጨዋታ ይወዳል ። በዚያ ላይ ቁመቱ ዘለግ ያለ፣ ቀጭን፣ በጣም መልከ መልካም ወጣት ነው ። ሴቶች ይሞቁለታል ። አብዛኛውን ጊዜ የመረጃ ምንጮቹ ሴቶች ናቸው ። መረጃ ማግኘት ይሆንለታል ። እሱም ከሴት ጉያ ምን ምስጢር ይታጣል የሚል ፈሊጥ አለው ። እና ከሴቶች ጉያ ምስጢር ሲቆፍር ይውላል፣ ያመሻል ። ይጠጣል ። ይጫወታል ። አደገኛ የመረጃ ሰው ፈጽሞ አይመስልም ። ሥራውን እንደ ቀልድ ነው የሚመለከተው ። ነገሩ የምር ከሆነ ያመራል ። ልዝብ፣ የዋህና ተጫዋች መስሎ የሚታየው ሰው ባንድ ጊዜ እውሬ ይሆናል ። በደፋርነቱ በሥራ ጓደኞቹ ዘንድ የታወቀና የተከበረ ሰው ነው ። የሥራ ጓደኞቹ ሁሉ በለጋስነቱ ይወዱታል ። ከኪሱ ቢያጣ ተበድሮ ያጠጣል ። ለነገ የሚለው ነገር የለውም ። ኰሎኔል በትሩ ተሰማ ተክላይ ዘድንግልን በሥራው የሚወደው ቢሆንም፣ ሥራውን የሚያከናውነው በቂም በቀል ስሜት ይሆናል ብሎ ስለሚያምን ቅር ይሰኝበታል፣ አብዛኛውን ጊዜ ውጣኒውንና ግምቱን ይጠረጥራል ። የተክላይ ታናሽ ወንድም አሥመራ አደ ባባይ ላይ በጥይት ተደብድቦ በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደለው በሻ ዕቢያ ፈዳይት ነበር ። ከእሱ ሌላ ወንድም አልነበረውም ። ታናሽ ወንድሙን በጣም ይወደው ነበር ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነበር ከተገንጣዮች ጋር የግል ጦርነት የከፈተው ።

ኰሎኔል በትሩ የወትሮ ፈገግታውን እያሳየው ፣ «ታዲያ ምናለ፣ በጊዜ ትተኛለህ ማለት ነው» አለው ።

«ጓድ ኰሎኔል» አለ ተከላይ — «ሰው'ኮ ለእንቅልፍ ብቻ አይደለም የተፈጠረው ።»

«ታዲያ ለቅብጠት ነው?»

ሁሉም ሳቁ ።

«እሱም የሕይወት አንዱ ፈርጅ ነው ። ምስጢር የት የሚገኝ ይመስሎታል፣ በሴቶች ጉያ»

ሁሉም እንደገና ሳቁ ።

«ማን አይመስሎትም?» አለ ተከላይ ።

«እዎ የሚያደርስውም ጥፋት ያንኑ ያህል ነው ። አንድ ቀን እዚያው ተቀብረህ እንዳትቀር እሰጋለሁ ። ሴቶች አደገኞች ናቸው ። በኛ ሥራ የለም ። ጭኗን የከፈተችልህ ሴት ሁሉ ልቧን የምትሰጥህ አይምሰልህ ። ይልቅ ጭኗን ሰጥታህ ልብህን ነው የምትሠርቅህ» አለው ኰሎኔል በትሩ ። በዚሁ አሳቡን አልገታም ። ቀጥሎም ፣ «ባሁኑ ወቅት ለእንቅልፍ የሚያስቸኩለን ነገር የለም ። በዚች ሰዓት በሊቀመንበሩ ቢሮ ምን መካሔድ ላይ እንዳለ ታውቃላችሁ፣ የስታፍ ስብሰባ እየተካሔደ ነው ። ምናልባት እስከጧት ሳይቀጥል አይቀርም ። ላለፉት ሰባት ዓመታት በቀበሮ ጉድጓድ የኖረው ወታደር ለእንቅልፍ እልቸ ኮለም ። በጊዜ እንቅልፍ ተኝቶ ማለዳ ጧት ለሥልጣን የመሰለፍ ነገር አይገባኝም» አለ ።

ቀጥሎ የተናገረው ሻለቃ ሥዩም ሠረቀብርሀን ነበር ።

«ባሳብዎ አልስማማም ጓድ ኰሎኔል» አለ ።

ሻለቃ ሥዩም ሁልጊዜ በሰው አሳብ አይስማማም ። ጥቁር ሆኖ አጭር ነው ። ሴታ ቢት መልክ አለው ። ጥርሶቹ በጣም ያምራሉ ።

«በየትኛው» አለው ኰሎኔል በትሩ ።

«ሴቶቻችን በመረጃ ሥራ ለምንም አይረቡም ።»

«እንዴት?»

«እርስዎ እንዳሉት ሳይሆን ጭናቸውን ለከፈላቸው ወንድ ሁሉ ነው ልባቸውንም ጭምር የሚሰጡት ። ክቡር ሰውነታቸውን ከመቸርቸር አልፈው ያገር ምስጢር ይሸጣሉ ። ለጌጣጌጥ እንጂ ላገር ደንታ የላቸውም ። በእነሱስ አልታደልንም» አለ ።

ኩሉኔል በትሩ የእጅ ሰዓቱን ተመለከተ ። በክርክር ጊዜውን ለማባከን የፈለገ አይመስልም ። እና ደግሞ ሻለቃ ሥዩም ሁልጊዜ ይበረብረዋል ። ወጣቱ የመረጃ መኮንን በሥራው በጣም ብቁ ቢሆንም ፤ ለሥልጣን በጣም ችኩል መሆኑን ኩሉኔል በትሩ ያውቃል ። በጉቦም ይጠራጠረዋል ። ሻለቃ ሥዩም ገንዘብ ፈጽሞ አይበቃውም ። ደመወዝ ካገኘ ባምስት ወይም ግፋ ቢል በአሥር ቀን ውስጥ ገንዘብ ኪሱ አይገኝም ። ተረፈውን ሐያ ወይም ሐያ አምስት ቀን እንዴት እንደሚያሳልፍ ኩሉኔል ሁልጊዜ ይገርመዋል ። ሆኖም እስካሁን በጉቦ ይዞት አያውቅም ። ግን አንድ ቀን.... አሰና በልቡ ፤ «ታዲያ የሚሸጡትን ምስጢር ከየት ያገኙታል ብለህ ታስባለህ?» ብሎ ሻለቃ ሥዩምን ጠየቀው ።

«ምናልባት በወንዶች ይሆናል ፤ አላውቅም» የሚል መልስ ሰጠው ።

«ምናልባት አትበል ። ምስጢር የሚያገኙት መቶ በመቶ ከወንዶች ነው ። ከውሽሞቻቸው ፤ ከባሎቻቸው ከወንድ ጓደኞቻቸው ። ወንድ ሴትን የማመን ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ አለው ።

«አዳምን ያሳሳተችው ሔዋን መሆኗን አትርሳ ። ውበት አደገኛና አሳሳች ነገር ነው ። አየህ ፤ አንድ ወንድ ጓደኛ ሳይኖረው ይችላል ። ግን ምንጊዜም ቢሆን አንድ ሴት ከጎኑ አትጠፋም ። ያች ሴት ልታጠፋውም ፤ ልታለማውም ትችላለች ። በታሪክ ብዙ ታላላቅ ሰዎች ሊወድቁም ፤ ሊነሱም የቻሉት አብዛኛውን ጊዜ በሴቶች ምክንያት ነው ።

«እንግዲህ ሴቶች ለኛ ሥራ በጣም አስፈላጊ ናቸው ። የታላላቅ መንግሥታት የስለላ ድርጅቶች ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሙት በሴቶች ነው ። ሴቶችን ከማግባር ይልቅ ማሠልጠኑ ይበጀን ነበር ። በቋንቋና በብልጠት እንኳ የሚስተካከላቸው የለም ። በነገራችን ላይ «ሴክስ ኤስፒዮናዥ» የሚለውን መጽሐፍ

አንብባችኋል ? በተለይ አንተ» አለ ወደ ተከላይ ዘድንግል እየ ተመለከተ ።

ሻለቃ ሥዩም ሠረቀ ብርሀን እየተጣደፈ ማስታወሻ ይወ ስድ ነበር ። ኰሎኔል በነገር ሊነካው ፈለገና ፥ «ጓድ ሥዩም አይዞህ አትቸገር ። ጥናቱ በቅድሚያ ለበላይ ባለሥልጣን ቀር ቧል ። በቅርቡ ሴቶችን የምናሠለጥንበት ትምህርት ቤት ይቋ ቋማል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ። እና ጓድ ተከላይ በምልመላው ሥራ ትረዳን ይሆናል ። አሁን ሥራችንን እንቀጥል ። ከማን እንጀምር?» አለና የእጅ ሰዓቱን ፈትቶ አፊቱ አኖረ ።

ሁሉም የኰሎኔል ሽሙጥ ገብቷቸው አቀረቀሩ ። ሥዩም የሰዎችን አሳብ ነጥቆ የራሱ በማስመሰል በሪፖርት መልክ ለበላይ ቶሎ የማቅረብ መጥፎ ልማድ አለበት ። በዚህም ላይ እኛ በሠራነው ሌላው ይሞገስበታል ፥ ይከበርበታል ፥ ይሾምበ ታል በማለት ሁልጊዜ ጉራ ይነዛል ። ተከላይ ቶሎ ብሎ እጁን አወጣ ።

« ኖ ኖ ። ያንተ ሪፖርት ለኋላ ይቆይ ። እስቲ ከሕዝባውያንና ከመንግሥት ድርጅቶች ደኅንነት ጥበቃ እንጀምር ። አይመስ ላችሁም? እህስ ጓድ የሙቶ አለቃ አሸብር?» አለ ።

አሸብር አሳት የላሰ ፈጣን ወጣት ነው ። መልኩ ቀይ ፥ ዓይ ኖቹ ቀያይ ፥ ቁመቱ ዘለግ ያለ ፥ ሽመል የመሰለ ሎጋ ወጣት ነው ። ሲፈጥን ከዓይን ይቀድማል ። ንፉስ ነው ። ጭራው አይ ያዝም ። እንደ ጥላ ውልብ ብሎ ይጠፋል ። አሁን እዚያ ታይቶ በዚያው ሰዓት ሌላ ቦታ ይታያል ። ሲጃራ አያጤስም ። መጠጥ አይጠጣም ። ገንዘቡን ምን ላይ እንደሚያውል የሚያውቅ የለም ። አይጋብዝም ። አይጋበዝም ። እጅግ ሲበዛ ተጠራጣሪ ነው ። የገዛ ጥላውን ይጠራጠራል ። ያለመረጃ ሌላ ነገር አይታየውም ፥ ቁራጭ ወረቀት ረግጦ ኢያልፍም ። እንስቶ ያገላብጣታል ። ሰው የተናገረውን ነገር ሁሉ ያሰላስላል ፥ ይመረምራል ፥ ምን ማለቱ ይሆን? በማለት ይተነትናል ። ሰዎች ይህን ዝንባሌውን ስለሚያው ቁበት ከእሱ ጋር ጭውውት አይወዱም ። ከሩቅ ይሸሹታል ። ሌላ የጊዜ ማሳለፊያ የለውም ። ብቻ በምድጃ ዳር ያደገ ይመስል ሲ መሽ እሳት አንድዶ እሳቱ ሲንቀለቀል ማየት ይወዳል ይባላል —

በተለይም ፍሙን ። ጓደኞቹ «አሳቱ» የሚሉት አለምክንያት አይደለም ። ግን እሳት የሚሰጠውን ትርጉም የሚያውቅ የለም ። እሱም አይናገርም ። አ/ሥመራ ከመጣ ወዲህ እሳት አይቶ አያውቅም ። እንጨት የለም ። ከሮምቦላ በመጫወት ጊዜውን ማሳለፍ ጀምሮአል ። ታዲያ ማዕዘን መርጦ ድንጋይ የመጣል ነገር አይደለም የሚያስደስተው ። ማተራመስ ደስ ይለዋል ። ድንጋይ በድንጋይ ተጋጭቶ ፣ ድንጋይ ሲበተን — ሲተራመስ ማየት ነው የሚያስደስተው ። ስለሆነም ማንም ከእሱ ጋር ከሮምቦላ መጫወት አይፈልግም ። ኰሎኔል ይወደዋል — በፍጥነቱ ፣ በድፍረቱ ፣ በጭካኔው ። ጨካኝ ነው ። ምጎረት የለውም ። በኰሎኔል መመዘኛ መሠረት ጥሩ የመረጃ ሰው የሚባለው ፣ ፈጣን ፣ ደፋር ፣ ጨካኝ ፣ ብልጥ እና የማይጠጣ እንደአሸብር ያለ ሰው ነው ። ቅር የሚሰኝበት ነገር ቢኖር ተናዳጅ በመሆኑና መረጃዎችን በሚገባ መዝና ለማወቅ ገና ባለመቻሉ ብቻ ነው ። ይህን ድንጉላ በደንብ የሚገርፈው ቢገኝ» ብሎ «እህሳ አሸብር?» አለው ።

አሸብር ሲናገር ትንሽ ይከላተፋል — «ባጠቃላይ በሕዝባውያን ድርጅቶችና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያለው ጥበቃ ተጠናክሮአል ። በጣም በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል ።» ብሎ ሪፖርቱን ቀጠለ — «ግን ሕዝቡን ለማሸበርና ዘመቻውን ካሁኑ ተስፋ ለማስቆረጥ አንድ የሆነ ፋብሪካ ወይም አየር ማረፊያውን ለመምታት አንድ ዝግጅት አድርገዋል የሚል መረጃ አለ....» ሲል —

ኰሎኔል በትሩ ንግግሩን አቋረጠውና ፣ «የመረጃው ምንጭ ምንድን ነው? ወይስ እንዲሁ በነሲብ የተደረሰበት መረጃ ነው? ለነሲብ ሥራ ቦታ የለንም ተጨባጭ ነገር ነው እንጂ የነሲብ ጥቆማ አይደለም» አለው ።

አሸብር በንዴት ጠጉሩን ነጨና ፣ «የነሲብ ሥራ አይደለም ። ዛሬ በዚች ከተማ ያልረገጥኩት ቦታ የለም ። በጸሎት በኩል ላውንቸር የያዙ ጥቂት ወንበዴዎች መታየታቸውን ካንድ ፃበሬ አረጋግጫለሁ ። አላማቸው ምን 1 የቱ? እንደሆነ ለማወቅ አልቻልኩም ። ግን አንድ ፋብሪካ ወይም አየር ማረፊያው ይሆናል ብዬ እገምታለሁ» አለው ።

ኰሎኔል በትሩ እንደ ፈረስ እናፋና ሰልኩን አንስቶ ደወለ ። ቴሌፎኑን የሚያነሳ ሰው እስኪገኝ ድረስ በጣቶቹ ጠረጴዛውን ይቆረቁር ነበር ።

«ሀሎ?! ማን ልበል?» አለ ጠረጴዛውን መቆርቆሩን አቁሞ ።
«አፕሬሽን መምሪያ.....?
«እኮ ማን ልበል?»
«ኰሎኔል ዓለማየሁ.....»
«አ ኰሎኔል ዓለማየሁ ። ኰሎኔል በትሩ ነኝ ። በትሩ ተሰማ»
«ምነው ድምጽህ ጐረናብኝ?»
«በድካም ይሆናል ።»

«ገና ምን ተይዞ! ብዙ ይቀረናል ። ስማ ኰሎኔል ዓለማየሁ ። ወንበዴዎች እኛን ለማደናገጥና ሕዝቡንም ለማሸበር አንድ ያቀዱት ተንኮል እንዳለ በመረጃ ደርሰንበታል ። ካሁኗ ደቂቃ ጀምሮ በጸሎት ፥ በጎዳይፍኛ በሰምበል በኩል ያሉት የጸጥታ ኃይሎች የጥበቃ ክልላቸውን በጣም ማስፋት ይኖርባቸዋል ። ላውንቸር ይዘዋል የሚል ግምት አለ ። ኋላ ኃላፊነቱ ከንተና ከኔ ራስ አይወርድም ። ገብቶሀል? ርእሰ ብሔሩ እዚህ ተቀምጠ ወንበዴዎች እዚህ ከተማ ውስጥ አንድ ነገር ቢያደርጉ ኋላ ምን ይባላል? እኔ በጣም የሚያሰጋኝ ድርጊቱ የሚያስከትለው የፖለቲካ ጉዳት ነው ። ስማ ዓለማየሁ ። ውለታ አይደለም የምጠይቅህ ። አድርግ ነው የምልህ..... አሁን!» ብሎ ቴሌፎኑን ዘጋና ወደ አሸብር እየተመለከተ ፥ «ሌላስ?» አለው ።

ያመጣው መረጃ እንደሌላ ጊዜ ተንቆ ወደ ጎን ሳይጣል ባስቸኳይ እጥቅም ላይ እንዲውል በመደረጉ አሸብር ውስጥ ውስጡን እየተደሰተ ፥ «ሌላው የከተማው ሕዝብ የመረበሽ ጉዳይ ነው ። ሕዝቡ አንድ ነገር ይሆናል በማለት በጊዜ ከቷል ። መንገዱ ሁሉ ባዶ ሆኗል ። ውስጥ ውስጡን ሕዝቡን የሚቀሰቅሱ የወንበዴዎች ደጋፊዎች አሉ ። ግን ምንጩን ልደርስበት አልቻልኩም ። እሁል ከገበያ ጠፍቷል ። ዋጋ ንሮአል ። ሕዝቡ ተር ቧል ። አደገኛ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው ። ሕዝቡ እልቂት ሊመጣ ነው ብሎ በጣም ሰግቷል ፥ ፈርቶአል» ካለ በኋላ ማስታወሻውን ገለበጠና ፥ «በሁለት ቀበሌዎች ስድስት የቀበሌ ተመራጮች

ዛሬ ጠፍተዋል» ብሎ የከፍተኞቹን ፣ የቀበሌዎቹን ቁጥሮችና የጠፉትን ሰዎች ስሞች ነገረው ።

ኰሎኔል በትሩ ማስታወሻ ሲወስድ ቆየና ፣ «ስለሰው መሸበር ፣ ስለ እህል መጥፋትና ዋጋ መናር ጸጋዬ ኃይለማርያም በቴሌቪዥን ጥሩ አድርጎ አቅርቦታል ። ሕዝቡን የማረጋጋት ተግባር የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊነት ነው ። ብዙ ገና ብዙ የሚሠራ አለ ። እንዲህ ዓይነቱን መረጃ እያጠናከርን ለፖለቲካ መምሪያ ብንሰጥ ይጠቅማል ። ያደባባይ ምስጢር ምስጢርነት የለውም ።

«በኛም በኩል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ፣ ጓዶች ። ያለበቂ ማስረጃ ሰዎችን መያዝ ፣ ማሰር ፣ ለጥያቄ መጥራት የለብንም ። ከዚህ አድራጎት የበለጠ ሰዎችን የሚያስበረግግ ነገር የለም ። በጣም መጠንቀቅ አለብን ። መብቱ ተደፈረ ፣ ነጻነቴ ተነካ የሚል ሰው ከበዛ ሥራችን አይቃናም ። ተባባሪም አናገኝም ። የዚህን ክፍለ ሀገር ሕዝብ አውቀዋለሁ ። መሐሉ ኖሬአለሁ ። ሠራተኛ ነው ። ሠላም ፈላጊ ነው ። ወሬ አታመልጠውም ። ይጠራጠራል ። እና ደግሞ ቶሎ ይበረግጋል ። በ1967 በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች በርግገው ጫካ የገቡት በወንበዴዎች ጥሪ ፣ ወይም አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ፣ ነጻነት ተቃርቧልና ወጣ ብለን አብረን ከበሮ እየመታን እንግባ በማለት ብቻ አይደለም ። አብዛኞዎቹ ከፍርሀት የተነሳ ነበር የወጡት ። ለደረ ሰው ሁኔታ በከፊል ልንወቀስ ይገባል ። ፍርሀትና ሽብር በልባቸው ስንለቅባቸው ምን ያድርጉ? ጅምላ ፍርድ ፣ ጅምላ እሥራት ፣ ጅምላ ግድያ ከሆነ ሰዎች ሕይወታቸውን ለማዳን መሮጥ አለባቸው ። ቀንደኛ ወንበዴ ካልሆነ በቀር ፣ ለሕይወቱ ፣ ለመብቱና ለነጻነቱ ዋስትና ያለው ሰው ተነስቶ በረሀ አይገባም ። እብድ አይደለም ። ያኔ ሽብርና ጥላቻ የፈጠሩት አብዮቱን የረዱ የሚመስላቸው አንዳንድ ጨቅላ ካድሬዎች ነበሩ ። አንዳንድ ሆዳም ጉቦኞችም ነበሩ ። ሆን ብለው ችግሩን በማባባስ ለአድኃሪ ዓላማቸው አብዮቱን ለማጥላላት ሰውር ተንኮል የሚሸርቡም ግለሰቦች ነበሩ ። አሁን ያ ጊዜ አልፎአል ። እንጠራጠር ። መጠራጠር የሙያችን አካል ነው ። ጨካኝም እንሁን ። ወንበዴ ያለጭካኔ ሌላ ቋንቋ አያውቅም ። ግን ለምናደርገው ነገር ሁሉ እርግጠኞች እንሁን ። በአብዮታዊ ስሜት መንደድ ፣ መቃጠል ብቻውን

አይበቃም ። ፍላጐት ብቻውን የትም አያደርስም ። ጥበብና ዘዴ ሊታከልበት ይገባል ። ንግግር አበዛሁ መሰለኝ» አለና ሰዓቱን ከተመለከተ በኋላ ፣ «ቢሆንም ካለፈው ስህተታችን መማር አለብን ። ካለፈው ስህተቱ የማይማር አብዮት አብዮት አይደ ለም» ብሎ ንግግሩን በመቀጠል «በ1966 አብዮት ሲፈነዳ የሻዕቢያ ኃይል ምን ያህል እንደነበረ ታውቃላችሁ? ከ450 አይበልጥም ነበር ይባላል ። ከ1967 እስከ 1969 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ከ8000 እስከ 10,000 የሚሆኑ ሰዎች ወደ ሻዕቢያ የገቡ መሆናቸው ይነገራል ። ለምን? ብዙ ምክንያቶች ነበሩ ። ዋና ዋናዎቹን ብቻ ከብዙ በጥቂቱ መጥቀስ ይበቃል ።

«ተጋደልቲ» ዛሬ ፣ ነገ ይገባሉ የሚለው ሥነ ልቦናዊ ሁኔታ ራሱ አስገዳጅ ነበር ። ማን ባወጣው ድል ማን ተንደላቆ ይኖራል? — የጊዜው ጥያቄ ነበር ። በማን? ወይም በምን ተመክቼ እቀራለሁ? — ሌላው ጥያቄ ። የድል አጥቢያ አርበኛ በዛ ። የሻዕቢያ ኃይል አበጠ ። ግን ፣ የድል አጥቢያ አርበኞችን ቁጥር ያበዛው ፣ ተገንጣዮች በከፍለ ሀገሩ የተቀዳጁት የበላይነት ወይም የሚያካሂዱት ፕሮፓጋንዳ ብቻ ሳይሆን ፣ ለአብዮቱ ቆመናል የሚሉት የአንዳንድ ግለሰቦችና እነዚህ ግለሰቦች አመራር የሚሰጧቸው መሥሪያ ቤቶች ያደረሱት ጥፋትም ጭምር ነበር ።

«የሕዝቡን ደኅንነት ለመጠበቅና መንግሥትንና ሕዝቡን ለማቀራረብ የተቋቋሙት ድርጅቶች ወደ ጥፋት ያዘነበሉበት ምክንያት ፣ አንዱም የጊዜው ሁኔታ ፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ የግል ጥቅምን ለማካበት አመች በመሆኑ ፣ ሁለትም ፣ በክፍለ ሀገሩ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩት ግለሰቦች በሁኔታው ተጠቅመው ግላዊ ፖለቲካዊ ፍላጐታቸውን ለማርካት የሚሸርቡት ስውር ተንኮል ነበር ። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥትም የኤርትራን ሁኔታ በመጠቀም የራሳቸውን ቁሳዊ ፍላጐትና ፖለቲካዊ ሥል ጣን ለማራመድ ያላሰለሰ ጥረት የሚያደርጉ ባለሥልጣኖች እን ደነበሩ ታሪክ መዝግቧል ። የጀኔራል ናደውና ጭፍሮቹ ድርጊት ምናልባት ከልዑል ራስ አሥራተ ካሣና ግብረአበሮቹ ድርጊት በዓላማም ሆነ በይዘት አንድም ሁለትም ሆነው ይገኛሉ ።

«እንግዲህ ፣ እነዚህ ድክመቶች ለሕዝቡ መበርገግና ለወ ንበዴዎቹ ኃይል ማበጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

«በጊዜው ጸጥታን ለማስከበር የመጣው ብሔራዊ ጦር በመባል ይታወቅ የነበረው ሠራዊት ለምን? ለማን? እንደሚዋጋ አያውቅም ነበር ይባላል ። የኤርትራ ሕዝብ በሙሉ ወንበዴ ነው የሚል እምነትም ነበረው ። ጦሩ በትንሽ ነገር ቶሎ ስለሚቆጣ ፣ ጥፋተኛውን ከደህናው ሳይለይ በደፈናው የቂም በቀል ርምጃ ይወስዳል ። ዘረፋ ያካሄዳል ፣ ቤቶችንና ልጃገረዶችን ይደፍራል። ተኩሶ ከጣለ በኋላ ቂም ይላል ። አስበርጋጊ ድርጊት ነበር ። በረሀ ሔዶ መሞት ይሻላል በማለት ዐቅም ያለው ነፍሱን ይዞ ወጣ ። ልጅዋ ፊቷ ሲደፋ ከማየት እናት መቀነቷን አጠበቀች ።

«በአንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ፣ በ15ኛ ብርጌድ የሚካሄድ የአሥመራ ከተማ የውስጥ ጥበቃ ኃላፊነት የተሰጠው ኃይል ነበር ። በኤክስፖ ቅጥር ግቢ ውስጥ የራሱ የምርመራ ክፍል ፣ የራሱ እሥር ቤት ፣ የራሱ ፍርድ ቤት ነበረው ። እንደፈለገው ያስራል ፤ ያለምንም ፍርድ የሞት ቅጣት ይበይናል ። እዚያው ረሸና እዚያው ይቀብራል ። የሚታፈሱት ፣ የሚገረፉት ፤ የሚታሰሩትና የሚረሸኑት ሰዎች አብዛኛዎቹ ጸረ አብዮተኞች ሆነው አልነበረም ። በጉቦ ፣ በሴትና በግላዊ ቂም በቀል ምክንያት ነበር ። ገንዘብ አለው? ቆንጆ ሚስት አለችው? ዛሬ ምን ያህል ብር ከባንክ አወጣ? የሚሉ ቀላል ጥያቄዎች ለሞት የሚያበቁበትም ጊዜ ነበር ። ልዩ ልዩ ተልዕኮ ናፘቸው ከበረሀ በወዶ ገብነት የሚመለሱት አንዳንድ ሰዎች ሆነ ብለው የሚሰጡትን መረጃ እንዳለ አሜን ብሎ የመቀበል ሁኔታ ስለነበረ ፣ ተገንጣዮች ለማድያ የሚፈልጓቸውን ሰዎች በዚሁ የውስጥ ጥበቃ ድርጅት በተዘዋዋሪ መንገድ ያስመቱ ነበር ። የሞተ አይናገርም ። ጸጥ ብሎ ቀርቷል ። ደግነቱ አብዮት ደንቆሮና እውር አይደለም!

«ከዚህም ሌላ ፣ ተመሳሳይ ተግባር የሚያካሂድ ፣ ኀብረት እዝ የተባለ ክፍል ነበር ። የዚህ ክፍል ኃላፊነት ፣ ጥፋተኞችን ፈልጎ የመያዝ ፣ የከተማውን ጸጥታ በስውር መቆጣጠር ፤ የታሠሩ ሰዎችን ቤት መፈተሽና ከወንጀል አድራጎት ጋር የተያያዙትን ንብረቶች ብቻ ለብስቦ ጉዳዩ ለሚመለከተው ክፍል በደረሰኝ ማስረከብ ነበር ። ክፍሉ የተቋቋመበት ዓላማ ይህ ሲሆን ከዚህ ለየት ያሉ ሁኔታዎች ተፈጽመው ይገኛሉ ።

«ሰዎች በጥርጣሬ ከመንገድ ይታፈሳሉ ። የተያዙት ሰዎች ወደ ተገቢው ምርመራ ክፍል መተላለፍ ሲገባቸው ፥ ምርመራው እዚያው ይፈጸማል ። ርምጃውም እዚያው ይወሰዳል ። ተጠያቂም ፥ ጠያቂም የለም ። ሰውዬው የደረሰበት አይታወቅም ። ለንብረቱም ደረሰኝ አይሰጥም ። ዝም ፥ ዝም ። ከከተማ መውጫ ኬላዎች ላይ ታንቆ ወይም ተረሽኖ የሚገኝ ሬሣ ብዙ ነበር ። ማን ገደለው? በምን ምክንያት? የሚጠይቅም ፥ መልስ የሚሰጥም የለም ። የሞተ ሰው አፍ የለውም ፥ አይናገርም ። ግን አብዮት ዲዳ አይደለም!

«ከደርግ ምርመራ ክፍል የተላከ ልዩ የምርመራ ቡድን የሚባልም አካል ነበር ። የቡድኑ አባሎች የበታች ሹማምንት ቢሆኑም ፥ በውጭ በሻምበልነትና በሻለቅነት ማዕረግ ነበር የሚታወቁት ። ይህም ቡድን የራሱ እፋኝ ጓድ ፥ የራሱ ምርመራ ክፍል በሥሩ አቋቁሞ የመሰለውን ውሣኔ ይሰጥ ነበር ። ማን በምን ምክንያት ታሠረ? ማን እንደወጣ ቀረ? የአብዮት አምላክ ብቻ ነበር መልሱን የሚያውቀው!

«በጊዜው የነበረው የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤትም ወጣቱን በማስበርገግ ረገድ የተጫወተው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። በጠባብ ብሔርተኛነትና በጭፍን ጀብደኝነት ስሜት የሚመሩ ግለሰቦች በውስጡ ነበሩ ። በመሆኑም ከአደራጅነት ጎናቸው ይልቅ የበታኝነት ጎናቸው አይሎ ይታይ ነበር ። አብዮት የማያቋርጥ ሂደት ነውና እንደ ኩሬ ውሀ አንድ ቦታ ላይ ረግቶ አይቆምም ፥ ወራጅ ውሀ እየጠራ ይሄዳል ።

«ዛሬ ይህ ሁሉ ያለፈ ታሪክ ነው ። አብዮታችን የዲሞክራሲያዊ ማዕከልነትን አመራር ተቀዳጅቷል ። ዲሞክራሲያዊ ማዕከልነት ጥንቃቄን ፥ ትዕግሥትን ፥ አስተዋይነትንና ቆራጥነትን ይጠይቃል ። የሰው ልጅ መሠረታዊ መብቶችን የማክበርና የማስከበር ግዴታን ይጠይቃል ። ይህን ካደረግን የሰዎችን ልብ የማንሰብበት ምክንያት የለም ። ሕዝቡ ራሱ ይተባበረናል ። ለደኅንነቱ የማያስብ ፍጡር የለም ። አሠራራችንም ይበልጥ ሕዝባዊ ሊሆን ይችላል ። ደኅንነት የሕዝብ ጉዳይ ነው ። የሚኒስቴራችንም ስም ከጸጥታ ወደ ሕዝብ ደኅንነት የተለወጠውም ይህንኑ በማመን ነው ። ይህን ሁሉ የምለፈልፈው አለምክንያት

አይደለም ። በምናሳየው አርአያ የሕዝቡን ልብ መሳብ አለብን ለማለት ነው ።

«ባንድ ሜዳ በምናደርገው ውጊያ የኤርትራን ችግር ለመፍ ታት የተነሳን የሚመስላቸው ወገኖች ሊኖሩ ይችላሉ ። ርግጥ የወንበዴዎችን አከርካሬ መስበር አለብን ። ግን የቀይ ኮከብ ዘመቻችን ዓላማ ረጅም ነው። ዘላቂ ዓላማችን በሕዝቦች መካ ከል መግባባትንና መተማመን መገንባት ነው ። የሚናፍቀኝ ነገር ቢኖር እርስ በእርሳችን መገዳደል ቀርቶ አንዳችን ለሌላው የምን ሞትበትን ቀን ማየት ነው»

«ተጨማሪ መረጃ አለኝ » አለ ሥዩም በረጅሙ ካዛጋው በኋላ ።

«ቀጥል ።»

«ካዲሳባ የመጡት ሰዎች ጉዳይ በጣም አሳስቦኛል....»

«እንዴት ?»

«በየሱቁ ፥ በየቡና ቤቱ ፥ በየመንገዱ ፥ የሚታዩት እነሱ ብቻ ናቸው ። ምናልባት አሁን ወደ ባቢሎን ብንሄድ ሠፈሩን ወረውት ይገኙ ይሆናል ። ትላልቆቹም በየ«ሲክሬቶው» ገብተው ተሰግስገዋል ። ኋላ አንድ ነገር ቢደርስባቸው የማን ኃላፊነት ይሆናል?» አለ ።

ኰሎኔል በትሩ ራሱን ነቀነቀና ፥ «ሁሉም በግሉ ኃላፊነት አለበት ። እዚህ የመጣነው ለሽርሽር አይደለም ። ግን አንድ ነገር እናደርጋለን ። ተከታትለን ሪፖርት ማድረግ አለብን — እያ ንዳንዳቸውን » አለ ።

«ግን ‘ኮ» አለ ሥዩም ።

«ግን ምን?»

«ወጭ የለንም ። መረጃ ያለገንዘብ አይገኝም ። ያለገንዘብ ምንም መሥራት አይቻልም ። ገንዘብ ያስፈልገናል....»

ኰሎኔል በትሩ ፈገግታውን እያሳየው ፥ «አዎ ፥ በተለይ አንተ ገንዘብ ያስፈልገሀል ። ኪስህ ቀዳዳ አለው መሰለኝ? ስለገን ዘብ አታስብ ። ሞልቷል ። ይልቅ ችግሩ ያለው እንዴት በዘዴ

እንጠቀምበት የሚለው ጥያቄ ላይ ነው ። ግን እንዳያበላሹህ ተጠንቀቅ ። ጉቦና ምልጃ የሚወዱ ብዙ ናቸው ። የዚህ አገር አብዛኛው ሰው አለምክንያት ቀዳዳ ሣንቲም አትወጣውም ። በጋበዘህ ማለዳ በጧት እገሌን አማልደኝ ፣ እገሌን ወይም እገሊትን አስፈታልኝ ፣ ለእገሌ ወይም ለእገሊት ፓስፖርት አስወጣልኝ ብሉ ዓይኑን አፍጥጦ ይመጣል ። ከመሐል አገር የሚመጣው ሰው ሁሉ ለችግራቸው ሁሉ መፍትሔ የሚያስገኝላቸው ይመስላቸዋል — በተለይ ሴቶቹ ። ተጠንቀቁ ጓዶች ። ባማላጅነት የመጣብኝ ሰው በምን ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው ። ራሳችሁን ከዚህ ነገር ጠብቁ ። ሌላውንም ተከታተሉ ። ወደ አንድ ነገር ማምራት አይቀርም ። እያንዳንዱ ድርጊት ከኋላው ተመጣጣኝ የሆነ ምክንያት አለው» ብሉ ንግግሩን እንደጨረሰ አሁንም ሥዩም እጁን አወጣ ።

ተከላይ ዘድንግል ሥዩምን በጥላቻ ዓይን ተመለከተው ። አዛጋ ። ሰልችቷል ። ሰዓቱን ተመለከተ ። ተስፋ ቆርጦ ወንበሩ ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠ ። አራተኛው ሰው ፣ ሽለቃ ጋረደው መኮንን ብዙ የሚናገር ሰው አይደለም ። ዝምተኛ ነው ። የሚያዳምጥም አይመስልም ። የምርመራ ክፍል ኃላፊ ነው ። በዚሁ ሥራ በአሥመራ ለብዙ ጊዜ ቆይቷል ። ብዙ ሰዎች ስሙን ሲሰሙ ይርበደበዳሉ ፣ ይንቀጠቀጣሉ ። «ገልብጠው!» ከማለት ሌላ ትእዛዝ አያውቅም ። በፖለቲካ እሥረኞች ላይ የሚጠቀመው ሳይኮሎጂ ቢኖር ፣ አንዳንዴ እንደ ጓደኛ አቅርቦ ያሳስቃቸዋል ፣ ያጫውታቸዋል ። በዚህ ዘዴ የሚፈልገውን ካላገኘ ፣ ወይም ለጥያቄው አመርቂ መልስ ካልሰጡት ማኩረፍ ይጀምራል ። ያኮረፈ ወይም ፊቱን ያዞረ ዕለት እሥረኛ ሁሉ በያለበት በቁሙ ሽንቱን ሲለቅ ነው የሚውለው ። ሲገርፍና ሲያስገርፍ ውሉ ማታ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር በሠላምና በእርጋታ ሲጫወት ላየው ሰው ያስገርማል ። የቤተሰብ ሰው ነው ። ቤተሰቡን በጣም ይወዳል ፣ ያከብራል ። ማምሸት አይወድም ። እንቅልፋም ነው ። ማታ በቶሎ ይተኛል — የሠላም እንቅልፍ ። ታዲያ ቢሞት ማታ የምርመራ ሥራ አያካሂድም ወይም እንዲካሄድ አያደርግም ። ሁሉም የሠላም እንቅልፍ እንዲተኛ ይፈልጋል ። ኰሉኔል በትሩ በልቡ ትንሽ ሳይኮሎጂ ቢማር አሁን ምን ነበረበት፣ አለና ወደ ሥዩም ዞር «እሺ ምን ነበር?» ብሉ ጠየቀው ።

ሥዩም ሰስ ከንፈሮቹን እሞጥሙጦ ፣ «ጓድ ኩሉኔል ፣ ይኸ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እየተባለ የሚነገረው ነገር ደስ አላለኝም» አለ ።

«እንዴት ማለት?»

«የቀይ ኮከብ ዘመቻ የታቀደው ለሦስት ወር ነው ፤ አይደለም?»

«ሊሆንም ላይሆንም ይችላል.....»

«በሦስት ወር ውስጥ ችግሩን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንፈታለን ብለን በይፋ መናገር ለፖለቲካችን ጥሩ አይመስለኝም ።»

«ለምን?»

«ኋላ ካልሆነልን መጥፎ ግምት ላይ ይጥለናል ብዬ ነው ። ጠቅላላ ያገሪቱንም አመራር አደጋ ላይ ይጥላል ። ይህን መጠቆም ግዴታችን ይመስለኛል.....»

«ጥሩ ነው ። ግን አትሰጋ» አለው ኩሉኔል በትሩ —

«በሦስት ወር ውስጥ በእዚህ ክፍለ ሀገር ያለውን ችግር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንፈታለን ያለ የለም ። እርግጥ በሚቀጥሉት ሦስት ወራት የተወሰነ ግብ ለመምታት ታቅዷል ። ግን ችግሩን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የመፍታት ትግሉ ይቀጥላል ። ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ የሚያውቅ የለም ። በዚህ እንጻር ነው አባባሉ መታየትና መተርጎም ያለበት ፣ ግን ጥሩ ነጥብ ነው ። የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ክፍል በዚህ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል ። ሌላ ነጥብ ያለው አለ?.....እሺ ወደ ምርመራ ክፍላችን እንሂድ ። ሻለቃ ጋረደው» አለ ።

ሻለቃ ጋረደው መኩንን ድምጹ ጉርናና ነው ። ሲናገር ከመሰልቸት የተነሳ የማይናገር ይመስላል ። ዓይኖቹ ፈጠጥ ፣ ፈጠጥ ያሉ ሆነው ቀያዮች ናቸው ። መልኩ የተቆጣ አንበሳ ፊት ይመስላል ።

«ብዙም መረጃ የለኝም ዛሬ» አለ ።

«ምነው ብዙ ሰዎች አልገለበጥክም መሰለኝ!» አለ ኩሉኔል ባሽሙር ።

«ወንበዴ ካልቆጠቆጠው መቸ ይናገራል......»

«ታዲያ ማነው እሺ ብሎ በፈቃዱ መረጃ የሚሰጠው?»

«እንደኛ ያለው ንዑስ ከበርቴ — ጫማና ምቾት የለመደው ። ገና ሳይገለብጡት ነው የባጡን የቆጡን የሚለፈልፈው......»

«እሺ!» በማለት ሪፖርቱን እንዲቀጥል ጋበዘው ።

«በቅርቡ ከናቅፋ አምልጠው የገቡ ወዶ ገቦች እንደሚና ገሩት የወገን ጦር አሰላለፍ መረጃ ደርሶአቸዋል ። የወገን ጦር አሰላለፍ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ብዛቱንና ጥንካሬውን ሁሉ አው ቀዋል ።»

«የእነሱስ ሁኔታ እንዴት ነው ይላሉ?»

«ሁሉም ጀሌዎች ስለሆኑ ስለወንበዴዎች ጦር ብዛትና ድርጅት የሚያውቁት ነገር የለም ። ግን ከፍተኛ ፍርሀት ፣ የሞ ራል ውድቀትና ረሀብ እንደደረሰባቸው ይናገራሉ ። አብዛኛ ዎቹ እድል ካገኙ ለማምለጥ እንደሚፈልጉም ይናገራሉ ። ስለሆነም ጥበቃው በጣም ተጠናክሮባቸዋል ይባላል ። ሁኔ ታው ይኸው ነው ። ግን ያገኘሁት ጠቃሚ መረጃ ቢኖር......» ብሎ ሳይጨርስ ፣ ኰሎኔል በትኩ «ምንድን ነው እሱ?» በማ ለት ጠየቀው ።

«ፈረንጣዮች የመርዝ ጢስ መከላከያ «ማስክ» በብዛት ሰጥተዋቸዋል የሚል መረጃ አለ......»

«አትለኝም?»

«እውነት ነው ። »

ኰሎኔል ማስታወሻ እየወሰደ ፣ ፈረንጣዮች ደግሞ እዚህ ውስጥ ምን አገባቸው? ጉድ ነው'ኮ ። ይህ ያረብ ቤንዚን የማይ ይሠራው ነገር የለም ። አሜሪካኖችም ቢሆኑ አይተኙልንም ። በስለላ ሳተላይቶቻቸው ሳይረዷቸው አይቀሩም ። ይህ ጦርነት ምናልባት አብዛኛው ወደፊት የምንቀይሰውን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ይመለከታል ። ግን ምን ማድረግ እንችላለን? ምን?» አለ በንዴት ።

ሁሉም ዝም አሉት ። የሚሰጡት መልስ አልነበራቸውም ። እሱም መጀመሪያውኑ መልስ እንዲሰጡት አልፈለገም ። ጥያቄውን ለራሱ ነበር ያቀረበው ። እንደ ፈረስ እናፉ ። የዓይን መነጽሩን አውልቆ በንጭ መሐረብ ጠራረገ ። አሥር አሥር ጊዜ መነጽሩን

መጥረግ ይወዳል ። «ደህና» አለ «ተክላይ ስለሰጠሁህ ሥራ ምን አደረክ?»

«የትኛው?»

ኰሎኔል አንድ ሥራ ብቻ አይሰጥም ። ደራርቦ ነው ሥራ የሚያሸክመው ።

«ሥዕላይ አሁን የት ነው?»

«ፈያሚታ ጊላይ ቤት ።»

«እርግጠኛ ነህ?»

ተክላይ ጥቁር መነጽሩን ሰልካካ አፍንጫው ላይ አስተካክሎ አስቀመጠው ። ሉጫ ጠጉሩን በጣቶቹ ቆፈር አደረገ ። ስስ ውሀ ሰማያዊ ልብስ ፣ ነጫጭ ነጥቦች ጣል ካሉበት ጥቁር ክራቫት ጋር ለብሷል ። ደረት ኪሱ ውስጥ እንደ ነገሩ ጠቅለል አድርጎ የሻጠው መሐረብ የክራቫቱ መንታ ነበር ።ያው እንደ ልማዱ ሽክ ብሎአል ። «መችም ሰዎቻችን ከጓድ ሰለሞን ቤት ጀምሮ ማይተመናይ ድረስ ተከታትለውት ነበር ። መኪናው አሁንም ፈያሚታ ጊላይ ቤት ደጃፍ ላይ ትገኛለች ፣ ብቻ ሰዎቹ ቤት ገብተው አላረጋገጡም ካስፈለገ ግን......» ሲል —

«ኖና ። አያስፈልግም ። ለጊዜው ተወው ። ግን ሥራዬ ብለህ ባይነቁራኛ እንድትከታተለው እፈልጋለሁ ። ሐያ አራት ሰዓት ። ግን በምንም ሁኔታ እንደምንከታተለው ማወቅ ቀርቶ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ እንኳ እንዲኖረው አያስፈልግም ። ልጅቱንም ተከታተላት ። ወደ አንድ ፍንጭ ታመራን ይሆናል ። እና አሁን እስቲ አብረን እናስብ ። ሥዕላይ ለምን መጣ ብላችሁ ታስባላችሁ?» በማለት ጥያቄ አቀረበላቸው ።

አራቱም ረዳቶች እቀርቅረው ያስቡ ጀመር ። ኰሎኔል ጠረጴዛውን በወፍራም ጣቶቹ ይቆረቁራል ። የአንበሳ ምልክት ያለበት ትልቅ የወርቅ ቀለበት ጣቱ ላይ ይታያል ።

«ለምን ገልብጠን አንሞክረውም?» አለ ሻለቃ ጋረደው መኰንን ።

ኰሎኔል በጥላቻ ዓይነት ተመለከተውና ፣ «መገልበጥ ሁል ጊዜ መፍትሔ አይሆንም ። መገልበጥ ለእሱ አዲስ ነገር አይደ

ለም ። ለምዶታል ። ሌላ ዘዴ መፈለግ አለብን» አለውና ዘጋው ።

ጋሪደው የምርመራን ሥራና ፖለቲካን ማጋጨት አይወ ድም ። ተናዶ ዝም አለ ።

ቀጥሎ የተናገረው ሥዩም ነበር — «ቀንደኛ ወንበዴዎች የነበሩ ሌሎች በሠላም እጃቸውን ሰጥተው ገብተዋል ። ላደረሱት በደል ከፍተኛ ካሣ እየከፈሉ ናቸው ። እነሱም እንደ ሥዕላይ በወንበዴዎች ድርጅቶች ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው ናቸው ። የሥዕላይ መምጣት ምን አዲስ ነገር ተገኘበትና ነው አሁን ስለእሱ የምንጨነቀው?» አለ ።

«ግን ለምን አሁን? ለምን ይህን ጊዜ ምርጫ መጣ? የተተከ ለብን ሰው ነው ወይስ በሀቅ ተመልሶ የመጣ? የተተከለብን ሰው ከሆነ ለምን ዐላማ? ይህን ነው ማወቅ ያለብን ። ሥዕላይ በጣም ብልጥ ነው ። የሚሰጠው መረጃ ሁሉ ትክክል ነው ። በሚናገረው ሁሉ ግልጽ ነው ። ግን ለምን እንደሆነ እንጃ ግልጽነቱን እጠ ራጠራለሁ» አለ ኰሎኔል አሁንም ጠረጴዛውን በጣቶቹ ከፋኛ እየቆረቆረ ።

ተክላይ ዘድንግል ጥቁር መነጽሩንና ከራቫቱን አስተካክሎ ሲያበቃ ፥ «ሥዕላይ አብሮ አደጌ ነው ። አውቀዋለሁ ። ከልጅነቱ ጀምሮ ጀብደኝነት ያጠቃዋል ። በጣም ራሱን የሚወድ ፥ አድር ባይ ሰው ነው ። ገንዘብና ሥልጣን በጣም ይወዳል ። አደገኛ ሰው ነው» ብሎ ቀጥሎ የሚናገረውን ነገር ሲያስብ ቆየና ፥ «ፈዶሬ ሽን ሲፈርስ ልጆች ነበርን ። ሾአተ አሥመራ ውስጥ ያስገባኝ እሱ ነው ። ስለሚደባደብ እንፈራው ነበር ። አንዳንድ ባለሥልጣ ኖች እንድንገድል ሁሉ ይገፋፋን ነበር ። ኋላ አጋለጠን ። በእሱ አመራር ሥር የነበርነው ስድስት ልጆች ታሠርን ። እኔ እንኳ በእሥር ቤት ብዙም አልቆየሁም ። አባቴ አስፈቱኝ ። አንድ ጓደ ኛው ፥ ተክስተ ገብራይ ሰባት ዓመት ጨርሶ ወጣ ። አሁን የፓራ ዲሶ ቡና ቤት ባለቤት ነው ። ከኔ ይልቅ ተክስተ ሊገልጸው በ ጣም ይፈልጋል ። ሥዕላይ ኋላ ቆይቶ የአውራጃ ገዢ ሆኖ ተሾመ። በረኸኞችንና መንግሥትን ለማስታረቅ ይሯሯጥ ነበር ። በዚያን ወቅት የሲ. አይ፥ ኤ. ሰላይም ሆኖ ይሠራ ነበር ። መኪናና ቤት እንደሸሚዝ ነበር የሚቀያይረው ። ማታ ማታ የሚያጠፋው ገንዘብ ልክ አልነበረውም ።

«አብዮት ፈነዳ ። የኃይል ሚዛን ተለወጠ ። በረሀ መግባቱን ሰማን ። ከጀብሐ ወጥቶ ወደ ሻዕቢያ የገባው እሱ እንደሚለው ሳይሆን የጀብሐን መዳከም በመረዳቱና የፈለገውንም ሥልጣን ባለማግኘቱ ነበር።ሻዕቢያ እጅዋን ዘርግታ ተቀበለችው። በጀብደኛነቱና በጭካኔው ስለሚታወቅ ካንድ ሥልጣን ወደ ሌላ ባጭር ጊዜ ውስጥ ተረማመደ ። ዝነኛም ሆነ ። በደቡብ ኤርትራ የተፈጸመውን በደል ሁላችንም እናውቃለን ።

«በነገራችን ላይ ታናሽ ወንድሜ የተገደለው ሥዕላይ በራኺ የሻዕቢያ ሐለዋ ሰውራ ኃላፊ በነበረበት ጊዜ ነው ። ወንድሜ እንዲገደል ትዕዛዝ የሰጠው እሱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ አለኝ ። ሊያገኘኝ ባለመቻሉ ነው እንጂ እኔን ነበር ማስገደል የፈለገው.....» ሲል—

ኰሎኔል ንግግሩን አቋረጠውና ፥ «ስለግል ቂም በቀል አይደለም አሁን የምንወያየው ። እንዲህ ዓይነቱ ስሜት በሥራችን ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው አይገባም ። ወደ ዋናው ነጥብ እንመልከት» አለው ።

ተክላይ በኃዘን አንገቱን ደፋ ። መነጽሩን አውልቆ ቀስ ብሎ እንባውን ከዓይኑ ላይ ጠረገ ። ለጥቂት ጊዜም ዝም ብሎ ቆየና ፥ «ነገሩን ተከታትዬ እንደደረስኩበት አሁን ተመልሶ የመጣው የሻዕቢያ ፖሊት ቢሮ አባል ለመሆን ፈልጎ ሳይሆንለት ስለቀረ እና በወንበዴዎችና በአብዮታዊ ጦር መካከል ያለው የኃይል ሚዛን መለወጡን ስላወቀ ነው ። እንዳልኩት አድርባይ ነው ። እስከማውቀው ድረስ ተመልሶ የመጣው በሌላ ምክንያት አይመስለኝም ። ሥልጣን እንዲሰጠው ካደረግነውና ገንዘብ ከሰጠነው ልንጠቀምበት የምንችል ይመስለኛል» አለ ጥርሱን ነክሶ ።

በሚናገርበት ጊዜ ሁሉ የታናሽ ወንድሙን ደም ሊበቀል የሚችልበትን መንገድ እያሰበ ነበር ። ከንፈሩን ክፉኛ ነከሰ ።

ኰሎኔል በትሩ የተክላይ ስሜት አላማረውም —

«የወዶ ገቦችን ደኅንነት የመጠበቅና እነሱን የመከታተል ኃላፊነት ያንተ መሆኑን እትርሳ ። መጠበቅ አለበት ። ምናልባት

ያስፈልገን ይሆናል ። የፈለገውን ገንዘብ ስጠው ። መኻታውም ከአልቤርጎ ቻው ወደ ኒያላ ይለወጥለት ። ግን ተመልሶ የመጣው አንተ አሁን ባልከው ምክንያት አይመስለኝም» አለ ።

አሸብር ለጠቀና፥«ታዲያ በምን ምክንያት ይመስልዎታል?» ብሎ ጠየቀ ።

«የተተከለብን ሰው ቢሆንስ? ነገሩን ከዚያ አቅጣጫ ለመ መልከት ሞክራችኋል?»

ሥዩም ስስ ከንፈሮቹን እንደ ልማዱ አሞጠሞጠና ፥ «ሻዕቢያ አሁን ማን ይሙት እንደ እሱ ያለ ብዙ ምስጢር የሚ ያውቅ ሰው ራሷን ለማጋለጥ ትልካለች? አይመስለኝም» አለ ።

«መጠራጠር አይከፋም ። ተከላይ በጥብቅ ተከታተለው ። ስለፍያሜታ ጊላይስ የምታውቀው ነገር አለ?» ብሎ ጠየቀው ።

«ቆንጆ መሆኗን ብቻ ነው የማውቀው ። ስለእሷ ሻለቃ ጋረደው ቢናገር ይሻላል ። ለጥቂት ወራት የከብር እንግዳው ነበ ረች» አለ ።

ጋረደው ተከላይን የጎሪጥ ተመለከተውና ዝም አለ ።
«እህስ ጋረደው — ስለ ፊያሜታ ጊላይ የምታውቀው ምን ነገር አለ?» ብሎ ኰሎኔል ጠየቀው ።

«ሐዝሐዝ ለሦስት ወር ታሥራ ነበር»
«መቼ?»
«በ1969»
«በምን ምክንያት?»
«መዋርሙ ከፋይ የጀብሐ አባል ነች ተብላ.....»
«እና?»

«እንደ እውነቱ ከሆነ መዋርሙ አልከፈለችም ፥ የጀብሐ አባልም አልነበረችም ። አንድ ማይተመናይ የነበረ የውስጥ ወን በዴ እቁብ ግቡ በማለት እያታለለ ገንዘብ ይሰበስብ ነበር ። ኋላ ሲያዝ እቁብተኞቹን የጀብሐ አባሎች ናቸው በማለት ጠቆመ ። ልጅቷ በሰውዬው ጥቆማ ከተያዙት ሰዎች ውስጥ አንዷ ነበረች ። ሌላ ኃጢአት አልነበረባትም» ብሎ ዝም አለ ።

«ገልብጠሀታል!»
«አልቻልኩም» አለ ለቆ ።
«እንዴት?»

ከመናገሩ በፊት ከት ብሎ ሳቀና ፣ «እንደ እሷ ያለች ሴት እሥረኛ አጋጥሞኝ አያውቅም» ብሎ ንግግሩን ጀመረ — «ትዝ እንደሚለኝ መስከረም ወር ላይ ነበር የታሠረችው ። ግቢው ውስጥ የበቀለውን ዓደይ አፀባ ሰብስባ የጀሮ ጉትቻ ፣ ያንገት ድሪ ፣ የእጅ አምባር እየሠራች ታጌጥበት ነበር ። እሥረኞቹ ሁሉ ልዕልት ፊያሜታ እያሉ ነበር የሚጠሯት ። እንደዚያ በ ዓደይ አበባ ታጌጥና ቁጠማ ጉዝጉዛ ቁጭ ስትል እውነትም ልዕ ልት ትመስል ነበር ። እሷም ይህን አውቃ ነው መሰለኝ የዓደይ አበባ አክሊል ሠርታ ራሷ ላይ ትደፋ ነበር ። አንድ ቀን እንኳ ከፍቶአት አይቼ አላውቅም ። ደስተኛ ነበረች ። እሥር ቤቱን እንደቀልድ እያየችው ነው መሰለኝ ያንታ አልነበራትም......

«አይሆኝ የእውነቱን ንገረኝ ፡ መዋጮ መክፈል ምንም አይደለም ። እንኳን እንቺ ከመሐል አገር የመጡ አንዳንድ ትልቅ ሰዎችም ቢሆኑ ለሕይወታቸው እየፈሩ ለወንበዴዎች መዋጮ ሲከፍሉ ቆይተዋል እያልኩ እያጫወትኩ ለማግባባት ብሞክ ርም ፣አኩርፌ ባስፈራራትም ፣ ሁልጊዜ የምትሰጠኝ መልስ ፣ «እኔ መዋጮ አልከፈልኩም ። የጀብሐ አባልም አይደለሁም ። ይኸ ጀብሐ ፣ ሻዕቢያ የምትሉትንም ነገር የሰማሁት እዚሁ ነው ። ሐያ ሐያ ብር በወር ሁለት ጊዜ ለእቁብ ከፍያለሁ ። መዋጮ ቢሆን ሐያ ብር ለምን እከፍላለሁ? ሁለት ወይም ሦስት ብር ይበቃ ነበር ። ሺ ብር የሚያገኙትም ከአምስትና ከአሥር ብር የበለጠ አይከፍሉም ሲባል እሰማለሁ ። ዋእ! ወንበዴዎች ሲመጡ እንዲያመሰግኑኝ ነው?» ትለኝ ነበር.....

«ታዲያ አንድ ቀን ወደ ምርመራ ክፍል ወሰድኳት ። ጋቢ ዋን ከላዩዋ ላይ ገፍፌ ጣልኩትና እውነቱን ትናገሪያለሽ ወይስ? አልኳት ። ምን አለችኝ መሰላችሁ? ይገርማል ። «ዋእ! አንተ ባለጌ! ሰቅለህ ልትገለብጠኝ ነው? እውይ ፣ አንተ ፣ አባቴ ይሙት ባለጌ ነህ። እስቲ ንካኝ» አለችኝ።ልገለብጣት አልቻልኩም ። ስቄ ለቀቅኋት ። ለምን እንደሆነ እንጃ ንጽሕት መስላ ታየችኝ ።» ብሎ ታሪኳን ነገራቸው ።

ተክላይ ዘድንግል የባሕር ዳር ቄጠማ የመሰለውን ስጋ ፥ ለግላጋ ውብ ገላዋን በዓይኑ ሕሊናው እያየ በልቡ ተመኛት ። በጭኖቿ መካከል የተደበቀ ትልቅ ምስጢር ታየው ። በሌላ በኩል ሥዕላይ በራኺን ለጊዜው ሊገድለው ባይችልም ፥ አንጀት ጉበቱን የሚያሳርርበት መንገድ በፊያሜታ ጊላይ ውበት አማካይነት ድን ገት ተገለጸለት ። ፈገግ አለ ።

ኰሎኔል በትሩ ተሰማ ጠረጴዛውን በጣቶቹ እየቆረቆረ አንድ ዓይኑን ከድኖ በሌላ ኢላማ ላይ ሲያነጣጥር ቆየና ፥ «እሺ ልጆች ። ጊዜው መሽቷል» ብሎ ጀመረ — «ስለያንዳንዱ ሰው በእጃችን ያለው መረጃ በቂ አይደለም ። ጓድ ጋረደው ፥ ከነገ ጀምሮ በዚህ ከተማ የሚኖሩትን ሰዎች የተሟላ ሕይወት ታሪክ መረጃ እፈልጋለሁ ። አንድ ባአግራፊካል ኢንተሊጀንስ ማእከል መፍጠር አለብን ። አስቸጋሪ መሆኑን አውቃለሁ ጓድ ። ግን መሆን አለበት ። ሕዝባውያን ድርጅቶች ባሉበት ባሁኑ ጊዜ ስለ ግለሰቦች መረጃ ማግኘት አያስቸግርም ። የት እንደ ተወለዱ? የት እንዳደጉ? የት እንደተማሩ? ምን ፍላጐት እንዳለባቸው? ምን እንደጻፉ? ከማን ጋር የት እንደሚውሉ? ከዚህ ቀደም ምን ሪከ ርድ እንዳላቸው? ከተቻለ ጠባያቸውም ጭምር ስለሰው ኃይል አትስጋ ። ነገ ስለሚያስፈልግህ ሰው ኃይልና ገንዘብ ሪፖርት አቅርብልኝና ሥራውን እንጀምራለን ።

«ጓድ አሸብር ከቀበሌዎች ስለጠፉት ሰዎች ማንነት ፥ ከማን ጋር ግንኙነት እንደነበራቸው ፥ በፊት እንዴትና ማን እንዳስመ ረጣቸው ካንተ በነገው ዕለት ዝርዝር ሪፖርት እፈልጋለሁ ። ስለ ሕዝባውያን ድርጅቶች ደኅንነት የምታቀርበው ሪፖርት ዘግይቶ መሆን የለበትም ። ካለኀበት ሪፖርት እንድታደርግልኝ እፈ ልጋለሁ ። በከተማው ዙሪያ እንደተባለው የጥበቃው ክልል ስፋት እንዲሰፋ ተደርጎ እንደሆነ ተመልክተህ አስቸኳይ ሪፖርት በጧት አቅርብልኝ ።

«ጓድ ሥዩም ፥ ከመሐል አገር ለዘመቻው የመጡትን ሰዎች ሁኔታ መከታተል ያንተ ኃላፊነት ነው ። የት እንደሚሔዱ? ከማን ጋር እንደ ሚገናኙ? ምን እንደሚያደርጉ? ምን እንደሚሉ? ስለ እያንዳንዳቸው ሕይወት ታሪክም ባጭሩ ሪፖርት እፈልጋለሁ ። የወንበዴዎች ሬዲዮ ማቢያ ከነገ ጀምሮ «ጃም» ይደረጋል ተብሎ

ተነግሮኛል ። ጋዜጠኞችን አላምንም ። መደረግ አለመደረጉን አንተ ተከታተል ። ሚዲያዎቻቹ የሚያስተላልፋአቸውን ፕሮግራሞች እንደዚሁ ።» አለና መነጽሩን አውልቆ እየጠራረገ ሲያስብ ከቆየ በኋላ ፣ እሺ ልጆች ። አንድ ቴዎሪ አለኝ ። ይህ ቴዎሪ ልክ ይሁን ወይም ስህተት የምታረጋግጥልኝ አንተ ፣ ተክላይ ዘድ ንግል ነህ ። ትልቅ ሥራ ነው ። ምናልባትም አንተ የምታመጣው መረጃ አጠቃላይ ሥራችንን ይወስን ይሆናል ።

«ቴዎሪው እንዲህ ነው ። ሥዕላይ ላንድ ተልዕኮ የመጣ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ ። የወንበዴዎችን ራዲዮ ጣቢያ ስም ታችሁ እንደሆነ ፣ የእሱ መምጣት በኛ ሚዲያዎች ከመገለጹ በፊት ፣ እሱን የሚያጥላላ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ማካሔድ ጀምረዋል ። በፊት ሌሎቹ ሲገቡ እንዲህ አድርገው አያውቁም ። አሁን ለምን? ሊያዘናጉን ይሆናል ብዬ አሰባለሁ ። ቅድም ፣ ሥዩም እሱን በመላክ ራሳቸውን እንዴት ያጋልጣሉ? ብለሀል ። ነጥቡ እዚህ ላይ ነው ። ስለ አንዳንድ ድርጅቶቻቸው በቀር ስለ እነሱ የማና ውቀው እምብዛም ነገር የለም ። ስለ ሻዕቢያ ምን አዲስ መረጃ ሊሰጠን ይችላል? ለፕሮፓጋንዳ ጥሩ ከመሆን ሌላ ጥቅም የለውም ።

«ታዲያ ለምን መጣ? በተለይ ጊዜውንና ሁኔታውን እን ዴት? በምን ምክንያት መርጦ መጣ? ተልዕኮው ምንድን ነው? መልሱን ማግኘት አለብን ። ከእሱ የምናገኘው መልስ ምናልባት ወደ «ቢሮክራሲ» ያመራን ይሆናል ። ቢሮክራሲ ማነው? የት ነው? ብዙ ስም ፣ ብዙ መልክ አለው ። እስካሁን ባደረግነው ክትትል ልንደርስበት አልቻልንም ። ጊዜው አሁን ነው ። በቀይ ኮከብ ዘመቻ ተረባርበን የወንበዴዎችን የስለላ መዋቅር አሁን ለመስበር ካልቻልን ምን ጊዜም ልንሰብረው አንችልም ። ወንበ ዴዎች ስለኛ የማያውቁት መረጃ የለም ። ወታደራዊ ንቅናቄአችንን ሁሉ አስቀድመው ደርሰውበታል ። እንዴት? ከየት? — ጉያችን ውስጥ አሉ ማለት ነው? እነማን ናቸው? አሁን በዘመቻው ወቅት መረጃ ሰብስበው በማቀበል ብቻ የሚወሰኑ አይመስለኝም ። ከሆነ ምን ለማድረግ አስበዋል? ሥዕላይ ለነዚህና እነዚህን ለመሰሉት ጥያቄዎች መልስ ወደምናገኝበት ቁልፍ ቦታ ያመራን ይሆናል ። ተስፋ አደርጋለሁ ። አላውቅም ። ንጹህ ሰው ሊሆንም ይችላል ። ግን እሱን መከታተል አለብን ። ተክላይ፣

ለዚህ ጥያቄ መልስ የማግኘት ኃላፊነት ያንተ ነው ። ካስፈለገ መቶ ሰው ከኋላው ልታሰልፍ ትችላለህ ። ለሸንት እንኳ ጊዜ እንዳይሰጠው እፈልጋለሁ ።

«ጓዶች ፥ በተጠመደ ቦምብ ላይ እንደተቀመጥን ያህል ነው የ ሚሰማኝ ። የተዘረጋብን የሸረሪት ድር ይታየኛል ። መበጣጠስ አለብን ። ምንም ነገር ንቀን መተው የለብንም ። የኀሊየድ ንቀት ፥ የኀልያድን ውድቀት ያስከትላል ይባላል ። ለእንቅልፍ ጊዜ የለንም......»

ተክላይ ዘድንግል ተስፋ ቆርጦ አዛጋ......

ከእንግዲህ ራሴን ማስተዋወቅ አስፈላጊ አልመሰለኝም ። መልክ ፣ ስም የለኝም ፣ ቦታና ጊዜ አይወስነኝም ብዬ ነበር ። እኔ ነኝ ። ነበርኩ ፣ አለሁ ፣ እኖራለሁ ። ባሕርዬ ወይም ተፈጥሮዬ ነው ። ታሪኩ ይቀጥላል ። ሕይወት እንደ ሸረሪት ድር ናት — ሸማኔ እንደዘረጋው ድር ቁልፍልፏ የወጣ...........

# ግዳጅ — አሮማይ

ሥዕላይ በራኺ ከሰለሞን ቤት እንደወጣ በቮክስ መኪናው በክረን መንገድ ሲበር ሔዶ ፊያሜታ ጊላይን ቤቷ ፡ በማይ ተመናይ ጣላት ። መንገድ ላይ አንድም ቃል አልተለዋወጡም ። እሱም ሆነ እሷ በግል አሳባቸው ተውጠው ነበር ። ከመኪናው ልትወርድ ስትል ፡ «ምሽቱ እንዴት ነበር?» አላት ።

«ጥሩ ነበር» አለችው ።

«ያንን ልጅ ስላገኘሽ ይሆናል ። ደስታሽ ዓይንሽ ላይ ይነበብ ነበር ። ያው የድሮዋ ፊያሜታ ነሽ ። ምንም አልተለወጥሽም ። አሁንም ልብሽን የሚማርከው ዝነኛ ሰው ነው ። አይደለም ግን ምን አየሽበት?» አላት ።

ማይ ተመናይ መብራት አልነበረም ። ጥቅጥቅ ያለው ጨለማ በእጅ የሚዳሰስ ይመስላል ። እና በጣም ይበርድ ነበር ። የመንደሩ ውሾች ሲጮሁ ይሰማል ።

«እሱ አያገባህም» ብላው ከመኪናው ልትወርድ ስትል እጅዋን ጠበቅ አድርጎ ያዛት ።»

«አልማስ !» አለችው ።

«አይዞሽ» አለ — «አሁን የፍቅር ጊዜ አይደለም ። አንድ ቀን እንደርስበታለን ። መኪናዋን እዚሁ ደጅሽ ነው የምተዋት ።»

«ለምን?» አለች ።

«ምክንያት አለኝ»

«እንደምን ያለ ምክንያት?»

«መናዘዝ አለብኝ፣ ያገሬ ልጅ — ላንቺ ነጻነት ነው ስደውን የኖርኩት.....»

«እና አሁን ምን ይሁን?»

«ከሐዲ ትይኝ ይሆናል በልብሽ.....»

«ወላ ከሐዲ እኔ ግድ የለኝም ።»

«አንቺ የመሐል አገር ሰው — አማራ ነው አሉ የምትወጂ ?»

«ፍቅር መሐል ፣ ዳር ፣ ሰሜን ፣ ደቡብ አይልም» አለች ።

«እሺ ። ለማንኛውም ነገር መኪናዬ እዚህ ትደርልኝ ። አንድ ቀን እከስሻለሁ ። እሺ እምባር?»

«እኔ ምንቸገረኝ ግን ጣጣ ውስጥ መግባት አልፈልግም ።»

«ምንም ጣጣ የለም ። ቤቴ ይሁንብሽ ። በጣም የሚያስቸኩል አንድ የግል ጉዳይ ስላለብኝ ነው ። ከእንግዲህ ጊዜ የለኝም ። ጥናት እንዳዘጋጅ ታዝዣለሁ ። እነዚህ ሰዎች ጊዜ አይሰጡኝም ። ስለወንበዴዎች አርባ ገጽ ጥናት አምጣ ይላሉ ። ለመቼ? ሲባሉ የሚሰጡት መልስ 'ነገ' የሚል ነው ። እሺ ። አሁን ልሒድ » አለ ።

መኪናውን ቆልፎ ጨለማ ውስጥ ገብቶ ጠፋ ። ከፊያሜታ ጊላይ ቤት ብዙ ርቆ አልሄደም ። ሌላ መኪና ይጠብቀው ነበር ። መኪናው ተነስቶ ትንሽ ከመሔዱ በአራተኛ ማርሽ ይበር ጀመር። ወደ ከተማ የተመለሱት በከረን መንገድ አልነበረም ። ወደ ሐዝሐዝና ወደ ሳምባ ነቀርሳ ሆስፒታል የሚወስደውን መንገድ ነበር የመረጡት ። ግን ዞረው ባንዳፍታ 'ፓራዲዞ' ደረሱ ። መኪናውን የሚነዳው አንድ ጠብደል ወጣት ነበር ። አንድ ቡና ቤት በር ላይ አወረደው ። ቡና ቤቱ በመንገዱ ስም ነው የተሰየመው — ፓራዲዞ ቡና ቤት ። ትንሽ ቡና ቤት ናት ። ሥዕላይ ስተት ብሎ ገባ ። ጥቁር ካፖርት ደርቧል ። ባርኔጣ አድርጓል ።

አምስት ሣንቲም ከኪሱ አውጥቶ ለባሬስታው አሳየ ።

«ባምስት ሣንቲም ቡና የለም» አለው ባሬስታው ።

«ቡና አይደለም የምፈልገው ።»

«ታዲያ ምን ትፈልጋለህ?»

«ንጹህ ሽንት ቤት ።»

ባሬስታው ትኩር ብሎ ሲመለከተው ቆየና ፣ «አለ ። ንጹህ ነው» ብሎት እየመራ ወደ ውስጥ አስገባው ። ሽንት ቤቱ ከፍቶ

አሳየው ። ትልቅ ሽንት ቤት ነበር ። የሽንት ቤቱ ወለልና ግድ ግዳ በነጭ 'ሴራሚክስ'ንጿል ። መሬት ውስጥ የተቀበረ ትልቅ 'ባኞ'ይታያል ። ሥዕላይ ግራ ገባው ። ባሬስታውን ሲመለከቱት የዋሕ ሽማግሌ ይመስላል ። ነጭ ኮትና ጥቁር 'ቢራቢሮ' ክራባት አስሮአል ። ግን ፈጣን ነበር ። ክፈት መቃጠቢያው ዛህን ሥር ያለውን የውሀ ቧንቧ መዘውር ሔዶ ማን ሲለው — በኮንክሪት የተቀበረ መስሎ ይታይ ነበረው ትልቅ ባኞ ተነስቶ ቆመ ። ሥዕላይ ደንግጦ ዞር አለ ። ራመድ ብሎ ባኞው አርፎበት የነበረበትን ጉድጓድ ተመለከተ ። የኤሌክትሪክ ብርሀን ኩሬ ጉድጓዱን ሞልቶታል ። ወደ ውስጥ የሚወስዱ ከብረት የተሠሩ ደረጃዎች ይታያሉ ። ባሬስታው ቶሎ ብሎ እንዲገባ በእጁ ነገ ረው ። ሥዕላይ ወደ ውስጥ ዘለቀ ። ባኞው ቦታው ተመለሰ ። ቦታው ተመልሶ ሲያዩት የትም ቤት የሚገኝ ተራ ባኞ ይመስ ላል ። ባሬስታው ሽንቱን ሸንቶ ፣ እጁን ታጥቦ ወደ ሥራው ተመ ለሰ ።

ሥዕላይ ታች ሲደርስ በምንጣፍ ያበደ ትልቅ የስብሰባ አዳ ራሽ ተንጣሎ ጠበቀው ። በአራቱም ማዕዘን ወደ ሌሎች ክፍ ሎች የሚያስገቡ በሮች ይታያሉ ። አራት ሰዎች በታላቅ ጉጉት ይጠብቁት ነበር ። ሞቅ ያለ ሠላምታ ሰጡት ። ከአራቱም ጋር ትከሻ ለትከሻ ተሳሳሙ ። እና ካፖርቱንና ባርኔጣውን አውልቆ ወረወረና ፣ «እሺ እዳ?» አላቸው ።

ከአራቱ ሰዎች ውስጥ አንዱ ፣ «ካንዲት ሴት ጋር ነበርክ — አይደለምን?» አለው ። ያደረበት ስጋት ጠይም ፣ ጠፋጣፋ ፊቱ ላይ ይታያል ። ትላልቅ ዓይኖቹ ድፍርስ ናቸው ። ያስማቋረጥ ያጤሳል ።

ሥዕላይ ነገሩን ለማቃለል ፈልጎ ፣ «አዎ ፣ ታዲያ ምን ይሁን? ምናለበት?» አለውና — «በረሀ ለባት ዓመት የቆየ ሰው በቅድሚያ ወደ ሴት ቢሮጥ ምን ያስገርማል? እዚህ ከተማ የምት ኖሩት ችግሩ ባይታያችሁ ነው ። የሴት ውበት ፣ ጥሩ የሴት ጠረን ይናፍቃል ። ስለቀንጆ ሴት ታስባለህ ፣ ታልማለህ ። ምክንያቱም በረሀ ዙሪያህ ያሉት ከሴትነት ተፈጥሮ ወጥተው ሴቶች አይመስ ሉም ። ከሩቅ ይሸታሉ ። ሴቶች ሲቆሽሹ ሽታቸው አይጣል ነው ። ሞዴስ ፣ የውስጥ ሱሪ የላቸውም ። እና የወር አበባቸው

በእግራቸው ሲወርድ ታያለህ ። ራስክን መጥላት ትጀምራለህ ። ሰው ከሥልጣኔ ውጭ ሲሆን ካውሬ ይብሳል ።»

ሰውዬው ፣ ተከስተ ገብራይ ፣ ሥዕላይ የሚለውን እያዳምጥም ነበር ። የሰውን አሳብ የማይቀበል ፣ ለጠየቀው ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ ብቻ የሚፈልግ ዓይነት ሰው ነው ።

«ማን ናት እሷ?» ብሎ ጠየቀው ።
«የድሮ ወዳጄ ናት.....»
«ስሟን ነው የጠየኩህ?»
«ፈያሜታ ጊላይ.....»
«ፈያሜታ ጊላይ?» ብሎ ፣ አንድ ትልቅ ፣ እብድ የሚያከል ፣ ጥቁር ፋይል አውጥቶ ቶሎ ቶሎ እያገላበጠ ይመለከት ጀመር ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፣ «አዎ — ይህች ናት — አይደለችም?» ብሎ ፎቶግራፍዋን ለሥዕላይ አሳየው ።
ሥዕላይ ባዎንታ ራሱን ነቀነቀ ።

«ጥሩ ልጅ አይደለችም» አለ ተከስተ ገብራይ በጥላቻ— «ካማሮች ጋር መዞር ትወዳለች ። የጀብሐ አባል ናት ተብላ ታስራም ነበር ። ለምን በቀላሉ ተለቀቀች? አሁን ምን እየሠራች ነው? በምን ነው እንዲህ በየቀኑ የምታጌጠው? የምትሽቀረቀረው? ለምን እንደሌሎች ሴቶች ወደ ጂዳ ፣ አቡዳቢ ፣ ዱባይ አልሄደችም? አጠራጣሪ ፍጡር ናት ። የኢትዮጵያ ሰላይ ልትሆን ትችላለች ። ብዙ ጊዜ የምትወጣው ከኰሎኔል ታሪኩ ጋር ነው ። ሴቶቻችን እንደ ድሮ አይደሉም ። ሸርሙጦች ሆነዋል ።» አለው በንዴት ።

ሥዕላይ ቀና ብሎ «ኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይን ነው የምትለው? ከመቼ ጀምሮ?» አለው ።

«ብዙ ጊዜያቸው ነው ። ከእሷ አይለይም ። ያለ የሌለ ሐብቱን ለእሷ ነው የሚያራግፈው ። ካለእሷ ሴት የሚያውቅ አይመስልም ። በጣም ይወዳታል» አለ ።

«እሷስ?» ብሎ ጠየቀው ።
«እሷ ምን ልብ አላት? ፍቅር አታውቅም ። ሴቶቻችን

ጥቅም አሳዳጆች ሆነዋል ። ከእሷ ልጅ ብትጠነቀቅ ይሻልሀል» አለው ድምጹን ከፍ አድርጎ ።

«ተስ በል ። እኔ የምሠራውን የማወቅ ሰው ነኝ......»

«ኤ!ማ ጓርዳንፓ» ብሎ ጠረጴዛውን ||በጡጢ ደበደበና ፣ «በሬሀ ቀየህ አልቀየህ ጉዳዩ አይደለም! እዚህ ዲሲፕሊን እን ዲኖር ያስፈልጋል ። እንዲህ ዓይነት ነገር ሁለተኛ እንዳይለምድህ እፈልጋለሁ ። እዚህ ቀልድ የለም ። የሞት ሽረት ትግል በማካሄድ ላይ ነው ያለነው ። ከተማው እንዳለ በሕዝብ ደህንነት ሰዎች ተወሯል ። ገባህ!?» አለው ።

ሥዕላይ ከተቀመጠበት ቀስ ብሎ ተነሳና ለተከስተ ጀር ባውን ሰጥቶ የተቀሩትን ሦስት ሰዎች በትናንሽ ዓይኖቹ ከቃኘ በኋላ ፣ ጥርሱን ነክሶ ሲያበቃ ፣ ድምጹን ዝቅ አድርጎ ፣ «የምታ ደርጉትን ጥንቃቄ አደንቃለሁ ። ከዛሬ ጀምሮ ማንኛውንም መመ ሪያ ፣ ትእዛዝ ፣ ውሣኔ የምትቀበሉት ከኔ ነው ። ግልጽ ነኝ?» ብሎ ፣ ከራቫቱን ፈቶ ሲያበቃ ፣ የሸሚዙን ኮሌታ ወደ ላይ በመገ ልበጥ ፣ ከእጥፋቱ ውስጥ እንደ መገተሪያ ሆኖ ተሸጉጦ የነበረ ወረቀት መዞ አውጥቶ ለተከስተ ወረወረለት ።

ተከስተ ገብራይ ወረቀቷን በቀስታ ዘርግቶ በሲጃራጭስ ው ስጥ ወረቀቷ ያዘለችውን መልእክት በጥንቃቄ አነበበ ። «አርባዕተ እሥመራ — ለተወሰነ ጊዜ ማንኛውንም ፣ መመሪያ ፣ ትእዛዝና ውሣኔ ከሥዕላይ ባራኺ እንድትቀበል እስታውቃለሁ» የሚል በራሱ በኢሣይያስ አፈወርቂ ፣ የሻዕቢያ ዋና ጸሐፊና የሻዕቢያ ጦር ዋና አዛዥ ፣ የተፈረመ ማዘዣ ነበር ። አርባዕተ እሥመራ የተከስተ ገብራይ ኮድ ስም ነው ።

«አነበብከው?» አለ ሥዕላይ ጥርሱን ነክሶ የፉንጮቹን ጡንቻዎች በመገተር ።

«አዎ ።»
«አቃጥለው ።»
ተከስተ እንደተነገረው አደረገ ።

ሥዕላይ ወረቀቷ ተቃጥላ ዓመድ እስክትሆን ድረስ ጠበቀና፣ «ከዚች ደቂቃ ጀምሮ ትእዛዝ የምትቀበሉት ከኔ ነው ። ቃሌ ሕግ ይሆናል» አላቸው ።

«ሥዕላይ ባራኺን ትንሽ እንኳ ከተጠራጠራችሁት ፡ ምንም ዓይነት የበላይ አካል ውሣኔ ሳትጠብቁ ባለበት ፡ በምንም ሁኔታ ፣ እንድታጠፉት» በቢሮክራሲ ተፈርሞ ከአዲስ አበባ የተላለፈውን ትእዛዝ በልቡ ቃስታወሰና ዝም አለ ። ትእዛዙን አውጥቶ ሊያቃጥለው አስቦ ነበር ። ሥዕላይ ይነቃብኛል ብሎ ፈራ ። ከሌላ በኩል የቢሮክራሲ ትእዛዝ አስገረመው ። «ቢሮክ ራሲ ረጅም ይሁን አጭር ፡ ቀይ ይሁን ጥቁር ፡ ወጣት ይሁን ሽማግሌ የሚያውቀው ነገር የለም ። ትእዛዙ ብቻ ይደርሰዋል ። አራቱ ሰዎች ምስጢራዊ አስተያየት ተያዩ ። እሳት! አመድ!

ተከስተ ገብራይ በሥዕላይ ላይ ለመወጣት የሚፈልገው የቆየ ቂም ነበረው ። አሁን ፊቱ ቆሞ ፣ ጀርባውን ሰጥቶት ሲመ ለከተው ውስጡ ተዳፍኖ የቆየው ጥላቻ ተቀሰቀሰበት ። ጥላቻው ልቡ ውስጥ ነፍስ ሲዘራ ተሰማው ። አቤት! እንዴት ይጠላው ነበር ። ሥዕላይ ሕይወቱን በሙሉ ጓደኞቹን በጉልበቱ ሲያስፈ ራራና ሲያጠቃ የኖረ ሰው ነበር።«እህ አሁን ደግሞ ይኸው ተመ ልሶ መጥቷል — ጉልበቱን ሊያሳየኝ ።»አለ ተከስተ ። ሥዕላይ ነበር በጉልበት አስፈራርቶ የማኅበር ሸአቴ አባል እንዲሆን ያደረገው ። እሱ በሚመራው ጎዋስ ውስጥ ነበር ተመድቦ የሚ ሠራው ። እና ፣ ራሱን ሲያጋልጥ ሌሎችን በጉልበቱና ባፉ እያ ስፈራራ የሚያጋፍጥ ፣ ራሱን በጣም የሚወድ ሰው እንደነበረ በምሬት አስታወሰ ። ግን የጥላቻው ዋና ምክንያት የሥዕላይ ራሱን ከማንም አብልጦ የመውደድ ነገር አልነበረም ። ካላበዪ በስተቀር ማን ራሱን ይጠላል! የለም ። የጥላቻው ዋና ምክንያት ሌላ ነበር ። ከጊዜ በኋላ ሥዕላይ በኃይለ ሥላሴ መንግሥት ተሹሞ ያውራጃ ገዢ ይሆናል — ዕድሜ ላባቱ ። አባቱ ፣ ደጃዝማች በራኺየ ፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን ባይሰጣቸውም በመንግሥት እና በሕዝብ ዘንድ ተሰሚነትና አክብሮት ነበራቸው ። በጣም ግለኛ አስተሳሰብ ስለነበራቸው ለደስሙላ ደጃዝማች ከመባል ሌላ ሥልጣን አልተሰጣቸውም ። ለማንኛውም ነገር ፣ ሥዕላይ ባባቱ ተጽዕኖ ከተሾመ በኋላ ፣ እሱ ይመራው በነበረው ማኅበር

ሽእቴ ጎዋስ ውስጥ ከእሱ ጋር ይሠሩ የነበሩትን ስድስት ወጣቶች አጋልጦ ያሳሰራቸዋል ።

ከስድስቱ ውስጥ አንዱ ተከስተ ገብሬይ ነበር ። ሰባት ዓመት ይፈረድበታል ። አንዳንዶቹ በወገን ብዛትና ብርታት ፍር ዳቸውን ሳይጨርሱ በነጻ ይለቀቃሉ ። ተከስተ ግን ወገን የሌለው ከድሃ ቤተሰብ የወጣ በመሆኑ ሰባቱን ዓመት ጠጥቶ ይወጣል ። ያለትምህርት ፣ ያለወገን ፣ ያለሥራ የት ይደረሳል? የት ይኬዳል? ሰው አንድ ነገር ሠርቶ መኖር አለበት ። የእሥር ቤት ኑሮ መን ፈሱን አሻክሮታል ፣ ሰውነቱን አጠንክሮታል ፣ ልቡን አጠጥሮ ጨካኝ አድርጎታል ። ሕይወት ርካሽ መሆኗን አይቷል ። የሰው ልጅ ልቅሶ ፣ ዋይታ ፣ ጩኸትና ስቃይ አሁን ምንም አይደሉም ። ለሱ እነዚህ ሁሉ ተራ ነገሮች ናቸው ። ሁሉንም በእስር ቤት ቤት አይቷቸዋል ። ከእሥር ቤት እንደወጣ ፣ ቀን ጨለማ ሆኖ በት በሚደናበርበት ወቅት እሰሁልህ ብሎት ሥራ የሰጠው ማን ነበር? ሻዕቢያ ነበረች ። የሚያውቀውና የተዘጋጀለት ቀላል ሥራ ነበር — ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ ። ‘ለመኖር መግደል’— ከዚያ ወዲህ ተግባራዊ መፈክሩ ሆኗል — ዕድሜ ለሥዕላይ ባራኺ ። ቀና ብሎ በሲጃራ ጢስ ውስጥ በቃየል ዓይን ተመለከተው ። ብድር በምድር...... ትንሽ ጥርጣሬ...... እስቀዋለሁ! አለ ። ለእሱ መግደል ነው ። ማሳቅ ማለት በዕድሜው ብዙ ሰዎች አስቋል ።

ሥዕላይ ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠርጎ ፣ «አሁን ስላድራጎቴ ላስረዳ....» ሲል ተከስተ በልቡ ያሰበውን የሰማበት ይመስል ደነገጠ ። ሥዕላይ ቀጠለ «ፈያሜታ ጊላይን የወሰድኳት በበቂ ምክንያት ነው ። ማን እንደሆነች አጥቼ አይደለም ። ከብዙ ጊዜ ጀምሮ አውቃታለሁ — ከትምህርት ቤት ጀምሮ ። ያው የድሮዋ ፊያሜታ ጊላይ ናት ። አልተለወጠችም ። ዕድሜ አልለወጣ ትም ። ከጨዋታና ሳቅ ሌላ አታውቅም ። ከሚያስደስታት ሰው ጋር ለመውጣት ግድ የላትም ። ሰው ምን ቢያስደስታት ደግሞ ፣ ሁለት ፣ ሦስት ቀን ከፊቷ ዞር ካለ ትረሳዋለች ። እስከዚህ ድረስ ነው የማውቃት ።

«ለማንኛውም ነገር ደስ ስላለችኝ ወይም ስለፈለኳት አይደለም ዛሬ ያወጣኋት ። እንዳልኩት በቂ ምክንያት ነበረኝ ። እንደኛ ፣ ሠላማዊና ዘላቂ ዓላማ ያለኝ ለማስመሰል ነበር ። እንደ

እሷ ያለች ቀንጆ ልጅ ይዞ ከመውጣት የበለጠ ምን የሚያሰኝን ነገር ይኖራል? ሁለተኛ ፣ የብዙ ጊዜ እሮኞዬ ናት ፣ ዛሬ ከእሷ ጋር ነው የማድረው ፣ በጣም ተነፋፍቀናል በማለት ፣ እሷ ቤት የማድር አስመስዬ ማንም ሳይጠረጥረኝ እዚህ ለመምጣት ጥሩ እድል እንዳገኝ ነበር ። ለዚህ ነበር ማይተመናይ እንድትጠብ ቀኝ ያደረግሁት ። መኪናዬ ከእሷ ቤት በር ላይ ነው የቆመችው ። ሶስተኛ ፣ ከአድጊዎቹ መካከል ደስ ያላትን መርጣ እንድትይዝ ለማድረግ ነበር ። ወደፊት ለሚጠብቀን ሥራ ትጠቅመናለች በማለት ፣ የኰሎኔል ቃሪኩ ወዳጅ መሆኗን አላወኩም ። ግን የሚያሳዝነው ነገር ቃላላቅ አድጊዎችን ትታ ፣ ሄዳ የወደቀችው አንድ ጺጋዬ የሚባል ተራ የቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ላይ ነው.....» ሲል፣

ዮሐንስ አስፍሐ የተባለው ረጃም ፣ ቀጭን ፣ ባለአፍሮ ወጣት ፣ «ማን አልከው?» ብሎ ጠየቀው ።

ድምጹም እንደ ሰውነቱ ቀጭን ነው ። ጆሮ ይወጋል ።
«ጺጋዬ ኃይለማርያም» አለ ሥዕላይ ።
«ዛሬ ማታ ያስተላለፈውን ፕሮግራም አይተሀል?» እንዴ ገና ዮሐንስ ነበር ።
«አዎ ።»
«አደገኛ ሰው ነው ። ደህና አድርጎ ነው የመታን ። በዚሁ ከቀጠለ ሕዝቡን ያሸፍትብናል.....» ሲል ፣

ሥዕላይ ተቆጣና ፣ «ሥራችሁን በሚገባ አልሠራችሁም ማለት ነው! ሕዝቡን በይበልጥ ማነሳሳትና ማስቆጣት — አርፎ እንዳይተኛ በአእምሮው ውስጥ ዘላቂና ቋሚ ሽብር መፍጠር አለባችሁ ። ማንም ያለስጋት መኖር የለበትም ። ሠላም የለም ። ከዛሬ ጀምሮ የምናተኩርበት አንዱ ተግባራችን ይህ ይሆናል — ብዳይ! ብዶት!» አለ ።

«ነጥቡን አልያዝክልኝም» አለ ዮሐንስ ።
«የቱን ነጥብ ።»
«ጺጋዬ ተራ ጋዜጠኛ አይደለም ። ለመረጃህ ያህል የቀይ ኮከብ ዘመቻው የፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ኃላፊ ነው.....» ብሎ የጀመረውን ሳይጨርስ ፣ ሥዕላይ አቋረጠውና ፣ «ስለ ኤርትራ ምንም [illegible] ኢስቱ ንገረኝ» አለው ።

«ብዙ ጊዜ እዚህ አገር ተመላልሷል ። ሕዝብ ጋር ይውላል ፤ ሕዝቡን ያነጋግራል ። እና ነገር እንደ ውሻ አሽቶ የማውጣት ችሎታ አለው ። ስለሆነም በሕዝብ ዘንድ ያለው ተደማጭነት ከፍተኛ ነው ። እንደ ሌሎች ጋዜጠኞች ዝም ብሎ የሚቀባጥር ሰው አይደለም ። ዛሬ ማታ ያስተላለፈው ፕሮግራም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው» ብሎት ጉሮሮውን ጠረገና ፤ «አደገኛነቱ በዚህም ብቻ የተወሰነ አይደለም ። ከነገ ጀምሮ ራዲዮ ጣቢያችንን ሕዝብ እንዳይሰማው ለማድረግ አቅዷል ። ምንድነው የሚባለው?......» ብሎ ነገሩን ለማስታወስ ሲሞክር ፤

ሥዕላይ ቀደመውና ፤ «ጃሚንግ» አለው ።

«አዎ ጃም ሊያደርገው ነው......»

«ይህን መረጃ ከየት አገኘኸው?» አለ ሥዕላይ ።

«ሰዎች አሉን ። ጸጋዬ ዛሬ ጧት ስለሰጠው መመሪያ ሙሉ መረጃ አለኝ ። በጣም አደገኛ ሰው ነው» አለ ።

ተከስተ ቀና ብሎ ፤ አደገኛ ከሆነ ቶሎ ማሳቅ ነው» አለ ።

ሥዕላይ በንቀት ተከስተን ተመልክቶ ሲያበቃ ፤ «አንተ ለሁሉም ነገር ከማሳቅ ሌላ የምታውቀው መፍትሔ የለህም!» አለው ።

ተከስተ በጥላቻ ዓይን እየተመለከተው ፤ «የሞተ ሰው አይ ትጻም ። ችግርን ከሥሩ ለማጥፋት ከማሳቅ የተሻለ መፍትሔ የለም» አለው ።

ሥዕላይ በመልሱ ቢናደድም መልስ አልሰጠውም ። ወደ ዮሐንስ ዞር ብሎ ፤ «ያገኘኸውን መረጃ ምን ሠራህበት?» በማለት ጠየቀው ።

«እስካሁን ምንም» የሚል መልስ ነበር ያገኘው ።

ሥዕላይ በቁጣ ፊቱ የነበረውን ጠረጴዛ በቡጢ ከመታ በኋላ ፤ «ጅል» ብሎ ሰደበውና ፤ ቀጥሎም ፤ «በእውነት ጅል ነህ ። እንዲህ ዓይነቱን ከባድና ጠቃሚ መረጃ ይዞህ «እስካሁን ምንም» ስትለኝ ይገርመኛል ። ወይም የመረጃው ነብደት አል ገባህ ይሆናል ። የመረጃውን ክብደት መገዘና የማያውቅ ሰው መረጃ ቢሰበስብ ምን ፋይዳ አለው? እንደ ሁኔታው አጥቅም ላይ ካላዋሉት በቀር ። ያ ሬዲዮ ለሕልውናችን በጣም አስፈላጊ

መሆኑን ታውቃለህ? ወይስ አታውቅም? በተለይም ባሁኑ ወቅት። ያ ራዲዮ ከታፈነ ሕዝቡ መኖራችንን በምን ያውቅልናል? እንቅስቃሴአችንን በምን ይረዳልናል ብለህ ትገምታለህ? የዚያ ራዲዮ መታፈን የኛ ድምጽ መታፈን ማለት ብቻ ሳይሆን ፣ ሕዝቡን ተስፋ የሚያስቆርጥ ይሆናል ። የሚያስከትለው የፖለቲካ ጉዳት እስከዚህ ድረስ ነው» በማለት ንግግር ካደረገለት በኋላ ፣ «ብል አሁን ፣ አሁን ነው የምልህ ፣ እንዴት እንደምታደርገው የኔ ጉዳይ አይደለም ። ብቻ መረጃውን አሁን ለቢሮክራሲ አስተላልፍለት ። እና ፣ በሁለት ወይም ከተቻለ በሶስት 'ሚትር ባንድ' ለመጠቀም እንዲዘጋጁ ንገረው ። ታፈነ ብለው በምንም ሁኔታ ተስፋ መቁረጥ የለባቸውም ፣ እንዲዘጋጁ ንገረው ። ለነዚህ አድጊዎች ትምህርት መስጠት አለብን» አለው ።

ዮሐንስ ፈዞ ቆሞ ቀረ ።
«ሰምተኸኛል!?» አለው ሥዕላይ ።

ተከስቶ የሲጃራ ጢስ እየተፋ ፣ «ሻሸመኔ ላይ ይተከላል የተባለው የራዲዮ መገናኛ ሥራ ቢያልቅ ከናቅፋ ጋር በቀጥታ ተገናኝተን እንነግራቸው ነበር» አለው ሥዕላይን ።

«ቢሮክራሲ ለንፎእል» አለው ።
«ታውቀዋለህ?፡

«አዎ አውቀዋለሁ ። ቢሮክራሲ ማን እንደሆነ የምናውቅ ሰዎች በቁጥር ከሦስት አንበልጥም ። እና እንዲህ መሆንም አለበት ። ተዝረከርከናል ። ከጀብሐ መማር አለብን ። አንድን ጎዋስ መረ ከሁለት ሰዎች በላይ ሊያውቁት አይገባም» አለው ።

«ምን ይመስላል?»

«ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?»

«ሽማግሌ ፣ ጠይም ፣ ቀጭን ፣ ብዙ ሲጃራ የሚያጨስ?....»

«ኖ ! ወጣት ፣ ሙልክ ሙልኪም ፣ ቀይ ፣ የማይጠጣ — የማያጨስ..... ይበቀሀል» አለው ።

ዮሐንስ ወደ አንድ ክፍል እንደገባ ፣ ሥዕላይ በረጂሙ ተንፈሰና ፣

«የሚጠጣ ነገር የላችሁም? ጉሮሮዬ ደረቀ» አለ ።

ግርማይ የሚባለው ረጅም ወጣት አንድ ብርጭቆ ውስኪ በደንኅሉ ቀላቅሎ ሰጠው ። ግርማይ የኮድ ስሙ ነው እንጂ የእውነት ስም አይደለም ። ሥዕላይ ከውስኪው በጣም ተጎነጨለትና «ጥሩ ነው ። አሁን ወደ ዋናው ሥራችን እንመለስ ። የመጣሁት ለትልቅ ሥራ ነው ። ግዳጁ — 'አርማይ' ይባላል ።ከዛሬ ጀምሮ በዚህ ኮድ ስም ነው የምታውቁኝ — አርማይ!» አላቸውና ከውስኪው እንደገና ተጎነጨ ። ትናንሽ አይኖቹ በስሜት ያበሩ ጀመር ። ድንገት ጠረጴዛው ላይ የነበረው ቀይ መብራት ብልጭ ድርግም ይል ጀመር ።

«ምንድን ነው?» አለ ሥዕላይ ደንግጦ ።
«አደገኛ ሰዎች አሉ ማለት ነው» አለ ተከስተ ።
«ምን ዓይነት አደገኛ ሰዎች?»

«የሴኩሪቲ ሰዎች ። አትስጋ ። ቀጥል ። ጥሩ ቡናችንን ፍለጋ ነው የሚመጡት ። በከተማው ውስጥ ግሩም ቡና ያለን እኛ ነን» አለው ። ተከስተ

ሥዕላይ በእርይታ ተንፈሰና ፣ «የአርማይ ዓላማና ግብ ፣ እንደኛ በዚህ በስድስተኛው ዙር ጦርነት ናቅፋ ላይ የማይሳካልን ሆኖ ከታየ ፣ እዚህ የሚገኙትን ከፍተኛ አድኂዎችና ተባባሪዎቻቸውን በሙሉ ባሉበት ለመደምሰስ ነው ፣ ሁለተኛ ፣ የኢኮኖሚ ግንባታ ሥራቸው እንዳይሳካ «ሳቦታጅ» ማድረግ ይሆናል ። ሦስተኛው ፣ በሕዝቡ ዘንድ ሥነ ልቦናዊ ሽብር መፍጠር ። አራተኛውና የመጨረሻው ተልእኮአችን ያው የተለመደውን የኢንተሌጀንስ ሥራችንን በተጠናከረ ሁኔታ ማካሄድ ይሆናል ። የምጽአት ቀን እየተቃረበ ነው» አለ ።

ግርማይ ፣ «እስከዚህ ድረስ ያሰጋል?» ብሎ ጠየቀው ።

«አዎ ፣ በአራት ግንባር ተከበናል ። በቃሮራ ፣ በአፍአበት ፣ በከርከበት ፣ በአልጌና ። ከከረን ተነስቶ ወደ ላይ የሚጓዝም ጦር አለ ። ከተፈጥሮአዊ ምሽጋችን ሌላ ኃይልና ጥንካሬ የለንም።እሱም ቢሆን የጊዜ ጉዳይ ነው ።በዚህ በኩል ገሀነብ እሳት ከሌፈጠርንባቸው ያሁኑ አድኂዎች የድሮዎቹ ዓይነት አድኂዎች አይደሉም ። ከገጸ ምድር ያጠፉናል ፣ ስለ ኢትዮጵያ ሠራዊት

የደረሰን መረጃ ትክክል አይደለም ። ለራዛ ዘመቻ ከተሰለፈው የገበሬ ሠራዊት ምንም አይሻሉም ተብሎ ነው የተነገረን ። እና ስትራተጂያችን በዚህ ላይ የተመሠረተ ነበር ። ወደ ናቅፋ ተሰባ ስበው እንዲመጡ አድርገን እዚያ ላይ ከመታናቸው በኋላ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከኋላ እየነዳናቸው ልንመጣ ነበር ። አሁን ሳየው ስህተት ነው ። የኢትዮጵያ ሠራዊት የሚበገር ኃይል ሆኖ አላገኘሁትም ።» አለውና ውስኪውን አንስቶ በንዴት ጨለጠው ።

፯

ተከስተ ሲጃራውን አቦነነና ፣ «የእነሱ 15ኛ ሻለቃ በናቅፋ ለሰባት ወር ከተዋጋን እኛ በዚያ ምድር ላይ ሰባት ዓመት ለመዋጋት የማንችልበት ምክንያት የለም ። እኛ ሶማሊዎች መሰልናቸው እንዴ በሦስት ወር ዘመቻ ሊደመስሱን የተነሱት፣ ፖሊቲካውን ወደ ጎን እንተውና እኛም እንደ እነሱ ኢትዮጵያውያን ነን ። በእነሱ ውስጥ ያለው ወኔና እልክ እኛም ዘንድ አለ» አለው ።

«አዎ» አለ ሥዕላይ — «ግን ችግሩ አሁን እነሱ ተጠናክረዋል ። እኛ በእርስ በርስ ጦርነት ተዳክመናል ። ከውጭ የምናገኘውም ድጋፍ እምብዛም ነው ።» ሥዕላይ ሲጃራ በብዛት ያጨሳል ። ግን በሲጃራ ብቻ አይረካም ። ሱረትም ባፍንጫው ቶሎ ቶሎ ይስባል ። ትምባሆም ይጉርሳል ። መቸም የበረሀ ኑሮ..... የማያስይዘው ሱስና በሽታ የለም ። ሌላ ውስኪ ተቀዳለት ። ሌላ ሲጃራ አቀጣጠለ ። ሱረቱን ሳበ ። ትምባሆውን ጉረሰ ። ስለ ጉበት በሽታው አማረረ ። በረሽኛ ሆኖ የጉበት በሽታ የሌለበት ሰው ከአሥር ሦስት አይገኝም ። እና ንግግሩን ቀጠለ — «ስዚህ ሥራ ራሱን የቻለ ሠራዊት ያስፈልገናል ። ዋናው ነገር አሁን ድርጅታዊ ሥራ ነው ። እና እኔ የተላኩትም ለዚህ ነው ። በዚህ በኩል ኀሀነባዊ ሽብር እንፈጥርላቸዋለን ። ችግሩ ሻዕቢያ እንደ ጀብሐ በከተሞች ሽብር የማካሔድ ልምድ የላትም ። ሀ ብለን መጀመርና ማደራጀት ይኖርብናል ። ጊዜ የለንም ። በጥቂት ቀኖች ውስጥ ማጥቃት ሳይጀምሩ አይቀሩም ። ማጥቃት የሚጀምሩበትን እርግጠኛውን ቀን ማወቅ አለብን.....» ሲል —

ተከስተ ንግግሩን አቋረጠውና ፣ «እናውቃለን ። መረጃውን አግኝተናል ። የካቲት ወር መጀመሪያው ሣምንት ላይ ሳይሆን አይቀርም ። ምናልባት የካቲት ፱ ወይም 10 ይሆናል የሚል ግምት አለ» አለው ።

«እናንተ» አለ ሥዕላይ ።
«መረጃውን አስተላልፈናል» አለው ።
«መልካም» አለና ሥዕላይ—«አሁን ለማወቅ የምፈልገው ከከተማው ውስጥ ስንት ሰዎች ፥ ምን ዓይነት ኃይል እንዳለን ነው?»
«የሰው ችግር የለንም ።»
«ሒሳብ?»
«ትልቁ ችግራችን ገንዘብና መሣሪያ ነው ።»

ሥዕላይ ደረቱን ነፋቶ ፥ በሁለቱም በኩል ችግር የለም ። አንድ ሚሊዮን ብር በቅድሚያ ለአርማይ ተመድቧል ። መሣሪያም እንደ ልብ ነው ። ይልቅ ዋናው ችግር መሣሪያዎቹን እንዴት እንደምናስገባ ነው ። አሁን ዘዴ ፥ ጥበብና ችሎታችንን የሚጠይቀው ይህ ይሆናል» አላቸው ።

ሁሉም ባሳብ ተውጠው ተቀመጡ ። ከባድ ዝምታ ቤቱ ላይ ወደቀ ።

ሥዕላይ ጥርሱን ነክሶ ፥ «መሣሪያዎችን እንዴት እንደምናስገባ በምናስብበት ጊዜ ፥ እነማንን መደምሰስ እንዳለብን ማወቅ ይኖርብናል ። ማንን? የት? እንዴት? መቼ? በምን? ዝርዝር ፕላን እፈልጋለሁ ። እና ኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይንና ሻለቃ ተክላይ ዘድንግልን በመጀመሪያ ያዝልኝ.....»ሲል —

ተክለተ ገብራይ የተክላይን ስም ሲሰማ ድንገት በጥፊ እንደተመታ ሰው ክው ብሎ ቀና አለ ።

«ምነው?» አለው ሥዕላይ ።
ተክለተ መልስ አልሰጠውም ፥ ዝም ብሎ ቀረ ።

«ይገባኛል» አለ ሥዕላይ — «የእሥር ቤት ጓደኞች ነበራችሁ ። ለዚሁ ደግሞ መወቀስ ያለበት ሰው እኔ ነኝ መሰለኝ፣ ስላለፈ ታሪክ ጊዜ ባናጠፋ ጥሩ ነው ። ሰው ወደ ኋላ አይኖርም ። እኔና አንተን ታሪክና ጊዜ ባንድ ግንባር ተክላይን በሌላ በኩል አድርጎናል ። አደገኛ ሰው ስለሆነ መሳቅ አለበት ።»

ተከስተ ራሱን በእምቢታ ነቀነቀና ፣ «ለጊዜው መኖሩ ይጠቅመናል ። ጓደኛዬ ስለሆነ በእሱ ከለላ ነው የምኖረው ። በእሱ ምክንያት የሚጠራጠረኝ ሰው የለም ። አብረን እንውላለን ፣ እን በላለን ፣ እንጠጣለን ። ጥያቄ አልጠየቅም ። ከድርጊቱና ከንቅናቄው ብዙ መረጃ አገኛለሁ ። እሱን መግደል ለኔ ችግር አይደለም ። ከሞቱ ይልቅ መኖሩ ይጠቅመናል ብዬ ነው ። በእሱ የተነሳ ቡና ቤታችን የሕዝብ ደኅንነት ሰዎች መዋያ ሆኗል ።

«ጊዜው ሲደርስ መሳቅ አለበት!» አለ ሥዕላይ በቁጣ ። «ካልክ ጥሩ ችግር የለም......»

«በተጨማሪ የኰሎኔል በትሩ ተሰማን ፣ የሰለሞን በትረንና የጸጋዬ ኃይለማርያምን ስም ያዝልኝ ። እና የከሐዲ ወዶገቦችን የተሟላ ሊስት በስቸኳይ እፈልጋለሁ ። እና ሊተባበሩን የሚችሉትን ሰዎች ስምና ሁኔታ ። ከላይ እስከታች ። ሲቪልና ወታደር ከውስጥ ድረስ ዘልቀን መግባት መቻል አለብን ።አሁን ሥራ እንጀምር ። እርማይ» አለ ።

ኮቱን አወለቀ ። የሸሚዙን እጅጊዎች ወደላይ ሰበሰበ ። ተከስተ ፈገግ አለ ። የሚያስቃቸው ብዙ ሰዎች ፊቱ ተደቅነው ፣ የአሥመራ መንገዶች በሙታን ፈገግታ ተሞልተው ይታዩት ነበር ። ብዙ ፋይሎች — የኢሠፓአኮ ተጠሪዎች — የመንግሥት ባለሥልጣኖች — ከፍተኛ መኰንኖች — የሕዝብ ደህንነት ሰዎች — የከፍተኛና የቀበሌ መሪዎች ፣ እና ሊተባበሩ የሚችሉ ሠላማዊና ወታደራዊ ግለሰቦችን ፋይል...... ወዘተ— እንደ እብድ እየሳቀ አገላበጠ ።

# መንገዶች ሁሉ
# ወደ አሥመራ ያመራሉ

## ምዕራፍ ሁለት

«ጓድ ጸጋዬ ፣ ቴሌፎን ካዲሳባ» አለችኝ ረዛን ።

ጸሐፊዬ አለቃዬ ልትሆን ምንም አልቀራትም ። በኔ ስም ፣ እኔንም ፣ ሁሉንም ታዛለች ።

እየተነጫነጭኩ ቴሌፎኑን ተቀበልኩና «ማን ልበል?» አልኩ ።

«ምነው ተቆጣህ?» አለችኝ ሮማን ሀለተወርቅ ከአዲስ አበባ ።

ሰሞኑን ስልክ አድርጌላት አላውቅም ። ሴቶች መቸም ጥሎባቸው ፣ ላንድ ሰሞን ቀርቶ ላንድ ቀንም ባጋጣሚ ዝም ካሏቸው ተንቀው የተረሱ ስለሚመስላቸው ያኮርፋሉ ። ዘላለም ተንከባከቡን የሚሉ ፍጡራን ናቸው ። ቁጣዋን ፈርቼ ድምፄን ዝቅና ለስለስ አደረኩና ፣ «አ! ሮሚዬ! ደህና ነሽ? ተቆጣሁ እንዴ?» አልኳት ።

«እንደ መብረቅ አንባረቅህብኝ እንጂ......»

«ምን ላድርግ እባክሽ? አለቆቼ ካዲሳባ በየደቂቃው እየደወሉ ይጨቀጭቁኛል ። እዚያ ሆነው እዚህ ሊያዙኝ ይፈልጋሉ ። ሥራቸውን የቀማኋቸው እየመሰላቸው ሆነ ብለው ሊያበሳጩኝ የሚፈልጉም አሉ ። ደህና ነሽ?» አልኳት የእጅ ሰዓቴን እየተመለከትኩ ። ጊዜ አልነበረኝም ። ሥራ አንገቴ ድረስ ውጦኛል ። ታሪካዊው የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ጉባዔ የሚከፈትበት አጥቢያ ነበር ። ሰው ሁሉ አብዷል ። አሥመራ ተደበላልቃለች ። ድብልቅልቁ ወጥቷል ። ድንገት

የኢትዮጵያ መንገዶች ወደ አሥመራ ማምራት የጀመሩ ይመስላሉ ። የማይታይ የሰው ዓይነት የለም ። ከመላ ኢትዮጵያ የመጡ የኢ. ሠ ፓ አ ኮ ተወካዮች ፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ፣ ሚኒስትሮች ፣ የጦር አዛዦች ፣ የአብዮታዊ ጦር ተወካዮች ፣ የሕዝባውያን መሪዎችና የልዩ ልዩ ብሔረ ሰቦች አባሎች ፣ የወሎ ፣ የትግራይ ፣ የጎጃም ኪነት ቡድኖች — የሰው ነጭ ይታያል ። የአሥመራ ነዋሪ ሕዝብ ቁጥር ድንገት አብጦ ከተማዋ ልትፈነዳ ደርሳለች ። እኔም በሥራ ውጥረት ልፈነዳ ትንሽ ቀርቶኛል ። ሮማን ስልክ ከያዘች አትለቅም ። በልቤ ትንሽ ጸሎት አደረስኩ ።

«ምነው እንዲህ ጠፋህ ልጄ?»

«አለሁ ። አለሁ ለማለትም አልችልም ። ውጥረት ላይ ነኝ» አልኳት ።

«ዘምባባዎች ጫካ ውስጥ ገብተህ ጠፋህ መሰለኝ! ያሥመራ ሹሩቤዎች እንዴት ናቸው?»

«እንዳፍሽ ባደረገልኝ.....»

«እሱን ተወው ። ስልክ መደወል ማንን ገደለ? ወይስ ስልክ ለመደወል ጊዜ አጣሁ ልትለኝ ነው?» አለችኝ ንጭ ንጭ ባለ ድምጽ ንዝንዝ በሚያደርግ ድምጽ ።

«እውነቴን ነው የምልሽ ፣ ትንፋሽ የለኝም ። እዚህ መጥ መጥተሽ ብታይው ሁሉም ነገር ያበደች ኳስ ሆኗል .....» እንዳልኳት ፣ ለምን እንደሆነ እንጃ ፣ ፊያሜታ ጊላይ ትዝ አለችኝ ። የቤትና የቢሮ ቴሌፎን ቁጥሯን ከወሰድኩ ወር ሊሆነኝ ነው ። እዚህ የደረስኩት ታኅሣሥ 19 ቀን ሲሆን ፣ ያገኘኋትም ያን ቀን ምሽት ላይ ነበር ። ከፊት የነበረውን የቀን መቁጠሪያ ስመለከት ጥር 16 ቀን ይላል ። ጊዜው እንዴት ይበራል? አልኩ ። አልደወልኩላትም ። እሷም እስካሁን ረስታኝ ይሆናል ብዬ ገዛም አልኩ ።

«ምነው ዘጋሽኝ ልጄ?»

«አለሁ ። አዲሳባችን እንዴት ናት?»

«ጭር ብላለች.....»

«እስሁ አለሁ የሚለው ሁሉ እዚህ ስለመጣ ይሆናል.....»

«እኔ ጨልሞብኛል.....»

«ይግረምሽና እኔ ያግጥ ቀኑ ሲመሽና ሲነጋ አይታወቅኝም ። ይሮጣል ። መሮጡስ ባልከፋም ነበር ። ቀኑ እንዲህ ከፈጠነ ሦስት ወር ነገ ናት ።»

«አዬ ጂጋዬ ። ረስተኸኛል ። እኔ እንጃ ልቤ ፈርቷል.....»

«ተይ እባክሽ ። ይልቅ የረሳሁት ራሴን ነው ። ቀይ ኮከብ ዘመቻ ከሚሉት ጫካ ውስጥ ገብቼ ጠፍቼለሁ ። አይዞሽ ሮሚ። ራሴን ባስታወስኩ ቁጥር ልቤ ካንቺ ጋር ነው ።»

«እሱን ተወው.....»

«እውነቴን ነው» ብዬ ተገዘትኩላት ። መገዘት ነበረብኝ ። መቸም ሴቶች ሲባሉ ፣ አሥር አሥር ጊዜ ካልማሉላቸውና ካል ተገዘቱላቸው የተወደዱ አይመስላቸውም ። በተለይ ሮማን ጥሎባት የምትወደድ መሆኗን ዘወትር ማረጋገጥ ትወዳለች ። በተፈጥሮ በጣም ኩሩ ነች።ተወዳ የምትከበርበት ቦታ መገኘት ሞቷ ነው ። ትሞታታለች እንጂ እዚያ አትደርስም ።

«ደህና» አለች ።

«ናፍቂኛለሁ.....»

«እኔም..... አንድ የቴ ፑ ክር ልኬልሀለሁ.....»

«የምን ክር ልጄ?»

«ዘፈን ። ናፍቆቴን የሚገልጽ ። እኔ እስካሁን መቶ ጊዜ ሰምቼው ይሆናል ። እሱኑ ነው ስሰማ ውዬ የማመሸው.....»

እንደገና ሰዓቴን አየሁ ። ጊዜው ይሮጣል ። ባጭሩ እንዳላ ቋርጣት ፈራኋት ። ለቁጣና ለኩርፊያ ትንሽ ጥርጣሬ ይበ ቃታል ። እኗ ሲበቃት ካልዘጋች ፣ ሰው አቻኩሎ ቴሌፎን ሲዘጋባት ፈጽሞ አትወድም ። የማትወደው ነገር ተቆጥሮ አያ ልቅም ። ቴሌፎኑን ቶሎ ብላ እንድትዘጋልኝ የፍቅርን አምላክ በልቤ ተማጸንኩና ፣ «አኬ ። አመሰግናለሁ ። እንደደረሰኝ ወስጄ አዳምጠዋለሁ ። ከዚህ የምትፈልጊው ነገር ካለ እልክ ልሻለሁ ።» አልኳት ።

«ምንም አልፈልግም ። እዚያ ያለ ሹራብ ምናለ? እሱም ኬሻ ነው ፣ አሥመራ ሴትና ሹራብ ነው የሞላው» አለችኝ ።

ባገር ውስጥ የተሠራ ነገር አትወድም ። በ'ሎካል'ነገር ማጌጥ ሞት ይመስላታል ። ምርጫዋ ግሩም ቢሆንም ፣ በዚህ ሁልጊዜ እንጣላለን ።

«ሌላስ?»

«ሌላማ የምፈልገው አንተን ነው ። ይህ ከተማ ሊውጠኝ ደርሷል ። ምንም ደስ አልለኝ ብሏል ። ቶሎ ናልኝ ።»

«እሺ ሮሚዩ ፡፡ ምናምኑን ቶሎ ቶሎ አያይዝር ወዳንቺ ፊትለክ ነው ፡፡»

«ቻውን» አለችኝና ቴሌፎኑን ዘጋችው ፡፡

ቴሌፎኑን እንዳኖርኩ ወደ ፊያሜታ ጊላይ ደውል የሚል ስሜት አደረብኝ ፡፡ ስሜቴን ልገታው ብሞክርም አልሆነልኝም ፡፡ ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ በስልክ ፈልጊያት እንዳጋጣሚ አጥቻ ታለሁ ፡፡ ስልኩን አንስቼ ልደውልላት ስል ጋዜጠኞች ተንጋግ ተው መጡብኝ ፡፡ ሁሉም ቀንዳቸው ቆሟል ፡፡

«ምን ተፈጠረ!?» አልኳቸው ፡፡

ከችግር ሌላ መፍትሔ ይዞልኝ የሚመጣ ሰው መቸም የለም፡፡ ሁሉም ትራንስፖርት ፈላጊዎች ነበሩ ፡፡ የራዲዮ ሰዎች ወደ ትራክ ቢ መሔድ ይፈልጋሉ ፡፡ አንደኛው የጋዜጠኞች ቡድን በዕዳጋ ሐሙስና በዕዳጋ ዓርቢ ትርኢት የሚያሳዩትን የኪነት ቡድኖች ዜና ሔዶ ለመሥራት ተቻኩሏል ፡፡ ሁለተኛው ቡድን ከአዲስ አበባ የሚመጡትን እንግዶች ሔዶ ለመቀበል ፈልጎ ተሽከርካሪ አጥቶ ተቸግሯል ፡፡ ሁሉም በየአቅጣጫው ለመብረር ይፈልጋል ፡፡

«እንዴት? ካሜራና ቴፕ ተሸክመን ከሰምበል እስከ አከ ሪያ በእግራችን እየሮጥን እንድንሠራ ነው የሚፈለገው!? ክንፍ የለን እንበር ፣ ባለሥልጣን አይደለን መኪና አይሰጠን ፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ እንደ ጨው በሁሉም ቦታ እንፈለጋለን ፡፡ በጊዜ ሳንደርስ ስንቀር እንደ ውሻ እንሰደባለን ፡፡ ዛሬ ፣ ትንሹም ትልቁም ስብሰባ ቲቪ ካሜራ ካልመጣ አይንቀሳቀስም ፡፡ ዘፋኙ አይዘፍንም ፡፡ ተናጋሪው አይናገርም ፡፡ ሰብሳቢው ስብሰባውን አይከፍትም ፡፡ እግዜር አይደለን ሁሉም ቦታ ባንድ ጊዜ ልንገኝ አንችል ፡፡ በዚህ ሁኔታ የዘመቻውን ታሪክ ቀርጸን ለማስቀረት አንችልም ፡፡ እኔ ኋላ በኃላፊነት አልጠየቅበትም ፡፡ እዚህ ሂዱ ፣ እዚያ ኑ እያሉ ትዕዛዝ መስጠት ብቻ አይበቃም ፡፡ እኛም ሰዎች ነን!» አለና የፊልም ማንሻ ካሜራውን መሰሉ ላይ ጣለው ፡፡

«ከመሣሪያህ ጋር ጥል የለህም ፡፡ እንዲህ ዓይነት ጠባይ ማየት አልፈልግም ፡፡ በል አሁን መሣሪያህን አንሳ» አልኩት ፡፡

የጠየቀው ነገር ሳይፈጸም መጣሪያውን ዳግመኛ ላለማንሳት ወስኖ ነበር የጣለው ። ኩራት ሲተናነቀው ከቆየ በኋላ ቀስ ብሎ ከሚራውን አነሳ ። ባያነሳ ኖሮ ምን እንደማደርግ አላውቅም ነበር ። በእፎይታ ተነፈስኩና ረዛን ከክፍለ ሀገሩ የትራንስፖርት አገልግሎት ማዕከል ጋር እንድታገናኘኝ አደረኩ ። ግራዝማች ላይ ሞሁኩባቸው ። ያገሩ ባለሥልጣን ሁሉ ግራዝማች ፣ ቀኛዝ ማች ፣ ፊታውራሪ ፣ ደጃዝማች ፣ ብላታ ፣ ባሻ ብቻ ነው ።

«ምን ላድርግ ተቸግሬ ነው» አሉኝ ።

«የለም'ኮ ጓድ...... አ...... ግራዝማች ። የሚዲያን ጠባይ የተረ ዱት አልመሰለኝም ፣ ፍጥነት ይጠይቃል ። የማያቋርጥ እንቅስ ቃሴ ነው ። እኛ ለነገ ወይም ለኋላ የምንለው ነገር የለም ። አሁን ሶስት መኪናዎች ባስቸኳይ እፈልጋለሁ ። በመኪና ችግር ምክ ንያት ሥራ ሳይሠራ ቢቀር ኋላ በኃላፊነት የሚጠየቀው ሰው ይጠየቃል» አልኳቸው ።

ሶስት መኪናዎች ወዲያውኑ ሊልኩልኝ ተስማሙ ። ያገሩ ሰው መቸም ሥልጣን ይወዳል ፣ ሥልጣንም ያከብራል ።

«ጓዶች ሌላ ችግር አለ?...... እሺ ። ጥያቄ ማቅረብ ብቻ ሳይ ሆን ችግሩንም አብረን ማየት አለብን ። ትንሽ ትዕግሥት ያስፈ ልገናል» አልኳቸውና ሸኘኋቸው ። እንጋገሬ አላሳመናቸውም ።

እነሱ እንደወጡ ቴሌፎኑን አንስቼ ወደ ፊያሚታ ጊላይ ደወልኩ ። ከሦስት ጥሪ በኋላ ቴሌፎኑን አነሳች ።

«ሄ — ሎ ?» አለች እንደመዝፈን እያለች ።
«አበይ ኢዩ!»
የመሥሪያ ቤቷን አድራሻ ሰጠችኝ ።
«መን ክብል!»
«ፊያሜታ......»
«ሰሚናዊት ጽብቐቲ ፣ ከመይ ቀኒ...... ። ጸጋዬ ኃይለማርያም ዝብሐል ትዝከርን 'ዶ?'»
«አንቴ እሂዳአ? የማን አጋሜ ነው የሚያነጋግረኝ ብዬ ነበር ።» አለችኝ ። ጠጉሯን እየነሰነሰች ስትናገር በዓይነ ሕሊናዬ ታየችኝ ።

«እንዴት?» አልኳት ።

«እንደነሱ ነዋ የምትነጋገረው» አለች ስቃ ።

«ይኸ እንኳ የሐማሴን ጥላቻ ነው......»

«ደህና ነህ? ምነው ጠፋህ? ማን በቲቪ ብዙ ጊዜ እየሀለሁ ። አወይ ውሸት!» አለችና እንደገና ሳቀች ።

«እየበላሽ ነው እንዴ የምታነጋግሪኝ?»

«ጥርሴን እየፋቅሁ ነው......»

«ቢሮ ውስጥ?» አልኳት ውብ ጥርሷ መጥተው ፊቴ እየተ ደቀኑ ። እዚህ አገር መቸም ሴቱ ፣ ወንዱ ፣ ሽማግሌው ፣ እንደ ጥርስ የቀራት አሮጊትም ብትሆን ፣ ሁሉም በየመንገዱ ጥርሱን እየፋቀ መሔድ ይወዳል ። ቀን ማታ አይሉም ። ቦታ አይመር ጡም፡የጥርስ መፋቂያሻጩ ነጋዴ ቁጥር ብዛትም ያንኑ ያህል ነው።

«እወ»

«እወ» አልኩ የእሷን ድምጽ ቀድቼ ። ኛው የምትል ትመ ስላለች ።

«ሐድ! አባቴ ይሙት ። እኔ አዳሉ ነው የምለው እንቴ» አለችኝ ።

«የስድብ መዓት አወረድሽብኝ አይደለም እንዴ? ውሸታም ደደብ እያልሽ»

«ጣፋጭ ደደብ ነህ.....»

«ሥዕላይ በራኺ እንዴት ነው?» አልኳት ።

«እውይ አልሰማህም እንዴ? ይህን ካልሰማህ ምን ዓይነት ጋዜጠኛ ነህ? አባቴ ይሙት ። ደደብ ጋዜጠኛ ። እፊታችን እሁድ ልንጋባ ነው ። እንዲያውም ከአቡ ዳቢ ያዘዘኩት 'ቬሎ' ስላልደረሰ ነው እንጂ ሠርጋችን ባለፈው እሁድ ይሆን ነበር» አለችኝ እየሳቀች ።

«አቡ ዳቢ መቸም የምትኮበልሉበትም ፣ ዕቃ የምታስመ ጡበትም ገነታችሁ ሆኗል ። ለማንኛውም ነገር እንኳን ደስ አላችሁ ። ታዲያ ለሠርጋችሁ አትርሱኝ ።»

«ሠርጋችንን የት ብናደርገው ይሻላል — እምባሶይራ ወይስ ኒያላ?»

«እንዳቅማችሁ.....»

«እውይ ደደብ ። ውሸቴን ነው እባክህ ። አንዳንዴ ዝም

ብሎ ውሸት ይመጣልኛል ። ውሸታም ነኝ አባቴ ይሙት ። ምን ዓይነት ሴት ነኝ ግን?» አለች ።

«ጣፋጭ ዋሾ!»

ሳቀችና «እሺ! ቀይ ኮከብ አሥመራ እንዴት ይዘሀል?» ብላ ጠየቀችኝ ።

«ተጨባጭ [ሁኔታ] ጨብጦኝ በውበቷ ገና መደሰት አልጀመርኩም....»

«ከተማዋን አጽድተን ስለተቀበልናችሁ ከከተማ ልታስወጡን ነው» አለችኝ እየሳቀች ።

«መቼ እንገናኝ? ትግርኛዬ ዝጓል»

«ምጽዋ ትሔዳለህ?»

«እዎ»

«ለምን እዚያ አንገናኝም? ለምጽዋ ፌስቲቫል ከጓደኞቼ ጋር ለመሔድ አስቤአለሁ ። ምጽዋ ሠርግና መልስ እየሆነ ነው አሉ» አለች ።

«እውነትነ?»

«ምነው ተጠራጠርከኝ?»

«ጣፋጭ ዋሾ ስለሆንሽ ነዋ!»

«እውይ! ደደብ ። አባቴ ይሙት ለመሔድ አስቤአለሁ ። ጉርጉሱም ላይ ፈልገኝ ። አባቴ ይሙት «ባኪኒ» ለብሼ ነው የምመጣው ። ቻው እምበአር ዘሐወይ» ብላ ቴሌፎኑን ዘጋች ። እውነቷን ይሆን ወይስ ውሸቷን? እርግጠኛ አልነበርኩም ። ወይስ በዲፕሎማቲክ ቋንቋ ዞር በል ፡ ገደል ግባ ማለቷ ይሆን? እንዴት አባቷ አድርጋ! ካሁኑ አልክአስያዘችኝ ። ተግደርዳሪ ሴቶች ለምን እልክ እንደሚያስይዙኝ አላውቅም ። የሆነ ሆኖ ስለ ፊያሜታ ጊላይ ብዙ ለማሰብ ጊዜ አላገኘሁም ። ፍሬው ዘሪ ይሁንና ሻለቃ ሥዩም ሠረቀ ብርሀን ተያይዘው ገቡ ። ገና ሲያዩው አስጠሉኝ ። ምንም ጊዜ የለኝም ። ማንም ጊዜ የለውም ። ሁሉም ጊዜ ይሻማል ። ብልጥ የሆነው አንዱ ላይ የሥራ ሸክም ጥሎ ይሮጣል ።

«እሁስ?» አልኳቸው ።

«እንሠራለን ቀን ማታ እንፐስታለን» አለኝ ፍሬው ዘሪሁን። የአሥመራ ከንቲባ የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶታል ። የማያው

ቃት ሠፈርና ተከርችም (ቤከሬቶ) በአ/ሥመራ ከተማ የለችም ። ዓይኑም ፣ ጥርሱም ፣ ፊቱም አንድ ላይ ይስቃል ። አጭር ቁመቱም ፣ ስቆ የሚያስቅ ሆኖ ይሰማል ።

«ምንድነው ደሞ እሱ?» አልኩት ፣ እንፐስታለን ያለው ነገር ጠፍቶኝ ።

«ፓስታ የሚለው ቃል መፐስት ከሚለው የግ/ሥ ዘር የመጣ ነው ። ሲረከም መፐስት ፣ ፐስተ ፣ እንፐስት ይሏል » አለ ።

«ፓስታ ተሰማምቶሀል መሰለኝ?»

ሆዱን ነፍቶ በእጆቹ መታ ፣ መታ አደረገና ፣ የማትወደው ቋንቋውን ስለማታውቅ ነው» አለኝ ።

«የምን ቋንቋ አለው ልጄ?»

«ጣልያንኛ ወይም ጥሩ ትግሪኛ ። ከነዚህ ቋንቋዎች ጋር ሲሆን ይስማማል ። በተለይ ከክልተ ቢኬሪ ነቢት ጋር ሲሆንማ ጽቡቕ እዩ ። ጅሮ ለማዶና! መፐስት ። ፐስተ ። ምግብ ለሥራ ። ማወራረጃው ጠፋ ። ፓስታ በውሀ አይሆንም ። ሙት እውነቴን ነው ። ሆድ ይነፋል ። ፓስታ ውሀ ስትጨምርበት ይባዛ የለም ። ፓስታ በልተህ ውሀ ስትጠጣበት እንደዚያ ይሆናል። ስትፐስት ከሁለት ቢኬሪ ነቢት ጋር ሲሆን ግን ጥሩ ነው ። ይፈጨዋል ። ጣልያን ለብልሐቱ ነው ፓስታ በልቶ ነቢት የሚጠጣው ፓስታ ። ወነቢት — ኤ ኮዛ ፋቻ!» በማለት ቀባጠረብኝ ።

«ጥሩ ቲዎሪ ነው» አልኩት ።

«ሲ ። ማ ኖንቼ ሶልዲ ። ብዘይ ገንዘብ እንታይ ትገብር? ይህ ከተማ ደግሞ ሰላቢ ነው ። ሴቶቹ እምቢ የሚል ቋንቋ አያውቁም ። እኔ ደግሞ ሆዴ አይጨክንም ። ምን ታረገዋለህ? አይደለም እንዴ ጓድ ሥዩም?» አለ ።

«የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነው አሉ ። ገንዘብ ልትጠይቁኝ እንዳልመጣችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ። አሁን ሥራ አለብኝ» አልኳቸው ።

ሥዩም እንደ ቆማጣ ጣቶቹን ቀልምሞ ፣ «በእንዳ ማርያም» አለኝ።

«ማርያም ትርዳአካ» አልኩት ።

«እረ ጋሼ በፈጠረህ ። ሣንቲም የለንም» አለ ፍሬው ፣

የሚስቁትን ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ።

ሰው አንድ ነገር ጠይቆኝ እምቢ ለማለት የማልችል ሞኝ ነኝና ሐያ ብር መዝገቤ ከሰጠኋቸው በኋላ ፡ «እነዚህን ያሥመራ ልጃገረዶች ኤት እና ካራቬል እየወሰዳችሁ ጀላቲ ማስላስ ብትተውኝ ለማኝ አትሆኑም ነበር» አልኳቸው ።

«ከእንግዲህ እንለምንም — አባቴ ይሙት» አለ ሥዩም ።

«እዩ?»

«ስልህ» አለኝ ።

ፍሬው «ጋሼ ሥዩም ደህና ንግድ ጀምሮአል...» ሲል— «ልባርግ!» በማለት ፍሬው እንዳይናገር ሥዩም ሊያስፈራራው ሞከረ ።

ፍሬው የሥዩምን ዛቻ ወደ ጎን ብሎ ፡ «ጋሼ ሙት ፡ ንግድ ጀምሮአል ። ምን የሚያደርግ መሰለህ? አዲሳባ ይደውልና ሴቶቹን ምን የመሰለ ሹራብ ፡ ጫማና ቦርሳ በርካሽ ዋጋ እግኝቼላችኋለሁና እንዳያመልጣችሁ ይላቸዋል ። መቼም የኛ ሴቶች ለጌጥ ሟች ናቸውና ያለ የሌላቸውን ብር መንዝረው ይልካሉ ። ከየሱቁ ርካሽ ሹራቦች ፡ ጫማዎችንና ቦርሳዎችን ያግበሰብስና ትርፉን ወደ ኪስ ። ካንዳንዶቹ እስከ ሠላሳ አርባ ብር ድረስ ያተርፋል ። ከዚህ የበሰጠ አስመጭና ላኪ ምናለ?» ብሎ የሥዩምን ጉድ ነገረኝ ።

ነገሩን ሰምቼ ዝም ለማለትም ሆነ ለመሳቅ አቃተኝ ። ሆኖም ሳቅሁኝ ።

«ይኸ ወስላታ ደግሞ ያደረገውን ልንገርህ» አለ ሥዩም ተራውን —

«እህቱ ከባሏ ጋር እዚህ እንደነበረች መቼም ታውቃለህ ። አሥመራ በወንበዴዎች ያኔ በተከበበችበትና የውስጥ ደጋፊዎቻቸው 'እነዚህን የመሐል አገር ሰዎች በጫማ ነው ወይስ በባዶ እግራቸው ነው ከዚህ የምናስወጣቸው' እያሉ በሚሳለቁበት ጊዜ ፡ እህቱ ከዚህ ጉድ በደህና ያወጣሽን እንደሆነ መቶ ብር እሰጥሻለሁ ብላ ለእንዳ ማርያም ተስላ ነበር ። ይኸውልህ በቀደም

ለት ፍሬው ስዕሉቱን እንዲሰጥላት ገንዘቡን በባንክ ላከችለት ። አጅሬ መቶ ብሩን መንዝሮ ጠጣበት» ብሎ ዝም ሲል—

«ከዚያ በኋላ ምን ሆነ? ቀጥል እንጂ!» አለው ፍሬው ። ሥዩም ዝም ብሎ ቀረ ።

«እኔ ነገሩን ልጨርስልህ ጋሼ» ብሎ ፍሬው ንግግሩን ቀጠለ «የሥዕለት ገንዘቡን ከባንክ ቓወጣሁለት ፣ መቼም ሆዱ በእሱ አይጨክንምና ወስጄ ጋበዝኩት ። አይዞህ ጠጣ አልኩት ። ይህን ያላበው ዝሁል ቢራ አምስቱን ከላፈ በኋላ ዛሬ ገንዘብ ከየት አገኘሽ?» አለኝ ። ገንዘቡ እንዴት እንደተገኘ ታሪኩን ከነገርኩት በኋላ ምን አደረገ መሰለህ? በል ወንድሜ እኔ በሥዕለት ገንዘብ አልጠጣም ። ሠይጣን! ብሎኝ የጠጣበትን አምስት ብር ከፍሎኝ እያማተበ ጥሎኝ ሔደ» አለና አጫወተኝ ።

ሥዩም ደንግጦ እያማተበ ሲወጣ እየታየኝ በጣም ሳቅሁኝ ።

«ይህ ከይሲ የሠራውን ሌላ ጉድ ላጫውትህ» አለ ሥዩም ሰስ ከንፈሮቹን እያሞጠሞጠ — «እንደ መጣን ሰሞን ነው ። ባም ስት ቀን ውስጥ 'ክሪዝ' መታን ። አጅሬ አንድ ቀጠሮ ነበረው ። ገንዘብ ቢፈልግ አጣ ። ሁሉም ብድር ፈላጊ ነበር ። አጅሬ አንድ አሳብ መጣለት ። አንድ ሽማግሌ አሉ — አልቤርጎ ቻው ። ስለ እርጅና ሲጨነቁና ሲያማርሩ ሁልጊዜ ይሰማል ። ታዲያ ያንጊዜ ወደ ፋርማሲ ጎራ ይልና ባላርጂን በሀምሣ ሣንቲም ገዝቶ በልዩ ቧት ያደርግና ያንድ የሆነ ስም ጽፎበት ሲያበቃ ወስዶ ለሽማግሌው ይሰጣቸዋል ። «ምንድን ነውባ» ይሉታል ። «ኃይል የሚሰጥ ነው ። ማታ ማታ ከራት በኋላ ሁለት እንክብል በኪኒቶ ከዋጡ ጎረምሣ ምስጋን ይጣ ። አንድ የማውቀው ጣልያን ሐኪም ጓደኛዬ ነው የሰጠኝ ። ዋጋው ሐያ ብር ብቻ ነው ። ሰውዬው ጓደኛዬ በመሆኑ ነው እንጂ መቶ ብርም ሲያንሰው ነው ይላቸዋል ። ሽማግሌው በጣም ገብጋባ ናቸው ። ሲወጡም ሲገቡም ብር ይቆጥራሉ ። ሣንቲም አትወጣቸውም ። ሌሊት ብራቸውን ተንተርሰው ነው የሚያድሩት ። ሰው አያምኑም ። ግን እሱን አመኑት ። እንዴ የከተማው ከንቲባ ተብሎ የለም ። ከንቲባ የማያውቀው ምን ነገር አለ? የሚል ዝና አትርፎአል — መቼም ። የያዙትን ገንዘብ እንዳያይባቸው ዞር ብለው ከቆጠሩ

በኋላ ይኸው ነው ያለኝ» ብለው አሥራ አምስት ብር ብቻ ሰጡት ። ይሁን መቸም በእውነት 5ብር አከስረውኛል ። ሌላ ጊዜ እንደሚከሱኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። ብኋቸው ወደ ቀጠሮው ሮጠ ። ራት ላይ ሽማግሌው አለወትሮአቸው ሸከ ብለው መጡ ። ተሠርቀን እንመለከታቸው ነበር ። ራት ከበሉ በኋላ ኪኖቶ አዘዙ ። ሰው እንዳያያቸው ነው መሰለኝ ቀስ ብለው ከኪናቸውን ከዋጡ በኋላ ከተማ ገብተው ጠፉ ። እጅሬ ጧት ቁርስ ላይ ፣ «ያ መድኃኒት እንዴት ነው?» አላቸው ። ኧረ ግሩም ነው ፣ ሌላ ካለህ ጨምርልኝ አሉት ። እጅሬ ምኑ ሞኝ ። እንዲሁ በቀላሉ የሚገኝ አይደለም ። እርስዎ ደግሞ አይከፍሉም እንዴት ይሆ ናል?» አላቸው ። «በኔ ይሁንብህ ። መድኃኒቱን ብቻ» አሉት ። ይኸውልህ እጅሬ የባላርጅን ደምበኛ አግኝቷል ።» አለኝ ።

«እናንተ ሰዎች ጉደኞች ናችሁ ፣ አባቴ ይሙት ። ይህን ከተማ ጉድ ሳታደርጉት ዘመቻው አያልቅም» አልኳቸው ።

«ቀልድ ነው ። አንዳንዴ ቀልድ ያስፈልጋል ። ሁልጊዜ አምረን ይህን ዘመቻ ልንወጣው አንችልም» አለና ቀጥሎም — «አንተ ግን ይህን የዘመቻ ሥራ በምር ይዘኸዋል ። ከድል በኋላ ትሾማለህ ያለህ ሰው አለ እንዴ? አለኝ ።»

ነገሩ አሳቀኝና ፣ «ጋዜጠኛና አዝማሪ ለሹመት ማን አድ ሏቸው? ዘላለም ጋዜጠኛ አዝማሪ እንደተባሉ ነው የሚሞቱት» አልኩት ።

«ለቀይ ኮከብ ዘመቻ የመጡት አብዛኛዎቹ ሰዎች ምን ይላሉ መሰለህ?»

«ምን ይላሉ?»

«ለቀይ ኮከብ ዘመቻ ተመልምለን የመጣን ቀይ ኮከብ ዘማቾች ስንመለስ በያለንበት እንሾማለን እያሉ ነው የሚ ያወሩት ።»

«ከንቱ ምኞት» አልኩት ።

«አዲሳባዎች ደግሞ ከዚያ ምን ይላሉ መሰለህ? እዚያ የሔ ዱት በቂ ሥራ የሌላቸው የማይፈለጉ ሰዎች ናቸው እያሉ ያስወራሉ» አለኝ ።

«ያው የተለመደ አሉባልታ ነው እባክህ ፡፡ መጥፎ ልማድ ፡፡ ከመተባበር መጠላለፍ ፣ የራስን ሥራ ወዝፎ የሌላውን ሥራ መን ቀፍ ፣ ችግር ካለበት ቦታ መሸሽ ፣ ምስጋና ባለበት ቦታ የሥራ ሰው መስሎ ቀድሞ መገኘት ይቀናናል» አልኩና ፣ ወደ ፍሬው ዘሪሁን መለስ ብዬ ፣ «ትንሣኤ አዳራሽን ከሥመራ ስቱዲዮ ጋር የሚያገናኘውን መስመር 'ቼክ' አድርገሀል?» በማለት ጠየቅሁት ፡፡

«አዎ ከዚያ ነው የመጣሁት» አለኝ ፡፡

«ከአዲሳባ ጋር ተነጋግረዋል?»

«አዎ ፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ በኩል ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው ፡፡ ብቻ አዲስ አባዎች እዚህ ያለነው ሰዎች ሥራውን የም ንችለው አልመሰላቸውም......»

«ሌላስ?»

«ባዘዝከኝ መሠረት ሁሉንም 'ቼክ' አድርጌአለሁ ፡፡ በየፕ ሮግራሙ ጣልቃ የምናሰማቸው መፈክሮች ፣ ሐተታዎችና መዝ ሙሮች ሁሉ ተዘጋጅተዋል ፡፡ ዝርዝር የሥራ ክፍፍል አድርገ ናል ፡፡ ዝግጁ ነን ፡፡ የድምጽ መቅጃ መሣሪያዎች ፣ ማይክሮፎኖች፣ ካሜራዎች ሁሉ ካሁኑ ቦታቸውን እንዲይዙ አድርገናል ፡፡ «ማይ ክሮዌቭ ሊንክም ተዘርግቷል ፡፡ ከአሥመራ አብዮት አደባባይና ከሳባ ስታዲዮም ጋር የሚያገናኙ መስመሮች ተዘርግተዋል ፡፡ የቀ ረን አንድም ነገር የለም» ብሎ ሪፖርት ሰጠኝ ፡፡

«ጎሽ ፡፡ ሁሉም ሰው የሥራ ድርሻውንና ኃላፊነቱን ዐውቆ ቢሠራ ኖሮ'ኮ ስጋት የሚባል ነገር አይኖርም ነበር» አል ኩት ፡፡

«ካንተ አፍ ምስጋና ሲወጣ ዛሬ ገና ሰማሁ» አለኝ ፡፡

«እንዴት እባክህ?»

«ምን አንተ የሰው ሥራ ቀርቶ የራስህም አያረካህም ፡፡ ደግሞ ዝም ብለህ ትሰጋለህ ፡፡ ሰው ማመንና በሰው መተማመን ይኖርብሃል» አለኝ ፡፡

«የሚተማመኑበት ሰው ካለ» አልኩት ፡፡

«መተማመን የጋራ ጉዳይ ነው ጓድ ፡፡ ሰውን እምነት ከጣ ልክበት ለመታመን ይሞክራል ፡፡ ይህ ዘመቻ ያንተ ብቻ አይደም

ስልህ ። የሁላችንም ነው ። ሁላችንም እኩል ኃላፊነት አለብን»
አለ ።

«ተስፋ አደርጋለሁ» አልኩት ።
«ይልቅ እኔ የምስጋው ላንተ ነው.....»
«ለምን ልጄ?»
«ብስጩ ነህ ። ቶሎ ትበሳጫለህ»

«አይዞህ ። በዘመቻ መሐል ብስጭትና እንቅልፍ የለም ። ስንቃችሁን ባህያ ፥ ዐመላችሁን በጉያ ተብለናል» አልኩት ።

ፍሬው እውነቱን ነው ። ጠባዩን ያውቃል ። የሰው ሥራ አይጥመኝም ። በዚህ ላይ በጣም ስጉ ነኝ ። ግን አሁን ሥራው ከመብዛቱና ሁሉ ነገር በጣም አጣዳፊ ከመሆኑ የተነሳ ሥራውን አክፋፍዬ ጸሎት ከማድረግ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም ። መቆጣ ጠር ደግሞ አይሆንልኝም ። እንደራሴ እየመሰለኝ ሰው እስ ጩንቆ መያዝ ይከብደኛል ። እንደማንኛውም አርቲስት ሲጫ ኑኝ አልወድም ። መንፈሴ ያምጻል ። የፈጠራ ሥራ በትዕዛዝ አይሆንም ። ራሱ ወዶ ከውስጥ መፍለቅ አለበት ። ቲቪ በአብ ዛኛው የፈጠራ ሥራ እንደመሆኑ መጠን ፥ ትዕዛዝ ሲበዛብኝ እበሳጫለሁ ። የቴሌቪዥን ሥራ እንደካርታ የተበወዙና የተያያዙ ፊልሞችን ቀርጾ የማሳየት ተግባር እንደሆነ የሚመስከቱ ሰዎች አሉ ። ያናድደኛል ። እና ሔጄ እተኛለሁ ። ያለ ዕድል ሆኖ መቸም ከአልጋዬ ሌላ ማኩረፊያ ቦታ የለኝም ። ታዲያ በዚህ የተነሳ አለቆቹ ዳተኛ ፥ ኩራተኛ የሚል ስም አውጥተውልኝ ይኖራሉ ። አበሾች ስንባል መቸም የሰውን ደካማ ጎን አጉልተን ማናፈስ ነው እንጂ በጎ ጎኑን ማመስገን ጥሎብን አይሆንልንም ።

«ካልክስ ኃይለኛ ስጋት አድሮብኛል» አልኩት ።
«ምን?» አለኝ ፍሬው ።

«ከውጭ የታዘዙት ጥሬ ፊልሞችና የቴሌቪዥን ካሜራዎች እስካሁን አልደረሱም ። ለጉባዔው ግድ የለም ። ባሥመራና በም ጽዋ ለሚደረገው እንቅስቃሴ በቂ ፊልምና ካሜራዎች አሉን ። የጦር ሜዳው እንቅስቃሴ የተጀመረ እንደሆነ ግን ምን እንደሚ

ውጠኝ አላውቅም ። ምን እንደማደርግ ጠፍቶኛል ። ከፊት መባነን ጀምሬ አለሁ» አልኩት ።

ፍሬው የሚስቁትን ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ፣

«አትስጋ ። ይደርሳል እባክህ ። እኛ ሥራ የሚሳካልን በመጨረሻዋ ሰዓት ነው» አለኝ ።

እንደ ፍሬው ዘሪሁን ሁልጊዜ ብሩህ ተስፋ የሚታየው ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም ። ሁልጊዜ የሕይወት ጸሐያማ ጎን የሚታየው ሰው ነው ። «እንዳፍህ ያድርግልኝ» አልኩት ።

ሥዩም ለጠቅ አለና ፣ «እኔ የመጣሁት ለሌላ ጉዳይ ነበር» አለኝ ።

«እኔ ዘንድ ምን መረጃ አገኛለሁ ብለህ ነው፤ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ምስጢርነት የለውም» አልኩት እየቀለድኩ ።

«ምልቶት» አለኝ እየሳቀ ። ሲስቅ ጥርሶቹ ደስ ይላሉ ።
«ምን ነበር?» አልኩት ።
«ስለምታካሂዱት ጃሚንግ ሥራ ነበር» አለኝ ።
«ደህና እየተካሄደ ነው ። ምን ሆነ?» አልኩት ።

«አሁንም የወንበዴዎች ሬዲዮ ጣቢያ ይሰማል ። ሥራውን ከውስጥ የሚያደናቅፉ ሰዎች ካሉ ይነገረንና ርምጃ እንውሰድ» አለ ፍርጥም ብሎ ።

አናደደኝ ። «ፈጽሞ አይሰማም!» አልኩት ድምጼን ከፍ አድርጌ — «ካዲሳባም ሆነ ከዚህ ቀንና ሌሊት በመረባረብ እየ ታገልን ነው ። ወንበዴዎቹ ባንድ ፕሮግራም ውስጥ ከሰባ እም ስት እስከ ሰማንያ ጊዜ ቦታ ይለዋውጣሉ ። እና ማፍ ይዛችሁ ይሰማል ማለት ትክክል አይደለም ። የሚቻለውን ሁሉ እያደረግን ነው ። እና ደግሞ ለወደፊትም ቢሆን በጨረፍታ የሰማችሁትን ለበላይ ሪፖርት ለማድረግ ከማሮጥ አስቀድማችሁ ለኛ ብትነግሩን ሥራው በይበልጥ ይቃናል ። የቀይ ኮከብ ዘመቻ የቡድን ሥራ ነው ፣ ግንኙነታችን ወደ ላይም ወደ ጎንም መሆን አለበት ተብ ሏል ። ግን ወደ ላይ መሮጥ ነው መሰለኝ የሚቀናን ። እንዱ

ሌላውን የማሳጣት አሽቅድድም ለዘመቻው የሚሰጠው ጥቅም የለውም ። ምንም!» በማለት እንደተልባ ተንጣጣሁበት ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሁሉም ትኩሳት እየጨመረ ስለሔደ ነው መሰለኝ እርስ በእርስ መጯጯህ ተራ ነገር ሆኗል ።

«ለምን ነገሩን በተቃራኒ መንገድ ታየዋለህ?» አለኝ ለስለስ ብሎ ።

«ነው እንጂ! በዚህ ነገር ስንቴ ተወቅሻለሁ ። ልጆቹ የተ ጧጧፈ የምገድ ጦርነት እያካሔዱ ነው ። ጦርነቱ ቀላል አይ ደለም ። ጀር ያደነቁራል ። ጎዋሳት ያቃውሳል ። ከቆየም ምና ልባት ያሳብዳል ። ሂድና እያቸው ። የተጧጧፈ ጦርነት ላይ ነው ያሉት ። እኛ እንደሆን የወንበዴዎችን ሠፈር እያርበደበድን ነው ። የሚያስተላልፉት የታፈነ ድምጽ ጨርሶ እንዳይሰማ ከተፈለገ ፥ ጣቢያውን መደምሰስ ነው ። ይህ የኛ ፈንታ አይ ደለም» አልኩት ።

«ቦታው በትክክል ቢታወቅ መደምሰሱ ቀላል ነበር» አለ ።

«ምነው ሥዕላይ ጠቁም የለም?»

«የሚጠቀሙት ተንቀሳቃሽ በሆነ ስቱዲዮና ባለ ‘ሌፐ አንቴና ሬዲዮ ነው ። ናቅፋ ተራራዎች ውስጥ የት ተብሎ ይገ ኛል ። ጣቢያው ያለበትን ለማግኘት ያልተደረገ ሙከራ የለም.....»

«እኔን የሚገርመኝ ነገር ልክ ‘ጃሚንግ’ በጀመርንበት ቀን ቦታ በመለዋወጥ ታክቲክ መጠቀማቸው ነው ። ከዚሁ ተዘጋ ጅተው ካልቆዩ በስተቀር በዚህ ታክቲክ ባንድ ጊዜ ሊጠቀሙ አይችሉም ነበር ። የእነሱ ሰው እኛው መካከል መኖር አለበት» አልኩ ።

«እኔም ‘ኮ ይህን ነበር የምለው» አለኝ ሥዩም ።

«ማን ይሆን?» አልኩ ።

«እስቲ ተስ ብለህ ተመራመር ። ጥቂ ሰዎች አይደሉም ። ልባቸው አይገኝም ። እንደ ከረገ መንገድ ጠመዝማዛ ነው ። የትግሬ ልብ የሚባለውን መንገድ አይተሀል? እንደ እሱ ነው» አለኝ ።

«እሱ ያንተ ሥራ ነው ጓድ»

አቅጣጫውን ለወጥ አድርጎ፣ «ፊያሜታ ጊላይ እንዴት ናት?» ብሎ ጠየቀኝ ።

«ከእሷ ጋር ምን አለው አሉህ?»

«ሰላንተ ትጠይቃለች እሱ ።»

«ሻለቃ ተከላይ ዘድንግል፡ም በቀደም ዕለት ይህንኑ ጥያቄ ጠይቆኝ ነበር። እንዴ! ስለኔና ስለእሷ ምን አስጨነቃችሁ?» ብዬ ጠየቅሁት ። ስለእሷ እኔን ለምን እንደሚመረምሩኝ እያስገረመኝ ፣ ቀጠልኩና —

«ስለ ፊያሜታ ከኔ ይልቅ ሥዕሶይ በራኺን ብትጠይቁት ይሻላል ። እኔ ስለእሷ የማውቀው ምንም ነገር የለኝም ። ባው ቅም የግል ጉዳዬ ነው ወይም ይሆናል» አልኩት ።

«ሥዕላይ በእሷ የተነሳ ባንተ ተናዷል»

«ምን አድርጌ?»

«ውብ ዓይኖቿን ስለጣለችብህ ። ተከላይ ዘድንግልም እን ዴት ተቀደምኩ? ብሎ አሯል ። ሴቶች እንኳ ጨክነው እምቢ አይሉትም ነበር ። አልሆንለትም ። ኃይለኛ ልጅ ናት» አለ ።

«አንተ ለምን እድልህን አትሞክርም?» አልኩት ።

«ሞክሬ ነበር......»

«እና?»

«እኔም አልሆነልኝም......»

«እሷን የማያባርር በከተማው የለም አትለኝም?» አልኩት ።

«አንተ ሞክር ። ይቀናህ ይሆናል ። በጣም ቀንደ ልጅ ናት ። ጨው ያላት ትመስላለች ። ስለእርመኛህ አታስብ ። ምን ትሆን ባታለህ? አትጧጧባትም — አይዞህ» አለኝ ።

«ስለምክሩ አመሰግናለሁ ። ግን አያስፈልገኝም......»

«እንዴት?»

«ሴቶች ይወድቁልሀል ። ቀንደ እንኳ አይደለህ ። ምስጢሩ ምንድነው?»

ሳቅሁና ፣ «ናቃቸው ይከተሉሀል ። ከመጡ አክብረህ ያዛቸው ፣ ይወዱሀል ። ውደዳቸው ፣ እርካቸው ግን አትመና ቸው አሥራ እንደኛው ቃላት (ምስጢሩ ይኸው ነው» አልኩት እየቀለድሁ......

ቴሴፎኔ ጥርር አለ ።

«ጓድ ጸጋዬ ቴሌፎን ካዲሳባ» አለች ረዛን ።

ቴሌፎኑን ተቀበልኩ ። አለቃዬ ነበር ።

«ከውጭ ስለታዘዙት ካሜራዎች ጉዳይ ነበር» አለኝ ።

«ደረሱ!?» አልኩት ደስ ብሎኝ ።

«ስማ!» አለኝ — «እኔ እዚህ ቁጭ ብዬ ኒውዮርክ ሎንደንና ጀኔቫን ላዝ አልችልም! ከቁጥጥራችን ውጭ ነው ። እና አሁንም በዚህ ሣምንት ሊደርሱ እንደማይችሉ ቴሌግራምና ቴሌክስ ደርሶኛል ። ይህንኑ አስረዳ ። እዚያሆነህ ለምን ታሳጣናለህ?»

«ምን አድርጌ»

«የለም ጸጋዬ ። የተላከው መሥሪያ ቤታችንን ለመወከል ነው እንጂ ልታሳጣን አይደለም ። ፍላጎት አንድ ነገር ነው ። ሥራ ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው» አለኝ ።

«ስለየትኛው ፍላጎት! ስለየትኛው ማሳጣት ነው የምታወራው!» አልኩት ድምጼን በኃይል ከፍ አድርጌ ።

«ታዲያ እዚህ እየደወሉ ምንም እንደማንሠራ አድርገው ለምንድነው የሚጨቀጭቁኝ!» አለ እሱም ቆጣ ብሎ ።

«አላወቅም! ለምን የደወሉልህን ሰዎች አትጠይቃቸውም! ስማ ጓድ ። ዱለታንና ዶላቾችን አልወድም ። ይዶልቱብኛል ብለህ ተጠራጥረህ ከሆነ ተሳስተሃል ። ሊጠራጠር ኩሁባለ ደግሞ ሰው የገዛ ጥላውን ሊጠራጠር ይችላል» አልኩት ። ዝም አለ ። ዝም አልኩት ። ዝም ዝም ሆነ ። ቴሌፎን ጸጥ ብሎ ቀረ ። ለመናደድ ጊዜ አላገኘሁም ። ለመናደድ ፣ ለማኩረፍ ጊዜ የለም ። ሌላ የቴሌፎን ጥሪ ነበር ።

«ሀሎ!» አልኩ ።

«ምነው ጆሮዩን በጠስከው ጃል?»

የፕሮቶኮል ሹሙ ነበር ።

«ይቅርታ.....»

«አይዞሽ ። መሮኽ የጀርመኺው አንቺ ብቻ አይደለሽም ። ሁሉም ይሮኽል ። ባስቸኳይ ትፈለጊያለሽ» አለኝ ።

«የት?»

«የት ልበልሽ? እዚህ ነዋ»

የእጅ ሰዓቴን ተመለከትኩ ። ስድስት ሰዓት አልፎአል ። ለምሳም ጊዜ የሚሰጥ የለም ፣ ለምን ይሆን የተፈለኩት? አልኩ በልቤ ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰው በደህና የሚፈልግ ሰው የለም ። ከውጭ ስለታዘዙት ካሜራዎችና ፊልሞች ይሆናል የተፈለኩት ብዬ አሰብኩ ። የተሰጠኝ የጊዜ ገደብ ጥር 1/1974 ነበር ። የጊዜው ገደብ ካለፈ ሣምንት ሊሆነው ነው ። ሰውዬው ምንም ነገር አይረሱም ። እንዴት ታወጣኝ ይሆን? አልኩ በልቤ ።

«ስማ ፍሬው ፣ ጋዜጠኞቻችን ጧት ልክ በአሥራ ሁለት ሰዓት ትንሣኤ አዳራሽ እንዲገኙ ንገርልኝ።በአሥራ ሁለት ሰዓት ፣ እና ሁሉም ደህና ልብስ ይልበሱ ። ሂፒ መሳይ ጋዜጠኞች እዚያ ማየት አልፈልግም» ብዬ እንደ ሽፕኋቸው «ሱስሎቭ» ስለታም ፊቱን አስቀድሞ ብቅ አለ ። ሲያዩት ኩሩ ይመስላል ።

«ስልክህ ሁልጊዜ እንደተያዘ ነው» አለኝ ።

«ሥራ ይበዛበታል ። እዚህ የማይደውል የለም ። ብዙ ሰዎች ዜና ለሁሉም ነገር መፍትሔ ነው ብለው ይገምታሉ መሰለኝ — በተለይ የቲቪ ካሜራ ። እና ሁሉም ታሪክ የሚሠሩ ይመስላቸዋል ። አንዳንድ ሰዎች አንድ ነገር አድርገው ዜናውን ሳንሠራ ፣ በተለይ በቲቪ ሳንቀርጽ የቀረን እንደሆን ፣ ታሪክ ምን ይላችኋል? የሚሉን አሉ» አልኩት ።

«አሁን የመጣሁት ስለፕሮፓጋንዳው ይዘት ላነጋግርህ ነው» አለኝ ።

ቁሞ ነበር የሚያነጋግረኝ ። ሰው ቢሮ ገብቶ መቀመጥ አይወድም ። ሲጃራ ያጨስ ነበር ። ከዚህ በፊት ሲጃራ ሲያጨስ አይቸው አላውቅም ።

«እሺ ። ግን ቤተ መንግሥት ተጠርቻለሁ.....»

«ጊዜ አይፈጅም ። የምናካሂደው ፕሮፓጋንዳ ስሜታዊ መሆን የለበትም ። እዚህ የመጣነው ጠባብ ብሔረተኛነትን ለመዋጋት ነው እንጂ ሌላ ጠባብነትን ለማስፋፋት ወይም ለማራመድ አይደለም ። ስለ አንድነት ስንናገር ፣ የጭቁኑን ሠርቶ አደር መደባዊ አንድነት ማለታችን እንደሆነ ከምን ከተለው ርዕዮተ ዓለም አንጻር ¦ ማብራራት የሚያስፈልግ

ይመስለኛል ። የትግላችን ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ባሕርይና ይዘት መንጸባረቅ ይኖርበታል ። በስሜት ተነሳስተን ዐረፍተ ነገሮችን ከመደርደር ይልቅ ሳይንሣዊ ትንታኔ ማድረግ ከስ ድብ ይልቅ ነባራዊ ሁኔታዎችን ማሳየት ያስፈልጋል ። ሳይን ሣዊ ርዕዮተ ዓለም ሳይንሣዊ ፕሮፓጋንዳ ይጠይቃል ። እና ደግሞ እባካችሁ በቃላት ላይ ጥንቃቄ ብታደርጉ ። እኔ የቃላት ጋጋታና ኳኳታ አልወድም» አለኝ ።

«ደህና ። እንሞክራለን» አልኩት — «እንዳልከው እኔም የቃላት ናዳ አልወድም ። የዘመኑ ግጥሞች የሚያስጠሉኝ ለዚህ ነው ። ሆኖም እንጩት ፣ እንጩት የሚል ደረቅ ፕሮፓጋንዳም ደስ አይለኝም ። ሰዎች ስሜት አላቸው ። ስሜታቸውን የሚነካ ነገር ይወዳሉ ።»

አልለማኝም ወይም መልሴ ደስ አላለውም ። ብቻ ፣ «የምታዘጋጃቸው ነገሮች አየር ላይ ወይም ጋዜጣ ላይ ከመውጣታቸው በፊት በቅድሚያ በማዕከላዊነት በጥንቃቄ ቢታዩ ይሻላል ብዬ አምናለሁ» ብሎኝ ወጣ ።

እኔም ተከትዬው ወጣሁ ።

ከሰለሞን በትረ ጋር ከፎቅ ስንወርድ ተገናኘን ። ሁለት ፣ ሁለት ደረጃዎች እየዘለለ ወደታች ይሮጥ ነበር ። ሁልጊዜ ይ ሮጣል ። አሁንም እርፎ ውስጥ እርፎ የተነሳ ይመስል ነበር ።

«እንዴት ነው ዝግጅቱ ሁሉ?» አለኝ ።

«ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው....»

«ከእንግዲህ የጉባዔው መሳካት ወይም አለመሳካት በእና ንተ ሥራ ላይ ያረፈ ነው....»

«እግዜር ይርዳን....»

«እግዜር ስፖለቲካ ጀር የለውም» አለኝና ሮጠ ። እኔም ከፖለቲካ መምሪያ ወጥቼ ወደ ቤተ መንግሥት ሮጥኩ ። የፕሮ ቶኮሉ ሹም፣ ጓድ ተድላ ረጋሣ ቢሮው ተቀበለኝ። ስገባ በቴሌፎን ስለ እንግዶች አቀጣመጥ መመሪያ ይሰጥ ነበር ። መመሪያውን እስተሳልፎ እስኪጨርስ ድረስ ጠበቅሁትና ፣ «መጥቻለሁ ጓድ ። ለምን ተፈለኩ?» አልኩት ።

«ምሣ እንድትበላ ታዘሀል» አለኝ ።
«መልከም ዜና ፓስታ እንደማይሆን ተስፋ አለኝ......»
«የለም ። የሚሊሽያ ድራፍት ነው የምናቀርብልህ» አለኝ ።
«ጥሩ ነው'ኮ እጋዴን በእሱ ብቻ ሦስት ቀን ኖሬአለሁ» አልኩት ።

«አዎ ፡ ለረሀብ ፣ ለጥማት ፣ በስኳር በጥብጠው ሦስት ቀን ካቆዩትም ለትንሽ ሞቅታ ጭምር ነው ። ዛሬ 'ሚሊ ድራፍት' ከጠፋ ጦሩ ያምፃል» አለኝና ያእጅ ሰዓቱን ተመልክቶ ብስጭት አለ ።

«ምነው? ምን ሆንክ?»
«የምግብ ሰዓት ማስከበር ፈጽሞ አቅቶኛል......» ሲል «ኮሬ ደሩ» ላይ ጋጋታ ሰምቶ ደስ አለው ።

ሊቀ መንበርን ተከትለን ወደ ቤተ መንግሥቱ ምግብ አዳ ራሽ ገባን ።

ሁለት እጃቸውን ወደኋላ አጣምረው በመያዝ እቀርቅረው ነበር የሚሄዱት ። አሳብ የተጫናቸው ይመስላሉ ። የቀረበው ምግብ እንጀራና ወጥ ነበር ። ወስፋቶቹ ተንጫጩ ። ግን እንጀ ራውን የቀረሰ ሰው አልነበረም ። ሊቀ መንበሩ ምግቡን ትተው በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ አሳብ ሲሰጡና ጥያቄ ሲያቀርቡ ነበር ። ቦታው ፣ የምግብ ቤት አዳራሽ መሆኑ ቀርቶ ቅልጥ ያለ የስብሰባ አዳራሽ መስሎ ታየኝ ። ሚኒስትሮች ፣ ኮሚሽነሮች ፣ የኃይል አዛዦች ወዘተ የሰውዬውን ጆሮ ለማግኘት ይሻማሉ ። አዲስ አበባ የቀረ ባለሥልጣን ያለ አይመስልም ፣ እንዳንዶቹ ምን ሥራ ኖሮአቸው እዚህ እንደመጡ ለማወቅ ባልችልም ቅሉ ። ከሥልጣን አካባቢ ርቆ መገኘት ብርድ ያስገባል ልበል! እና ፣ ያው እንደተለመደው እንዳንዶቹ ይበልጥ ይናገሩ ነበር ። ንግግሮቹ ያተኮሩት በመጀመሪያ ርዳታ መስጫ ክሊኒኮች ፣ በሆስፒታሎች ፣ በማገገሚያ ጣቢያዎችና በኮንስትራክሽን ሥራ ዎች ላይ ነበር ። እንዳንድ የኃይል አዛዦች ስለ ሎጂስቲክ ችግር አጥብቀው ሲያነሱ ይሰማሉ ። አንዱ ሌላውን ለማሳጣት የሚደረገው ዙሪያ ጥምጥም ሙከራ ደስ አላለኝም ። ፊቴ የቀረ በውን እንጀራ አይቼ በጣም ራበኝ ። ጓድ ሊቀ መንበር አንዴ

ጎረሱ። ሁሉም እሳቸውን ተከትሎ እንጀራውን ይቆርስ ጀመር ። ሊቀ መንበሩ ለምግብ ደንታ ያላቸው አይመስሉም ። ከስተው ታዩኝ ። እኔም እንጀራዬን ልቆርስ ስል ፣

«የሚዲያው ዝግጅት እንዴት ነው?» አሉኝ ። የቆረስኳትን እንጀራ ጥዬ ፣ «ጓድ ሊቀ መንበር ተዘጋጅተናል» አልኩ ።

«መላው የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ የዚህ ክፍለ ሀገር ችግር በራዲዮ ፣ በጋዜጣ ፣ በቴሌቪዥን ለመከታተል እንዲችል ማድረግ ያስፈልጋል ። ዛሬ ኢትዮጵያ ከዚህ የባሰ ሌላ ችግር የላትም ። የዚህ ክፍለ ሀገር ችግር ነቀርሳ ወይም ካንሰር ነው» አሉ ።

«ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው» አልኩ ።

«ከውጭ የታዘዙት መሣሪያዎችስ?»

ገና እንዳልደረሱና ለምን እንዳልደረሱ ፣ ቢሆንም በሚቀጥለው ሣምንት ምናልባት ሊደርሱ እንደሚችሉ ፣ እስከዚያ ድረስ ግን ባሉን መሣሪያዎችና ፊልሞች ሥራውን ለመሸፈን ምንም ችግር እንደሌለብን ለማስረዳት ሞከርኩ ። አመለካከታቸው ደስ አላለኝም ። ሌላ ጥያቄ ሊያቀርቡልኝ ፈልገው ነበር ። የሁ ገ አ ዘ ዋና ጸሐፊ ከምግባቸው ላይ ቀና ብለው ፣ «ጓድ ሊቀ መንበር ፣ እባክዎን ይብሉ ። የቢሮ ሥራችን ወደ ገበታ ይዘን መቅረብ የለብንም ። ለ'ዳይጀሽን' ጥሩ አይደለም» አሏቸው ። «ጣፋጭ ነትስ!»

ጓድ ሊቀመንበር ስቀው መመገብ ጀመሩ ። እኔ ግን የምግብ ፍላጎቴ ጠፍቶ ነበር......

# የቀይ ኮኮብ ዘመቻ ጥሪ
# «ጦርነትና ሠላም»

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ከዓባይ ሸለቆ እስከ ቀይ ባሕር ባለው የተፈጥሮ ክልል መሐል ሕዝቧ ሲጋደልላት የኖረች አገር መሆኗን ለመካድ አይቻልም ።

በዚህ በሰሜን የሀገራችን ክፍል ዛሬ የገጠመን አኩል በባሕርይው ለየት ያለ ቢሆንም ፣ አካባቢው ለአያሌ ዘመናት ለተደጋጋሚ ጦርነቶች ተጋልጦ ኖርአል ። ቱርኮች ፣ ግብጾች ፣ ኢጣልያኖችና መሰሎቻቸው መላ ሀገራችንን ለመውረር በተደ ጋጋሚ ጥቃት የሰነዘሩብን በዚህ በቀይ ባሕር በራችን በኩል ነው ።

ይህ የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የሥልጣኔያችን እምብርት እንደመሆኑ የኢትዮጵያችን ልዩ መታወቂያ የሆኑት የባሕል ቅርሶች ፣ ሀይማኖቶች ፣ ፊደላትና የመሳሰሉት መሠረታቸው ከ ዚሁ መሆኑ በተጨባጭ የተመሰከረለትና ሊካድ የማይችል ሲሆን የዚያኑ ያህል ተደጋጋሚ የውጭ ጥቃት የተሰነዘረብን ከዚህ አቅጣጫ መሆኑም የማያከራክር ነው ።

ይህን ታሪካዊ አንድነት ለመጠበቅና ለማስከበር ካሌብ ካዶሊስ የቀይ ባሕርን ሞገድ ሲገዛ ፣ ልብነ ድንግል በዱር ሲንከራተት ፣ ዮሐንስ መተማ ላይ አንገቱን ለሠይፍ ሲሰጥ ፣ አሉላ አባ ነጋ ፣ «ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ ተፈጥሮ በር ነው» እያለ ዶጋሊ ላይ ቂም በለው ሲል ፣ ቴዎድሮስ ፣ «የቱ ወንድ ከንዴን ይይዛል!» ብሎ መቅደላ ላይ የመጨረሻ ጥይቱን ሲጠጣ ፣ ምኒልክና ጣይቱ አድዋ ላይ «ድሉ ያንተ ነው ያገሬ ጀግና!» እያሉ ምድሪቱን እቶን እሳት ሲያደርጓት ...»የሚል ንግግር ስሰማ የዘመናት ተጋድሎ ፉቴ ድቅን ብሎ ታየኝ። ሠላም ዘላለም እንደ ውሀ የሚጠማት የፈረደባት አገር!

የመላ ኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ተወካዮች አንድ ላይ ተሰብስበው በተገኙበት ታሪካዊ ጉባኤ ፥ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ይዘት ፥ ዓላማና ግብ ጥር 17 ቀን 1974 እሥመራ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኘው ትንሣኤ አዳራሽ ለመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ተበሠረ ። የኢትዮጵያ ከተሞችና መንደሮች ፥ አምባዎችና ሸለቆዎች ጆሮ ብቻ ሆነው የዋሉበት ታሪካዊ ቀን ነበር ።

ቢሮዬ ቁጭ ብዬ ትንሣኤ አዳራሽ ውስጥ የሚገኘውን ጊዜያዊ ስቱዲዮውንና የአሥመራን ራዲዮ ጣቢያ በልዩ የስልክ መስመር በማስተባበር ታሪካዊውን ንግግር በራዲዮ «ሞኒተር» እያደረኩ ሳዳምጥ ፥ በመላ ኢትዮጵያ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ፥ በየፋብሪካቸው ፥ በየማሳቸው ፥ በየቢሮአቸው በየንግድ ቤታቸውና በየመኖሪያ ቤታቸው ጆሮዎቻቸውን ትራንዚስተር ሬዲዮኖች ላይ ተክለው እያዳመጡ ሲደነቁ ፥ ሲቆጩና ወኔያቸው በቁጣ ሲቀሰቀስ በዓይኔ ሕሊናዬ ይታየኝ ነበር ። በእርግጥም ንግግሩ የሚያስደንቅ ፥ ስሜት የሚነካ ፥ የሚያስቆጭና ወኔ የሚቀሰቅስ ፥ ባንዳሩም የተገንጣዮችን ታሪካዊ አነሳስና ዕድገት ፥ዓላማና አቋም ፥ አሁን ያሉበትን ሁኔታና ፖለቲካዊ ክስረት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ንግግር ነበር ። በሌላ መልኩ ግልጽ ውይይትም ነበር ። እና በመጨረሻም ፥ የክፍለ ሀገሩን ችግር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍታት በቁርጠኛነት የተገባ ቃል ኪዳን ነበር ። የቀይ ኮከብ መደበኛ ጦርነት ታወጀ ። የቀይ ኮከብ ሠላም ጥሪ ቀረበ።ጦርነትና ሠላም ። ላለፉት ስምንት ዓመታት ሠላም እየናፈቀን በየማንባሩ ጦርነት ስንዋጋ ኖረናል ። መቸ ይሆን የአብዮት አምላክ ይቅር ብሎ ሠላም የሚሠጠን? አልኩ ። ከእንግዲህ አንዱ ሲሞት ሌላው ተመልካች የሚሆንበት ሁኔታ ከየት መጣ? አከተመ ። ለክፍለ ሀገሩ ሕዝብ የውሣኔ ቀን ነበር ።

ኵሉኔል በትሩ ተሰማ ቢሮዬ መጥቶ ነበር ። የጠመድኩትን ሬዲዮ አይቶ ፥ «ድስት የጣደች መልካም ባለሙያ መስለህ የለም እንዴ?» አለኝ ።

«ሥራ ቤት አይደለን? እመት አይሞላልሽ» አልኩት ።

«እንዲያው እውነት ፥ ንግግሩ በመላ ኢትዮጵያ ይሰማል አሁን?» አለኝ ።

«አሳምር ፡ ለማረጋገጥ ትፈልጋለህ?»
«እንዴት ብዬ»

«ቀላል ነው» አልኩትና ፣ ጎንደር ፣ ጎጃም ፣ መቀሌና አዲስ አበባ ከሚገኙት ዜና አገልግሎት መሥሪያ ቤቶች ጋር በስልክ አገናኘሁት ። በዜና አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት አማካ ይነት ሐረርጌ ፣ ወሎ ፣ ኢሉባቡር ፣ አርሲና ሲዳሞ ፣ ጋሞ ጎፋም ሳይቀር ንግግሩ በመሰማት ላይ እንዳለ አረጋገጥን ።

«አሁን አመንክ? ዕድሜ ለትራንዚስተር ራዲዮ ። ኢትዮጵያ ዛሬ ጆሮ ብቻ ሆናለች ።» አልኩት ። የወትሮው ፈገግታው ጠፍቷል ። ጸሐይ ያልነካው ቀይ ፊቱ ገርጥቷል ። ቀጠልኩና ፣ «ምነው አሳብ የገባህ ትመስላለህ? አልኩት ።

«በጣም ሰግቻለሁ» አለኝ ።
«ምነው?»

ጥያቄዬ አስገርሞት ሳቀና ፣ «እንዴት ምነው? ብለህ ትጠይቀኛለህ? ያገሪቱ መሪዎች እንዳሉ አንድ አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው እንዴት አልሰጋም? ወቸ ጉድ!» አለ ።

«ምን ይሆናሉ ብለህ ነው?» አልኩት ።

«ምንም ነገር ሊሆን ይችላል ። እነዚህ ወንበዴዎች ዋዛ ሰዎች አይደሉም ። ጀብደኞች ናቸው ። የዓለምን ጆሮ ወደ እነሱ ለመሳብ አንድ ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ» አለ በመስኮት ሩቅ እየተመለከተ ።

ውብ ጸሐይ ወጥታለች ። ቀዝቃዛ አየር ይነፍሳል ። ዘምባባ ዎች በዝግታ ሙዚቃ የሚደንሱ ይመስላሉ ።

«እውነትም ኮ ያሰጋል ። ባሁኑ ወቅት አንድ ቅርጫት ውስጥ እንደምንገኝ እንቁላሎች ነን» አልኩት ።

የኰሎኔል በትሩ ሲጋቱ እኔም ላይ ተጋባ ። ባለፈው ሰሞን ከተማውን ለመረበሽ ካንድም ሁለት ጊዜ ሙከራ አድርገው

ነበር ። እነ ኰሎኔል በትሩ በሠላም አልከረሙም ። አንድ ሌላ ኰሎኔል በዚሁ ምክንያት የተነሳ ከሥራው ተፈናቅሏል ። ኰሎኔል በትሩ ያለምክንያት አልሰጋም ። የቀይ ኮከብ ዘመቻ የብዙ ሰዎችን ደም ብዛት ከፍ ሳያደርግ አልቀረም ። እኔም ደህና አልነበርኩም ።

«ከተማውንና የከተማውን ክልል በስፋት ወጥረናል ። ቢሆ ንም ..... ቢሆንም.....» አለ የመስኮቱን መስተዋት በጣቶቹ እየቆ ረቆረ ። ትክሻው የቆጁ ሣጥን ይመስላል ። ግዱ ተደራርቦ ማጅራቱ ላይ ሲታይ ትንሽ የእርከን ሥራ ይመስላል ።

«ታዲያ ምን አሰጋህ? » አልኩት ።

«አንድ የተጠነሰሰ ሤራ ቢኖርስ?» አለኝ ።

«እንደምን ያለ ሤራ?»

«ለምሳሌ እንደ ግድያና ሽብር.....»

«ካለ ዛሬ ያደርጉታል ወይም ሰሞኑን ፥ ምናልባት ላይ.....» «ኖኖ ሁሉም ነገር እንደተወጠረ ያውቃሉ ። ግን አንድ ቦታ ፥ አንድ ነገር ይሸተኛል» በማለት ፊቱን ወደ እኔ መልሶ ፥ በነ ራችን ላይ ፥ ሥዕላይን ኢንተርቪው ያደረክበት ቴፕ አለህ? » ብሎ ጠየቀኝ ።

በቴፕ የተቀዳ የሥዕላይ ኢንተርቪው ነበረኝ ።

«ምን ያደርግልሀል?» አልኩት ።

«ያስፈልገኛል ።»

«የምትጠራጠረው ነገር አለህ?»

«ምን ቸገረህ? ቴፑ ካለ ስጠኝ» አለኝ ትዕግሥቱን እንደ መጨረስ ብሎ ።

«ከተጠራጠርክ ሰውዬውን ሰቅሎ መጠየቅ አይቀልም ወይ?» አልኩት ።

«እንዲህ ዓይነቱን ዘዴ መጠቀም ካቆምን ቆይተናል ። ሳያ ሰቃዩ መረጃ ማግኘት ይቻላል ። በዚህ ዓለም ተደብቆ የሚቀር ምስጢር የለም ። አንድ ሰው ምስጢሩን ላንድ ሌላ ሰው መግለጽ አለበት ። ምስጢራቸውን በልባቸው ይዘው የሚሞቱት ጥቂት ሰዎች ናቸው ።

«ምስጢሩን አፍና ከያዘ ይፈነዳል ማለቴ አይደለም። እርግጥ ምስጢራቸውን ላንድ ሰው ካልገለጹ የሚፈነዱ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ ። ግን ሰው ሰውን መሣሪያ ስለሚያደርግ አንድ ቦታ ላንድ ሰው ምስጢሩን ለማካፈል ይገደዳል ። ዘዴው ሳይታክቱ በር ማንኳኳት ነው» አለኝ ።

«ግን እነዚህ ሰዎች ፈጣኖች መሆናቸውን አትርሳ ። እንደ ምሰማው ከሆነ ፣ ለዓላማቸው የሚያስልፏቸው ሰዎች ጨርሶ የማይጠረጠሩ ዓይነቶቹን ነው ይባላል ። ያ ሰው ታማኝ ጎረ ቤትህ ወይም ጓደኛህ ሊሆን ይችላል ወይም የታመነ የመንግሥት ባለሥልጣን ፣ ወይም የሕዝባውያን ድርጅቶች ግንባር ቀደም መሪ» አልኩት ።

«ስለ እነሱ ብዙ የምታውቅ ትመስላለህ....»

«ጋዜጠኛ መሆኔን አትርሳ» አልኩትና የሥዕላይን ቴፕ ከጠረጴዛ መሳቢያ ውስጥ እየፈለኩ ፣ «ቴፑ ምንም አዲስ ነገር የለበትም ። የሰጠኝ ኢንተርቪው እንዳሰብኩት አልነበረም ። አንተ ከጨመከው በኋላ ነው እኔ ያገኘሁት ። አስቀድማችሁ ብታስረዱን የተሻለ ነገር ሊገኝ ይችላል ። ግን ይህን አታደርጉም። ላንድ ዓላማ የምንሠራ አይመስላችሁም መሰለኝ!

«በኔ ግምት ፣ ከሥዕላይ ይልቅ ቀደም ብለው የገቡት በተ ለይም ሁለቱ ጓዶች ፣ ሻዕቢያ ላይ ከባድ ጉዳት ያደረሱ ይመስ ለኛል ። እንደምሰማው በሁለቱ ወዶገቦች ምክንያት ሻዕቢያ መላ ይዘቷንና ታክቲኳን ፣ የድርጅቷ ቦታዎች ሁሉ ሳይቀር ለመለወጥ ተገዳለች ይባላል ። ሥዕላይ የሰጠው ኢንተርቪው እንዲያው ነው ። የጎዳቸው ይመስል በሬዲዮ ጣቢያቸው ስለእሱ ዘመትር ለምን እንደሚያላዝኑ አይገባኝም» አልኩት ።

«ነጥቡ እዚህ ላይ ነው ። ለምን!» አለኝ ።

«እንጃ ። ግን ሥዕላይ ከሰጠኝ ኢንተርቪው ልቢ የገባው አንድ ነገር ብቻ ነው ። እሱ እየቆጠቆጣቸው ይሆናል ጨትጓታ የሚወርዱበት....»

«የቱ?» አለኝ ተቻኩሎ ።

«ነጻ አውጭዎች ነን እንላለን ። ግን እንደ እውነቱ ከሆነ ነጻ አውጭዎች አይደለንም ። የኤርትራን ሕዝብ ከማነው ነጻ የምናወጣው? ኢትዮጵያ ፣ ለምሳሌ ፣ እንደ እንግሊዝ ፣ እንደፈ ረንሣይ ፣ እንደ ጣሊያን ፣ እንደ ፖርቱጋል ወይም እንደ ደቡብ አፍሪካ ወዘተ ኰሎኒያሊስት አገር መሆኗን ለማስረዳትና ለማሳ መን እስካልቻልን ድረስ ትግላችን ከንቱና መሠረተቢስ ነው ። እንደ አልጄሪያ ፣ እንደ አንጎላ እንደናሚቢያ ወይም እንደ ዚም ባቡዌ ሕዝቦች ጸረ ኮሎኒያሊስት ትግል የምናካሂድ አይደለንም ። እንደ አምስቱ ዓመት የኢትዮጵያ አርበኞች ትግል ።

«ፖለቲካዊ ለውጥ ለማምጣት የእርስ በእርስ ጦርነት እያካ ሔድን ነው እንዳንል አይደለም ፣ ለምሳሌ በቻይና ፣ በኩባ ፣ በቪዬትናም እንደተካሔዱት ሕዝባዊ ትግሎች ። ቀደምም ሲል በፈረንሣይ ፣ በስፓኝ ፣ በሩሲያ እንደተደረጉት የእርስ በእርስ ጦርነቶች ፣ ወይም አሁን በኤል ሳልቫዶር በመደረግ ላይ ያለው የእርስ በእርስ ጦርነት ። የኛ ትግል ከነዚህ ትግሎች ጋር የይዘትም ሆነ የዓላማ ግንኙነት ወይም ተመሳሳይነት የለውም ። በአጠ ቃላይ ፖለቲካዊ ለውጥ ለማምጣት አይደለም የምንታገለው ። ቢሆን ኖሮ በኢትዮጵያ ሶሻሊስታዊ ሥርዓተ ማኅበርን ለመመሥ ረት የሚደረገውን ጥረት መጣሪያ አንስተን እንወጋም ነበር ። ታዲያ የትግላችን ይዘትና ዓላማ ፣ መነሻና መድረሻ ምንድነው? ባጭሩ በእብሪት ያበጠ ጠባብነት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትርጉም የለውም ያለው ብቻ ነው ጥሩ አድርጎ የሚታወሰኝ» አልኩት ።

«የሚናገረውን ሁሉ የሚያምንበት ይመስልሃል?» ብሎ ጠየቀኝ ።

«እንጃ ። እውነቱን ይሁን ውሸቱን በምን ዐውቃለሁ ። ግን ቢያምንበትም ባያምንበትም አባባሉ ሐቅ ነው ። ጠኛማእስከሆነ ድረስ ባንድ አገር ውስጥ አንዱ ብሔረሰብ ሌላውን ቢንቅ ወይም በሌላው ላይ ቢቀልድ ምንም አይደለም ። ያለ ነገር ነው ። ግን መናናቅ ያገርን አንድነት እስከማጥፋት ድረስ መሔድ የለበትም ። ይህነው የሚያናድደኝ ። አልኩትና ቴፑን አውጥቼ ከሰጠሁት በኋላ ፣ «ወንበዴዎች ናቅፋ ላይ መሽገው ከመቆየት ሌላ ምርጫ የላቸውም» ያለውን ግን አሁንም አላመንኩበትም» ብዬ ጥርጣ ሬዬን ገለጽኩለት ።

«ለምን አላመንከበትም?»
«ሰው በራሱ ላይ እልቂት ይጋብዛል?»
«ታዲያ ምን ያደርጋሉ ብለህ ታስባለህ?»

«እንጃ ፡ ይኸ የወታደራዊ ኢንተሊጀንስ ጉዳይ ነው ። ብቻ ፣ ናቅፋ መሽገው እንደሚቆዩ መስለው በማወናበድ ፣ የወገን ጦር ወደዚያ ሲሔድ እነሱ ወደዚህ ቢመጡስ?» አልኩት ።

ሳቀብኝና ፣ «የለም የናቅፋ 'ቤዝ' ለሕልውናቸው ያስፈልጋቸዋል ። የኅሬላ ንቅናቄ አድጎ ወደ 'ኮንቬንሽናል» አቋም ከተለወጠ በኋላ ተመልሶ ሊበታተን አይችልም ። ወደ ዜሮ መመለስ ማለት ነው ። ወደዜሮ ከተመለሰ በተናጠል ሊሙቱ ይችላሉ ። የለም ፣ ይህ ጦርነት ለእነሱም ሆነ ለኛ ወሳኝ ነው ። ቁልፍ ቦታ ናቅፋ ትሆናለች» ካለኝ በኋላ ፣ ዓይኖቼን እያሻሸ ፣ «ፊያሜታ ጊላይን አግኝተሀት ታውቃለህ?» ሲል ጠየቀኝ ።

«ለምንድነው ሰው ሁሉ ስለእሷ የሚጠይቀኝ?? ከእሷ ጋር ምንም የለኝም ። አንድ ቀን ብቻ ነው ያየኋት ። ከዚያን ቀን በኋላ በስልክ ነው እንጂ ፊት ለፊት ተገናኝተን አናውቅም» በማለት ተናዘዝኩለት ።

«ለምን እንድትገናኙ አታደርግም?» አለኝ ።
«ለምን አደርጋለሁ? እስቲ ንገረኝ?»
«ቆንጆ ናት ። ይኸ ራሱ በቂ ምክንያት አይሆንም?»
«ገባኝ» አልኩት ።
«ምኑ?»
«ከእሷ የምትፈልገው ነገር ያለ ይመስለኛል»
«ካልክ እዎን»
«እኔን ትተህ ለምን በራስህ ልጆች አትጠቀምም ። እሳት የሳሱ ልጆች አሉህ ። እኔ ጋዜጠኛ ነኝ እንጂ ሰላይ አይደለሁም ፣ ልምዱም የለኝም» አልኩት ።

ለወሬ የሚያሸት ጥሩ አፍንጫ ያለው ሰው ጥሩ ሰላይ ነው ። በዚያ ላይ ደግሞ ጥሩ የእርበኝነት ስሜት ያለህ ይመስለኛል» አለ ።

«አርበኝነት ከዚህ ጋር ምን ግንኙነት አለው?»

«ላገሩ ፣ ላብዮቱ ፣ ባጠቃላይ ለሕዝብ ደኅንነት የሚሰልል ሁሉ ባሁኑ ጊዜ አርበኛ ነው ። ሕዝብ ደኅንነት እንደ ድሮ ጸረ ሕዝብ አይደለም ። ለማንኛውም ነገር አስብበት» ብሎኝ ሊሔድ ሲል ፣ «ለምንድነው ፊያሚታን በቅርብ እንዳውቃት የምትፈል ገው?» አልኩት ።

«በእሷ አማካይነት ሌላ ሰው እንድትቀርብ ነው» አለኝ ።

«ለምሳሌ እንደማን ያለ ሰው?»

«ሥዕላይ በራኺ» ብሎኝ ሔደ ።

ሳልወድ ስለ ሥዕላይ በራኺ ማሰብ ጀመርኩ ። ድምፂ ሐፋሽ የተባለው የወንበዴዎች ራዲዮ ጣቢያ ከሐዲ — አድርባይ እያለ በየቀኑ ይወርድበታል ። ግን ለምን? እነ ኢሣይያስ አፈወርቂን ከመሠረቱ ጀምሮ ከሲ አይ ኤ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደነበራቸው ማጋለጡ ይሆን የቀጠቀጣቸው? አሁን ሳስበው ፣ የግንኙነቱ ይፋ መውጣት ባሁኑ ወቅት ለእነሱ የሚበጅ እንጂ የሚከፋ መስሎ አልታየኝም ። ከጉዳቱ ጥቅሙ ያመዝናል ። አሜሪካ በኢትዮጵያ የደረሰባትን ጉዳት አትረሳም ። ቀይ ባሕርን የመሰለ ስትራተጂካዊ ሥፍራና ቃኘው ጣቢያን የሚያክል ዘመናዊ መገናኛ ማጣት ቀላል ጉዳት ባይሆንም ፣ ወደ ጥቁር አፍሪካ እመቾ መሸጋገሪያ የሆነች እንደ ኢትዮጵያ ያለች ታላቅ መድረክ ማጣት ዘላለም የሚያስቆጭ ነው ። ኢትዮጵያን አጥቶ ሶማሊያን ማግኘት ምንጊዜም ቢሆን ለአሜሪካኖች ምትክ ወይም ካሣ ሊሆን አይችልም ። እና አሁን አሜሪካኖች ከተገንጣዮች ሌላ በዚህ አካባቢ ምን መሣሪያ አላቸው? ከተቻላቸው በተገንጣዮች ትከሻ ተመልሰው ወደ 'ትራክ ኤ'ወደ 'ትራክ ቢ' ለመምጣት ይፈልጋሉ ። ቀይ ባሕር ። «ብራይት ስታር» ። ሥዕላይ የ'ብራይት ስታር'ን ዓላማ ከውስጥ ለማራመድ ይሆን ተመልሶ የመጣው?...... ባንድ ፊት አሳዘነኝ ። ከሁለት ዛፍ ያጣ ጉሬዛ!...... ግን ምን ሊያደርግ ይችላል?...... የጋዜጠኞች ጋጋታ አሳቤን አቋረጠው ።

የቴሌቪዥን ሰዎች ነበሩ ። ሲሠሩ የዋሉትን ፊልም በካርቶን አሸገው ይዘዋል ።

«ታዲያስ ልጆች እንዴት ነበር?»

«ሞቶናል ። ግን ፊልሙ ጥሩ ሳይወጣ አይቀርም ። ምናልባት አንዳንድ ቦታ ድምጽ ይበላሽ ይሆናል ። ዛሬ ማታ ማሳየት ከቻልን ተአምር ይሆናል» አለ አንዱ ከመካከላቸው ።

«በኔ ይሁንብህ» አልኩትና ፣ ወደሌላው የጋዜጠኞች ቡድን መለስ ብዬ ፣» እናንተስ ተሳካላችሁ? በማለት ጠየኳቸው።

ሕዝቡ ቢያለበት ንግግሩን በምን ሁኔታ ሲከታተል እንደዋለና ፣ ያለውን እስተያየትና ያደረበትን ስሜት በፊልም ፣ በፎቶግራፍና በዜና እንዲሠሩ ፣ አንድ የተሟላ የጋዜጠኛ ቡድን ወደ ከተማ ልኬ ነበር ።

«በጥሩ ሁኔታ ። ግሩም ነው ። ያልደረስንበት ቦታ የለም ። ግን ደክሞናል ። ጉሮሮአችን ደርቋል ። መሎቲ ቢራ ፋብሪካ ጋን ላይ ተቀምጠን ዝሑል ቢራ ሲጠማን ያሳዝናል» አለ ።

«ጋዜጠኞች ስትባሉ መቸም ገንዘብ አይበቃችሁም!» ብዬ ለዝሑል ቢራ አሥር ብር ጣልኩላቸውና ፣ «ግን ምሳችሁን እንደበላችሁ በቀጥታ ወደ ምጽዋ ። ፍጥነት ። እዚያ እንገናኛለን። እና በፈጠራችሁ ደግሞ መብራት ፣ ባትሪ ፣ ገመድ ምናምን እንዳትረሱ» አልኳቸውና ፊልሞቹንና ፎቶግራፎቹን ይዤ ወደ አርሚ አቪዬሽን በረርኩ ። ለዚሁ ሥራ የተመደበ የአርሚ አቪዬሽን ልዩ አይሮፕላን ተዘጋጅቶ ይጠብቀኝ ነበር ። ቲራቮሌን ወደኋላ እየተውኩ ወደ አርሚ አቪዬሽን በምበርበት ጊዜ ፣ ሁኔታው አሳቀኝ ፣ አወይ አለመታደል ። አሥመራ ላይ ጧት የተደረገውን ነገር ወደ አዲስ አበባ በአይሮፕላን ልክ ማታ በቴሌቪዥን እንዲቀርብ ማድረግ እንደተአምር የሚታይ ነገር ይሁን? ለዚያውም ተሳክቶ ቢሆንልን! ሠላም ፣ ሠላም ፣ አልኩ የኢትዮጵያ ዋና ፣ ዋና ከተሞች በሁለት አቅጣጫዎች በቴሌቪዥን መስመሮችና በራዲዮ መገናኛዎች ተገናኝተው ፣ ነገር ዓለም እንደ እሳት ሲቀጣጠል እየታየኝ። ቅዠት አይሉት ራእይ።ሠላም ይምጣ ፣ ብቻ የሚያሳዝነው ነገር ሚዲያዎችን ዞር ብሎ የሚያስታውስ የለም ። የዳቦ ጉዳይ ይቀድማል ። ሌኒን አንድ ጊዜ፣«ኮሚዩኒስቶች ሕልም ያያሉ?» ተብሎ ሲጠየቅ ፣ «ታዲያ ዳቦ ጠግበው ቢያገሱ የሚያድሩ መሰለህ? አዎ እናልማለን ፣ እኛ የምናልመው የተቻለ ዓለም ነው» በማለት የተናገረው ትዝ አለኝ ። ዓለም

ያለሚዲያ ምንድር ናት፤ እና ወደፊት ለችግራችን መፍትሔ የምንሻው በየትኛው መድረክ ላይ ይሆናል፤ በጦር ሜዳ ሆኖ መቅረት የለበትም አለበለዚያ መኖር ምን ይጠቅማል፤ የመግባባት፣የሠላምና የዕድገት መሣሪያ ካልሆነ ። የሚዲያ ማወናበድ ተጨምሮበት ይቅርና ፣ እንዲሁም ቢሆን ፣ ዓለም ተግባብቶ ለመኖር አልቻለም ። ምስኪን ዓለም! እና ደግሞ የመሐን ልጅ ትመስል ምትክ የሌላት እንድ ራሷን ፣ አንድ ብቻዋን ናት......

ሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ እንዲ ድሮው በፈገግታ አልተቀበለኝም። ሰውነቱ ከሳ ብሎአል ። እንዲያው ሲመለከቱት ስጋት ያለበት ሰው ይመስላል ። ሥራ በዝቶበት ይሆናል በማለት ቀዝቀዝ ስላለብኝ ቅር አላለኝም ። የጦር አይሮፕላኖች ፣ ሄሊኮፕተሮች ፣ ትናንሽ አይሮፕላኖች በየደቂቃው ይነሳሉ ፣ ይወርዳሉ ፣ ሰውና ዕቃ ይጫንና ይወርዳል ፣ አርሚ አቪዬሽን የእብድ ሠፈር መስሏል ። ግን ሻለቃ ታደሰ አይሮፕላኖች ሲነሱና ሲያርፉ ማየት እንደ በፊቱ ደስ የሚለው አይመስልም ። እንዲያውም አያያቸውም ።

«ምን እንዲህ አዘገየህ!» አለኝ ። ቁጣ እንጂ ጥያቄ አልነበረም ።

«ንግግሩ ትንሽ ዘግይቶ ስላለቀ ነው ። አይሮፕላኗ ለዚሁ ሥራ ብቻ አይደለም እንዴ የተመደበችው፤ ይደርሳል» አልኩት ።

«ቢሆንስ!» አለኝ እንደገና በቁጣ ።

ይህ ሰው ዛሬ ጤና የለውም እንዴ አልኩና በሆዴ ፣

«እሺ ጓድ ሻለቃ ። ነገሩ ከቁጥጥሬ ውጭ ሆኖብኝ ነው እንጂ አልዘገይም ነበር» አልኩትና ፊልሞቹን ሰጠሁት ።

በሌሎች ጊዜያት ወታደር ጠርቶ ያስጭን ነበር ። ዛሬ ግን ፣ ፊልሞቹ የታሸጉበትን ካርቶን ራሱ ይዞ ወደተዘጋጀችው አይሮፕላን ሲሮጥ በማየቴ ደስ አለኝ ። ወደ መኪናዬ ተመለስኩ ። ሠፈሩ ጆሮ ያደነቁራል ። የጦር አይሮፕላኖች ፣ አንቶኖቮች ይነሳሉ ፣ ያርፋሉ ። የመኪናዬን ሞተር አስነስቼ ልሔድ ስል ፣ ኪሴ ውስጥ የዘነጋሁት አንድ ጥቅል ፊልም ትዝ ብሎኝ ፣ ሞተሩን አጠፋሁና ተነስቼ ሻለቃ ታደሰን ፍለጋ ሮጥኩ ። አገኘሁት ። ካንድ ረጂም ፣ ቀጭን ፣ የመካኒክ ቱታ ከለበሰ ጠይም ወጣት

ጋር በሹክሹክታ እየተነጋገረ ፣ ፊልም ወደ አዲስ አበባ እንድት ወስድልኝ ከተመደበችው ልዩ አይሮፕላን ላይ ዕቃ ይጭን ነበር ። የማዳም መሎቲ አይሮፕላን የነበረች ናት ። ዘወር ባለ ሥፍራ ነበር የቆመችው ። በሚለዋወጡት የሹክሹክታ ንግግር ተመስጠው ነበር መሰለኝ ፣ ከኋላቸው ስመጣ ሁለቱም አላዩኝም ፣ አልሰሙኝም ። የያዙትን ሥራ ያጣድፋሉ ።

«ጓድ ሻለቃ» ብዬ ጠራሁት ።

ሻለቃ ታደሰ ድንገት ወደኔ ዞር አለ ፣ ለሁለት ይዘውት የነበረው ከባድ ካርቶን ከሁለተኛው ሰው እጅ አምልጦ ፣ አስፋልት ላይ ወርዶ ዘጭ ሲል ፣ ታሽጎ የነበረው ካርቶን ፣ ካንድ ጎን ተበጥርቆ አፉን ከፈተ ። ዓይኖቼ መሬት ከወደቀው ካርቶን ላይ ተተክለው ቀሩ ። ገና ከፋብሪካ የወጡ የሚመስሉ አዳዲስ ክላሺን መትረየስ መሣሪያዎች ብቅ ብለው ይታዩ ነበር ። አላስገረመኝም ። ሥፍራው አርሚ አቪዬሽን ነው ። ሁልጊዜ መሣሪያ ይጫናል ፣ ይወርዳል ። አዲስ ነገር አይደለም ። ዜና ሊሆን አይችልም ። ካርቶኑ ወድቆ ቢፈነዳና ፣ ፈንጂው አይሮፕላኗን ከተጫነችው ፊልም ጋር ቢያቃጥል ኖሮ ዜና ብቻ ሳይሆን ትራጀዲ ይሆን ነበር ። ይልቅ እንደ አዲስ ነገር ሆኖ ያስገረመኝ ነገር ቢኖር የሁለቱ ሰዎች ድንጋጤ ነበር ። ምን አስደነገጣቸው፣ ሁለተኛውን ሰው ከዚህ በፊት አንድ ቦታ ያየሁት መሰለኝ ፣ ቢሆንም ቦታው ጠፋኝ ። ወጣቱ መካኒክ ቶሎ ብሎ ነፍስ በመግዛት ፣ ምንም ነገር እንዳልሆነ አስመስሎ ካርቶኑን በመሸፋፈን በሲባጎ ያስር ጀመር ።

«ምንድን ነው!» አለኝ ሻለቃ ታደሰ በጎረና ድምጽ ።

«ይህችን ፊልም እኪሴ ውስጥ ረስቼ ነው ። »

«የምን መዝረክረክ ነው፣ ለምን በፊት አታስብበትም ኖሮአል?»

አለኝና የፊልሟን ጥቅል ከእጄ ምንጭቅ አድርጎ ወሰዳት ። ሁኔታው ደስ አላለኝም — «ጓድ ሻለቃ ፣ ሥራ ሲበዛ ምን ይደረግ፣ ይኸው እንደምታየው ነው» አልኩትና ለማግባባት ያህል ፣ «ለመሆኑ መቸ ጊዜ ታገኘልኛለህ?» ብዬ ጠየኩት ።

«ለምን?»

«ስለዚህ ኢንተርቪው ጉዳይ.....»

«ጊዜ የለኝም.....»

«ይገባኛል ። ሥራ ይበዛብሀል ። ቢሆንም ከሰሞኑ ጊዜ ታገኝልኛለህ ብዬ ተስፋ አድርጌአለሁ ። ጡረታ ከመውጣትህ በፊት አንተን ኢንተርቪው ማድረግ አለብኝ ። ጥሩ ታሪክ ይወጣል» አልኩት ።

«አስብበታለሁ» አለኝ ሻለቃ ታደሰ ።

ሽበት በዝቶበታል ። ባለፈው ሰሞን ሳየው ብዙ ሽበት አልነበረውም ። ፊቱም ጠቋቁሮአል ። ሽበት ያልጨመረና ያልጠቆረ ማን አለ? የቀይ ኮከብ ዘመቻ ጊዜ ብዙ ሰዎች ያሸብታል ፣ ያጠቁራል ፣ ያከሳል ። እኔም ጥቂት ሽበት ሳላበቅል አልቀረሁም።

ከመሔዴ በፊት ፣ «በነገራችን ላይ» አልኩት —

«ያው እንደተለመደው አዲሳባ አርሚ አቪዬሽን ሔደው ነው የኛ ሰዎች ፊልሙን የሚወስዱትን?»

«አይደለም ። ቦሌ» አለና ጀርባውን ሰጥቶኝ ፣ «ሌላ ጥያቄ ከሌለህ አሁን ሥራ ይበዛብኛል» ብሎ ነገረኝ ። አባባሉ ከዚህ ጥፋ እንደማለት ያህል ነበር ። እኔም ጊዜ አልነበረኝም ። አሳቤ ወደ ምጽዋ ሔዶ ነበር ።

# ታላቅ በዓል
# በርእሰ ምድሪ

ከአሥመራ ወደ ምጽዋ መሔድ ከ7,500 ሜማ ከፍታ በጭንቅላት ወደ ታች ተወርውሮ ቀይ ባሕር ውስጥ እንደ መደፈቅ ያህል ነው ። ደግነቱ የምጽዋ ሙቀት በወላፈናዊ ፈገግታው እጅ ነስቶ አልተቀበለኝም ። ምጽዋ በጥር ወር ክረምት ስለሆነ ትንሽ ይበርዳል ። ቢሆንም ፣ ለምጽዋ «ፌስቲቫል» ከኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ጉባኤ ላይ እንዳለ ተነስቶ በየብስና በአየር ወደ ምጽዋ የተገለበጠው ሕዝብ ለበዓሉ በተለይ የተሠራውን ሹራብ ለብሶ ርእሰ ምድሪን አጣቦ ይታያል ። ምጽዋ የበዓል ስሜት አድሮባታል ። የበዓል አየር ይነፍስበታል ። የበዓል ሰንደቅ ዓላማዎች ይውለበለቡባታል ። ጸጥ ብሎ የተነጠፈው ቀይ ባሕር ፣ የምሽት ጀምበር ወርቃማ ጨረሮች ከላይ እየዘነቡ የሚሞሉት የቀለጠ ብር ፍሳሽ ሐይቅ መስሎ ተንጥፎአል ። የምጽዋ አድማስ ቀይ ብርቱካን በመሰለ ቀለም ነዷል ። ወደ ምሽት ላይ ነበር ምጽዋ የደረስኩት ።

ምጽዋ በበዓል ስሜት ታድማና አሸብርቃ ብትታይም ፣ ውበቷ የሚማርከው ቀን ሳይሆን ማታ ነው ። ቀን ፣ ቀን ታንቀላፋለች ። ማታ ሲሆን ነው የምትነቃውና የምትደምቀው ። ቢሆንም የድሮ ውበቷንና ድምቀቷን አጥታለች ። ከሦስት ዓመት በፊት አሰቃቂ እልቂትና ጥፋት የታየባት የጦርነት ዐውድማ ነበረች ። ጠበሳ ዕዳጋ ፊት ላይ አሁንም ይታያል ።

ሻዕቢያ ፣ ከታህሣሥ ወር 1970 ጀምሮ ለዘጠኝ ወሮች ፣ ምጽዋ ከሚገኙት አሥራ ሦስት ቀበሌዎች ውስጥ አሥሩን በቁጥጥር ሥር አድርጋ ነበር ። ዕዳጋ ፣ ከነዳጅ ማጠራቀሚያው አካባቢ ጀምራ ፣ የባሕሩን ጠርዝ ሳትለቅ ፣ በጉርጉሱም እስከ ስሚንቶ ፋብሪካ ድረስ በመመሸግና ፣ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ላይ ሦስት ባለ ሀምሳ ካሊቨር መትረየሶች በመጥመድ

«ይገባኛል ። ሥራ ይበዛብሀል ። ቢሆንም ከሰሞኑ ጊዜ ታገኝልኛለህ ብዬ ተስፋ አድርጌአለሁ ። ጡረታ ከመውጣትህ በፊት አንተን ኢንተርቪው ማድረግ አለብኝ ። ጥሩ ታሪክ ይወጣል» አልኩት ።

«አስብበታለሁ» አለኝ ሻለቃ ታደሰ ።

ሽበት በዝቶበታል ። ባለፈው ሰሞን ሳየው ብዙ ሽበት አልነበረውም ። ፊቱም ጠቍሮአል ። ሽበት ያልጨመረና ያልጠቆረ ማን አለ? የቀይ ኮከብ ዘመቻ ጊዜ ብዙ ሰዎች ያሸብታል ፣ ያጠቁራል ፣ ያከሳል ። እኔም ጥቂት ሽበት ሳላበቅል አልቀረሁም።

ከመሔዴ በፊት ፣ «በነገራችን ላይ» አልኩት —

«ያው እንደተለመደው አዲሳባ እርሚ አቪዩሽን ሔደው ነው የኛ ሰዎች ፊልሙን የሚወስዱት?»

«አይደለም ። ቦሌ» አለና ጀርባውን ሰጥቶኝ ፣ «ሌላ ጥያቄ ከሌለህ አሁን ሥራ ይበዛብኛል» ብሎ ነገረኝ ። አባባሉ ከዚህ ጥፋ እንደማለት ያህል ነበር ። እኔም ጊዜ አልነበረኝም ። አሳቤ ወደ ምጽዋ ሔዶ ነበር ።

# ታ ላ ቅ  በ ዓ ል
# በ ር እ ሰ  ም ድ ሪ

ከአሥመራ ወደ ምጽዋ መሔድ ከ7,500 ጫማ ከፍታ በጭ ንቅላት ወደ ታች ተወርውሮ ቀይ ባሕር ውስጥ እንደ መደፈቅ ያህል ነው ። ደግነቱ የምጽዋ ሙቀት በወላፈናዊ ፈገግታው እጅ ነስቶ አልተቀበለኝም ። ምጽዋ በጥር ወር ክረምት ስለሆነ ትንሽ ይበርዳል ። ቢሆንም ፣ ለምጽዋ «ፌስቲቫል» ከኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ጉባኤ ላይ እን ዳለ ተነስቶ በየብስና በአየር ወደ ምጽዋ የተገለበጠው ሕዝብ ለበዓሉ በተለይ የተሠራውን ሹራብ ለብሶ ርእሰ ምድሪን እጣበ ይታያል ። ምጽዋ የበዓል ስሜት አድሮባታል ። የበዓል አየር ይነፍስበታል ። የበዓል ስንደቅ ዓላማዎች ይውለበለቡ ባታል ። ጸጥ ብሎ የተነጠፈው ቀይ ባሕር ፣ የምሽት ጀምበር ወርቃማ ጨረሮች ከላይ እየዘነቡ የሚሞሉት የቀለጠ ብር ፍሳሽ ሐይቅ መስሎ ተነጥፎአል ። የምጽዋ አድማስ ቀይ ብርቱካን በመሰለ ቀለም ነዷል ። ወደ ምሽት ላይ ነበር ምጽዋ የደረስኩት ።

ምጽዋ በበዓል ስሜት ታድማና አሸብርቃ ብትታይም ፣ ውበቷ የሚግርከው ቀን ሳይሆን ማታ ነው ። ቀን ፣ ቀን ታንቀ ላፋለች ። ማታ ሲሆን ነው የምትነቃውና የምትደምቀው ። ቢሆ ንም የድሮ ውበቷንና ድምቀቷን አጥታለች ። ከሦስት ዓመት በፊት አስቃቂ እልቂትና ጥፋት የታየባት የጦርነት ዐውድማ ነበረች ። ጠበሳ ዕዳጋ ፊት ላይ አሁንም ይታያል ።

ሻዕቢያ ፣ ከታህሣሥ ወር 1970 ጀምሮ ለዘጠኝ ወሮች ፣ ምጽዋ ከሚገኙት አሥራ ሦስት ቀበሌዎች ውስጥ አሥሩን በቁጥጥር ሥር አድርጋ ነበር ። ዕዳጋ ፣ ከነዳጅ ማጠራቀሚ ያው አካባቢ ጀምራ ፣ የባሕሩን ጠርዝ ሳትለቅ ፣ በጉርጉሱም እስከ ስሚንቶ ፋብሪካ ድረስ በመመሸግና ፣ ሚካኤል ቤተ ክርስ ቲያን ላይ ሦስት ባለ ሀምሳ ካሊቨር መትረየሶች በመጥመድ

ወይ ንቅንቅ ፣ ወይ ፍንክች ያባ ቢላዎ ልጅ ብላ ነበር ። ዕዳጋንና በወገን ጦር ቁጥጥር ሥር የነበሩትን ሦስት ቀበሌዎች ፣ ማለትም ጢሌትንና ሁለቱን ምጽዋዎች የሚያገናኘውን ብቸኛ ድልድይ እላሽጋግር አለች ። ወደ ምሽጐቿ መጠጋት የሚቻለው ጨው በሚመረትበት ረግረግ መሬት ብቻ ነበር ። በዚያ መሔድ ደግሞ እልቂትን በራስ ላይ እንደመጋበዝ ነበር ።

፯

አብዮታዊው ነጻ እውጭ ሠራዊት ዕዳጋ ላይ የነበሩትን የሻዕቢያን ምሽጎች ሰባብሮ እንዴት ለመግባት እንደቻለ ወደ ኋላ መለስ ብዬ አሁን ባስበው በጣም ደነቀኝ ። እጅግ የሚያስደ ንቅና በእውነትም ትንፋሽ የሚያሲይዝ ወኔ የተሞላበት ጀብዱ ፣ ቆራጥነት የተሞላበት መስዋእትነትና እኩሪ አብዮታዊ እርበኝ ነት የታየበት ፣ ቀይ ሰው የጠቆረበት ፣ ጥቁሩ ሰው የቀላበት ፣ ሳንጃ ሲሞሻለቅ ፣ የሰው ልጅ አንገት ላንገት ተናንቆ የተዋደ ቀበት አሰቃቂ ጦርነት ነበር ። ራስን አሳልፎ ለሞት የመዳረግ ተልእኮ ነበር ።

ተልእኮው እንዲህ ነበር ። የሻዕቢያ አመሻሸግና አሰላለፍ ሲጠና ቆይቶ ዕቅድ ወጣ ። እቅዱን በማውጣት ላይ የተሳተፉት መኰንኖች ከዘመቻው እዳራሽ ለተወሰነ ጊዜ እንዳይወጡ ተደረገ ምስጢር እየባከነ አስቸግሮ ነበር ። ያለ ዕድል ሆኖ አብዮታዊው ሠራዊት ከወገንም ከጠላትም ጋር ተመሳጥሮ ነው የሚኖረው ። ውጊያ እንደማታ ሊሆን ፣ ቀን ሠራዊቱ እንዲዝናና ተደረገ ። ማታ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ ፊሽካ ተነፋ ። ዕቅዱን የሚያው ቁት መኰንኖች ጦራቸውን ይዘው ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ወጡ።የማወናበጃ ተኩስ ጎሕ ቀደደ ። አንዱ ግንባር ከናቫል ቤዝ ተነስቶ ረግረጉን መሬት በመያዝ በሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ ሲሔድ ፣ ሁለተኛው ግንባር ከጢሌት ተነስቶ እናት ምጽዋንና ዕዳጋን ወደሚያገናኘው ትልቁ ድልድይ ገሰገሰ ።

«ምንድን ነው የምትጠብቀው !» እለ አስተኳሽ መኰንን ።
«እንዴት ብዬ? »

«ተኩስ ነው የምልህ!» ብሎ ሽጉጥ እወጣበት ። ተኳሹ «ቅዱስ ሚካኤል ይቅር በለኝ» በማለት ሁለቱ አማተበና መድ ፉን ለቀቀው ። ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ላይ ተጠምዶው

የነበሩት የሻዕቢያ መትረየሶች ጭጭ ፣ ምጭጭ አሉ ። የወገን ጦር በሁለቱም ግንባር ሳንጃ ባፈሙዝ ብሎ የእጅ ቦምቡን እንደ ያዘ ከጠላት ምሽጐች ውስጥ እየዘለለ ይገባ ጀመር ። ከቀኑ አምስት ሰዓት ላይ የሻዕቢያ ምሽጎች እንዳሉ ተሰበሩ ። የወንበዴ መንጋ ተረፈረፈ ። የዕዳጋ ጦርነት ፍጻሜ ሆነ ። ከወገን ጦር 6 ሺህ ሰዎች ይሰዋሉ ተብሎ ተገምቶ ነበር ። በዕዳጋ ጦርነት የሞቱት ስድስት መቶ ሰዎች ብቻ ነበሩ ። የሻዕቢያ ምርጥ ተዋጊ ዎች እንዳሉ ያለቁበት ፣ ምሽግ የመመሸግ ጥበቧና ጀብደኝነቷ የታየበት ጦርነት ነበር ። ዕዳጋ ከፎርቶ አጠገብ ፣ አሸዋ ውስጥ ተቀብረው የቆዩ ሁለት የሰው ጭንቅላት አጥንቶች አግኝቼ እየተመለከትኩ ሳስብ ነበር የቆየሁት ። በመጨረሻ ሁለቱን አጥንቶች አስተያየሁ ። የትኛው ይሆን የቱ? አንዱን ከሌላው ለይቼ ለማወቅ አልቻልኩም ። ሁለቱም አንድ ዓይነት ቅርጽ ያላቸው የኢትዮጵያውያን ጭንቅላት አጥንቶች ነበሩ ። ሁለቱንም አጥንቶች ካገኘኋቸው ሥፍራ መልሼ በጥንቃቄ አሸዋ ካለበስ ኳቸው በኋላ እያዘንኩ ወደ መኪናዩ ስሔድ እንደ ንፋስ የሚበሩ ቶዮታ ክሩዘር መኪናዎች ወደኔ አቅጣጫ ሲመጡ አየሁና ቆም አልኩ......

«ጺጋዬ ! »

ሰሎሞን በትረ ነበር ። እሱ ድንገት የመኪናውን ፍሬን ሲይዝ ዓይኖቼን ጨፈንኩ ። ከኋላው ይበሩ የነበሩ አጃቢ መኪና ዎች ሲላተሙ ነበር ። እሱ ደንታ አልሰጠውም ።

«ምን ታረጋለህ እዚህ?»

«ጉብኝት ላይ ነበርኩ......»

«ከመቼው?»

«ንቅናቄ የሙያችን አንዱ አካል አይደለ?» አልኩት ።

«ግባ» አለኝ ።

«ወዴት?»

«ጉርጉሱም ላይ የሚደረገውን ዝግጅት አይተን እንመለ ሳለን ። ግባ» አለኝ ።

«መኪናዩስ?»

«ምንም አትሆንም ። መንገዱም ፣ ከተማውም ተወጥሯል ። ከአሥመራ እስከ ምጽዋ ያለው መንገድ እንዴት እንደተወ ጠረ አላየህም?» አለኝ ።

መኪናው ላይ ወጥቼ ተሳፈርኩ ። ፒፓ ባፉ ይዟል ። መኪናው ባንዳፍታ ተንስታ መብረር ጀመረች ። እንደ እብድ ነው የሚነዳው ። በጠየቀኝ መሠረት ከአሥመራ ወደ ምጽዋ ከእሱ ጋር ባለመምጣቴ ዕድሌን አመሰገንኩ ። በነፋሲት ፣ በእምባቲካላ ፣ በጊንዳዕ ፣ በዶንጎሎና በዶጋሊ ገደላ ገደል ጠርዞች ላይ እንደዚህ እየበረረ ቢያመጣኝ ኖሮ ይኸኔ ቢያንስ ሁለት ኪሎ ክብደት ቀንሼ ነበር ። የምጽዋ መንገድ እንኳን በረውበት እንዲሁም ሲያዩት የራስ ጠጉር ተነስቶ እስኪቆም ድረስ ያስፈራል ።

«የጢቱ ሥራ እንዴት ተሳካልህ?» አለኝ ።
«ጥሩ ነበር ። ኢትዮጵያ ጆሮ ብቻ ሆና ነበር ።»

«ተአምር ነው!» ብሎ ፒፓውን እንደነከሰ በጥርሶቹ መካከል በመነጋገር ፣ «መኘታ አገኘተሀል?» ሲል ጠየቀኝ ።
«እዎ ፣ ዕድሜ ላንተ ዳሕላክ ክፍል ተይዞልኛል ። ግን ብዙ ሰዎች ክፍል አጥተው ሲያገርሩ ሰምቻለሁ ።»

ፒፓውን ካፉ አወጣና ፣ «ተዋቸው እባክህ! የፕሮቶኮል በሽታ ያለባቸው ሰዎች አሉ ። እኔን የሚያሳስበኝ ያንዳንድ ሰዎች ማማረር ሳይሆን የአጠቃላዩ ሥራ መሳካት ነው» እንዳለኝ ከጉርጉሱም ወደ ምጽዋ ይጓዝ የነበረው ባቡር ሲያልፍ አይቶ «ሌላው ተአምር ደግሞ ያውልህ» አለ — «ወንበዴዎች ሰባብረው ለምሽግ የተጠቀሙበት ሐዲድ የተሠራው ባሥራ አምስት ቀን ነው። ሰው መሥራት ከፈለገ የማይሠራው ተአምር የለም ። የጣሊያን ኪነት ቡድን፥ «ፈጣን ነው ባቡሩ ባቡሩ» የሚለው ዘፈን እየዘፈነ በሐዲዱ ላይ ሲጓዝ አይታይህም?»
«ይታየኛል » አልኩት ።

«ታውቃለህ? እስቲ አስብ» አለና እንደገና ፒፓውን ካፉ አውጥቶ «እንዳንዴ ባስበው ይህ አብዮት ያስደንቀኛል ። 56 ሺህ ተማሪዎችን ባንድ ጊዜ ለዕድገት በኅብረት ዘመቻ ማሰለፍ ፣ ታጠቅ ጦር ሠፈርን ከመቅጽበት ማቋቋም፣300,000 ሺህ ሚሊሺያ በጥቂት ወራት ውስጥ አሠልጥኖና አስታጥቆ ለውጊያ ብቁ ማድረግ — ይህ ሁሉ እና አሁን ደግሞ ለቀይ ኮከብ ዘመቻ ጉባኤ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን ከመላ ኢትዮጵያ አሰባስቦ ጢት አሥመራ ፣ ከሰዓት በኋላ ምጽዋ እንዲገኙ ማድረግ — ቀላል ሥራ

አይደለም ። ድርጅታዊ አሠራር ይጠይቃል ። ከአብዮቱ በፊት ኢትዮጵያ ስንት ከፍለ ጦር እንደነበራት ታውቃለህ? አራት ብቻ ነበሩ ። አሁን ስንት እንዳለን ታውቃለህ? ሦስት እጅ እጥፍ ። በእውነት ያብዮት የማደራጀት ችሎታ ያስደንቀኛል ።

«እውነቱን ነው የምልህ ። በአብዮት ሂደት ውስጥ አልፈን እዚህ ለመድረስ ዕድሜ ያገኘን ሰዎች ባገኘነው ልምድ ፣ ወደፊት አብዮት ለማካሔድ የሚነሱትን ሕዝቦች ልንረዳ እንችላለን። ከነጋፉ ሶሻሊስት አገሮች ልምድ ይልቅ ፣ አብዮት ለማካሔድም ሆነ ለመከላከል የኛ ልምድ ይበልጥ ይጠቅማቸዋል ። አንዳንዴ ሳስበው ስለአብዮት የሚያማክር ኩባንያ ለምን አላቋቁምም? እላለሁ ። የኛ አብዮት ታሪክ የድርጊት ገድል ነው ።»

የመኪናውን ፍጥነት ቀነሰ ። ጉርጉሱም ባሕር ዳርቻ ላይ የድንኳን ከተማ አብቦ ይታያል — ቅጠልያ ፣ ቀይ ፣ ሰማያዊ ፣ ብጫ ድንኳኖች ።

«ማን ይህ ሁሉ በምን ኪሣራ?» አልኩት ።
«የቱ?»
«አሁን ያልከው ሁሉ ። »

መኪናውን አቆመ ። ሞተሩን አጠፋ ። ከኋላ ይከተሉት የነበሩት አጃቢዎች ከመቼው ተስፈንጥረው እንደወረዱ ባላውቅም ፣ ከሰለሞን መኪና ዙሪያ ፈንጠር ፣ ፈንጠር ብለው ቆመው ነበር ። ከመኪናው ከመውረዱ በፊት ፣ «ጋዜጠኞች ስትባሉ ፣ ከሙያችሁ መነጽር ጉድለት የተነሳ ነው መሰለኝ ፣ ሁልጊዜ ተቃራኒውን ነገር የምታዩ ተጠራጣሪ ፍጡሮች ናችሁ ። ታውቃለህ? የሰው ልጆች ታሪክ በሙሉ የድርጅታዊ አሠራር ዕድገትና ጥንካሬ ታሪክ ነው» አለኝና ከመኪናው ወረደ ።

የምጽዋ ፌስቲቫል ኮሚቴ አባሎች መጥተው ከበውት ነበር። ተፈጥሮአችን ሆኖ ባለሥልጣን ከበብ ፣ ከበብ ፣ አጀብ ፣ አጀብ ፣ ተሽቀዳድሞ ግንባር ማስመታት እንወዳለን ልበል! ወዲያውኑ መዓት ሰዎች መካከል ገብቶ ጠፋብኝ ። ጉርጉሱም ባሕር ዳርቻ ውብ ነው ። ማዕበል በማዕበል ላይ እየተደራረበ ፣ እያሰመሰመ ፣ እንደ ጋራ እየተናደ መጥቶ ፣ ለባሕሩ ዳርቻ የሚሰግድ ይመስል

ወደ ላይ ተነስቶ ተመልሶ ይወድቅና አሸዋውን እጥቦ ይመለሳል ። ከመሐል አገር የመጡ ፣ ምናልባትም ባሕር ምን እንደሚመስል በሕይወታቸው አይተው የማያውቁ የሚመስሉ ብዙ ሰዎች ፣ ወንዶችና ሴቶች ፣ የሰማይ ስባሪ መስሎ የተነጠፈውን የባሕሩን ስፋት ፣ የማዕበሎቹን ያነሳስና ያወዳደቅ ተፈጥሮአዊ ስልት ጨዋታ ፣ ዝም ብለው አፋቸውን ከፍተው በአድናቆት ይመለከታሉ ። ከባሕሩ ወለል ጉብታ ላይ ወጥታ የተንሳፈፈች የምትመስል መርከብ ካድማሱ ትግ ቆማ ከሩቅ ትታያለች ። የኤሌክትሪክ ብርሀን ጨረሮች ባሕሩ ላይ እየተንጸባረቁ ልዩ ልዩ ጥላዎች በመፍጠር የቀለማት ትርኢት ማሳየት ጀምረዋል ። በብዙ መቶ የሚቆጠሩ እንግዶች ከየድንኳኖቻቸው ወጥተው ባሕር ዳርቻው ላይ ፈሰው ይታያሉ ። የባሕር ዳርቻው የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች አባላት ፣ የሀይማኖት መሪዎችና የሕዝባውያን ድርጅቶች ተወካዮች አንድ ላይ ተሰብስበው የተገኙበት የድንኳን ከተማ ሆኗል ። የምጽዋ ፌስቲቫል የሚከፈትበት ቀን ዋዜማ እንደመሆኑ ፣ አዲስ አበባ ከሚገኙ ቲያትር ቤቶችና ከልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገር የመጡ የኪነት ጓዶች በየሠፈራቸው የሚያሰሙት ጥዑመ ሙዚቃ አየሩ ላይ እየተንጣለለ ይሰማል — ከባሕሩ ላይ ይንሳፈፋል ፣ ከማዕበሎቹ ጋር እየተላጋ ይወድቃል ።...... ሰለሞን በትሩ አስጠራኝ......

«የት ነበርክ?» አለኝ ።
«እየዞርኩ ስመለከት ነበር ።»
«ዝግጅቱ እንዴት ነው? ደስ አይልም ወይ?»
«ጥሩ ነው ። ደስ ይላል ።»

«አዎ ፣ ነገ ጉርጉስም ላይ መብላት ፣ መጠጣት ፣ መጨፈር ነው ። ኢትዮጵያ ላለፉት አራት መቶ ዓመታት እዚህ ባሕር በሯ ላይ ተደስታ አታውቅም ። ቀይ ባሕር ላይ ስትደማ ነው የኖረችው ። ባንጻሩም ፣ ቀይ ባሕር ለሕልውናችን ምን ያሀል አስፈላጊ እንደ ሆነ — ሕይወታችን ትንፋሻችን መሆኑን ማወቅ ይጠቅማል ።

እርግጠኛ ነኝ ፣ ከመሐል አገር ተጋብዘው ከመጡት ውስጥ ብዙዎቹ ቀይ ባሕር የት እንደሆነና ምን እንደሚመስል አይተው አያውቁም ። ለብዙዎቻችን የአስተሳሰብ አድማሳችን ከመንደራችን ፣ ከወንዛችን አልፎ አይሔድም ። እውነቱን ነው ፣ የኢትዮ

ጽያ ሕዝብ በሙሉ እዚህ መጥቶ ቀይ ባሕርን ለመመልከት ቢ ችል እንዴት ደስ ባለኝ — ያባቶቹን ተጋድሎ ታሪክ በቀላሉ ይረዳ ነበር ። የቀይ ኮከብ ዘመቻችንንም ትግል ዓላማ ይበልጥ ይገነዘብ ነበር» በማለት ንግግር አደረገልኝ ።

ሰለሞን እንዴ መናገር ከጀመረ ሙሉ ንግግር አድርጎ ሳይ ጨርስ ንግግሩን አያቋርጥም ። ከንግግሩ ትንሽ ማስታወሻ ወሰ ድኩለት ። ቀይ ባሕርንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕልውና በሚመለ ከት አንዳንድ ጥሩ ነጥቦች ነበሩት ። ቀጠለና ፣ «እነዚያ ትኩሎች ይታዩሀል?» አለኝ በጣቱ ወደ ትኩሎቹ እየጠቆመኝ ።

በተደረገው ዝግጅት ሁሉ የተደሰተ ይመስላል ። የምጽዋ ፌስቲቫል ኮሚቴ እንደ ንብ ሲሠራ ነበር የከረመው ። አንዳን ዶቹ የኮሚቴው አባሎች ከድካምና ከስጋት የተነሳ ሰውነታቸው ሊፈርስ የደረሰ ይመስላሉ ።

«አዎ ፣ ይታዩኛል» አልኩት ። ሁለት ትላልቅ ትኩሎች ተሠርተው ነበር ።

«በአይሮፕላን ሣር የተሜነላቸው ትኩሎች ናቸው» አለኝ። ዝም አልኩ ።

«በምን ኪሣራ አትለኝም?» አለኝ ወደ መኪናው እየሔደ ። የቸኮለ ይመስላል ። ሁልጊዜ ይቸኩላል ። መኪናዬ ጋ እደረሰ ኝና ፣ «ተከተለኝ» አለኝ ።

«ወዴት ደግሞ?»

«ወደ ካሌብ አዳራሽ የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽን ዝግጅት ማየት እፈልጋለሁ.....»

«እዚያ ነበርኩ ። አዳራሹ ውስጥ ማድረግ ያለብንን ዝግ ጅት ሁሉ አጠናቀናል ። በበዓሉም ሥፍራ አስፈላጊው ሁሉ ተደርጓል ። ለነገ ተዘጋጅተናል ። አሁን የሚያስፈልገኝ ነገር ቢኖር እረፍት ብቻ ነው» አልኩት ።

«የፌስቲቫሉ ጠቅላላ ፕሮግራም ደርሶሀል?» አለኝ ።

«አዎ ። ዶጋሊ ላይ ነገ የሚደረገው ሥርዓት በስንት ሰዓት እንደሆነ ግን አላውቅም.....»

«ባሥራ ሁለት ሰዓት እዚያ መገኘት ነው ። ትክክለኛውን ሰዓት እኔም አላውቅም» ብሎኝ በረረ ።

በጊዜ ለመተኛት አስቤ ነበር ወደ ሆቴሌ የተመለስኩት ። ባሕሩ በመስኮቴ ወለል ብሎ ይታያል ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ የመብራት ነጸብራቆች ባሕሩ ላይ ይጫወታሉ ። ማዕበሎች እየተነሱና እየወደቁ መጥተው የባሕሩን ዳርቻ አጥበው ሲመለሱ ይሰማል ። እንቅልፍ እምቢ አለኝ ። «ሻወር» ወስድኩና ወደ ሆቴሉ ቡና ቤት ወረድኩ ። ቢራ ጠምቶኝ ነበር ። ችግሩ ለእግር መረማመጃ ቦታ አልነበረም ፡ ከጉባኤው ላይ ተነስተው የመጡት ባለሥልጣኖች ቡና ቤቱን አጣበውት ይታያሉ ። አንዳንዶቹ ይሳሳቃሉ ። ሌሎቹ ይከራከሯሉ ፣ ጥቂቶቹ በምር የሚወያዩ ይመስላሉ ። አንዳንዶቹ ደግሞ ቢራ የሚያልቅባቸው መስሏቸው ሳይሆን አይቀርም ፣ ባንኮኒውን ተደግፈው ይህን ያላበው ቢራ ባናት ባናቱ ይሉታል — ይከለብሱታል ። በመስተንግዶው መዝረክረክ የሚያማርሩም ሰዎች ነበሩ ። ትርምስ ነበር ። ኩሉኔል በትሩ ተሰማ ጥግ ይዞ ቆሞ ባለሥልጣኖችን በዓይኑ የሚቆጥር ይመስላል ። ነገሩ ፍየሎችን እንደማገድ ሳይሆንበት አልቀረም ። ተከላይ ዘድንግል ካንድ ረጅም ሰው ጋር ያወራ ነበር ። የሰውዬው መልክ ትዝ አለኝ ። ቀትር ላይ እርሚ አቪዬሽን ከሻለቃ ታደሰ ጋር ያየሁት ወጣት መካኒክ ነበር ። በፊትም ይህን ሰው ያየሁት ከተከላይ ጋር እንደሆነ አሁን ትዝ አለኝ ። ወደእነሱ ልሔድ ስል ሥዕላይ በራኺ በባለሥልጣኖች መካከል ሲሽሎከለክ አየሁትና ፣ ተሽሎከልኬ ሔጄ ትከሻውን ያዝኩት ።

«ሃይ ሳልሼ ብጻይ ጸጋዬ ። አለኝ»
«የት ጠፍተህ ከረምክ?» አልኩት ።

«አለሁ ። ከነገ ወዲያ ማታ በሲምፖዚየሙ ላይ የማቀርበውን ጥናት ሳዘጋጅ ነበር የከረምኩት ። ሰሰው ጊዜ አትስጡም» አለ ።

«የምንሰጠው ጊዜ ስለሌለን ነዋ.....»
«ሩጫው እንደሚያዛልቃችሁ ተስፋ አደርጋለሁ.....»
«እንዴ አንተ ማን ነህና?»
«እኔ..... እኔማ ወዶ ገብ ነኝ» አለ በምሬት.....

«ወዶገብ ማለት ትተናል ። አሁን«በሠላም ወደ ማኅበረሰቡ የተመለሱ» እያልን ነው የምንናገረው አሁን ደስ አለህ?»

«በሙላም አልከውን»
«ታዲያ ምን እንበል?»

ምጸታዊ ፈገግታ አሳይቶኝ ዝም አለ ። ዓይኖቹ ይቅበዘበዛሉ ። የሚጠብቀው ሰው ያለ ይመስላል ። የረጋ መንፈስ አይታይበትም ።

«የምታቀርበው ጥናት ስለምንድነው?»
«ሻዕቢያ ከሲ አይ ኤ ጋር ስላላት ግንኙነት...»
«ምን ይጠቅማል?»

«አድሐሪ አቋም ያላት መሆኗን ለማጋለጥ ይረዳል ። እንዴት ምን ይጠቅማል ትላለህ?» አለኝ ፊቴን በጥንቃቄ እያጠና ።

«ታሪካዊ ግንኙነታቸውን ማጠናከር ይሆናል ብዬ ነው ። አዲስ ከስተት አይደለም ። ሲ አይ ኤ ለጥቅሙ ፣ ሻዕቢያ ለሕልውናዋ ሁለቱም ለጥቅማቸው እንደሚፈላለጉ እናውቃለን ፣ ወይስ አይደለም?» አልኩት ።

የንዴት ጥላ ከፊቱ ላይ ውልብ ሲል አየሁ ። መልስ አልሰጠኝም ቀጠልኩና ፣ «ሻዕቢያ እንደ ጦጣዎች ናቅፋ ተራራዎች ላይ ተንጠላጥላ ከመጠበቅ ሌላ ምርጫ የላትም» ያልከውን ነገር አሁንም ከልቤ አልተቀበልኩትም አልኩት ።

«ለምን? ሌላ ምን ምርጫ ይኖራታል?»

«ኃይሏን እንደገና በትና የደፈጣ ውጊያ ማካሄድ፣በከተሞች ሽብር መፍጠር — የልማት ሥራ እንዳይካሔድ ማድረግ — ሕዝቡ እንዳይደራጅ የገበሬ ማኅበሮች መሪዎችን ማፈን — እንደዚህ ያሉትን ነገሮች ለማድረግ ምን ይሳናታል?» አልኩት ።

«ዝጋ በቃ...! ታላቅ ምናብ አለህ!» አለና በነገሩ ሳቀ ።

«በቅርብ ጊዜ የመጣህ እንደመሆንህ ይህን ነገር ማወቅ ነበረብህ ። እንዴት ሳታውቅ ትቀራለህ? የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልም ነበርክ» አልኩት ።

እንደገና ፊቴን በጥንቃቄ ሲያጠና ከቆየ በኋላ ፣ «የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሁሉ ምስጢር ያውቃል አሉህ? በተለይ ፣ የሻዕቢያ አመራር ዝግ ነው ። ትእዛዝ ትፈጽማለህ እንጂ አትወያይበትም ። ለማንኛውም ነገር የመረጃ ሰዎች ሚና መጫወት ይቅርብህ ። በጋዜጠኛነትህ ብትረጋ ይሻልሀል ። ወይስ ሙያህን ልትቀይር አሰበህል? ግን አዝናለሁ» አለኝ ።

«ምን የሚያሳዝንህ ነገር ተናገርኩ?»
«ተጠራጠርከኝ.....ግን አንተ ምን ታደርግ? ዕድላችን ነው..»

«መጠራጠሬ አይደለም ። ለማወቅ ፈልጌ ነው ። እውነቴን ነው የምልህ እኛ ጋዜጠኞች ጥያቄ በመጠየቅ ነው አንድ ነገር ለማወቅ የምንችለው ። እና ደግሞ ካሁኑ ሙያዬን መቀየር አል ፈልግም ። ማይክሮፎን ላይ ነው የምሞተው ። ጋዜጠኛ ሲያረጅ ባይሆን ዲፕሎማት ይሆናል እንጂ ሰላይ አይሆንም» ስለው—

«ለምን?» ብሎ ጠየቀኝ ።
«ዲፕሎማት ከሆን ምንም ባይሠራ እንኳን በብርጭቆ እያያዙ እያሳፍርም ፣ ያሳምረዋል ። ለምን ቢራ አልጋብዝህም?» አልኩት ።

«ሌላ ጊዜ ። አሁን የምጠብቀው ሰው አለኝ ። ምን አስቸኮ ለህ? አብረን የምናከብራቸው ብዙ ድሎች ይጠብቁናል» ብሎኝ ሔደ ። ቢራ ፍለጋ ሔድኩ።የሚጠብቀው ፊያሜታ ጊላይን ይሆን? እያልኩ አስብ ነበር ።

«ሚስተር ቲቪ!»
መጽሐፊ ዳንኤል ነበር።ባንኮኒውን ተደግፎ ቢራ ይጠጣል።
«ታዲያስ ሚስተር ኢኮኖሚ!» አልኩት ።

ነጭ የበጋ ልብስ ፣ እንደ በረዶ የነጣ ስስ ሸሚዝ ፣ ከሰማያዊ ክራቫት ጋር ለብሶ ሽክ ብሎአል ። የተቀባው የወንድ ሽቶ ከሩቅ ይጣራል ።

«ውሽንብር ፣ ውሽንብር ነግሿል!»
«ምን ሆንክ!» አልኩት ።

«ተቀብሎ የሚያስተናግደን የለ ፥ መኝታ አልተያዘልን ። ቢራ በነጻ መስሎኝ ነበር ። እንዲህ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ከአሥመራ እግሬን አላነሳም ነበር» አለ ።

«ስለመኝታ ምን ችግር አለ? ጉርጉሱም ላይ ሺ ድንኳኖች ተተክለው ፥ የእንግዳ ያለህ ይላሉ...»

«ማ እኔ! አሸዋ ላይ ድንኳን ውስጥ ላድር?»

አዎ ፥ መጽሐፈ አሸዋ ላይ መተኛት ቀርቶ በእግሩ መሬት ለመርገጥም ይጠየፋል ።

«ስትዞር ማደር ነዋ ። ምጽዋ የሰዓት ገደብ የለም ። እዚህ የሚነጋው ሲመሽ ነው ።»

«የት ይኬዳል? ሴቶቹ ጠፍተዋል» አለ...

«ልክ ነህ ። የኤርትራ ቆንጆዎች ወደ ጅዳ ፥ አቡ ዳቢ ኮብል ለዋል ። ገንታቸው እዚያ ሆኖ የለም እንዴ? » አልኩት ።

«ነፍሳቸው ትኮነን ! » ብሎ ቀለደና ፥ ሥራው እንዴት ነው? አለኝ ።

«እንደ ውሻ መርዋ ፥ የውሻ ሕይወት ነው ። ቤተክርስቲያን እንደ ገባች ውሻ መዋከብ» አልኩትና ግማሽ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ቢራ ጨልጦ ቸስ እያደረገኝ ሲወርድ በእርካታ ከተነፈስኩ በኋላ ፥ «በኢኮኖሚስ ግንባር?» ብዬ ጠየኩት ።

ሳይናገር መሳቅ ይወዳል ። ዞር ብሎ ትከሻው ላይ የሚስቃት ልዩ ሳቅ አለችው ። ዛሬ እንደአጋጣሚ ንጭንጭ አላለም ። መነጫነጭ ሲጀምር እንደ አውሬ ሰው ይሸሻል ። ሰው እያነጋገርም ። ብቻውን ይሔዳል ። ብቻውን ይበላል በሽታው ሲነሳ ። ዶክተር ዮሐንስ ቤት ባንድ ጣራ ሥር ከእሱ ጋር የምንኖር ሰዎች ለማምንት የማናየው ጊዜ አለ ። ስናጣው አክስቱ ጋ ሔዶ ይሆናል እያልን እንቀልድበታለን ። የሚሔድባቸውን ሴቶች አክስቶቼ ናቸው ይላቸዋል ። እና ብዙ አክስቶች አሉት ።

«የደም ብዛቴ ተነስቶብኛል» አለ ።

«ሆድህስ ተሻለው?»

«እናንተ ጋዜጠኞች በሰው እንደቀለዳችሁ ነው የምትኖሩት» አለኝ ።

«እናንተ ኢኮኖሚስቶችስ?» አልኩት ።

«እኛ ቀልድ አናውቅም ። ዓለምን ለመለወጥ የሚሠሩ [illegible] ። እነማን ናቸው ዓለምን የለወጧት — ታው [illegible]

[illegible] ዓለምን ይለውጣሉ» አለ ።

«እና አንተ እዚህ ከመጣህ ምን ለውጥ አስገኘህ!» አልኩት።

«ዶፖዎቹን ሞልቻለሁ ። የኮንስትራክሽኑ ሥራ ተያይዟል ። በቅርቡ አገልግሎት መስጠት የሚጀምሩ ክሊኒኮችና ሆስፒታሎች ይገኛሉ ። ስንዴና ሸቀጣ ሸቀጦች እንደ ልብ ናቸው ። የጭነት መኪናዎች ሞልተዋል ። ምን ትፈልጋለህ ሁሉም ነገር በሽ በሽ ሆኗል» አለ በምጸታዊ አነጋገር ።

«ዕድሜ ላንተ» አልኩት ።
«ወድጄን መሰለህ!»
«እህሳ!»

«ኧረ ይህ አይቻልም የሚል ቋንቋ የለም ። ይቻላል ማለት ብቻ ነው ፣ ማንኛውም አይቻልም ፣ አያዋጣም የሚል ቃል የአድኃሪዎች ቋንቋ እንዲሆን አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች አሉ ። ግን ኢኮኖሚያችን እየደማ ነው» አለ ።

«መድማቱን እንዲያቆም ምን ማድረግ አሰብን ትላለህ!»
«ዲፕሎማሲ ወዳጄ ። ይህ ዓለም በስጠኝና ልስጥህ ፍልስፍና ነው የሚገዛው ። እና ኢንቬስትመንት ። ሥራ መፍጠር ። ሠርቶ በሠላም የመኖር ዕድል ከተፈጠረ ወንበዴዎች ዘላለማቸውን እየቀመሉ በረሀ ለመኖር የሚመርጡ ይመስልሀል? ወንበዴዎች ምን እያሉ መዝፈን እንደጀመሩ ሰምተሀል!» አለ ።

«ምን!»
«አታ እምላኸ አታ ፈጣሪ
ወዲ ሠብዶ አብ በረኻ ይበሊ
ካብ ዓይንናስ ዓይነጁ እንዶ ይፈሪ» እያሉ መዝፈን ጀምረዋል አሉ ። «ግራር ጥላ ሥር ቁጭ ብለው ቅማል ከሰውነታቸው

ላይ መልቀምን የሚመርጡ አይምሰልህ ። እያንዳንዷን ቅማል ቅጭ አድርገው በነደሉ ቁጥር በልባቸው አገሬ ማሪኝ ሳይሉ አይቀሩም» አለር [illegible]

---

[illegible]

ማሲ ፍጻሜ ቅጥያ ነው [illegible]

[illegible] ብዬው ሌላ ቢራ ካዘዝኩ በኋላ ፣ «የተቀሩት አምስት ረጅም ሰዎች የት ሔዱ?» አልኩት ።

ዶክቶር ዮሐንስ ቤት አንድ ላይ የምንኖረው ሰባት ሰዎች ፣ «ሰባት ረጅም ሰዎች» የሚል ቅጽል ስም ወጥቶልናል ። አልቤርጎ ቻዎ የሚኖሩት የቀይ ኮከብ ዘማቾች መቸም ለሰው የማያወጡት ስምና የማይፈጥሩት ቀልድ የለም ። እንደ እውነቱ ከሆነ ረጅም የምንባል ሰዎች አይደለንም ። ምናልባት ጥላዎቻችንን አይተው ይሆናል ። መጽሐፈ መልስ ይሰጠኛል ብዬ አልነበረም የጠየቅሁት ። የት ፣ የት እንደሚገኙ ጥሩ ግምት ነበረኝ ። ሱስሎቭ ይኸኔ ተኝቶ አብድ የሚያክል የቲዎሪ መጽሐፍ ያገላብጣል ። ሌላውም እንደ ልማዱ በጊዜ ሔዶ ተኝቶ ይሆናል ። በጊዜ እንደ ዶሮ መስፈር ይወዳል ። ሦስተኛው ከአዲስ አበባ ጋር ስልክ ይዞ ይሆናል ። ሲጃራ አከታትሎ እያቀጣጠለ ከባለቤቱ ጋር በስልክ አንድ ሰዓት ሳያወራ አይተኛም ። ሲጃራ ለመተው በየቀኑ ይጥራል ። ሲጃራ የሚያስጥል ነገር ይፈልጋል ። ብልሐቱን ይጠይቃል ። በቀን ሁለት ፓኮ ኢያላ ያጤሳል ። ጢሱን አይውጥም ። ላፍ ፣ ላፍ ፣ ቡን ፣ ቡን ያደርጋዋል ። ሐቀኛና ቁም ነገረኛ በለሆነ እናከብረዋለን ። አጉል ቀልድ አይወድም ። አራተኛው «አጅሬ ያራዳ ልጅ» ይኸኔ ተኳኩሉ ወጥቶ ቆንጆ ልጅ ፍለጋ ቡተማውን በማሰስ ላይ ይገኛል ። በእጭ ተጥዶ የሚያድር ይመስላል — ሲያዩት ። አምስተኛው ከቢራ ሌላ ፍላጐት የለውም ። ይኸኔ «ቢራን የፈጠረ አምላክ» እያለ ቢራ ፣ ቢራ ይላል ።

«ሁሉም እንደ ጠባያቸው በተግባር ተሰማርተው ይሆናል» የማለት መጽሐፈ ያልጠበኩትን መልስ ሰጠኝ ።

«ምን ለማለት ፈልገህ ነው?» አልኩት ።
«የተፈጥሮ ግዴታ...»

«አክሰቶች! ለመሆኑ ስንት አክሰቶች አሉህ?» ሳቀና ፣ «ምን እንደተባልን ሰምተሀል?» አለኝ ።

«ምን ተባልን?»
«ቀይ ኮከቦች በናቅፋና ባሥመራ ሴቶች ላይ ነው ለመዝመት የመጡት እንባላለን.....»

፯

ነገሩ አሳቀኝና ፣ «ታዲያ ምናለበት ። ጦርነትና ፍቅር አይለያዩም ። መጣንላቸው እንጂ አልመጣንባቸውም ። ይግረምሀና ብዙዎቹ ያሥመራ ሴትላጤዎች ከትግሬ ወንድ ይልቅ ከመሐል አገር የመጣውን ይመርጣሉ ይባላል ። የመሐል አገር ሰው እንደ ጣሊያን ሴት አክባሪ ነው የሚሉት ፈሊጥ አላቸው ። ባንጻሩ ፣ የትግሬ ወንድ እንኳን የሚያውቃትን ቀርቶ የማያውቃትንም 'የኔ ነች ፣ ነበረች' እያለ ማውራት ይወዳል እያሉ ይፈራሉ» ብዬው የጀመርኩትን አሳብ ጨርሼ ሳልነግረው ፣ ሥዩም ሡረቀ ብርሀንና አሸብር እየተጣደፉ ወደ ባንኮኒው ሲመጡ አየኋቸውና ሠላምታ ሰጠኋቸው ።

«ቢራ ልጋብዝህ?» አለኝ ሥዩም ።
«ኩባንያህ ማትረፍ ጀምሮአል መሰለኝ?» አልኩት ።

«አሳምሮ ። ያዲሳባ ሴቶች ለጌጥ ሚች እስከሆኑ ድረስ ምን ችግር ይኖራል?» አለና ቢራውን ባንድ ትንፋሽ ጨለጠው ።

«የቸኮላችሁ ትመስላላችሁ.....»
«ሁለት ሬሣዎች በእጃችን ላይ ይገኛሉ.....»
«የምን ሬሣዎች ?»
«ኋላ እነግርሃለሁ» ብሎኝ ሊሔድ ሲል ያዝኩት ። ሰው ወሬ ጀምሮልኝ ሲያቋርጥብኝ አልወድም ። ሆዴን ያመኛል ።

«የመሐል አገር ሰዎች ናቸው ይሆን?»

«አይደሉም ሁለቱም የእዚህ አገር ሰዎች ናቸው ።አንድ ሴት ፣ አንድ ወንድ ። ሴትዮዋ በአሥመራ እኔ ነኝ ያለች ያናጠጠች ሐብታም የታወቀ ሴክሬቶ ባለቤት ነበረች ። ሰውዬው እሁን በቅርቡ ያንድ ቀበሌ ሊቀ መንበር ሆኖ የተመረጠ ነበር ። ሁለቱም ያሥመራ ኗሪዎች ነበሩ» አለኝ ።

«ምን ሆነው ሞቱ?»

«ባሕር ላይ ተንሳፈው ነው የተገኙት.....»

«ምክንያቱ ምን ይሆን?»

«ተገድለው ባሕር ውስጥ የተጣሉ ይመስላል።አሁን ልሒድ?» አለኝ ።

«ፖለቲካዊ ግድያ ይሆን?»

«መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው የምንቸኩለው» አለ ኝና ሔደ ። ተያይዘው ሮጡ — ሥዩምና አሸብር ።

«ምን ነበር የሚሉህ እነዚህ የሕዝብ ደኅንነት ልጆች?» አለኝ መጽሐፌ ።

«ሁለት ሬሣዎች ባሕር ላይ በመንሳፈፍ ላይ ይገኛሉ ነው የሚሉት ። ጥሩ ዜና ይወጣዋል ። ሁኔታውን መከታተል አለብኝ» አልኩት ።

«እናንተ ጋዜጠኞች ትገርሙኛላችሁ» አለኝ ።

«ምነው?»

«ጥሩ ዜና ይሆናል ብሎ ነገር! ሰው ሲያጣጥር ብትደርሱ ፣ ምን ይሰማዎታል? ነገሩን እንዴት ያዩታል?» ብላችሁ ሳትጠይ ቁት አትቀሩም ። በል ወንድሜ ፣ እኔ በጊዜ ማደሪያዬን ልፈልግ» አለኝ ።

«ምነው ፈራህ?»

«በዚህ ግርግርና ውዥንብር ውስጥ ምን የማይሆን ነገር አለ ብለህ ነው? ጧት ባሕር ላይ ተንሳፍፌ መገኘት አልፈልግም ።» እንደ መጽሐፌ ለሕይወቱ የሚጨነቅና የሚሰጋ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም ። የጠጣሁት ሁለት ቢራ ሥራውን ሠራ መሰለኝ ፣ እድሮብኝ የነበረው ድካም ለቀቀኝ ። ምሽቱም ገና ለጋ ነበር ። ምጽዋ ላይ ሲመሽ ነውና የሚነጋው በጊዜ ሔዶ መተኛት ኃጢ አት መሰሎ ስለታየኝ መጽሐፌ ዳንኤልን ትቼ ጋዜጠኞቹን ፍለጋ ወጣሁ ። እየዞርኩ በየቡና ቤቱ ፈለኳቸው ። ይኸ ከመሐል አገር የመጣው ሰው የፈረደበትን ቀዝቃዛ ቢራ ከነአረፋው እያነሳ ዝም ብሎ ይጋታል ። ጋዜጠኞቹ የትም አልነበሩም ። እነዚህ ጨሉፈ ዎች ወደ ጉርጉሱም ሔደው ይሆናል በማለት ወደዚያ በረርኩ። በሙቶ የሚቆጠሩ መኪናዎች ወደ ጉርጉሱም ባሕር ዳርቻ ሲሔ

ዱም ከዚያ ሲመለሱም መንገዱ ላይ ይታዩ ነበር። የድንኳን ከተማው ሺ ደመራ ተደምሮ የተቀጣጠለበት መስሏል ። ጭፈራውና ዘፈኑ ይቀልጣል — እዚህ የትግሬ — እዚያ ያማራ — ወዲህ የኦሮሞ ወዲያ የጉራጌ ። ቀዝቀዝ ያለው አየር ከጭፈራውና ከዘፈኑ ጋር ተዳምሮ መንፈስ ያድሳል ። ቅርብ መስሎ ከሚታየው ጥቁር ሰማይ ላይ የፈሰሱት ከዋክብት በደስታ የሚደንሱ ይመስላሉ ። እና የቀይ ባሕር ማዕበሎችም ያረግዱ ነበር ። አንዳንዴ ማዕበሎቹ ላንዳፍታ ጸጥ ሲሉ በየቦታው የሚነደው እሳት ነጸብራቅ ፥ ዘመናዊ ሰዓሊ የሳለው የሕይወት ጥላ የሚመስሉ ዝብርቅርቅ ጥላዎች ባሕሩ ወለል ላይ ይፈጥራል ። አሁን እንዲያው ከተፈጥሮ የበለጠ ስዕል የት ይኖራል? እያልኩ የባሕሩን ጠርዝ ይዤ እየተከዝኩ ሳዘግም ፥ አንዲት ልጅ ብቻዋን ፥ ካንድ ጠርብ ድንጋይ ላይ ቆማ ማዶ — ሰማዩና ባሕሩ የሚሳሳሙበትን አድማስ ስትመለከት አዩሁ ። ባሕሩ የቆመችበትን ድንጋይ እያጠበ ይመለሳል ። ከባሕር የሚመጣው ቀዝቃዛ አየር ጠጉሯን እያነሳ አየር ላይ ይነሰን ሰው ነበር ። በቀጭን መያዣ ከብ ትከሻዋ ላይ ተንጠልጥሎ ጀርባዋን ገልጦ የሚያሳይ ነጭ ፥ አጠር ያለ የበጋ ቀሚስ ለብሳለች ። የባሕርን አምላክ የምታመልክ ነጭ ርግብ መስላ ታየችኝ ። ፎቶግራፍ ማንሻ ምነው በያዝኩ ኖሮ አልኩ ። ከድንኳኖች መንደር የተተኮሰው ርችት ጥቁሩ ሰማይ ላይ ድንገት ሲፈነዳ በሺ የሚቆጠሩ ልዩ ልዩ አበባዎች ዉለማው ላይ ረገፉ ። ደንግጣ ዞር ስትል መልኳ ታየኝ ። ከሩቅ ተወርውሮ የሚመጣው የኤሌክትሪክ ብርሀን ትንሽ ፥ ትንሽ ያሳያል ። እሷ ትሆን? ወይስ አይደለችም? እያልኩ ተጠጋኋት ። እሷ ነበረች ።

«ፊያሜታ!»

በመጀመሪያ ማን እንደሆንኩ አላወቀችኝም ። በጣም ተጠጋኋትና ፥ «ጸጋዬ እባላለሁ ። ታስታውሺኛለሽ?» አልኳት ።

«ዋኦ! እሂዶአ?»
«ብቻሽን እዚህ ምን ታ'ረጊያለሽ?»
«ብቻዬን አይደለሁም ።»
ዞር ፥ ዞር አልኩ ሰው ፍለጋ ። ማንም አልነበረም ።
«ማን አለ?» አልኳት ።

«ባሕሩ ። ከባሕር ጋር ሆኖ ማንም ሰው ብቻዩን ነኝ ለማለት የሚችል አይመስለኝም ። ባሕር ላይ እንጂ ደስ ይለኛል ፣ ደግሞም አዝናለሁኝ ። የባሕር ስፋትና ጥልቀት ያሟሙተኛል ። ሌላ ጓደኛ ምን ያስፈልጋል? — አባቴ ይሙት» አለች ።

በረዶ መሳይ ጥርሶቿ የልብ ቅርጽ ካላቸው ከንፈሮቿ መካከል ተፈልቅቀው ወጥተው ብቅ አሉ ።

«ምናልባት ልክ ነሽ ። ባሕር ሕይወት ነው» ካልኳት በኋላ ፣ «ብዙ ጊዜ እዚህ ትመጫያለሽ?» ብዬ ጠየኳት ።

ነፋስ አየር ላይ የሚነሰንሰውን ጠጉሯን ከፊቷ ላይ ወደኋላ እያደረገችና ፣ «አው ። በፊት ብዙ ጊዜ እመጣ ነበር ። ለመጨረሻ ጊዜ የመጣሁት ከስምንት ዓመት በላይ ይሆናል» አለች ።

«በስልክ ምጽዋ እንገናኝ ስትይኝ ቀልድሽን መሰሎኝ ነበር። እንዲጋጣሚ ሆኖ ተገናኘን» አልኩ ፣ የባሕሩን ስፋት በዓይኔ እየተከተልኩ ።

«ለምን ቀልዴን መሰለህ?»
«እንጃ ። ምናልባት ካነጋገርሽ ይሆናል ።»
«ኖኖ ። ቀልዴን አልነበረም ። ቀይ ባሕርን ማየት ናፍቆኝ ነበር ። ፌስቲቫሉ ጥሩ አጋጣሚ ሆነልኝ...»
«ብቻሽን ነው የመጣሺው?»
«ኖኖ ። ከሰዎች ጋር ነው ።»
«ከሥዕሏይ ጋር?»
«አውን» አለችና ሳቀች ።
«ታዲያ እንዳንቺ ያለች ቆንጆ ልጅ በዚህ ጨለማ ብቻዋን ለመልቀቅ ሆዱ እንዴት ቻለው» አልኳት ።

ጠጉሯን እየነሰነሰች ፣ «ውሸቱን ነው አባቴ ይሙት ። ቀጥታ መልስ መስጠት አይሆንልኝም ። ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ?» አለች ።

«ጣፋጭ ቀሾ...»

«አንቴ ደግሞ ጣፋጭ ደደብ» አለችኝ ።
ሳቅሁኝ ። ሳቀች ። ተሳሳቅን ።
«ታዲያስ የባሕር አማልክት?» አልኳት ።

«አማልክት ካልከኝ ፣ እስኪ ስገድልኝ» አለችኝ ። ጸሎት እንደሚያደርስ ሰው እጆቼን አንድ ላይ አጣምሬ ፀንድ ጉልበቷ ፊቷ ተንበረከኩ ።

ሳቀችና ፣ «አባቴ ይሙት ያበደ ደደብ ነህ ። በሥነ ሥርዓት» አለችኝ ።
«አው ። በሥነ ሥርዓት» አልኩ የእሷን አነጋገር አስመስዬ።
«እኔ እንደሱ ነው የምለው አንቴ? አባቴ ይሙት ፣ በሥነ ሥርዓት ደደብ ነህ.....»
«የትኛው ሆቴል ነው ያረፍሺው?»

ዝም ብላ ቀረች ። ድንገተኛ የሆነ የስሜት ለውጥ እንዳደረ ባት ተሰማኝ ።
«ምነው የማይሆን ጥያቄ ጠየኩ?» አልኳት ፣ ይህች ልጅ ቤት ነብር ሳትሆን አትቀርም እያልኩ በልቤ ።

«ኖ ኖ!»
«እህሳ?»
«መኝታ አልያዝኩም.....»
«አዬ አንቺ ጣፋጭ ዋሾ! አሁንስ አልታለልልሽም.....»
«አባቴ ይሙት — እውነቴን ነው ። አንቴ ፣ ኋላ እውነትም ብናገርህ ላታምነኝ ነው'ኮ?»

አመንኳት ።

«እስካሁን ምን አቆየሽ? ወይስ እዚሁ ከባሕር ዳርቻ ከናፈ ቅሺው ባሕር አጠገብ ለማደር ፈልገሽ ይሆን?»

«ክፍል ተይዞልኝ ነበር.....»
«ታዲያስ?»
«እዚያ ለማደር አልፈለኩም ።»
«ምነው ጥሩ ክፍል አይደለም?»

«ኖ ኖ — ስለክፍሉ አይደለም.....»
«ታዲያ ምንድነው?»

ምክንያቱን ልትነግረኝ አልፈለገችም ። ምክንያቱን ሳትነግረኝ በመቅረቷ ሆዴን ይበላኝ ጀመር ። ቅርታዬ ስለተሰማት ነው መሰለኝ ቆይታ ምክንያቱን አጫወተችኝ ።

ወደ ምጽዋ የመጣችው ፍቅረኞች የሆኑ አንድ ወንድና ሴት ባደረጉላት ግብዣ መሠረት ነበር ። ሴትዬዋ በጣም የልብ ጓደኛዋ ናት ። ምጽዋ እንደደረሱ ፍቅረኞቹ አንድ ክፍል ብቻ ይይዛሉ ። እሷም ምናልባት ክፍሉ ውስጥ ሁለት አልጋዎች ይኖራሉ ብላ በማሰብ ዝም ትላለች ። ክፍሉን ከፍተው ሲገቡ አንድ ትንሽ አልጋ ብቻ ነበረች ። ጓደኛዋ ፥ ለእሷ ቀደም ብሉ ክፍል ተይዞላት እንደቆየ ትነግራትና ወስዳ ክፍሉን ታሳያታለች ። በሩ ክፍት ነበር ። የወንድ ልብሶች ወንበር ላይ ተጥለው ይታያሉ ። ፈያሜታ ትገረማለች ። ቀጥላ ፥ የጓደኛዋን ዓላማ በመረዳቷ ትናደዳለች ። ከንዴትም አልፋ እንባዋ ይመጣል ። ክፍሉን የያዘው ሰው ፥ ከመሐል አገር የመጣ ፥ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚገኝ ፥ የጓደኛዋ ቅርብ ዘመድ ነበር ። ፈያሜታ በንዴት በርራ ወደ ጉርጉሱም ትመጣለች ። እና የት እንደምታድር አታውቅም ነበር ። አላሰበችበትም ። አልተጨነቀችበትም ። ደንታ አልነበራትም ። ያገኘኋት ባሕር ዳር ቆማ ከባሕሩ ጋር እየተወያየች ። ጓደኛዋን ስትታዘብና ንዴቷን ስታስታምም ነበር ። በመጨረሻ ፥ «ዋእ እኔ! ምን መሰልኳት እባክህ? ለሺያጭ የሚቀርብ ከብት? አንዳንድ ሴቶች ያስገርሙኛል — አባቴ ይሙት ። የሰው ልክ አያውቁም ። ከፈለኩ እኔ ወንድ አጣሁ? የምን ማቃጠር ነው እሱ? እኔ ከማልፈልገው ሰው ጋር አልሔድም ። ሰውነቴን አልሸጣትም ። እኔ ሸርሙጣ አይደለሁም» በማለት ጠጉሯን እየነሰነሰች ንዴቷን ተነፈሰችልኝ ።

«ምንም አይደለም ። እንዲህ ያለው ነገር አንዳንዴ በጓደኞች መካከል ሊደርስ ይችላል ። በጣም በቅርብ ስለምናውቃቸው ጓደኞቻችን አንዳንዴ እንሳሳታለን» ብዬ ላጽናናት ሞከርኩ ።

ዘፈኑና ጭፈራው አሁንም እንደቀጠለ ነበር ። እንዲያያውም ከበፊቱ በጣም ደርቷል ። በየቦታው እሳት ይንቦገቦጋል ። እየዞርን

ዘፈን ስንሰማና ጭፈራ ስንመለከት ቆየን ። በየቦታው የነበረው የመፈቃቀርና የመተሳሰብ ስሜት ደስ ያሰኝ ነበር ። ሳይታወቀን እኔና ፊያሜታ እጅ ለእጅ ተያይዘን ነበር የምንዞረው — ለተመለከተን ሰው ዛሬ ገና የተገናኘን ሳይሆን ለብዙ ጊዜ የምንተዋወቅ ፍቅረኞች ሳንመስለው አንቀርም ። ጊዜው በጣም መሽቶ ነበር ። ወደከተማ ተመለስን ። ርእሰ ምድሪ ንቅታለች ። ሌና ሬስቶራንት ራት ጋበዝኳት ። ለራት ያዘዝነው ምግብ ኮንሱሚ ዲ ብሮዶ ፣ ቲቪ ኢንባያንኮ ቦሊቶ ኮንማይኒዚ ፣ ሳላታ ቪርዲና ፖጌዲ ስፖኛ ከቀዝቃዛ ቪኖ ቢያንኮ ቤርቶሊ ጋር ነበር ። ቀለል ያለ በጣም ገሩም ምግብ ነበር ። የፊያሜታ ምርጫ ነበር ። ሲርበኝ ከመብላት በቀር ስለምግብ ዓይነት እምብዛም የማውቀው ነገር የለኝም ። የወጥ ቤት ኪነትና የሆድ ሳይንስ መስኬ አይደለም ። ሙዚቃውም የእሷ ምርጫ ነበር ። «ኪ ሲራ ሲራ» የሚባለው በሙዚቃ መግሪያዎች ብቻ የተቀነባበረ የድር ዘፈን ነበር ። ብዙ ጊዜ የሰማሁት ዘፈን ቢሆንም ዛሬ ወደድኩት ። የወደፊቱን ማን ያውቃል? ይሆን ይሆናል ። የማይሆን ደግሞ አይሆንም.....

የሌና ሆቴል ባለቤቶች እየመጡ «ማንጂ ማንጂ» ይሉናል ። አንደኛው እንካሳ ነው ። ሁለተኛው ጀር ደገፍ የያዘው ይመስላል ። ፓፓያ የሚያክል እብጠት ጀር ግንዱ ላይ አለ ። «ብሉ» ከማለት ሌላ ቋንቋ የሚያውቁ አይመስሉም ። ለእነሱ ምግብ ሁሉም ነገር ነው ። ከራት በኋላ «ወደ ርእሰ ምድሪ እንሂድ» አለችኝ ።

«ለምን?» አልኳት ።

«ከመተኛቴ በፊት ባሕሩን እንደገና ማየት አለብኝ ። የባሕር ሙዚቃ መስማት ደስ ይለኛል» አለች ።

ወደ ርእሰ ምድሪ ተያይዘን ሔድን ። ለመርከቦች ምልክት የሚሰጠው ሰንትት አሌፎ ጥቁሩ ባሕር ላይ ብርሆን ይፈነጥቃል ። ዐረፋ የሚመስሉ ማዕበሎች በጨለማ ውስጥ ከሩቅ እየተንከባለሉ መጥተው ጠረፉን በመሳም ተመልሰው ወደ ባሕሩ ይወድቃሉ ። ውብ የሆነ የተፈጥሮ ሙዚቃ ይሰማል — የባሕር ሙዚቃ።

አብ ከተማ ምጽዋዕ ጥቓ ደንደስ· ባሕሪ
ትገዝ ኢሉ ተዘኪሩኒ ዘሕለፍኩዎ ፍቕሪ
ጸሐይ ዕራርቦ እዋን ምስይ ምስበለ
እቲ ሙቕት ጠፊኡ ምድሪ ‘ውን ዘሐለ
ይሕሰብ ነበርኩ ከደናፈቕ ጀሚረ
መሪር ሐዘን ኮነኒ ድሮ ‘ኳ እኔኹ ንብዓተይ ዓቒረ
አብ ከተማ ምጽዋዕ ጥቓ ደንደስ ባሕሪ
ትዝ ኢሉ ተዘኪሩኒ ዘሕለፍኩዎ ጻዕሪ
ጥቓ ደንደስ ባሕሪን በይነይ ኮፍ ኢለ
ሰፍርኡ ድምዋ ‘ዩ ርእሲ ምድሪ ዝተባህለ
አርኪቡኒ ፍቕሪ እኔኹ አስጊለ
ሐሳበይ ተበቲኑ አእምሮይ ሰለለ
እዚ ኪብል ከለኹ አዋልድ ሀገረይ
አፍቂርከን አይትጥለማ ተቓበላ ምኽረይ
ሐደራ ከይርከብ ከም'ዚ ሐዘን ናተይ
ከይተበሳጭውኦም መታን ንመንእሰያት አሕዋተይ
ንኹላቶም አሕወተይ

«ውብ አይደለም?» አለች ።
«ውብ ነው.....»
«ልቤ አብሮአት ይዘፍናል ። ባሕር የፍቅር ሙዚቃ ነው የሚዘፍነው ።
«አይመስልህም? »
«አዎን ፣ »
«ባሕር ጨው ነው ። የሰው ስሜትም ካ ጨው ፣ ጨው ነው የሚለው...»
«ቀምሰሽዋል?»
«ለምን አትስመኝም?»

«ሳምኳት ። የባሕሩን ሙዚቃ ስናዳምጥ ቆየን ። ወደ ሆቴል እንሂድ ብዬ አልጠየኳትም ። ዝም ብዬ ወሰድኳት ። ተኛን ።

ለፍቅሯ ተርቤ ነበር ። እሷም ስሜቷን አልቆጠበችብኝም ። የስሜቴን አጸፋ በስሜት ትመልስልኝ ነበር ። ውብ ነበረች ። ቆይታ ቆይታ ኋላ ነበር ፣ «አንቴ አባቴ ይሙት ፣ ምን ዓይነት ሌባ ነህ!» አለችኝ ።

«እንዴት?»

«ዝም ብለህ ታመጣኛለህ?»

«ብጠይቅሽ ይሻል ነበር አል?»

«አባቴ ይሙት ፣ ብትጠይቀኝ እሺ ብዬ አልመጣልህም ነበር። ሂድ! አባቴ ይሙት፣ሌባ ነህ፣ በምን ሥርዓት» አለችኝ ።

«ነገርሽ ሁሉ ጣፋጭ ነው__»

«ደደብ ፣ ጣፋጭ ደደብ ።»

«ለብዙ ጊዜ እንደማውቅሽ ያህል ሆኖ ነው የሚሰማኝ»

«እኔም ። አባቴ ይሙት ። ለምንድነው ግን ?»

«ሞትና ፍቅር አንድ ቀን ነው ይባላል ። ወይስ ለይደለም?»

«ወይም» አለች ።

«ወይም ምን?»

«መዋደድ እንደ ቁማር ነው ። ይገኛል ወይም አይገኝም ። ሙሽ?»

እንደገና አቀፍኳት ። የፍቅር አምላክ እንደገና ለመመለክ ፈልጎ ነበር ። እና ቁጣውን ለማብረድ እንደገና መመለክ ነበረበት ። እንደገና ያቀረብነውን የፍቅር መስዋዕት የፍቅር አምላክ በደስታ ተቀብሎ እንደገና ባረከልን — ኃያሉ የፍቅር አምላክ!

«እውይ ፣ እዚህ ቤት የሚጠጣ ነገር የለም ወይ? ተቃጠልኩ» አለች ።

«እኔም ቀዝቃዛ ነገር አስፈልጎኛል ፣ አልኳትና የሆነ ልብስ እንስቼ እንደነገሩ ከለበስኩ በኋላ ፣ ታች ቡና ቤት ወርጄ ሁለት ቢራና አንድ ስፕራይት ይዤ ስመለስ ኩሉኔል በትሩ ሊፍቱ አጠገብ ያዘኝ ።

«አሀስ አጅሬ!? አለኝ የያዝኳቸውን መጠጦች እየተመለከተ ።

«እስካሁን አልተኛህም እንዴ?» አልኩት እንደማፈር ብዬ ። ከማን ጋር እንደሆንኩ የሚያውቅ መሆኑን የሆነ ነገር ነገረኝ ።

«አንቅልፍ የማይዞርበት ሌት ነው ። እናንተን ከመጠበቅ ፍየል ማገድ ይሻላል ።»

«ምን አጠፋን?» አልኩት ትቼው ቶሎ ለመሔድ እየፈለኩ ።

«ሁለት ቢራና ስፕራይት ምን ያ'ረግልሀል?» አለኝ በጥርሱ ሳይሆን በዓይኖቹ እየሳቀብኝ ።

«ጠምቶኛል ። እንደ አሚና ስለፈልፍ አይደለም የምው ለው? ቢራ ከስፕራይት ጋር እወዳለሁ...»

«ፈያሜታ እንዴት ናት?»

«እንደ እግዜር የማታየው ነገር ከጸሐይ በታች የለም ማለት ነው!»

«ደህና ናት» ብዬው ሌሔድ ስል ፥ «ገንዘብ ትፈልጋለህ?» ብሎ ጠየቀኝ ።

«ሲያስፈልገኝ እነግርሀለሁ...»

«እንደ ፈያሜታ ያሉት ሴቶች ውዶች ናቸው...»

«ስማ ጓድ ኰሎኔል» አልኩ — «ከኔ የምትፈልገው ነገር ይገባኛል ። ጊዜ ስጠኝ ። ሥራዬን ሥሥራ እግረ መንገዴን አንዳንድ ፍንጭ ያገኘሁ ይመስለኛል ። በኔ ግምት የተሟላ ሥዕል ያገኘሁ ሲመስለኝ ወይም እርግጠኛ ነኝ የምልበት ነገር ሳገኝ አመጣለሁ ። የዘመቻው ዓላማ መሳካት የሁላችንም ኃላፊነት ነው ። ግን አንዳንድ ፍንጭ አገኘሁ ብዬ የምሮጥ ሰው ዓይነት አይደለሁም ። የሰው ነገር ይጨንቀኛል ። በዚያ ላይ ተሳስቼ ላሳስትህ አልፈልግም ። በእውነት የምደብቅህ ነገር አይኖረኝም ። ዓላማችን አንድ ነው ። አንድ ላይ ነን ። ጊዜ ስጠኝ። ዘመቻውን ከጠላት መጠበቅ ግዴታዬ ነው ፥ ሥራዬም ነው» ስለው ፤

ፈገግ ብሎ «እናንተ ጋዜጠኞች የማትደርሱበት ቦታ የለም ። ለዚህ ብዬ ነው ። እኔም እንዳንተ አልቸኰልም ። የቸኰለ ቀንድ ይነከሳል እንዲሉ ። እርግጥ አንተ ፍንጭ ነው የምትለው ነገር ለኛ የተሟላ ሥዕል ሆኖ ሊገኝ ይችላል ። ግን ፍንጮቹ ምን እንደሆኑ አሁን እንድትነግረኝ አላስቸግርህም ። የፈለከውን ያህል ጊዜ ልትቆይ ትችላለህ ። ይቅናህ» ብሎኝ ሔደ ።

ነገሩ ውስጥ ውስጡን እየከነከነኝ ወደ ክፍሌ ተመለስኩ ። ስለነገሩ የተሟላ ሥዕል እስካሁን ባለማግኘቴ ነደደኝ ። ፈያሜታ ያደረብኝን ስሜት አላጤነችም ። ጥሟን አረካችና ፥ «አባቴ ይሙት ፥ ቢራ በስፕራይት እንደዚህ ጣፍጦኝ አያውቅም» ካለች በኋላ ፥ «አንቴ ፥ ቅደም እንደሔድክ ትንሽ ቆይቶ ሰው መጥቶ

ነበር ። አሊገባም ። እንጂ ፣ ቆሞ ሲያዳምጥ ቆይቶ ተመልሶ ሔደ»
አለች ።

«መኝታ ያጣ ሰው ይሆናል ። ታች ሰው እንደ ጉድ እየተተ
ራመሰ ነው» አልኳት ።

የጠረጴዛው ደብዛዛ መብራት ሙሉ የበጋ ጨረቃ ከሚመ
ስለው ሙሉ ገላጣ ደረቷ ላይ አርፎአል ። የተኮላ ብር የሚመስ
ሉት ዓይኖቿ ከጉድጓዶቻቸው ውስጥ ይገላበጣሉ ።

«ከሥዕላይ በራኺ ጋር የመጣሽ መሰሉኝ ነበር» አልኳት ።
«ለምን?»
«መጀመሪያ ያገኘሁሽ ከእሱ ጋር ሆነሽ ነበር ። እና እሱም
እዚህ ይገኛል.....»
«ይገርመኛል አባቴ ይሙት.....»
«ምኑ»

«ሰው ሁሉ ስለእሱ ለምን እንደሚጠይቀኝ አይገባኝም ።
«ምንሽ ነው ፣ የት ነው የምታውቂው? ምን ይልሻል?» ስለእሱ
በየጊዜው የሚቀርቡልኝ ጥያቄዎች አሰልችተውኛል ። እንዳ
ንድ ደፋሮች እንዲያውም ከዚህ አልፈው ፣ «ያን ምሽት የት
ወሰደሽ?አንድ ላይ አደራችሁ ወይ?»እያሉ ይጠይቁኛል.....»ስትል

«ለምሳሌ እንደ ተክላይ ዘድንግል ያሉት?» አልኳት ።
«በምን አወቅህ!?»
«እንዲሁ ። ምናልባትም እንውጣ ብሎ ሳይጠይቅሽ የቀረ
አይመስለኝም?»
«እኔ ፣ እሱ እንደ ካልሲ ከሚቀያይራቸው ቆንጆ ሴቶች
እንዷ መሆን አልፈልግም.....»

«አንቺ ቆንጆ ነሽ ያለሽ ማነው?»
«ራሴ ። አንተ ግናይ» ብላ ሳቀች ።
ፍልቅቅ ያሉት ወብ ጥርሶቿ ልቤን ፈለቀቁት ።

«ቆንጆ ነሽ..... በእውነት ። ለሚናዊት ጽብቅቲ ። የቀይ
ባሕር ርግብ» አልኳትና ቀጥዬ ፣ «እና እውነት ፣ ያን ምሽት
የት ሔዳችሁ?» ብዬ ጠየኳት

«ዋእ! ቤቴ ። የት እንሔዳለን እንበላ ሆቴል?!»

«እዚያ አደረ ማለት ነው?»

«አንተ ግናይ! ሴክሬቶ የማካሔድ መሰለህ? ከናት ፡ ካባቴ ጋር ነው የምኖረው…»

«ታዲያ የት አደረ?»

«እንጃ! ግን ለምን ትጠይቀኛለህ? ወይስ ላንተ በቀላሉ ስለመጣሁልህ ፡ ሌላ ጊዜም እንዲሁ ርካሽ ሴት ናት ብለህ ገምተኸኝ ነው!» አለች ፡ ንዴትና ጸጸት በተቀላቀለበት ድምጽ ።

«እውነት ፊያሜታ እመኚኝ ። እንዲህ ዓይነት ግምት ኖሮኝ አይደለም» አልኳትና ጉንጯን ሳምኳት ።

ገፈተረችኝና ፡ «ታዲያስ?!» አለችኝ ።

«ሥዕላይ እሷ ቤት ነው ያደርኩት ይላል ሲሉ ሰምቼ ነው…»

«ፍጹም ውሸት! እርግጥ መኪናውን ቤታችን ደጅ ጥሎ ሔዷል…»

«የት ሔደ?»

«እንጃ! በምን ዐውቃለሁ? ግን ሰው መጥቶ የጠየቀኝ እንደሆነ እዚ አለ ብለሽ ንገሪልኝ ብሎ ለምኖኝ ነበር ። ይህን ብቻ ነው የማውቀው ። ስለእሱ መጠየቅ ሰልችቶኛል!» አለች ።

«አሁን ያልሺውን ለሌሎች ነግረሻል?»

«ለምን እነግራቸዋለሁ? በገል ሕይወቴ ምን ያገባቸዋል?» አለች ።

«ለምን ለኔ ነገርሺኝ?»

«ደደብ ። አባቴ ይሙት ደደብ ነህ በሥነ ሥርዓት»

እምነት ጥላብኝ ከምስጢሯ እንድካፈል ልዩ ዕድልና መብት ስለሰጠችኝ እንጂቴ ገባች ። የት አድሮ ይሆን? ስለ ሥዕላይ ለማሰብ ጊዜና ዐቅም አልነበረኝም ። እንደፊያሚታ ጊላይ ካለች ቆንጆ ልጅ ጋር ተኝቶ ማን ያስባል? ውበቷ አስክ ሮኝ ነበር ። ሕይወት እንዳንገዶ ለጋስ ናት ። ሮማን ትዝ አለችኝ ። የጸደቀች ነፍሴ የተኮነነች ይመስል ፡ ማሪኝ ሮሚ አልኩ በልቤ ። ነገ የሚጠብቀኝ ረጅም አድካሚ ቀን መጥቶ ፊቴ ድቅን አለ ።

በአሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል የአሉላ አባ ነጋ መታሰቢያ ሐውልት መሠረት ድንጋይ ዶጋሊ ላይ ሲጣል መገኘት ፣ በሦስት ሰዓት ምጽዋ ፣ ቀይ ባሕር ዳርቻ ላይ የሚደረገውን የምጽዋ በዓል መክፈቻ ሥነ ሥርዓትና ሕዝባዊ ሠልፍ መከታተል ፣ ቀን ቀን በየቦታው የሚደረገውን ጉብኝት ዜና ማቀነባበር ። ማታ በምጽዋ ቤተመንግሥት የሚከፈተውን የሥዕል ኤግዚቢሽንና ኤክስፖ ተከታትሎ ፣ ወዲያውኑ ደግሞ ጉርጉሱም ባሕር ዳርቻ በሚደረገው ሕዝባዊ በዓል ላይ መገኘት...... ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ። ዓይኖቼን ከደንኩ.....

የሰው ማስታወስ ችሎታ አጭር ነው ። በሕይወት ያጋጠመንን ነገር ሁሉ ለማስታወስ አንፈልግም ፣ በተለይም ከፉዎቹን ነገሮች ። ኑሮ ራሱ ስቃይ ነው ። አይደለም እንዴ? ረስተኸኝ ከሆነ ደራሲው ነኝ እንደገና ። በእውነት ተሰቃይቻለሁ ። በሁሉም ቦታና ጊዜ መገኘትና በሁሉም ነገር ውስጥ ገብቼ መኖር ስቃይ ሆኖብኛል ። እኔ ነኝ ፣ ነበርኩ ፣ አለሁ ፣ እኖራለሁ ። ይህ አልበቃኝ ብሎ በሁሉም ነገር ውስጥ ገብቼ ለመኖር ወይም ለመገኘት ምን እንደሚያስመኘኝ አይገባኝም ። ምናልባት ከስቃይና ከፍቅሬ የተነሳ ይሆናል ። ሕይወት ያለስቃይ ምንድነው? ፍቅር ስቃይ ነው ። እና ደግሞ ፍቅር ሕይወት ነው ወይም ሕይወት ፍቅር ። ጸጋዬ ፍቅር ላይ ነው ። ፍቅር እንዳልኩት ጣፋጭም ስቃይም ነው ። እና ጸጋዬ የሚወደውም ይህን ነው— ይህችን ጣፋጭና ስቃይ የሆነች ውብ ሕይወት። ታሪኩ ቀጥሏል።

# እ ን ቅ ል ፍ
# የ ማ ይ ዞ ር በ ት  ቤ ት

ኮሎኔል በትሩ በንዴት ፊቱ የነበረውን ትንሽ ጠረጴዛ በቡጢ አንዴ ነረተና ከተቀመጠበት ግዙፍ ሰውነቱን በቀላሉ ይዞ ተነሳ ። እንደ ነጐድጓድ አጉረመረመ ። ዳሕላክ ሆቴል ሁለተኛ ፎቅ ላይ ለመኝታም ሆነ ለቢሮ የሚያገለግል ትልቅ ክፍል ይዟል ። «እኔ የሞቱትን ሰዎች ስምና አድራሻ ለመስማት አይደለም የጠራኋችሁ! በምን ምክንያት እንደሞቱ? ማን እንደገደላቸው? ነው ማወቅ የምፈልገው! የትራፊክ ጽሕፈት ቤት አይደለም የማካሒደው» አለ ።

አሸብር አጨንቁር ይመለከተው ነበር ። ሥዩም በጣም የተከፋ ይመስላል ። ተክላይ ዘድንግል ጥቁር መነጽሩን አጥልቆ ስለነበረ ፣ ቁጭ ብሎ ያንቀላፋ እንደሆነ ወይም በማዳመጥ ላይ እንዳለ እርግጠኛውን ለማወቅ ያጠራጥራል ።

አሸብር ቀና ብሎ «እሥመራም ሆነ እዚህ ሰዎቻችን ባሁኑ ወቅት የአሟሟታቸውን ሁኔታ ለማጣራት በመሯሯጥ ላይ ይገኛሉ ። ፍንጭ የሚሰጠን ነገር ለማግኘት የሟቾቹ ቤት እየተፈተሸ ነው ። መንገዶችን ዘግተናል ። ጀልባዎች እንዳይንቀሳቀሱ አድርገናል ። አንዳንድ የሚያጠራጥሩ ሰዎችንም ይዘናል...» ሲል የስልክ ጥሪ መጣ ።

ኮሎኔል በትሩ በልቡ እየተራገመ ሔዶ ስልኩን አነሳ ። ያንድ ባለሥልጣን ጥሪ መስሎት ነበር ።

«ማን ልበል?» አለ ።
«ጋረደው ነኝ ጌታዬ...»
«ማን?»
«ጋረደው መኩንን ከአሥመራ...»
«ስብሰባ ላይ ነኝ ሻለቃ ምንድነው?»

«ባጭሩ ፣ ዛሬ ምሽት ላይ ሦስት ሰዎች በየቦታው ፣ ለጊዜው ባልታወቀ ምክንያት ፣ ሞተው ተገኝተዋል — ማይተመናይ ፣ ነጅሬትና ገዛ ብርሀን ። አንደኛው የፓራዲዞ ቡና ቤት ባሬስታ ነበር ። ሁለተኛው ሰው በኮከብ አምራችነቱ የታወቀና የተከበረ ወዛደር ነበር ። ሦስተኛዋ ሴት ናት ። የመንግሥት ሠራተኛ ። ቤት ላጤ ነበረች» አለና ስማቸውን ሰጠው ።

ኰሎኔል በትሩ ማስታወሻ ወሰደና ፣ «እና አሁን ምን እያደረጋችሁ ነው!?» አለው ።

«ጉዳዩን እየተከታተልን ነው....»
«እስካሁን ምንም ፍንጭ አልተገኘም?»
«ገና ምንም አላገኘንም....»

«ታዲያ ቁጭ ብለህ ምን ትጠብቃለህ? ወይስ ወንጀለኞቹ አንተ እንዳትደክም አስበው ቢሮህ ድረስ የሚመጡልህ መስ ለህ! ጧት የተሟላ ሪፖርት እፈልጋለሁ ። ጋዜጠኞች የሚያቀ ርቡት ዓይነት ሪፖርት መስማት ሰልችቶኛል!» ብሎት ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋበት ።

ሁኔታውን በማጤን ሦስቱም ደንግጠው ስብሰብ ብለው ተቀመጡ ። ኰሎኔል የሰው ድድ ለማውለቅ የተዘጋጀ ይመስል ቡጢ ጨብጦና ፣ «ዛሬ አሥመራ ላይ የሆነውን ሰምታችኋል? በተጨማሪ ሦስት ሰዎች በየቦታው ሞተው ተገኝተዋል ። ሁለት ወንዶች ፣ አንድ ሴት በዛሬው ቀን ብቻ አምስት ሰዎች ። ምናልባት ነገ ደግሞ አሥር...... ከነገ ወዲያ ሐያ...... ሀምሣ...... መቶ ። ይህ ነገር ባጋጣሚ የሆነ አይደለም ። ሊሆን አይችልም ። አፍን ጫችን ሥር ሠይጣናዊ ሤራ ሲካሔድ እያየን እጃችንን አጣም ረንና ቁጭ ብለን ምንድነው የምንጠብቀው?! እስቲ ንገሩኝ? ወይስ መጥተው እኛንም አንድ ባንድ እስኪደፉን ድረስ ነው ዝም ብለን የምናየው?» አለ ።

ሦስቱም ፣ ምን አድርጉ ነው የሚለን? የሚሉ ይመስላሉ ። እሱም ቢሆን አንድ የሆነ ነገር ላይ እጁን ለማሳረፍ ከመጨነ ቅና ከመጓጓት በስተቀር ፣ ይህን አድርጉ ብሎ የሚሰጣቸው አሳብ ወይም መመሪያ አልነበረውም ። ስልክ አንስቶ ወደ ፖሊስ

ኮሚሽነር ዘንድ ደወለ ። ስልክ ብዙ ጊዜ ሲደውል ቆየ..... ተናዶ ሊዘጋ ሲል ነበር ኮሚሽነሩ በተዘጋ ድምጽ «ሀሎ?» ያለው ፣ መጀመሪያ ከእንቅልፍ ድንገት የተቀሰቀሰ ሰው የድካም ትንፋሽ ሲያሰማው ከቆየ በኋላ ።

«በጊዜ ሔደህ ተጋድመሐል መሰለኝ?»
«ማ.....ን ልበል?»..... አያዛጋ ።

«ኰሎኔል በትሩ ነኝ ። ምናለ ፣ ሌባ ፣ ሰካራምና ማጅራት መቺ ከያዛችሁ ለናንተ አገሩ ሠላም ነው ። መጠጥ ቤት ተዘጋ..... ትራፊክ ቆመ..... በቃ እንቅልፍ መሰጠጥ ነው....»

«ምነው ምን ደረሰ?!» — ኮሚሽነሩ ደንግጦ ነቃ ። የኰሎኔል በትሩ ስም የማያስደነግጠው ሰው የለም ። «የትራፊክ አደጋ ደርሶ ነው የምደውለው» ብሎ ቀለደበት ። ኮሚሽነሩ ቀልድ መሆኑ አልገባውም — «የት?» ብሎ ጠየቀው ።

«ጓድ ኮሚሽነር ፣ በእንቅልፍ ልብ ከሆነ የምታነጋግረኝ እንቅልፍህን ከጠገብህ በኋላ ጧት ብንነጋገር ይሻላል ።....»

«ነቅቻለሁ..... ነቅቻለሁ»

«ሰሞኑን እንቅልፍ የሚተኙ ሰዎች በእውነት ዕድለኞች ናቸው» ብሎ አሽሟጠጠውና ቀጥሎም ፣ «ጥሩ ። እንግዲያውስ ስማኝ ። በዛሬው ቀን የአምስት ሰዎች ሬሣ በየቦታው ወድቆ ተገኝቷል ። በነገራችን ላይ ፣ የሞቱት በትራፊክ አደጋ አይመስለኝም ፣ ማጅራት መቺዎች ይሆናሉ የገደሏቸው የሚል ግምትም የለኝም ። አንድ የሆነ ሤራ አፍንጫችን ሥር በመካሔድ ላይ ያለ ይመስለኛል ፣ ወይም እምናለሁ..... ያንተ ኃይል ትብብርና ርዳታ ያስፈልገኛል ። የተደራጀ መንግሥታዊ ኃይል ይዘን የምንበለ ጥበት ምክንያት ከቶ አይታየኝም ። አዎ ፣ መንግሥታዊ ኃይል ይዘን የምንበለጥበት ምክንያት ከቶ አይታየኝም ። አዎ ፣ ይህ ያንተ ሥራ ነው ፣ የኔ አይደለም ፣ እኔን አያገባኝም እያልን ስንፎ ካከር ነው'ኮ የምንበለጠው ። የቶከከር ቤት ሳይዘጋ ያድራል ይባል የለ ፣ እንደዚያ ነው....

«ስማኝ ጓድ ኮሚሽነር ፣ በየመንገዱና በየቦታው ጥብቅ ቍጥጥር እንዲደረግ እፈልጋለሁ ። ማንኛውም እንግዳ የሆነ ንቅናቄ የትም ሆነ የት ቢታይ ይነገረኝ — በማንኛውም ሰዓት ። የምትጠራጠሩት ሰው ከተገኘ ፣ ማንም ይሁን ማን ፣ ማመንታት አያስፈልግም — ይዛችሁ መጠየቅ ነው ። ተጨማሪ የሞት አደጋ ካጋጠመ ፣ ይደወልልኝ ። እያንዳንዷን ደንጋይ መፈንቀል አለብን» አለውና ከኮሚሽነሩ መልስ ሳይጠብቅ ስልኩን ከዘጋ በኋላ ፣ ወደ ልጆቹ መለስ ብሎ ፣

«ለናንተም የምሰጠው መመሪያ ይኸው ነው ። እንንቀሳቀስ ጓዶች!» አላቸው ።

ሦስቱም ተያይዘው ወጡ ። ኮሪዶሩ ላይ ሲደርሱ ፣

«ይህ ሰው ጡረታ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ሳይገድለን አይቀርም» አለ ሥዩም ።

«የጡረታ ጊዜ ሲደርስ ሥልጣን ይጣፍጣል ልበል! ባንዱ እንዲህ ትጉ ያደረገው ነገር ምን እንደሆነ አልገባኝም!» አለ አሸብር ።

«የጡረታው ጊዜ እንዲራዘምለት ፈልጎ ይሆናል» አለ ሥዩም ። ተከላይ ዘድንገል ጥቁር መነጽሩን አወለቀና ፣ «ቦታውን ለመያዝ ቸኩለህ እንደ? አትቸኩል» አለው ሥዩምን ።

ኩሉኔል በትሩ ተክላይን ጠራው ። ተክላይ እየሮጠ ተመለሰ ።

«ሥዕላይ የት ነው?»

«ሉና ራት እበላለሁ ብሎ ሔዷል ። የሚከተሉት ሰዎች አሉኝ ።»

«በነገራችን ላይ ከእሱ ጋር የነበሩት ሁለት ሰዎች እነማን ናቸው? አንዱ ረዘም ያለው ወጣት ካንተ ጋር ያወራ ነበር...»

«ሁለቱም የድሮ ጓደኞቹ ናቸው ። አጠር ያለው ሰው ድሮ ከኔ ጋር ታስሮ ነበር ። አሁን የፓራዲሶ ቡና ቤት ባለቤት ነው ። የምጽዋ መንገድ ደህና ከሆነ እዚህም ቡና ቤት ለመክፈት ይፈ

ሊጋል ። ወጣቱ ያርማ አቪዬሽን መካኒክ ነው.... »

«የማን ቡና ቤት አልከኝ?»

«ፓራዲዞ.....»

«እንዴ? የእሱ ቡና ቤት ባሬስታ አይደለም ሞተ የተባለው? ወይስ በዚሁ ስም የሚጠራ ሌላ ቡና ቤት አለ?»

ነገሩ ተከላይን እንደ ድንጋይ መታው ።

«በአሥመራ በዚህ ስም የሚጠራ ሌላ ቡና ቤት የለም.....»

«ስምቶ ይሆን?»

«እንጃ ።»

«ድረስበት ። የሚለውን ለመስማት እፈልጋለሁ ። እና ስለእግዜር ብለህ ፣ በዘዴ ተጠቀም ። ይኸ የጀምስ ቦንድ ዓይነት ጀብደኛነት ያስ አይለኝም ። የመረጃ ሥራ የጭንቅላት ሥራ ነው» ብሎት በሩን ፊቱ ላይ ዘጋበት...

በዚያን ወቅት ሥዕላይ በራኺ ፣ ተከበተ ገብራይና ሦስተኛው ሰው ፣ ወጣቱ ሜካኒክ ሌና ራት ይበሉ ነበር ። ወጣቱ መካኒክ እቁባ ሲላ ይባላል ። አብዛኛው ሰው የሚጠራው ወዲ ሲላ እያለ ነው ። ቅንድቡን ያልበዋል ። የተቀመጡበት ጠረጴዛ ፣ በምግብ ፣ በመጠጥ ፣ በጨዋታና በሳቅ ሞቅ ብሏል ። ይጠጣሉ ፣ ይበላሉ ፣ ይጫወታሉ ፣ ይስቃሉ ። አንዳንዴ ሳቃቸው እውጭ ድረስ ይሰማል ። ሰው ሁሉ ዞር እያለ ያያቸዋል ። ምግብ ቤቱ ውስጥ እስከዚህም ብዙ ሰዎች አልነበሩም ። ካሉትም ውስጥ አብዛኛዎቹ ትንሽ ሞቅ ያላቸው ፣ ለኤርትራ ከፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ጉባዔና ለምጽዋ ፌስቲቫል ከመሐል አገር የመጡ እንግዶች ነበሩ ። የሌና ባለቤት የሆኑት ሁለት ሽማግሌ ጣልያኖች የደራ ገበያ ስላገኙ ደስ ብሎአቸው ፣ ጡብ እርግፍ በማለት እንግዶቻቸውን በፈገግታና በትሕትና ያስተናግዳሉ ። እነ ሥዕላይ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲጫወቱና ሲሶቱ ይቆዩና ደግሞ ቀስ ብለው እየተንሾካሸኩ ማውራት ይጀምራሉ..... እና በመጨረሻ ፣ ሥዕላይ ድምጹን ዝቅ አድርጎ ። «ለምንድነው የፈለጋችሁኝ? እኔ ካልፈለኳችሁ በስተቀር በምንም ሁኔታ እንዳትመጡብኝ ብያችሁ አልነበረምን?» አላቸው ።

ተከስተ ፣ «አዎ ፣ ግን በጣም አስቸኳይ ነገር ገጥሞን ነውን» ካለው በኋላ ገልመጥ ፣ ገልመጥ ብሎ ፣ «ግን ፣ ይህን ቦታ ምን አስመረጠህ?» አለው ።

«አጀኛ ግልጽ ነገር አብዛኛውን ጊዜ ስውር ነው ። አንተ እዚያ ዋሻህ ውስጥ ካልሆንክ በቀር ሌላ ቦታ ደህና አይመስልህም» አለውና ድምጹን ከፍ አድርጎ የውሸት ሳቅ ሳቀ ። ተከስተና ወዲ ቢሮ እስኪ ተከትለው ሳቁ... ሥዕላይ ቀጠለና ፣ «የምንፈልጋ ቸው ሰዎች ሊስት ተዘጋጅቷል?» ብሎ ተከስተን ጠየቀው ።

ተከስተ ተናደደ ። ስለሰዎች ሊስት ጉዳይ ለመነጋገር አልነበረም የመጣው ። ቢሆንም ፣ «አዎ ፣ የ211 ሰዎች ስም ይዘናል ። መቸ? የት? እንዴት? በማን? ልክ ባልከው መሠረት ። ስለእሱ ግድ የለህም ። ተዘጋጅተናል ። ያንተን ትእዛዝ ብቻ ነው የምንጠብቀው» በማለት አጭር መልስ ሰጠው ።

ተከስተ ወደ መጣበት ጉዳይ ከማምራቱ በፊት ፣ ሥዕላይ ፣ «የመሣሪያዎቹስ ሁኔታ» ብሎ ሌላ ጥያቄ አቀረበለት ።

ተከስተ አሁንም እየቸኮለ ፣ «ጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ያለነው ። እርግጥ ቁጥጥሩ ጠብቋል ። ቢሆንም እንደምንም እያልን መሣ ሪያ እያስገባን ነው ። አንድ ወር ጊዜ ብናገኝ በአሥመራ ከተማ ውስጥ አፍንጫው ድረስ የታጠቀ ኅቡዕ ሠራዊት ሊኖረን ይች ላል» አለው ።

«አንድ ወር ጊዜ የለንም ። እኛም እንደኑሱ ከጊዜ ጋር እየታገልን ነው ። አሥራ አምስት ቀን ። በዚህ ጊዜ ውስጥ የታጠቀ የከተማ ሠራዊት አደራጅተን መገኘት ይኖርብናል ። አዲስ አበባ ያሉትም መሣሪያ! መሣሪያ! በማለት እየጮሁ ነው ። መጀመሪያ መደረግ ያለበት ነገር ሁሉ ቅድሚያ እንዲሰ ጠው እፈልጋለሁ ። ይህ ነገር ቀልድ አይደለም ። ለእነሱም ሆነ ለኛ ነገሩ አንድ ነው —ሳንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሁን ካዳ ከሙን ዳግመኛ ለማንሠራራት እንችልም፥በንችልም ብዙ ዓመት ይጠይቀናል» አለውና ማሀኑን ከፊቱ ገፍቶ እንደ ነገሳ በኋላ ፣ «እሺ እምባር ፣ ለምንድነው የፈለጋችሁኝ?» በማለት ጠየ ቃቸው ።

ተከስተ ቁራጭ ሲጃራ ከሙኮስተሪያ ውስጥ አወደመና ሌላ ሲጃራ አውጥቶ ካቀጣጠለ በኋላ ባበነነው የሲጃራ ጢስ ውስጥ ሥዕላይን በቀያይ ዓይኖቹ እያየው ፣ «ያልጠበቅነው ነገር ተፈጥሮአል…» ከማለቱ —

ሥዕላይ ቸኩሉ ፣ «እንድያግን ያለ ነገር!?» ብሎ ጠየቀው ።
«ዛሬ አምስት ሰዎች መደምሰስ ነበረብን…»
«እና?»
«ደምስሰናቸዋል ።»
«በማን ትእዛዝ!» አለ ።

ድምጹን ከፍ አድርጎ ነበር የተናገረው ። ዞር ፣ ዞር ብሎ ምግብ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ተመለከተ ። የሰማው ሰው አልነበረም ። ሁሉም ይህን ሳዛኝ ፣ ታላቂሊና ማካሮኒ ሳሊታታ እቀርቅረው ይውጡ ነበር ።

«ትእዛዝ ለመጠበቅ ጊዜ አልነበረንም ። ማድረግ ነበረ ብን…።»
«ለምን? ምን ተፈጠረ?»
«ሳይቀድሙን መቅደም ነበረብን ። ጊዜ አልነበረኝም ። ካንተ ትእዛዝ ብጠብቅ ኖሮ ይኸኔ ለፖሊሶች አሳልፈው ይሰ ጡን ነበር ። አንተን በጊዜ ለማግኘት ደግሞ አልቻልኩም ። ይህን ልንነግርህ ነው የመጣነው» አለው ።

«እነማን ናቸው?»

«በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ምስጢራችንን የሚ ያውቁ ሰዎች ነበሩ ። ዝም ማሰኘት ነበረብን ። ምርጫ አልነበ ረንም ።…»

«በምንመለምላቸው ሰዎች ላይ መጀመሪያውኑ ጥንቃቄ ብና ደርግ ይህ ሁኔታ አይደርስም ነበር ። ግን አናደርገውም ፣ አይደ ለም? ችግሩ እዚህ ላይ ነው ። የልጆች ጨዋታ አይደለም የምን ጫወተው ። ማድረግ ነበረብን ብሎ ነገር! አንድ ነገር ከሆነ በኋላ የሚነግረኝ አሻንጉሊት አይደለሁም…… ታላቁ ዓላማችን ላይ ሳንደርስ በምንፈጽመው ጥቃቅን ስህተት ብንያዝ አሁን

ምን ይባላል! የናቅፋ ተራሮች በሙሉ የውርደት ሳቅ ይስቁብ ናል ። ቴስታ ዲጋሊናየ» ብሎ የገዛ ግንባሩን በቡጢ ገጨው ።

«ችግሩ ከጥንቃቄ ጉድለት አይደለም ። እምስቱም ታማኞች ነበሩ......»

«ታዲያ ችግሩ ከምን ላይ ነው ልትለኝ ነው? ዝርክርክነት ነው ። ሌላ አይደለም.....»

«ለምሳሌ አቦይ ተኽሌን እንውሰድ.....»

«የቱ አቦይ ተኽሌ?»

«ና! አትለኝም?»

«ያ ብስብስ ሽማግሌ ሊከዳን ነበር.....»

«ግን ለምን?»

«ምነው ነገሩን እያወቅኸው ። ኤ ኮዘ ፋሬ? ጊዜው ተለው ጧል ። ሁሉም በሠላም መኖር ፈልጓል ። ሁሉም በኛ ተስፋ እየቆረጠ ሔዷል ። በተለይም ይህ ቀይሕ ኮኸብ ዘመቻ ከመጣ ወዲህ አብዛኛው ሰው ማፈግፈግ ጀምሯል ። ሐያ ዓመት ቀላል ጊዜ አይደለም ። ሁልጊዜ ማርሻ ኢንዲትሮ!» አለና በ1970 አካባቢ የተዘፈነው ዘፈን ትዝ ብሎት —

«አንታ እነ ገሪሙኒ
ማርሻ ኢንዴትሮ ዶ
ዝመልስ መሲሉኒ»

«ተብሎ የተዘፈነው ዘፈን ሰምተሀል? ሰው አይፈረድ በትም ። ከቤቱ ወጥቶ ተሰደደ ። ታሰረ ። ተገደለ ። በየበረሀው ሞቶ ቀረ ። በባዕዳን አገሮች የመከራ ኑሮ ገፋ ፣ ተሰቃየ ፣ ተን ከራተተ ። ምን ተፈጠረ? ምንም ። ነጻነት እንደሆነች ሲቀርቧት እንደ ሰሜናዊ ኮኸብ ከፊታችን እየራቀች የምትሔድ ሆናለች ። እና ምን ሰጥተናቸው እናውቃለን? ከባዶ ተስፋ በቀር ። እና አሁን ሕዝቡ ሠላም ቢፈልግ ፣ ቢከዳንና ቢጠላን አይገርመኝም ። ከአቦይ ተኽሌ የበለጠ የሚታመን ሰው የት ነበር?» አለ ።

«አንተም ተስፋ እንደቆረጠ ሰው ነው የምትናገረው ። ከእንዳንተ ያለ ሰው እንዲህ ዓይነቱን ነገር መስማት አልፈል

ግም ። በእውነቱ የከተማ ዲሲፕሊን ይገርመኛል ። በረኻ ቢሆን ኖሮ አሁን ያልከው ነገር በሞት ያስቀጣህ ነበር» አለው ሥዕላይ ተቆጥቶ ።

«የሆነ ሆኗል ። ተከስተ እንዳለው ሳይቀድሙን በፊት መቅደም አስፈላጊና አማራጭ የሌለው ርምጃ ነበር ። ለማንኛውም ነገር አቦይ ተኽሌና መሰሎቹን ነፍሳቸውን ይማር።የፈለጉትን ሁላም አገኙተዋል» አለ ወዲ ሲሳ ለመጀመሪያ ጊዜ እየሳቀ ። ሁሉም አንድ ላይ ሳቁ ።

ሥዕላይ «የአቦይ ተኽሌ ልጅ ያባቱ መርዶ እንዲደርሰው አድርግ» አለው ተከስተን ።

«የት ነው?»

«ናቅፋ ። ሻዕቢያ ብርጌድ አዛዥ ነው ። ስሙ ጥር ተሞጊ ሆኗል ። እና በነገራችን ላይ ፣ አቦትህን መንግሥት ነው የገደለው ብለህ ንገረው» ብሎ ቪኖውን ጨልጦ ሲጃራ ካቀጣጠለ በኋላ ፣ «ስለእግዚር ብለን የሞተ ሰው አይናገርም በማለት እን ሸፍና ። የሞቱት ፍንጭ እንዳልተው ፣ እኛም የሞኝ ሥራ ሠር ተን እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ ። እና ከዛሬ ጀምሮ እኔ ሳላ ውቅ ምንም ዓይነት ርምጃ መወሰድ የለበትም ። ይህ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነው» አላቸው ።

«ስለ እሱ አትስጋ ። ጥራት ያለው ሥራ ሠርተናል ። ቤታቸውን አንድም ሳይቀር ፈትሸናል ። የሚያስጋን ነገር የለም ። ግን አሁንም ቢሆን ተመሳሳይ ሁኔታ ካጋጠመን ትንሽ ነጻነት እንድ ትሰጠን በጥብቅ አሳስባለሁ ። ያለንበትን አሳሳቢ ሁኔታ መረዳት አለብህ» አለ ተከስተ ።

ድምጹ ፍቻም ያዘለ ነበር ። ሁለቱ ሰዎች ዓይን ለዓይን ተያዩ ። ሁለቱም ፊት ላይ የመኖር ጥያቄ ይነበብ ነበር ።

«እንዳል ! ። ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት» ከማለት ሌላ ምርጫ አልነበረውም ። በየጊዜው ከእሱ የሚጠበቀውን ውሣኔ በተፈለገበት ቦታ ተገኝቶ ለመስጠት እንደማይ

ችል በትክክል ተገንዝቧል ። ቅር እያለው የተከሰተን ሀሣብ ተቀብሎ ሥልጣን ሰጠው ።

«የሕዝብ ደኅንነት ሰዎች እንደ ጉንዳን እንደሚከተሉህ መቸም ታውቃለህ ብዬ ነው» አለ ተከሰተ ።

ረዘም ያለ ዝምታ በመካከላቸው ሰፈነ ። ራታቸውን በልተው የጨረሱ አንዳንድ ሰዎች ሲወጡ ፣ ራት የሚፈልጉ ሌሎች ሰዎች ይመጡ ነበር ። ፀሌና ባለቤቶች አይደክማቸውም ። የመጣውን ደንበኛ ሁሉ በደስታ ተቀብለው ያስተናግዳሉ ። የለንም ፣ ወይም አልቋል የሚሉት የምግብ ዓይነት የለም ። ብዙ ጊዜ ሥራ ፈተው የቆዩ ይመስላሉ ። ሥራ ፈተው የቆዩበትን ጊዜ ለማካካስ ሳይሆን አይቀርም ፣ ዋጋቸው የመርዶ ያህል ነበር ። እውነትም አንዳንድ ሰዎች ሂሣብ ሲቀርብላቸው አቀርቅረው ትንሽ የሕሊና ጸሎት ሲያደርሱ ይታዩ ነበር ።

«ጊዜው አስቸጋሪ ሆኗል» አለ ተከሰተ ከረጅም ዝምታ በኋላ ።

«አዎ ፣ በገዛ እጃችን ነው አስቸጋሪ ያደረግነው ። አንተብ በርም ፣ ጠላቶቻችን ፊት እርስ በእርሳችን እንፋጃለን ። የተረገምን ሕዝብ ነን ። ትናንት ስንንቃቸውና ስንጠላቸው የነበሩት የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር ሰዎች ብቻ ናቸው ዛሬ የሚተባበሩን፣ እሱም ቢሆን ዘላቂነት የለውም ። ያሳዝናል» አለና እዝን ብሎ ከቆየ በኋላ ፣ ወደ ወዲ ሲላ መለስ በማለት ፣ «ይህ የአርሚ አቢዮሽን ሰውዬ ስሙ ማነው አልከኝ?» አለው ።

«ሻለቃ ታደሰ ቆሪቾ ።»
«የሚታመን ሰው ነው?»

«ከእንግዲህ ምርጫ የለውም ። እኛ ትብብሩን እንፈልጋለን ፣ እሱ ገንዘባችንን ይፈልጋል ። ጡረታ የመውጫው ጊዜ የደረሰ ሰው ነው ። ግን ገንዘብ ከየጠየቀ አስቸግሮአል» አለው ።

«የጠየቀውን ክፈሉት ። ሰውዬው ያስፈልገናል ።»
«ዛሬ ጉድ ሆነን ነበር» አለ ወዲ ሲላ ።

«ምን ሁናችሁ?» አለ ሥዕላይ ።

«አዲሳባዎች የጠየቁንን መሣሪያ ስንጭን ጸጋዬ ፣ ጋዜጠኛው ደርሶብን ነበር ። ጅሉ ደንግጦ ካርቶኑን ለቀቀው.....»

«እና!» አለ ሥዕላይ ቅንድቦቹን ከፍና ዝቅ እያደረገ ። «መሣሪያዎቹን አይቷል ። ግን የገባው ነገር ያለ አይመስለኝም....»

«ይመስልሀል! እንዲህ ዓይነቱን ጅልነት ነው የምጠላው! ጸጋዬ ጅል አይምሰልህ ። ልምድ ያለው ጋዜጠኛ ነው ። ስላይ ባይሆንም አንድና አንድ ሁለት ማለት እያቅተውም ።» ብሎ ሞኸበት ።

ወዲ ቢላ ቅንድቡን አላበው ። ሁልጊዜ ቅንድቡን ያልበዋል ። ላቡን ከቅንድቡ ላይ በመሐረብ ጠረገና ፣ «ከቁጥጥሬ ውጭ የሆነ አደጋ ሲደርስ ምን አረጋለሁ?» አለ ።

«ያውቅሀል?»
«አይመስለኝም.....»

«ካላወቀህ ከእሱ ራቅ ። አደገኛ ልጅ ነው.....» ሲል ተከስተ ትብራይ በነገራቸው ግልቃ ገባና ፣ «አሁን ከማን ጋር እንዳለ ታውቃለህ?» በማለት ሥዕላይን ጠየቀው ።

«ከማን ጋር ነው?»
«ከፊያሜታ ጊላይ ጋር ዳሕላክ ሆቴል ። የኛ የሆነ ሰው አጣርቶልኛል....»
«አትለኝም!»
«ቁጥር አሥራ ሦስት....»
«ፊልዩ ዲካን!» አለ ሥዕላይ ።
«ድሮውን ለምን እንዲህ ያለ የሞኝ ሥራ ሠራህ?»
«ስታይ ዚቶ!»

ተከስተ ዝም አላለም — «ያን ሌሊት ከእሷ ጋር እንዳላደርክ እርግጠኛ ነኝ ትነግረዋለች ። እስካሁን ለማንም አልነገረችም ነበር ።»

«ለእሱ እንደምትናገር በምን ታውቃለህ?»
«አሳምሬ ።»
«ፈልዩ ዲ ካነ!» አለ እንደገና ጥርሱን ነክሶ ።
«ስድብ አይበቃም…»
«ታዲያ ምን ይሁን ነው የምትለው?»
«ሁለቱንም ማጥፋት …»
«የባሰ ጅልነት ይሆናል …»
«ለምን?»

«እንደማውቃት ያውቃሉ ። እየተከታተሉ ስለኔ ሲጠይቋት ቆይተዋል ። ጅሉች አይደሉም ። ስትጠፋ በተለይም ከእጋዬ ጋር ፣ አንድና አንድ ሁለት ማለታቸው አይቀርም ። ይልቅ…» ብሎ አሳቡን ጨርሶ ሳይገልጽላቸው ፣ ተክላይ ዘድንገል ወደ እነሱ ጠረጴዛ ሲመጣ አዩና በሳቅ ፈነዱ ። ሁሉቱም እሱን አይተው ሳቁ ።

ተክላይ መጥቶ ፣ ወንበር ስቦ እየተቀመጠ ፣ «እንዲህ የሚያስቃችሁ ቀልድ ምንድነው?» በማለት ተቀላቀላቸው ።

«አንዳንድ ቀልድ እያወራን ነበር» አለ ሥዕላይ ።

«እንደምን ያለ ቀልድ?» አለ ተክላይ ዐውቆ ። ደረቅ ሳቅ ይስቁ እንደነበረ አውቋል ወይም ተሰምቶታል ። ሥዕላይ የተክላይ ጥያቄ አዝማሚያ ቶሎ ስለገባው ፣

«ሲያስቀን የነበረው ቀልድ? ከሐማሴን አውራጃ የመጡ አንድ ሽማግሌ ምን አደረጉ ይባላል መሰለህ? ነገሩ እውነት ነው ። ቀልድ አይደለም ። አሥመራ ይመጡና ጠመንጃ ስጥታች ሁን ሔጂ እነዚህን ወንበዴዎች ካልወጋሁ ሞቼ እገኛለሁ ይላሉ ። «ምንው? ምን ሆኑ?» ሲባሉ ። «ወንበዴዎች ርስቴን ቀምተው ለሌሎች ሰዎች ሰጡብኝ ይላሉ ።» ታዲያ መንግሥት ርስትዎን ከሌሎች ጋር በጋራ አርሰው እንዲኖሩ ቢያደርግ ምን ያደርጋሉ?» ተብለው ሲጠየቁ ምን ብለው መለሱ መሰለህ? «ዋእ! ጥሩ ። ጠብመንጃውን ስጡኝ ብቻ ። እናንተንም እወጋበታለሁ» አሉ ይባላል በማለት ድንገት የፈጠረውን ቀልድ ፈጥኖ ነገረውና ሳቀ ። ሌሎችም ሳቁ ።

ተከስተ ገብራይ ቀጠለና ፣ «እኔም ሌላ ቀልድ ላጫውታ ችሁ» ብሎ ጀመረ — «አንድ ሚሲሽያ ወደ ጠላ ሻጭ ቤት ይሔዳል ። ጠላ አልቆባት ነበረና ፣ ተወዲኡ! ተወዲኡ! ትለ ዋለች ። «ግድ የለሽም ፣ ቢወደድም ዋጋ ጨምሬ እጠጣለሁ» ይላታል ። ኋላ አንድ የጎረቤት ልጅ ምን ማለቷ እንደሆነ ያስረ ዳል ። ነገሩ ገብቶት ሊሔድ ሲል ፣ ቤትዬዋ ታዝንለትና ከጎረቤ ቶች ጠላ ፈልጋ ታጠጣዋለች ። ይተዋወቃሉ ። አንድ ቀን ተኝ ተው ሲጫዋወቱ...... እለ አይደለ...... ማዓረይ ማዓረይ ስትለው ይሰማና እይ ፣ ይህች ሴት ማር አምሮአት ይሆናል ይልና በሌላ ቀን ማር ይዞላት ይመጣል ። አሁንም ሲጫዋወቱ ፣ ሽኮሬይ ሽኮሬይ ትለዋለች ። በበነጋታው ደግሞ ስኳር ይዞላት ይመጣል ። መዓሬይ ሽኮረይ ስትለው ትውላለች ። ስኳርና ማር ይዞ ከተፍ ። እንዲሁ ሲል ፣ አንድ ጓደኛው አንድ ቀን ፣ ጠጅ ነጋዴ ያዝክ እንዴ? ብሎ ይጠይቀዋል ። የለም ፣ እሷስ ጠላ ነጋዴ ናት ። ማርና ስኳር ትወዳለች መሰለኝ በሔድኩቁጥር «መዓሬ ፣ስኳሬ» እያለች ታስቸግረኛለች አለው ይባላል ብሎ አጫወታቸው ።

ተክላይ ቀልዳቸውን ሲሰማ ቆየና፣ «እኔ ደግሞ የሚያሳዝን መርዶ ልንገራችሁ» አለ ።

ሥዕላይ «ከላ!» ብሎ እጁን አወናጨፈና ፣ «የሚያሳዝን ነገር ማን መስማት ይፈልጋል ብለህ ነው? ሕይወት እንዲሁም አሳዛኝ ናት ። ቀልድ ካለህ ንገረን ። መሳቅ እንፈልጋለን ሳቅ ደግ ነው» አለው ።

«ኃዘን'ኮ የሳቅ ሌላው ገጽታ ነው......»

«ኤ. ዳይ! እንጠጣ» ብሎት ብርጭቆ ሙሉ ቪኖ ቀዳለትና ፣

«አብረን ላሳለፍነው የልጅነት ጊዜ ። እና ለቀይ ኮከብ ዘመቻ» አለና ብርጭቆወን አነሳ ።

ሁሉም ብርጭቆአቸውን አንስተው አጋጩ ።

ተክላይ ቀስ ብሎ ብርጭቆውን በእጁ እያዞረ ፣

«አቦይ ተኽሌ መጥታቸውን ሰምተሀል?» አለው ተከስተን።

«የቱ አቦይ ተኸሌ? የኔ አቦይ ተኸሌ!»

ተክላይ በጥቁር ሙንጆሩ የተከስተን ስሜት ቀስ ብሎ እያ

ጨኑ ፣ ረጋ ብሎ ፣ «እዎ ፣ ያንተ ባሬስታ» አለው ።

ተከስተ ድንግጦ ከመቀመጫው ተስፈንጥሮ ተነሳ ። ተመልሶ ወንበሩ ላይ ዘጭ አለና ራሱን በሁለት እጆቹ ይዞ አንገቱን ደፋ ።

ሥዕላይም የደነገጠ ሰው መስሎ ፣ «ምነው፣ ምን ሆነው ሞቱ፣ መቼ?» በማለት ወተወተ ።

«የሞቱበት ትክክለኛ ሰዓት ለጊዜው አልታወቀም ። ምናልባት በግምት ከሦስት ሰዓት በፊት ይሆናል...» ተከስተ ወደ ስምንት ሰዓት ገደማ ስላያቸው «ሥራ ላይ ነበሩ ። እና ደህና ነበሩ ። አውይ አቦይ ተኽሌ» ብሎ እንባውን ጠረገ ።

«ምን ሆነው ሞቱ?» —ሥዕላይ ነበር ።

«ምክንያቱ አልታወቀም ። ለጊዜው ግን ከሁኔታው ሰው የገደላቸው ይመስላል ።»

ተከላይ ቀስ ብሎ ፊታቸውን ለማንበብ ይሞክር ነበር ። በሆነ ምክንያት ፣ ጭምብል ያጠለቁ ተዋንያን መሰለው ታዩት ፣ ወይም ተሰማው ። እነጋገራቸው ሁሉ የታሰበበት ፣ የሚገልጹት ስሜት ሁሉ የተጠና መስሎ ቢሰማውም ፣ የተቀነባበረ ለመሆኑ ምንም ማስረጃ አላገኘም ። ውስጡ በብሽቀት ቅጥል ፣ እርር ፣ ድብን ፣ ኩምትር አለ ። ብርጭቆውን አንስቶ ፉት ቢና ቢያንኮ ሴኮ ቸለሰበት ።

«ሰው ገደላቸው ለማለት የሚያስችል ምን ምክንያት ተገኘ?» አለው ሥዕላይ ።

«መኖሪያ ቤታቸው ምስቅልቅሉ ወጥቶ ነው የተገኘው ። ከእሳቸው አንድ ነገር የሚፈልግ ሰው ያለ ይመስላል ወይም ብዙ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ ።» ብሎ መለሰለት ።

ተከስተ እንባውን እንደገና ጠርጎ «ምስኪን! አቦይ ተኽሌን ለመግደል የሚፈልግ ምን ጠላት ይገኛል? ለሁሉም እንደ አባት ነበሩ ። ምስኪን ሽማግሌ!» አለ ።

ተከላይ ፣ መነጽሩን አፍንጫው ላይ አስተካከለና ፣ «ይልቅ አሁን ባለንበት ጊዜ ማን ወዳጅ አለው? ብትል ይሻላል» አለው በምጸት ።

ሥዕላይም ፥ «አባባልህ ልክ ነው ። ባሁኑ ጊዜ ወዳጅ አለኝ ብሎ መመካት ሞኝነት ይሆናል ። ከወዳጅ ጠላት ይሰውረን ማለት ነው» ብሎ በነገር ነካ አደረገው ።

ተከስተ አፍንጫውንና ዓይኑን ጠረገና በጥልቅ ኃዘን ተውጦ ፥ «ምስኪን አቦይ ተኸሌ! ከሚያፈሉበት መኪና ሌላ ሰው ቀና ብለው አያነጋግሩም ነበር ። ያ የቡና ማፊያ መኪናና እሳቸው ላለፉት ሐያ አምስት ዓመታት አንድ ቀን እንኳን ተለ ያይተው ውለው አያውቁም ። እንደሰው ያነጋግሩት ነበር ። መኪናውም ያለ እሳቸው እሺ ብሎ አይሠራም ። እና ተጋግ ዘው ፥ በአሥመራ በጣዕሙ ወደር የሌለው ቡና ያፈሉ ነበር ። ምስኪን! መኪናውም ከእንግዲህ ያለእሳቸው አይሠራም ። እሱም ሞቷል ። እና ከእነሱ ጋር የፓራዲዞ ቡና» አለ ።

ሥዕላይ በሳቅ ፈነዳ ።
«ምን አሳቀህ?» አለ ተከስተ ።
«ለንግድህ ስታለቅስ ታይቶኝ ነው......»

«ምን ያስቃል? አዲስ ነገር አይደለም ። ሁሉም ስለራሱ ነው የሚያለቅሰው — አይደለም እንዴ? የሞቱትማ ሞተዋል ። መቃብራቸው ምን ይናገራል? ወይስ ይናገር ይሆን?» አለ ተክላይ እየተፈላሰፈ ። ትንሽ ቆየና ሌላ ፊያሽኮ ቪኖ ሴኮ አዘዘ ...... «እስካለን ድረስ እንጠጣ ። ለጤናችን...... ጤና ካለን» አለ ።

ሥዕላይ ብርጭቆውን አንስቶ ፥ «ምነው ፥ ለመሞት አስ ብሃል ?» አለው ።

«ማን ለዘላለም ይኖራል !» አለ ።
ቀይ ባሕር ላይ የንጋት ቅንድብ ብቅ ሊል ምንም አልቀረ ውም......

፮

## ፊያሜታና እኔ

# ከቀይ ኮከብ መጋረጃ በስተጀርባ

## ምዕራፍ ሦስት

ጥር 18 ቀን 1974 የሥራ ሠርግና ምላሽ ሆኖ ዋለ ። ዳሩ ጥር የሠርግና ምላሽ ወር አይደል ፣ ቀኑን ሙሉ ትንፋሽ አልነበረኝም ። ክንፍ አውጥቶ ከጊዜ ጋር እንደመብረር ነበር ። ሩጫው ባልከፋ ፣ ቀኑን ሙሉ ሲሠራ የዋለውን ዜና ፣ የቴሌቪዥን ፊልሞች ፣ ፎቶግራፎችና የቴፕ ክሮች በጊዜ ወደ አሥመራ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ አስተባብሮ መላኩ ኅዋሳት የማያናጋ ሌላው ራስ ምታት ነበር ። ምጽዋ ቤተ መንግሥት አዳራሽ ውስጥ የተካሔደውን የሥዕል ኤግዚቢሽንና የኤክስፖ መክፈቻ ሥነ ሥርዓት ሥራ ጨርሼ ላይ ወደ ሆቴል ስመለስ ፣ ፊያሜታ ጊላይ ተዝናንታ አልጋዬ ላይ ጋደም ብላ ባገኘኋት ጊዜ እንደ ድንጋይ ተጭኖኝ የነበረው ድካም ከላዬ ላይ እንደ በጋ ጉም በኖ ጠፋ ። እጥፍ ዘርጋ የሚለው ሽንጧ ፍቅር የተራበ ይመስላል ።

«ኢሂ ደአ ፊያሜታ ሴሌሳ?»
«ላዕሊ ። ከመይ ውዕልካ?»
«ጽቡቕ ፣ ሚያ ሰሜናዊት ጸብቒቲ»

ከተጋደመችበት እጅዋን ዘረጋችልኝ። ጡቶቿ «እጅ ወደ ላይ» የሚሉ ይመስላሉ — አፈሙዛቸውን ደግነው ፣ ወድረው ።

«ላብ በላብ ሆኘ እሸታለሁ። በፈጠረሽ ቢራ እዘዥልኝ ። ተቃጥያለሁ» ብያት ሻወር ለመውሰድ ወደ መታጠቢያ ቤት ሔድኩ ። ቀዝቃዛው ውሀ መንፈሴን አደሰው ። ቀዝቃዛው ቢራ ነፍሴን ፈወሳት ።

«አንቴ ፣ አባቴ ይሙት ባለጌ ነህ» አለችኝ ።
«ምን አጠፋሁ?» አልኳት ደንግጬ ።

«እርግጠኛ ። ደስ ይለኛል ። እልክ ውስጥ እገባለሁ ። እልክ ውስጥ ስገባ እሰቃያለሁ ። እና እወደዋለሁ» አለች ።

«ጉድ ነው ። እጮኛ ባይኖረኝስ ኖሮ ?»

«አልፈልግህም ነበር ፣ እባቴ ይሙት ። እውይ ጸግዬ ፣ ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ? እስቲ ንገረኝ» አለች ።

«ጣፋጭ» አልኳት ።

«ደደብ ነህ አባቴ ይሙት.....»

«እንቺ ልጅ ተይ ደደብ አትበይኝ» አልኳት ።

«ለምን? እስቲ ንገረኝ?»

«ባገራችሁ ወንድ ይከበራል፣አይደለም? መከበር አለብኝ.....»

«እውይ ማን አለህ?»

«ዐውቃለሁ ። ገዢሚ የማትስጥ ሴት ባል አታገኝም ። እና ታዲያ ይህ ምን ማለት ይመስልሃል? ወንድ ከቡር ነው ማለት ነው ። አይደለም?»

«ደደብ ። አባቴ ይሙት ደደብ ነህ ። ለምንድነው ግን ደደብ የምልህ? ምን ዓይነት ሴት ነኝ?»

«እንደገና 'ጣፋጭ'» አልኳት ።

እና ፣ ሌቱን በሙሉ ጣፋጭ ነበረች ። የምጽዋ ፌስቲቫል ገና ላንድ ቀን የሚቆይ ቢሆንም ፣ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ጉባዔ ከምጽዋ ተመልሶ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ቀደም ብዬ ያን ጧት ወደ አሥመራ መመለስ ነበረብኝ ። ብዙ ሥራ ይጠብቀኛል ። እና ፣ ከነገ ጀምሮ ለሚቀጥሉት ሦስት ወይም አራት ቀናት በትንሣኤ አዳራሽ የሚካሔደው የጉባኤው ውይይት ፣ እያንዳንዱ የጉባኤው አባል በጉዳዩ ላይ ያለው አስተያየትና አቋም ፣ እንዲሁም በመጨረሻ ጉባኤው በማኒፌስቶ መልክ የሚያስተላልፈው ውሣኔ ፣ ከዳራሹ ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀጥታ መተላለፍ ነበረበት ። ይህ እንኳን አላስጋኝም ። የጥር ወር የሥራ ሠርግና ምላሽ ሁለተኛ ተፈጥሮዬ ሆኗል ። ይልቅ በጣም እያሳሰበኝና ስጋት ላይ እየጣለኝ የሔደው ከውጭ የታዘዙት መሣሪያዎች የውሀ ሽታ ሆነው የመቅረት ጉዳይ ነበር ። ብዙ ጊዜ ያደረስኩት ጸሎት አልረዳኝም ። እንደ አቡነ ተክለሀይማኖት ሰባት ዓመት ባንድ እግሬ ቆሜ እንዳልጸልይ ጊዜ አልነበረኝም ። በጉባዔው ፍጻሜ ማግስት የውጊያ ትእዛዝ ድንገት ቢሰጥ ምን ተይዞ በሦስት ግንባር ናቅፋ ሊዘሙት ይሆን? ከአዲስ አበባ ያመጣነው ፊልምና የቴፕ ክር ወደ

መገባደዱ ላይ ነበር ። ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ እንዲሉ ፥ የምን ፊልም ቁጠባ! ይህን ታሪክ ያልቀረጸ ፊልም ለመቸ! ከዶጅ የተለቀመ ጭራሮ ይመስል ዝም ብሎ ማቃጠል ነበር ። በእጃችን የቀረው ጥሬ ፊልም ፥ ሌላው ቀርቶ ፥ የጉባዔውን ሥራ ካስጨረስን ምንኛ ደግ በሆነ ። በእጃችን ያሉት የቴሌቪዥን ካሜራዎች ያረጁ ከመሆናቸውም በላይ ለመስክ ሥራ ይህን ያህል የሚያስተማምኑ አልነበሩም ። ታሪክ በድዱ ሲስቅብኝ ታየኝ ። ለሚሰማኝ አምላክ ፥ እሱም ካለ ፥ የመጨረሻ ጸሎት አደረስኩና ፊያሜታን ቀሰቀስኳት ። እሷም ከኔ ጋር ወደ አሥመራ ለመመለስ ፈልጋ ነበር ።

«ባሰኜ ነህ አባቴ ይሙት!» ብላ ወደ ውስጥ ገባች ። ብርድ ልብሱን ከነእንሶላው ገፈፍኳት ። እርቃኗን ቀረች ።

«እውይ አባቴ ይሙት ደደብ ነህ ። ምን አድርጊ ነው የምትለኝ? ምን ባደርግህ ይሻላል ግን? እንተግናይ!» አለችኝ እየተነጫነጨች ።

«ላ ሚ ኝ» አልኳት......

ሳመችኝ ። ትንፋሿ እንደ ዱር ጽጌረዳ ሁልጊዜ ደስ ይላል ። እየተነጫነጨች የግዷን ተነሳች ። ለመልበስ ጊዜ አልፈጀባትም ። በቀላሉ የማጌጥና የመዋብ ችሎታ አላት ። ወይም የወጣትነት ዕድሜዋ ይሆናል የሚረዳት ። መኳኳል አታበዛም ። ልብሶቿም ሆኑ ጌጦቿ ውድና ቀላል ውብ ነገሮች ናቸው ። ወደ አሥመራ ከመነሳታችን በፊት ለቁርስ ወደ ምግብ ቤቱ ተያይዘን ሔድን ። ኰሎኔል በትሩ አይቶን ፥ በዓይኑ ጠቅሶ አበረታታኝ ። ከፊያሜታ ጋር ሆኘ በማየቱ ደስ የተሰኘ ይመስላል ።

«አንድ ጊዜ ይቅርታ» ብያት ወደ ኰሎኔል በትሩ አመራሁ።

ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ፥ «እንቅልፍ ባይንህ የዞረ አትመስልም» አለኝ ።

*

«ፊያሜታን ከመሰለች ልጅ ጋር ተኝቶ ማን ዓይኑን ሊከድን ይችላል?» አልኩትና ቀጥዬ ፥ «በነገራችን ላይ ፥ ሥዕላይ በራሂ ያን ምሽት ከእሷ ጋር አላደረም ። ታዲያ የት አደረ ብለህ አትጠይቀኝ ። እሷም ሆነች እኔ አናውቅም» ብዬ ነገርኩት ።

ፈገግ ብሎ ፣ «አየህ አይደለም?» አለኝ
«ምኑን?»
«የቅርብ ግንኙነት ለመረጃ ጠቃሚ መሆኑን?» አለኝ ።
«ማን ጉዳት እንዲደርስባት አልፈልግም» አልኩት ።
«አትስጋ ። እንግሊዞች እንደሚሉት ወርቅ ዕንቁላል የም ትጥል ዶሮ አትገደልም ። ለመረጃው አመሰግናለሁ ። ቀጥል ንድ ። ወደምንፈልገው ቦታ ታመራን ይሆናል ። ግን ፍቅር እውር እንዳያደርግህ እሰጋለሁ» ብሎኝ ሔደ ።

ወደ ፊያሜታ ተመለስኩና ፣ የብርቱካን ጭማቂ ስላል ነበረ ቀዝቃዛ ፋንታ አዘዝኩ ።

«ቪያ! እሱ መጠጥ አስካሮኛ ነው !» አለች ። እያንገ ፈገፋት ፣ እያንገሸገሻት ።
«ከፋንታ ምን ጥል አለሽ?» አልኳት ።
«አስካሮኛ ነው» አለች ጠጉሯን እየነስነሰች ። ስትናገር አንገቷን መነቅነቅ ይቀናታል ። ጠጉሯም አብሮ ይነሰነሳል ።
«ለምን?» አልኳት ።
«ባንድ ቀን ቀጠሮ ፣ ባንድ ፋንታ ግብዣ ነው ክብርናዬን ያጣሁት ። ስካሮኛ!» አለች ።
አሳቀችኝ ።
«ለዚያውም አልጨረስኩትም ፣ አባቴ ይሙት ። ግማሽ ላይ ነበር የተውኩት.....»
እንደገና ሳቅሁና ፣ «አሺ፣ባባትሽ ታሪኩን በሙሉ ንገሪኝ» ብዬ ለመንኳት ።

ፋንታ ጠልታ የቀረችበትን ምክንያት ጭንቅላቷን እየነቀ ነቀችና ጠጉሯን እየነሰነሰች ከሥሩ ጀምራ አጫወተችኝ ። ታሪኩ እንዲህ ነበር ።

አንድ በጣም የምትወደው ሰው ነበራት ። የተማረ ፣ ሀብ ታም ፣ መልከ መልካም ወጣት ነበር ። ዶክተር አቤል ይባላል ። ከመላላም ሌላ ፍቅር አታውቅም ። እና ደግሞ የልብ ጓደኛዋ የሆነች አንዲት ልጅ ነበረች ። ልጅቷ ፣ በዕድሜም ሆነ በአስ ተሳሰብ የበሰለች ፣ ሁልጊዜ «ነገር አለዎ» እያለች ፣ ዘወትር

መፋቂያ የማይለያቸውን ውብ ፣ ድንቅ ጥርሶቿን ወንድ ላይ ብልጭ ድል በማድረግ በወንድ ስሜት የምትጫወት ፣ ካንድ መኪና ወርዳ ወደ ሌላ የምትገባ በቀን ፍቅረኛዋ መኪና ከሌት ፍቅረኛዋ ቤት የምትደርስ ። ፈገግ ብላ «ነገር አለዎ» ከማለት በቀር ፣ ከፉም ሆነ ደግ የማትናገር ፣ እሳት ልላ የምታስልስ ነበረች።ሰሚራ ትባላለች።ፊያሜታ ዶክተር አቤል ቤት የምትሔደው ከሰሚራ ጋር ነበር — ሁልጊዜ ሰሚራና አቤል አንቺ'ኮ አታውቂም እንጂ እኛ የሥጋ ዝምድና አለን እያሉ ያወሯታል ። ከጊዜ በኋላ የፊያሜታ ጆሮ ጉድ ይሰማል ። ሰሚራና አቤል አብረው መውጣት ጀምረዋል የሚል ወሬ ይደርሳታል ። ለጊዜው አታምንበትም ። ወሬው ስለተደጋገመባት ፣ ከዚያ በፊት ብቻዋን ወንድ ቤት ገብታ የማታውቀው ልጅ ተነስታ ዶክተር አቤል ቤት ትሔዳለች ። ቀኑ አይረባትም ። ቅዳሜ ነበር ። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ...... ሰሚራና አቤል ፍቅር አድከሟቸው ፣ ተቃቅፈው ተኝተው ታገኛቻቸዋለች...... እንባዋን እየዘራች በመጣችበት እግሯ ወደቤቷ ተመልሳ ከመሮጥ በስተቀር የምታደርገው ነገር አልነበራትም ። ጊዜ ያልፋል ። ሰሚራና አቤል ይሰያያሉ ። ፊያሜታ ትታጫለችና ሠርጉ በጥር ወር እንዲሆን ተቆረጠ ። ቀኑም እየተቃረበ ሔደ ። በርበሬም ይቀነጠስ ጀመር ። ገዚምም ተዘጋጀ ። አንድ ቀን እንዳጋጣሚ ሰሚራ መታጨቷን ካንድ ጓደኛዋ ትሰማለች ። እንዲጋጣሚ ሆኖ የሰሚራን እጮኛ ታውቀው ነበር ። ከዚያ በፊት ፣ ካንድም ሁለት ጊዜ እንውጣ ብሎ ለምኗት እምቢ ያለችው ልጅ ነበር ። አፈወርቂ ይባላል ። የስልክ ቁጥሩንም ይዛ ነበር ። ስልክ አንስታ ትደውልለታለች ። ሰማታ ይቃጠራሉ ። ቤቱ ወስዶ ፋንታ ይጋብዛታል ። ያኔ ፣ ፋንታ አዲስ የመጣ ለስላሳ መጠጥ እንደመሆኑ ብርቅ ነበር ። የተጋበዘችውን ፋንታ ጠጥታ ሳትጨርስ የሆነው ሆነ ። በስንት መከራ ከብዙ የመንገድ ሌቦች ጠብቃ ያቆየቻትን ብርቅዬና ውድ ክብርናዋን አጣች ። «በግማሽ ጠርሙስ ፋንታ ሼጥኳት አባቱ ይሙት» ስትል በጣም አስቃኝ ነበር ። ከጊዜ በኋላ አረገዘች ። እናቷ ያረገዘች መሆኗን ያውቁባታል ። እሷማ ፣ እህል በሽተታት ቁጥር ፣ ልቧ እስኪጠፋ ድረስ ቋቅ ሲያሰኛት ፣ ኮሌራ የያዛት መስሏት ነበር ። ቃሪያና አዋዜ ብቻ ነበር የሚያምራት ። እናትና አባቷ በዕድላቸው ከማዘን ሌላ የሚያደርጉት ነገር አልነበረም ። የሆነ ሆኗል ። ምን ሊያደርጉ ይችላሉ ። እና ደግሞ ያለ እሷ ሌላ ሴት ልጅ የላቸውም።የቤተሰቧ ዓይን ማረፊያ

ጌጥ ነበረች ። ወንድሞቿ ሲገድሏት ተነስተው ነበር ። እናትና አባት አናስነካትም በማለት ከጎኗ ቆሙ ። እንዳጋጣሚ እናትና አባቷም የተገናኙት አሁን ልጃቸው ላይ በደረሰው ሁኔታ ነበር ። ፊያሜታና አፈውርቂ እንዲጋቡ ከማድረግ ሌላ ምርጫ አልነበረም ። ቃል ኪዳን ፈርሶ ፊያሜታና አፈወርቂ ተጋቡ ። ጋብቻው አልሠመረም ። ጽንሱ አስወረዳት ። በተጋቡ በሰባት ወራቸው ተፋቱ ።

«እውይ አባቴ ይሙት ፣ እልከ ይገድለኛል'ኮ ። ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ ?» አለች በመጨረሻ ።

«ጣፋጭ እልከኛ!» አልኳት ።

«ምን ዓይነት ሴት ነኝ?» ባለችኝ ቁጥር ፣ ለምን እንደሆነ እንጃ ፡ «ጣፋጭ ነሽ» ማለት ይቀናኛል ። እና ደግሞ ጣፋጭ ናት ። ጨው ያላት ልጅ ናት ።

«ሙት ፣ እልከኛ ነኝ ። አባቴ ይሙት ። ወንድ ፣ ቀንድ አስበቅላለሁ......»

«ምን እያደረግሽ?»

«ታየኛለህ ......»

«እናያለና.....»

«ደሞ ከአንድ ወንድ ጋር ብዙ ጊዜ መቆየት አልችልም ። ሳየው ጥለሺው ብረሪ ብረሪ ይለኛል ።»

«ስለሱ አትስጊ ። ግፋ ቢል የሦስት ወር ፍቅረኞች ነው የምንሆነው ። ከዚያ ፈትለክ ነው» አልኳት ።

እና ተነስተን ወደ አሥመራ ተፈተለክን ። ከምጽዋ ወደ አሥመራ ጉዞ ሰማዩን ለመግጨት ሽቅብ እንደመብረር ነው ። ደግነቱ ከፍ እያሉ በሔዱ ቁጥር ሰማዩም ወደ ላይ ይሸሻል ። አሥመራ ደረስን ። ከተማው ጭር ብሏል ። ሰው ሁሉ ከተማውን ጥሎ ወደ ምጽዋ የኮበለለ ይመስላል ። በፊያሜታ መሪነት በቀጥታ ወደ ማይተመናይ አመራን ። የማይተመናይ ሠፈር ቤቶች በቁጠባ ዘዴ በፕላን የተሠሩና እንደ ሰንሰለት የተያያዙ ቤቶች ናቸው ። አሠራራቸውን ሲመለከቱ ፣ ሠፈሩ የአረቦች መንደር መስሎ ይታያል ። ግን ፣ ሠፈሩ ከዳር እስከ ዳር የሐማሴኖች ሠፈር ነው ሲባል ሰምቻለሁ ። ቀይ ኮከብ ዘማቾች ሠፈሩን ከሩቅ ይፈሩታል ። ቤቷ አጠገብ ስንደርስ ልቅሶ ሰማን ።

«ኡውይ ! ወይኔን ግዲ ! » አለች ራሷን ይዛ ።
ደንግጬ ፥ «ምነው፣ ምን ሆንሽ ! » አልኳት ።
«እናቴ ትሆንን፣ ምን ይሻለኛል ጸጋዬ፣ አባቴ ይሙት እኔ ከዚህ መኪና አልወርድም» አለች ።
«ታመው ነበር ?»
«አዎ ፥ ልቤን ስትል ነበር......»

ከመኪናዬ ወርጄ አንዱን የመንደር ጎረምሳ በመጥራት ሁኔታውን አጣራሁና ተመልሼ ፥ «እባክሽ አቦ ፥ አታሟርች ባቸው ። እናትሽ ደህና ናቸው ። አቦይ ተኽሉ የሚባሉ ሰው ናቸው የሞቱት» አልኳት ።

«እውይ አቦይ ተኽሉ ! » አለች

የባለጌ መርዶ ነጋሪ ሆኘ ተሰማኝ ። ምን አውቄ ፥ አያቷ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም አጎቷ ። የትግሬ ዝምድና እንደ ሰንሰለት የተቆላለፈ ነው ይባላል ። ዓይኖቿ እንባ ቋጥረው ነበር ። ሰምን እንደሆነ እንጃ የሰማሁት አንድ ቀልድ ትዝ አለኝ ። አንዱ ጥሬ መንዜ ሌላውን አፋፍ ላይ ቆሞ ይጠራውና ፥ እናትህ ሞታ ለች ፡ ጧት መጥቼ ስለማረዳህ ከቤት እንዳትጠፋ ይለዋል ። ሰውዬው እዬዬውን ማቅለጥ ሲጀምር ፥ እሳ ፥ የማን ሞኝ ነህ፣ አሁን ማን አረዳኝ ብለህ ነው የምታለቅሰው፣ ብሎት ይሔዳል ። አልሳቅሁም ። «ሰውዬውን ታውቂያቸው ኖሮአል፣ አዝናለሁ» አልኳት ።

«አቦይ ተኽሉን፣ ከሕጻንነቴ ጀምሮ ነው የማውቃቸው ። በሕጻንነቴ ሁልጊዜ ከረሜላ ይዘውልኝ ይመጡ ነበር ። በጣም ይወዱኝ ነበር ። አሁንም በታመሙ ቁጥር እኔን ነበር የሚያስጠሩኝ ። ዕድሜ ልካቸውን የፓራዲዞ ቡና ቤት ባሬስታ ነበሩ» ብላ እንባዋን ለቀቀችው ።

፮

ሰዚያን ቀን ምሽት አድርገነው የነበረውን ቀጠሮ በአቦይ ተኽሉ ሞት ምክንያት ለሌላ ጊዜ አስተላልፈን ተለያየን ። ሙታ ንም የድርሻቸውን ማግኘት አለባቸው ። ቀኑ ሳይታወቀኝ አለፈ ። ዝም ብሎ እንደ ሚግ 23 ተዋጊ አይሮፕላን ይበራል ። ከውጭ ስለታዘዙት መሣሪያዎችና ፊልሞች ጉዳይ ምንም አስደሳች

ዜና አልሰማሁም ። ገና አልደረሱም የሚል መጥፎ ዜና ነበር የደረሰኝ ። ከማን ጋር ልጣላ! እግዜሩም የድሮ እግዜር አይደለም መሰለኝ ሊሰማኝ አልቻለም ። ምናልባት እሱም አርጅቶ ይሆናል ። ከአሥመራ አብዮት አደባባይ፣ ወደ ሳባ ስታዲዮም ፣ ከሳባ ስታዲዮም ፣ ወደ አሥመራ ራዲዮ ስቱዲዮ ፣ ከስቱዲዮ ወደ ትንሣኤ አዳራሽ መሮጥ ነበረብኝ ። ሌላ የት ቦታ እንደደረስኩ እግዜር ነው የሚያውቀው ። ለመኖር መሮጥ ያስፈልጋል ። እና እንደ እብድ ስሮጥ ነበር የዋልኩት ። ሌቱም እንደ ቀኑ ፣ እንደ በጋ ጥላ በርሮ አለፈ ። ቀይ ኮከብ ዘመቻ የጊዜን ስልት የቀየረ ይመስላል ። ሕልም አልባ የሆነ ሌት ነበር ። አንዴም ጎኔ የተገላበጠ አይመስለኝም ። እንደ ወደቀ ዛፍ ባንድ ጎኔ ተጋድሜ ነበር ያደርኩት ።

የኤርትራ ክፍለ ሀገር ቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ጉባኤ አባሎች ከምሽዋ ፌስቲቫል ተመልሰው መደበኛ ስብሰባቸውን በትንሣኤ አዳራሽ ቀጥለዋል ። ጉባኤው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ጧት በማለዳ የዘርዓይ ድረስ መታሰቢያ ሐውልት መሠረተ ድንጋይ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተጥሎ ነበር ። አንዱ ተናጋሪ በሌላ እግር እየተተካ ንግግር በንግግር ሆነ ። አዳራሹ ጭብጨባ በጭብጨባ ሆኖ ተናጋ ። በብዙ ሺ ሜትር የሚቆጠሩ ፊልሞች ዞሩ ፣ ተሽከረከሩ ። ካሜራዎች ጋሉ ነደዱ ። ከትንሣኤ አዳራሽ ጋር በቀጥታ የተያያዘው የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ድምጽ ራዲዮ የጉባዔውን ሂደት በመላ ኢትዮጵያ አስተጋባ ፣ ሔደ ፣ ነጎደ ፣ ወንዝና ጅረቱን ፣ ዳገት ቁልቁለቱን ፣ ሜዳ ተራራውን እየተሻገረ ። የጋዜጠኞች ብዕር ፈሰሰ ። የሬዲዮና የቴሌቪዥን ተናጋሪዎች ትናጋ ተንበለበለች ፣ ነደደች ፣ ደረቀች ። ዛለ ወገብ፣ ጀሮ ግንድ ተቃጠለ ። ከዳ ጉልበት ፣ አእምሮ ጋለ ፣ ደነዘ ። አንዳንዱም በእንቅልፍ ተንገላጀጀ ፣ ሽለብታ ፣ ኩርፊያ እስኪቃጣው ድረስ ። ያን ቀን ሐያ ተናጋሪዎች ብቻ ነበሩ ንግግር ያደረጉት ። አርባ ዘጠኝ ይቀራሉ ። አርባ ዘጠኝ ንግግሮች በሁለት ቀን ውስጥ ጆሮ ምንኛ ይደንቀው! ብርታቱን ይስጠን ብቻ ። በዚሁ ሁኔታ የታሪክ ጎማ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ሲሽከረከር ቆየ ። በጉባዔው ሂደት ጣልቃ «ኢትዮጵያ ወይም ሞት» የሚል ዓርማ አንግበው ለአንድነት ለታገሉና መስዋእት ለሆኑ የኤርትራ አርበኞችና ፣ «አብዮታዊት ኢትዮጵያ ወይም ሞት» በማለት ለአንድነትና ለአብዮቱ ሲታገሉ ለወደቁት የአብዮታዊ ጦር አባሎች

መቃሰቢያ ሐውልቶች የመሠረት ድንጋይ ተጥለው ነበር ። ጥር 23 ቀን 1974 ታሪካዊው የአሥመራ ማኒፌስቶ ወጣ ። ታላቅ ቀን ነበር ።

የወጣው ባለ ሰባት ነጥብ ማኒፌስቶ ፤

1ኛ/ አርቆ አስተዋዩና ቆራጡ አብዮታዊ መሪያችን ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና የኢሠፓአኮ ሊቀ መንበር የአብዮታዊው ጦር ጠቅላይ አዛዥ ፣ ጥር 17 ቀን 1974 በአሥመራ ከተማ በተሰበሰበው የቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ ጉባዔ ላይ የዓለም አቀፍ፡የአካባቢያችንና የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በተለይም የኤርትራን ክፍለ ሀገር ችግር በማስመልከት ለመላ የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ ላደረጉት ታሪካዊ ንግግር በአንድ ድምጽ ሙሉ ድጋፋችንን እየሰጠን በወንበዴዎች የወደመውን የኤርትራ ክፍለ ሀገር ኢኮኖሚ በቀይ ኮከብ ሁለገብ አብዮታዊ ዘመቻ መልሶ ለማቋቋምና ሕዝቡንም ነጻ ለማውጣት የሰጡትን አብዮታዊ መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግና ወደፊትም አብዮታዊው መንግሥት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚነድፋቸውን የሥራ ዕቅዶች ሁሉ ለመፈጸም በግንባር ቀደምትነት ተሰልፈን አስፈላጊውን መስዋዕትነት እስከ ሕይወት ድረስ ለመክፈል ዝግጁ መሆናችንን በአንድነት ቃል እንገባለን ።

2ኛ/ ከኀብረተሰቡ የተተፉ ኢምፔሪያሊዝምንና የአድኀሮት ኃይላትን በስተቀር ማንንም የማይወክሉ ጸረ ነጻነት ፣ ጸረ አንድነት ፣ ጸረ ሕዝብና ጸረ ሠላም የሆኑት የወንበዴ ቡድኖች የጥፋት መልዕክታቸው ከእንግዲህ ወዲያ መቀጠል ስለሌለበት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በሰፊው ሕዝብ ክንድ መደምሰስ አለባቸው ። በተጨማሪም ለእነዚህ ወንበዴዎች ድጋፍ የሚሰጡ የውስጥ ተባባሪዎቻቸው ጭምር የሰፊው ሕዝብ ጠላቶች ስለሆኑ እነሱንም በተባበረ ክንዳችን የምንደመስሳቸው መሆኑን እናረጋግጣለን ። በዚህም መሠረት አብዮታዊ ሠራዊታችን በሚያካሂደው የመከላከል ውጊያ የሚወስደውን ማናቸውንም እርምጃ ሁሉ ከመደገፍም ባሻገር በቆራጥነት ከጐኑ የቆምንና በደጀንነትም የተሰለፍን መሆኑን በሙሉ ቃል እናረጋግጣለን ።

3ኛ/ በወንበዴው ተቋም ውስጥ ሳያውቁ በስህተት ሳይወዱ በግድ በጥፋቱ ዓላማ በቀጥታ የተሰለፉ የጭቁኑ ሕዝብ ወገኖችና በውጭ አገር የሚንገላቱ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ሁሉ በሕዝብ ደም የሚነግዱትን የለየላቸውን ወንበዴዎች ታግለው አብዮታዊ መንግሥት ያደረገላቸውን ሙሉ ምኅረት ተቀብለው ወደ እናት አገራቸው በአስቸኳይ እንዲመለሱና ከሕዝቡም ጎን እንዲሰለፉ ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ጥሪውን ያስተላልፋል ፡፡

4ኛ/ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የሚገነባውን የሶሻሊስት ኢኮኖሚና በተለይም በአሁኑ የክፍለ ሀገሩ እንገብጋቢ ችግር እንጸር ኅብረተሰቡ ዳግመኛ በእንዲህ ያለ ውጥረት ውስጥ እንዳይወድቅ ዋስትናው መደራጀት እንደመሆኑ በአብዮታዊው መሪያችን በጓድ ሊቀ መንበር መመሪያ መሠረት ገበሬው በወጣለት ፕሮግራም በአስቸኳይ በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲደራጅ ጥሪ እያቀረብን አስፈላጊውንም እርዳታ ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጣለን ፡፡

5ኛ/ የኢትዮጵያ ሕዝብ የለየላቸው ጠላቶች በጸረ ነጻነት ፣ በጸረ አንድነትና በጸረ ሠላም አቋማቸው በጭቁን ደም የሚነግዱትን ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች የሚረዱትን የውጭ ኃይሎችና የስለላ ድርጅቶች ሁሉ በብርቱ እናወግዛለን ፡፡ ድጋፋቸውንም እንዲያቆሙ እናስጠነቅቃለን ፡፡

6ኛ/ ለብዙ ሺ ዘመን ጸንቶ የቆየውን የተከበረ የኢትዮጵያ ታሪክ በመበከል በቅኝ ገዢዎችና በኢምፔሪያሊስቶች ተጽዕኖ የተስፋፋውን የባዕድ ገናናነትና የባሕል ቅሪት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጫኑ መሆኑን በመገንዘብ ፣ በአሁኑ ጊዜ አብዮታዊ መንግሥት የኢትዮጵያን የነጻነትና የትግል ታሪክ በጥልቀት ገምግሞ የወደቀው የፊውዶ ቡርዧዋ ሥርዓት አፍኖ ይዞት የነበረውን ታሪክ በማደስ ለሀገራቸው ነጻነትና አንድነት ለሞቱት ለቀሩትም የኢትዮጵያ ጀግኖች የመታሰቢያ ሐውልት እንዲሠራ ባሳለፈው ውሣኔ መሠረት ፣ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግና የኢሠፓአኮ ሊቀ መንበር

የአብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ፣ በዶ.ጋዓሊ የስመጥር ጀግና የራስ አሉላን ፣ በአሥመራ የዘርዓይ ድረስን «ኢትዮጵያ ወይም ሞት» የሚል አርማ እንግበው ለአንድነት ለታገሉትና መስዋዕት ለሆኑ እንዲሁም «አብዮታዊት ኢትዮጵያ ወይም ሞት» በማለት ለአንድነትና ለአብዮቱ ሲታገሉ ለወደቁት የአብዮታዊ ጦር አባሎች መታሰቢያ የመሠረት ድንጋይ ማስቀመጣቸውን ከልብ እያደነቅን ፣ ለወደፊቱም አብዮታዊ መንግሥት የከፍለ ሀገሩን ታሪክ እያጠና በቅኝ ገዢዎች የተሰጡትን ማናቸውንም ስያሜዎችና የተዘረጋውን የባሕል ወረራና ተጽዕኖ ወደ እውነተኛ ታሪክ በመለወጥ እርምጃ እንዲወስድ እንጠይቃለን ።

7ኛ/ የወቅቱ የመደብ ትግል በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚከሰትበት በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል ካለው ትግል ባሻገር ከቀይ ባሕርና ከመካከለኛው ምሥራቅ የጂኦፖለቲካ አንጻር ሲታይ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ የሚካሄደው የኢምፔሪያሊዝም ሴራ በዚህ ከፍለ ዓለም አካባቢ ያለውን የኃይል ሚዛን ለኢምፔሪያሊዝም እንደሚረዳ አድርጎ ለመለወጥ መሆኑ ግልጽ ነው ። የኢትዮጵያ አብዮት ማሸነፍ የጸረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ድል ማድረግ የኢትዮጵያ አብዮት መሸነፍ የእነዚህ ኃይሎች ድል መደረግ በመሆኑ ትግላችን በአካባቢው ብሎም በዓለም አቀፍ ሁኔታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ በከፍተኛ የዓለም አቀፋዊ ኃላፊነት ስሜት እንገነዘባለን ። ይህን በመገንዘብና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የምናደርገው መራራ ትግል የዓለም አቀፍ ጸረ ኢምፔሪያሊስት ትግል አካል በመሆኑ የዓለም ጸረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ቀደም ሲል ከጎናችን እንደ ቆሙት ሁሉ አሁንም የትግል አንድነታቸውን በበለጠ እንዲያድሱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን» የሚል ነበር ።

ማኒፌስቶው የመላ ኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ጥሪና የሙሉ ምኞቱና ብሔራዊ ፈቃዱ ጠንካራ መግለጫ ነበር — የናቅፋ ተራሮች ስሚ ጆሮና አስተዋይ ልብ ካላቸው! ምከረው ፣ ምከረው — እምቢ ካለ መከራ ይምከረው ። ማኒፌስቶው ያንዱ ሥራ ምዕራፍ ማሳረጊያ ፣ የሚቀጥለው ሥራ ምዕራፍ አሐዱ — የፍጻሜ መጀመሪያ ነበር ።

«ቀይ ኮከብ ዘመቻ የትግል አርማችን
ዓለም አቀፍ ይዘት ሶሻሊስት ፈራችን
የልማት ያንድነት ብሩህ ተስፋችን»

«አባባ እማማ ሁላችሁ
እንኳን በደህና መጣችሁ ፣
አቦና አዴና ኩሉ....ም
እንቋዕ ብድሐን መጸኡኩም»

«በእጃችን ይዘን ዘንባባ
ሕጻናት የዛሬ አበባ
ብሩህ ቀናችን ሲጠባ
እንበል ጉሮ ወሸባ....»

«ቀይ ኮከብ ዘመቻ» እና «ሠላም አባባ እማማ» የሚሉ መዝሙሮች አስተጋቡ ። የአበባ ቅንጣቢዎችና የዘንባባ ዝንጣፊዎች ተበተኑ ። እንደ ተለመደው ፊልሞች ፎቶ ግራፎችና የቴፕ ክሮች ይዤ ወደ አርሚ አቪዬሽን በረርኩ ። ምን እንደነካው አላውቅም ፣ ሻለቃ ታደሰ ቀርቾ ፈጽሞ ተሰውጦብኛል ። በሔድኩ ቁጥር ሊያነጋግረኝ ቀርቶ በዓይኑ ሊያየኝም አይፈልግም ነበር ።

«ምንድነው እንዲህ የሚያዘገይህ» ብሎ እንዳሸከሩ ጮኸብኝ ።

ነገሩ ስለባሰብኝ ነው መሰለኝ እኔም አልታገስኩትም —

«ምን ማለትህ ነው! አይሮፕላኑ ለዚህ ሥራ ነው የተመደበው ። ደግሞም'ኮ እኔ ካልፈለኩ ሊንቃነቅ አይችልም ። ካንተ ይልቅ ችኮላ በኔ አይብስም!» አልኩት ።

እሳት የሚተፉ የሠይጣን ቁራጭ ዓይኖቹ ውስጥ ያየሁ መሰለኝ ። ጤና ያለው ሰው መስሎ አልታየኝም ። የመንፈስ ጭንቀት ያደረበት ሰው ይመስላል ። ሥራ በዝቶበት ይሆናል በማለት ተመልሼ አዘንኩለት ። ታምቆ የተያዘን ንዴት ፣ በትንሽ ምክንያት ፣ እርስ በእርሳችን ላይ እንደ በምብ ማፈንዳት መቻም

የተለመደ ነገር ሆኗል ። ወጣቱ መካኒክ ከኛ ፈንጠር ብሎ ቆሞ ይመለከተን ነበር ።

«ሻለቃ! ፈጠን በል እንጂ!» አለው ።
ሻለቃ ታደሰ የበላይ ባለሥልጣን ያዘዘው ይመስል በካርቶን የታሸጉትን ፈልሞች ራሱ ተሸክሞ ሲሔድ ሲል ፣ «ማነው ይህ ሰው?» አልኩት ።

ለጥያቄዬ መልስ ሳይሰጠኝ ፣ «የረሳኸው ነገር አለ?»አለኝ ። በአርሚ አቪዬሽን ግዳጁ እንደ እንበሳ እየተንጎማለለና እያገሳ ምድረ ዓለምን እንደ ልቡ ሲያዝ የነበረው ሰው ፣ አሁን እንዲህ ሲሽቆጠቆጥ በማየቴ የሆነ ነገር ሸተተኝ ።

«ካልክስ አለ» አልኩት ።
«ምን?» ብሎ አፈጠጠብኝ ።
«ፈ ል ም — »
«የት ነው ያለው!»
«መንገድ ላይ ። እየጠበኩ ነው ። ይቅርታ ፣ ትንሽ መጠበቅ ይኖርብናል» አልኩት ።

ወጣቱ መካኒክ ትእግሥቱን ጨርሶ ነው መሰለኝ ወደ እኛ መጣ ። ረጅም ቁመቱ ድንክ አደረገኝ ።
«ምንድነው የምንጠብቀው !? » አለ ።
ሻለቃ ታደሰ ሁኔታውን አስረዳው ። ወጣቱ ያደረበትን ብስጭት ለመሸሸግ ቢሞክርም አልሆነለትም ።

«ጎድ እንተዋወቅ ጸጋዬ ኃይለማርያም እባላለሁ» አልኩት።
ትንሽ አመነታና ፣ «ዕቁበ ሲላ እባላለሁ» ብሎኝ ፈገግ አለ ። ሠላሳ ጥርሶች ብቻ ያሉት አይመስልም ። ዘጠና ዘጠኝ ጥርሶች ያሉት መሰሎ ታየኝ ።

«ጥድፊያው ምንድነው? አይሮፕላኗ እንደ ሆነች ለኛ ሥራ ብቻ ነው የታዘዘችው አይደለም እንዴ?» አልኩት ።

«ቢሆንም ፣ በጊዜ መሔድና መምጣት አለባት...»
«መካኒክ ነህ — አይደለህም?»

«ነኝ ። ምነው?»

«በትራፊክ ቁጥጥር ሥራ ታዲያ ምን ያገባሀል? ብዬ ነው» አልኩት ።

ሻለቃ ታደሰ ያልበው ጀመር ።

«በማንኛውም ሥራ መተባበር ኃጢአት ነው እንዴ?» ብሎኝ ቀጠለና ፥ «አንዱ አይሮፕላን ከመሄዱ በፊት የሌላውን ጥገና ሥራ ለመጀመር አልችልም ። እና በዚህ ለምን ማንም ጊዜ የለውም» አለኝ ።

እንደሚያታልለኝ ገባኝ ። የሻለቃ ታደሰ ሁኔታ የዕቁባይን ውሸት አጋልጦ ያሳይ ነበር ። ምን እንደሚሠሩ ወይም ምን ለማድረግ እንደተዘጋጁ ባላውቅም ቅሉ ፥ ከዚህ ቀደም ከእጃ ቸው አምልጦ የወደቀው መጣሪያ መጥቶ ፊቴ ድቅን አለ ። የሻለቃ ታደሰ ድንጋጤ ታየኝ ። ኰሎኔል በትሩ ተሰማ ፥ አሥመራ የገባን ለት...... በተለይም ዕድሜው ለጡረታ የደረሰና የገንዘብ ችግር ያለበትን ሰው አሳደው ነው የሚጠቀሙበት...... ሲል የተና ገራቸው ቃላት ከጆሮዬ ላይ ደወሉ።ፍጹም ሊሆን አይችልም፤ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሻለቃ ታደሰን የመሰለ ጀግና ሰው ክብረ ሕሊናውን ለጥቅም አሳልፎ ሊሸጥ አይችልም አልኩ በልቤ ። አሳቤ ልጓም ለቆ እንዳሻው በመጋለቡ ራሴን መልሼ ታዘብኩት ። ስለእነሱ ትቼ ስለራሴ ማሰብ ጀመርኩ ። በገዛ እጄ ከገባሁበት ማጥ የምወጣበት መንገድ ጠፋኝ...... ድንገት አሳብ መጣልኝ ።

«እዚህ አካባቢ ስልክ ይኖር ይሆን?» ብዬ ጠየቅኋቸው ።

«አለ ፥ ምነው?» አለኝ ሻለቃ ታደሰ ።

«ወደኋላ የቀረው ፊልም በቶሎ ይደርስ እንደሆን ለመጠየቅ ነው ። የሚዘገይ ከሆነ አይሮፕላኑ ሊሔድ ይችላል» አልኩት ።

ሻለቃ ታደሰ በእፎይታ ሲተነፍስ አየሁት ። እቁበም ዘና አለ ። ሻለቃ ታደሰ ወደ አየር ኃይል መኰንኖች ክለብ ወሰደኝ ። መኰንኖቹ ምግብ በያይነቱ ቀርቦላቸው ይበሉ ነበር ። ከመብ ረራቸው በፊትና በርረው ከተመለሱም በኋላ መብላት አለባ

ቸው ይባላል ። ከአበላላቸው ጥሩ የምግብ ፍላጐት ያላቸው ይመስላሉ ። ሁሉም የውጊያ ልብስ ለብሰዋል ። ወደ ቢሮዬ ደወልኩ ። ረዛን ነበረች ስልኩን ያነሳችው...... ገና «ሀሎ!» ከማለቴ ፣ «እኔም እፈልገዎት ነበር» አለችኝ ።

«ምነው፣ ምን መጣ?»

«ከውጭ የታዘዙት ካሜራዎችና ፊልሞች መጥተዋል ። አሁን ከአይሮፕላን ማረፊያ ተደውሎልኝ ሰው ልኬአለሁ......»

«እንዲያው ምን ላርግሽ! አልውጥሽ ነገር?»

«ምን አሉ?»

«ማለቴ ፣ መጣሁ ! ሌላስ? » አልኳት በደስታ እየፈነደቅሁ ።

«ጓድ ኰሎኔል በትሩ በጣም ይፈልጉዎት ነበር......»

«መጣሁ...... አሁን»

ስልኩን ዘግቼ ፣ ሻለቃ ታደሰን «ፊልሙ ይዘገያል ። አይሮፕላኑ ይሂድ» አልኩትና ወደ ከተማ በረርኩ ።

ቀይ ኮከብ ዘመቻ የትግል አርማችን የሚለውን መዝሙር በፉጨት እለው ነበር ። ዘምባባዎች ሁሉ ልዩ ውበት ተጎናጽፈው ይታዩኝ ነበር ። የአሥመራ «ሹሩቤዎች» በነፍስ ወከፍ ወጥተው ከመንገዶች ዳር የተሰለፉ ይመስላሉ — ዘምባባዎቹ ። ረዛን ከኰሎኔል በትሩ ተሰማ ጋር በስልክ አገናኘችኝ ።

«ምነው ፈለከኝ?» አልኩት ።

«ስለጀሚንግ ነበር» አለኝ ።

ጠጉሬ ቆመ ። ስለጀሚንግ መሰማት አስጠልቶኛል ።

«ምን ተፈጠረ?» አልኩት ።

«ይሰማል ። አሁን ደግሞ በ41 ሜትር ባንድ ማስተላለፍ ጀምረዋል ። ምንድነው የምትጠቅቁት!»

«ምን ይላሉ?»

«ደርግ ፣ አሁን በያዘው ስድስተኛ ዙር ዘመቻ ሊጨርስህ ተነስቷል ። ስድስተኛው ዙር ዘመቻ ለደርግ ወሳኝ እንደመሆኑ

«ሠርግቸው!»
«የበላይ ውሣኔ ያስፈልጋል.....»

«ውሣኔውን ከምትጠይቅበት ቦታ ጠይቅ ወንድም ። ሥራው ግን መሠራት አለበት ከዛሬ ጀምሮ ። እዚህ ያለው ቴክኒሻን ዝርዝሩን በስልክ ይነግርሀል ። ትራክ ቢ ያሉትንም አንቴናዎች አሻሽሎ የመሥራቱ ጉዳይ ከሁኑ መፋጠን አለበት» በማለት በትእዛዝ ናዳ ጭንቅል ጭንቅላቱን ከመታሁቱ በኋላ ፣ እዚያ ሆናችሁ እዚህ ያለው የእሳት ወላፈን አይሰማችሁም መሰለኝ፣ በናንተ የተነሳ እኔ እዚህ ተጥጄ የምለበለብበት ምክንያት የለም ።

«አዲስ አበባ—አሥመራ ማለትን አሁን ምን አመጣው፣ እዚህም ሆነ እዚያ ሥራው ዞሮ የኛን ኃላፊነት ይጠይቃል» ብዬ አማረርኩ ...........

የወጣውን ታሪካዊ የአሥመራ ማኒፌስቶ በመቀበል ፣ የአሥመራ ኗሪ ሕዝብ በሳባ ስታዲዮም ነገ ስለሚያደርገው የድጋፍ ሠልፍ አስፈላጊውን ቅንብርና ዝግጅት ሳደርግ ውዬ ፣ ምሽት ላይ ከአዲስ አበባ ጃሚንጉ ሥራ ተጀምሮ በጥሩ በመካሔድ ላይ መሆኑ ተነገረኝ ። ቢሮዬ ውስጥ እንደ መድፍ በረድፍ የተደረደሩትን አዳዲስ ባለ 300 ሚሊሜትር ሌንስ ካሜራዎች እንደ አዛዥ መኰንን በዓይኔ ጎበኘሁ ። ለውጊያ ተዘጋጅተናል አልኩ ። ከሞላ ጎደል መጥፎ ቀን አልነበረም ። ሥራ ማንን ገደለ፣ ጭቅጭቁም ቢሆን በከፋት አይደለም ። ከራሴም ሆነ ከሀለም ጋር በሠላም ታረቅሁ ። ውብ ሆና የዋለችው ጸሐይ የበሰለ የጊንዳዕ ብርቱካን መስላ ፣ ተውባ ነበር የጠለቀችው ። ለፊያሜታ ደወልኩላት ። ባለፋት ሦስት ቀኖች አልደወልኩላትም ነበር ። በምን ምክንያት እንደጠፋሁ ለማስረዳት ጥረት አልጠየቀችም ። «ሥራ እንደበዛብህ ማታ ፣ ማታ በቲቪ አያለሁ» በማለት ይቅርታ አደረገችልኝ ። ከምሽቱ ባንድ ሰዓት ኒያላ ሆቴል ፊት ለፊት ለመገናኘት ቀጠሮ አደረግን...... ልክ በቀጠሮአችን ሰዓት በተባለው ቦታ ተገናኘን ። ቀዝቀዝ ያለ ግሩም ምሽት ነበር ። ሙሉ ጨረቃ የብር ሠፌድ መስላ...... ትታያለች ። ከዋክብት ጥቂቱን ሰማይ አጊጠውታል ። ከጉባኤው ላይ የተነሳው ሕዝብ የበዓል ስሜት አድሮበት መንገዱን አጣቦ ይታያል ።

መኪናዬ ላይ ተሳፍራ ጎኔ ሻጥ ካለች በኋላ ፣ ጠጉሯን እየነሰነሰች ፣ «ኢሂ ደአ የሦስት ወር ፍቅረኛ?» አለችኝ ።

አቀማመጡን ታሳምረዋለች ። ፊቷን ወደኔ ዞር ፣ ትከሻዋን ከመኪናው መስተዋት ላይ ደገፍ ፣ ደረቷን ነፋ ፣ እግሮቿን ዘርጋ አድርጋ የእጅ ቦርሳዋን ከኋላ መቀመጫ ላይ ወረወረችውና ቀሚሷን ገለብ አድርጋ ጎንበስ በማለት ሰውነቷን አሸተተች ።

«ምን ማድረግሽ ነው?» አልኳት ተገርሜ ።
«ዓሣ ዓሣ አሸት እንደሆነ ለማወቅ ነው ። ደደብ» አለችኝ
«ጉደኛ ነሽ!»

«ታዲያስ የሦስት ወር ፍቅረኛ!» አለችኝ መልሳ ።
«ማን ያውቃል? ከዚያም በላይ እቆይ ይሆናል» አልኳት ።
«አውይ! እሱማ ሳይታሰም የተፈታ ነው» አለችኝ ።
«እንዴት ?»
«ናቅፋ በሦስት ወር ይያዛል ብለህ ነው? ፍጹም ።»

«ለምን አይያዝም ?» ብዬ ቀጠልኩና ፣ «የመሬቱ አቀማመጥ ያስቸግረን እንደሆነ ነው እንጂ የሻዕቢያ ወኔ አያግደንም ። የናቅፋ መሬት ገዳይ መሬት ነው» አልኳት ።

እሷም ፣ «አቤት ጉራ!» ብላ ቀጠለችና ፣ «አባቴ ይሙት ፣ ይህን አገር የሚያጠፋ ያማራ ጉራና የሐማሴን ውሸት ነው» አለች ።

ነገሯ እያሳቀኝ የመኪናዬን ሞተር አስነሳሁና ፣ «ወዴት እንሂድ?» ብዬ ጠየኳት ።

«ወደ ፈለከበት» አለች ።
«የለም ፣ አንቺ ምረጭ ። አሥመራ ያንቺ ከተማ ናት ። ባንቺ ዓይን ሳያት እፈልጋለሁ ......»

«አትቀልድ ባባትህ..........»
«ቀልዴን አይደለም..........»

«አሁን አንቴ አሥመራን አጣኸውና ነው? ቀይ ኮከቦች ምን የማታውቁት ቦታ አለ? ሁለገብ ናችሁ — አይደላችሁም እንዴ?» አለች ።

«እንዴት ሁለገብ?»

«ዋእ! ከተማውን በቁጥጥራችሁ ሥር አውላችሁታል ። የፍቅር ዘመቻ ! »

«ዘለቄታ ያለውም እሱ ነው የቀይ ኮከብ ዘመቻ ሴቶችንም ያቅፋል» አልኳትና ፥ «እውነት ወዴት እንሂድ?» ብዬ በድጋሚ ጠየኳት ።

«ካራቫል» አለች ።

ካራቫል ከኒያላ ሆቴል ብዙም አይርቅም ። እዚያው አካባቢ ነው፡ማህን ላይ የተጋገረ ትኩስ ላዛኛ ፓስታልፎርኖ በማቅረብ የታወቀ ባር ሬስቶራንት ነው ሲሉ ሰምቻለሁ ። መኪናዬን አዞርኩና ፥ «እውነቱን ነው ። አሥመራን ባንቺ ዓይን ማየት እፈልጋለሁ ። ያንድ ከተማ ውበቱ ፥ የሕንጻዎቹ ታላቅነትና ማማር ፥ ወይም የመንገዶቹ ስፋትና ንጽሕና አይደለም ። በኔ ግምት ፥ ያንድ ከተማ ውበት ፥ ይበልጥ ውብ ወይም መጥፎ የሚያደርጉት በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ናቸው ። ማለቴ ፥ ያለ ሰው ልብ ከተማ ብቻውን ምንም አይደለም ፥ ትርጉም የለውም ። የሕንጻዎች ጫካ ወይም የተጠረቡ ድንጋዮች ክምር ይሆናል — ያለ ሰው ልብ» አልኳትና አንድ ባለቅኔ ስለ አሥመራ ከተማ የገጠመውን ግጥም በቃሌ አነበነብኩላት —

> «ከጎራው ዘልቄ እስኪ ልነጋገር
> ካለሰው ቢወዱት ምን ያደርጋል አገር?
> የኔ ውብ ከተማ —
> ሕንጻ መች ሆነና የድንጋይ ክምር ፤
> የኔ ውብ ከተማ—
> መንገድ መች ሆነና የድንጋይ አጥር ፤
> የኔ ውብ ከተማ የኔ ውብ አገር
> የሰው ልጅ ልብ ነው
> የሌለው ዳርቻ የሌለው ድንበር ።

ሕንጻው ምን ቢረዝም ፥ ምን ቢጸዳ ቤቱ፡
መንገዱ ቢሰፋ ቢንጣለል አስፋልቱ፡
ሰው ሰው ካልሸተተ ምንድነው ውበቱ?
እኔ ውብ የምለው
የሰውን ልብ ነው ።
ምን ቢነድ ከተማው ተንቦግቡጎ ቢጠና
ቢሞላ መንገዱ በሺ ብርሀን ኩሬ
በሺ ብርሀን ጎርፍ ፥
ምን ያደርጋል?
ምን ያሳያል?
ካለሰው ልብ ብርሀን

ያ ዘላለማዊ ነበልባል ያ የተሰፋ ፍማ
ጨለማ ነው
ሁሉም ጨለማ ።
ሙሽ?
ሱ!»

«ለምን ደራሲ አትሆንም? አባቴ ይሙት» አለችኝ ።

«በምን ዕድሌ! ደራሲ ለመሆን ደምና ላብ ይጠይቃል ይላሉ ። እያንዳንዱ ሰው በልቡ ውስጥ አንድ መጽሐፍ አለው ። ግን ብዙዎቻችን አንጽፈውም ። ይዘነው እንሞታለን ። ደራሲ የሚሆኑት ልዩ ፍጡሮች ናቸው ። የሰው ልጅ ተማሪዎች ናቸው» ስላት —

«የሐማሴን ልብ በቀላሉ አይገኝም» አለችኝ ። ነገሩን ቦር አድርጋ ።

«ለምን አይገኝም? ተገቢው ቦታ ላይ ከተነካ የማንም ልብ ይገኛል አይመስልሽም?» አልኳት ።

«ብራቮ ቀይ ኮከብ!» ብላ ለጠቀችና ፥ «ሆዱን ብትነኩት ይሻላል ። የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል ትሉ የለም? ሆድ ካልሞላ ልብ አይገኝም ። ያጣነው ጤፍ ነው እንጂ ነገር አይደለም፥ ወሬ ሞልቷል» አለች ።

ካራቫል ሬስቶራንት ደጅ ብዙ መኪናዎች ተኮልኩለ ዋል ። ከመኪና ሳይወጡ ምግብና መጠጥ ታዞ የሚመጣበት ቦታ ነው ። መኪናዬን አስተካክዬ አቆምኩና ፣ «ታዲያስ ፋንታ ይምጣልሽ?» አልኳት ።

«ሺያ ! » አለች ።

የሚበሳ ነገር አልፈለገችም ። ለእሷ ቢራና ስፕራይት ፣ ለኔ ውስኪ አዘዝን ። አስተናጋጆቹ እንደ አዲስ አበባዎቹ ትእግሥት አያስጨርሱም ። ፈጣኖች ናቸው ። አሥመራ ፣ የቡና ቤት አያያ ዝና መስተንግዶ እንደ ኪነት ነው ። በተሰማራበት ሥራ ሁሉ ተደሳችና ታታሪ ነው ። ሥራ ክቡር ነው ። ሥልጣን ይከበራል ። የአሠራር ቅልጥፍናው ያስደስታል ። በሥራ ልማመት የለም ። አሠራሩ ሁሉ ሥርዓት ያለው ይመስላል ። ችግሩ ፣ የቢሮክራሲ ደንብና ሥነ ሥርዓት ትንሽ ዝንፍ ካለች ንቅንቅ የለችም ።

ውስኪዬን ቀመስኩና ፣ «በእውነት ዛሬ ቆንጆተሻል» አልኳት ።

የነጭ ሸሮ መልክ ያለው ባለጥልፍ «እጥርጥር» ቀሚስ ከነጠላው ጋር ለብሳ ነበር ።

«አለባበሴ?» አለች ።
«አዎ ፣ ውብ ነው ። ያምርብሻል» አልኳት ።

«ያሥመራ ሴቶች አሁን ኢሠፓአኮ ከመጣ ወዲህ ነው'ኮ መልበስና ማጌጥ ፣ ከተማ መውጣት የጀመርነው» አለች ።

«በፊትስ?»
«እውይ! የቷ ሴት አጊጣ ትወጣ ነበር?»
«ለምን?»

«ከመንገድ እንታፈስ ወዶ እንበሳ ሆቴል? ዓይን እንዳን ስብ ሸበጥ አድርገንና ጋቢ ደርበን ነበር የምንወጣው ። እውይ! ከ1967 እስከ 1971 ድረስ ያሳለፍነውን ጊዜ ሳስታውሰው መጥፎ ቅዠት ይመስለኛል» አለች ።

ትዝታው እንደ እሬት እንገፈገፋት ። ቀጠለችና ፡ «አባቴ ይሙት ፣ አሁን ምን አሳብ አለብን ? ኢሥፓአኮ ከመጣ ወዲህ በጉልበት የሚደፍረን የለም ። እንደልባችን ለብሰንና አጊጠን እንወጣለን — በሥነ ሥርዓት ። ሴቶች መልበስ ፡ ማጌጥና መውጣት ሲጀምሩ የሠላም ምልክት መሆኑን ታውቃለህ? ወይስ አታውቅም?» አለች ።

«አውቃለሁ ። ወደፊትማ ምኑ ቅጡ!» አልኳት ።

«አሮማይ ፡ ቀይ ኮከብ ከመጣ ወዲህ? ሆ ሽቶው በየመንገዱ ከሩቅ ይጣራል» አለች ።

«ጥሩ ነው ። ይህንን ነው የምንፈልገው ። ሴቱም ወንዱም ፣ ፍርሀት ሳይሆን ኩራት እየተሰማው ቀና ብሎ እንዲሔድ፡ በራሱ ላይ እምነት እንዲኖረው — ባለመብት መሆኑን እንዲያውቅ ። እነዚህ ጥቃቅን ሰብአዊ ነገሮች በጣም አስፈላጊ ናቸው ። በኢትዮጵያዊነታችን ሁላችንም እኩል የምንኮራበት ሁኔታ መፈጠር አለበት ። የቀይ ኮከብ ዘመቻ ዓላማ ከዚህ የተለየ አይደለም » በማለት ንግግር ብጤ አደረኩላት ።

«የ ጊዜ ተመልሶ እንደማይመጣ ተስፋ አለኝ» አለች ።

«እኔም» አልኳት ።

«ተመልሶ ቢመጣ ግን ቪያ! ቪያ ካሚሌ» አለች ።

«በፊት ከመኮብለል ምን አስቀረሽ?»

«እንጃ! አባቴ ይሙት ፡ ቤት ገብቼ ያለአሳብ አደይ እንጀራ ሀብኒ ማለት ለምጄ ይሆናል ። ከጓደኞቼ መሐል እዚህ የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ ። አባቴ ይሙት ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ? ግን እውነቱን ልንገርህ ። እኔ ካገሬ አልሰደድድም ። ያረብ ገረድ ሆኘ ከምኖር ብሞት ይሻለኛል» አለች ።

«የታማኝ ዜጋ ሚዳይ ይገባሻል ፡ ፊዮሚታ ሙች፡» አልኳት በቀልድ ።

«ጂዳና አቡ ዳቢ ያሚረካን ብር ሞልቶ..... ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ?»

«ጣፋጭና ኩሩ»

እኔ ውስኪ ደገምኩ ። እሷ እምቢ አለች ። ሌላ ቡታም ለመ ሔድ አልፈለገችም ። ዝም ብላ ጥርሷን መፋቅ ጀመረች ። መፋቂያ ከእጅዋ አይጠፋም ፣ ከጥርሷ አይለይም ። ጥርስ አፋ ፋቿ ኪነታዊ ነው ። መፋቂያ ያስተከዘኛል ትላለች ። ጥርሷን ስት ፍቅ ቆየችና ድንገት ፣ «ኤሎሚኖህ ምን ዓይነት የልብስ ቀለም ነው የምትወደው?» ብላ ጠየቀችኝ ።

ጥያቄዋ ፣ አንድ ልጠይቃት ፈልጌ የረሳሁትን ነገር አስታ ወሰኝ ። ሆኖም ፣ «ምን ያደርግልሻል?» አልኳት ።

«ለማወቅ እፈልጋለሁ ። ንገረኝ ፣ ባባትህ.....»

«አረንጓዴና ጥቁር ቀለም ይመስለኛል» አልኳት ።

«አባቴ ይሙት ፣ ሁለተኛ አረንጓዴና ጥቁር ቀለም ያለው ልብስ አልለብስም ___»

«አትማይ» አልኳት ።

ቀጠለችና ፣ «ምን ዓይነት ሽቶ ነው የምትቀባው?» ብላ ጠየቀችኝ ።

«ሻኔል ፋይቭ....»

«ሁለተኛ ሻኔል አልቀባም አባቴ ይሙት ። ወይስ ልቀባ ልህ?»

«በፈጠረሽ እንዲህ ያለውን ጥያቄ ተይኝ» አልኳት ።

«ምነው ትዝ አለችህ? አይዞህ ፣ ትሔድላታለህ ። ከሦስት ወር በኋላ ፣ እሺ?»

የቀልድ አነጋገር አልነበረም ። ድምጿ ኃዘኔታ ያዘለ ነበር ። የብር ስፌድ የመሰለችው ሙሉ ጨረቃ ከዘምባባዎች ዛፍ መካከል ብቅ ብላ ትታያለች ፣ የዘምባባዎቹን እናት ለመሳም ዝቅ ያለች ትመስላለች ።

«ፈያሜታ ፣ አንድ ነገር ልጠይቅሽ» አልኳት ።

«ምን?» አለች ጥርሷን መፋቅ ትታ ።

«ባንቺና በኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይ መካከል ምን አለ?» ብዬ ጠየኳት ።

ኰሎኔል ታሪኩ ወደ አፍአበት ሔዷል ። ወደ አፍአበት የሚሔድ አይሮፕላን ሲጠብቅ እንዳጋጣሚ አግኝቼው ነበር ።

ጠጉሩ ከበፊቱ ቢያንስ ሦስት ኢንች አድጓል ። «ከመሔድህ በፊት ምናለ ብትቆረጠው? » ብየው ነበር ። ጉልበቱ እንደ ሳምሶን ጠጉሩ ላይ ያለ ይመስል መቆስ ሳያስነካው ይኖራል ። «ከድል በኋላ» አለኝ በቀዘቀዘ ድምጽና ስሜት ። ሊያየኝም የፈለገ አይመስልም ። ለምን እንደተሰወጠብኝ ለጊዜው አልገባኝም ። ከተለያየን በኋላ ነበር ያን ምሽት ፣ ከፈያሚታ ጋር በዓይን የተለዋወጡት ጥላቻ ይሁን ወይም ፍቅር ትዝ ያለኝ ። እና ፣ ፈያሚታን ልጠይቃት እየፈለኩ በመርሳት እስካሁን ሳል ጠይቃት ቆየሁ ።

«ምንም» አለችኝ ሳታመነታ ። ወዲያውኑ ቀጠለችና ፣ «ግን ለምን ጠየከኝ?» ብላ ጥያቄውን ወደኔው መለሰችው ።

«ጓድ ስለሞን በትሩ ቤት ያሳለፍነው ምሽት ትዝ ይልሻል?»

«አወ ፣ በሥነ ሥርዓት ፣ ለምን ትዝ እንደሚለኝ ታውቃለህ?»

«ለምንድነው?»

«አንቴን ያገኘሁህ በዚያን ምሽት በመሆኑ ነው....»

«ወይስ እኔ ነኝ ያገኘሁሽ?» በማለት የልብ ኩራቷን አጠናከርኩላትና ፣ ወደ መጀመሪያ ጥያቄኘ ልመለስና ፣ ያን ምሽት አንቺና ኩሎኔል ታሪኩ ድንገት ፊት ለፊት ስትገናኙ በዓይን የተለዋወጣችሁት ነገር ፍቅር ይሁን ወይም ጥላቻ ፣ የቱ እንደሆነ ስላልገባኝ ነው» አልኳት ።

ሴቶችን በሚመለከት ሁለት መርሆች አለኝ ። አንደኛ ፣ አብሬ የምወጣቸውን ሴቶች የሕይወት ታሪክ ማወቅ እፈልጋለሁ ። ሳላውቅ ከቀረሁ ሆዴን ያመኛል ። የአዲስ አበባ ሴቶች ሆዴን እንዳሳመሙኝ አሉ ። ዝግ ናቸው ። ሁሉንም ነገር በሆዳቸው ስለሚይዙ ምስጢራዊነታቸው ያናድደኛል ። ሁለተኛ ፣ ሴቶች ፈልገውኝ ቢመጡም ፣ እኔ ፈልጌ እንዳመጣኋቸው አድርጌ ነው የምይዛቸው ። ሴት ልጅ ከኔ ጋር ሆና ኩራትና ክብር እንዲሰማት እፈልጋለሁ ። ሴት ልጅ በፍቅር ቀርቶ በጥልም ቢሆን መከበር አለባት የሚል ጽኑ እምነት አለኝ ። ግን ለፈያሚታ ያቀረብኩላት ጥያቄ ከነዚህ ሁለት መሠረታዊ መርሆች የመነጨ አልነበረም ። ከዚያ የጠለቀ ነበር ። የኩሎኔል ታሪኩ ፍቅረኛ

ነኝ ወይም ከእሱ ጋር ግንኙነት አለኝ ብትለኝ ኖሮ ምን እንደ ማደርግ አላውቅም ነበር ። ምናልባት በዚያችው ደቂቃ እዚያው ደህና ሁኚ ብዬ እሊያት ነበር ። ለአብዮታዊት ኢትዮጵያ አንድነ ትትና ክብር በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ቀን ሰውነቱን በናቅፋ ሐሩር እየተቀቀለ ፣ ሌት በቁር እየተኰማተረ ፣ ለመስዋዕትነት ራሱን አዘጋጅቶ የሚዋጋ የጦር ሜዳ ጀግና ፍቅረኛ ይገፎ በአሥመራ መንገዶች ላይ ስቀብጥ ብገኝ የሕሊና በትር ዕድሜዬን ሙሉ እረፍት የሚሰጠኝ አይመስለኝም ። እና በተጨማሪ ፣ «ፈያ ሜታ በፈጠረሽ ሐቁን ንገሪኝ!» ብዬ በቁም ነገር ለመንኳት ።

«ከእሱ ጋር ምንም የለኝም ብዬሀለሁ.....»
«እስቲ እጇን ምችኝ ።»
ግጥም አድርጋ እጇን መታችኝ ።
«ማን ፈያሜታ»

«አይ እንግዲህ! ምክንያት ትፈልግብኝ እንደሆነ ወርጄ ልሔድልህ እችላለሁ ። ያፈጠጠብኝ ሁሉ ወዳጄ ነው ማለት አይደለም ። የሰው ምኞት አይከለከልም ። ሴት ልጅ ደግሞ የምኞት ኢላማ ናት» አለችኝ ። አመንኳት ። ከዚያ ቀን ምሽት በኋላ የአሥመራ ከተማ እየጠበበችን ሐደች ። ከሥራ በኋላ ዘወትር ማታ እንገናኝ ጀመር ።

ለጥሩ ጀላቲ አሳ ፣ ለጥሩ መጠጥና የፈረንጅ ምግብ ካራ ቬል ፣ ለጥሩ ካፑሮቶና ውስኪ ቬል ፣ ለጥሩ ቶስት አጂፕ ፣ለጥሩ የፓፓዬ ወይም የማንጎ ወይም የሙዝ ወይም የብርቱካን ጭማቂ ማይጃሕጃሕ ቁርስ ቤት ፣ ለጥሩ ቡና ቴሬሰቴሌ.....

እሑድ እሑድ ለጥሩ አየር ሰምበል ፣ አይሮፕላን ማረፊያ ፣ ለሽርሽር በከረን ፣ በምጽዋ ፣ በመንደፍራ መንገዶች እስከ ብሎ ኮዎቹ ድረስ — ዓለም የኛ ብቻ ሆና ነበረች ። ሲደክመን ዘም ባባ ጥላ ሥር እናርፋለን ። ሲያስፕን እጅ ለእጅ ተያይዘን እንሮ ጣለን ። አንዳንዴ ዘምባባ ዛፍ ስር ቁጭ ብለን ጀምበሯ የጋለ የብረት አሎሎ መስላ ሰማዩን በሺ ቀለማት በማንደድ ስትጠ ልቅ በዝምታ እናደንቃለን ። ሳንገናኝ ውለን ስናድር መነፋፈቅ መጣ ። በጣም ተለማመድን ። የፍቅር መነሻው መቸም ልማድ ነው ። ልማድ ያቀራኛል ። ከእሥር ቤቱ መውጣትም ስቃይ

ይሆናል ። እንደ ነገሩ ፍቅር የጣፋጭ ስቃይ እሥር ቤት ነው ። እና ሁለታችንም — እኔም የእሷ ፣ እሷም የኔ — እሥረኞች ሆነን ነበር ። ቃል ኪዳን አላሰርንም ። አልተጋባንም ። ግን የፍቅር ሙሽሮች ነበርን ። ፍቅር ይሞሽራል ፣ ያስጌጣል ፣ ያስውባል ። የወጣቱን ልብ ቀርቶ አሮጌም ልብ ወጣት ያደርጋል ። ሁለታችንም በፍቅር እንሞሸር ፣ እናጌጥ ፣ እንዋብ ነበር ። ዓለም የኛ የግላችን ነበረች ። ያለእኛ ማንም የሚኖርባት አይመስለንም ነበር ። ዓይኖቻችን ሌላ አያዩም ነበር ። ፍቅር ለራሱ እውር ሆኖ እውር ያደርጋል ይባል የለ! ሁሉን ነገር ቆንጆ ፣ ውብ አድርጎ ያሳያል ። በፍቅር ዓይን ዓለም የጽጌረዳዎች እቅፍ ትሆናለች ። ማንኛውም ድምጽ ወደ ጥዑመ ሙዚቃ ይለወጣል — ዝግ ያለ አሳዛኝ ሙዚቃ ። ኃዘን በተሞላበት ሁኔታ ውስጥ ደስተኛ መሆን ይመጣል ። በፍቅር ዓይን የማይታመነው ይታመናል ፣ የሚታመነው ነገር ደግሞ ያጠራጥራል ፣ ያነጣንጣል ፣ ያናድዳል። ፍቅር ወደ ልጅነት ይለውጣል — ውብ ልጅነት ወይስ ውብ ጅልነት! እንደ ልማዳችን ወደ ምሽት ላይ ተገናኘን ። ጥር አክትሟል ። የካቲት ገብቶ ነበር ። ምሽቱ ይወብቃል ።

«ዛሬ ደስ ያለህ ትመስላለህ ፣ ምን አገኘህ?» አለችኝ ።

እውነትም ጥሩ ስሜት ነበረኝ — «ዕድሜ ላንቺ ፣ ፍቅር ይዞኛል» አልኳት ።

«ማናይ! ከማን ጋር?» አለችኝ ።

«ከአሥመራ ጋር ።»

«እኔም ከቀይ ኮከብ ዘመቻ ጋር ፍቅር ይዞኛል ። እውነት ፡ አባቴ ይሙት ። በሥነ ሥርዓት ግን ሠላም አይሰጠኝም ። ፍቅር ሠላም አይሰጥም» አለች ። ወደ አይሮፕላን ማረፊያ መንገድ ሔድን ። የምሽቱ ጀምበር ውብ ነበረች ። አሥመራ ላይ የምትጠልቅ የምሽት ጀምበር ሁልጊዜ ውብ ነች ። ወደ ከተማ ስንመለስ ወደ ፓራዲዞ ቡና ቤት በቀጥታ አመራሁ ።

«ወደየት ልትሔድ ነው?» አለችኝ ።

«ፓራዲዞ ። ጥሩ ቡና እምሮኛል» አልኳት ።

«ኖኖ ፣ እዚያ አንጠጣም ። ቴሬስቴላ እንሂድ» አለች ፣ ጠጉሯን እየነሰነሰች ፣ መፋቂያዋን ይዛ ።

«ምነው? ለምን እዚህ እንጠጣም? በከተማው ውስጥ ጥሩ ቡና የሚገኘው እዚህ ነው ይባላል...»

«አቦይ ተኽሌ ከሞቱ ወዲህ ቡናቸው ተበላሽቷል ይላሉ ። አልቀመስኩትም ። ጥሩም ቢሆን እዚህ ቆሜ ቡና አልጠጣም አቦይ ተኽሌን እያስታወስኩ ማዘን አልፈልግም ። ለኃዘን አልተ ፈጠርኩም» አለች ።

«ታዲያ ለምንድነው የተፈጠርሺው?»
«ለፍቅር ፥ ለደስታ ።»

«ይሁንልሽ» ብዬ ወደ ቴሬስቱ አመራሁ ። መንገዶቹ ላይ ብዙ ሰዎች አይታዩም ። መንገዶቹ ባዶ ስለሆኑ ስፋት የጨ መሩ ይመስላሉ ። ጥርሷን ዝም ብላ ስትፍቅ ቆየችና ፥ «ግን አሁን ደስታም ሆነ ሠላም የለኝም ። ልቤ ዝም ብሎ ያዝናል ። አንዳንዴ አልቅሺ ፥ አልቅሺ ይለኛል ። ድሮ እኮ እንዲህ አልነበርኩም አባቴ ይሙት ። ግን ምን ነካኝ? እስቲ ንገረኝ» አለችኝ ።

«ምን ሆነሽ ነው?» አልኳት ።
«ሰንጃ አባትህ! ደደብ» አለችኝ ።

ትሬስቴያ ደርሰን ነበር ። እሷ ቡና አልፈለገችም ። ሻይ በሎሚ ነበር ያዘዘችው ። አሥመራ ቡና በብዛት አይጠጣም ። አብዛኛው ሰው በብዛት የሚጠጣው ሻይ ነው — ሻይ በራድ ኪያንቲ መዓመር ። ቢያንስ ስምንት ሲኒ ሻይ በቀን ።

«ድሮ እንዴት ነበርሽ?» ብዬ ጠየኳት ። መቸም ጥሎብኝ የጥያቄዎች አባት ነኝ ።

«ለምንም ነገር ግድ አልነበረኝም ። ደስተኛ ነበርኩ ። አሁን ግን ያልነበረኝ ጠባይ ይታይብኛል ። ለምንድነው ግን? ተወው ። አንቴ አታውቀውም አይገባህም ። አባቴ ይሙት ደደብ ነህ...

«እስቲ ስለእጮኛህ ንገረኝ? ግን ተወው ። ስለእሷ መስማት አልፈልግም ። ምን አባቷ! ግን አሁን እዚህ ብትመጣ ምንድ ነው የማደርገው? እንጃ! ግን አንተ ብትሞት አሁን ምናለበት?

ቀይ ኮከብ መቃብርህ ላይ አደርግልህ ነበር ። ግን እትሙት ። እንቴ ብትሞት ማን ውሸት ያወራል? በማለት ስትቀላልድ ቆየ ችና ፣ «ግን አንተ የሔድክ ለት ምን ይውጠኛል? መድረሻዬ የት ይሆናል? » አለች ። ጥያቄዎቹን ያቀረበችው ለኔ ሳይሆን ለራሷ ነበር ።

«እንዲህ ዓይነቱን ነገር ተይኝ እባክሽ ። አሁን ለምንድ ነው ስለመለያየት የምናወራው፣ ስለሌላ ነገር እንጫወት» አልኳት ።

«ትወደኛለህ? እስቲ ንገረኝ.....»
«ልቤ የናቅፋ አለት መሰለሽ?»

«አባቴ ይሙት ፣ እኔ'ኮ መወሰን አልችልም ። ሁሉንም ነገር እንደቀልድ ፣ እንደ ጨዋታ ነበር የምወስደው ። አልጠፋሁ ወይ እርፎ አልኖር ። የ ራሴ ቤት የለኝም ። ትዳር አልያዝኩም ። ሴንካ ካዛ ሴንዛ ማራቶ ። ግን ምንድን ነኝ? መወሰን የማልችል ሴት» ብላ ዝም አለች ።

ስሜታችን ፣ ውሉ እንደጠፋ ልቃቂት እየተወሳሰበ ሲ ሔድ ተሰማኝ ። እንደ ቀልድ ፣ እንደ ጨዋታ ፣ እንደጊዜ ማሳለ ፊያ የጀመርኩት ነገር ከቁጥጥሬ ውጭ ከኔ በላይ ሆኖ እያስመ ጠኝ ሲሔድ ታየኝ ። እንደኛዬን ሰምጨ ለመቅረትም ሆነ ወ ይም ዘልዬ ለመውጣት ፣ እኔም እንደ እሷ መወሰን አልቻልኩም ። ዝም ብዬ እየተንሳፈፍኩ ነበር የምሔደው ። ወዴት? አላውቅም ወዴት እንደምሔድ ስማየ ሰማያት ብቻ ነበር የሚያውቀው ።

ቡናና ሻይ ያመጣልን ሳይሆን ሌላ ቦይ መጥቶ ሂሣቡን ተቀበለን ። ፊያሜታን ሲያያት ደስ ብሎት ሠላምታ ተለዋ ወጡ ። በትግርኛ ነበር የሚነጋገሩት ። ስለ አቦይ ትኸሌ ነበር የሚጨዋወቱት ። ቦዩ ከሔደ በኋላ ፣ «ማነው?» አልኳት ።

«ያቦይ ተኸሌ ወንድም ልጅ ነው» አለችኝ ።
«አጠይቅሻለሁ ስል ፣ አቦይ ተኸሌ እንዴት ነው የሞቱት?»
ብዬ ጠየኳት ።

«ምን እላቸው ብቻ ታላቅ እህታቸውም በሁለተኛው ቀን ሞተው ተገኙ ። አበይ ተኽሉ ባለቤታቸው ከሞተች ወዲህ ከታላቅ እህታቸው ጋር ነበር የሚኖሩት።ለብዙ ዘመን እንደነሱ የሚዋደዱ ወንድምና እህት አይቼም ሰምቼም አላውቅም ። ያሳዝናል ። ፖቨሪኒ!» ብላ የሕሊና ጸሎት የምታደርግላቸው ይመስል አቀርቅራ ትንሽ ከተከዘች በኋላ ፡ «አበይ ተኽሉን ፈዳይኖች ናቸው የገደሏቸው ። እህታቸው ግን የሞቱበት ምክንያት አልታወቀም ። በልብ ሕመም ነው ይላሉ ። ግን እኔ ሳውቃቸው ጤነኛ አሮጊት ነበሩ» አለች ። ቀጠለችና ፡ «አደይ ለምለምን በጣም እወዳቸው ነበር ። የናቴ ጓደኛ ነበሩ ። በኃዘንም ሆነ በደስታ ጊዜ አይለያዩም ነበር ። አይ አደይ ለምለም! መብላት ፡ መጠጣት ይወዱ ነበር ። እውይ የቤት እያያዝ ሲያውቁበት የነበሩ! ከቤታቸው ወለል ላይ እንጀራ ቢበላ እያስጠይፍም አባቴ ይሙት በሕጻንነቴ እሔድ ፡ እሔድ አብልተው ፡ አጠጥተው ፡ ለሲኒማ ገንዘብ ይሰጡኝ ነበር ። ከእናት አባት ዘመዶቼ ቤት ከመሔድ ይልቅ እሳቸው ቤት መሔድ በጣም ደስ ይለኝ ነበር ። ግሀን እ ጠቡ ፡ ዕቃ አንስ አይሉም ። ሰነፍ ነኝ ጥ ከድሮ ጀምሮ አባቴ ይሙት» አለች ።

«እሺ» አልኳት ታሪኩን እንድትቀጥል ፈልጌ ።

«አደይ ለምለም ከመሞታቸው አንድ ቀን በፊት ስለ ወንድማቸው አጫውተዋት ለናቴ አጫውተዋት ነበር.....»

«ምን ብለው ልጄ?»

«አበይ ተኽሉ ፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነገሩ ሁሉ አላማረኝም ፡ ሥራዬ ሁሉ አደገኛ እየሆነ ሔዷል ለመልቀቅም ፈራሁ ፡ ምን ባደርግ ይሻለኛል? እያሉ ይጨነቁ ነበር» በማለት ለእህታቸው ያጫወቱትን አንስታ አጫወተችኝ ።

«ምን ይሆን ልጂ እንዲህ ሲያስጨንቃቸው የነበረው?» ብዬ ጠየኳት ።

«እንጃ ፡ እንዳልኩህ በፊት ደስተኛ ሰው ነበሩ» የሚል መልስ ሰጥታኝ ዝም አለች ።

ፊያሚታ ጊላይ አንድ ጠባይ አላት ። እውነትና ውሸት ደባልቃ ነው የምትናገረው ። ትንሽ እውነት ይዛ ውሸት ትጨ

ምርበታለች ። እና ከምትናገረው ውስጥ የትኛው እውነት፣ የት ኛው ውሸት፣ መሆኑን ለይቶ ማወቅ ያስቸግራል ። ታዲያ እን ዲህ የምታደርገው ዓመል ሆኖባት ነው እንጂ ለክፋት አይደ ለም ። አንድ ቀን ከቢሮዋ ስልክ ደውላ ያደረገችኝ ነገር ትዝ አለኝ...

— እናቴ አሁን ደውላልኝ ነበር ።
— ምነው?
— ቤታችን ተከቧል ።
— ምን!
— እው ፣ አልጊታን ታውቃት የለም?
— አዎ ፣ ምን ሆነች?

አልጋነሽ የፊያሜታ ጓደኛ ናት ፡ ጎረቤቶች ናቸው ። አብ ረው ይበላሉ ። ተቃቅፈው ያድራሉ ። አይለያዩም ። አልጋነሽ በጣም ቀጥተኛ ልጅ ናት ። ስትናገር ለነገ አትልም ። በዚህ ላይ ቅብጥብጥ ናት ። አንድ ቦታ እርፍ መቀመጥ አይሆንላትም ። ከፍ ያሜታ ጊላይ ጋር ካንድም ሁለት ጊዜ ጋብዣታለሁ ። እሷም ግሩም የትግሬ ሽሮ ወጥ ሠርታ ቤቷ ጋብዛኝ ነበር ።

«ቤቷ መግሪያ ተገኘ» አለችኝ ።

«አትይኝም!» አልኳት ከወንበሬ ተነስቼ ። ባንድ ፊት ሻዕ ቢያ በምብ ላይ ተቀምጦ የትግሬ ሽሮ ስወጥ ናሯል ለካ! እያ ልኩ ።

— ወው ፡ ይዘዋታል አለችኝ ።
— ታዲያ አንቺ ምን ሆንሽ?
— እኔንም እየፈለጉኝ ነው ፡ አሁን የምደውልልህ ያለሁት ከሌላ ቦታ ነው...
— ለምንድነው የምትፈለጊው?

— መሥሪያ ቤቷ እንደነበረ ይውቃለሁ ። እርግጠኛ ነኝ ትነግራቸዋለች ። እህ አሁን መጥፎቴ ነው ሐዘሐዘ ሁለተኛ መግባት አልፈልግም ደህና ሁንልኝ አዋሬ ግሬ ። ቻው ።

— ቆይ ፊያሜታ ስልኩን አትዝጊ የማይሆን ነገር አት ሥሪ ። የት ነው ያለሽው? እያልኩ ስጮህ ስልኩን በጆሮዬ ላይ

ዘጋችብኝ ። ሳጽናናት ፈለግሁ ። ባንድ ጊዜ ብዙ አሳብ መጣብኝ ። ተነስቼ የት እንደምሔድና ምን እንደማደርግ ተጨንቄ ሳስብ እንደገና ስልክ ደወለችልኝ ።

«በፈጠረሽ የት ነሽ? ንገሪኝ መጣሁ» ስል — ሳቀችና ፣ «እናቴ ትሙት ውሸቴን ነው።ደደብ» አለችኝ ።

በጣም ተናድጄ ስልኩን ጆሮዋ ላይ ዘጋሁባት ። አጠገቤ ብትሆን ኖሮ በቃሪያ ጥፊ ጆሮ ግንዷን አቃጥለው ነበር ። ኋላ ስንገናኝ ፣ «አባቴ ይሙት ፣ እኔ ምን ይሻለኛል? ዝም ብሎ ውሸት ይመጣልኛል ። ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ?» ስትለኝ ፣ «ጣፋጭ ዋሾ» ከማለት ሌላ ምንም አላልኳትም።ጣፋጭ ውሸቷን ተላም ጀዋለሁ ። ቢሆንም አንዳንድ ነገር እጠራጠራታለሁ ። ግን «እናቴ ትሙት» ካለች አትዋሽም ።

«ማነው የፓራዲዞ ባለቤት?» ብዬ ጠየኳት ።
«እንጃ እንዴት ላውቅ እችላለሁ?»

«ከተማዋ ትንሽ ስለሆነች ሁሉም ይተዋወቃል ብዬ ነው ። ፓራዲዞ ደግሞ የታወቀ ነው — በቡናው «ካልኳት በኋላ ቀጥዬ «ስለ አበይ ተኸሌ የነገርሺኝ እውነት ይሆን?» ብዬ ጠየኳት ።

ያው እንደልማዷ ፣ «ዋእ እን (አታግናይ) እውነትም ብነግርሀ አታምነኝም ። ደደብ» ካለች በኋላ ፣ «እናቴ ትሙት እውነት ነው» አለችኝ ።

እንደ ዋዛ ያጫወተችኝ ነገር በጣም አሳሰበኝ ። ፓራዲዞ እውስጡ ምን በመካሄድ ላይ ይሆን? አበይ ተኸሌ ምን ቢፈሩ ነው የተጨነቁትን? ምን ያውቁ ነበር? እና ለሞት ያበቃቸው ነገር ምንድነው? ነገሩ ይበልጥ ከነከነኝ ። የመረጃው አደገኛነትም ታየኝ ። በጣም የሰጋሁት ስለፊያሜታ ነበር ። የሚያሳዝነው ነገር ሳታውቅ የደረሰችበት መረጃ ዋጋና አደገኝነት ምን እንደ ሆነ እንኳን አታውቅም ። የሆነ ሆኖ ፣ «ስሚኝ ፊያሜታ» አልኳት የምሬን — «አሁን የነገርሺኝን ለማንም እንዳትነግሪ ። አደገኛ ነው ። ይገባሻል? ቀልድ አይደለም ። የሁላችንንም ሕይ

ወት የሚያሰጋ ነገር ነው ። እናትሽም ዝም እንዲሉ ንገሪያቸው ። በጣም አደገኛ ነው» በማለት አስጠነቀቅኋት ።

«ለምን? ምንድነው እሱ?» አለች ።

«አሁን ምን እንደሆነ አላውቅም ። አንድ ቀን በቅርቡ እደር ስበት ይሆናል ። ግን በፈጠረሽ ስለዚህ ጉዳይ አንድ ቃል ካፍሽ እንዳይወጣ» ብዬ ቤቷ ወሰድኳት ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ማይተመናይ በጨለማ መሔድ አስፈራኝ። ሆኖም እንድታውቅብኝ አልፈለግሁም ፡ እንዳጋጣሚ በሠፈሩ መብራት አልነበረም ።

«እኔንስ አስጠነቀቅኸኝ ። አንተ ግን ለምን አትጠነቀቅም?» አለችኝ ።

«እንዴት?» አልኳት ።

«ነጻ ነህ ። የፈለከበት ትሔዳለህ ። እንደሌሎቹ እጃቢ የለህም ፡ እታ ግናይ.....»

«የሚሞትበትን የሚያውቅ ማን አለ? በነጻነትኑሮ በነጻነት መሞት ይሻላል ። ለማንኛውም ነገር ስለሞት አስቤ አላውቅም» አልኳት ።

ደህና ዋል ወይም ደህና እደር አትለኝም ሁልጊዜ ፡ «አይትንእሰ እሺ እምባእር?» ለችኝ እንደልማዷ ። «አይትን እስ» አልኳት እንዳስተማረችኝ ።

ከማይተማናይ በርሬ ወጣሁ ። ቤት ስገባ ስልኬ ይጮህ ነበር ።

«ሀሎ?» አልኩ ፊያሜታ መሰላኝ ። ሀሎ ፊያሜታ ልል ነበር ። እግዜር ለትንሽ አወጣኝ ። ሮማንኢሮኛዬ ነበረች።

«ምነው ልጄ? የት ጠፋህ? እንዲሁ ስልኩን ስቀጠቅጥ ነው ያመሸሁት» አለች ።

«መውጫና መግቢያዬ ምን ይታወቃል ብለሽ ነው፣ ሥራ ይበዛል» ብዬ ዋሸኋት ።

«እስካሁን?»

የእጅ ሰዓቴን ተመለከትኩ ። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ሆኗል ።

ትዝ ብሎኝ ፣ «ቡናሽ በጣም ናፍቆኛል» አልኳት ።

«ማፍላቱን ትቻለሁ» አለች ።

«ለምን ልጇ? እማንሽን ቦግ እ'ርገሽ አድባሯን ብትለማምኝልኝ ደስ ይለኝ ነበር.....»

«አስጠልቶኛል ። ሳንተ ሳፈላልህ ነበር ደስ የሚለኝ..... ሐድራው የሚሞላልኝ ።»

«ይብላኝ ለጀበናዎችሽ!»

እንዴያው የሰው ልጅ የሚመስሉ ጀበናዎች አሏት ። ጀበናዎቿ ያምራሉ ።

«ሥራ ፈትቷል» አለች ኃዘን በተሞላበት ድምፀት ።

ሮማን ቡና ማፍላትን ወደ ኪነታዊ ፈጠራ ከፍ ታደርገዋለች ። ለሱስ አይደለም ቡና የምታፈላው ፣ ሳምልከትም አይመስለኝም ። ለኪነታዊ ውበቱ ሰትል ይመስለኛል ፣ ወይም ነው ። እሷም ቡና በማፍላት ጥበቧ ትኮራበታለች ። «ቡና እና ፈሳለን ብለው ደፋ ደፋ የሚሉ ቤቶች ይገርሙኛል ፣ ቡናን ማፍላት ረጋ ብሎ እያሳመሩ ነው ፣ ሥነ ሥርዓቱ ፣ ውበቱ ፣ ነው ደስ የሚለኝ ። እለዚያ ጥቅሙ ምን ድነው?» ትላለች ። ቡና ከማፍላቷ በፊት ተጣጥባ ረጅም ያገር ልብሷን ትለብሳለች ፣ የቡና ልብሷን ፣ ገርዳሳ ሽብ ፣ ቀጭን ነጠላ ከብ ትከሻዋ ላይ ጣል ታደርግና የቡና ልዕልት መስላ ከልዩ በርጩማዋ ላይ ቁጭ ትላለች ። በጥሩ ሁኔታ የነደደ እሳት ለጥሩ ቡና አስፈላጊ ነው ስለምትል ትርክክ ብሎ የነደደ ከሰል በልዩ የከሰል ምድጃ ታስቀርባለች ። እና ልዩ የብረት ምጣዷን ከመጣዷ በፊት ለስሜቷ ተስማሚ የሆነ ሙዚቃ ትከፍታለች ። ቡናውን የምትቆላው ሙዚቃውን እየተከተለች በስልት ነው ። እንደ እሷ ልዩ ወዝ ያለው ቡና የምትቆላ ሌላ ቤት አላየሁም ። አንድ ፍሬ ቡና አያርባትም ። አንድ መልክ ፣ አንድ ወዝ ይዘው ይወጣሉ ። በሙዚቃው እየታጀበችና በስልት እየተራመደች ከፍሉን ታሻትታለች ። ማሻተት ትወዳለች ። መአዛው ብቻ ሱስ ይቆርጣል ። እንደሌሎች ቤቶች ራሷ የቆላችውን ቡና ሌላ ሰው አታስወቅጥም ፣ ራሷ ናት የምትወቅጠው ። አውቃቀጡ ፍጹም መሆን አለበት ትላለች ። ከሰሉ እንደገና ይራገባል ። እሳቱ ትርክክ ሲል በጥንቃቄ ታጥበው ከሚቀመጡት ጀበናዎቿ ውስጥ አንዱን ትጥዳለች ። ሌላ ሙዚቃ

ትለውጣለች ። እንግዲህ ዓይኖቿ ከጀበናው ላይ አይነሱም ። ውሀው ለተወሰነ ደቂቃ ይፈላል ፣ ቡናው በተወሰነ ደቂቃ ይጨመራል ፣ ለተወሰነ ደቂቃ ይንተከተካል ፣ በተወሰነ ደቂቃ ይከለሳል ። ሲኒዎች በቀይ ጨርቅ በተሸፈነ ረከቦት ይቀርባሉ ። ሰው ይኑር አይኑር የሚቀርቡት ሲኒዎች ቁጥር ደግሞ ስድስት መሆን አለበት ። ደግሞም ጆሮ የሌላቸው የቡና ሲኒዎች መሆን አለባቸው ። የቡና ሲኒ አያያዝም እኮ የራሱ የሆነ ሥነ ሥርዓት እንዲኖረው ያስፈልጋል ባይ ነች ። አይ ሲኒ አያያዝ! አይ ቡና አጠጣጥ! ይምጣብኝ ።

ጀበናው በሥነ ሥርዓት ይወጣል ፣ እጣኑ በሥነ ሥርዓት ይጨሳል ። ቡናው እየተንተከተከ ሲፎከር ፣ እጣኑ ቦግ ብሎ ሲጨስ ፣ የእጣኑ ሽታና የአቦል ቡናው መዓዛ ተዋሕደው አፍንጫ ሲያውዱ ፣ እጇቿን እንደገና ተጣጥባ ፣ ቡናው እስኪሰክን ድረስ ከእጣኑ ጢስ ጋር ባሳብ ትባከናለች — ፈገግ ብላ ፣ ፈገግታ ተጎናጽፋ ። ቡናው ይሰክናል ፣ አሳቧ ይሰክናል ፣ ሕይወት ትሰክናለች ። ለዘብ ያለ ሙዚቃ ታደርጋለች ። ጀበናውን ከፍ አድርጋ ፣ ቡናውን በረጅሙ ፣ በቀስታ ፣ በቀጭኑ ትቀዳለች ። የምታፈላው ቡና እኮ እንዲያው ቡና አይደለም — ብርቅ የፈረንሣይ ኮኛክ እንጂ! አንዱ ብቻ ይበቃል ፣ እሷም ብትሆን የምታፈላው ቡና ከሦስት ሲኒ አይበልጥም ። እጣኑ ቦግ ሲል በዓይነ ሕሊናዬ ታየኝ — እሷም በእጣኑ ጢስ ውስጥ ። የቡናዋ መአዛ መጣብኝ ። እና ከቡና ማፍላቱ በኋላ የሚከተለው ሥነ ሥርዓት ትዝታ..... አሁን አሁን አለኝ ። ፊት ለፊቷ ካልተቀመጥኩ እሺ ብላ ቡና አታፈላም ።

«ምነው ዝም አልከ?» አለችኝ ።
«ቡናሽ ትዝ ብሎኝ» አልኳት ።
«መጥፎ ትዝታ እቴ» ብላ ዝም አለች ።
ትንሽ ቆየችና «እሥመራ እንዴት ይዞሀል? ስልክ መደወልም ትተሀል» አለች ።
አነጋገሯ ጤነኛ አልነበረም ። ነገር ነገር ያላት ትመስላለች ።

«ሥራ ይበዛል እንጂ ደህና ነው ። ምግብ ለሥራ እያለ ምን እሆናለሁ ብለሽ ነው? ሁለመናዬ ፓስታ ፓስታ መሽተት ጀምሯል ። እኔም ፓስታ መስያለሁ» በማለት የባጡን ፣ የቆጡን ቀባጠርኩላት ።

«በቴቪ ሳይህ ያሥመራ» ሹሩቤዎች «ግጠው የጨረሱህ ትመስላለህ»?

«እንዲያው ሴቶች ስትባሉ ወንድ ከቤት ፍለጋ ሌላ ሥራ ያለው አይመስላችሁም!»

«እስቲ ጸግዬ በሞቴ ንገረኝ......»

«ምን ?»

«እስካሁን የትም አልሔድክም?»

«እባክሽ ዝም በይ እኮ!»

«አንድ ነገር ብሰማ ገድዬህ ነው የምሞተው ። ይህን ታው ቃለህ? እውነት ጸግዬ ፣ የኔ ፣ የግሌ ብቻ ነህ? ኤጭ! ግን አንተ የሁሉም ነህ ። የሁሉም ፍቅረኛ ። ግን ምን ይደረጋል እቴ? ቢሆንም ልቤ የእሷ ነው በላቸው፣ ፍርጃ ነው 'ኮ' በማለት ስት ነማነጭብኝ ቆይታ በመጨረሻ ፣

«ለመሆኑ መቼ ነው የምትመጣው?» ብላ ጠየቀችኝ ።

«በንመጣ በተነገረን መሠረት ከእንግዲህ ሁለት ወር ይቀ ረኛል......»

«እንደምታወራው ወሬ ከሆነ ግን ሁለትም ሣምንት የም ትቆዩ አትመስሉም......»

«ፍቅር ፣ የጦር ሜዳው ፍልሚያ ገና አልተጀመረ ። ገና ምን ተይዞ?» አልኳት ።

«እሱ ምን ጊዜ ይፈጃል?» አለች ።

«ቀላል አይደለም ። ያፍሪካ ረጅም ጦርነት ባንድ አዳር የሚያልቅ አይደለም ። ጠላቶቻችንም የሚናቁ ሰዎች አይምሰ ሉሽ ። የናቅፋ መሬት አቀማመጥ ራሱ ብዙ ትግልና መስዋእት ነት የሚጠይቅ ነው» በማለት ነገሩ እንዲሁ በቀላሉ የማይታይ መሆኑን ላስረዳት ከሞከርኩ በኋላ ፣

«እኔም በቅርቡ ወደዚያ ሳልሔድ አልቀርም» አልኳት ።

«አንተ ደግሞ እዚያ ምን ታደርጋለህ? ወታደር አይደለህ» አለች ።

«ጋዜጠኛም እንዳቅሙ ወታደር ነው ። ወታደር ይተኩሳል ፣ ጋዜጠኛ ታሪክ ይቀርጻል ። እንደ ሁኔታው ሁለቱም ይዋጋሉ......»

«ወይ እድሌ!» ብላ ማልቀስ ጀመረች ። ሮማን እንባ ይቀናታል ።

«እንግዲህ ጀመርሽ ። አሁን ምን ሆንኩ ብለሽ ነው የምታለቅሺው? አይዞሽ ምንም አይነካኝም» በማለት ላጽናናት ሞከርኩ ።

ስትነፋነፍ ቆየችና ፣ «ያስቴርን ቴፕ ክር ልኬልሀለሁ ። ነገ ይደርስሀል ። እኔም ከጥቂት ሣምንት በኋላ የዓመት እረፍቴን ወስጄ መጥቼ አይሀለሁ ። ፍቅር በስልክ አይጠገብም» አለችኝ ። ፊያሜታ በበኩሏ የኩኩን ክር ሰጥታኝ ነበር ። እስካሁን ምናልባት መቶ ጊዜ ሳልሰማው የቀረሁ አይመስለኝም ። ሁለት የፍቅር ክር!

«የጎጆአችንስ ጉዳይ?» አልኳት ።

«እየተሟላ ነው ። ግሩም መጋረጃዎች አሠርቻለሁ ። አሁን የሚቀረኝ ነገር ቢኖር አልጋውን መለወጥ ነው ። አልወደውም» አለች ።

ከሮማን ጋር ጨርሼ ስልኩን እንደዘጋሁ ሌላ ጥሪ ወዲያውኑ ተከትሎ መጣ ። ፊያሜታ ጊላይ ነበረች ።

«ከማን ጋር ነው ለግማሽ ሰዓት ስታወራ የቆየኸው እታገናይከ» አለችኝ ።

«ከማን ጋር ይመስልሻል?»

«ከእጮኛህ ጋር.....»

«ልክ ነሽ.....»

«ምን ነበር የምትለው? ምን ትፈልጋለች? ለእሷ ስልክ ለመደወል ነው እኔን ዝም ብለህ ወደ ቤቴ ያመጣኸኝ? አባቴ ይሙት ፣ የሠራሁት ግፍ ሳይሆን አይቀርም እንዲህ የሚያዋርደኝ ። ቅሌት ነው ። ቅሌታም ሆንኩ አባቴ ይሙት» እያለች ነገር ትፈልገኝ ጀመር ።

«እንሂድ ብዬሽ ነበርኮ ። አንቺው ነሽ ቤቴ ውሰደኝ ያልሺኝ ፣ አይደለም እንዴ?» አልኳት ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፊት የማላውቀው አዲስ ጠባይ ይታ

ይባታል ። ከኔ ጋር እደረ ስላት እሺ አትለኝም ። በፈቃዷ መሠረት ወስጄ ቤት ሳደርሳት ደግሞ ታኮርፈኛለች ።

«ብልህስ ታዲያ!»
«እሺ ምን አድርግ ነው የምትይኝ!»

- - - - - - - - - -

«እሺ አሁን ልምጣና ልውሰድሽ....»
«አልመጣልህም!»
«እሺ ምንይሁን!»
«እንጃልህ!»
«እሺ ለምንኝ የምትይ ከሆነ አሁን ልለምንሽ....»
«ቤቴ ወስደህ እንደ ዕቃ ከጣልከኝ በኋላ? አውይ ብሞት!» ብላ ስልኩን ጆሮዬ ላይ ዘጋችብኝ ።

መልሼ ልደውልላት ፈልጌ ስልኩን ካነሳሁ በኋላ ተውኩት። ኩራቷ ታገለኝ ። ተሟገትኩት ። አሸነፈኝ ። ጥሪዬን እንደምትጠብቅ ቢገባኝም ጨክኘ ተኛሁ ። ግን እንቅልፍ አልወሰደኝም ። ምን እንደነካኝ አላውቅም ። እንዲህ አልነበርኩም ። ድንገት ለራሴ ባዶ እንደሆንኩ ተሰማኝ ። የፍቅር ስመመን አባዜ ይዞኝ ይሆናል እንዳልል ዕድሜዬ እንዲህ ዓይነቱን ነገር የሚፈቅድ አልመሰለኝም ። የአሥራ ስምንት ዓመት ጎረምሳ አይደለሁም ፣ ወይስ ስመመን የዕድሜ ክልል የለውም? አላውቅም ። ግን የያዘኝ አባዜ ስመመን አልመሰለኝም ። ገረመኝ ። መከረኛው አርጊ ልቤ ሁለት ሴቶች እንዴት ብሎ እኩል ሊወድ ይችላል? ብዬ ተገረምኩ ። ሕይወት እንግዳ ነገር ነው ። ብዙውን ቀልድ ነው ። አንዳንድ ጊዜ ቀልዱ ይመራል ። በሁለቱ መካከል መወሰን አልቻልኩም ። ለደግም ሆነ ለክፉ መወሰን አለመቻል ስቃይ ነው ። ልቤ ሲደማ ተሰማኝ ። ያበርኩት ቃል ኪዳን እንደ እሾህ ወጋኝ ። በዘምባባዎች ጥላ ሥር አዲስ ያገኙት ፍቅርና ደስታ እንዲሁ በቀላሉ የሚረሳ ባለመሆኑ የሚደማውን ልቤን የባሰውኑ ጨመቀው ። ከፍቅርም ሌላ በፈያሚታ ሕይወት ላይ የሚያንዣብበው የአደጋ ጥላ ፣ ይሉኝታ ፈጠረብኝ ። አሁን ልለያት አልችልም ። እንዴት ብዬ? ሰው ወዶ ፣ ወዶ ድንገት በቃኸኝ ወይም በቃሽኝ ለማለት እንዴት ይቻላል? እንዲህ ለማድረግ የሚችሉት የታደሉ ፣ ብርቱዎች ናቸው ። እኔ በዚህ አልታደል

ኩም ። በዚህ ረገድ ደካማ ነኝ ። ተዋውቆ መለየት ያቅተኛል ። እንጀቴ አይችልም ። ትዝታዬን መርሳት ያስቸግረኛል ። ስቃይ ይሆንብኛል ። የማደርገው ነገር ሁሉ በሚቴን ስለሚነካ የኔ ፣ የራሴ ፣ የግሌ አድርጌ ሳስቀረው እፈልጋለሁ ። እና እንዲህ ዓይነቱ ነገር ደግሞ ጅልነት ነው ። ምን ላድርግ? ጅል ነኝ — በእውነት

[illegible]

ቢሮው አልነበረም ። ቤቱ ደወልኩ ። ቤቱም አልነበረም ። በማ ከታተል ወደ አምባሶይራ እና ወደ ኒያላ ሆቴል ደወልኩ ። ሁለ ቱም ቦታ አልነበረም ። ምን ጉድጓድ ዋጠው? የበላውም ጅብ አልጮህ አለ ። የት ይሆን? እየመሸ ሔደ ። እንደገና ሌላ ዙር የስልክ ጥሪ ማድረግ ጀመርኩ — ኰሎኔል በትሩን ፍለጋ ። የትም አልነበረም ። የፈንጂ ድምጽ ከሩቅ ድንገት ተሰማ ። ሌቱ ጸጥ አለ ። ተኛሁ ። መኝታዬ ላይ ተገላበጥኩ ። ወበቀኝ ። ያን ሌት እንቅልፍ እምብዛም አልወሰደኝም ። ጧት በመጥፎ ስሜት ነበር ወደ ሥራ የሔድኩት ። ወዲያውኑ ስልክ ከወዲህና ከወዲያ ይጮህ ጀመር ።

«እንደ ጓድ ጸጋዬ ፣ ጦሩ'ኮ ጊዜ የለውም ። እናንተን ቆሞ አይጠብቅም ። ምን መሆናችሁ ነው? ጋዜጠኞች ዛሬ ከሰዓት በኋላ ምስሉም ጦር ግንባር ገብተው ማደር አለባቸው ። ትእዛዝ ነው» አለኝ ። ጓድ ኰሎኔል አምበሉ ከወታደራዊ ጉዳይ ፖለቲካ መምሪያ ደውሎ ።

ማን በየትኛው ጦር ግንባር ምን ይዞ እንደሚሰለፍ ድል ድል አውጥቼ ጨርሼ ነበር ። «ዝግጁ ናቸው ። በስንት ሰዓት አርሚ አቪዬሽን ይድረሱ?» አልኩት ።

«ልክ በ14 መቶ ሰዓት»
«ተቀብያለሁ ጓድ» አልኩት በወታደር ቋንቋ ።
«ከውጭ የታዘዙት መሣሪያዎች ደርሰዋል ፣ አይደለም?»
«ደርሰዋል ጓድ ። ዝግጁ ናቸው.....»
«ጦር ሜዳ የሚበተኑትስ በራሪ ጽሑፎች?»
«እነሱም ተዘጋጅተዋል ። ለመረከብ ይቻላል.....»
«በ13 መቶ ሰዓት መልሼ እደውላለሁ.....»
«እሺ ጓድ ። ትዕዛዙን ተቀብያለሁ»

ስቀ ስልኩን ዘጋ ። በወታደራዊ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ስፌ ልምድ ያለው የወታደራዊ መረጃ መኰንን ነው ። ስለ ኤርትራ ችግር የላቀ እውቀት አለው ። ብዙ አይናገርም ። ግን በኃይል ይሠራል ። ወንበሩ ላይ በሚስግር የተመቻታ ይመስል ከቢሮው አይወጣም ። በግድ ካልኮረኮሩት የውሸት ጥርሱን ብቅ አያደር ግም ። አሥመራ በወንበዴዎች በተከበበችበት በዚያን ቀውጢ ወቅት የሚቀምሰው እህል እያጣ ከመራብ የተነሳ ነበር የፊት ጥርሶቹ የረገፉት ። ወንበዴዎችን እንደጥርሱ ሳያረግፍ የትም መሔድ የሚፈልግ አይመስልም ። እና በኃይል ይሠራል ። የአብዮታዊ ጦራችን የተጋድሎና የመስዋእትነት ነገር ሲነሳበት እንባው ይመጣል ..... ረዛን ወደ ጦር ግንባሮች የሚሔዱትን የዜና ፣ የሬዲዮ ፣ የቴሌቪዥን ፣ የሲኒማ ፊልምና የፎቶግራፍ ጋዜጠኞችን በመካከሉ ጠርታልኝ ነበር ። በወታደራዊ ትጥቅ አዲስ ምልምል ወታደሮች መስለዋል ። ሁሉም ወጣቶች ናቸው ። በተሰጣቸው ትጥቅ ኮርተዋል ።

«እሺ ጓዶች ፣ የተደለደላችሁበትን ግንባር ሁላችሁም አውቃችኋል?» አልኳቸው ።

ሁሉም ያውቃሉ ። ከመካከላቸው ለቡድን መሪነት የተመ ረጡትን ልጆች ስም እየጠራሁ አስተዋወቅሁ ። ተቃውሞ አልነ በረም ። በጭብጨባ ተቀበሏቸው ፣ መንፈሳቸው ልቤን ነካው ። የጥሩ ወኔ መንፈስ ነበር ። ወደ ጦር ግንባሮች ለመሔድ የነበ ራቸው ጉጉትና ስሜት ከወጣት መልካቸው ላይ በጉልህ ተጽፎ ይነበብ ነበር ። በተፈጥሮዬ ስሜታዊ ነኝና ስሜቴ ተነካ ። ግን መናገር አልቻልኩም — «እሺ ልጆች ፣ ከእንግዲህ ግዳጃችሁን የምታውቁ ወታደሮች ስለሆናችሁ ምክር አያስፈልጋችሁም ። ግን በፈጠራችሁ አንገታችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ያዙ ። ይቅና ችሁ ። ቻው ። እናሸንፋለን» ብዬ ፊቴን ዞር አደረኩ ። እንባዬ መጥቶ ነበር ። ጥሩ አዋጊ መኰንን እንደማልሆን ገባኝ ፣ ወይስ አዛዥ መኰንኖችም የውጊያ ትእዛዝ ሲሰጡ እንደኔው ይሰማቸው ይሆን?..... ሌሎቹ ሲወጡ ፍሬው ዘሪሁን ወደኋላ ቀርቶ ሳቂታ ፊቱን ፣ ዓይኑን ፣ ጥርሱን እቁለጨለጨብኝ ።

«ገንዘብ እንዳትለኝ ብቻ አንተ ሰውዬ» አልኩት ። «አሁን አያስፈልገኝም ። «ሚሊ. ድራፍት» ይጠብቀኛል»

አለኝ ።

«ታዲያ ምንድነው?» አልኩት ።
«ከመሔዴ በፊት አንድ ነገር ልንገርህ ብዬ ነው.....»
«ቀጥል» አልኩ ።
«ጋሼ ሁኔታህ ደስ አላለኝም.....»
«የቱ ሁኔታዬ ልጄ!» አልኩት ።
እንቅልፍ አጥቶ ያደረው ዓይኔ ቀልቷል ።

«ከዚያች ፊያሜታ ጊላይ ከምትባለው ልጅ ጋር ተጣብቀህ መቅረትህ አሳዝኖኛል» አለኝ ።

«የት ታውቃታለህ?!» አልኩት ገርሞኝ ።
«ምን እኔ ብቻ ፣ ከተማው ሁሉ ያውቃታል» አለኝ ።
«በምን»

«ለስንቱ ቤት መፍረስ ምክንያት የሆነች አጫራሽ ናት ይላሉ ። በአሥመራ የታወቀች ናት ። እንዱን ስትቀበል ፣ ሌላ ውን ስትሸኝ ትኖራለች ይባላል ። ስንቱን ቤት ያፈረሰች ስን ቱን ጀግና ሽጉጥ ያግዘዘች ፣ ስንቱን ጤነኛ ሰው አሳብዳ ያስ ቀረች ሴት ናት ይላሉ ። ድሮ ከአሜሪካኖች ሥር አትጠፋም ነበር ይባላል ። አሁን ደግሞ ከመሐል አገር ሰዎች አትለይም ። አደገኛም ልትሆን ትችላለች ። አስብበት» አለኝ ።

«ስለእሷ ሌላ የምታውቀው ነገር አለ?» አልኩት ።
«በአሥመራ ሴቶች ጉዳይ ኤክስፐርት ነኝ» አለኝ ።
«ከንቲባ አይደለህ»።
«እውነቴን ነው.....»
«እሺ ፣ ስለአሥመራ ሴቶች ንገረኝ» ብዬ ጋበዝኩት ።
ከንቲባ ጊዜ አላጠፋም ። ጊዜ የሚያጠፋ ሰው አይደለም ።

«ስማ ልንገርህ ፣ የአሥመራ ሴቶች ጥቅምና ጉራ ነው እንጂ ፍቅር የሚባል ነገር አያውቁም ። የሚወዱህ መስለው ቢታዩህ እውነት አይምሰልህ ። ንጹህና ግልጽ መስለው ይቀር ቡሀል ፣ የውሸት ፍቅር ያሳዩሀል። በውሸት ፍቅር በጣም የተካኑ ናቸው ። ጉራቸው ደግሞ አይጣል ነው ። እገሌም እገሌም ፣ ያም ፣ ይሀም ደህናው ሰው ሁሉ የኔ ነው ወይም ነበር ማለት ይወዳሉ።

ባንድ በኩል ፍቅር እያሳዩህ በሌላ በኩል ሊያስቀኑህ ይጥራሉ ። ይጨቀጭቁሀል ። እረፍት አይሰጡህም ። ይጠራጠሩሀል ። ቅናት ያደረባቸው አስመስለው ያስቃዩሀል ። ይህ ሁሉ ከልብ አይደ ለም ። ሠሽታቸውን ነው ። ጥሩ አክተሮች ናቸው ። ሞኝ ሞኙ ወጥመዳቸው ውስጥ ገብቶ ይቀራል ። ደምህን መጥጠውና አጥንትህን ግጠው እስኪጨርሱህ ድረስ አይለቁህም ፤ እንደ መሽገር ይጣበቁብሀል ። አንተ ብትሔድ የት እገባለሁ? ምን ይውጠኛል? ከእንግዲህ ፍቅር የሚባል ነገር ሲያልፍም አይነካ ኝም ፤ እንዴት እሆናለሁ? ለምን ጥለኸኝ ትሔዳለህ? ይሉሀል ። እውነት መስሎህ ማዘን ትጀምራለህ ፤ ልብህ መከፋፈል ይጀም ራል ። ቀስ ብለው ደግሞ ፤ «ሚስትህ ወይም እጮኛህ ከኔ የበ ለጠ አንተ ላይ ምን መብት አላት? እኔም እወድሀለሁ ፤ አፈቅር ሀለሁ ማለት ይጀምራሉ ። ዓላማቸው ግልጽ ነው ። አንድም ልብህን ሰልበው ሊግጡህ ፤ ሁለትም ከሚስትህና ከእጮኛህ ሊያስጥሉህ ነው ። የአሥመራ ሴተ ላጤዎች አንድን ወንድ ከሚስቱ ወይም ከእጮኛው ማስጣል እንደ ትልቅ ጀብዱ ይቆጥ ሩታል ። እይ! ስንቱን ወንድ ከሚስቱ ያስጣለች ወይም ያጣላች ናት መባል ደስታቸው ነው ።

«የምታወጣት ሴት ብቻዋን ብትግጥህ እንኳን አንድ ነገር ነው ። ማታ ማታ እንደ ጅብ እየተጠራሩ ይረባረቡብሀል ። የመሐል አገር ሰው ይሉኝታ ፤ ጉራና ፍቅር ስለሚያጠቃው ተበ ድሮም ሆነ ተራቁቶ ፤ አጭበርብሮም ሆነ ጉቦ በልቶ ለሷም ሆነ ለጓደኞቿ በየምሽቱ ግብዣ ማቅለጥና ስጦታ ማሽጎድጎድ ፤ የጠ የቁትን ሁሉ ለመፈጸም ቃል መግባት ይጀምራል ። አንዷ ሥራ አስገባኝ ትለዋለች ። ቃል ይገባል ። ሌላው ፓስፖርት እባክህ ትለዋለች ፤ ቃል ይገባል ። ሦስተኛዋ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ዝውውር እፈልጋለሁ ትለዋለች ፤ ቃል ይገባል ። ሌሎቹ ወንድሟን ወይም እህቷን ወይም እኅቷን አስፈታልን ይሉታል ፤ ቃል ይገባል ። የማያስገቡት ቃል የለም ።

«ምስኪኑ ሰው በሚያወጣት ልጅና በጓደኞቿ ችግርና እሳብ ሁጠመዳል ። ብረትን በግለቱ እንዲሉ ጊዜና ፋታ አይሰ ጡትም ። ሰውዬው ሥራውንና ኃላፊነቱን እርግፍ አድርጎ ትቶ ስለሚወዳት ልጅና ስለጓደኞቿ መጨነቅ ይጀምራል ። የወደደ ሰው ዓይን የለውም ። ጓደኞቿ ተሰባስበው አጥንቱን እየጋጡ

ትና በልባቸው እየሳቁበት ስለሚወዳት ልጅ ዝናና ውበት ሊጋ ነው ያሚውቱታል ። ያግሉታል ፣ ያሳብዱታል ።

«አንዳንድ ሞኝ የመሐል አገር ሰው እውነት መስሎት ሚ ስቱንና ልጆቹን ወይም እጮኛውን ይከዳል ፣ እነሱም ቢሆኑ አያርፉም ። የቤቱን አድራሻ ፈልገው ፣ ወይም በሰው አድርገው ከሚስቱና ከእጮኛው ጋር ያጣሉታል ፣ ያፋጁታል ። ድሮው ንም የላላ ጋብቻ ከሆነ ባንድ ጊዜ ይፈርሳል ። መሠረት ያለው ጋብቻ ከሆነ መንቃንቅ ይጀምራል ።

«ግጠው ከጨረሱት በኋላ ወይም መሔጃው ሲቃረብ ምን ያደርጉታል መሰለህ? ልጅቷ ከመሬት ተነስታ መነጫነጭ ፣ ማኩ ረፍ ፣ ሁለተኛ ዓይንህን አላይም ማለት ትጀምራለች ። ጓደኞቿም አንድ ባንድ ይሸሹሀል ። መሔጃዬ ስለተቃረበ ይሆናል እንዲህ የምትሆነው ብለህ በማዘን በይበልጥ ልታስደስታት ትሞክራ ለህ ፣ እስከ መጨረሻ ማንቲምህ ድረስ።ግን ምንም ቢሆን አትተ ውህም ፣ ምክንያት ፈልጋ ፣ ፍቅርና ቅናት ያደረባት አስመስላ በመጨረሻ ትጣላሀለች ። አንተ ገንዘብህን ከስክሰህ ጨርሰህ ፣ በሺ ብር የሚቆጠር እዳ ውስጥ ተነክረህ የሰው መሳቂያና መሳ ለቂያ ሆነህ ፣ ስለተለየሀት ተናዳ ነው የተጣላችኝ እያልክ በልብህ አዝነህ ስትሔድ እሷ በሆዷ ትስቅብሀለች ። በመጨረሻ ሆነ ብለው የሚጣሉህ ወደውህ ሳይሆን ለተንኮላቸው ነው ። ርካሽነ ታቸውን ለመሸፈን ነው ። ርካሾች ናቸው ። መውደቂያ ሳያበጁ ደግሞ የሚጣሉህ አይምሰልህ ፣ እዚሁ እያለህ ከሌላ ወንድ ጋር መውጣት የሚጀምሩም አሉ ። አስቀንተው ቀንድ ሊያስበቅሉህ ይጥራሉ ፣ አንዳንዶቹ ወንድ ሲጣላባቸው ደስታቸው ነው ። የመሐል አገር ሰው ሞኝ ነውና ሔዶ አምባጓሮ ያነሳል ። አንዳን ዶቹ ግን እንደ ወደዱህ የተለየሀቸው ለማስመሰል የማያደርጉት ሙከራ የለም ።

«እንደወደዱህ የተለየሀቸው ለማስመሰል የሚፈልጉት ለ ምን መሰለህ? ቤትህም ገብተህ እንዳታርፍ ነው ። እንድታስባ ቸው ነው — ለአዲስ ዓመት ፣ ለገና ለፋሲካ እያልክ ። ዋዛ ሰ ዎች አይደሉም ። አካሔዳቸው አይታወቅም ። የማር ውስጥ እባቦች ናቸው ። ለፍቅር ደንታ የላቸውም ። ፍቅር ምን እንደሆነ አያውቁም ። እነሱ የሚያውቁት ጥቅም ማሳደድ ብቻ ነው.....»

«ያዲሳባ ሴቶች ይምጡብኝ አቦ! ከመልክ መልክ ፥ ከጠባይ ጠባይ የታደሉ እመቤቶች ናቸው ። ከወደዱህ ይወዱሃል ፥ ከጠሉህም ያንኑ ያህል ነው ። ከጥቅም ፍቅርን ያስቀድማሉ ። በደመወዝ ሰሞን ጋብዘኝ የምትል ያዲሳባ ሴት የለችም ። በአፍንጫህ እስኪወጣ ድረስ ትጋብዝሀለች። ሌላም ጊዜ ቢሆን መቶ ገርሆን ካየች ዝም አትልህም ፥ ያላትን መዛ ትሰጥሃለች ። የአሥመራ ሴተ ላጤዎች ግን ምን ቢናሩቸው አምጣ ነው እንጂ እንካ የሚባል ቃል አያውቁም ። ቀዳዳ ግንቲም አትወጣቸውም ። ግፋ ቢል ያንን የትግሬ ሽር ይጋብዙሀል ፥ ለሱም በስንት ልመና ። እጃቸውም ሆነ ልባቸው አይፈታም ። አንድ ቀን ሆናልኝ መጽሐፍ ብጽፍ ፥ «ከአሥመራ ሴቶች ተጠንቀቁ!» የሚል መጠሪያ ብጤ እጽፍ ነበር» ብሎ ስለ አሥመራ ሴቶች ጠባይ አጫወተኝ ።

«ብዙ አቁስለውሀል መሰለኝ?» አልኩት ።

«ብዙዎቹን ታዝቤአቸዋለሁ ። ግን ወጥመዳቸው ውስጥ አልገባም ። ይህን ሁሉ የምናገርህ እንድትጠነቀቅ ነው ። ጥቅም ማሳደድን እንጂ ፍቅር አያውቁም» አለኝ ።

«ከአጠቃላይ ነገር ተነስተን ሁሉም እንዲህ ናቸው ለማለት አንችልም ። እንዲያ የሚያደርጉ አንዳንድ ሴቶች ይኖሩ ይሆናል ። ሁሉም አይደሉም ፥ አይመስለኝም» በማለት ልከራከረው ሞከርኩ ።

«ቆይ ታያለህ ። ከጎንህ ታገኛቸዋለህ ። በተለይም ያንተዋ ልጅ የመሐል አገር ወንዶችን በማግባባትና በማታለል የታወቀች ናት ። ብዙ የመሐል አገር ወንዶችን ቀንድ ያስበቀለች ፥ ትዳር ያናጋች ፥ ሸጉጥ ያማዘዘች ሴት ናት ። ይቅርታ አድርግልኝና አትሞኝ ። አንተ ገር ነህ ፥ ልብህ ንጹህ ነው ። ቀና አስተሳሰብና ስሜት አለህ ። ለሰው ታዝናለህ ፥ በተፈጥሮ ሩህሩህ ነህ ። ወስላታ ሴት በንጹህ ስሜትህ ላይ ስትጫወት ለማየት አልፈልግም ። ይኸው ነው» አለኝ ።

ከንቲባ ሲናገር በጆሮዬ እያዳመጥኩት በልቤ ስለኔና ስለ ፈያሜታ ጊላይ ግንኙነት ነበር የማስበው ። እውነት ነው ፥ ሳይታወቀኝ ደሜ ውስጥ ገብታለች ። ቀን በስልክ ማታ በአካል

ከኔ አትለይም ። ተጣብቃብኛለች ፣ እኔም ሁኔታዋን በማየት ተጣ ብቄባታለሁ ። ከንቲባ እንዳለው በልማድና በስሜት ወጥራ ይዛ ልክ አስገብታኛለች ። ፍቅር ምንድነው? ልምድ ነው ፣ መለማመድ ነው ። ለምጄታለሁ ወይም ለማዳዋ ሆኛለሁ ። መለማመድ ያቆራኛል ፣ ትዝታን ያስከትላል ፣ መለያየት ስቃይ ይሆናል ። የመለማመድ ስቃይ መጥፎ ቅናትን በልብ ውስጥ ይጭራል ። እና የልማድ ባሪያና ተገዥ መሆን ይመጣል ። እዚህ ደረጃ ላይ ልደርስ ምንም አልቀረኝም ። ከንቲባ እንዳለው ስታታልለኝ ይሆን? ፈያሜታ ታታልለኛለች ብዬ ለማመን አቃተኝ ።

ከንቲባ እንዳለው እኔና ፈያሜታ አብረን መውጣት የጀመርን ሰሞን አንድ ወይም ሁለት ጓደኞቿ ከመኪናዬ ውስጥ አይጠፉም ነበር ። ተሳቢ ሬሞርኪ ሆነውብኝ ነበር ። ግን ስለምወዳት እወዳቸዋለሁ ፣ ስለማከብራት አከብራቸዋለሁ ፣ እሷን ማስደሰት ደስ ስለሚለኝ አስደስታቸዋለሁ ። ይህን የማደርገው ለጉራ ወይም ለሌላ ነገር ሳይሆን ከፍቅር የተነሳ ነበር ። ሊያታልሉኝ ፣ ሊልጡኝ ሊያራግፉኝ ይሆን? በሆዳቸው የሚጋጥ አዲስ ጅል ተገኘ በማለት በኔ ኪሣራ እየበሉና እየጠጡ በሆዳቸው ይስቁብኝ ነበር ወይ? እንዴት እንዲህ ልታደርገኝ ትችላለች? ይሆናል ብዬ ለማመን አስቸገረኝ ። እውነት ነው ። ከንቲባ እንዳለው ጓደኞቿ በሙሉ ስለፈያሜታ ውበትና ዝና አጉልተውና አጋንነው ከማውራት ሌላ ወሬ የላቸውም ። በተዘዋዋሪ መንገድ እሷን በማግኘቴ እድለኛ መሆኔን ነገሩኝና በባሰ ሁኔታ ከእሷ ጋር ተጣብቄ እንድቀር ሊያደርጉኝ ፈልገው ይሆን? እናያለን ። ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፈያሜታ ተለውጣብኛለች ። እንዳለፈው ጊዜ ጓደኞቿን አትጠራም ። እንዳያቸውም አትፈልግም ። ከፍራፍሬ ጭማቂና ከወትት ሌላ አትጠጣም ፣ አትጋበዝም ። እኔም እንድጠጣ አትፈልግም ። ገንዘብ ሳወጣ ደስ አይላትም ። አዝናልኝ ይሆን ወይስ በግብዣ ላይ የማጠፋውን ገንዘብ ቆጥቤ እሷ ላይ ብቻ እንዳፈስ ፈልጋ የቱ ይሆን? ለጥቅሟ ስትል ይሆን የተጣበቀችብኝ? ወይስ ከእርሜኛዬ ልታስጥለኝና የጉራ መንገዣ ልታደርገኝ? የቱ ይሆን? ወይም ሁለቱንም ለማድረግ ፈልጋ ይሆን? ጥርጣሬ አደረብኝ ። ለማወቅ ፈለኩ ። እና ደግሞ ልትነግረኝ የማትፈልገው ነገር ምን ይሆን? መነሻነቷ ፣ ማኩረፍ ፣ ከኔ ጋር ሆና ባሳብ ጭልጥ ብላ መሔድ ጀምራለች ። ምን ይሆን?

«እንግዲያውስ አታውቃትም ። ይላሉ! ይባላል! የስም አጥ ፊዎች ወሬ ነው ። ይህ ከተማ ደግሞ በዚህ የታወቀ ነው ። ልጃገረድ አይደለችም ። ትወጣለች ። ግን የምትወጣው እንደ ሌሎች ሴቶች ጋቢ ተጀቡና ሳይሆን ፊት ለፊት ነው ።» አልኩት ።

«እንደፈለክ ። በፍቅር ረገድ እኔ የማምነው በ፡አ፡አ፡አ፡ሊ. ነው» አለኝ ።

የፍቅር ማእከል ተፈጠረ እንዴ! «አልኩና ቀልዴን— መኢሠማ ፣ መኢገማ ፣ አኢሴማ ፣ አኢወማ ፣ ኢሠፓአኮ ፣ ሁገአዘ ፣ ገማገል ፣ ወዘተ ..... እያሉ በም ሕጻረ ቃላት መናገር የጊዜያችን 'ፋሽን' እየሆነ መሔዱ ትዝ ብሎኝ ።

«አግኛቸው ፣ አምጣቸው ፣ አስደስታቸው ፣ አባራቸው ማለት ነው ። እኔ በዚህ ነው የማምነው ። እነሱም ቢሆኑ እንዲህ ዓይነቱን አያያዝ ይወዳሉ — የምድር ጨው» አለ ።

ሴቶችን የምድር ጨው እያለ መጥራት ይወዳል ። ለእሱ ሴቶች ሁሉ የምድር ጨው ናቸው ።

«አይ ከንቲባ! ይህ ከተማ ያላንተ ምን ይሆናል?» አልኩት ።

«መሔዴን ሳሥመራ ምድር ጨዎች ሁሉ ንገርልኝ — በራዲዮ..... ከንቲባ ከድል በኋላ ተመልሶ ይመጣል በላቸው..... ቻው» አለ ።

«ከንቲባ ፣ ራስክን ጠብቅ ። እሺ? » አልኩት ።

ከንቲባ ጥርጣሬ አሳድሮብኝ ሐደ ። ብከላከልላትም ከጥር ጣሬ ፈጽሞ ነጻ ለመሆን አልቻልኩም ። በእርግጥ ሰዎች እንደ ሚሏት ትሆን? ስለጠባዩዋ ተጋኖ ሊወራ ይችላል ። ሰው ከሰው ራስ አይወርድም ። በዓይኑ ውስጥ ያለውን ግንድ ትቶ በሌላው ሰው ዓይን ውስጥ ስላለው ጉድፍ ያወራል ። በሌላ በኩል እሳት ከሌለበት ጢስ አይታይም ይባላል ። ቢሆንም የጀመርነውን ጨዋታ ፣ ጨዋታ ከሆነ ፣ ልቀጥልበት ፈለኩ ። እንገቴ ድረስ ከገባሁበት በኋላ ለምን አጵርጠዋለሁ? ወይም ፣ ምናልባት አንድ ወይም ሁለት ትምህርት አገኝበት ይሆናል አልኩ ። እስተሳሰቤ ትክክል እንዳልሆነ አላጣሁትም ምናልባት ከእሷ ጋር ፍቅር ይዞኝ ይሆናል ። ለዚህ ይሆናል በትክክል ማሰብ

ያታተኝ ። የያዘው ሰው በትክክል አያስብም ይባላል ። ፍቅር የሌለ ፀመል ያወጣል ፣ ትልቁን ሰው ትንሽ ፣ ጨዋውን ባለጌ ፣ ኩሩውን ወራዳ፣ ጭምቱን ቅብጥብጥ ፣ ብልሁን ሞኝ ፣ ዝምተኛውን ተናጋሪ ፣ ዓይናማውን እውር ያደርጋል ፣ ይሉኝታ ያሳጣል ይባላል ። ፍቅር አንድን ሰው የማይሠራው ሥራ የለም ። በተቃራኒው ፈሪውን ሰው ልበ ሙሉ ጀግና፣ ባለጌውን ጨዋ ፣ ስስታሙን ቸር ፣ ሞኙን ብልህ ፣ ለፍላፊውን ዝምተኛ ፣ ሴሰኛውን ቆራቢ ፣ ቅብጥብጡን ጭምት ሊያደርግ ይችላል ። እኔን ምን ሠርቶኝ ይሆን? አልኩ ። አላውቅም ። ስለራሴ ለማወቅ ፈለኩ ። እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ራስን ማምኘት ነው ሊባል ይችል ይሆናል ። ይሁን ። ወደ ኰሎኔል በትሩ ቢሮ ደወልኩ ። ጸሐፊው ላስቸኳይ ጉዳይ ወደ አዲስ አበባ ድንገት ተነስቶ የሔደ መሆኑን ነገረኝ ።

«መቼ ይመለሳል?»
«አላውቅም ጌታዬ.....»
«በጣም ለሚያስቸኩል ብርቱ ጉዳይ ነበር.....»
«የሚመለሱበትን ቀን አልነገሩኝም ጌታዬ.....»

ስልኩን ዘጋሁት ። የሕዝብ ደኅንነት ሰዎች ማንኛውንም ነገር በምስጢር ነው የሚይዙት ። ዜና ቢላከላቸው እንኳን ምስጢር! ብለው በሚስጥር ፋይል ያኖሩታል ። ስለ ጋራዲዞ የደረሰኝን ጥቆማ ለማን እንደምነግረው ጠፍቶኝ ዝም አልኩ ። ለማይሆን ሰው ነግሬ ባለማወቅ ወይም በጀብደኝነት ጠላትን እን ዳናንቃ በመስጋት ኰሎኔል በትሩን መጠበቅ የግድ ሆነብኝ ። ሌላ የማደርገው ነገር አልነበረኝም ።

ቀን መጣ ። ቀን ሔደ ። ሮማን የላከችልኝ የቴፕ ክር ደርሶኝ እንደሆነ ለመጠየቅ ስልክ አድርጋልኝ ነበር ። የቴፕ ክሩ ደርሶኛል ። ግን ለዚህ ብቻ አልነበረም ስልክ የደወለችው ። እሥመራ የምትመጣበትን ቀን ልትነግረኝ ነበር ። ወደ ጦር ግንባር ለመሔድ እንደ ተዘጋጀሁና ፣ በማንኛውም ቀን ከዚህ ልነሳ እንደ ምችል ነገርኳት ። በእውነት ፣ አልዋሸኋትም ። ወደ ጦር ግንባር ለመሔድ ተዘጋጅቼ ነበር ። መቼ እንደምሔድ እስኪነገረኝ ብቻ ነበር የምጠባበቀው ። ጦርነቱ በማንኛውም ቀንና ሰዓት ይጀምራል ተብሎ ይጠበቅ ነበር ። እና የሁሉም ጆሮ ወደ ናቅፋ

አተኩሮአል ። በሁሉም ቦታ ውጥረት ሰፍኖ ነበር ። ቀይ ኮከቦች ፊት ላይ ጭንቀት ይነበባል ። የጓድ ሊቀ መንበሩን ፊት ለማየት የማይቸኩል ጓድ አልነበረም — የዕለቱን ታሪክ ለማንበብ ። የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ዕለታዊ ታሪክ ፣ ድሉና ሽንፈቱ ፣ ደስ ታውና ኃዘኑ ፣ ተስፋውና ብሶቱ ፣ መፍትሔውና ችግሩ እንዳለ ተመዝግቦ የሚታይበት ፊት ነው ።

የአሥመራ ከተማ ኗሪዎች ሰሞኑን ምን እንደሰሙ አይታ ወቅም በጊዜ ወደ ቤት ገብተው እንደ ዶሮ መስፈር ጀምረዋል ። ከተማው ጭር ብሎ ይታያል ። የአሥመራ መንገዶች የኔና የፊያ ሜታ ጊላይ ብቻ ነበሩ ። እንደወትሮ ካራቪል ባር ሬስቶራንት ደጅ የመኪናዎች ሰልፍ አይታይም ። አታገኝና ውሾቿ ብቻ ነበሩ መንገድ ላይ የሚታዩት ። አታገኝና ውሾቿ ከካራቪል ደጅ አይጠፉም ። አታገኝ እብድ ሴት ናት ። «ከሰው ውሻ ይሻ ላል! » እያለች ስትጮህ ታድራለች ። ቡችሎቹንም በቅርጫት ይዛ ትዞራለች ። ውሾቹ በሔደችበት ይከተሏታል ። ከበዋት ይተ ኛሉ ። እነሱ እያሉ ማን ወንድ ደፍሮ ይነካታል—በጫጭቀው ይጥሉታል ። አታገኝ በጣም የምትወደው ሰው ነበራት ይባላል ። ከሕይወቷ አስበልጣ ስትወደውና ከራሷ አብልጣ ስታምነው ከዳት ። እና አበደች ። «እኔ ሰው አልወልድም! የውሻ እናት በሉኝ!» ትላለች።አንዳንዴ አላፊው አግዳሚው ዝም ብሎ ሣን ቲም ይጥልላታል ። ቆንጆ ድምጽ አላት ።

«ምነው ዘጋኸኝ? እኔ እንኳ አልዘጋሁህ» አለችኝ ፊያሜታ ።

ከሰው ውሻ ይሻላል ትላለች ፣ ማን ይኸውና ያለሰው መኖር አትችልም ፣ ያለ ሰው ማን ሊኖር ይችላል? ምናልባት እግዜርም ራሱ ያለ ሰው ሕልውና የለውም እያልኩ ስለእብዷ አታገኝና ስለ ፍልስፍናዋ ሳስብ ነበር ። ዝም ስላት አትወድም ። መላ አሳ ቤና ትኩረቴ ወደ እሷ እንዲሆን ትፈልጋለች ። ዝም ስል ስለ ሮማን የማስብ ይመስላታል ። እና ነገር ትጀምረኛለች ።

«ምን ሆንሽና ትዘጊኛለሽ? » አልኳት ።

«አንተ የምትሔድበትን ቀን እያሰብኩ ፣ እንደ እርጉዝ ቀን መቁጠር ሰለቸኝ አባቴ ይሙት ። አይ ይህ ቀይ ኮከብ ዘመቻ!» በማለት ዕድሏን አማረረች ።

ከሰምኑ ቀልድና ሳቋ ጠፍተው ከኃዘን አገር የመጣች እንግዳ መስላለች ።

«እናገ» አልኳት ።

«እና ፥ እንተን የሚያስረሳኝ ወንድ መፈለግ አለብኝ ። አንተም ወደ እጮኛህ» አለችኝ ።

«ይህ ኖርአልገ» አልኩ ።

ከቅርብ ቀኖች ወዲህ የውሸት ኩርፊያዋን ትታ ማምረር ጀምራለች ። አዝን ፥ ትክዝ ፥ ፍዝዝ ፥ ድንግዝ ትላለች ። እኔ እንዳነጋግራት የምትፈልገውን ያህል ፥ እሷ አንዳንዴ በከባድ ዝምታ ተውጣ ፥ ትክዝ ፥ ፍዝዝ ፥ በማለት እንደእዲስ ሰው ለረ ጅም ጊዜ አተኩራ ታየኛለች ። እንዲህ ስትሆን በፍቅር ዓይን እንደምታየኝ ይሰማኛል ። እሷን ዘልቄ ለማየት እየፈለኩ እጨ ነቃለሁ ።

«አሁን ገባኝ ። ልትተይኝ አሰበሻልገ» ብያት ቀልድ ጨመ ርኩበትና «እናንተ መቸም ፍቅረኛ ቀርቶ እግር ትከዱ የለ!» አልኳት ።

ቀልዴ በጣም አሳቃት ።

«አዎ ፥ እንዲህ ስትስቂ ነው ደስ የምትይው ። ኃዘን አያምርብሽም» አልኳት ።

«ከእንግዲህ አልስቅም ፥ አባቴ ይሙት ......»

«ለምን ፈያሜታ»

«አይገባህም እባክህ ። ወየ እኔ ግዲ!» ብላ ከንፈሯን በኃዘን መጠጠችና «ልከዳህ የማስብ ይመስልሀልገአስቲ እጄን ምታኝ» አለች ።

«ታዲያ ምንድነውገ» ብዬ እጅዋን መታሁ ።

«ትገርማለህ እባቴ ይሙት! ደደብ» አለችኝ ።

«ሌላ ምን አለገ ንገሪኝ» አልኳት ።

«አልነግርህም......»

«ከኔ የምትደብቂው ነገር አለገ እንዴት ፈያሜታ ይኸው ነው የኔና ያንቺ ነገርገ» አልኳት ።

«የራሴ ችግር ነው ። እኔው ራሴ እወጣዋለሁ» አለች ።
«ምንም የምረዳሽ ነገር የለም ማለት ነው?»
«ምንም» ብላ እንባዋን አፈሰሰች ።

ሳልጠይቃት ዝም ብዬ ግረረፌያ ቤቴ ወሰድኳት ። እሷን አሲመጠየቅ ይሻላል ። የጠየቋትን ነገር እሺም እምቢም አትልም ። ታስጨንቃለች ። አትቆርጥም ። አትወስንም ። ከወስኑ ሳት ግን ምንም አትልም ። እሷም ብትሆን ተቃውሞ አላነሳችም ። ስለምትሔድበት ቦታ ሳይሆን ስለችግሯ ነበር በይበልጥ ስታስብ የነበረው ። ስለምትሔድበት ሥፍራ ደንታ አልነበራትም ። በሌላ በኩል ደግሞ ከኔ ለመለየት የፈለገች አልመሰለኝም ፣ ቅርቤ ለመሆን የምትፈልግ መሆኗ ተሰማኝ ። ያን ምሽት የሕይወት ራብ ድንገት የተሰማት ይመስል አልጋ ላይ ተስገብግባ ነበር ። ጨካኝና «ሳዲጅ» ሆና ነበር ። ለመበጠስ ከደረሰ የሕይወት ቀጭን ክር ላይ ተንጠላጥላ ለመዳን ይመስል ባለ በሌለ ኃይሏ ትሟጥጥ ነበር ። ከጣፋጭ ሲቃይ የስሜት ምንጭ የሚፈልቅ እንባም ታፈስ ነበር ። ሮማን የላከችልኝ የአስቴር ዘፈን ጣልቃ ገብቶ በመካከላችን የነበረውን ጥሩ ስሜት ባያደፈርሰው ኖሮ ፣ ችግሯ ምን እንደሆን ልጠይቃት ነበር ። እና እንደምትነግረኝም እርግጠኛ ነበርኩ ።

«ምነው እግር አወጣህ እንዴት ፈረደብኝ
«ያም አንተን ያም አንተን እዬ ጉድ በዛብኝ
«ወዴት ነው መዋያህ ፈራሁ እኔ እንጃልኝ
«ዓይን በዝቶብሀል ሸሽግ በልልኝ______

ፊያሜታ ዝም ብላ ዘፈኑን ትሰማ ነበር ። አንዱ ዘፈን አልፋ ሌላው ቀጠለ ። ከሩ ቴፕ ሪኮርደሩ ላይ እንደተጠመደ በመርሳቴ ራሴን ረገምኩ ።

«ሙናዬ ሙናዬ
አንተ ነህ ገላዬ
እየዋለ ሲያድር ፍቅርህ እየለብኝ
ጤና አሳጥቶኛል መውደድህ በዝቶብኝ
ስወድህ ውደደኝ ጠበቅ አ'ርገህ ያዘኝ
አልችልም ብቻዬን ፍቅርህን አግዘኝ

ፍቅርህ አሸነፈኝ መውደድህ የረባኝ
አይዞሽ በለኝ እንጂ ተው አታንገላታኝ
አንተ ነህ በሽታዬ የጎዳኝ ፍቅር ነው
አልችልም ብቻዬን ብታግዘኝ ምነው?.....

እንደፈራሁት አልቀረልኝም ።

«ይህን ዘፈን ከየት አመጣሽው?» ብላ ጠየቀችኝ ። ልዋሻት አልቻልኩም — «እጮኛዬ ናት የላከችልኝ» አልኳት ።

ከአልጋው ላይ ዘላ ወርዳ..... ከሩን መዛ ፣ መዛ ፣ ቦጭቃ ቦጫጭቃ ወለሉ ላይ ከመረችው ። በዚህም አልበቃትም ። ተቦጫጭቆ የወደቀውን ከር አፍላ ፊቴ ላይ በተነችው ። እና ልብሷን መልበስ ጀመረች ። ራቁቷን ነበረች ። በንዴቷ ላይ የተናደደች አግልከት መስላ ታየችኝ ።

«የት ልትሔጂ ነው?»
«ቤቴ..........»
«ሰዓት አላፈውስ?»

ከምሽቱ አምስት ሰዓት ከሩብ ሆኖ ነበር ። አሥመራ በር ንድ ካልሆነ በቀር ከአምስት ሰዓት በኋላ ንቅንቅ ማለት አይ ቻልም ። ወንበር ስባ ቁጭ ከማለት ሌላ የምታደርገው ነገር አ ጣች ። እኔም ተነስቼ ከአልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ አልኩ ። ሁለ ታችንም በጭንቀት ተውጠን ቀረን ። እዚህ ጣጣ ውስጥ እንዴት እንደገባሁ ነበር የማስበው ። ግን በይበልጥ ያሳስበኝ የነበረው በገዛ እጇ ከገባሁበት ጣጣ መውጫ ቀዳዳ ማጣቴ ነበር ። እሷም በበኩሏ ምናልባት እኔን ያወቀችበትን ቀን በልቧ ትረግም ነበር ። እኔም በራሴ ፣ እሷም በራሷ ሐሳብ ተውጠን ምንም ሳንባባል ቆየን ። እንደ እጡነቱ ከሆነ ጭንቅላቴ ዝም ብሎ ይዞኝ ነበር እንጂ ምንም የተጨበጠ ነገር አላስብም ነበር ። ጊዜውም ሔደ ።

በመጨረሻ በረጅሙ ተነፈስኩና ፣ «እባክሽ ስሚኝ ፊያ ሜታ ። በቂ ጊዜ አልሰጠሺኝም ። ለማሰብ ጊዜ አላገኘሁም ። እንደ እውነቱ ከሆነ ምን እንደማስብም አላውቅም ። ትንሽ ጊዜ ስጪኝ» አልኳት ።

«የምሰጥህ ጊዜ የለኝም ። ቢኖረኝ ደስ ይለኝ ነበር» አለች ።

«ምን ማለትሽ ነው? ለኔ እንዴት ጊዜ ታጭያለሽ? አብረን ያሳለፍነውን ውብ ጊዜና ጣፋጭ ትዝታ እንዲሁ ባንድ ጊዜ ከልብ አውጥቶ መወርወር አይቻልም ፤ ወይስ እንዲህ ለማድረግ የሚችል አንጀት አለሽ? እስቲ ንገሪኝ?» አልኳት ።

ምንም አልነገረችኝም ። ይልቅ ፤ «መቼ ነው የምትሔደው» ብላ ጠየቀችኝ ።

«የት?»
«ወደ ጦር ግንባር.....»
«አላውቅም ። ምናልባት ነገ ከነገ ወዲያ.........»
«ቶሎ ብትሔድ ጥሩ ነው ። ችግሬን ያቃልልልኛል.....»
«እኔ ነኝ ችግር የሆንኩብሽ?»
«ደደብ» አለችኝ ።

«ለኔም ጥሩ ነው ። ለማሰብ ጊዜ አገኛለሁ ። ለክፉም ሆነ ለደግ ከሚወዱት ሰው ትንሽ ራቅ ብሎ የማሰብ እድል ማግኘት ይጠቅማል ። ርቀት ፍቅራችንን ያጠናክራል ወይም እውነቱን ግልጽ አድርጎ ያሳየናል ። አይመስልሽም?» አልኳት ።

«ደደብ» አለችኝ ።

ብዙ ሙከራ አደረኩ ። ችግሯ ምን እንደሆነ ልትነግረኝ አልፈለገችም ። እና እንደገና ተቃቀፍን ። ጦርነትና ሠላም ። ምናልባት ወደፊት እንደዚሁ እንቀጥል ይሆናል — ሁልጊዜ..... ይህች ሕይወት.....

# ቀ ይ ት ር ኢ ት

## ና ቅ ፋ የ ደ ም ጎ ራ

### ምዕራፍ አራት

አርሚ አቪዬሽን ሜዳ እንድገኝ የተሰጠኝ ጊዜ በጣም አጭር ነበር ። ወታደራዊ ትእዛዝ ያለምንም ቅድሚያ ማስጠን ቀቂያ ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚሰጥበት ምክንያት አልገባህ እያለ ታንጾ ስላልተዘጋጀ ይሆናል ። ህዋሳቴ ቶሎ እሺ ብለው አጭር ትእዛዝ አይቀበሉም ። ጊዜ አልነበረኝም ። የተሰጠኝ ጊዜ ልብስ ለመለወጥ ብቻ የሚበቃ ነበር ። «ወቴ» ቀልድ አያውቅም ። ለጦር ሜዳ ተብሎ የተሰጠኝን ትጥቅ እንደ ነገሩ ታጠቅሁና እግረ መንገዴን ፊያሜታ ጊላይን ደህና ስንብች ለማለት ስልክ ደወል ኩላት ። አብረን ነበር ያደርነው ። ባለፉት ሦስት አራት ቀኖች ደግሞ አዲስ ጠባይ ማሳየት ጀምራለች ። እንደ በፊቱ አብረን የትም እንድንታይ አትፈልግም ። ቤቷም እንዳደርሳት ጨርሶ አትፈቅድልኝም ። «ላታዛልቀኝ ለምን ካንተ ጋር በየአደባባዩ እታያለሁ?» የሚል ምክንያት ልትሰጠኝ ትሞክራለች ። ግን ምክ ንያቷ ይህ እንዳልሆነ ይሰማኛል ፣ እሷ ደግሞ የእውነቱን ልትነግ ረኝ አትፈልግም ። የምትደብቀኝ ነገር ነበራት። ካላመነችብት ወይም ካልመሰላት ያው እንደ ሐማሴን ዘሮቿ ግትር ናት ። በመኪና ስንሔድ ፣ ጠፍቶባት በየመንገዱ የምትፈልገው ሰው ያለ ይመስል አሥሬ ትገላመጣለች ። ሰው ወደ መኪናችን ሲጠጋ ባየች ቁጥር ፣ ጠፍቷት ስትፈልገው የቆየችውን ፍጡር ድንገት ያገኘችው ይመስል ሰውነቷ ድንቁት ሽምቅቅ ይልና ትኩር ብላ ትመለከተዋለች ። ከዚያ በአካል አጠገቤ እያለች ባሳብ ጭልጥ ብላ ከአጠገቤ ትጠፋለች ። አይኖቿ ያዩኛል ። ግን በእውነት የሚ ያዩኝ አይመስሉም ።

«ሰው የጠፋብሽ ትመስያለሽ ። ማን ጠፋብሽ? እስቲ በ ሞቴ ንገሪኝ?» ስላት ፣ «እንጃ አባትህ ። ደደብ» የሚል መልስ ትሰጠኛለች ።

«የምሰጥህ ጊዜ የለኝም ። ቢኖረኝ ደስ ይለኝ ነበር» አለች ።

«ምን ማለትሽ ነው? ለኔ እንዴት ጊዜ ታጭያለሽ? አብረን ያሳለፍነውን ውብ ጊዜና ጣፋጭ ትዝታ እንዲሁ ባንድ ጊዜ ከልብ አውጥቶ መወርወር አይቻልም ፤ ወይስ እንዲህ ለማድረግ የሚችል አንጀት አለሽ? እስቲ ንገሪኝ!» አልኳት ።

ምንም አልነገረችኝም ። ይልቅ ፤ «መቼ ነው የምትሔደው» ብላ ጠየቀችኝ ።

«የት?»
«ወደ ጦር ግንባር.....»
«አላውቅም ። ምናልባት ነገ ከነገ ወዲያ..........»
«ቶሎ ብትሔድ ጥሩ ነው ። ችግሬን ያቃልልልኛል.....»
«እኔ ነኝ ችግር የሆንኩብሽ?»
«ደደብ» አለችኝ ።

«ለኔም ጥሩ ነው ። ለማሰብ ጊዜ አገኛለሁ ። ለክፉም ሆነ ለደግ ከሚወዱት ሰው ትንሽ ራቅ ብሎ የማሰብ እድል ማግኘት ይጠቅማል ። ርቀት ፍቅራችንን ያጠናክራል ወይም እውነቱን ግልጽ አድርጎ ያሳየናል ። አይመስልሽም?» አልኳት ።

«ደደብ» አለችኝ ።

ብዙ ሙከራ አደረኩ ። ችግሯ ምን እንደሆነ ልትነግረኝ አልፈለገችም ። እና እንደገና ተቃቀፍን ። ጦርነትና ሠላም ። ምናልባት ወደፊት እንደዚሁ እንቀጥል ይሆናል — ሁልጊዜ.... ይህች ሕይወት....

# ቀ ይ ት ር ኢ ት

## ና ቅ ፋ የ ደ ም ጎ ራ

## ምዕራፍ አራት

አርሚ እቪዮሽን ሜዳ እንድገኝ የተሰጠኝ ጊዜ በጣም አጭር ነበር ። ወታደራዊ ትእዛዝ ያለምንም ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚሰጥበት ምክንያት አልገባህ እያለ ታንጾ ስላልተዘጋጀ ይሆናል ። ህዋሳቱ ቶሎ እሺ ብለው አጭር ትእዛዝ አይቀበሉም ። ጊዜ አልነበረኝም ። የተሰጠኝ ጊዜ ልብስ ለመለወጥ ብቻ የሚበቃ ነበር ። «ወቴ» ቀልድ አያውቅም ። ለጦር ሜዳ ተብሎ የተሰጠኝን ትጥቅ እንደ ነገሩ ታጠቅሁና እግረ መንገዴን ፊያሜታ ጊላይን ደህና ሰንብች ለማለት ስልክ ደወልኩላት ። አብረን ነበር ያደርነው ። ባለፉት ሦስት አራት ቀኖች ደግሞ አዲስ ጠባይ ማሳየት ጀምራለች ። እንደ በፊቱ አብረን የትም እንድንታይ አትፈልግም ። ቤቷም እንዳደርሳት ጨርሳ አትፈቅድልኝም ። «ላታዛልቀኝ ለምን ካንተ ጋር በየአደባባዩ እታያለሁ?» የሚል ምክንያት ልትሰጠኝ ትሞክራለች ። ግን ምክንያቷ ይህ እንዳልሆነ ይሰማኛል ፤ እሷ ደግሞ የእውነቱን ልትነግረኝ አትፈልግም ። የምትደብቀኝ ነገር ነበራት። ካላመነችበት ወይም ካልመሰላት ያው እንደ ሐማሴን ዘሮቿ ግትር ናት ። በመኪና ስንሔድ ፣ ጠፍቶባት በየመንገዱ የምትፈልገው ሰው ያለ ይመስል አሥሬ ትገላመጣለች ። ሰው ወደ መኪናችን ሲጠጋ ባየች ቁጥር ፣ ጠፍቷት ስትፈልገው የቆየችውን ፍጡር ድንገት ያገኘችው ይመስል ለውነቷ ድንገት ሽምቅቅ ይልና ትኩር ብላ ትመለከተዋለች ። ከዚያ በአካል አጠገቤ እያለች ባሳብ ጭልጥ ብላ ከአጠገቤ ትጠፋለች ። አይኖቿ ያዩኛል ። ግን በእውነት የሚያዩኝ አይመስሉም ።

«ሰው የጠፋብሽ ትመስያለሽ ። ማን ጠፋብሽ? እስቲ በሞቴ ንገሪኝ?» ስላት ፣ «እንጃ አባትህ ። ደደብ» የሚል መልስ ትሰጠኛለች ።

«ታዲያስ ፌያሜታ?» አልኳት ።

«ለምንድነው ደግሞ ዛሬ ወታደሩ ኋላውን ያዞረብን?» አለችኝ ።

ወታደሮች በየአውራ መንገዶች ተሰልፈው ነበር ። ወታደሮች «ኋላቸውን» ወደ መንገድ አዙረው ሲቆሙ ፣ የአሥመራ ሕዝብ አንድ ታላቅ እንግዳ ይሔዳል ወይም ይመጣል የሚል ግምት አስቀድሞ ያሳድራል ።

«ጸጋዬ ይሔዳል ሲሉ ሰምተው ይሆናል» በማለት ቀለድኩባትና ፤

«እውነት ፌያሜታ አሁን ወደ አፍአበት መሔዴ ነው ። አሁን ነው የተነገረኝ ። ልሰናበትሽ ነው የደወልኩት» አልኳት ። በመጀመሪያ አላመነችኝም ።

«እውነቴን ነው ፌያሜታ ሙች ። ያንቺ ውሸት የተጋባብኝ መሰለሽ እንዴ? መሔዴ ነው ። በወታደር ልብስ ብታይኝ ሌላ መሰያለሁ» አልኳት ። ዝም ብላ ቆየችና ፣ «በወታደር ልብስ ላይህ አልፈልግም — አባቴ ይሙት » አለች ።

«ለምን?»

«እነሱ ሁልጊዜ ደሀና ሁኑ እንዳሉ ነው» አለች ።

«ብዙ ወታደር ወዳጆች ነበሩሽ መሰለኝ!» አልኳት ድንገት ብልጭ ብሎብኝ ። ቅንዓት በስለታም ጥርሱ ልቤን መብላት ጀምሮአል ። ቅንዓት — የፍቅር እሳት! የፍቅር ጢስ! «አንቴን ከማወቄ በፊት ለሆነው ምን ያገባሀል?» አለችኝ።ልክ ነበረች ። እኔን ከማወቋ በፊት ያደረገችው ነገር አያገባኝም ። ቢሆንም አንድ ወንድ ለክብሩ ያለውን ቀናኢነትና ለቤቱ ያለውን ቅናት ያለፈው ታሪክ መጋረጃ አብዛኛውን ጊዜ ሊጋርደው አይችልም ። ያለፈውም ነገር ያስቀናል ። መጀመሪያውኑ ለምን የገባ አል ነበረችም! ከሌሎች ወንዶች ጋር ጨዋታዋ እንዴት ነበር ታስታውሳቸው ይሆን? ትዝታን በሰው ጭንቅላት ውስጥ መግደል አይቻልም ። ሁልጊዜ ይኖራል ። እና ቅናት ይፈጥራል ። ትክክለኛ አስተሳሰብ አይደለም ። ግን ቅናት አብዛኛውን ጊዜ ከትክክለኛ አስተሳሰብ ነው የሚመነጨው ያለው ግንወደ ፍቅር ሁልጊዜ የትክክለኛ አስተሳሰብ ሕግጋት ተከትሎ የሚሔድ ነገር ቢሆን ጣፋጭና ስቃይ ይሆን ነበር? አላውቅም.....

«ፈያሜታ፣ ስለችግርሽ በእውነት ልትነግሪኝ አትፈልጊም?» አልኳት ፣ መሐዴ ስለሆነ ምናልባት አሁን ትነግረኛለች በማለት ። ሆዴን እየቆረጠኝ መሐድ ደስ አላለኝም ።

«አንተም ወደ ጦር ግንባርህ ፣ እኔም ወደ ጦር ግንባሬ» አለችኝ ።

«ያንቺ ደግሞ የቱ ግንባር ነው?»

«የፍቅር ግንባር.........»

«ደህና ፣ ፍቅር ግንባር ላይ በድል እንገናኝ »

«የምንገናኝ አይመስለኝም ጓጋዬ» አለችኝ ።

«ምን ማለትሽ ነው?»

ድንገት ደግሞ ድምጿን ወደ ቀልድ ለወጠችና ፣

«ድል ተገኘ ። ያሥመራ ቤቶች ተጻረሱ ። ሥጋ አለቀ ። ከዚያ በኋላ ቀይ ኮኮቦች ምን ይጠብቃሉ? እንዳልከው ፈትለክ ነው!» አለች ።

እምርሬ «ፈያሜታ ቀልዱን ተይና እውነቱን ንገሪኝ» አልኳት ።

«ስትመለስ ትደርስበታለህ» ብላ በኃይል ስልኩ ላይ ተንፈሰችና፣ «ከናትፉ የምታመጣልኝ ነገር አለ አባቱ ይሙት» አለች።

«ምን?......ንገሪኝ»

«ድል ።»

«ስለእሱ አትጠራጠሪ» ብያት ልቤ እንደ ድንጋይ እየከበደኝ ፤

«ፈያሜታ ፣ ልትነግሪኝ የማትፈልጊው ነገር እንዳለ አውቃለሁ ። ግን ምን ይሁን፤ ምንም የሚያሳዝነኝ ነገር እንዳማታ ደርጊ ተሰፋ አለኝ ። እንገናኛለን ። ደህና ሁኝ ማለት አልችልም ። አይትንአሲ እሺ እምባር....?» ብያት ተነስቼ ወደ አርሚ እቪዬሽን በረርኩ ። ስለፈያሜታ ነበር የማስበው ። አንድ ወንድ ስለአንድ ሴት ሳያቋርጥ ማሰብ ሲጀምር ፍቅር ይዞታል ወይም ጭኝ ሆኗል ለማለት ይቻላል ። ሁለቱንም ነበርኩ ፣ ወይም መሰለኝ ። እሥመራዬን ፣ ውብ የዘምባባ ከተማዬን ፣ ናተይ ለሚናዊት ጽብቅቲ ፣ ወደኋላ ትቻት ስሔድ ልቤ ኃዘን ተጭኖት እንደ ድንጋይ ይከብደኝ ጀመር ። ከእሥመራም ጋር ፍቅር ይዞኝ

ነበር ። የሚገርመው ነገር አሥመራንና ፊያሜታ ጊላይን ለይቼ አላያቸውም ። ባሳቤ አንድም ሁለትም ሆነው ይታዩኛል ።

የአርሚ አቪዬሽን ሜዳ ንቅናቄ በዝቶበታል ። በየደቂቃው ተዋጊ አይሮፕላኖች ተከታትለው ይነሳሉ ፤ ተከታትለው መጥ ተው ያርፋሉ ። እንቶኖቮች ይነሳሉ ፤ ይወርዳሉ ። መሣሪያዎችና ወታደሮች ይጫናሉ ። አይሮፕላን ጠጋኞች ይጣደፋሉ ፤ የአየር ኃይል ተዋጊዎች ከነሙሉ ትጥቃቸው ይሮጣሉ ፤ ይሔዳሉ ፤ ይመጣሉ ። ሜዳው ድብልቅልቁ ወጥቷል ። አንዳንድ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችና የኃይል አዛዦችም ሜዳው ላይ ነበሩ ። ወደ አፍአበት የሚወስደኝ ልዩ አይሮፕላን እስኪዘጋጅ ነበር የም ጠብቀው ።

«የወታደር ልብስ ይቀበልሀል ጃል» የሚል ድምጽ ከበስተ ኋላዬ ሰማሁና ዞር አልኩ ። ኮሎኔል በትሩ ተሰማ ነበር ።

ሳየው ደስ አለኝ ።
«ሰሞኑን በጣም ስፈልግህ ነበር..........»
«አዲሳባ ነበርኩ ። አሁን ገና መግባቴ ነው» አለኝ ።

«እንኳን መጣህ.....»
«የት ልትሔድ ነው?»

«አፍአበት ። የታሸገ ኤንቨሎፕ ትቼልሀለሁ ። ወዴት እንደሚያመራህ አላውቅም ግን ጠቃሚ መረጃ ይመስለኛል ። ፓራዲዞ ስለሚባል አንድ ቡና ቤት ነው» አልኩት ። «ፓራ ዲዞ?» ብሎ ሲያስብ ቆየና ፤ «እሱማ መኖሪያ ቤቴ አካባቢ አይ ደለም እንዴ? ምንድነው እሱ?» አለኝ ።

«በጽሑፍ ትቼልሀለሁ ። ጊዜ የለኝም» አልኩት ።

ዓይኖቹ ከረጢት አብጅተዋል ። ድካም ይታይበታል ። ዕድሜውን መስሎአል ።

ጠጋ አለኝና ድምጹን ዝቅ አድርጎ ፤ «ቢርክራሲ ስለሚ ባል ሰው ሰምተህ ታውቃለህ?» ብሎ ጠየቀኝ ።
«ምንድነው እሱ?»

«የኮድ ስም ነው ። ስውዬው ግርማይ ፣ ኅይቶም ፣ ነራአዩ ፣ አፈወርቂ ሊሆን ይችላል ። ወይም በሁሉም ስም የሚጠቀም ሰው ሊሆን ይችላል ። እዚሁ አጠገባችን ያለ ሰው ሊሆን ይችላል። ብዙ ስምና መልክ ያለው ሰው ነው» አለኝ ።

«ምን የሚሠራ ሰው ነው?»
«በጣም አደገኛ ሰው ነው ካልኩህ ይበቃል.........»

ዕቁባይ ሲላ ትዝ አለኝ ። እሱ ይሆን? አልኩ በልቤ ወይስ ሥዕላይ? የአቦይ ተኽሌ ፍርሀት ሞት ፣ የሻለቃ ታደሰ ቀሪቾና የዕቁባይ አጠራጣሪ ግንኙነት ሁሉ ትዝ አለኝና ፤—

«ከዚህ በፊት ስለሻለቃ ታደሰ ቀሪቾ የሰጠሁህን መረጃ ምን አደረስከው?» ብዬ ጠየኩት ።

«በጥብቅ እየተከታተልነው ነው ። ከትትሉ ጥንቃቄ ያስፈ ልገዋል ። የጅብ ችኩል መሆን የለብንም ። ሙሉ ሥዕል የሚ ሰጠን መረጃ ካላገኘን አንድ ወይም ሁለት ሰው መያዝ ሌሎቹን ማስበርገግ ይሆናል ። አትስጋ ። እሱን ለኔ ተውልኝ» አለኝ ።

«አመራርህ ደስ ይለኛል.....»
«ፊያሜታ ጊላይ እንዴት ናት?»
«ደህና ነች ። ስሞኑን ትንሽ ተለውጣብኛለች.....»
«እንዴት?»

«የማያስጨንቃት አንድ ነገር አለ ። ግን ምን እንደሆነ ልትነግረኝ አልፈለገችም ። ከፉ ነገር እንደማይደርስባት ተስፋ አደርጋለሁ ። ከመደሰት ሌላ የምታውቀው ነገር የለም» አልኩት።

«አይዞህ ፣ ስለእሷ ደኅንነት አትስጋ» በማለት አጽናናኝና ፣ «ሥዕላይ በራኺስ እንዴት ነው?» ብሎ ጠየቀኝ ።

«ይህን ሰሞን አይቼው አላውቅም» አልኩት
«እሱ ቀበሮ ነው»
«እንዴት?»

«በጣም አስቸጋሪ ፍጡር ነው ። በጣም ብልጥ ነው ። ጭራው አይያዝም» አለኝ ።

«በእሱ የቀረብክ ትመስላለህ!»

«ምናልባት የሁሉም ነገር ቁልፍ እሱ ሳይሆን አይቀርም...... ምናልባት.... ምናልባት» ብሎ ሲያስብ ቆየና ፤

«ኦሮማይ ሲባል ሰምተሀል?» ብሎ ጠየቀኝ ።

«ምነው? እዎ ። ሁሉም የሚለው ነው ። የአሥመራ ሕዝብ ቢያንስ አሥር ጊዜ ኦሮማይ ሳይል አይውልም» አልኩት ።

«ትርጉሙን ማለቴ ነው.....»

«ሆነ ፤ አበቃ ፤ አለቀ ፤ ማለት ነው ።»

«እሱን አውቃለሁ.....»

«ታዲያስ?»

«ሌላ ትርጉም እንዳለው ታውቅ እንደሆነ ብዬ ነው?» አለኝ ።

«ማለቴ ፤ ለምሳሌ 'ኦሮማይ' የሚባል የሆነ ተልዕኮ መና ሩን ታውቅ እንደሆነ ብዬ ነው.....»

«እንዴት ላውቅ እችላለሁ? ቢሮክራሲ! ኦሮማይ! ጓድ መደበኛ ሥራዬኮ ስለላ አይደለም» አልኩት ።

ፈገግ ብሎ ፤ «እሱን አውቃለሁ» አለኝ ።

«እህሳ?»

«የመረጃ ሥራ የመረጃ ሰዎች ብቻ የሥራ ክልል አይደለም ባሁኑ ጊዜ ። ሕዝባዊ ባሕርይና መሠረት ሊኖረው ይገባል ። ሁሉም ለአብዮቱና ላገሩ አንድነት ሰላይ መሆን አለበት ። አብዮ ተኛ ነኝ ማለት አይበቃም — ጓድ ፤ መለኪያው ተግባር ነው» አለኝ ።

«ስለትምህርቱ አመሰግናለሁ» ካልኩት በኋላ ፤ ቀጠል አደረኩና «የተውኩልህ ማስታወሻ ይጠቅምሀል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ። ፊያሜታን አደራ ። ቻው» ብዬው ወደ አይሮፕላን ሔድኩ ።

ከሠላሳ ደቂቃዎች በረራ በኋላ አፍአበት ደረስን ። የአፍአ በቅ አቧራና ግለት ተቀበሉን ። አቧራው በጥፊ ይማታል ። አፍንጫ ቀዳዳዎች ውስጥ ገብቶ ስለሚጋገር ያፍናል ። ግለቱ እያሳደደ ይጋረፋል ። የትም ቢገቡ ከእለንጋው ምላስ ለማምለጥ አይቻልም ። ከሌሎች ሥፍራዎች ጋር ሲነጻጸር አፍአበት ገነት አይደለም እንዴ? ሲሉ ሰምቼ ካሁኑ ሐሞቴ ይፈስ ጀመር ።

ያን ምሽት የናደው እዝ አዛዥ ከአሥመራ ለመጡ አንዳንድ የበላይ አዛዦች የፖለቲካ መምሪያና የፖለቲካ ክፍል ኃላፊዎችና የፖለቲካ ኮሚሳሮች ስለውጊያው ሁኔታ ገለጻ አድርጎልን ነበር ። ሁሉም ስለውጊያው አካሔድ አስቀድመው የሚያውቁ ቢሆኑም ሳይሰለቹ መስማት ነበረባቸው ። ለኔ ግን አዲስ ነበር ፣ እዚያ በመገኘቴ ዕድለኛም ነበርኩ ። የውጊያው አጠቃላይ ዝግጅት እንዲህ ነበር ። ሁለተኛው ነጻ አውጭ አብዮታዊ ሠራዊት በሦስት ዋና ዋና ግንባሮች ፣ ማለትም በአፍአበት ፣ በከርከበትና በአልጌና ግንባሮች ይሰለፋል ። በከርከበት ግንባር 21ኛና 24ኛ ክፍለ ጦሮችን ከስንጥቅ ብረት ለበስ ብርጌድ ጋር አቅፎ የተሰለፈው መብረቅ ዕዝ ይባላል ። 19ኛ ፣ 15ኛ እና 23ኛ ክፍለ ጦሮችን ይዞ በአልጌና ግንባር የተሰለፈው ደግሞ ውቃው ዕዝ ይባላል ። የመብረቅና የውቃው እዞች ዓይነተኛ ግዳጅ ወይም «ሚሽን» ጠላት ከናቅፋ ሰብሮ እንዳይወጣ ወይም ወደ ናቅፋ ሰብሮ ገብቶ ኃይሉን እንዳያጠናክር በደጀንነት የመከላከል ውጊያ እያካሔዱ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ ማጥቃት ነበር ። የጠላት ደጀንና ጠቅላይ ሠፈር ሆና የቆየችውን ናቅፋን በግንባር ቀደምትነት ሰብሮ የመግባት «ሚሽን» የተሰጠው 3ኛ ፣ 17ኛ እና 22ኛ ተራራ ክፍለ ጦሮችን አቅፎ ለተደራጀው ለናደው እዝ ነበር ። የማጥቃቱ ርምጃ የካቲት 8 ቀን 1974 በ24 መቶ ሰዓት እንዲጀመር ታቅዶ ነበር ። በዚሁ መሠረት 3ኛ ፣ 17ኛ እና 22ኛ ክፍለ ጦሮች ከአፍአበት ወደ ሰሜን መንቃነቅ ጀምረዋል ። ንቅናቄው ከተጀመረ ሦስት ቀን ሆኖታል ። እኔ የደረስኩት የ22ኛ ክፍለ ጦር የመጨረሻው ኃይል ሲንቃነቅ ነበር ። አብዛኛዎቹ ሎጋ ወጣቶች ነበሩ ። እና ሁሉም ወደ ውጊያ ወረዳዎች የሚሔዱ አይመስሉም ነበር ። ሲጨዋወቱና ሲስቁ ነበር ። መልካቸው ትዝ አይለኝም ። ግን የሁሉም መልክ የኔኑ ነበር የሚመስለው ። የኔ ፊት ነበር… የኢትዮጵያ መልክ ነበር ።

ሁሉም ግዳጅ ነበራቸው ። 3ኛው ክፍለ ጦር ከአፍአበት ተነስቶ ጉዞውን ወደ ማማዶ በመቀጠል የማበላን ሸለቆ ይዞ ፣ ናቅፋንና አልጌናን የሚያገናኘውን መንገድ ከዘጋ በኋላ ፣ በዚሁ ግንባር ተከማችቶ የአብዮታዊውን ሠራዊት ንቅናቄ የሚገታውን የጠላት ኃይል ማጥቃት እርስ በእርሱ እንዳይረዳዳ ማድረግ ነበር ። ለ17ኛ ክፍለ ጦር የተሰጠው ግዳጅ ደግሞ ከማሚድ ጠቅላይ ሠፈር በመነሳት በከምጨዋ ጅረት አድርጎ ቲከሲንና የሀረዋ ተራራን ከፍታ ነጥብ 2059 በመከተል በከፍታ ነጥብ 1725 1755 1702 ላይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የማጥቃት ርምጃ ከወሰደ በኋላ ናቅፋን እንዲይዝ የሚል ሲሆን ፣ የ22ኛ ክፍለ ጦር ግዳጅ በበኩሉ ፣ አንደኛ ፣ አፍአበትን በደጀንነት መከላከል ፣ ሁለተኛ ፣ በኩበኩብ ፣ በኤላገርገር ፣ በሰሰነብ ምንዳድ ሸለቆዎች በማድረግ የሚሆን ወንዝ ተከትሎ ሔዶ ናቅፋን ከደቡብ ምዕራብ ማጥቃትና መያዝ ነበር ። የወጣው እቅድ ናቅፋን...... በ270 ዲግሪ ከበ ለማጥቃት የሚያስችል ዕቅድ ነበር ። እና ይገኛል ተብሎ የታሰበው ውጤት የተመሠረተው በሁሉም እዞች የተቀናጀና የተቀነባበረ የመከላከልና የማጥቃት ርምጃና ንቅናቄ ላይ ነበር ።

በሌላ በኩል የጠላት አሰላለፍ እንደሚከተለው ነበር ። አንደኛ ቀለበት ፣ በአፍአበት ዙሪያ የሰሰነብ ምንዳብ ሸለቆ ፣ ከፍታ ነጥብ 2001 ፣ የኩኩብንና የማሚዶን በር እና የመርሳ ጉልጉብን ወደብ ይዘው መሽገዋል ። አንደኛው ቀለበት ከተሰበረ በሁለተኛው ቀለበት ይከላከላሉ ። ሁለተኛው ቀለበት የባሻሩ እ ምባን ፣ የራስ አርማስን ፣ የአንጋብን ፣ የሮሆረትንና የጋዱድን ከፍታ ነጥቦች — 1940 1627 1603 1541 1643 1290 1735 የመከላከያ ምሽጎች ያጠቃልላል ። ሁለተኛው ቀለበት ምናልባት ቢሰበር ፣ የናቅፋን በር ፣ የማሆን ወንዝ ፣ የደንደንን ተራራዎች የአልጌናና ናቅፋን መንገድ ተረተሮች ፣ የሀረዋን ተረተርና የአድሆባን ሸለቆ ይዘው መሽገዋል ። የአድሆባ ሸለቆ በተለይ የማምለጫ በራቸው ስለሆነ በተጠናከረ ኃይል እንደሚከላከ ሉት ታውቋል ።

የወገንና የጠላት ኃይል አሰላለፍ ከሞላ ጎደል እንዲህ ሆኖ ሳለ ፣ ለጠላት ኃይል የሚያደሉ አንዳንድ ሁኔታዎች ነበሩ ። የወገን ጦር በማጥቃት ስልት ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ መ ጠን ኃይሉ ከጠላት ሠራዊት ኃይል ቢያንስ ሦስት እጅ በልጦ

መገኘት ነበረበት ። ይህ ምስት ለአንድ የሚባለው የኃይል ሚዛን የሚሠራው አመች በሆኑ የውጊያ ወረዳዎች ላይ ብቻ ነው ይባላል ። የሣሕል በረሀ መሬት አቀማመጥ ምናልባትም በጦርነት ታሪክ ውስጥ በአስቸጋሪነቱ ተወዳዳሪ የሌለው የመሬት ገጽታ እንደመሆኑ መጠን የወገን ጦር የማጥቃት ርምጃ በሚጀምርበት ጊዜ ከጠላት ጦር በምን ያህል በልጦ መሰለፍ እንዳለበት ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነበር ። ከአሥመራ ወደ አፍአበት በአይሮፕላን ስመጣ የሣሕልን የመሬት አቀማመጥ ከሰማይ በመጠኑም ቢሆን ቃኝቼዋለሁ ። ገዳይ መሬት ነው ።

ሣሕል እንደ ሰንሰለት ተያይዘው ከአድማስ አድማስ ከዓይን እየራቁ በሚነጉዱ ፥ እንደ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ከመሬት ወደ ኅዋው ቀጥ ብለው በሚወረወሩ ፥ ሹል ፥ ድንጋያማ ተራራዎች ፥ እንደ ገሀነብ አፋቸውን በከፈቱ ፥ እንደ ሲኦል በሚያዛጉ ተረተሮች ሸለቆዎች የተሞላ ፥ የተረገመ መሬት ይመስላል ። እውነት ርግማን ያለበት መሬት ሳይሆን አይቀርም! እግዜር ዓለምን ሲፈጥር ተናዶ በከርን እየደቀሰ የተማታበት መሬት ይመስላል ። ንዴቱ ከመሬቱ ገጽታ ላይ ተጽፎአል ። ተደራርበው የተቀመጡት ያገጠጡ ድንጋዮች ተፈጥሮ በዘመናት የቆለላቸው አይመስሉም ፥ አንድ ኃይል ለምጽአት ቀን በጥበብ ጠርቦ ያስቀመጣቸው የመቃብር ድንጋዮች እንጂ ። ተራሮች መረማመጃ ቀርቶ ለእግር መቆናጠጫ የሚሆን ቦታ የላቸውም ። ለሰው ቀርቶ ለዝንጀሮዎችም ቢሆን አያመቹም ። እንዱን የተረገመ ተራራ ሲያልፉ ፥ ከእሱ የባሰ የተራቆተ ፥ ያገጠጠ ሌላ ተራራ ብቅ ይላል — ደብረ እመን ፥ መግዛእቲ! ታምሩ ተራራ! ፤ ደንደን ፥ ጋልደንደን ፥ ካታር ፥ ጉዋ ፥ ሒልሚት ፥ ገረግር ፥ ሐጸይነት ፥ ሮራ ጸሊም ። እና ከሩቅ ሲመለከቷቸው ከል ለብሰው ኃዘን ላይ የተቀመጡ መስለው ይታያሉ ፥ የተራሮቹን ገጽታ እየሸረሸሩ የሚወርዱት ደረቅ ፥ ኖራ መሳይ ቦዮች ደግሞ የኃዘን እንባ ። አንዳንዶቹ ተራሮች እስከ ትከሻቸው ድረስ ጉም ለብሰው ሲታዩ ዓለምን በመናቅ የአመጽ ጋቢ ቈከናንበ በእብሪት ተወጥሮ የቆመ ወንበዴ ይመስላሉ ። ጠላት የመረጠው እንዲህ ያለውን የተፈጥሮ ምሽግ የሆነ የውጊያ ወረዳ ነበር ። እና የወገን ጦር ጠላት በመረጠው የውጊያ ወረዳ መዋጋት ነበረበት ። ጠላት በተፈጥሮ ምሽጉ ብቻ ተማምኖ አልተቀመጠም ። ባለፉት ሰባት ዓመታት ፥ መሬቱን እንደፍልፈል ፈልፍሎ ፥ ድንጋዩን ስርስሮ ፥

እንኳን ከሰማይ ከቅርብ ሩቅም በዓይን የማይታዩ ሰው ሠራሽ ምሽጎች ከዳር እስከዳር ገጥግጦበታል ። እያንዳንዱ ምሽግ በእር ግጥም የሞት ወጥመድ ነበር ። በእንደዚህ ያለው የውጊያ ወረዳ ከባድ መሣሪያ ፣ ታንክና የጦር አይሮፕላን የሚሠሩት እም ብዛም ፋይዳ አልነበረውም ። የሰው ልጅና የተፈጥሮ መራራ ጦርነት ብቻ ነበር ። እና የተፈለገውን ለማስገኘት የሚያስፈል ገው የሰው ልጅ ወኔና ቆራጥነት ከዚያም ባሻገር ከተአምር ያላ ነስ ድርጊት ነበር ።

በተጨማሪ ፣ ጠላት የውጊያ ወረዳዎቹን ሁኔታ በመጠቀም ፣ ያቀደው የውጊያ ስልት የአብዮታዊውን ጦር ንቅናቄ በስፋት ለጥጦ ወይም ወጥሮ በመግታት ታክቲክ ላይ የተመሠረተ ነበር ። ይህን ለማድረግ ቀላል ነበር ። ቁልፍ በሆኑ አንዳንድ የከፍታ ነጥቦችና መተላለፊያዎች ላይ ባለ 50 ካሊበር መትረየሶች ጠምዶ የስብጥር ተኩስ መከፈት ብቻ ይበቃል።ሠራዊቱ «ካሚን» ውስጥ ገብቶ (ሀ ፊደል ቅርጽ) እንዳይቆረጥና እንዳይመታ በግድ መሰጠጥ ይኖርበታል ። ይህ ደግሞ ከፍተኛ የሰው ኃይል ይጠይ ቃል ። እነዚህን ቁልፍ ገገር መሬቶች እንዲከላከል ያደረጉት በአብዛኛው ከአካለ ስንኩላን ተውጣጥቶ የተቋቋመው 75ኛ ብርጌድ ነው ይባላል ። አብዛኛዎቹ እግር የላቸውም ። ወደኋላ ሊያፈገፍጉ አይችሉም ። እና ባለ 50 ካሊበር የያዘ አንድ አካለ ስንኩል ወንበዴ ባለበት ከልተደመሰሰ በስተቀር አንድ ሻለቃ ጦር ገትሮ ሊይዝ ይችላል ። በዚህ ላይ ጠላት የተማመነው ፈጥኖ በመንቃንቅ ችሎታው ላይ ነበር ። ተረተሩን ያውቀዋል ። መግቢያ መውጫውን አጥንቷል ። አየሩን ተለማምዶታል ። እንደ በረሀ ግመል ውሀ ሳይጠጣ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ይችላል ። ውሀ የሚገኝበትንም ነጥብ ያውቃል ። ውሀ ሕይወት ነውና ውጊያው በአብዛኛው የውሀ ነጥቦችን በመያዝ ተጋድሎ ላይ የሚመሠ ረት ይሆናል ።

ባንጻሩ ፣ አብዮታዊው ሠራዊት በካርታ ላይ ካልሆነ በስ ተቀር የውጊያ ወረዳዎቹን እምብዛም አያውቃቸውም ። ካርታዎ ቹም ላይ ሠፍረው የሚገኙት ያንዳንድ የውጊያ ወረዳዎች ስም ርቀት ፣ ከፍታና ስፋት አልፎ አልፎ በትክክል ተመዝግበው አይገኙም ። አቅጣጫን ስቶ የመጥፋት ዕድል ሊያጋጥም ይች ላል ። በዚህ ላይ ደሞ እንደሽሮ ደም አፍልቶ የሚያንተከትከው የአካባቢው አየር ሁኔታ አለ ። ለሠራዊቱ እንግዳ የሆነ የአየር

ጠባይ ነው ። እየሩ ራሱ ገጻይ ነው ። ይህም ይሁን የሰው ልጅ ከፈለገና ከቆረጠ የማይቋቋመው ነገር የለምና ፣ ውሀ ጥማቱንና ግለቱን ይቋቋመው ይሆናል ። ዋናው ችግር እየተዋጉ እንደ ፎቅ ቀጥ ብለው የቆሙትን ተራራዎች ከመውጣቱ ላይ ነበር ። የና ቅፋ ተራራዎችን ፣ ስንቅና ትጥቅ ይዞ እየተዋጉ የሚወጡ መሆ ናቸው ይቅርና ፣ በባዶ እጅም እየቧጠጡም በቀላሉ የሚሞከሩ አይደሉም ። አይበገሩም ። ተራሮቹ ማፍ ላይ መሽጎ የተከማቸው ጠላት ደግሞ ዝም ብሎ አይጠብቅም ። ራሱን ለመከላከል ብዙ ጥረት ማድረግም የለበትም ። ምቹ ሥፍራ ላይ ተቀምጦ ፣ በምብ ማዝነብና የድንጋይ ናዳ ውርጅብኝ ማውረድ ብቻ ይበ ቃል ። እንዲህ ዓይነቱ ውጊያ ነበር አብዮታዊ ጦሩን የሚ ጠብቀው ። ራስን ለመስዋእትነት የማቅረብ ሚሽን ወይም ተልዕኮ ነበር ። እና ለዚህ ተዘጋጅተዋል ። ዝግጁነታቸው ፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር ። እየሁት ። ኮራሁ ።

ገለጻውን ያደረገልን አንድ ረዘም ያለ ፣ ቀጭን ፣ መልከ መልካም ፣ ወጣት ብርጋዴር ጄኔራል ነበር ። አሁን በቅርብ ቀን ነበር ሠራዊቱ ፊት የብርጋዴር ጄኔራልነት ማዕረግ የተሰ ጠው ። ቀይ ፣ መልከ መልካም ፊቱን የሣሕል ንዳድ አክስሎ ታል ፣ የሣሕል ቁር አርሶታል ፣ የሣሕል ከሚሲን አኾጎርጉሮ ታል ። ብዙ አይናገርም ። እንደ ፈላስፋ ረጋ ብሎ እያሰበ ረጃም ጢሙን በረጃጅም ጣቶቹ ይነነትሳል ። ጥቁር የብረት ከዘራ ከእጁ አትለይም ፣ ይመረኮዝባታል ፣ ካርታ ያሳይባታል ፣ በእሷ ረዳቶቹን ይጠራል ፣ ይሸኛል ። ረዳቶቹ ከፊቱ ይልቅ የከዘራውን ንቅናቄ ነው የሚመለከቱት ። ትእግሥቱንና ቆራጥነቱን እደነቅ ሁለት ። በተለይም ፣ «ከነዚህ ሰዎች ጋር አንድ ላይ ብንቆም ፣ ይህን ገዢ መሬት ይዘን ፣ የሚበግረን የውጭ ጠላት ከቶ አይኖ ርም ነበር ። ሁለታችንም ወኔ ለወኔ የምንተዋወቅ ያንዲት ኢት ዮጵያ ልጆች ነበርን ። ያለመታደል ነው ። ለዚህም ነው ይህ ጦር ነት እጅግ አሳዛኝ ፣ እጅግ መራራና አሰቃቂ የሚሆነው» በማ ለት በመጨረሻ የተናገረው ነገር በጣም አድርጎ ልቤን ነክቶት ነበር ።

ኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ነበር ስለጠላት የውጊያ ስትራተ ጂና ታክቲክ ሲገልጽ የቆየው ። ጠቁሮአል ፣ ከስቷል ፣ ጠጉሩ

የባሰውን ረዝሟል ። ጢሙ አድጓል ። ጠጉር ብቻ ሆኖ ነበር የሚታየው ። እና ቁመት የጨመረ መስሎ ታይቶኝ ነበር ። በገለጻው መደምደሚያ ላይ ፣ «በአጠቃላይ የምናካሂደው ጦርነት መስዋእትነትን የሚጠይቅ ነው ። ለዚህ ተዘጋጅተናል ። በብዙ ዎቻችን የአብዮታዊ ጦር አባሎች ክቡር ሬሣ ላይ የድል አርማ ችን እንደሚያውለበልብ ጥርጥር የለኝም» ብሎ ነበር ። አል ተጠራጠርኩም ። ኰሎኔል ታሪኩ የማያደርገውን ነገር የሚናገር ሰው አይደለም ። ግን ለምን እንደሚሸሸኝ አልገባኝም ። እፍአ በት ከደረስኩበት ጊዜ ጀምሮ ባየሁት ቁጥር ከሩቅ ይሸሸኛል ። ራሱን ለመስዋዕትነት በገዛ ፈቃዱ ያዘጋጀ ፣ ቀይ እንቡጥ የተባለ አንድ ሻለቃ ምልምል ጦር ይዞ ከፍታ ነጥብ 1702 ላይ ለመዝ መት እየተዘጋጀ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ ።

የቀይ እንቡጥ ሻለቃ ጦር አባሎች በሙሉ ከእሱ ሳይለዩ ከአጋዴን እስከ ሣሕል ሲዋጉ የቆዩ ናቸው ይባላል ። እንደ ወንድም ይወዱታል ፣ እንደ ጦር አለቃ ያከብሩታል ። እሱም እንደራሱ አድርጎ ይወዳቸዋል ። እያንዳንዳቸውን በሙያቸውና በስማቸው ያውቃቸዋል ይባላል ። ባንድ ልብ ፣ ባንድ መንፈስ ፣ ላንድ ዓላማ ወደከፍታ ነጥብ 1702 ለመዝመት ሁሉም ዝግጁ ነበሩ ።

ከፍታ ነጥብ 1702 ትልቁ ተራራ ሆኖ አይደለም ። ከእሱ የሚበልጡ ፣ ለምሳሌ እንደ ከፍታ ነጥብ 2059 ያሉ ተራራዎች አሉ ። ምናልባትም ከዚህም የሚበልጡ ሌሎች ይኖራሉ ። ነገር ግን ፣ ከፍታ ነጥብ 1702 የናቅፋ በር ቁልፍ ነው እየተባለ የሚነ ገርለት ከናቅፋ አየር ሜዳ በስተጀርባ በአራት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ስትራተጂካዊ ተራራ ነው ። ይህን ገዢ መሬት ከያዙ የናቅፋን በር ለመቆጣጠር ይቻላል ። እና የኰሎኔል ታሪኩ ኢላማ ይህ ገዢ መሬት ነበር ። እንደሰማሁት ስለ ከፍታ ነጥብ 1702 ሲያስብና ሲያልም እየዋለ ያድራል ይባላል ። ስለእሱ ያስባል ፣ ስለእሱ ያልማል ። ስለእሱ ይናገራል ። ሌት ፣ አንዳንዴ በቅዠት ልቡ እየባነነ ይነሳል ይባላል ። ያ ተራራ የከረረ ስሜት አሳድሮበት እብድ አድርጎታል ሲሉ ሰምቻለሁ ። ግን ከሩቅ የሚ ሸሸኝ በዚህ ምክንያት የተነሳ አልመሰለኝም ። በፈያሚታ ጊላይ ምክንያት መሆን አለበት አልኩ በልቤ ። ሌላ ምን ይኖራል፣ ጠብ የለንም ። ከዚህ ቀደም የተጻረስንበት ነገር የለም ። ሥራና

ጊዜ ባያራርቀን በልጅነት ጓደኞች ነበርን ። ወይስ ዕድሜ አራር ቀን ይሆን ? ዕድሜ ሰዎችን ይለውጣል ። ጓደኞች እንደ ባዳ ሊ ተያዩ ይችላሉ ። ምክንያቱን ለማወቅ ፈለኩ ፤ እሱን ለማነጋገር የምፈልግበት ሌላም ምክንያት ነበረኝ ። ከእሱ ጋር ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 ለመሔድ ቀርጬ ነበር ። ስለዚህ ወደማረፊያዬ አልሔድኩም ። ኰሎኔል ታሪኩን መፈለግ...... ነበረብኝ ። ዕድሜ ለፍሬው ዘሪሁን ኰሎኔል ታሪኩን ለማግኘት ጊዜ አልወሰደ ብኝም ። ፍሬው የአፍአበትም ከንቲባ ሆኗል ። የደረሰበት ከተማ ሁሉ ከተማው ይሆናል ። ዝናው ቀድሞት አፍአበት ደርሶ ኖሮ ፣ ጦሩ ሁሉ «ከንቲባ» እያለ ነበር የሚጠራው ። ከመቼው ደርሶ በሁሉም ዘንድ ተወዳጅነትን ለማትረፍ እንደቻለ በጣም ያስገ ርማል ። ኰሎኔል ታሪኩን ተከትለን ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 ለመሔድ ተስማምተን ነበር ። ሌሎች ሦስት ጋዜጠኞች ፣ አንድ ቴሌቪዥን ፊልም አንሺና ረዳቱ ፣ እንዲሁም አንድ ፎቶግራፍ አንሺ፣ በቀልድ «ከአዝማቻችን እንዴት ተለይተን እንቀራለን!» በማለት ከኔ ጋር ለመሔድ ቀርጠው ነበር ።

የቀይ እንቡጥ ሻለቃ ጦር ሠፈር ከአፍአበት ሆስፒታል ፊት ለፊት ነበር ። የጦሩ አባሎች እሳት እንድደው የፈላ «ሚሊ ድራ ፍት» እየጠጡ ይዘፍኑና ይጨፍሩ ነበር ። የጦርነት ዳንኪራ ነበር የሚረግጡት ። የኰሎኔል ታሪኩ ረዳት ድንኳኑን አሳየኝ ። የፋኖስ መብራት ነበር ። ኰሎኔል ታሪኩ ጠርሙስ ውስኪ ፊቱ ገትሮ ፣ ካንድ ትንሽ እግዳሚ የእንጨት መቀመጫ ላይ በመሆን ሽጉጡን ይወለውል ነበር ። እኔን ማየት ደስ ያለው አልመሰለ ኝም ። ቢሆንም ፣ «ይህችን ጠርሙስ ብቻህን ልትጨርሳት ኖሮ አል!?» አልኩና ከፊት ለፊቱ ቁጭ አልኩ ።

የማዱን «ያዝ» አለና ጋቢጣ ሰጠኝ ። ብርጭቆ አልነበረም ። «ለድል እና በልጅነት አብረን ላሳለፍነው ጊዜ!» ብዬው ጋቢጣ ዬን አነሳሁ ።

«ምናልባት የመጨረሻ ጠርሙሳችንም ፣ የመጨረሻ ጽዋዬም ናት ። ከሥጦሩ ነው ይገፎአት የመጣሁት ለድል!» ብሎ እሱም ጋቢጣውን አነሳ ። ጋቢጣዎቻችንን አጋጨን ። ደረቁን ውስኪ ደህና አድርጌ ከተጎነጨሁ በኋላ ፣ «ለምን እንዲህ ትላ ለህ?» ብዬ ጠየኩት ።

«የምመራው ራሱን ለመስዋዕት ያዘጋጀ ጦር መሆኑን ታውቃለህ?» አለኝ ።

«አውቃለሁ ። ግን በድል ትመለሳለህ ። እና ገና ብዙ ጽዋ ዎች አብረን እናነሳለን» አልኩት ።

«ተስፋ አለኝ ።» ብሎ ሽጉጡን ቀጭ ፣ ቀጭ አድርጎ ከፈ ተሸ በኋላ መያዣው ውስጥ ጨምሮ ዝም አለ ።

ዓይኔን ይሸሽ ነበር ። ደረቁ ውስኪ ድፍረት ስለሰጠኝ ነው መሰለኝ በቀጥታ ወደመጣሁበት ወደ መጀመሪያው ጉዳይ አመራሁና «ምን አደረኩህ? ለምንድነው የምትሸሸኝ?» ብዬ ጠየኩት ።

ከአንገት በላይ በሆነ አነጋገር ፣ «የምሸሽህ ይመስልሀል እንዴ?» አለኝ ።

«እውነት ታሪኩ ንገረኝ ። በኔና ባንተ መካከል ምን የሆነ ነገር አለ? ለማወቅ እፈልጋለሁ» አልኩት ።

«ምን ማለትህ ነው? ምን ሆነ?»

«ፊያሜታ ጊላይ ትሆን ያቀያየመችን?»

«ማን ናት ፊያሜታ ጊላይ?» ቢልም ፊቱ ድንገት ሲለወጥ ታየኝ ።

«እውነቱን ንገረኝ ። እኔ እያወቅሁ አንተን ቀርቶ ሌላም ሰው በዚህ የማስቀይም ሰው አይደለሁም» አልኩት ።

«በእንደዚህ ዓይነት ነገር ላይ መነጋገር አሁን ብንተው ይሻላል» በማለት በነገሩ ወደፊት ላለመግፋት በቁርጠኛነት ከወሰነ በኋላ ፤

«ስለጦርነቱ እንጫወት ። እዚህ ምን አመጣህ?» ብሎ ጠየ ቀኝ ። እኔም ሁኔታውን በማየት ነገሩን ትቼ ፣ «ጦርነቱ የጋዜጠ ኞችም ጦርነት ነው ። ታሪክ ለመመዝገብ ነው የመጣሁት» ካል ኩት በኋላ ቀጥዬ ፣ «ፈቃድህ ከሆነ ካንተ ጋር ለመሔድ እፈል ጋለሁ» ብዬ ምኞቴን ገለጽኩለት ።

«ወዴት?»

«ወደ ነጥብ 1702..........»

«አብደሀል!»

«ምነው? አንተ አብደሀል?»
«የመስዋእትነት ተልእኮ ነው..........»

«አውቃለሁ ። የኔ ደም ብርቅ ነው ያለህ ማነው? ወይስ ለመስዋእት የሚቀርብ የሰባ ጣቦት መስዬ አልታየሁህም?» ብዬ አሳቅሁት ።

ሁላችንም ጋቤጣዎቻችንን እንደገና ሞላን ።

ደስ እያለው ሔዶ ነበር — «ጥሩ አሳብ ነው ። ቆራጥ መሆንከን አደንቃለሁ...... እውነት ። ግን እኔ ልወስንልህ አል ችልም ። የበላይ ውሣኔ ይጠይቃል » አለኝ ።

«የማንን?»

«የእዝ አዛዡን» ብሎ ቀጠለና ፣ «ይህ ወታደራዊ ኦፕሬሽን ነው ። በውጊያ ወረዳ ጋዜጠኞችን የማስተናገድ ልምድ የለንም ።
«ስለእሱ አትስጋ ። ራሳችንን እንጠብቃለን» ብዬው ቀጠልኩና ፣ «ጄኔራልን እጠይቀዋለሁ ። አንተ ከደገፍከኝ እሱ እምቢ አይልም ። ስለታሪክ እሱ ከኔ ይበልጥ ይጨነቃል ። ሸከም እንደማንሆንብህ በዚህ ውስኪ እምልልሀለሁ» አልኩት ።

«እዎ ፣ ብዙዎቻችን ስለግል ታሪካችን ይበልጥ እንጨነ ቃለን ። ልክ ነህ» አለኝ ።

«ይህን ማለቴ አልነበረም ። ግን ፣ እንዴት?» አልኩት ።

«ዛሬ በአዛዥነት የተሠማራነው ሁሉ ወጣት መኰንኖች ነን ። እና አብዛኞዎቻችን የሥልጣን ጉጉት ሳይኖረን አይቀርም ። በደህና ሁኔታ ብዙዎቻችን ምናልባት ከብርጌድ መሪነት እናል ፍም ነበር ። በቢሮክራሲም ውስጥ ምናልባት እንደዚሁ ሳይ ሆን አይቀርም ። ያንድ ክፍል ኃላፊ መሆን የማይገባው ዛሬ የመምሪያ ኃላፊ ሆኖ ይገኛል ። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በግድ የሥልጣን ጉጉትን ይፈጥራል — ያራባል...... እና ያለብንን ኃላፊነት ወደ ጎን እያልን ሥልጣን ስናባርር ፣ ተንኮል ስንሸ ርብ ፣ እንዱን በሾኬ ጥለን እንዴት እንደምናልፈው ስናውጠ

ነጥን እንውላለን ። አደገኛ አዝማሚያ ነው ። አዎ ፣ እንዳልኩት ተራ ረዳት ሆነው ከመሥራት ደረጃ ሊያልፉ የማይችሉ ብዙ ግለሰቦች ዛሬ ፣ ዕድሜ ላብዮቱ ፣ ቱባ ሹማምንት ሆነዋል ። ጥሩ ነው ። አብዮት የመደብ ሹም ሽረት አይደል? ነው'ኮ ። ግን ለሥልጣን ሽሚያ ሠፊ በር የተከፈተ እንደሆነ ደግ አይደለም ። ጓደኛው ካጠገቡ እንደቀስት ወደ ላይ ተወርውሮ ሥልጣን ኮርቻ ላይ ጉብ ሲል ያየ ሰው ሁሉ ፣ ዛሬ እኔስ ከማን እንሳለሁ? እገ ሌን አላያችሁትም እንዴ? ትናንት ምን ነበር? በማለት ሥልጣን ፈላጊና አሳዳጅ እየሆነ ነው ። ሥልጣን የምንፈልገው ለሕዝብ ጥቅም ፣ ዕድገትና ብልጽግና ፣ ኩራትና ልዕልና ቢሆን ኖሮ ባል ከፋም ነበር ። ግን አይደለም ።

«ለግል ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ሥልጣን የሚያሳድዱ ሰዎች በዝተዋል ። አደገኛ አዝማሚያ ነው — በሦስት ነገሮች ምክንያት ፣ ያለምንም ችሎታ ሥልጣን የሚፈልጉ ወይም ሥል ጣን ላይ የወጡ ሰዎች ሲበዙ አገር ይበደላል፣አንደኛ አገር ቀል ድ አይደለም ። አገር ፣ ታውቀኛለህ ፣ አውቅሀለሁ፣ጀርባዬን እከ ከልኝ እከልህለሁ በሚል መርሕ ተጠራርተው በተሰበሰቡ ሰዎች አትመራም ። ሁለተኛ ፣ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በሥልጣን አካ ባቢ እየበዙ ከሔዱ አድህሮት መከተሉ አይቀርም ። ሚሴቫን ጂላስ እንዳለው አዲስ መደብ እንዳይፈጠር ያሰጋል ። ሦስተኛ ፣ የሥልጣን መባለግ የማይቀር ነው ። ለምን መሰለህ? በርስት ፣ በቤት ኪራይ ፣ በልዩ ልዩ ገቢ መኩራራትና መንደላቀቅ ዛሬ ቀርቷል ። የበፊቱ የገቢ ምንጭ ደርቋል ። የብዙዎቻችን ግላዊ ሱስ ግን እንዳለ ነው ። አብዮቱ አልወረሳቸውም ። ታዲያ ምን ይሁን? ብልሐቱ ቶሎ ዘሎ ሥልጣን መጨበጥ ነው — በመም ሰልና በማስመሰል ፣ በብልጠት ፣ ባፈጮሌነት ፣ በዘዴ ፣ በተን ኮል ። የተንኮል ገበያ ደርቷል ። ከዚያ እንግዲህ ምናለ? መኪናና ቪላ ማማረጥ ፣ ጥሩ መብላት ፣ መጠጣት ፣ መልበስ ፣ መሽቀርቀር ፣ በየዕለቱ የበሰለ ብርቱካን እየመሰሉ መሔድ — እንዲያም ሲል ቆንጆ ቆንጆዎችን እያማረጡ ሕይወትን መቅጨት ። በስልክ ሀሎ! እያሉ ቤት ለምትፈልገው ማስፈያ ቤት ፣ ሥራ ለምትፈል ገው ማስፈያ ሥራ ፣ የደመወዝ ጭማሪ ለምትፈልገው ማስፈያ ጭማሪ ። ተጠቅሞ መጥቀም ፣ በልቶ ማብላት ፣ ማብላትና መብ ላት ። በሥልጣን እየተጠቀሙ ጥቅሞችን ለወደዱትና ለፈለጉት እንደ ጠበል ማርከፍከፍ ። ይህ ሁሉ እየታየ ነው ። እኔ የምሰጋው

በሕዝብ ስም ተነስተን ከሕዝብ እየራቅን — ለሕዝብ ባዳ እየሆን እንዳንሔድ ነው ። ጥራት! ጥራት! በሕዝብ ስም ከሚነግዱ ነጋዴዎች አብዮቱን ማጥራት ያስፈልጋል ። ለግል ታሪክ ፣ ለግል ዝና ይበልጥ ስለምንጨነቅ ኅብረት ጠፍቶ ግላዊ ሩጫና ጀብደኝነት ይነግሣል ። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በተለይ በጦር ሜዳ አደገኛ ነው ። እኔ ከጠላት ይልቅ በጣም የሚያሰጋኝ ይህ ነው» ብሎ አጫወተኝ ።

«ምን ይደረግ! አብዮት ነው ። ያብዮት ወቅት ነው ። አብዮት የውሀ ልኩን እስኪያገኝ ድረስ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ይኖራል» አልኩት ።

«አብዮት የንፁስ ከበርቴዎች ሽግሽግ ማለት አይደለም» ብሎ ድንኳኑ ውስጥ ተሰቅሎ የሚገኘውን አንድ አርማ በልዩ ትኩረት ሲመለከት ከቆዬ በኋላ ፣ «በቅድሚያ የሰፊውን ሕዝብ ኑሮ መኖር ፣ ሞቱን መሞት መማር አለብን ። ከእሱ ምኞት ውጭ የሆነ ምኞት ሊኖረን አይገባም ። ይህን እንተውና እንጠጣ ጃል» ብሎ ጋቢጣውን አነሳ ።

ጠጣን ። ድንገት ጸጥ ብሎ ቀረ ። የቀይ እንቡጥ ጦር ፉከራና ቀረርቶ ይሰማ ነበር ። ዛሬ ዘፈንና ጨዋታ ፣ ነገ ጦርነትና ሞት ። የወታደር ኑሮ...... ሕይወት...... «የመንደራችን ልጆች እየሰበሰብክ የጦርነት ጨዋታ ስታጫውተን የምትውለው ትዝ ይልሀል?» አልኩት ።

ፈገግ ብሎ ፣ «የወደፊት ኑሮዬ ይታየኝ ነበር መሰለኝ!» አለ ።

«መኖር ደግ ። እውነተኛውን ጨዋታ አብረን ልንጫወት ነው» አልኩት ።

«አዎ ፣ መኖር ደግ ነው» ብሎ በረጅሙ ተነፈሰና ፣ «አሥመራ እንዴት ናት» አለኝ ።

«አልተለወጠችም ። አሁንም ውብና አሳዛኝ ከተማ ናት» አልኩት ።

«ኤርትራ በሙሉ ውብና አሳዛኝ ናት» አለኝ ።

«በቀይ ኮከብ ዘመቻችን አንድ ዓይነት ተሐድሶ ታገኛለች ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» አልኩት ።

«የኔም ተስፋ ይኸው ነው» ብሎኝ ዝም አለ ።

የውስኪ ጠርሙሳችን ባዶ ሆናለች ። የቀይ እንቡጥ ጦር ፋከራ ፣ ቀረርቶና ጭፈራ ከበፊቱ አይሎ ይሰማ ነበር ።

በመጨረሻ—«የሚያሳዝነው ተገንጣይነት በኤርትራ ምድር ያልበቀለ ፣ ከኤርትራውያን ጭንቅላት ያልወጣ የባዕዳን ተጽዕኖ መሆኑ ነው ። ሌላው የሚያሳዝነው ነገር ይህን የባዕዳንን የበኩር ልጅ በመሣሪያነት የሚያገለግሉትም ሆኑ የሚዋጉት የዚሁ ክፍለ ሀገር ተወላጆች መሆናቸው ነው ። በሺህ የሚቆጠሩ ኤር ትራውያን ይህችን ውብ የሆነችና አሳዛኝ አገር የሚያደሙትን ያህል ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ኤርትራውያን ደግሞ ባንጻሩ ፣ ለዚች አገር ክብርና አንድነት እየደሙላት ነው ። ለምሳሌ እንዳንተ ያሉት ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጭ የለውም ። ሕልውናው አንድነቱ ብቻ ነው ። አንድ ኢትዮጵያዊ አንድነቱን አጥቶ እን ዴት ሊኖር እንደሚችል አይታየውም!» አልኩት ።

«እኔም አይታየኝም ። መቸም ሰብእናውን አጥቶ የሚኖር ሕዝብ የለም» አለኝ ።

በጣም አድርጎ ሲከነክነኝ የቆየ ነገር ስለነበረ ፣ ያኔ በድል አድራጊነት ሲገሠግሥ የመጣው ሠራዊት ፣ ተፈተው በመፈር ጠጥ ላይ የነበሩትን ወንበዴዎች እያሳደደ ሳይደመስስ ለምን ቀረ? ወንበዴዎቹ ፋታ አግኝተው ናቅፋ ላይ እንዲሰባሰቡና እንዲጠናከሩ የሆነበት ምክንያት ምን ነበር? ድሉን በማስፋት ያኔ ቢደመሰሱ ኖሮ ፣ ዛሬ ተጨማሪ መስዋእት እንከፍል ነበር ወይ? ብዬ በጥያቄ አጣደፍኩት ።

«ምናልባት ፣ ሠራዊቱ ድሉን በማስፋት የጠላትን ወገን እስከመጨረሻው ሰው ከመደምሰስ የተገታበት ምክንያት ፣ ጠላት ሽንፈቱን ተገንዝቦ የውይይትና የእርቅ መንገድ ይመር ጣል በሚል ግምት ይሆናል ። እርግጠኛ አይደለሁም ። የኤርትራ ችግር እንዳያልቅ የሚፈልግ ማን ይኖራል?» ብሎኝ ዝም አለ ።

ብዙ ሊያናግረኝ አልፈለገም ። ልቡ ከቀይ እምቡጥ ጦሩ ጋር ነበር ። በፊያሜታና በእሱ መካከል ስላለው ግንኙነት ለማወቅ የምችልበት መንገድ በማጣቴ ነደደኝ......

# ም ዕ ራ ፍ

## አ ራ ት — 2

የጋዜጠኞች ቡድን ቀይ እምቡጥ ከተባለው ልዩ ሻለቃ ጦር ጋር ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 እንዲሔድ ለማሳመን የተደረገው ጥረት ቀላል አልነበረም ። በመጀመሪያ አከራካሪ የነበረው ነጥብ ማን ኃላፊነቱን ይወስዳል? የሚል ጥያቄ ነበር ። ታሪክን ቀርጾ በማስቀረት ለትውልድ እንዲቆይ በማድረግ ረገድ ጋዜጠኞችም እኩል ኃላፊነት ያለባቸው ስለሆነ ፣ ኃላፊነትን መውሰድ የእነሱ ፈንታ ነው ፣ መሆንም አለበት የሚለው ነጥብ እምብዛም አላከራከረም ። ይልቅ በጣም አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ነጥብ ፣ ቀይ እምቡጥ የተባለውን ጦር ተከትላችሁ ለመሔድ ምን አስመረጣችሁ? የሚለው ፣ ልዩ ግብረ ኃይል ፣ ማለትም ፣ ራሱን በፈቃደኝነት ለመስዋእትነት ያዘጋጀ ግብረ ኃይል እንደመሆኑ መጠን እሱን አጅባችሁ መሔድ አጉል ጀብደኝነት ይሆናል በማለት ፣ ይህን ልዩ ግብረ ኃይል አጅበን እንዳንሔድ የሚከላከሉን አንዳንድ አዛዦች ሲኖሩ ፣ ከቀይ እምቡጥ ጦር የበለጠ ተልእኮ ያላቸው ጦሮች አሉ ፣ እነሱን ተከትላችሁ ብትሔዱ ፣ ሁኔታው ለሥራችሁ ያመቻል ፣ እንደምትሉት በእርግጥ ታሪክን ቀርጻችሁ ለትውልድ የማስቀረት ዓላማ ካላችሁ ፀዚሁ ግንባር ከሚዘምቱት ብርጌዶች ጋር ብትሰለፉ ይሻላል በማለት የከረረ ክርክር የሚያቀርቡም ነበሩ ። በግልጽ ፣ ከእኔ ጋር ለምን አትመጡም? የሚሉ አዛዦችና የፖለቲካ መምሪያ ኃላፊዎችም ነበሩ ። ከቀይ እምቡጥ ልዩ ጦር ጋር ለመዝመት አንደኛውን ቆርጨ ነበርና በአሳቤ ጸናሁ ።

«ጓድ ጸጋዬ ፣ በጦር ሜዳ አሳበ ግትርነት ሁታ የሊውም» አለኝ ፣ የናደው እዝ አዛዥ ጢሙን እየጎነተለ ።

«እኛም በፈቃደኛነት ራሳችንን ለመስዋእትነት ለማቅረብ መብት አለን ። ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 እንሔዳለን ቢቃ ። በዚህ ነጥብ ላይ በመከራከር ጊዜ ለምን እንደምናጠፋ አይገባኝም?» በማለት የመጨረሻ አሳቤን አጠናክሬ ገለጽኩ ። ምን ችግረኝና? ጦር ፍርድ ቤት የለኝም! አሳቤን የሚያስለውጠኝ ነገር አልነበረም ። እኔም እንደ ኰሎኔል ታሪኩና እንደ ቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች ፣ ከፍታ ነጥብ 1702 የከረረና የጋለ ስሜት እያሳደረብኝ

ሔዶ ነበር ። ወኔያቸው ወኔዬ ፣ ሕልማቸው ሕልሜ ሆኗል ። ድላቸው ድሌ ይሆናል ፣

ሞታቸውም ሞቴ ። ቀንም ሆነ ሌት ፣ ከፍታ ነጥብ 1702 ጫፍ ላይ ወጥቼ ስቆም በእውኔም ሆነ በሕልሜ ይታየኝ ጀምሮ አል ። ከፍታ ነጥብ 1702 ሁለተኛ ተፈጥሮዬ ሊሆን ምንም አልቀረውም ።

ከስብሰባው ስንወጣ ፣ ኰሎኔል ታሪኩን ፣ «ምነው ዝም አልክ? ልትደግፈኝ ይገባ ነበር» አልኩ ።

«ምን ብዬ?» አለኝ ።
«ወሳኝ ተልእኮ ነው በማለት.....»
«ደግሞ ለራሱ ታሪክ ሲል ነው ይበሉኝ?»
«ቢሉህስ?»

«እኔ የማስብለትና የምጨነቅለት የግል ታሪክ የለኝም» ካለኝ በኋላ ፣ ረጀጅም እጆቹን የት እንደሚያስገባቸው እየተቸገረ ፣ «ለማንኛውም ነገር እንኳን ደስ ያለህ ። ከዛሬ ጀምሮ በኔ ቁጥጥር ሥር መሆንክን እወቅ ። እና ቀልድ የለም ። እመነኝ ፣ ምን አቀበጠኝ? ብለህ የምትቆጭበት ጊዜ ሩቅ አይደለም» ብሎኝ ሔደ ረጃጅም ቅልጥሞቹን እየዘረጋ ። ጠበንጃ ሲይዝ ብቻ ነው እጆቹን ምን ላይ እንደሚያውላቸው የሚያውቀው ። እግሮቹም ቅልጥፍና የሚያገኙት በጦር ሜዳ ብቻ ነው ይባላል ። ካልጐተጐቱት በስተቀር ብዙ አይናገርም ። ጊዜውን የሚያሳልፍበት ልዩ ነገር የለውም ። ጠርሙስ ውስኪ ፊቱ ገትሮ ዝም ብሎ ይጠጣል ። አንዳንዴ፣ በጦር ሜዳዎች ካጠገቡ የወደቁትን የጦር ባልደረቦቹን እያሰበ ዝም ብሎ እንባውን ያፈሳል ። ተጫዋችና ደስተኛ የሚሆነው በጦር ሜዳ ነው ይባላል ። እሱን በጦር ሜዳ የማይበት ጊዜው ሩቅ አልነበረም ። ቀይ እምቡጥ ሻለቃ ጦር ያን ቀን ከሰዓት በኋላ ፣ በ1300 ሰዓት እንዲንቀሳቀስ ታዞ ነበር ።

ልክ በተባለው ሰዓት ከእፍእበት ተንቀሳቀስን ። ቀይ እምቡጥ ጦር እግረ መንገዱን ፣ ቀይም ብሎ ለተንቃንቀው ለ17ኛ ክፍለ ጦር ብርጌዶች ስንቅ የማድረስ ተልዕኮ ነበረው ። ስንቅ የጫኑ ብዙ የሲቪል ከባድ መኪናዎች ከጦሩ ጋር አብረው ተንቀሳቀሱ ። ቀይ እምቡጥ ጦር የታጠቀው ቀላል መሣሪያዎች ብቻ ነበር ።

ጦሩ ከሠፈሩ የተንቃንቀው በጠንካራ ሞራልና በጋለ ስሜት ነበር ። ጦሩ በጥሩ ሞራል የተንቃንቀው ፣ ቀደም ሲል ወደ ሰሜን የተንቃንቁት 17ኛ እና አንበሳው 3ኛ ክፍለ ጦሮች የመጀመሪያ ምዕራፍ ግዳጃቸውን በተሳካ ሁኔታ ፈጽመዋል የሚል አስደሳች ዜና ስለደረሰ ነበር ። የቀይ ባሕርን ዳርቻዎች ይዞ ወደ አልጌና የሚገሠግሥ በመምሰል ወደ ሰሜን የሔደው የአንበሳው 3ኛ ክፍለ ጦር አንድ ክንፍ ድንገት ወደ ግራ በመታጠፍ ፣ ጠላት ባላሰበውና ባልጠበቀው መንገድ በሚያስደንቅ ፍጥነትና ቅልጥፍና ሮራ ጸሊም የተባለውን ቁልፍ የሆነ ወታደራዊ መሬት በቁጥጥሩ ሥር አዋለ ። የወገን ጦር አመጣጥ ድንገተኛ ስለሆነበት ግራ ጎኑ የተጋለጠው የጠላት ጦር የመከላከል ውጊያ ለማድረግ አልቻለም ። ሞኙ 3ኛ ክፍለ ጦር ወደ አልጌና በመጓዝ ላይ ነው የሚል ግምት በጠላት ዘንድ በማደሩ ፍጹም ተዘናግቶ ነበር ። የጠላት ወገን የሞተው ሞቶ ፣ የተማረከው ተማርኮ ፣ የተረፈው እግሬ አውጭኝ እያለ ፣ ትጥቁን ጥሎ ፣ ነፍሱን ይዞ ፈረጠጠ ። ከደረሰው ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው 2000 የጠላት ሬሣ አስቀጥረው 77 ማርከው ከ317 በላይ ልዩ ልዩ መሣሪያዎችንና የመገናኛ ሬዲዮኖችን የተረከቡበት ውጊያ ነበር ። በእርግጥም ፣ ፍጹም የሆነ ታክቲካዊ ድል ነበር ።

እንዲሁም ከቀምጨዋ ተነስቶ በናሮ ሜዳና በቲክሲ ሽለቆ መሐል ለመሐል እየሰነጠቀ ወደ ሮሆረት የተሰበቀው 17ኛ ክፍለ ጦር ካንድ የድል ምዕራፍ ወደ ሌላ የድል እርከን በእስ ደናቂ ፍጥነት እየተሸጋገረ ሔዶ ፣ የጠላትን የግራ ሰበራ እየጠበቀና ስርጦችን እየዘጋ የጊልሳን (ቲክሲን) ዝቅተኛ መሬት ግራና ቀኝ እና ከምዕራብ በኩል የሚገኙትን ከፍተኛ ወታደራዊ ገዢ መሬቶች ከቁጥጥሩ ሥር በማዋል የናቅፋን በር በማንኳኳት ላይ ይገኛል የሚል ዜና በደረሰ ጊዜ በቀይ እምቡጥ ጦር ላይ ያደረው ደስታ ከዳር እስከ ዳር አስተጋባ ። ጦሩ በሞራል እየተሰበቀ ወደፊት ይወረወር ጀመር ። ቃኝ ወይም አብሪ ኃይል ማስቀደም አልነበረበትም ። ዝም ብሎ ወደ ግቡ መምዘግዘግ ነበር ።

ቀይ እምቡጥ ጦር ፣ 17ኛ ክፍለ ጦር ሰባብሮና ጠርጎ ባለፋቸው የድል ጎዳናዎች ስለነበረ የሚጓዘው በመንገድ ላይ የጠላት እክል እንደማያጋጥመው አስቀድሞ አውቋል ። የ17ኛ

ክፍለ ጦር አንዱ ግዳጅ ለቀይ እምቡጥ ሻለቃ ጦር መንገድ እያጸዳ ሁኔታዎችን አመቻችቶ መቆየት ነበር ። ቀይ እምቡጥ ለልዩ ተልእኮ የተሰለፈ እንደመሆኑ መጠን ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 እየተዋጋ እንዲሄድ አስቀድሞውኑ አልተፈለገም ።

3ኛ እና 17ኛ ክፍለ ጦሮች ናቅፋ ለመግባት ከጊልሳ ሸዊ አልፎ የሚሔደውን የእግር መንገድና ወደ ናቅፋ አልጌና የሚያገናኘውን መንገድ መዝጋት ፣ እስካሁን የያዟቸውን ቁልፍ ቦታዎችና ግራና ቀኝ ከንፋቸውን ማጠናከር ነበረባቸው ። ነገር ግን ይህን ለማድረግ የመሬቱ ቅርጽና ስፋት አይፈቅድም ። በዚህ ላይ ጠላት መንገዱን ለመዝጋት ይሻማል ። ጠላት ተሻምቶ መን ገድ እንዳይዘጋም ሆነ ፣ ወደ ናቅፋ የሚያረማምዱትን እንደ 1521 ፣ 1527 ፣ 1969 ያሉትን ከፍታ ነጥቦች ለመያዝ ፣ ለነዚህ ሁሉ ቁልፍ የሆነውን ከፍታ ነጥብ 1702 በቅድሚያ መስበር በጣም አስፈላጊ ሆኗል ። ጠላትም ይህንኑ ዐውቆ ይህን ገዢ መሬት ላለመልቀቅ «ነጥብ 1702 ወይም ሞት» በማለት መሽጎ ይጠብቃል ። እና የ3ኛና የ17ኛ ክፍለ ጦሮች ቀሪ ግብ በቀይ እምቡጥ ጦር ተልእኮ መሳካት ወይም አለመሳካት ላይ ያረፈ ነበር ። የተጣለበትን ኃላፊነትና አደራ የማያውቅ አንድም የቀይ እምቡጥ ጦር አባል አልነበረም......

«ይኮሩብናል»
«እናሳፍራቸውም»
«በኛ ሬሣ ከምር ላይ ወደ ናቅፋ ይረማመዳሉ ።»
«ነጥብ 1702 ላይ የቀይ ኮከብ ዘመቻችንን ቀይ ትርኢት እናሳያለን ።»
«እጅህን አትስጥ ። ልቡ ላይም መቆም ነው ። ማን ይፈራል ሞት ?»

«ታሪኩን የመሰለ ጀግና የጦር ገበሬ ፣ ይዘን የወንበዴዎች ጦር ፊታችን ማን አባቱ ሊቆም ! እንደታሪኩ ደረታችንን ገል ብጠን ነው የምንገባበት!» የሚሉ ኃይለ ቃላት በጦሩ ዘንድ በየቦታው ይነገሩ ነበር ።

አሸዋማው መሬት ብቻ ነበር እልፎ እልፎ የጦሩን ፈጣን ጉዞ የሚገታው ። ሁለት ከባድ የጭነት መኪናዎች አሸዋ ውስጥ

ገብተው ተቀረቀሩ ። የአየሩ ግለት እያየለ ሔዷል ። እንፋሎት የመተንፈስ ያህል ነበር ። የምንጓዘው ሸለቆዎችን ተከትለን ስለነበር ንፋስ ጨርሶ የሚነፍስ አይመስልም ። እፍን ያደርጋል ። አያስተነፍስም ። በማጅር ግንድ የሚንቆረቆረው ላብ እንደ ውሀ ይጨመቃል ። እያንዳንዱን ሰው ከወደ ጀርባው ሲመለከቱት ዝናብ የዘነበበት መስሎ ይታያል ። መኪናዎቹ ተገፍተውና ተጎትተው እስኪወጡ ድረስ ጦሩ ተገን ፣ ተገን ይዞ ቆመ ። ያለ ግራር ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ሌላ የሚታይ የዛፍ ዘር የለም ። አካባቢው ድንጋያማ ኮረብታዎች ይበዙበታል ። ጥቂት ወታደሮች አካባቢውን ለመቃኘት ሔደው ነበር ። ሌሎች ብዙ ወታደሮች አሸዋ ውስጥ ገብተው የተቀረቀሩትን መኪናዎች ይገፋሉ ፣ ይጎትታሉ ። ኰሎኔል ታሪኩም ከወታደሮቹ ጋር አብሮ ይሠራል ። ወታደሮቹን ፣ እሱ የማይሠራውን ነገር ፈጽሞ አያሠራቸውም ። የሚገርመው ነገር ላብ የሚባል ነገር አይታይበትም ። ድንገት ቅልጥ ያለ ተኩስ ይሰማ ጀመር ። ጦሩ በያለበት በደረቱ መሬት ያዘ ። የማደርገው ነገር ጠፍቶኝ ባለሁበት ተገትሬ ቀረሁ ።

ኰሎኔል ታሪኩ ፣ «መሬት ያዝ!» ብሎ ጮኸብኝ ። ሽጉጡን መዞ ቆሞ ነበር ። በደረቴ ለጥ አልኩ ። ትንሽ ቆይቶ ሁለት ቦምቦች ፈነዱ ። ሸለቆው አስተጋባ ። ምድርና ሰማይ የተደበላለቀ መሰለኝ ። ከዚያ በኋላ ጸጥ አለ ። ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ ። ቀደም ሲል አካባቢውን ለመቃኘት የሔዱት ወታደሮች በሙተ ጋገዝ የቆሰሉ ሰዎች ተሸከመው መጡ ። ኋላ እንደተረዳሁት የቆሰሉት ሰዎች ተቆርጠው የቀሩ የጠላት ወገኖች ነበሩ ። ሦስቱ ቀደም ሲል ሞተዋል ። የተቀሩት ሁለት ሰዎች ክፉኛ ቆስለው ያጣጥራሉ ። ሳያቸው ዘገነነኝ ። ሰውነታቸው በቦምብ ተጨማልቋል ። ለመጀመሪያ ጊዜ የጦርነት አሰቃቂና አስቀያሚ ገጽታ ታየኝ ። ሆዴ ክፉኛ ታወከ ። ሰው እንዳያየኝ ዞር ብዬ መራራ ሐሞት እስኪያስመልሰኝ ድረስ አስታወኩ ። ቀጥሎ የሆነው ነገር ነበር አደንዝዞ ያስቀረኝ ። ክፉኛ ቆስለው የሚያጣጥሩትን ሰዎች በመርዳት ረገድ ሊደረግ የሚችል አንዳችም ነገር አልነበረም ። ስቃያቸው የከፋ ቢሆንም ፣ ሞት አልገላገላችሁም ብሎ ይተናነቃቸዋል ። ኰሎኔል ታሪኩ ሽጉጡን መዞ በሁለት ጥይት ገላገላቸው ። የሰው አንጎል ወጥቶ ሳይ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር ። ፊዝዤ ቀረሁ...... ኰሎኔል ታሪኩ መጥቶ እስከሚያናግረኝ ድረስ

የት እንደ ነበርኩ ፤ በእውን ይሁን ወይም በቅዠት ዓለም ውስጥ እንዳለሁ አላውቅም ነበር ።

«እንዴት ነው'ኮ ታሪክ የምትቀርጹት?» ባለኝ ጊዜ ነበር ወደ እውነት ዓለም የተመለስኩት ። ከሰውነቴ ውስጥ ያለ የሌለ ፈሳሽ ነገር ተጨምቆ የወጣ ይመስል አያልበኝም ነበር ። ሙቀቱ ምኑም አልነበረም ። የምሰጠውም መልስ አልነበረኝም ። ቀጠለና ፤ «ገና የባሰ ታያለህ ። በጦር ሜዳ ሞት ምንም አይደለም ። እንደ መተንፈስ ወይም እንደ መብላት ተራ ነገር ነው ። የጦርነት መልክ አስቀያሚ ነው ። ቢሆንም ጻግመኛ እንደማታስታውስ ተስፋ አለኝ» ብሎ ሳቀብኝ ።

«እንደዚያ ማድረግ ነበረብህ?» አልኩት ።
«ምን?»
«ሰዎቹን ።»

ወታደሮች ሡፈ ጉድጓድ ቆፍረው ሬሣዎቹን አፈር ማልበስ ላይ ነበሩ ። ከመቸው ያንን የሚያክል ጉድጓድ እንደቆፈሩ ይገርማል ።

«መሞታቸው አይቀርም ነበር ። ከሚሰቃዩ ይሻላል ብዬ ነው ። ሌላም ምክንያት ነበረኝ» አለ ።
«እንደምን ያለ?»
«እንዳየሆቸው ሰውነታቸው ተቆራርጦ ነበር ። ጉደሎ ሰውነት ይዞ ከመኖር መሞት ይሻላል ።»

«እውነት ይህን ታስባለህ!»

«የለም ፤ እኔ ኢትዮጵያን ነው የማስበው ። አካለ ጉደሎ የሆነች ኢትዮጵያን ማየት አልፈልግም» እንዳለኝ ፤ ረዳቱ መጥቶ ወታደራዊ ሠላምታ ከሰጠው በኋላ ፤ «የውሀ ሰዓት ደርሷል ጓድ ኰሎኔል» አለው ።

የኰሎኔል ታሪኩ ረዳት የመቶ አለቃ ጠና ጋሻ ይባላል ። በቅርብ ጊዜ ከተራ ወታደርነት ባንድ ጊዜ የመቶ እልቅና ማዕረግ የተሰጠው በዕድሜ ጠና ያለ ቆፍጣና ወታደር ነው ።

«እጅህን አትስጥ ። ጠላት ልብ ላይ ቁም ። ማን ይፈራል ሞት» የሚል ኃይል ቃል ከአፉ አይለይም ። በጀግንነቱ ብዙ የጦር ሜዳ ሜዳዮች የተሸለመ ወታደር ነው ። አብዛኞዎቹ የቀይ እም ቡጥ ጦር አባሎች እንደ እሱ በልዩ ልዩ ጦር ሜዳዎች ባሳዩት ጀግንነትና በሠሩት ጀብዱ ልዩ ልዩ ሽልማት ያገኙ ምርጥ ወታደሮች ናቸው ። ፊሽካ ተነፋ ፤

«ለንቅናቄ ተዘጋጁ !»
ሁሉም ባንድ ጊዜ ተዘጋጀ ።
«ኮዳ አውጣ!»
ሁሉም ኮዳውን አውጥቶ በእጁ ይዞ ቆመ ።
«ኮዳ ወደ አፍ!»
ሁሉም ኮዳውን ወደ አፍ ይዞ ይጠብቅ ጀመር ።
«ጠጣ!»
ወታደሩ ሁሉ ውሀውን ይጠጣ ጀመር ።
«ኮዳህን መልስ!»
ሁሉም ኮዳውን መልሶ ከጐኑ ላይ ሻጠ ።
«ወደፊት!»

ኰሎኔል ታሪኩ ወደ መኪናው ከመሔዱ በፊት ፣
«እናንተ ጋዜጠኞች ውሀ በፈለጋችሁ ጊዜ ልትጠጡ ትች ላላችሁ» አለኝ ።

ኮዳዬን አውጥቼ ውሀ ጠጣሁ ። ሙቅ ነበር ። ቀዝቃዛ ውሀ በዓይኔ ዞረ ። አንድ ጠርሙስ ቀዝቃዛ ውሀ ባገኝ የተጠ የኩትን ዋጋ እከፍል ነበር ። በ1700 ሰዓት ሠፈር ተመርጦ አዳር እዚያው እንዲሆን ተደረገ ። 17ኛ ክፍለ ጦር የሠፈረበት ቦታ ነበር ። ትልቁ ግራር ላይ «አምባሣይራ» የሚል ጽሑፍ ተለጥ ፎበታል ። መለስ ካለው ግራር ላይ ደግሞ «ኒያላ» የሚል ጽሑፍ ይታያል ። የበረሀ ሐረጎችን በማያያዝ የተሠሩት ዳስ መሳይ ነገሮች ላይ ፣ «አምባሳደር ፣» «ቻዉ ፣» «ከረን» የሚሉ የሆቴል ስሞች ተጽፈው ይነበባሉ ። መቸም የሰው ልጅ ገሀነብ ውስጥ ቢወድቅም ገነት መመኘቱ አይቀርምና ፣ ነገሩ ያሳቀኝን ያህል አሳዛነኝ ። ሠፈሩ ባንድ ጊዜ በወታደራዊ እንቅስቃሴ ተሞላ ። ዘቦች ቦታ ቦታቸውን ያዙ ። ሹካ እና ማንኪያ የሚል የመተላለፊያ ኮድ ተሰጠ ። ውሀ አቀዝቅዞ ለመጠጣት የሚደረገው ሩጫና

ጥሬት የሚያስደንቅ ነበር ። አንዳንዱ ኮዳውን በእርጥብ ጀንያ አስሮ ከዛፍ ላይ ይሰቅላል ፣ ሌላው ኮዳውን ወስዶ ከደረቅ ወንዝ ዳር አሸዋ ውስጥ ይቀብራል ። የመቶ አሊቃ ጋሻ ጠና የኔን ኮዳ ወስዶ የት እንደሔደ አላውቅም ። ጋዜጠኞች እንደ እንቁላል የሚሰበሩ ይመስል የጠሩ አባሎች በሙሉ ሊንከባከቡን ይጥሩ ነበር ። አንዳንዶቹ ከንፈራቸውን በኃዘን እየመጠጡ ያዝኑልናል። አሁን እንዲያው እዚህ ምን አመጣችሁ? የሚሉ ይመስላሉ ።

ጸሐይ ከመጥለቋ በፊት የሬሻይዳ ብሔረሰብ አባሎች ከየት መጡ ሳይባል ፣ ተሰባስበው በመምጣት ከጠሩ ሠፈር ትንሽ ራቅ ብላ በምትገኝ ገላጣ ሥፍራ ላይ ተከማችተው ይታዩ ነበር ። ከእግር ጥፍራቸው እስከ ራስ ጠጉራቸው በጥቁር ጨርቅ የተሸፈኑ ሴቶች ከወንዶች ኋላ ተቀምጠዋል ። ፊታቸው አይታ ይም ። አንድ የራሻይዳ ሴት በአሥር ወይም በአሥራ ሁለት ዓመቷ ከተዳረች በኋላ ከባሏ ሌላ ማንም ወንድ ፊቷን ሳያይ ኖራ ትሞታለች ሲባል ሰምቻለሁ ። ምግብ ስትበላም ሆነ ውሀ ስትጠጣ ተሸፍና ስለሆነ ባሏም ቢሆን ከንፈሯን አያይም ይባ ላል ። ምን ይመስሉ ይሆን? ያንዷን ፊት ገልጩ ባየሁት የሚል ስሜት ቢያድርብኝም ፣ የራሻይዳ ባል የሚሰቱን ፊት ገልጦ ያየበትን ወንድ እጅ በያዘው ሠይፍ ቆርጦ ሳይጥል አይመለስም የሚል ታሪክ ስላለ ፣ አንዱ የእጇን ዋጋ ቢሰጠኝስ በማለት ስሜቴን ገትቼ ዝም አልኩ ። የቴሌቪዥን ፊልም አንሺያችን ያንድን ሴት ፊት ገልጦ ለማንሳት ሲሞክር አይቼ ሩጬ ሔጄ ያዝኩት ። አንዱ የራሻይዳ ጎረምሳ ሠይፉን ለመምዘዝ ይዳዳው ነበር ፣ ወይም መሰለኝ ። ፊልም አንሺያችንን ፣ አሸብር ዳርጌን ታሪኩን ሳጫውተው ደንግጦ የያዘውን የፊልም ማንሻ መሣሪያ ጥሎ ሊሮጥ ምንም አልቀረውም ።

ወደ ጠሩ ፖለቲካ ኮሚሳር ጠጋ ብዬ ፣ «እነዚህ ሰዎች ምን ሊፈልጉ ነው የመጡት?» ብዬ ጠየኩት የጠሩ ፖለቲካ ኮሚ ሳር ሻምበል ዋለልኝ ደርጋ ይባላል ።

«የወባ መድኃኒት» አለኝ ።
«ምነው ሁሉም ታመዋል?»
«የለም ፣ አብዛኞዎቹ ከኪኒኑ ጋር ለሚሰጠው ውሀ ሲሉ ነው የሚመጡት» በማለት መለሰልኝ ።

ውሀ ማግኘት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ ጭንቅላቴን መታኝ ። የሰው ልጅ በእንደዚሀ ያለ የተረገመ ምድር መኖርን የሚመርጥበት ምድራዊ ምክንያት አልታይህ አለኝ ። ነገሩ ገረመኝ ። መጀመሪያውኑ የሰው ልጅ የሚኖርበት አካባቢ አልመሰለኝም ነበር ። የትናገ እንዴትገ እንደሚኖሩ የሣ ሕል በረሀ እግዜር ብቻ ነበር የሚያውቀው ። በሌላ በኩል በአ ብዮታዊው ጦር ላይ ያላቸው እምነት ያስደንቀኝ ነበር ። ደረቅ ስንቅ፣ ውሀና የወባ መከላከያ ክኒን ከታደላቸው በኋላ ሻምበል ዋለልኝ ሴቶቹ ወደፊት እንዲመጡ ጋበዛቸው ። ፊት የተቀመ ጡት ወንዶች በመጀመሪያ ነገሩን እንደ ቀልድ በማየት እየተጠ ቃቀሱ ይስቁ ጀመር ። ሻምበል ዋለልኝ አምርሮ ሴቶቹ በግድ ወደፊት እንዲመጡ ለማድረግ ሲል ፣ ወንዶቹም አምርረው ተነሱ ። በራሻይዶች ልማድ ሴት ልጅ በምንም ሁኔታ ከወንድ ቀድማ አትሄድም ፣ ከወንድ ፊት አትቀመጥም ። ያልታሰበ ውጥረት ድንገት ተፈጠረ ። ኰሎኔል ታሪኩ መጥቶ ሁኔታውን ከተረዳ በኋላ ፣ ሻምበል ዋለልኝን «ተዋቸው ። እንደልማዳቸው ይሁኑ ። ችግር መፍጠር የለብንም» አለው ።

ሻምበል ዋለልኝ ፣ «እንዲሀ ዓይነቱን ጎታች ባሕል እያየን ዝም ማለት የለብንም ። እነዚሀ ሴቶች ዘላለማቸውን የወንዶች ተገዢዎችና ባሪያ ሆነው እስከ መቼ ይኖራሉገ ማንቃት አለብን ። የጠሩ አንዱ ተልእኮ ማንቃትና ማደራጀት ነው» በማለት ለመከራከር ሞክሮ ነበር ።

«አዎ ፣ ጓድ» አለ ኰሎኔል ታሪኩ በርጋታ ፣ «ልክ ነሀ ። ግን እንዲሀ ዓይነቱ ነገር ጊዜ ይወስዳል ። ንቃት ሲባል ከሕ ዝቡ ንቃተ ሕሊና ውጭ ወይም በላይ ሊሆን አይችልም ። ነጥ ቡን ይሊቃል ። ጓድ ፣ ንቃት ጊዜ ይወስዳል.... ጊዜን ይጠይ ቃል ፣ በግድ የሚሆን ነገር አይደለም ። እነሱን ለማንቃት እነ ሱን መምሰል አለብን ።»

፮

ለራት ጋሌጣና የቆርቆሮ ምግብ ተሰጠን ። ከቆርቆሮ ም ግብ ውስጥ ሽሮ፣ ዝግኒ ወይም አትክልት መርጦ መብላት ይቻ ላል ። ከሁሉም አንጀት ገብቶ የሚፈውሰው ግን «ሚሊ ድራፍት» ነበር ። የበሰ ብጥብጥ ነው ። በስኳር ተበጥብጦ ካደረ ትንሽ ስለሚፈላ ትንሽ ሞቅ ያደርጋል ። ስራብ! ስውሀ ጥም! ለመጠጥ!

ምን ጊዜም «ሚሊድራፍት!» ይላል የጦር ሜዳው ማስታወ ቂያ ። ሁሉም በስኳርና በውሀ በጥብጦ ያቀዘቀዘውን ሚሊ ድራ ፍት ሲጋብዘን ይፎረፉጥ ነበር ። «ከንቲባ» ከአምባሦይራ ኒያላ ፣ ከኒያላ ከረን እያለ የቀዘቀዘ ሚሊ ድራፍት በጋቤጣ መለጋት ጀ ምሮ አል ። «ከንቲባ በሞቴ!» የማይለው ወታደር አልነበረም ። በጊዜ ተኛን ። ልብስ ፣ ጫማ ማውለቅ የለም ። ከነጫማህ ትውላለህ ፣ ታድራለህ ፣ ትሞታለህ ። እባብና ጊንጥ ያስፈራል ። ሲቀፈኝ ሔጄ አሸዋ ውስጥ ተኛሁ ። ሁሉም እንደኔ በጀርባው ተኝቶ ኮከብ ይቆጥር ነበር ። የጠራው ሰማይ ቀረብ ያለ መስሎ ይታያል ። ቢደከመኝም እንቅልፍ እምቢ አለኝ ። ያሳለፍኩት ማዕከላዊ ሕይወት ባሳቤ መጣ ። ከሁሉም ትዝ ያለኝ በወህኒ ቤት ሲሚንቶ ላይ እየተኛሁ ያሳለፍኩት ያንድ ዓመት ጊዜ ነበር ። አሁን ሳስበው እንድ ዓመት ብቻ ሆኖ አይታየኝም ። አሥር ዓመት ሆኖ ይሰማኛል ። ቀኖቹም ረጂም ነበሩ ። ምግቡና መኝ ታው በጣም መጥፎ ነበር ። እና የታሰርኩት ደግሞ ከተራ ሌቦ ችና ማጅራት መቺዎች ጋር ነበር ። ለእነሱ እሥር ቤቱ እንደቤ ታቸው ነበር ። ፍርዳቸውን ጨርሰው የተለቀቁ እለት እንዴት እንደሚሰርቁና ማጅራት እንደሚመቱ ከማሰብ ሌላ አሳብ አል ነበራቸውም ። እኔም በሌብነት ነበር የታሠርኩት ፣ በፍቅር ሌብነት ። በጣም የምወዳት አንድ ልጅ ነበረች ። ሂሩት አንናፍር ትባላለች ። የ17 ዓመት ልጃገረድ ነበረች ። እኔም የሐያ ዓመት ጎረምሳ ነበርኩ ። ተዋደድን ። ይገሯት ኮበለልኩ ። ገንዘብ አልነ በረኝም ። አብዛኛውን ጊዜ ምግባችን ፍቅር ነበር ። የአሥራ ሁለተኛ መልቀቂያ ፈተና ለመውሰድ ስዘጋጅ ነበር ይገሯት የኮበለልኩት ። እሷ የአሥረኛ ክፍል ተማሪ ነበረች። ከአንድ ወር በኋላ ታድነን ተያዝን ። ቤተሰቦቿ ከመኳንንት ዘር ነበሩ ። በተለይም እናቷ ከእቴጌ ጋር የቅርብ የሥጋ ዝምድና አላቸው ይባል ነበር ። ልጅቷ በዘመድ ዛቻና በእባቷ ዱላ ብዛት ፣ ፍርድ ቤት ቀርባ ፣ ያለውዴታዋ በግድ ያስኮበለልኳት መሆኔን በመ ሐላ መሰከረች ። ለመከራከር አልቻልኩም ። ጠጉሬን ተላጭቼ ወህኒ ቤት ወረድኩ ። ለፍቅር የተከፈለ ከቡር ዋጋ ነበር ። ገና ወደፊት ፍቅር የሚጠይቀኝ የበለጠ ዋጋ ይኖር ይሆን? ብዬ አሰ ብኩ ። በሮማን ኀለተ ወርቅ ቀርጨ ነበር ። አሁን ግን እርግጠኛ አይደለሁም ። ፊያሜታ ጊላይ ከቀይ ኮከብ ዘመቻ ጋር ድንገት ልቤ ውስጥ ገብታለች ። ከሮሚ ጋር ላወዳድራት አልፈለኩም

ግን ብልህነቷ ፣ ንጽሕናዋ ፣ ቀልድና ለሕይወት ያላት ፍቅር ለጊዜው አመዘነብኝ ። ምናልባት የቅርብ ጉዳይ ይሆናል ። አላውቅም ። ጠፍቻለሁ ። ምናልባት እንደ እድል ሆኖ በዚህ ጦር ሜዳ ራሴን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አውቀው ወይም አገኘው ይሆናል ፣ ወይም ለዘላለም እንደጠፋሁ እቀር ይሆናል ......

ዘሕይወት ከለውጥ በቀር ምን ቋሚ ነገር አለ?...... ምን አሰጋህ ብዬ ፣ አሸዋ ውስጥ ተገላበጥኩ ። ምንም የሚያስጋ ነገር በዚህ ዓለም የለም ፤ ትኖራለህ ወይም ትሞታለህ ። ስጋቱ ምንድነው፤ ሕይወት እንዳመጣጡ ከያዙት የሚያሰጋ ነገር የለም......

«እንቅልፍ እምቢ አለህ እንዴ?» አለኝ የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና ። አጠገቤ ተኝቶ ነበር ።

«ያለ ጣራ አይሆንልኝም መሰለኝ?»

«የኛ ጣራ ሰማይ ፣ መኝታችን ዐፈር ነው ። የትም እንቅልፍ ይወስደናል» አለኝ ።

«ልምድ ይጠይቃል» አልኩት ።

«ምነው አይለመድ? ይኸውና ከሰማይ በቀር ጣራ ላይ ስምንት ዓመት ሊሆንኝ ነው ። ባለፉት ስምንት ዓመታት ጣራዬ የኦጋዴንና የባሌ ሰማዮች ነበሩ አሁን ደግሞ የኤርትራ ሰማይ ። እጅ አለመስጠት ነው ። ልቡ ላይ መቆም ። ማን ይፈራል ሞት!» አለ ·

«በውትድርና ነዋ የኖርከው?»

«ዕድሜዬን ሙሉ ። ሌላ ሥራ አላውቅም ። እንዋጋለን ፣ እንገድላለን እንሞታለን ። የቁማር ኑሮ ነው የምንኖረው ። እጅ አለመስጠት ነው!» ካለ በኋላ በውትድርና ስላሳለፈው ሕይወት አንስቶ ያጫውተኝ ጀመር ።

በሐያ ዓመቱ ነበር ወታደር የሆነው ። በትምህርቱ ጎበዝ ነበር ። ወታደር ለመሆን የመረጠበትን ምክንያት አያውቅም ። ምናልባት ዩኒፎርሙ ይሆናል የሳበው ። እግረኛ ወታደር መሆን የመረጠበትንም ምክንያት አያውቅም ። የአየር ኃይል ወይም

የባሕር ኃይል ፣ ወይም የታንከኛ ወይም የመድፈኛ ብርጌድ አባል ለመሆን ይችል ነበር ። ባይሆን ከጣራ ሥር የሚተኛበት አልጋ ይኖረው ነበር ። የእግረኛ ወታደር ሕይወት የአህያ ሕይ ወት ነው ይላል ። ግን ከእግረኛ ወታደር ሕይወት ተለይቶ መኖር አይፈልግም ። የእግረኛ ወታደር ሕይወት ትምህርት ቤቱም ሕይ ወቱም ሆኖ ቆይቷል ። የእግረኛ ወታደር ሕይወት የአህያ ሕይ ወት ነው ያለበትን ምክንያት አስረዳኝ ።

አንድ ወታደራዊ መሬት ያለ እግረኛ ወታደር ተጋድሎ አይያዝም ። ከአየርና ከየብስ ምን በአይሮፕላንና በመድፍ ቢደ በደብ ያለ እግረኛ ወታደር የሞት ሽረት ትግል ፣ ሩጫ ፣ ላብና ደም ፣ ስቃይና ሞት አይሆንም ። በመጨረሻ የሚዋጉት ሰዎች ናቸው ። ጦርነትን የሚዋጉት አውሬዎች ወይም እማልክት አይ ደሉም ። ሰዎች ናቸው ። እግረኛ ወታደሮች ናቸው ። እንደ ማንኛውም ሰው ለመኖር ፣ ለማግባት ፣ ለመሳቅና ለመጫወት የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው ። እግረኛ ወታደር ነው በመጨረሻ ሳንጃውን ወድሮ ጠላትን የሚያጠቃው ፣ ለሞት ወይም ለመግ ደል የሚሮጠው ፣ ወደ ጠላት ወረዳ በደረቱ እየተሳበ የሚሔ ደው ፣ ላቡን የሚያንቆረቁረው ደሙን የሚያፈሰው ። ታሪክ ያስታውሰው ይሆን? የለም ። እዎ ፣ ታሪክ ይጻፋል ። ግን የሚ ጻፈው ታሪክ ምናልባት የሚያስታውሰው ነገር ቢኖር የጊዜውን ታክቲክና ስትራተጂ ፣ ከዚያም ግፋ ቢል የአዛዥ መኰንኑን ትርታ ይሆናል ። ታሪክ ጨካኝ ነው ። የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና ማን ነበር?የታሪክ ነገር ጉዳዩም አይደለም።ስም ነበር — በቃ ። በጦር ሜዳ ምንም ነገር እውን መስሎ አይታይም ። እውን ሆኖ የሚታየው ቁጥር ብቻ ነው ። ይህን ያህል ሰው ሞተ ፣ ቆሰለ ፣ ተማረከ ፣ ጠፋ — በቃ ። የተያዘውን ወረዳ ማጠናከር ፣ በተረፈው ቁጥር ላይ ተመስርቶ ለነገ ውጊያ እቅድ ማውጣት — ማጥቃት — ማፈግፈግ ። «ይኸው ነው የእግረኛ ወታደር ሕይወት» አለኝ በመጨረሻ ። በፈቃዱ ራሱን ለቀይ እምቡጥ ጦር ተልእኮ ለምን እንዳዘጋጀ ሊያስረዳኝ አልቻለም ። ለታሪክ ብሎ አልነበረም ። አሁን ጋሻ ጠናን ማን ያስታውሳል? የሚል ነበር መልሱ ። ወይም ሹመትና ሽልማት ፈልጎ አልነበረም ። ጋሻ ጠና የአለት ጉርሱንና የዓመት ልብሱን ካገኘና ጤና ከሆነ ስለኑሮ የሚያስብና የሚጨነቅ ሰው አይደለም ። ሞትን ፈልጎ አልነበረም ። እንደማንኛውም ሰው ሕይወቱን ፣ ሕይወትን ይወ

ዳል ። ወይም ሳገሩ ክብርና ለአብዮቱ መሳካት ከሌሎች ይበልጥ ተቆርቋሪና አሳቢ ሆኖ አልነበረም ። «እንጃ ፣ ብቻ ጥቂቶቻችን ራሳችንን አሳልፈን ለመስጠት ካልተዘጋጀን ሌላው እንዴት ሊኖር ይችላል ?» የሚል አሳብ ወይም እምነት ነበረው ። አባ ባሉ ትርጉም ሰጠኝ ። ሕይወትን መውደድ ብቻውን አይበ ቃም ፣ ሌሎችም እንዲወዱት ማስተማር ያስፈልጋል ፣ አዎ ፣ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ፍቅርን ያስተማረው በምን ነበር? ራሱን አሳልፎ በመስጠት ተግባር ነበር...... ውይይታችን ሔዶ ፣ ሔዶ ወደ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም አመራ ።

«አጋጆን አብረን ነበር ፣ ካብዮቱ በፊት» አለኝ ።
«እውነትነ?» አልኩት ።

«ያኔም እንዳሁኑ ጀግና ነበሩ ። ጀግና ሰው ደስ ይለኛል» አለ ።
«በቅርብ ታውቃቸው ነበር?» ብዬ ስጠይቀው ፣ ስለሊቀ መንበሩ የሚከተለውን ታሪክ አጫወተኝ ።

«መሐንዲስ የሆነ አንድ ወጣት መኰንን ነበር ። ሰጦሩ ጥቂት ቤቶች እንዲሠራ ይታዘዛል ። የተፈቀደለትን በጀት ቆጥቦ የተፈለጉትን ቤቶች ከታሰበው በላይ በጥሩ ሁኔታ ከሠራ በኋላ ፣ ቆጥቦ ባተረፈው ገንዘብ ለጦሩ ማለፊያ የመዝናኛ ሥፍ ራዎች ይሠራል ። ጦሩ በሙሉ በሥራው ተደሰተ ። በመጨረሻ ከፍተኛ መኰንኖች ያሉበት የቁጥጥር ኮሚቴ መጣ ። የቁጥጥር ቡድኑ የሚመራው በአንድ ጄኔራል ነበር ። ሥራው ተጎብኝቶ ገለጻ ከተደረገ በኋላ ጄኔራሉ ምሥጋና ያቀርባሉ ተብለው ሲጠ በቁ ፣ ያልታዘዝከውን ማን ሥራ አለህ? በማለት በወጣቱ የጦር መሐንዲስ ላይ የተግሳጽ ናዳ ያወርዱ ጀመር ። የጄኔራሉን ፊት ያዩ ሌሎች መኰንኖችም ፣ በወታደራዊ ደንብ ያልታዘዙትን መሥራት አግባብ አይደለም ሲሉ ተቹ ። ወጣቱ መሐንዲስ እንባው መጣ ። በመጨረሻ የተናገሩት ጓድ ሊቀ መንበር ፣ የያ ኻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ነበሩ ። «የተረፈው ገንዘብ ለተባለው ሥራ ወጥቷል ተብሎ ቢበላ ኖሮ ፣ በተጨማሪ ምን ተሠራ? ለምን ተሠራ? የሚለው ጥያቄ አሁን አጠያያቂ አይሆ ንም ነበር ፣ ቅን ሥራ የሚያስወቅስ ከሆነ ያሳዝናል!» ማለት የጄኔራሉን ቀንድ እንዴት እንደሰበሩና ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የእን

በሳው የመሣሪያ ግምጃ ቤት መኰንን ሆነው በሚሠሩበት ወቅት ፣ አንድ ሌላ ጄኔራል ፣ አንድ ቀን የመኪና መለዋወጫ ዕቃ ባስቸኳይ ላክ ብሎ ሲልክባቸው ለግል አውቶሞቢል ቀርቶ ለጦሩም የሚሆን መለዋወጫ ዕቃ የለም ብለው ስለሰጡት መልስ ካሜወተኝ በኋላ ቀጥሎም ፣ «መቸ ይሀ ብቻ አንድ ቀን ደግሞ እንዲህ ሆነልህ ። ንጉሡ ለጉብኝት ይመጣሉ ። ተመል ካች አጥተው የወደቁ መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎችን ትተው ደህና ደህናውን ነገር ብቻ እንዲጎበኙ ከበላይ ትእዛዝ ይሰጣል ። የሚያስቆጭና የሚያናድድ ትእዛዝ ነበር ። እንዲያስጎበኙ የታዘ ዘ ትም እሳቸው ነበሩ ። እንደታዘዙት ደህና ደህናውን ነገር ያስጎበኙና በመጨረሻ እንዲደበቁ የተደረገ ትንም ጥምር ንጉ ሡን ወስደው ያሳያሉ ። ንጉሡ በመቆጣት ካባቸውን አጥፈው ይሔዳሉ ። በዚህ ምክንያት ፣ በአለቆቻቸው ዘንድ ፣ አደገኛ መኰንን ነው እየተባሉ ሲጋዙና የማዕረግ እድገት ሲታለፉ ነው የቆዩት ። አይ ወንድ! አይ ጀግና! ከዚህ ጀግና ሰው ጋር ቁሞ መቆጋትና መውደቅ በእውነት ክብር ነው» በማለት ስለሰው ዬው የሚያውቀውን ያህል ነገረኝ ።

እንደምንም እንቅልፍ አሸለበኝ ። ዓይኔን ስከፍት ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ሆኖ ነበር ። የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና ባይቀሰ ቅሰኝ ኖሮ በጦር ሜዳም የጧት እንቅልፍ አሸንፎኝ እዚያው እቀር ነበር ። ጦሩ ለመንቃነቅ ተዘጋጅቷል ። ፍሬው ዘሪሁን መጥቶ «ማታ ጉድ ልንሆንልህ ነበር» አለኝ ፡

«ምን ሆናችሁ?»

«እኔና አሸብር ማታ ሜዳ ወጥተን ስንመለስ ዘቡ ፣ «ቁም! አንተ ማነህ?» ሲሉ ጉድ ፈላልህ ሁለታችንም ደንግጠን ነው መሰለኝ ፣ የይለፍ ቃሉ ተረሳን ። አሸብር አስታውሶ ፣ «እረ በፈ ጠረህ! «ሹኮች ነን!» ባይለው ኖሮ ይጨርሰን ነበር» አለኝ ።

ሳቅሁና «ከንቲባ ነኝ አትለውም ኖሮአል?» አልኩት ።

ነገሩ በጦሩ ዘንድ ተሰምቶ ኖሮ ፣ ጋዜጠኞች መባላችን ቀርቶ ፣ «ሹኮች» እየተባልን መሳቂያ ሆነን ነበር ። ኰሎኔል ታሪኩ ነበር መጥቶ በመጀመሪያ ፣ «ሹኮች» እንደምን አደራችሁ? ያለን ።

«ጦር ሜዳ ይለማማሀል ልበል?» አልኩት ።
«እንዴት?» አለኝ ።
«ደልቶህ ያደርክ ትመስላለህ»

ፊቱ ያበራ ነበር ። ሰብእናውም ተለውጧል።ጥሩ ፈገግታ ከፊቱ ላይ ይታያል ። ካላሽን የጨበጠው እጁ ሥራ ይዟል ። ርምጃውም ቅልጥፍና የተሞላበት ነበር ።

«ወታደር ነፍስ የሚዘራው ሥራው ላይ ነው» አለኝ ።
«ሹኮችም ከእንግዲህ ነፍስ ይዘራሉ ። ታያለህ» አልኩት ።

ምን ምን እንደምሸትና ምን እንደምመስል ካሁኑ ጠፍቶኛል ። ምን ምን እንደምሸት አላውቅም ። ምኞትና ሕልውና ትርጉም አልነበራቸውም ። እውን ሆኖ የሚታየኝ ነገር ቢኖር ከፍታ ነጥብ 1702 ብቻ ነበር ። እና እያንዳንዱ ሰው ወደ መጨረሻ ግቡ ፣ ወደ ተወሰነለት ጥሪ ፣ ይፈጥን ነበር ። በፍጥነት ነበር የምንጓዘው እንዴ ብቻ ነበር ለውሀ የቆምነው ። የሞቀ ውሀ እየተሰማማኝ ሔዷል ። ወታደሩ በዚህ በረሀ ከቀዝቃዛ ይልቅ ትንሽ ሞቅ ያለ ውሀ ነው ጥም የሚቆርጠው ሲለኝ ይገርመኝ ነበር ። ነገሩ እውነት ሆኖ አገኘቼዋለሁ ። ጸሐይ ከመጥለቋ በፊት እንደ ገሠገሥን ሔደን ፣ የ17ኛ ክፍለ ጦር መሰብሰቢያ ወረዳ ከሆነው ከከፍታ ነጥብ 492 ደረስን ። የ17ኛ ክፍለ ጦር አባሎች በሆታና በጭብጨባ ደማቅ የሆነ አቀባበል አደረጉልን ። እጅግ የሚያስደስት አቀባበል ነበር ። የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች ራሳቸውን ለውጊያ ከማዘጋጀት በቀር በሠፈሩ ሌላ ግዳጅ አልነበራቸውም ። እንዲያውም የ17ኛ ክፍለ ጦር አባሎች አስተናጋጅ በመሆን ምግብ ፣ ውሀ ከማቅረብም ሌላ ልብሶቻቸውን ወስደው ያጥቡላቸው ነበር ። የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች ሰውነታቸውን እንዳ የጸዱ ታዘዙ ። ካሜራችን ተከተላቸው ። ገላቸውን ሲታጠቡ አፋፍ ላይ ቆሜ እመለከታቸው ነበር ። ራሳቸውን ለሞት የሚያጠምቁ መሰለው ታዩኝ ። ለዚህ አደገኛ ተልእኮ እያንዳንዳቸውን ያነሳሳው ነገር ምን እንደሆነ አላውቅም ። እያንዳንዳቸው ለዚች አገርና ለዚህ አብዮት ከሌሎች ይበልጥ ተቆርቋሪ ሆነው አይደለም ፣ ወይም አይመስለኝም ። ግን አንድ ነገር ይሰማኝ ነበር ። በውስጣቸው የሕይወት እሳት የሚነድ ነጻ ሰዎች ነ

በሩ ። ነጺ ሰው ውብ ነው ፣ ቆንጆ ነው ። እና ሁሉም ውቦች ፣ ቆንጆዎች ነበሩ ። ልቤ በጣም አዘነ ። ጀምበሯ ከናቅፋ ተራሮች በስተጀርባ ልትጠልቅ አሽቆልቁላለች። ሰማዩ እንደ ደም ቀልቶ ይታይ ነበር ። ቀጥሎ የሆነው ነገር ነው በይበልጥ ልቤን የነካው ።

የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች ለዘመዶቻቸው ወይም ለተወካ ዮቻቸው ፣ ወይም ለሚመለከተው ሰው የሚያስተላልፉት መል እክት ካላቸው እንዲጽፉ ተጠይቀው ነበር ። ምን መልእክት እንደሚተው ለማወቅ ፍላጎት ስላደረብኝ አንዳንዶቹ የጻፉትን እንዲያሳዩኝ ጠይቄአቸው ነበር...... «ምናልባት አደጋ ደርሶብኝ የሞትኩ እንደሆነ ያለኝ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ለቀይ ኮከብ ዘመቻ እንዲሰጥልኝ እጠይቃለሁ» የሚሉ መልእክቶች ብዙ ነበሩ ። አሳልፈው የሚሰጡት ውድ ሕይወታቸው አልበቃ ብሎአቸው ይሆን? በማለት ተገረምኩ ። ለሚ ት ፣ ለልጅ ፣ ለወንድም ፣
ይሆን? በማለት ተገረምኩ ። ለሚስት ፣ ለልጅ ፣ ለወንድም ፣
ለእህት ፣ ለአባት ወይም ለዘመድ የተጻፉ ደብዳቤዎች ጥቂት አልነበሩም ። አንዳንዶቹ ፣ ስለጉዞአቸውና አሁን ስለሚጠብቃ ቸው ተልእኮ ነበር የጻፉት ። እና አብዛኛዎቹ ደብዳቤዎች ፣ «ከዚህ በኋላ የሚሆነውን ሌላ ጊዜ እጽፋለሁ ። ስለኔ አታስቡ ። ደህና ነኝ ። ለምንድነው የማትጽፉልኝ? እኔ ካንቺ...... ወይም ካንተ ናፍቆት በስተቀር ሌላ አሳብ የለኝም......» በሚሉ ዐረፍተ ነገሮች የተደመደሙ ነበሩ ። ከዚህም ባሻገር ፣ «ናቅፋ ደርሰናል ። እንደ ኢያያዛችን ከሆነ ይህ ጦርነት ጊዜ የሚፈጅ አይመስልም ። በቅ ርብ ቀን እመጣለሁ ። እስከዚያ ድረስ ገንዘብ ካለ ላኪ (ወይም ላክ) ። ራዲዮና ቴፕሪኮርደር አልጌናና አፍአበት በርካሽ ዋጋ ይገኛል ።» ካሉ በኋላ ፣ ሲመለሱ ምን ለማድረግ እንዳሰቡ በዝ ርዝር የጻፉ ሰዎችም ነበሩ ። አንዱ ባጠራቀመው ገንዘብ ያቺኑ ማሳ እንዴት እንደሚያለማና ያቺን ጎጆ እንዴት እንደሚያቃና ይጽፋል ። ሌላው በችግር ምክንያት ያቋረጠውን ትምህርት እን ዴት አድርጎ እንደሚቀጥልና እምን ደረጃ ድረስ ለመማር እን ደሚፈልግ ያትታል ። ከጦር ሜዳ አያሌ ጠቃሚ ትምህርት አገኛቻለሁ ።

ተለውጫለሁ ፣ ከእንግዲህ እንዳለፈው ጊዜ ተመልሼ የም ቀብጥ አይመስለኝም ። መጠጥ የሚባል ነገር ትቻለሁ ። እንደ

ድሮው በትንሹም በትልቁም ነገር አልናደድም፡፡ጦር ሜዳ ያስከ ፍል ፡፡ ውዶ ሙች ፣ ቅናትም ትቻለሁ ፡፡ አሁን የምቀናው በሕይ ወት ብቻ ነው ፡፡ አሁን የምመኘው ነገር ቢኖር ደስታና ተድላ የሰፈነበት ፣ የሰከነና የቀዘቀዘ ኑሮ መኖር ብቻ ነው ፡፡ ወደፊት የምንኖረው ኑሮ ይታየኛል ፣ ልጄን ሳሚልኝ ፡፡ ስመለስ የበደል ኳችሁን በደል ሁሉ ድርብ አድርጌ እከሳለሁ በማለት የፉጸ ሌሎችም ነበሩ ፡፡ አዎ ፣ በሰው ልብ ተስፋ ምንጊዜም አይሞት ፡፡ ሕይወት ካለች ተስፋ ምን ጊዜም ይኖራል ፡፡ «በማደርገው መራራ ትግል ወድቄአለሁ»፣ «ለድል በሚደረገው ትግል ተሠው ቻለሁ» ፣ «ናቅፋ የኔ መቃብር ፣ ያብዮቴ አምባ ትሆናለች» ፣ «ሞት አይቀርምና የሚሞቱበትን ቦታና ሁኔታ መርጦ መሞት ታላቅ እድል ነው ፡፡ ግን ናቅፋን አደራ ፣ እኔ የታሪክ ሰው አይደ ለሁም ፡፡ ተራ ወታደር ነኝ ፡፡ ግን ለኢትዮጵያችን ሕልውና ኤርት ራን ወሳኝ ናት ሲሉ ሰምቻለሁ ፡፡ ለኢትዮጵያ ሕልውና ተሰው ቻለሁ ፡፡ ከሕይወቴ በቀር ላገሬ የማበረክተው ሌላ ውድ ነገር የለኝም ፡፡ ወገኔ ፣ ከኢትዮጵያ ሕልውና ሌላ አደራ የለኝም ፡፡ አደራህን ፡፡ በኤርትራ ምድር የተከሰከሰው አጥንቴ በቁጣ እንዳ ይጮህ አደራ!» ወዘተ የሚሉም መልእክቶች ነበሩ ፡፡ የሚ ገርመው ነገር እኔ የማስተላልፈው መልእክት አልነበረኝም ፡፡ ጨርሶም አላሰብኩበትም ነበር ፡፡ ስለሞት አስቤ አላውቅም ፡፡ የሙያዬ ባሕርይ ፣ ያለምንም ስጋትና ጭንቀት በማያቋርጥ አሁን» ሁኔታ ውስጥ የመኖር ልማድ አሳድሮብኛል ፡፡ ስለወ ደፊት ለምን ይታሰባል? ትኩስ ዜና ፣ ትኩስ ሕይወት! ሞት ለኔ ምኔም አልነበረም ፣ ሆኖም አያውቅም ፡፡ ትኩስ ዜና ከማጣት ፣ አበቦችን ካላማየትና የቆንጆ ሴት እጅን ለመንካት ካለመቻል የበለጠ ስቃይና መለየት ምን ይኖራል! ሞት ትርጉም ሰጥቶኝ አያውቅም ፡፡ ምናልባት እድሜ ስላልተጫኑኝ ይሆናል ፡፡ ሞት ሲቃረብ አሳቤ ምናልባት ሳይለወጥ አይቀርም ፡፡ አላውቅም ፡፡ አሁን ግን ሞት ሩቅ ሆኖ ነው የሚታየኝ ፡፡ ምን የሚያሰጋ ነገር አለ ? ከሞትክ ሁለት ነገር ብቻ ያስገሀል — መንግሥተ ሰማ ያት ትገባለህ ወይም ገሀነብ ትወርዳለህ — እንዲህ ያለ ነገር ካለ ማለቴ ነው ፡፡ መንግሥተ ሰማያት ከገባህ ምንም የሚያሰጋህ ነገር የለም ፡፡ ገሀነብም ከወረድክ የሚያሰጋህ ነገር የለም ፡፡ ከጓ ደኞችህ ጋር እጅ ለእጅ ስትጨባበጥ ለስጋት ጊዜ አይኖርህም» የሚል ጥቅስ የት እንዳነበብኩ ቦታው ጠፋኝ ፡፡ ከከፍታ ነጥብ

1702 ሌላ የሚያሰጋኝ ነገር አልነበረም ። እሱም ቢሆን ምን ያሰጋል፣ ይያዛል ወይም አይያዝም ። ይልቅ ጭንቀቴ ዜናውን እንዴት አድርጌ እንደማስተላልፍ ነበር ። ጭንቀቴ ምንድነው፣ ዜናውም ቢሆን ይተላለፋል ወይም አይተላለፍም ። ነገ ምን ትር ጉም አለው፣ ሬ.ው ለምን ይጨነቃል፣ እውን ነገር አሁን ብቻ ነው ። አሁን አለሁ ፣ ደህና ነኝ ፣ እተነፍሳለሁ ፣ ውብ ኮከቦች እቆጥራለሁ ፣ ይበቃል ። አሁን አለህ ወይም የለህም ። ጭንቀቱ ምንድነው፣...... ሲሊት ሁለት ጊዜ በእንቅልፍ ልቤ ቃዢቼ በመ ባነን ነቅቼ ነበር ። ሁለቱንም ጊዜ ላብ አስምጦኝ ነበር ። አንድ ጥይት በሑድኩበት እየተከተለች ታባርረኛለች ። እንዳትመታኝ እሮጣለሁ ። ላመልጣት አልችልም ፣ ትደርስብኛለች ። ገደል አፋፍ ላይ እደርሳለሁ ፣ መሔጃ የለኝም ። እና ጥይቷ እየተወረ ወረች ትመጣብኛለች ። ባንኜ እነቃለሁ ። በሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ከፍታ ነጥብ 1702 ላይ የወጣን ይመስለኛል ። ጠላት የለም ። ተራራው እንደ ሰው ልብ ሲመታ ይሰማኛል ። ቆይቶ የተራራው ትርታ አደንቋሪ ይሆናል ። ልቤ አብሮ ይሸበራል ፣ ነፍሴ ተጨን ቃለች ። ተራራው ተጠምዶ እንደቆየ በምብ ድንገት ይፈነዳል ፣ ዓለም ይደበላለቃል ፣ ምጽዓት ይሆናል ፣ ጠርብ ድንጋዮች ሰማ ዩን ያለብሱታል ። እንደገና እያላበኝ እነቃለሁ ።

ልክ በ10 ሰዓት ከመሰብሰቢያ ወረዳችን ከከፍታ ነጥብ 492 ተንቀሳቀስን ። ቲከሲ ላይ ቶሎ ይነጋል ። ሮራ ጸሊም ላይ የንጋት ጸሐይ በሙሉ ድምቀቷና ውበቷ ስትወጣ ማየት እጅግ ያስደንቃል ። ተፈጥሮ ውብ የንጋት ትርኢት የምታሳይበት ቦታ ነው ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍታ ነጥብ 1702ን ከሩቅ አየሁ።የአካ ባቢው ትልቁ ተራራ ባይሆንም ከሌሎቹ ይልቅ ግርማ ሞገስ ተጎናጽፎ ታየኝ ። ቀጥ ብሎ ከምድር ወደ ሰማይ የተወረወረ ሹል ተራራ ነው ። የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና ነበር ተራራውን ያመ ለከተኝ ። የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች በሙሉ አንጋጠው ተራራ ውን በአድናቆት ይመለከቱ ነበር ። ፊታቸው ያበራል ። ያውና የመጨረሻ ግባቸው፣ የልባቸውን ትርታ የሰማሁ መሰለኝ ፣ እንደእውነቱ ከሆነ ግን የራሴን የልብ ትርታ ነበር የማዳምጠው ።

ኮሎኔል ታሪኩ ወደኔ ሲመጣ አየሁት ። አረማመዱ ሁሉ ፈጣንና ቀልጣፋ ሁኗል ። አዲስ ዩኒፎርም ለብሷል ። ተርብ መስሏል ።

«ዛሬ አምሮብሀል» አልኩት ።

«የክት ልብሴን ነው» ብሎኝ ፡ ከሩቅ የሚታየውን ተራራ በዓይኖቹ ሲቃኝ ከቆየ በኋላ ፡ «ቆንጂ ተራራ ነው ። መቃብሬ እዚያ ላይ ቢሆን አይከፋኝም ። ለሰማይ ቅርብ ነው ፡ አይመስ ልህም?» አለኝ ።

«እኔስ ለመቃብሬ አዲስ አበባን ነው የምመርጠው ። ብዙ አበባዎች ያሉበት ቦታ ይሻለኛል» አልኩት ።

«እኛ ይህን ተራራ መርጠናል» አለኝ ።

«የሚሞትበትን ቦታ ማንም ሊመርጥ አይችልም ፡ ጀግኖ ችም ቢሆኑ» አልኩት ።

«ደርሰናል እንግዲህ» ብሎኝ ጦሩን ተከትለን ወደ ውጊያ ወረዳው እንዴት እንደምንሔድ አስረዳኝ ። ከጦሩ ኋላ መሆን ነበረብን ። የሕክምና ጓድ ኃላፊ የሆነ አንድ አሥር አለቃ በባል ደረባነት ተሰጠን ። ማንኛውንም መመሪያና ትእዛዝ መቀበልም ያለብን ከእሱ ነበር ። ወደ ከፍተኛ ነጥብ 1702 የሚወስደው መጠጊያ መንገድ ሁሉ በፈንጂ ታጥሮአል ። እና ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ። አለዚያ በፈንጂ ድንገት ወደ ሰማይ ጉነን እንደምንቀር የታወቀ ነገር ነበር ።

«አይዞህ ፡ ስለኛ አታስብ» አልኩት ።

«እንድትሞቱ አልፈልግም ። የወሬ ስንቅ ይዛችሁ ብትመ ለሱ ይሻላል» አለኝ ።

«ንገረኝ ታሪኩ በሞቴ ፡ ስለሞት አስበህ ታውቃለህ?» አልኩት ። ከብረት ቆቡ ውስጥ ወጥቶ የተንጠለጠለውን ረጂም ጠጉሩን መዞ እየገመደ ፡ «ወታደር በውጊያ ሜዳ ስለሞት አያስብም» አለኝ ።

፮

«እንዴት?» አልኩት ።

«የቀበሮ ጉድጓድ ስንቆፍርና ፡ በደረት ስንሳብ ፡ ስንፏቀቅ ፡ በቀበሮ ጉድጓዳችን ውስጥ ሆነን ሲያልበንና ስንሰጋ ፡ ሰናጠቃና ስናፈገግፍግ ፡ ስለሞት ለማሰብ ጊዜ የለንም ። እንዴት ልበልህ?

ጠላት ነው ሁልጊዜ የሚሞተው ፣ አንተ አይደለህም» ካለ በኋላ ፣ ባሳብ ተውጦ ቆየና ፣ «ይልቅ ሕይወት ነው የሚያሳስበው ፣ ሞት አይደለም» ብሎ የእጅ ሰዓቱን ተመለከተና ፣ ውጊያው የሚጀመርበት ጊዜ ተቃርቧል ። አደራችሁን ተጠንቀቁ ። ቻው ። ከፍታ ነጥብ 1702 ላይ እንገናኛለን» በማለት በጣቶቹ የድል ምልክት አሳየኝና ትንሽ ከሔደ በኋላ ተመልሶ መጣ ። አተኩሮ ተመለከተኝ ። አንድ ነገር ሊነግረኝ ነው ብዬ ስጠብቅ አሳቡን ለውጠና ምንም ሳይለኝ ዝም ብሎ ተመልሶ ሔደ ። ምን ሊነግረኝ ፈልጎ ይሆን? ሆዴን ቆረጠኝ ።

ከዝቅተኛ መሬት በመጀመር ቀጥተኛ ግድለት ያለውን ተረተር በግራ በኩል ይዘን ወደ ግባችን እንጢጋ ጀመር ። አካሔዳችን ስንዝር በስንዝር ነበር ። ጊዜ ራሱ ድንገት ቀጥ ብሎ የቀረ መሰለኝ ። ተራራው ተረተሩ ፣ ሸለቆውና ግድለቱ እንደ መቃብር ጸጥ ብሎአል ። የዓለም ልብ ትርታ ድንገት ቀጥ ብሎ ፣ ሕይወት ለዘላለም አሸልባ የቀረች ያህል ሆኖ ነበር የሚሰማው ። የሰፈነው ጸጥታ ከባድ ውጥረትና ጭንቀት ሰው ላይ ያሳድራል ፣ ስጋት ይፈጥራል ፣ ያስጨንቃል ። የ17ኛ ክፍለ ጦር አካል የሆኑት 19ኛ እና 11ኛ ብርጌዶች ሥርጡን ይዘው ከቀይ እምቡጥ ሻሊቃ ጦር ግራና ቀኝ ተሰልፈዋል ። ሁለቱም ብርጌዶች ቀደም ብለው በውጊያ ወረዳው በመገኘት መሽገዋል ። ሁሉም ከቀበሮ ጉድጓዳቸው ውስጥ ሆነው ይታያሉ ። ሙቀቱ አይጣል ፣ 38 ድግሪ ሴንቲግሬድ ደርሷል ። ኰሎኔል ታሪኩ የተናገረው ሐቅ በመጠኑም ቢሆን ተከሰተልኝ ። ጦርነት ሲባል ሁልጊዜ የጨበጣ ውጊያ ማለት አይደለም ። በአብዛኛው ከቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ የጠላትን ተኩስ ውርጅብኝ እያዳመጡ ላብ የመድፈቅ ፣ በስጋት የመጨነቅ ፣ በደረት እንደድመት የመሳብ ፣ የመንፏቀቅ ፣ ወሳኝ ሰዓት ስትደርስ የማጥቃት ፣ ቦታ የመያዝ ካልሆነም የማፈግፈግ ተግባር ነው ። ጦርነት እንደ ዳማ ጨዋታ ነው ። ግራና ቀኝ ጎንህንና ጀርባህን እየጠበቅህና የጠላትን ደካማ ጐን እያየህ እንደሁኔታው ታጠቃለህ ፣ ወይም ታፈገፍጋለህ ። የጠላት ተኩስና ኃይል ከበረታብህ ታፈገፍጋለህ ፣ ከተከበብክና መውጫ ካጣህ እጅህን ትሰጣለህ ። የጦርነት ጨዋታ ደንብ እንዲሁ ቢሆንም ፣ አብዛኛውን ጊዜ ደንቡ በተግባር አይውልም ። የጠላት ተኩስ ምን ቢበዛ፣ ኃይሉ ምን ቢጠናከርና ከበባው ምን ፍጹም ቢሆን ፣ ሰዎች

አብዛኛውን ጊዜ እስከመጨረሻው ሰው ድረስ ይዋጋሉ ። በጦር ሜዳ ሎጂክ አይሠራም ። የተረፉት ጀግኖች ይሆናሉ ። የሞቱትስ? ክብር ለሙታን። በእውነት ጦርነት አስቀያሚ ነው ። ያስጠላል ። ግን የሰው ልጅ ያለ ጦርነት የኖረበት ጊዜ የለም ። የሰው ልጅ ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው ። የሰው ልጅ ያለጦርነት የሚኖርበት ጊዜ ይመጣ ይሆን? ምኞት ነው። የጦርነትን ጥፋት በሰው ልጆች ላይ የሚጋብዙ ሠይጣናዊ ኃይሎች እስካሉ ድረስ ምን ተስፋ ይኖራል?

በየተራራውና በየተረተሩ ሰፍኖ የቆየው ከባድ ጸጥታ ድንገት ተናግቶ ምድር ቀውጢ በመሆን ፣ መድፎች ያጓሩ ፣ የስታሊን አርጋኖች ተራራውንና ተረተሩን ያናግሩ ፣ መትረየሶች ይንፈቀፈቁ ከላሽኖች በየጎራው ይንጣጡ ጀመር ። ባንድ ጊዜ ድብልቅልቁ ወጣ ። እየሩ በፈንጂ ጢስና በጥይት ባሩድ ሽታ ተበከሏል ። ተዋጊ አይሮፕላኖች እንደ ቀስት ከሰማይ ወደ መሬት እየተወረወሩ አስበርጋጊና አስፈሪ ድምጽ ሲያሰሙ ከቆዩ በኋላ ከፍታ ነጥብ 1702 ፣ ካርታ ቁጥር 5044 ላይ የቦምብ ዝናብ ያዘንቡ ጀመር ። የወገን ከባድ መሣሪያ ከግራና ከቀኝ ያለ ማቋረጥ ያጓራል ። ተራራው ፣ ይቃጠላል ፣ ይነዳል ፣ ይጋያል ። የጠላት ባለ 50 ካሊበር መትረየሶች ከየተራራው ጫፍ ይንተከተካሉ ፣ ያስካካሉ ። ጸረ አይሮፕላኑን ያደበላልቁታል ። ቢ—10 ጸረ ታንክ መሣሪያዎች ይተኮሳሉ ። የእጅ ቦምቦችና ፈንጂዎች እንደ ነጎድጓድ ይጮሀሉ ። ሰዓቱ ደረሰ!

ባልደረባችን ያስር አለቃ ዳምጤ መሣሪያዎቹን በድምጽ እየለየ ያመለክተኝ ነበር።መድፍ —ቦምብ —ፈንጂ —ሞርታር —ጸረ ታንክ —ጸረ አይሮፕላን አር ሦ.ጂ —ዶሽካ ሦቴ አር ዙ23— ቢ.ኤም — ወ.ዘ.ተ ። ካሜራችንን አንድ ምቹ ቦታ ላይ ጠምደን ነበር ። ፊልሙ ይዞራል ።

«እንዴት ነው?» አልኩት አሸብርን ።

«እስካሁን ጥሩ ነው ። ተራራው ጥሩ ሆኖ ይታያል ። ግን ለመጠጋት እንዴት ነው የምንችለው?» አለኝ ።

«ለመጠጋት ፈጽሞ አትችሉም ። እንኳን ለናንተ ለወታደሩም አስቸጋሪ ነው ። የሞት ተራራ ነው» አለኝ ። ያ10/ አለቃ ዳምጤ

«ከዚህ በኋላ ምንድነው የሚሆነው?» አልኩት ።

«እንግዲህ የቀይ እምቡጥ ጦር ግዳጅ ተቃርቧል ። አሁን መሐል ለመሐል ወደ ተራራው እየተጠጉ ናቸው ። ጊዜው ሲደርስ ከ11ኛ ብርጌድ በስተጀርባ ድንገት በመዞር ፥ በግራ በኩል ሰብ ረው ለመውጣት ነው የተዘጋጁት » አለኝ ።

«በዚያ በኩል ግድሰቱ ቀጥተኛ ስለሆነ አስቸጋሪ አይሆን ባቸውም ወይ?» አልኩት ።

«የተመረጠውም በዚህ ምክንያት ነው.....»

«እንዴት? ለምን?»

«በዚያ በኩል ይመጡብናል ብለው አያስቡም ተብሎ ስለ ታሰበ ነው» በማለት አስረዳኝ ።

«እስቲ ተስፋ እናድርግ» አልኩት ።

ከ58ኛ እና ከ51ኛየጠላት ብርጌዶች የተውጣጣ 1ኛ እና 3ኛ ሻለቃ ጠንካራ ኃይል ከፍተኛ ነጥብ 1702 ላይ መሽጎ የሚጠ ባበቅ መሆኑ ታውቋል ። ትኩረታቸው መሐል ለመሐል ሰንጥቆ በሚመጣው ቀዳሚ ጦርና ተደራቢና ደጀን ጦር ላይ መሆኑን ከአኳኋናቸው ለመረዳት ይቻል ነበር ። የተፈለገውም ይህ ነበር ። ተራራውን በከባድ መሣሪያና በተዋጊ አይሮፕላኖች የመደብደቡ ሥራ ቀጥሏል ። ዓለም ተደበላልቋል ። የሚሰማው የተኩስ ድምጽ እብዶች ተሰባስበው በምጽአተ መድረክ ላይ እንደሚጫወቱት ሙዚቃ ነበር!በተዋጊ አይሮፕላኖች የታጀቡ ትላልቅ አይሮፕላን መዋተው ተራራው ላይ ፓራ ኮማንዶዎችን በጃንጥላ ያወርዱ ጀመር ። የጠላት ተኩስ በረከተ ። ልቤ ተሰቀለ ። ግን ዓይኖቼን ለመክደን አልቻልኩም ።

«ምነው! ለእልቂት መዳረግ አይሆንም!» አልኩት ያሥር አለቃ ዳምጤን ።

«አይዞህ! ደሚዎች ናቸው» አለኝ ።

ደሚዎች ከሩቅ ሲመለከቷቸው ልክ የእውነት ሰዎች ይመ ስላሉ ።

«በቃ አሁን ነው!» አለ ።

«ከንቲባ» ስሜት ይዞት ወደ ፊት ሮጠ ። እንዲመለስ ብሎ ሀበትም ሊሰማኝ አልቻለም ። ተከተልኩት ። ደመ ነፍሴን ነበር የምሮጠው ፣ እሱን ለመያዝ ይሁን ወይም ከእሱ ጋር ለመሑድ ፣ የማደርገውን ነገር አላውቅም ነበር ። 19ኛ እና 11ኛ ብርጌዶች በቀኝና በግራ በኩል ሣንጃ ወድረው እየተኮሱ ተንቃነቁ ። የቀይ እምቡጥ ጦር አባሎች ልክ እንደተባለው ከ11ኛ ብርጌድ በስተጀርባ ዞረው ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 የሚያወጣውን አስቸጋሪ ግድለት ተያይዘውት ነበር ። ኰሎኔል ታሪኩ ፣ ሰዎቹን በያዘው ሽጉጥ ወደፊት እንዲሔዱ እየጋበዘ ፣ ካንዱ መረማመጃ ድንጋይ ወደ ሌላ በመዝለል ፣ ከጦር ጓዶቹ ፊት ቀድሞ ተራራውን ተያይዞታል ። የመቶ አለቃ ጋሻ ጠና ከጎኑ ነበር ። ጦሩ ከሚተኩሰው ጥይት ይልቅ በወኔ የሚያሰማው የውጊያ ጩኸት ይበልጥ የሚያስፈራ እና የሚያስበረግግ ነበር ።

ከንቲባን ደርሼበታለሁ ። ግን ተመለስ አላልኩትም ። ቀይ እምቡጦችን ተከትለን ጋራውን እንቧጥጥ ጀመር ። የድንጋይ ናዳ ግራና ቀኛችንን ይበራል ። ፈንጂና ቦምብ ምድሪቱን ያናውጣል ፣ የጠላት መትረየስ ያለማቋረጥ ይንተከተካል ፣ ይንፈቀፈቃል ። ጠላት ነቅቶ ወደ ቀይ እምቡጦች አቅጣጫ ዞሮ ነበር ። ግን ፣ ቀይ እምቡጦች የእጅ ቦምብ እንደጨበጡ ከጠላት ምሽጎች እየዘለሉ መግባት ጀምረዋል ። የፈንጂ ጢስና የባሩድ ሽታ ያፍናል ፣ ያስለቅሳል ። ካንድ በኩል ያለማቋረጥ እየተንፈቀፈቀ አላራምድ ያለ የጠላት መትረየስ ነበር ። የተኩስ እሩምታ ይረጭበታል ፣ የቦምብ ጋጋታ ይወርድበታል ። ግን መትረየሱ ላንቃውን አይዘጋም ፣ መረማመጃ በር ዘግቶ ዝም ብሎ ይንጣጣል ። አንድ ቀይ እምቡጥ እንደ ነብር እያደባና በደረቱ መሬት ይዞ የሞት ላንቃውን ወደማይዘጋው የጠላት መትረየስ ሲሳብ ድንገት አየሁትና ትንፋሼን ውጬ ዝም አልኩ ። ከንቲባም እንዲሁ አይቶት ኖሮ ፣ ቀጥሎ የሚሆነውን ነገር በውል ለማየት ጓጉቶ ሳይሆን አይቀርም ፣ አንገቱን ቀና አደረገ ።

«አብደሀል እንዴ! መሬት ያዝ!» አልኩት ።

ዞር ሲል በእፉ ደም ሲወጣ አየሁ ።

«ከንቲባ!» ብዬ ጮህኩ ።

አልሰማኝም ። የጠላት መትረየስ ወደሚንጣጣበት አቅጣጫ ቴፑን እንደያዘ በረረ ። በዚያኑ ጊዜ ወደ መትረየሱ ይሳብ

የነበረው ቀይ እምቡጥ በደረቱ እንደተኛ አንድ ቦምብ ከወረወረ በኋላ ፣ እንደ ነብር ዘሎ መትረየሱ ተጠምዶበት ወደ ነበረው ምሽግ ገባ ። ከንቲባ መሐል መንገድ ሲደርስ ወደቀ ። ከተኛሁ በት ተነስቼ ወደ ከንቲባ ሮጥኩ ።

«ከንቲባ! ከንቲባ!»

አይሰማኝም ። ጸጥ ብሎ ቀርቷል ። ወዙ እንዳለ ነበር ። የምጸት ሳቅ የሚስቅብኝ መስሎ ታየኝ ። አንገቱ ላይ ተጠምጥሞ የሚ ሳምኩት ። እና እንደአበደ ሰው ተነስቼ መትረየሱ የሞት ላንቃውን ይከፍትበት ወደነበረው ምሽግ ሮጥኩ ። የመትረየሱ ላንቃ በመዘጋቱ ቀይ እምቡጦች ሆ!ብለው ወደ መጨረሻ ግባቸው መረማመድ ጀምረዋል ። እንደ ሮጥኩ ሔጄ ከምሽጉ ገባሁ ። መትረየሱና ተኳሹ በቦምብ ጋይተዋል ። ቀይ እምቡጡ የሌላውን ጠላት ጉሮሮ እንዳነቀ ውድቋል ። ከመትረየሱ ኋላ ጋይቶ የወደ ቀው ጠላት እግረ ቀራጣ ነበር ። የቀይ እምቡጡን ከላሺን አነሳ ሁና የጠላት ሬሣዎችን ወደላይ እየተን ጠራራሁና እየጮሁኩ በሳ ንጃ ወጋሁ...... ወጋሁ...... እስከሚበቃኝ ድረስ ። እና ቁጭ ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ ።

እንደ ሞተ ሰው ሆኘ ነበር በሙታን መካከል የምዘዋወ ረው ። ግንባሩ በጥይት ተነድሎ የወደቀ ፣ ሰውነቱ እንደ ወንፊት በጥይት ተበሳስቶ የተዘረረ ፣ ጭንቅላቱ ተቆርጦ ከላዩ ላይ የበ ረረ ፣ እጅና እግሩን አጥቶ የተንጋለለ ፣ የተሰበረ ፣ የጋየ ምሽግ። ደሙን እያዘራ «ስለ ወንድ ልጅ ፣ ውሀ አባካችሁ......» እያለ ጠብታ ውሀ የሚለምን ፣ በሞትና በመኖር ስቃይ መሐል ተይዞ ፣ «አባካ ችሁን ስለወንድ ልጅ አትለዩኝ ፣ ጨርሱኝ ፣ ለነፍስ እሆናችኋ ለሁ ....» እያለ የሚማጠን ድምጽ ፣ እዚህም እዚያም ሰውነታ ቸው በታላቅ ፍርሀት የሚርበደበድ እንገታቸውን የደፉ ምርኮ ኞች ። በገሀነብ አዳራሽ ውስጥ እንደመዘዋወር ነበር ። የጠላት ወገን የሞተው ሞቶ ፣ የቆሰለው ቆስሎ ፣ የተማረከው ተማርኮ ፣ የተቀረው ትጥቁን እንዳለ ጥሎ ፈርጥጧል ። ካሚራችን ወዲህና ወዲያ ይሮጥ ነበር ። ከፍተኛ ነጥብ 1702 በቀይ እንቡጥ ቁጥጥር ሥር ቢውልም አልፎ አልፎ ተኩስ ይሰማል ፣ ስለታሪክ ምንም ደንታ አልነበረኝም ። የሰው ልጅ ስቃይ ታሪክ ምን ታሪክ ይሆ

ናል? ታሪክነቱ ምኑ ላይ ነው? ጭንቅላቱ ዝም ብሎ ይሞኝ ነበር ። ጥላቻ ብቻ ነበር ልቤን የሞላው ። እና ቀይ እምቡጦች ለምርኮኞች ደረቅ ራሽንና ውሀ ሲሰጡ ፣ የቆሰለውን ሲያክሙና አይዞህ እያሉ ሲያጽናኑ ተመልክቼ ፣ በንዴትና በጥላቻ ፣ «እነዚህን የታሪክ ዲቃላዎች ለምን አትኳቸውም!» በማለት ጮህኩባቸው።

ትዕዛዜን የሚቀበል ወይም የሚሰማኝ ሰው አልነበረም፣ ያበድኩ መስያቸው ሳይሆን አይቀርም ሁሉም በመገረም ዝም ብለው ይመለከቱኝ ነበር ።

«ምን ታዩኛላችሁ! ጅሎች! እውነቴን ነው ። እነዚህ የታሪክ ዲቃላዎች ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ያለምንም ርኅራኄ በጭካኔ ሲጨፈጭፉን የነበሩ አውሬዎች ናቸው ። እኛ ለእነሱ ሰዎች አይደለንም ፣ የማናስብ አድጊዎች ወይም ጥሬ ሥጋ የሚጎምዱ «ሌሌዎች» ነን! ለእነሱ እኛ አሁንም ቅኝ ገዢዎችና ወራሪዎች ነን ። በእነሱ ግምት እኛ እንኳን ሌላውን ራሳችንንም ለማስተዳደር የማንችል አሀዮች ነን! እድል ካገኙ አይምሩንም ። ጨካኝ አውሬዎች ናቸው.....» እያልኩ ስጮኽ አንድ ሰው ትከሻዬን ይዞ ወደኋላ ጉተተኝ ። ኰሎኔል ታሪኩ ነበር ።

«አይዞህ» አለኝ ።
«ምን አይዞህ ትለኛለህ? በላቸው!»

«ኧረ ጸጋዬ ፣ አይዞህ ። ይህ ጦርነት ነው ። ስህተቱ የነዚህ ምስኪን ሰዎች አይደለም ። ያለመታደል ሆኖ ነው እንጂ ፣ በሌላ ጊዜና ሁኔታ ከነዚህ ሰዎች ጋር እንደወንድማማች አብረን እንሰቅና እንጫወት ነበር» በማለት ሊያጽናናኝ ሲሞክር ከምርኮኞቹ መካከል አንዱ የተሰጠውን ደረቅ ራሽን አንድ ቀይ እምቡጥ ፊት ላይ በድፍረት ወርውሮ ሊያንቀው ተነሳ ።

ኰሎኔል ታሪኩ እኔን ለቀቀኝና ሔዶ ፣ ምንድነው? አለው ።
«አንተ ነጻ አታወጣኝም!»
«ታዲያ ማነው ነጻ የሚያወጣህ!»
«ፔትሮ ዶላር መጥቶ ነጻ እስከሚያወጣው ይጠብቅ! በለው! አልኩኝ ።
«ሻዕቢያ ለዘላለም ትኑር!» አለ ።

ሌላው ምርኮኛ በታላቅ ቁጣ «ሻዕቢያ ትውደም!» ብሎ ቀጠለና ፣ «ይህ ሰው እኛን አይወክለንም» ከጥቂት ጊዜ በፊት ከኋላ በጥይት እየደበደበን ሲያዋጋን የነበረ አረመኔ ነው ። ኑሮ እችን ከኋላችን እሳት ከፊታችን እሳት ነበር ። አሁን ነጻ ወጥተ ናል ፣ ወንድሞቼ ነጻ ወጥተናል» አለና እንባውን ዱብ ዱብ አደረገ ።

ኰሎኔል ታሪኩ ወደ ደንፊው ምርኮኛ መለስ ብሎ ፣ «ይህን ሰው ፈትሸው» በማለት የመቶ አለቃ ጋሻ ጠናን አዘዘው ።

ጋሻ ጠና እንደታዘዘው ምርኮኛውን ሊፈትሽ ጠጋ ሲ ለው ፣ መሣሪያውን ለመቀማት ይታገለው ጀመር ። ኰሎኔል ታሪኩ ራመድ ብሎ በግራ እጅ አንቆ ያዘውና ፣ አትሞትም! ይህች ምድር ከወንበዴዎች ነጻ መውጣቷን ሳታይ አትሞትም! ውሰዱት ይህን ወስላታ!» አለ ።

ወንበዴው አልተበገረም። ኰሎኔል ታሪኩን ፊቱ ላይ ተፋበ በት ። ታሪኩ አልተናደደም ። ለጥቂት ሴኮንዶች ዝም ብሎ ተመ ለከተው ። በግራ እጁ ወደ እሱ ሳብ አደረገውና ግንባሩ ላይ ሳመው ። እና ሽጉጡን መዞ እዚያው ግንባሩ ላይ ባንድ ጥይት ነድሎ ጣለው ። ሌሎቹን ምርኮኞች ብርክ ያዛቸው ። መቆም ስላ ቃታቸው ። ወደቁ......

«ከፊቴ ውሰዷቸው !» አለ ኰሎኔል ታሪኩ ። ተመትቶ የወ ደቀው ወንበዴ የጓድ መሪ ነበር ። ኪሱ ሲፈተሽ አንድ ቁራጭ ወረቀት ተገኘች ። አጭር መመሪያ ተጽፎበታል ። መመሪያው ፣ «አሥመራ ባስቸኳይ ሔደህ ለሥዕላይ በራኺ ሪፖርት አድርግ ። ፓራዲዞ ቡና ቤት ታገኘዋለህ ። እና አሮማይ የሚለውን ኮድ አስታውስ» ይላል ። ኮዱ በመመሪያው ላይ አልተገለጸም ። ብዙ ገንዘብ በኪሱ ይዞ ነበር ። «አሮማይ» የሚለው ቃል ጭንቅላቴን መታኝ ። ኰሎኔል በትሩ ተሰማ ስለ አሮማይ የጠየቀኝ ጥያቄ ትዝ አለኝ ። የሰውዬው መገደል ቢጸጽተኝም ምንም ማድረግ አልተቻለም ። ሞቱን የፈለገበት ምክንያት አሁን ገባኝ ። እና ሬሣውን ረገምኩ ። ቢሆንም የሥዕላይ በራኺን ማንነት በማወቂ ደስ አለኝ ። ሥዕላይ በራኺ! እጉያችን ውስጥ! ገረመኝ ። የኰሎ ኔል በትሩ ጥርጣሬም አስደነቀኝ ። አሮጌ ቀበሮ!

ብዙ ቀይ እምቡጦች ብናጣም ድሉ የኛ ሆኗል ። ከንቲባ አንዱ ቀይ እምቡጥ ነበር ። የከንቲባን ሞት መቀበል ወይም ማመን አልቻልኩም ። በቅርብ የሚያውቁትና የሚወዱት ሰው ሲሞት ማመን ያስቸግራል ። ትዝታው አይሞትም ። በዚያኑ እለት ዘጠኝ መቶ የጠላት ሬሣ ተቆጠረ ። በበምብ ከጋዩት ሌላ አያሌ መሣሪያዎች በወገን ጦር እጅ ገቡ ። የቀይ እምቡጥ ዘመቻ ዓርማ ከከፍታ ነጥብ 1702 ላይ ሲተከል የነበረው ስሜት እጅግ አድርጎ ልብ የሚነካ ነበር ። ለወደቁት የቀይ እምቡጥ ጀግኖች እሩምታ ተተኮሰ ፣ የሕሊና ጸሎትም ተደረገላቸው ። ሁሉም የሞቱት የጀግና ሞት ነበር ። አብዛኛዎቹ የሞቱት የእጅ ቦምብ እንደጨበጡ ጠላት ምሽግ ውስጥ ዘሎ በመግባት ነበር ። ብቻውን የወደቀ አንድም የቀይ እምቡጥ ጀግና አላየሁም ። የጠላት አንገት አንቀው የወደቁ ብቻ ነበሩ ። ጓዶቻቸው ወደፊት እንዲራመዱ መስዋእት የሆኑ ነበሩ ። ኰሎኔል ታሪኩ ለቀይ እምቡጥ ዘመቻ ዓርማ ወታደራዊ ሠላምታ በሚሰጥበት ጊዜ ፣ እንባው ጉንጮቹን አቋርጦ ሜካ ከመሰለው ጢሙ ውስጥ ገብቶ ሲጠፋ ይታይ ነበር ። ጀምበሯ አቀልቁላለች ። ሮራ ጸሊም ጠቁርአል ። ሰማዩ በሺህ ቀለማት አሽብርቆ ቀልቷል ። አድሆባ ሸለቆ ላይ ጸሐይ ስትጠልቅ ማየት ሌላው የተፈጥሮ ትንግርትና ተአምር ነበር ። ይገርማል ፣ የሰው ልጅ የመኖር ናፍቆት እንዲያድርበት ተፈጥሮ ዘላለም እንደጋበዘችው ትኖራለች ። የተረፍነው ጥሬዋን ተቀብለን በደም የያዝነውን የውጊያ ወረዳ ማጠናከር ጀምረን ነበር ። ሥራው ብዙ ጥረት አልጠየቀም ። ተጠናክሮ የቆየውን የጠላት ምሽግ በይበልጥ የማጠናከር ሥራ ነበር ። ቲክሲ ወደሚገኘው የወገን ማዘዣ ነጥብ ተመልሼ እዚያ እንዳድር ኰሎኔል ታሪኩ ጠይቆኝ ነበር ። ግን እሳቡን አልተቀበልኩትም — «ለምንድነው እንዳንዳችሁ የማትቀጥረኝ!» በማለት ።

«ይሁን ። እንዳችን ነህ» በማለት ተወኝ ።

«እንኳን ደስ ያለህ» አልኩት ።

«አስደናቂ ድል ነው ። ግን ድሉ የቀይ እምቡጦች ብቻ አይደለም ። ከጥሩ ቅንብርና እቅድ የተገኘ የጋራ ድል ነው» አለኝ ።

ልክ ነበር ። አሁን ሳስበው እቅዱና ቅንብሩ በጣም የሚያስ ደንቅና የሚያስመሰግን ነበር ። ቀጠለና ፣ «ግን ፣ አሁን አንድ ችግር ይታየኛል» አለኝ ።

«ምን ?»

«ጠላት ድንገት ሆኖበት ነው እንጂ ይህን ነጥብ በቀላሉ አይለቅም ነበር ። አሁንም ተስፋ ቆርጦ አይቀርም ። ይህ ነጥብ ከተያዘ ሌሎችም ነጥቦች አንድ ባንድ ይወድቃሉ ። የናቅፋ በር ተከፈተ ማለት ነው ። እንደምታየው ናቅፋ ከዚህ ነጥብ በስተጀርባ ናት ። ስለዚህ ጠላት ያለ የሌለ ኃይሉን አሰባስቦ መልሶ የማጥቃት ርምጃ የሚወስድ መሆኑ የማይቀር ነገር ነው ። ፈጥነን በመንቃነቅ ድሉን ካላሰፋን ኋላ ችግር ይገጥመናል» አለኝ ።

«ታዲያ ችግሩ ምንድነው?»

«ፍጥነትና የሰው ኃይል ። እኛ የሽምቅ ተዋጊዎች ፍጥነት የለንም ። በዚህ ላይ ደግሞ አንዳንድ ኃይሎቻችን ልምድ ያንሳቸዋል ። አሁን ወሳኙ ነገር ፍጥነት ነው» አለኝ ።

ለናቅፋ መንደርደሪያና መሸጋገሪያ ድልድይ የሆነው ከፍታ ነጥብ 1702 በመያዙ ፣ የ17ኛ ክፍለ ጦር ዋስትና የሆነው የግራ ክንፍ 11ኛ ብርጌድ በሁለተኛው ቀን ወደ ከፍታ ነጥቦችን 1521 1527 1590 በአንድ ምዕራፍ እጥቅቶ ለመያዝ ተንቃነቀ ። በ1807 ሰዓት እነዚህ ነጥቦች በሙሉ በወገን ጦር እጅ የወደቁ መሆናቸውን በታላቅ ደስታ ሰማን ። ከእንግዲህ የናቅፋ መውደቅ የጊዜ ጉዳይ ነበር ። ጋቢጣዎቻችንን እያጋጨን የፈላ ሚሊ ድራፍት ስንጠጣ አመሸን ። ካሁኑ ስለናቅፋ ማለም ጀምሬ ነበር ። ናቅፋ ካለንበት ከሰባት ኪሎ ሜትር በላይ አትርቅም ። አጠቃላዩ የድል ምሥራች ደወል ሲደውል ይሰማኝ ነበር ። አንዱ ቀን ሔደ ፣ ሌላው ቀን መጣ ። ካንድ ድንጋይ ጥላ ሥር ቁጭ ብዬ ማስታወሻዬን እየተመለከትኩ ሳስተካክል ከከፍታ ነጥብ 1702 በስተቀኝ ድንገት ከባድ ተኩስ ተከፈተ ። ድብልቅልቁ የወጣ የከባድ መሣሪያዎች ተኩስ ነበር ። ምን ይሆን ? እያልኩ ሳስብ ኩሉኔል ታሪኩ ረዳቱን ልኮ አስጠራኝ ። ናቅፋ ለመግባት የሚደረገው የማጥቃት ርምጃ የተጀመረ መስሎኝ ደስ ብሎኝ ነበር ። ግን የታሪኩን ፊት ላይ አድርብኝ የነበረው የደስታ ስሜት እንደ በጋ ጉም ከውስጤ በንኖ ጠፋ ።

«ምንድነው?» አልኩት ።

«ከፍታ ነጥብ 1702ን ለቀን መውጣት አለብን» ብሎኝ የእጅ ሰዓቱን ተመለከተና ፣ «ልክ በ18 መቶ ሰዓት» አለኝ ።

«ትቀልዳለህ!»

«ትዕዛዝ ነው» አለኝ ።

«ግን ፣ ለምን? ምን መጣ?»

ሁኔታውን ረጋ ብሎ አስረዳኝ ። ጠላት ያለ የሌለ ኃይሉን አሰባስቦ በመስበቅና ፣ ቢ— 10 ጸረ ታንክ ፣ 120 እና 82 ሚ.ሚ. ሞርታሮች ወደፊት በማቅረብ ፣ እንዲሁም መድፍና ታንክ በርቀት በመጠቀም 19ኛ ብርጌድ ይዞት የነበረውን ከፍታ ነጥብ 1755ን ሰብሮ በመግባት አስለቅቋል ። ከፍታ ነጥብ 1755 ጠላት እጅ ተመልሶ ከወደቀ ፣ ከፍታ ነጥብ 1702 በግራ ክንፍ በኩል ከፉኛ ስለሚጋለጥ ለመከላከል እጅግ ያስቸግራል ። እንዲያውም ለመከላከል አይቻልም ። የመከላከሉን ኃይል ለማጠናከር እን ዳይቻል ደግሞ አንጋባች ኃይሎች ስለዘገዩ በወቅቱ አይደርሱም ። ሌላ አዲስ ተዋጊ ኃይል ለማሰለፍ የጊዜው ሁኔታ አልፈቀደም ። በመካሔድ ላይ ያለው ውጊያ የወገንና የጠላት ጦር በጠባብ ወረዳ ላይ የተሰባጠረበት ሁኔታ ስለሆነ በተዋጊ አይሮፕላኖችም ሆነ በከባድ መሣሪያዎች ለመጠቀም አላመቸም ። በዚህ ላይ ውጊያ የሚደረግባቸው ወረዳዎች ሁሉ በጣም ጠባብ ስለሆኑ አሁን ተጨማሪ የሰው ኃይል ቢገኝም እንደልብ ማሰለፍ ያስ ቸግራል ። ሌላው ችግር ጠላት ያደረገው የተጠናከረ ዝግጅት ነበር ። ጠላት የወገንን ጦር ንቅናቄና አሰላለፍ በሚገባ ያው ቃል ። በቂ መረጃ አለው ። የመረጃ ምንጫቸው ከልተዘጋ የወገን ጦር በጦር ሜዳ የሚያደርገው ፍልሚያ ሊሰምር አይችልም ። ስለዚህ ስጊዜው ያለው አማራጭ የተያዙትን ወታደራዊ መሬቶች ለቆ ወደኋላ ማፈግፈግ ወይም በጠላት ተቆርጦና ተከቦ እየተዋጉ ማለቅ ወይም እጅ መስጠት ብቻ ነው ።

«እውነትክን ነው?» አልኩት ።

«ይኸው ነው» አለኝና በራዲዮ መገናኛ በኮድ መልክ የደ ረሰውን አጭር ትእዛዝ እንደገና ካነበበ በኋላ የመቶ አለቃ ጋሻ ጠናን ጠርቶ ፣ ቀይ እምቡጦች ልክ በ18 መቶ ሰዓት ነጥባቸውን ለቀው ለመውጣት እንዲዘጋጁ አዘዘው ።

ይህን ስትራተጂካዊ ነጥብ ለማስለቀቅ ውድ ሕይወታቸውን እሳልፈው የለውት ቀይ እምቡጦች ታዩኝ ። በታላቅ ንዴትና ቁጣ ፣ «ይህን ሁሉ ቀደም ብለን ለምን አላሰብንበትም ነበር! ናቅፋ ለመድረስ የቀረን ለባት ኪሎ ሜትር ብቻ ነው ። አሁን እነዚህን ነጥቦች መልቀቅ ምን ማለት ነው? ወይስ ወታደራዊ ቀልድ ነው!» አልኩት ።

«የለም ጸግሽ ፣ የጦርነት ጨዋታ ነው ። ማጥቃት እንዳለ ሁሉ ማፈግፈግም ይኖራል ። የበላይ አለቆቼ የዚህን ገዥ መሬት ወሳኝነት ያውቃሉ ። ለቀን እንድንወጣ የፈለጉት ለሕይወታችን ሰግተው ነው ። ግን እኛ የመጣነው በፊትም በሕይወታችን ቆርጠን ነው ። ለቅን መውጣት የለብንም» ብሎ መልእክቱን እኪሱ ከተተ ። ደስ የሚል ፈገግታ ፊቱ ላይ ይታይ ነበር ። ባሳቡ የቆረጠ መሆኑ ያስታውቃል ። ቀጠለና «እኔ አልሄድም ። ይህ ተራራ የኔ ተራራ ነው ። በእጇ የተከልኩትን ዓርማና ቀይ ሰንደቅ በእጇ ከመንቀሌ ሞቴን እመርጣለሁ!» አለኝ ።

ላጭር ጊዜ ከባድ አሳብ ዋጠኝ ። ግን የማስበውን ነገር አላወቅሁም ። ከባድ ዝምታ ብለው ይሻላል ። የጋሻው ጠና ተመልሶ መምጣት ነበር ከዝምታዬ የቀሰቀሰኝ ። በጓዶቻቸው ደም የያዙትን ነጥብ ለቆ ለመሔድ የሚፈልግ አንድም ቀይ እምቡጥ እንደሌለ ለኰሎኔል ታሪኩ ነገረው ።

«እርግጠኛ ነህ?» አለው
«እርግጠኛ ነኝ ጓድ ኰሎኔል.....»
«እኔም ከእነሱ እንደማልለይ ንገራቸው ። እዚሁ እንሞታለን.....»
«የበላይ ትእዛዙስ ጓድ?»

«ስለእሱ አትጨነቅ፣ ይህን ገዥ ወታደራዊ መሬት መልቀቅ የለብንም ። እስከ መጨረሻ ሰው ድረስ እንዋጋለን ። የማስረዳቱ ኃላፊነት የኔ ነው » ብሎ አስናበተውና ወደኔ መለስ በማለት ፣ «አንተና ጓዶችህ አሁን መሔድ አለባችሁ» አለኝ ።

«ማን አለህ! » አልኩት ።
ሳቀና ፣ «ወታደራዊ ትዕዛዝ ነው» አለኝ ።

«አንደኛ እኔ ወታደር አይደለሁም ። ሁለተኛ ምነው አንተ አልተቀበልከውን» አልኩት ።

ከተቀመጠበት ተነስቶ ፊቴ ሲንጐራደድ ቆየና ፣ «ለግኝ ጸጋዬ ፣ ከበላይ የተሰጠው ትእዛዝ ልክ ነው ። ለሕይወታችን ታስቦ ነው ። ግን ይህ ገዥ መሬት ነው ። በምንም ሁኔታ መል ቀቅ የለብንም ። ከዚህ ቀደም እንዳልኩህ በጦር ሜዳ ምክን ያትና ሎጂክ ሁልጊዜ አይሠራም ። መኖር የሰው ምኞት ነው ። ግን እኛ አሁን ከሎጂክ ውጭ ሆነናል ። እና አሁን የኛን አስተ ተሳሰብ የሚለውጥ ምንም ኃይል የለም ። እዚሁ ለመሞት ፈልገ ናል ። እና እዚሁ እንሞታለን» አለኝ ።

«እኔም» አልኩት ።

«እንድትሔድ የምፈልግበት ሁለት ምክንያቶች አሉኝ......»

«ምንና ምን?»

«አንድ እዚሁ ብትቀር ማን ታሪካችንን ያቀርብልናል?»

«ታሪክ ገደል አባቱ ይግባ!»

«ሁለት ፣ የምታደርስልኝ የግል መልእክት አለኝ......»

«ምን ?»

የታሸገ ኢንቬሎፕ ከደረት ኪሱ አውጥቶ ሰጠኝና ፣

«መልእክቱ ምንና ለማን እንደሆነ አልነግርህም ። በሕይ ወት ከተገናኘን መልሰህ ትሰጠኛለህ ። ካልሆነም ኢንቮሎፑን ከፍተህ ምን እንደሆነ ካየህ በኋላ ለሚመለከተው መልእክቱን ታደርስልኛለህ ። ይህችን ውለታ አድርግልኝ» ብሎ እጄን ጨ ብጦ ያዘና «መልእክቱ ቁም ነገር ኖሮት አይደለም ። እንደ እው ነቱ ከሆነ ጅልነት ነው ። ግን ዋናው ነገር ያንተና የጓዶችህ መሞት ጥቅም የለውም ። የምትጽፏቸውና የምትናገሯቸው ነገሮች ፣ የምታትሟቸው ፎቶግራፎችና የምታሳዩዋቸው ፊል ሞች ላሁኑ ብቻ ሳይሆን ለመጪውም ትውልድ ይጠቅማሉ ፣ ትምህርት ይሆናሉ» በማለት እንድንሔድ ሲያግባባኝ ከቆየ በኋላ ፣ በመጨረሻ ፣ «እምቢ ብትልም በግድ እሰድሀለሁ ። እውነቴን ነው ። ምንም ቢሆን ኃላፊነት ይሰማኛል» አለኝ ። ቀልዱን አልነበረም ። የምሩን እንደሆነ ፊቱ ይናገር ነበር ።

«ለምን?» አልኩት ።

«ለታሪክ» አለኝ ።

በግድም ሆነ በውድ መሔድ ነበረብኝ ። የገሊ መልእክቱን እንዳደርስለት የጣለብኝ ኃላፊነትና አደራ በጣም ከብዶኝ ነበር ። 18 መቶ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ቀይ እምቡጦችን ከተሰነባበትን በኋላ ወደ ቲከሲ ለመሔድ ተነሳን ። እንባዬን ቋጥሬ ለመያዝ አልቻልኩም ። ኰሎኔል ቃሪኩ በመጨረሻ ስሞ ከተሰናበተኝ በኋላ ፣ የሚዳ መነጽሩን ካንገቱ ላይ አውልቆ ሰጠኝ ።

«ምን ያደርግልኛል?» አልኩት ።

«ከእንግዲህ ምን ይጠቅመኛል?» ጠላት ወደኔ ነው እንጂ የሚመጣው እኔ ወደ እሱ አልሄድም ። ባይሆን ከሩቅ እንድታየኝ ይረዳሀል ፣ ሩቅ አይበት ። ቻው» ብሎ እንደለመደው በጣቶቹ የድል ምልክት አሳየኝ ።

ትዝ ብሎኝ ከተገደለው ወንበዴ ላይ የተወሰደውን መመሪያ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት ።

«ምን ትሠራበታለህ?» አለኝ ።
«ያስፈልገኝ ይሆናል» አልኩት ።

ወረቀቷን ፣ ከያዘው ኮሮጆ ውስጥ አውጥቶ ሌሎችም ወረ ቀቶች ጨምሮ ሰጠኝ ። ሌሎቹ ወረቀቶች ላዛኝ መኩንኑ የሚ ሰጡ ነበሩ ። እኔም እንደእሱ በጣቶቼ የድል ምልክት አሳየሁትና ፣

«በድል እንገናኛለን» አልኩት ።
«በእርግጥ ድል ከኛ ጋር ነው» አለኝ ።

አገላብጨ ሳምኩትና አጃቢዎቻችንን ተከትለን ቁልቁለቱን ተያያዝነው ። ሆዴ አላስችለኝ ስላለ ወደኋላ መለስ ብዬ አየሁት ። ቀጭን ሽንጡን ይዞ ቁሞ ሳየው ናቅፋ ተራሮች ላይ በግርማ ሞገስ የሚያንገዋብብ ንስር መስሎ ነበር ።

አጃቢዎቻችን ለሌሎች የወገን ጦሮች ካስረከቡን በኋላ ከመንገድ ተመለሱ ። በፍጥነት ነበር የምንጓዘው ። በየመንገዱና በየሥርጡ ከፍተኛ ወታደራዊ እንቅስቃሴ ይታያል ። በወሳንሳ የሚ ሔዱ ቁስለኞችም ነበሩ ። አንድ ቁስለኛ ከተኛበት ተነስቶ ተኩስ ወደበረከተበት አቅጣጫ ታላቅ ድምጽ እያሰማ ሲሮጥ አየሁ ።

ልቀቁን በማለት ከጓደኞቻቸው ጋር የሚተናነቁ ሌሎችም ቁስለ ኞች ነበሩ ። ዓይኔ ግን ያረፈው አንድ ወጣት ቁስለኛ ላይ ነበር ። ከፉኛ ቆስሏል ። የምርታር ፍንጣሪ እግሩን ቆርጦታል ። ደጋግሞ፣ ሲቃየን እያያችሁ ምነው ዝም ትሉኛላችሁ? በምብና መሣሪያዬን አስጨብጣችሁኝ እዚያው ብትተውኝ ወይም ብትጨርሱኝ ምን ነበረበት! እባካችሁን ጨርሱኝ!» እያለ ይማጸናል ። እንዲሁ ሲማጸን ትንሽ መንገድ እንደሔድን ፣ አንዱ አሳርፉኝ ብሎ ጓደኞቹን ለመነ ። ካንድ ቁጥቋጦ ጥላ ሥር ትንሽ እንዲያርፍ እድል ሰጡት ። አንዱን ወታደር ጠራውና የሆነ ነገር ነገረው ። ወታደሩ የሰማውን ስምቶ ዞር ከማለቱ ቁስለኛው ወጣት ከተዘና ጋው ወታደር ሽጉጡን ከመቅጽበት ላጥ አድርጎ በዚያው ቅጽ በታዊ ፍጥነት ራሱን ጨረሰ ። ትራጀዲ ሲበዛ ያደነዝዛል መሰ ለኝ ደርቄ ቀረሁ ። ስሜት ከውስጤ ተጨምቆ አልቆ ባዶ የሆንኩ ያህል ሆኖ ነበር የሚሰማኝ ። ከበስተቀኛችን ጦርነቱ እንደተፋፋ መና እንደተቀጣጠለ ነበር ። ምንም እክል ሳይገጥመን ምሽት ላይ ቲከሲ ፣ ማዘዣ ነጥብ ደረስን ። ለእዛዥ መኰንኑ ኰሎኔል ታሪኩ የላካቸውን ወረቀቶችንና ካርታዎችን አስረከብኩ። በብ ረት ከዘራው መሬት እየወጋ በንዴት ይቃጠል ነበር ። የኰሎኔል ታሪኩና የቀይ እምቡጦች መልእክት ቀደም ሲል ደርሶታል ። እንዳንዴ እንደ እበደ ሰው ዝም ብሎ በጥቁር ብረት ከዘራው ካርታ እሸዋ ላይ ይስላል ። አይናገርም ። ቀይቶ ፣ ቀይቶ ፣ እሳት ይተነፍሳል ። ረዳቶቹ ከበውት ቆመዋል ። መሣሪያ አልታጠ ቀም ። ረዳቶቹ ሆነ ብለው መሣሪያውን ያስፈቱት ይመስላል ። አሥር ዓይነት ጥያቄ ቢያቀርብልኝም ኰሎኔል ታሪኩ በላከው መልእክት ላይ የማክለው አሳብ አልነበረኝም ።

«ለምን! ለምን!» ብሎ የብረት ከዘራውን አሸዋ ላይ ተከ ላት ። ከከፍታ ነጥብ 1702 የሚመጣውን ዜና ወይም መልእክት ለመስማት ከራዲዮ መገናኛ ዙሪያ ተሰብስበን አመሸን ። መጨ ረሻ የደረሰን መልእክት ፣ «ተከበናል — ቆሎ አልቆብናል — ቢ ሆንም ድሉ የኛ ይሆናል — ውጭ !» የሚል ነበር ። የታሪኩ ድምጽ ነበር ። ከድምጹ በስተጀርባ ከባድ ተኩስ ይሰማ ነበር ። የራዲዮ መገናኛ መሣሪያውን ከበን ቆየን ። ስንት ሰዓት እንደ ቆየን አላውቅም ። ጊዜ ትርጉም አልነበረውም ።

«ቀይ እምቡጥ ና! ቀይ እምቡጥ ! ናደው ነኝ ። ትሰማኛ ለህ? ቀይ እምቡጥ!..... ቀይ እምቡጥ !..........»

ከከፍታ ነጥብ 1702 የሚመጣ አንዳችም መልስ አልነበረም ። የሙታን — የመቃብር — የጀግኖች — የቀይ እምቡጦች ዝምታ! መልስ አልነበረም ። ከፍታ ነጥብ 1702 መልስ አይሰጥም ። ጸጥ ብሎ ቀርቷል ። እንዳልኩት የሚወጣኝ እንባ አልነበረኝም ። ደርቄአለሁ ። ውስጤ ደረቅ አሸዋ — ደረቅ የማሕል አሸዋ ሆኗል ። ውስጤ እንደ ደረቁ የማሕል አሸዋ ይፋጃል ። ግን የስሜት ጠብታ አልነበረውም ። ያን ሌሊት እንቅልፍ በዓይኔ አልዞረም ። እንደ ማሕል በረሀ ደርቄ አደርኩ ።

ተስፋ ማድረግ ሰው መሆን አይደል ። ተስፋ አልቆረጥኩም። ተስፋ ሁሉ ጠፍቶ ፣ ተስፋ ማድረግ አይቀርምና ፣ ከከፍታ ነጥብ 1702 መልእክት መጥቶ እንደሆነ በማለት ወደ ራዲዮ መገናኛው ሔድኩ ። የመጣ መልእክት አልነበረም ። ብልግና ከተሞላበት ከወንበዴዎች ስድብ ሌላ ምንም እንደሌለ ራዲዮ ኦፕሬተሩ ነገረኝ ። ከማዘዣው ነጥብ ላይ ወጥቼ ፣ ታሪኩ በሰጠኝ የሚዳ መነጽር ወደ ከፍታ ነጥብ 1702 ተመለከትኩ ። ታሪኩ የለም ። ግን ተራራው የታሪኩ መንፈስ መስሎ ታየኝ ። የወገን ጦር ለጊዜው ቲከሲንም ለቆ ወደ ሌላ ማዘዣ ነጥብ መንቃንቅ ጀምሮአል ። ወደኋላ የማፈግፈጉ ንቅናቄ ድርጅታዊ ቅንጅት የተሞላበትና ሥርዓት የሰፈነበት ነበር ። የጦርነቱ ፍጻሜ አልነበረም ። እንዲያውም አዲስ ጦርነት ይቀጥላል ። አሁን ወይም ነገ ናቅፋ ትወድቃለች ። ታሪኩ እዚያ አይገኝም ። ግን ታሪኩን የመሰሉ ጀግኖች ይኖራሉ ፣ ናቅፋ ይደርሳሉ ። ሁሉም ታሪኩ ናቸው ፣ እሱም እነሱን ነው ። አንድ ናቸው ። አደራ ያለኝን ኤንቬሎፕ ከፍቼ መልእክቱን ተመለከትኩት ። ከመደንገጤ የተነሳ ለትንሽ ጊዜ ልቤ ቀጥ አለ ። ትንፋሽም አጠረኝ ። ዓይኔንም ለማመን አቃተኝ ። ኤንቬሎፑ ውስጥ ከፊያሜታ ጊላይ ፎቶግራፍ ሌላ መልእክት አልነበረም ። ከጀርባዋ ላይ «አልተገናኘንም ፣ ደህና ሁኚ» የሚሉ ቃላት በቀይ ቀለም ተጽፈው ይነበባሉ ። «ደህች ውቧ! የውቧ ልጅ!» ከማለት ሌላ የምለው ነገር አልነበረኝም ። ሰማይ ፣ የልቤን መራራ ጩኸት ሳይሰማው አልቀረም ።

# ደብዳቤ

## ምዕራፍ አምስት

ወጊያ የሚደረግባቸውን ወረዳዎች ወደኋላ እየተውኩ
ርቄ በሔድኩ መጠን የተኩስ ድምጽም ከጀርባ እየራቀ ይሔድ
ነበር ። ይህን ያበደ የተኩስ ሙዚቃ ጀርባ ስለለመደው አንድ
ነገር የጠፋብኝ ይመስል ቅር ፣ ቅር ይለኛል ። ገሀነብን ማጣት
ቅር የሚያሰኝበት ምክንያት ባይገባኝም ቅሉ ። ገሀነብ ነበር ።
የሚቀር ነገር ቢኖር ምናልባት ጥላቻ ብቻ ሳይሆን አይቀርም ።
ባይሆን ለኔ እንደዚያ ነበረ የተሰማኝ ። ሰው ሰውን ለመግደል
እንደ አውሬ ጥርሱን አግጦ ሲሮጥ ታያለህ ። ያስጠላሀል ።
የሰው ስቃይ ታያለህ ። ያስጠላሀል ። የምትወዳቸውን ጓደኞች
ህን ድንገት ካጠገብህ ታጣቸዋለህ ። ያስጠላሀል ። ድል ታገ
ኛለህ ፣ ግን ያንን ድል ያገኘኸው የሰው ሕይወት በማጣት
ስለሆነ ያስጠላሀል ። እና በደህና ከጦር ሜዳ መመለስም ምና
ልባት ሳያስጠላ አይቀርም ። ሞትን አይተሀል ። ከሞት ጋር ፊት
ለፊት ስትፋጠጥ እንዴት ነበርክ — ጀግና ወይስ ፈሪ? ስለራስህ
ማንነት አዲስ ያገኘኸው እውቀት ያስጠላሀል ። እና ታብዳለህ ።
ምክንያቱም እንዲህ ነኝ በማለት ስለራስህ የነበረህ አሳብ
ይለወጥና ማን እንደነበርክና ምን እንደሆንክ ይሳከርብህና እው
ነታ ይጋጭብሀል ። አብደህና አካለ ስንኩል ሆነህ ትቀራለህ ።
በእውነት ጦር ሜዳ የቀሩት ይሻሉ ይሆን? ሁሉንም አግኝተው ፣
ሁሉንም ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አጥተዋልና። የጦርነትን አስቀ
ያሚ ገጽታ ዳግመኛ አያዩትምና ነው ። ከጭንቀትና ከስቃይ ባሻ
ገር ሆነዋል ። በሕይወት ያለነውስ? ደስታና ሠላም የሰፈነበት ፣
ከጦርነት ጭንቀትና ስቃይ ነጻ ፲ሆነ ሕይወት የምንኖርበትን
ጊዜ በመናፈቅ ተስፋ ማድረጋችንንና መሰቃየታችንን መቀጠል
አለብን ። መኖር ድፍረትን ይጠይቃል ...... ግን ለመፈላሰፍ
ፋታ አላገኘሁም ። ያሳክከኝ ነበር ። የለበስኩትን ልብስና ያደረ

ግሁትን ማግ ሳላወልቅ አሥር ቀን ሆኖኛል ። ደም እስከሚወጣኝ ድረስ ነበር የማከው ። እና ደግሞ የሆድ ድርቀት ይዞኝ ነበር ። ሰውነቴ ሁሉ እንደበሰበሰ ፋንዶ ነበር የሚሸተው ። እከክ ፣ ድርቀት ፣ ግማት ፣ ይህም ያስጠላል ።

አፍአበት ስደርስ ጉልበቴ ከዳኝ ። ሰውነቴ ተንቀሻቁሾ ያለቀ መሆኑ የተሰማኝ እዚያ ስደርስ ነበር ። በየትኛው አቅም እንቀሳቀስ እንደነበረ አሁን ሳስበው ገረመኝ ። ምናልባት የመኖር ፍላጎት ብቻ ሳይሆን አይቀርም ሲገፋፋኝ የነበረው ። ያለ እድል ሆኖ ለእረፍት ጊዜ አልነበረኝም ። ባንድ ሰዓት ውስጥ ወደ አሥመራ መብረር ነበረብኝ ። ጋዜጠኛ ለእረፍት ያልታደለ ፍጡር ይሆን? ጊዜ የሚሰጠው ሰው የለም ። ሌሎች በሚወስኑለት ጊዜ ነው የሚኖረው ። ዜናም ቢሆን የእሱን ምቾት ጠብቆ አይደለም የሚደርሰው ። የጋዜጠኛ ሕይወት በማያቋርጥ በረራ ይመስላል ። ቢሆንም ደስ አለኝ ። ያገኘሁትን መረጃ ለኰሎኔል በትሩ ለማድረስ በጣም ቸኩዬ ነበር ።

ወደ አሥመራ የምትበረው አይሮፕላን ሰለሞን በትረን ፣ የሺጥላ ማስረኛን (ሱስ ሎብ) እና መጽሐፈ ዳንኤልን ብቻ ነበር የምትጠብቀው ። ወንበዴዎች አፍርሰውት የሔዱት የአፍአበት ሆስፒታል ጥገና ሥራ አልቆ ስለነበረ እሱን ለማየት ነበር ያንጪት ከአሥመራ የመጡት ። ሆስፒታሉ ትንሽ ስለሆን ቁስለኞች ድንኳን ውስጥ ነበር የሚተኙት ። የጦር ሜዳውን ምስል መልሶ አመጣብኝ ። በመቶ የሚቆጠሩ ቁስለኞች በጣር ተይዘው ያቃስታሉ ። ገና የሚመጡ አዲስ ቁስለኞችም ነበሩ ። ያፈጠጠ ቁስል ደም — የሞት ሽታ ፣ በየክፍሉ ፣ በየድንኳኑ ። ሐኪሙና አስታማሚዎቹ አሳዘኑኝ ፣ እረፍትና እንቅልፍ ካጡ ብዙ ቀን የሆናቸው ይመስላሉ ። ሐኪሙ አሁን ገና ከኦፕራሲዮን ክፍል መውጣቱ ነበር ። ኦፕራሲዮን የተደረገው ሰው ሞቶአል ። ክፉኛ የቆሰለ ሌላ ሰው በቃሬዛ አልጋ እየተሳበ ወደ ኦፕራሲዮን ክፍል ይወሰድ ነበር ። ሐኪሙ ዝም ብሎ ወደ ስሚን ይመለከታል ። በሕልም ዓለም ውስጥ ያለ መሰለኝ ። ወጣት ሐኪም ነበር ። የሚያስበውን የማውቅም መሰለኝ ። እንደ ሕይወት ያለ ውድ ነገር ማጣት ያሳዝናል ። ጦርነት ያስጠላል ..........

አፍአበት አየር ማረፊያ ስደርስ እንዳጋጣሚ እነ ሰለሞን በትረም መጡ ። ሰለሞን አሁንም እንደቸኮለ ነበር ። የድካም

ምልክት አይታይበትም ። መጥቶ ሲስመኝ ሲል ፥ «በፈጠረህ ተወኝ» ብዬው እጄን ዘረጋሁለት ።

«ምነው?» አለኝ ።
«ፋንዶ ፥ ፋንዶ ነው የምሸተው...»
«እዎን ፥ ከሩቅ ይሰማኛል ። እባካችሁን ከዚህ ገሀነብ ቶሎ እንውጣ» አለ መጽሐፈ ዳንኤል ።

«ሁለት ሰዓት እዚህ መቆየት እንዴት አስቻለህ?!» አልኩት።
«የግድ ሆኖብኝ ። ቶሎ እንሂድ!» አለ ።

መጽሐፈ ቀልዱን አልነበረም ። ከአፍአበት ቶሎ ለመውጣት ቸኩሏል ። እንደ አፍአበት ያለ አቧራማ ቦታ ቀርቶ የጸዳ ቤትም አይመችውም ። ለምግብ ስንቀርብ ተነስቶ ማህኑን ካላጠበ አይበላም ። አቧራ ካየ ይጮሀል ። ቢት የለበሰውን ከሰዓት በኋላ ካልለወጠ አይወጣም ። ቀጠለና «አፍአበት የሠለጠነ ሰው የሚኖርበት ቦታ አይደለም ። እንሂድ» አለ ።

ሰለሞን ተጠጋኝና «መልእክት ትቼልህ ልሔድ ነበር ። እንኳን አገኘሁህ» አለኝ ።

«የምን መልእክት?»
«ኢሮኞህ እሥመራ መጥታለች...»
«መቼ?»
«ምስት ቀን ሆኗታል ። ቶሎ ሔደህ ገላህን ታጠብ» አለኝ ።
«መቼ ነው ወጥ ሠርተህ የምታበላኝ?» አልኩት ።
እንጀራና ወጥ በጣም አምሮኝ ነበር ።
«ጊዜ ጠፋ» አለኝ ።
«ሱስሎቭ» ወታደራዊ ካድሬዎችን ያነጋግር ነበር ። መጥቶ ሠላምታ ከሰጠኝ በኋላ ፥ «ጦርነቱ እንዴት ነበር?» አለኝ ። ስለ ታም ቀንጆ ፊቱ የባሰውን ተስኗል ። ቀጠለና ፥ «የጦሩ ሞራል ግሰቱ ነው» አለኝ ።

«ጥሩ ነው» አልኩት ።
«ተአምረኛ ሠራዊት እያበበ ነው ። ለዓለም ጭቁኖች ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ታላቅ ቀይ ሠራዊት ይሆ

ናል ። ናቅፋ ምንም አይደለችም ። ትግላችን ከናቅፋ ባሻገር ነው ። ሺ ናቅፋዎች ወደፊት ይጠብቁናል ። እና የምናካሂደው ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ መቀየስ ያለበት ከዚያ አኳያ ነው» በማለት ነገረኝ ።

«ጓድ ፣ እኔ አንድ ናቅፋ ካሁኑ በቅቶኛል» አልኩት ።

ያየሁትን አይቻለሁ ። ይበቃል ። ዳግመኛ የጦርነትን አስ ቃቂና አስቀያሚ ገጽታ ላለማየት ቆርጫለሁ ።

«ሱስሎቭ» ያሳብ ልዩነት የሚያናድደው ዓይነት ሰው አይ ደለም ። የሰው አሳብ አክብሮ ይቀበላል ። የራሱንም አቋም በጥሞና እያስረዳ ለማሳመን ይሞክራል ። «ማኅበራዊ ፍትሕን የሚዋጉ ኃይሎች እስካሉ ድረስ ከመታገል ሌላ ምን ምርጫ ይኖረናል? አሳብህ ጥሩ ነው ። የዓለም ተራማጅ ኃይሎች ጦርነት አይፈልጉም ። ግን ጦርነትን ለማስወገድ የምንችለው ተስፋ በመ ቁረጥ አይደለም» አለኝ ።

በመሠረቱ ልክ ነበር ። ካሳቡ ጋር ጥል አልነበረኝም ። ግን ሕይወት ካሁኑ ብዙ ስላቆሰለችኝ ነው መሰለኝ ፣ የሰው ልጅ በመሠረቱ ቅን ነው የሚለው አስተሳሰብ እያጠራጠረኝ መሄድ ጀምሮአል ። ሰው በመሠረቱ ቅን ነው የሚለውን አስተሳሰብ የሚያረጋግጥልኝ ምንም ነገር እስካሁን አላገኘሁም ።

አይሮፕላናችን ከአፍአበት ተነስታ ወደ አሥመራ መብረር ጀምራለች ። ውይይታችን ወደ ጦርነቱ አምርቷል ። መጽሐፈ ዳንኤል ነበር ፣ «ይህን ሁሉ ጦር አሰልፈን ፣ ይህን ሁሉ ዝግጅት አድርገን ፣ ናቅፋን መያዝ እንዴት ያቅተናል? ምንድነው'ኮ ችግራችን? ወይስ ከኛ የተሰወረ ነገር ይኖራል? ማነው'ኮ ይህን እንቆቅልሽ የሚያስረዳኝ?» በማለት ውይይቱን የከፈተው ። በጥ ያቄዎች ሰው መተንኮስ ይወዳል ።

ሰለሞን በትረ ፣ «የዓይን ምስክር ይናገር» በማለት የመጽ ሐፈን ጥያቄዎች ወደኔ መራቸው ።

የሚያናድዱ ጥያቄዎች ነበሩ ። ስለሆነም መልስ ከመስጠት ይልቅ የስድብ ውርጅብኝ ነበር እንደመጣልኝ የማወርደው ፣

ቁጭ ብሎ መተቸት ቀላል ነው ። ግንም ተቀጣጭ ሊተች ይች ላል ። ናቅፋን አሁን መያዝ እንዴት ያቅተናል? ብሎ መጠየቅ አንድ ነገር ነው ። ናቅፋን ሔዶ መያዝ ሌላ ነገር ነው ። የናቅፋን ተራሮች ሔዶ ያየ ማነው? ሔደው የሞከሩት ሞተዋል ወይም ቆስለዋል ። በተደረገው የመጀመሪያ የማጥቃት ርምጃ ናቅፋ ሳይያዝ የቀረው የወገን ጦር ጀግንነት አንሶት ወይም ሰንፎ አይ ደለም ። በሺህ የሚቆጠሩ አብዮታዊ አርበኞች ወንበዴን ሳይ ሆን የማይበገር የተፈጥሮን ምሽግ ሲዕጥሙ ወድቀዋል ፣ ደምተ ዋል ። ናቅፋ ለምን አሁን አልተያዘችም? በግለት የሚቀረቀር ሰው ካለ ፣ ሔዶ ቦታውን ረግጦ መሞከር አለበት ። ያኔ ነው የአብዮታዊው ሠራዊት ወኔና ጀግንነት ፣ ተጋድሎና መስዋእት ነት ፣ ጥንካሬና ሞራል በውል ሊገባው የሚችለው ። የምን እን ቆቅልሽ! የምን ምስጢር! የናቅፋ ውጊያ የተሰወረ ምስጢር የለውም ። ተፈጥሮ በሰው ወኔ ላይ ስታምጽ ምን ይደረጋል! ሰማይ አይጧጠጥ ወይም ይህ ጀግና ሠራዊት ራሱን ለአልቂት እንዲዳርግ አይደረግ! እኮ ምን? አሁን ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ነው ። የጠላትን መውጫና መግቢያ ነጥቦች አንድ በአንድ በቀስታ ፣ ግን በእርግጥ እየዘጉና ቀስ ብለው እየከበቡ ፣ የከበባ ውን ቀለበት እያጠበቡ ፣ እያጠበቡ ሔደው በመጨረሻ ፍልፈሎ ቹን መደበቂያ ጎሬአቸው ውስጥ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አጋ ይቶ ማስቀረት ። ሌላ አማራጭ የለም ። ጊዜና ትእግሥትን ይጠ ይቃል ። ግን የናቅፋ መውደቅ እርግጥ ነው ። ጊዜው ሩቅ አይ ደለም ። እስከዚያ ድረስ ኢኮኖሚያችን ይደማ ይሆናል ። አሁንም እየደማ ነው ። ቃዲያ ምን ይሁን ! ያገር ሕልውና ከሌለ ኢኮኖሚ ምንድነው! ለማነው? ጦርነትን አልወድም ፣ ያስጠላኛል ። ከሆነ ልኝ ዳግመኛ ሳየው አልፈልግም ። ግን ፣ ጦርነትን በሰው ልጆች ላይ የሚጋብዙ ጥፋተኞች እስካሉ ድረስ መቀጣት ይኖርባቸዋል ። ይቀጣሉም ። አመጽ በአመጽ ብቻ ነው የሚፈታው ። ከናቅፋ ተራሮች ላይ የጀግኖች ደም ይጮሃል!..... አሁን እሰማዋለሁ...... እሰማዋለሁ...... አይሮፕላኗ አሥመራ ደርሳ ባታርፍ ኖሮ ንግግሬን እቀጥል ነበር ።

ጢት ረፋዱ ላይ ነበር አሥመራ የደረስነው ። አየሩ ይወ ብቃል ።

ከአይሮፕላኗ ስንወርድ ፣ «ግን አንድ ነገር ልንገርህ» አለኝ ። «ሱብሎብ» ።

«ምንድነው?» አልኩት ።

«በሰው ልጅ ላይ ተስፋ አትቁረጥ ። ያለው የመጨረሻ ተስፋ ምናልባት እሱ ብቻ ነው» አለኝ ።

«በሰው ልጅ ላይ ያለኝን እምነት የሚያጠናክርልኝ ነገር ባገኝ ደስ ይለኝ ነበር ። እስካሁን ያየሁት ግን እምነቴን የሚንድ እንጂ የሚያጠና ክርሆና አላገኘሁትም» ብዬው ሔድኩ ።

ገና ቤት ከመድረሴ ለኰሎኔል በትሩ ስልክ ደወልኩ ። ስልኩን ያነሳው ጸሐፊው ነበር ።

«ጓድ ኰሎኔልን ነበር የምፈልገው ። ጸጋዬ ኃይለ ማርያም እባላለሁ ። ለአስቸኳይ ጉዳይ ነው......»

«ምጽዋ ሔደዋል..........»

ወይ አጋጣሚ! ለብርቱ ጉዳይ በፈለኩት ቁጥር ከከተማ የመጥፋቱ ነገር አስገረመኝ ።

«መቼ?»

«ዛሬ..........»

«መቼ ይመለሳል?

«ዛሬ ማምሻውን.....»

«እዚያ የሚገኝበትን ስልክ ልትሰጠኝ ትችላለህ......»

«አልታዘዝኩም..........»

«እሺ አንተ ደውለህ ልትነግረው ትችላለህ? የሞትና ሽረት ጉዳይ ነው..........»

«ምን ብዬ?»

«ጸጋዬ ኃይለማርያም በጣም ላስቸኳይ ጉዳይ ይፈልግሀል ብለህ ።»

«እሺ እሞክራለሁ ።»

የሞቀ ውሀ ውስጥ ገብቼ ከመነከር ሌላ የሚታየኝ ነገር አልነበረም ። ውሀን የፈጠረ አምላክ! እያልኩ በደስታ ዋኘሁ ። የጦርነትን ኃጢአት ከላዬ ላይ እጥቤ እንደማወጣ ያህል ነበር ሰውነቴን የማሸውና የምፈትገው ። ፈያሚታ ጊላይንም እንደ ቆሻሻ ነገር ከላዬ ላይ እጥቤ አወጣኋት ። ስላታለለችኝ በልቤ ውስጥ ያደረው ጥላቻ ነፍስ ዘርቶ ሲገላበጥ ይሰማኛል ። በዚህ

ዓለም ማንን ማመን ይቻላል? እና ሰው በመሠረቱ ቀና ነው የምን ለውስ እንዴት ነው? እያልኩ አስብ ነበር ። የሱስሎቭ ምክር አልዋጥ እለኝ ። ዛሬ ለመጨረሻ ጊዜ አያታለሁ..... ፎቶግራፏን እሰጣታለሁ..... እና ደህና ሁኝ እላታለሁ ። ከዚያ በኋላ ይህችን ውሻ ዳግመኛ ባይኔ አላያትም ..... ብዬ ወሰንኩ ። በሮሚ መምጣ ትም ዕድሌን አመሰገንኩ ። ሁልጊዜም ቢሆን እድለኛ ነበርኩ ። አሁን ሳስበው ሕይወትን ይህን ያህል የማማርርበት ምክንያት የለኝም ፡ ሕይወት ይህን ያህል አላንገላታችኝም ። ሮሚ ልክ በጊዜው በመምጣቷ ደስ አለኝ ። ሕይወት አስባ ስትክስ ደስ ይ ላል ። ሮሚ የት እንዳለች የነገረኝ የለም ። እና ተነስቼ ለረዛን ደወልኩላት ።

«መቼ መጡ!» አለች ረዛን ።

«ካንድ ሰዓት በፊት ። ሥራው እንዴት ነው?»

«ኩሎኔል በትሩ ተሰማ ብዙ ጊዜ እልመጣም ወይ እያሉ ይጠይቁኛል.........»

«ሌላስ?»

«ወይዘሪት ሮማን የሚባሉ ብዙ ጊዜ ይደውላሉ.....»

«አድራሻዋን ነግራሻለች?»

«አዎ ፡ ከረን ሆቴል ። ቁጥር 19፡ስልክ ቁጥሩን ይፈልጋሉ?»

«ግድ የለም ።»

ወደ ፊያሚታ ጊላይ ደወልኩ ። ስሜን ስትሰማ ተደናገ ጠች ። አሳቧም ፡ ድምጿም ተሰባበረብኝ ።

«ምነው ጠፋሁሽ?» አልኳት ።

«እደውልልሀለሁ ስል ደወልክልኝ» አለች በሚሰባበር ድምጽ ።

«መምጣቴን እንዴት ዐወቅሽ?»

ዝም አለች ።

«ምን ሆነሻል?»

«ምንም»

«ዛሬ ማታ የት ላግኝሽ?»

ቶሎ መልስ አልሰጠችኝም ። ቆየችና «ናቅፋ እንዴት ነው?» አለችኝ ።

«ምነው? ደህና ነው» አልኳት ።
«አልሆነላችሁም ይባላል......»
«የጊዜ ጉዳይ ነው ። አንድ ቀን ይሆናል ።»
ካንገት በላይ ሳቅ ሳቀችና ፣ «ይመስልሀል?» አለችኝ ።

«እርግጠኛ ነኝ ። ለምን እንደምትጠሉን አይገባኝም? ቢሆንም ፍቅር በመጨረሻ ማሸነፉ አይቀርም ። ምን ጊዜም ቢሆን በጥላቻ የሚመራና በአታላይነት የሚኖር ሰው ወይም ኃይል በመጨረሻ ይወድቃል ። የናቅፋ ተራራዎች እንደደበቁት አይቀሩም» አልኳትና ወደ ጥያቄዬ ተመልሼ «ላገኝሽ እፈልጋለሁ ። ጉዳይ አለኝ ። በስንት ሰዓት ላግኝሽ?» ብዬ ጠየኳት ።

«እጮኛህን የት ጥለህ?» አለችኝ ።
«መምጣቷን ሰምተሻል?»

«አዎ ፣ አሥመራ ትንሽ ከተማ ናት ። የምትደብቀው ነገር የላትም» ብላ ፣ አሁንም ካንገት በላይ የሆነ ሳቅ ሳቀችና ፣ «አይቻታለሁ ። ቆንጆ ናት አባቴ ይሙት ። ግን ሁለተኛ አታየኝም ። ለምን ታየኛለህ?» አለችኝ ።

እልክ ይሁን ወይም ንዴት ጉሮሮዬን እየተናነቀው ፣ «አንቺን ለማየት የምፈልግበት ጉዳይ አለኝ» አልኳት ።

ፎቶግራፉን ሰጥቻት ፣ ደህና ሁኚ ብዬ ከእሷ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከመለየት ሌላ የምፈልገው ነገር አልነበረኝም ። እንደተጫወተችብኝ እንድትቀር አልፈለኩም ። ባሳቤ ሰው ለመጉዳት አይሆንልኝም ። ከመጣብኝ ግን ሰይጣን ነኝ ። አንዳንድ በቅርብ የሚያውቁኝ ሰዎች በዚህ የተነሳ ለዘብተኛ ሠይጣን ይሉኛል ። በዚህ ዓለም ላይ ሁሉ እኩል አታላይና ራሱን ወዳድ እንዳልሆነ ማወቅ አለበት ፣ በሰው ንጹሕ ስሜት እየተጫወተች የምትኖር ፣ ይህችን ውሻ ትምህርት ማስተማር አለብኝ ብዬ ነበር የተነሳሁት ። በስልክ ልነግራት እችል ነበር ። ግን ፣ የጎዳችኝን ያህል ልጎዳት ፈለኩ ። ይሁን እንጂ ፣ ከጥፋቷ የሚማር ልብ ይኖራት ይሆን? አጠራጠረኝ ። ልቢ ናቅፋ ተራራ ባይሆን ኖሮ መቼ እንዲህ ጉድ ትሠራኝ ነበር? ኰሎኔል ታሪኩን አስታወስኩት ። መላ ሰውነቴን ዘገነነኝ ። ምን ሊያስተምረኝ ፈልጎ ይሆን ፎቶግራፏን የሰጠኝ ? ብዬ አሰብኩ ። እሱ ሞቷል ፣ አርፍዋል ። እኔ እሰቃያለሁ ።

«በኋላ እደውላለሁ» አለችኝ ።
«መቼ?»
«ከአምስት ደቂቃ በኋላ..........»
«ጊዜ የለኝም ። ለምን አሁን አትነግሪኝም?»
«እመኛሁን ለማየት ከቻልክ ሂድ! ከረን ሆቴል ናት» አለች ።
«እሺ ይሁን፤ አምስት ደቂቃ» አልኳት ።

ምን ለማድረግ እንደፈለገች ባይገባኝም ቅሉ አምስት ደቂቃ ጠበኳት ። እውነትም ከአምስት ደቂቃ በኋላ መልሳ ደወለችልኝ ።

«አንድ ሰዓት ላይ ኒያላ አካባቢ ጠብቀኝ» አለችኝ ።

ወደ ከረን ሆቴል ከመሔዴ በፊት በቪያ ፓራዲዞ አድርጌ በፓራዲዞ ቡና ቤት በኩል አለፍኩ ። ቡና ቤቷ እዚያው ነበረች ፣ የትም አልሔደችም። ኰሎኔል በትሩን በማጣቴ ልቤ ተንጠለጠለ። ወደ ከረን ሆቴል በቀጥታ ሔድኩ ። ሻለቃ ተክላይ ዘድንግል ቡና ቤቱ ውስጥ ያንዣብብ ነበር ። ከላይ እስከ ታች ባለመስመር ጥቁር ልብስ ለብሶ ሽክ ብሎአል ።

«ግብዣ አለብህ እንዴ?» አልኩት አለባበሱን እያደነቅሁ ።
ባናውቀው ነው እንጂ ሕይወት ሁልጊዜ እንደጋበዘችን ነው» አለኝ ።
«እዚህ ምን የሚታደን ነገር አገኘህ?»
«ማ! ኮሚ ቤላ!» ብሎ ጣቶቹን ሳመና ፣ ከአዲስ አበባ በቅርብ ቀን የመጣች ጽጌረዳ የምትመስል ፣ ቆንጆ ልጅ ቁጥር 19 መኝታ ክፍል የምትገኝ መሆኗን ነገረኝ ።
«እውነት?» አልኩት ።
«መኝታ ቤቷ ውስጥ ተቆልፋ ምን እንደምትሠራ አላውቅም ግን በእውነት ኃጢአተኛ ናት» አለኝ ።

«ለምን?»

«ያንን የመሰለ ውበት መደበቅ ኃጢአት ነው» ብሎ ፣ ክራቫቱን አስተካከለና ፣ «አሊቃዬ በጣም ይፈልግህ ነበር» ሲል ነገረኝ ።

«ከኔ ምን ይፈልጋል?»
«አላውቅም ። ግን ይፈልግሀል ..........»
«ሥራ እንዴት ነው?» ብዬ ጠየኩት ።

የገቢ ሊለኝ ፈልጎ ነበር ። ሮሚን ለማየት ቸኩዬ ነበርና ግብዣውን እምቢ አልኩት ። ወደ አንድ ጥግ ጐተተኝና ድም ጹን ዝቅ አድርጎ ፣ «ብትጠነቀቅ ጥሩ ነው» አለኝ ።

«ምነው?»
«ለማድያ እንደምትፈለግ ደርሰንበታል..........»
«ለምን? ማነው እኔን ለመግደል የሚፈልገው?»

ቀስ ብሎ ማፍ ማፉን ነገረኝ ። አሮማይ የሚባል የወንበ ዴዎች ኅቡዕ ድርጅት ተቋቁሟል ። የአሮማይ ዓላማ ፣ የወንበዴ ዎችን የመጨረሻ ምሽግ ለመደምሰስ የሚደረገውን ንቅናቄ መግ ታት ፣ የወገን ጦር ባለበት ቦታ ሁሉ ድንገተኛ ወረራ በመክፈት ማበሳጨት ፣ የጦሩን የስንቅና የትጥቅ መንገዶችን መዝጋትና እንዳመቹ አደጋ መጣል ፣ መገናኛዎችን መቁረጥና መጥለፍ ፣ እንደዚሁም አጥፍቶ የሚጠፋ ጓድ በማሰማራት በሰውና በንብረ ቶች ላይ ጉዳት ማድረስ ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የከፍለ ሀገ ሩን ሕዝብ ከፍተኛ ወኸኩንብር ላይ መጣል እንደሆነ ከነገረኝ በኋላ ፣ «እንዳልኩት አንተ አንዱ ኢላማቸው ስለሆንክ መጠን ቀቅ አለብህ ። ይህን ሁሉ ለማወቅ ችለናል ። አሁን ያቃተን ነገር ቢኖር «ሴላቸውን» ማግኘት ነው ። በተጠጋን ቁጥር ፍንጩን ያጠፉብናል ። ሰዎች ድንገት ሞተው ይገኛሉ ፣ ወይም ደርሰንባ ቸው ስንል ራሳቸውን ያጠፋሉ ። በውስጥ የዘረጉትን መረብ ካልበጣጠስነው ፣ በጦር ሜዳ የምናካሂደው ፍልሚያ ሊሰምር አይችልም ። የሴላቸው መረጃ የለም» አለኝ ።

«ሴላቸውን ማግኘት አሁን ቀላል ሳይሆን አይቀርም» አል ኩት ።
«እንዴት?
«በተአምር» አልኩት ። ልነግረው አልፈለኩም ።
«ሴላቸው» ያለበትን ቦታ የሚጠቁመን ሰው ብናገኝ ሚሊ ዮን ብር እንከፍለዋለን ። አሮማይ ብቻ አይምሰልህ ። ቢሮክራሲ

የሚባል አካል እንዳላቸውም እናውቃለን ። ችግሩ ፣ ማን? የት የሚለው ጥያቄ ነው» አለኝ ።

«ሥዕላይ አለ ወይ? » ብዬ ጠየኩት ።

«አለ ። አሁን መከተል ጥላ እንደማባረር ነው» አለኝ ።

«ፓራዲዞ ቡና ቤት ደህና ነው?»

«ለምን ጠየከኝ?»

«ጥሩ ቡና አምሮኝ ነው»

«ወስጄ ልጋብዝህ..........»

«አመሰግናለሁ ። ሁሉም ነገር ሠላም ነዋ? » አልኩት ።

«አትስጋ ። ከተማዋ በቁጥጥራችን ሥር ናት ። ወደ ግባችን እየተቃረብን ነው ። መቼ? የት? አላውቅም ። ብቻ አንድ ነገር ከቅርብ ይሸተኛል» አለኝ ።

«ኮሎኔል በትሩ ከምጽዋ እንደተመለሰ ሚሊዮን ብር አዘጋጅተህ ጠብቀኝ በለው ። እመጣለሁ ። አሁን 19 ቁጥር የምትጠብቀኝ ልጅ አለች ። ቸኩያለሁ» አልኩት ።

በሁለቱም ጉዳዮች አሳመነኝም። የምቀልድ ነበር የመሰለው። እዚያው ትቼው ወደ ፎቅ ወጣሁ ። ሮማን ድምጼን ባትሰማ ኖሮ በሩን አትከፍትም ነበር ። በናፍቆት ከተላሳምን በኋላ ፣ «እክፍልሽ ውስጥ ተዘግተሽ ምን ታደርጊያለሽ?» አልኳት

«ሆ! ምን ዓይነት አገር ነው ልጄ!» አለች ።

«ምንው?»

«ወንዱ በመንገድ እያስኬድም ። በዓይናቸው ቀሚሴን ሲያወልቁ ይታየኛል » ብላ ፣ በናፍቆት ዓይን ስትመለከተኝ ከቆየች በኋላ ፣ «ከስተሃል ፣ ጠቁረሃል» አለችኝ ።

«ልክ ነሽ ፣ እረፍት ላይ አልነበርኩም» አልኳት ።

«ሺ ስማንያ ኪሎ ሜትር አጥርሬ ያዝኩህ አይደለም?» አለችና ቀጥላ ፣ «መቸ ነው ይህ ዘዴቻ የሚያልቀው?» ብላ ጠየቀችኝ ።

«እንጃ ፣ በእውነት አላውቅም ።...»

«ማጣ ነው እቴ ። በኔ ላይ የመጣ ፍርጃ ሳይሆን አይቀርም» አለች ።

ከሆቴሉ ወጥታ እኔ ካለሁበት ቤት ውስጥ እንድታርፍ አግ ባባኋትና ለመሔድ ተነሳን ። የሆቴሉን ሂሣብ ለመክፈል ስን ሔድ ተክላይ ዘድንግልን አየሁት ። ሮሚን ወስጄ ፣ «ተክላይ ይባላል ። ጓደኛዬ ነው ። ሮማን እኅቴ ናት» በማለት አስተ ዋወቅኋቸው ።

ሮሚ ሲታየው ደስ አላላትም ። እሷ ዞር ስትል የሌባ ጣቱን ቀስሮ የቀልድ ዛቻ ዛተብኝ ። መኪና ውስጥ ከገባን በኋላ ፣ «ምን ጓደኛዬ ነው ትላለህ? አላስገባ ፣ አላስወጣ እያለ እንዲሁ መከራዬን ሲያበላኝ ነው የከረመው» አለች ።

«ተይው ። ደህና ልጅ ነው ። ቢመኝስ ምናለበት፣ ውብ ነሽ ። እሱም ሸጋ ነው ። ለከፋት ብሎ አይደለም ። ሕይወትንና ሴቶችን ይወዳል ። ምናለበት?» በማለት አጽናናኋት ።

«ገነት ውስጥ አይደለም እንዴ ያረፋችሁት?» በማለት ግቢውንና ቤቱን አደነቀች ። ግቢው በልዩ ልዩ አበባዎችና ሐረጎች ፣ ጥዶችና ዘምባባዎች የጌጠና የተዋበ ነበር ። ክፍሎቹም በጣም ያማሩና ምቾት ያላቸው ነበሩ ። ዘመቻ እንዲህ ከሆነ መቆየቱ ምን ይከፋል?» አለችና ሻንጣዋን ሳትፈታ መኝታ ቤቱን ማስተካከል ጀመረች ። የተዝረከረከ ነገር ማየት አትወድም ። ልብሶቼም ፣ ጫማዎቼም ፣ እግር ሹራቦቼም በየቦታው ተጥለው ይታያሉ ።

አንድ የቴፕ ክር አንስታ ስትመለከት አየኋት ። ቴፕ ክሩን መሬት እንደጣልኩት እዚያው እረስቼው ነበር ። ምንም ለማድረግ አልቻልኩም ። አሁን ነገሩ ዘማይቷል ። ከጁዋ አልቀ ማው ነገር! ራሴን ረገምኩት ። ፈያሜታ ጊላይ የሰጠችኝ ክር ነበር ። ስሟ ተጽፎበታል ። የሮማን ፊት በቁጣ ሲቀላ አየሁት ። ምን ለማለት ወይም ምን ለማድረግ እችላለሁ? ዝም ብዬ ቆሜ ቀረሁ ። ሬዲዮ ቴፑን አስነስታ ዘፈኑን ማዳመጥ ጀመረች…… ግጥሙን በቃሌ እወጣዋለሁ ። የኩኩ ዘፈን ነበር ። ምናልባት መቶ ጊዜ ሰምቼው ይሆናል ።

«ከሰው የተለየሀ ፣ እኔ ምን አውቃለሁ?
እኔ ምን አውቃለሁ

ሳይህ ደስ ይለኛል ስላንተ አስባለሁ
ስላንተ አስባለሁ
አመመኝ ደከመኝ አጣሁ መድኃኒት
ፍቅርህ አስጨነቀኝ እንደ ልብ ውጋት
መውደዴ ከሆነ እኔ አንተን ማየቱ
ልቤ ከተሰማው የፍቅርህ ግለቱ
ገረመኝ እራሴን ሳየው ሁኔታዬን
አንተም እንደኔው ነህ ፣ ወይ እኔ ብቻዬን?
ወዳንተ እያደላ እምቢ አለኝ ተው ብለው
ነጋ ጠባ አንተን ነው የሚያሰላስለው
ልቤ ተቀልፎ ያስባል ለብቻው
ለምወደው ልጅ ግን ያውና መክፈቻው......

ከሩ ላይ ሌላ ዘፈን አልነበረም ። «ጥሩ የፍቅር ዘፈን ነው» አለች ።

ጠጉሬን አክኬ ዝም አልኩ ። ሮማን ተናዳ ጉንጮቿ ሲቀሉ የፈካ ጽጌረዳ አበባ ትመስላለች ።

«ፊያሜታ ጊላይ ማን ናት?» አለች ።

ምን መልስ እንደምሰጣት አጥቼ አሁንም ዝም ብዬ ቀረሁ ። ሸንጣዋን ይዛ ብድግ አለች ።

«የት ልትሔጂ ነው?» ብዬ ሸንጣውን ያዝኩባት ።

«የኔ ወንድም ተወኝ ልሒድበት............»

«የሆነውን ሁሉ አስረዳሻለሁ ። ዕድል ስጪኝ ፣ እባክሽ» በማለት ልመና ገባሁ ።

«ምንም የምታስረዳኝ ነገር የለም ። ተወኝ!» አለች ።

«እባክሽ ሮሚ ስሚኝ............»

«ይህንኑ ነበር የፈራሁት............»

«ምን?»

«አንተ የደረስክበት ቦታ ሁሉ ቤትህ ነው ። በደረስክበት ትለምዳለህ ። መጥኔ እቴ ። ግን አንተ ምን ታደርግ? እኔ ነኝ ቅሌታሟ ። በራሴ ነው የማዝነው ። ባንተ አይደለም......»

«ያለፈው አልፎአል ። አልሰማ አልሺኝ እንጂ አሁን እነግርሽ ነበር ። ልጅቷ ወስላታ ነች ። አዝናለሁ ። እባክሽን ሮሚ ፣

ይቅርታ አድርጊልኝ ። ልለምንሽ ። አትሒጅ» በማለት ለመ ንኳት ሁሉንም ነገር እዚያው ልናዘዝላት ፈልጌ ነበር ።

ልመናዬን አልሰማችም ። «ተወኝ ነው የምልህ! አለዚያ ውርደት ይከተላል! » ብላ የባሰውኑ አፈጠጠችብኝ ።

ግራ ገብቶኝ ራሴን ይገር ቆምኩ ። የማደርገው ነገር ጠፋኝ ። ንዴት ጉሮሮዬን አነቀኝ ። ከዚህ በላይ መለማመጥ ደግሞ አልሆ ነልኝም ፣ አይሆንልኝም ። ሴቶች አለ በቂ ምክንያት ሲነጣ ነጩብኝና አልሰማ ሲሉኝ ቶሎ ግልፍ ይለኛል ። ከዚያ በኋላ መለማመጥ ፈጽሞ አይሆንልኝም ። ሴቶች በመሠረቱ የሚለማመ ጣቸውን ወንድ ይወዳሉ መሰለኝ ፣ ዝም ብዬ ስተዋቸው ብዙ ሴቶች ፣ እሱ እረመኔ ነው ፣ ጨካኝ ነው የሚል ስም አውጥተው ልኛል ። እንኳን በድለው ይቅርና ሴት በድላም ብትሆን መካስ ትወዳለች ። እኔ ግን እንዲህ አይደለሁም ። ከሴት ጋር እልከ መጋባትም አልወድም ። የማታዳምጠኝ ከሆነ ጥያት መሔድ ብቻ ነው የማውቀው ። አዎ ፣ ሮማንን በድያት ይሆናል ፣ ግን ለምን አታዳምጠኝም! ለምን አይገባትም!

«ከፈለግሽ ልትሒጂ ትችያለሽ!» ብዬ መንገዱን ለቀቅሁላት።

ሻንጣዋን አንጠልጥላ ወጣች ። ግድግዳውን በቡጢ. አልኩ ትና ተከትያት ወጣሁ ።

«እሺ ፣ መሔዱንስ ሒጂ ። የት ነው የምትሔጂው? ላድር ስሽ» አልኳት ።

«አልፈልግም ራሴ እሄዳለሁ.........»

«እባክሽ ሮሚ ፣ አሁን ባታስቸግሪኝ ምናለበት?»

«እኔ የማስቸግር ሴት አይደለሁም ። ታክሲ ሞልቷል ። አትቸገር» ብላ መንገዷን ቀጠለች ።

በሠላም ተውኳት ። ሜዳ ላይ ግብ ግብ ልገጥማት አልችልም። በሠላም እንድትሔድ ከመተው ሌላ ምን ማድረግ እችላለሁ? እንደ እሳት እየነደድኩ ቆሜ ቀረሁ ። ባንድ ፊት ሮማን እንዲህ ጨክና አውላላ ሜዳ ላይ ጥላኝ ትሔዳለች ብዬ በልቤ አላመን ኩም ። ተከትያት እንዳልሔድም እልከ ያዘኝ ። ሰው የሚጣላ በትና የሚለያይበት ጥቃቅን ምክንያቶች አናደዱኝ ። አዘንኩኝ ። ሰው ቢደማመጥ አሁን ምናለበት? ከስንቱ ስቃይና ስጋት ራሳች ንን ከደን ነበር!........ እና ፊያሜታ ጊላይን ከልቤ ረገምኳት ።

ሞኝ በመሆኔም ራሴን ጠላሁት ። ለመጮህም ሆነ እንባ አውጥቼ ለማልቀስ አልቻልኩም ። መፈንዳትም አልሆነልኝም ። እንዲህ ሲኮን ምን ይሰማል? እንደተጠመደ የጊዜ ቦምብ ትር ፣ ትር ሲሉ ከመዋል ሌላ ምን ይደረጋል? ልትፈነዳ ትፈልጋለህ ፣ ግን አት ፈነዳም ። ንዴቴንና ቁጭቴን ፊያሚታ ጊላይ ላይ ለመወጣት ፈልጌ ነበር ። ሔጄ እሷ ላይ ከመፈንዳት ሌላ ምኞትና አሳብ አል ነበረኝም ። ኮሎኔል በትሩ ቢሮ አሥሬ ይሆናል ስልክ የደወልኩ ት ። ከምጽዋ አልተመለሰም ። ያገኘሁትን መረጃ ልነግረው አሁን በቸኮልኩበት ጊዜ እሱን በማጣቴ ነደደኝ ። ከመረጃው ጋር የም ሞት ወይም የምፈነዳም መስሎ ተሰማኝ ። የትረገመ እድል! እንደምንም መሸልኝ ። እንደዚያን ቀን ጊዜ ረዝሞብኝ አያው ቅም ።

ኒያላ ሆቴል አካባቢ ፊያሚታን መጠበቅ ጀመርኩ ። አንድ ሰዓት ሆነ ። ቀጠሮ አክባሪ ነበረች ። ግን በቀጠረችኝ ሰዓት አልመጣችም ። ደቂቃዎች አለፉ ። ደቂቃዎች መጡ ። ሴቶችን አምስት ደቂቃ መጠበቅ ግዴታ ነው ፣ ይባላል ። አሥር ደቂቃ መስጠት ጨዋነት ነው ። ከዚያ በላይ መቆየት ግን ሞኝነት ነው የሚል መርህ ቢኖረኝም እንደሞኝ መንገድ መንገዱን እያየሁ ጠበቅኳት ። አንድ ሰዓት ከሐያ ደቂቃ ሆነ ፊያሚታ ባገሩም የለችም ። አሁንም ተስፋ አልቆረጥኩም ። በተጨማሪ አሥር ደቂቃ ያህል ጠበኳት ። አሁንም አልመጣችም ። ይቺ ውሽ ነቅታ ብኝ ይሆናል የጠፋችው ፣ ቆይ ግድ የለም በማለት እየዛትኩና እየተናደድኩ ሮማንን ፍለጋ ወደ ክረን ሆቴል ሔድኩ ። ከሮሚ ጋር ለመታረቅ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ፈልጌ ነበር ፣ መቸም ጊዜ የማይለውጠው ነገር የለም በማለት አንዳችን የግድ የልብ ኩራታችንን ውጠን ካልተሰበርን ፍቅራችን ይበጠሳል ። ለፍቅር ማጎንበስ ያስፈልጋል ። እኔና ሮማን ስንጣላ የመጀመሪያ ጊዜአችን አይደለም ። አንድ ጊዜ ተጣልተን የተኳረፍንበት ሁ ኔታ ከሁሉም ትዝ ይለኛል ። ጠጉር ሠሪ ቤት ወስጃት ነበር ። በተ ባባልነው ሰዓት ተመልሼ ልወስዳት አልቻልኩም ። በጣም ዘገየሁባት ። አጣዳፊ ሥራ ነበረኝ ቋወንድ ልጅ ብዙውን ጊዜ የራሱ ጊዜ የለውም ። ልወስዳት ስመጣ አኩረፈችኝ ። አንድ ግብዣ ላይ መገኘት ነበረብን ። መኪናዬ ላይ አልወጣም አለች ። ብላት ፣ ብሠራት አሻፈረኝ ብላ ቀረች ። «ታዲያ ለዚህ ከሆነ መ ጀመሪያውኑ እስካሁን ለምን ጠበቅሽኝ?» አልኳት ።

«እንጃልህ!» ብላ ታክሲ ይዛ ጭልጥ አለች ። በጣም ስላና ደደችኝ ለሣምንት ያህል ጠፋሁባት ። የትግል ሣምንት ነበር ። ከልቤ ጋር ስሟገት ጥርሴን ነክሼ ሣምንቱን አሳለፍኩት ። ቅዳሜ ማታ ስልክ ደወለችልኝ ። ያለችኝ ሁሉ ትዝ ይለኛል...... «አንተ ኩራተኛ አሰህ? ዛሬ ከቤት ባጣህ ኖሮ ዳግመኛ አልደውልም ነበር ። ጨካኝ ። መጥፎ ጨካኝ ነህ......እሺ እኔስ ካንተ መኪና ላይ አልወጣም ብዬ ታክሲ ይዤ ልሒድ ። ይገባኛል ። አንተ ተከትለኸኝ እንዳትመጣ ያደረገህ ነገር ምንድነው? ቤቱን ታውቀዋለህ ። ኩራት ፣ ንቀት ፣ እብሪት ነው ያስቀረህ አይደለም? ስለ ሴት ምንም ነገር አይገባህም ። የሴት አያያዝ አታውቅም ። ፍቅር ምን እንደሆነ አይገባህም ። በእውነት የምትገርምና የምታሳዝን ፍጡር ነህ......»

ተመሳሳይ የሆነ ጥፋት በመድገሜ ራሴን ታዘብኩት ። ልሒድ ብላ በተነሳችበት ጊዜ በግድ ይዤ ማስቀረት ነበረብኝ። ዝም ብዬ መልቀቅ አልነበረብኝም ። ያውም በማታውቀውና አስታራቂ በሌለበት አገር ።

ሮማን ከረን ሆቴል አልነበረችም ። ወደዚያ እንዳልተመለሰች ተነገረኝ ። የት ገብታ ይሆን? በማለት ኒያላና እምባሦይራ ሒጄ ጠየኩ ። ሁለቱም ቦታ አልነበረችም ። ሌሎች ሁለት ሆቴል ቤቶች ሞከርኩ ። የትም አልነበረችም ። ሌላ የማደርገው ነገር አልነበረኝም ። ተስፋ አልቆረጥኩም፣ ምናልባት ወደ ቤት ተመልሳ ይሆናል በማለት ወደ ቤቴ አመራሁ ።

ግቢውን ከሚጠብቁት ወታደሮች አንዱ በእንቨሎፕ የታሸገ ወፍራም ደብዳቤ በሩ ላይ ሰጠኝ ። ስምና አድራሻ አልተጻፈበትም ። የሮማን ደብዳቤ መስሎኝ ይዤ ወደ መኝታ ቤቴ ገባሁ ። የፊያሚታ ጊላይ ደብዳቤ ነበር ። ወረቀቱ ወጥ ወጥ ይሸታል ። ገረመኝ ። ፊያሚታ የነካችው ነገር ቀርቶ ያለፈች በትም መንገድ ሽቶ ሽቶ ነበር የሚሸተው ።

«ጸጋዬ ፣ ይህ የመጨረሻ ቃሌ ነው ። የተገናኘንበትን ቀን እረግመዋለሁ ። ቀይ ኮከብ ነው ጉድ የሠራኝ አባቴ ይሙት ። ቀይ ኮከብ አንተን ባያመጣብኝ ኖሮ ጣጣ ውስጥ አልገባም ነበር ። እኔ የተፈጠርኩት ለደስታ ነው ብዬህ የለም? ቀይ ኮከብ አንተን

ባያመጣብኝ ኖሮ ደስ ካለኝ ወንድ ጋር እየገባሁና እየወጣሁ በደ ስታ እኖር ነበር ። አሁን ግን ደስታ የለኝም ። ደስታን አጥቼ ዋለሁ ። ሕይወት ስቃይ ሆናብኛለች ፣ ዕድሜ ላንቴ ። ስካሮኛ ነህ አባቴ ይሙት ።

«አሁን ሳስበው አንተን ከማወቄ በፊት ያሳለፍኩትም ሕይ ወት የደስታ ጊዜ ነበር ለማለት አልችልም ። የምወደውና የሚ ወደኝን ልጅ ስፈልግ ነበር የኖርኩት ። እንዳጋጣሚ አንቴን አገ ኘሁህ ፣ ያለ ዕድል ሆኖ አጣሁህ ፣ ወይም ላጣህ ነው ።

«ለምን ወደድኩህ? የሚያከብረኝ ፣ የሚግባባኝና የሚወደኝ ወንድ ስፈልግ ኖሬአለሁ ። አንተ ሦስቱንም ታሟላስህ ። የራስ ክን ደስታ ብቻ በማሰብ ወደ መኝታ የምትጎትተኝ ሆነህ አላገኘ ሁህም፣ እንደሌሎቹ የመሐል አገር ወንዶች የቱሪስት ጠባይ የለህ ም ። ወደድኩሽ ፣ ሞትኩልሽ ሲሉ ከርመው በመጨረሻ መሔጃ ቸው ሲቃረብ ይከዱሀል ። አባቴ ይሙት ባለጌ ናቸው ። አይገር ምም ። ድሮውንም ከቱሪስት ምን ይጠበቃል ። አንተ ግን እንደሱ አይደለህም ። ስለሆነም ፣ ካንተ ጋር ስሆን መላ ሰውነቴ ይዝናና ናል ። ነፍሴ በደስታ ባሕር ውስጥ ትዋኛለች ። የምደብቅህ ወይም የምቆጥብብህ ነገር የለኝም ። ካንተ ጋር ስሆን ሰውነቴን እረሳዋለሁ ። ይሉኝታ የለኝም ። እፍረት አይሰማኝም ። እወድ ሀለሁ ። ጠረንህ ጠረኔ ሆኗል ። ሰውነቴ ሰውነትህ ። ከሚወዱት ሰው ጋር ፣ ከሚግባቡት ሰው ጋር አንዷት ደቂቃም ብትሆን ማሳለፉ ዓቤት ደስ ሲል! ያለ ፍቅር አንድጣራ ስር አብሮ መኖር ᎐ኮ ቁም ነገር የለውም ። ግን አንተም ብትቆይ ያው የቱሪስት ጠባይ ሳታሳየኝ አትቀርም ነበር ። ይሆን ከማየቴ በፊት መሞቴ ደስ ይለኛል ። እንዴት አዝን ነበር? አባቴ ይሙት ።

«የሚያሳዝነው የሚወዱትን ፣ ሲፈልጉት የኖሩትን ሰው አግኝቶ ማጣት ነው ። አጣሁህ ። ምነው ባላወቅሁህ? ለደስታ ነው የተፈጠርኩት ብዬ አስብ ነበር ። ግን አይደለም ። ለመከራ የተፈጠርኩ መሆኔ ገብቶኛል ፣ ዕድሜ ላንቴ ። አንተ ከእጮኛህ ጋር ተደሰት ። መጥታልህ የለም? እንኳን ደስ ያለህ ። እስቲ ባባትህ ንገረኝ ፣ እንደኔ ትሆንልህለች? እንደኔ ትወድህለች? ከኔ የበለጠ አንቴ ላይ ምን መብት አላት? የተለዋወጣችሁት ቀለበት ነው ቁም ነገሩ? ባታውቀው ነው እንጂ እኔ ሕይወቴን ልለውጥልህ ነው ። ደደብ ። አባቴ ይሙት ደደብ ነህ ። ግን

ለምንድነው? ምን ዓይነት ሴት ነኝ? እስቲ ንገረኝ፤ ግን ልትነግረኝ አትችልም ። ከእንግዲህ አታየኝም ፤ በሕይወት አታገኘኝም ።

«ጸግዬ ፣ ስለኔ ሁሉን ነገር አጫውቼሀለሁ ። ላንተ ግልጽ እንደሆንኩ ለማንም ሆኘ አላውቅም ። አንድ ነገር ብቻ አልነገርኩሀም ። ለምን ሳልነግርህ እንደቀረሁ ምክንያቱ አይገባኝም ። ከዛሬ ነገ እነግረዋለሁ እያልኩ አስብ ነበር ። ሳልነግርህ የቀረሁት ምናልባት አጣዋለሁ በማለት ይሆናል ። አትፍረድብኝ ። የወደደ ሰው እውር ነው ። አሁን ልንገርህ ።

«ከኰሎኔል ታሪኩ ወልዳይ ጋር ሰባት ዓመት አብረን ወጥተናል ። አከብረዋለሁ ፣ ያከብረኛል ። ደግ ነው ። የዋለልኝ ውለታ ብዙ ነው፣ግን ይሉኝታና አክብሮት ብቻቸውን ለፍቅር መሠረት ሊሆኑ አይችሉም ። የሚያስታውሰኝና የሚጠራኝ በፈለገኝ ጊዜ ብቻ ነበር ። ሌላ ጊዜ ትዝ የምለው አይመስለኝም ። በሕይወቱ ውስጥ አልነበርኩም ። እሱም በሕይወቴ ውስጥ አልነበረም ። እና አንተን መውደዴ ኃጢአት ይሆንብኛል? የፈለኩትን ለመውደድ መብት የለኝም ወይ? ከሰው የተፈጠርኩ አይደለሁም ወይ? የፈለኩትን ለመውደድ መብት አለኝ ። የሠራሁት ኃጢአት የለም ። ባል ወይም እጮኛ የለኝም ። ያልነገርኩህ ትቀናለህ ብዬ አይደለም ። ጦር ሜዳ ከሚዋጋ ሰው ወዳጅ ጋር እንዴት እወጣለሁ? የምትል ስለመሰለኝ ነው ። ስለወደድኩህ በዚህ ምክንያት ላጣህ አልፈለኩም ። ይህን እንዴት ለማወቅ ቻልሽ? ትለኝ ይሆናል ። ተሰማኝ ። አብዛኛውን የሴት እውቀት የሚመነጨው ከስሜት ነው ። እውቀቷ ቀጥተኛ ነው ። አትፍረድብኝ እሺ? ደደብ ።

«እኔ ያለ ፍቅር የማውቀው ነገር የለኝም ። ወንዶችን ፍቅር ማስያዝ ደስ ይለኛል ። ወንዶችን ፍቅር ማስያዝ ቀላል ነው ። እንዴት መሰለህ? መጀመሪያ ሳገኘው ልክ ስፈልገው የኖርኩት ሰው አስመስዬ የልብ ልብ እሰጠዋለሁ ። ግልጽ እሆንለታለሁ ። ፍቅር አሳየዋለሁ፣ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለጥቂት ሣምንታት አልለየውም ። ሳላየው ውዬ አላድርም ። ሌላ ሴት እንዲያይ ወይም አሳብ እንዲኖረው ጊዜ አልሰጠውም።እንዲለምደኝ አደርገዋለሁ፣ ደሙ ውስጥ እገባለሁ ። ጠንድ ሞኝ ነው ፣ ውሻ ነው ። ቶሎ

ይሰምዳል ። የለመደኝና ደሙ ውስጥ የገባሁ መሆኔን ካወቅሁ በኋላ ገሸሽ ላደርገው እጀምራለሁ ፤ ዛሬ አይቀርቸኝም ፤ ነገም አይ ሆንልኝም ማለት እመጣለሁ ፤ ካመረረ እሔድለታለሁ ። ብሔድ ለትም የመንፈስ እረፍት አልሰጠውም ። በፊት የማውቃቸውን ወዳጆቼን ስም እየጠራሁና ዝናቸውንና ደግነታቸውን ፤ ኃይላቸ ውንና ወንድነታቸውን እያነሳሁ አስቀናዋለሁ ። ከእንግዲህ የፍ ቅርና የቅናት እሳት ተማረ ማለት ነው ። አንተንም እንዲህ ላደርግህ ጀምሬ ነበር ። ግን አሳዘንከኝ ። ለምን እንደሆነ እንጃ ልማወትብህ አልቻልኩም ። አታላይ ስላልሆንክ ላታልልህ አልፈለኩም ። የልማድና የቅናት እሳት በሚማርበት ጊዜ ልዩ ልዩ ወዳጆች የተለያየ ርምጃ ይወስዳሉ ። አንዳንድ ወንዶች እልክ ይገቡና ጨት ማታ ዱላ ይጀምራሉ ። የባሰባቸውም ይገድ ላሉ ። ሚስቴን ፈትቼ ካላገባሁሽ ሞቼ እገኛለሁ የሚሉም ይገ ኛሉ ። ታውረዋል በቃ ። በሆዴ እስቃለሁ ። ጅልነታቸው ያስ ቀኛል ። እታዘባቸዋለሁ ፤ እንቃቸዋለሁ ። እስቲ ባባትህ እየው ፤ ስንት ዘመን ትዳር ይዞ የኖረ ፤ ልጆች ያለው ሰው ፤ ድንገት እዚህ ለሥራ መጥቶ አገባሻለሁ ፤ ጠብቂኝ ፤ አትለይኝ ሲልህ ምን ትለዋለህ? ውሸቱን ነው ፤ የሚፈልገው የለመደውን ሰውነ ቴን ብቻ ነው ። እስካስ ድረስ ሌላ ወንድ እንዲነካበት ስለማይ ፈልግ ብቻ ነው ፤ ቅናት ስለሚያሳርረው ብቻ ነው ። እባቴ ይሙት ፤ ወንዶች ስትባሉ በመሠረቱ ከእውሬ አትሻሉም ። ሴቶችን ውሻ ትላላችሁ እንጂ ከወንዶች የባሰ ውሻ የለም ።

«ሌሎች ወንዶች ደግሞ ቅናት ይዟቸው እልክ ሲገቡ ያለ የሌለ ገንዘባቸውን በላዩ ላይ ማፍሰስ ይጀምራሉ ። ጨት ማታ ፤ ዘወትር ግብዣውና ስጦታው ይጎርፋል ። በቀን እስከ መቶ ብር መመንዘር ይመጣል ። ከየት ነው ይህን ሁሉ ገንዘብ የሚያመ ጡት? እዚህ አገር የሚመጡት አብዛኛዎቹ ወንዶች ግፋ ቢል ደመወዛቸው ከስምንት መቶ እና ወይም ከሺህ ብር አይበልጥም ። በዚያ ላይ ሚስት ፤ ልጆች አሏቸው ። እንድም ፤ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን እያስራቡና እያስጠሙ ፤ ቤታቸውን እያራቆቱና ልጆቻቸውን ካላማማ እያስቀሩ መሆን አለበት ። እየተበደሩና እየተሰቀቁ መሆን አለበት።ይህ አልበቃ ሲል ምን ይከናል? ጉቦ መብላት ፤ ማጭበርበርና በሥልጣን ተጠቅሞ መበዝበዝ ይመ ጣል ። እንዲህ ዓይነት ወንዶች በመሠረቱ ያልሆኑትን ሆነው መታየት የሚፈልጉ ጉረኞች ናቸው ። በየምሽቱ መቶ ብር በመ

ምዘዝ ፣ ውስኪ እንደ ውሀ በመጠጣትና በመጋበዝ ፡ ስጦታ በማዥጎድጎድ የሴትን ልብ ለመማረክ የሚጥሩ ርካሾች ስለሆኑ በሆዴ እስቅባቸዋለሁ ፣ በልቤ እንቃቸዋለሁ ። ግን እንዲህ ዓይነቱ ወንዶች ይሻሉኛል ። ከተደሰትኩ ምን ቸገረኝ? የምፈልገውም ይህንኑ ነው ። አሁን ባባትህ ስታስበው እንዲህ የማጌጠውና የምሽቀረቀረው በማገኛት ደመወዜ መሰለህ? የማገኛት ደመወዝ ለሽቶም አትበቃኝም ።

«እኔ የምጠላው የሚደባደቡትን ወንዶች ነው ። አንዳንድ ወንዶች ከአህያ ፍቅር ሌላ አያውቁም ። ፍቅር በግድ ይሆናል? አይሆንም ። ሴት ደብድበህና አድምተህ ፣ ደም አስተፍተህ በግድ ብትተኛት ኃጢአትም ወንጀልም ነው ፣ ሴትን ልጅ ያለውዴታዋ በግድ ፣ በጉልበት መድፈርና ጧት ማታ «ዶሮ ጠባቂ አድርጌ ባላስቀርሽ እኔ ወንድ አይደለሁም» እያሉ ማስፈራራት በርግጥ ወንጀል ነው ። ይህን ስለምፈራ ነው ባለሥልጣኖችን የምመርጠው ። አንድ ሰው ባለሥልጣን ከሆነ ክብሩን ስለሚጠብቅ ከነውር ሥራ ይቆጠባል ። አይደባደብም ፡ ሌሊት ሰክሮ መጥቶ ቤት ሰብሮ ልግባ አይልም ፣ ወይም በየመንገዱ በመኪና እያሳደደ ነይ ሙረጂ በማለት አምባጓሮ አይፈጥርም የሚል ግምት ነበረኝ ። አሁን አሳቤን ለውጫለሁ ። አንድ ባለሥልጣን ነው አሳቤን ያስለወጠኝ ። በጠፋሁበት ቁጥር ቤቴ ቀርቶ ቢሮዬ ድረስ እየመጣ ከሥራ ጓደኞቼና ከአለቃዬ ፊት ደም ያስተፋኝ ነበር ። ምን ይደረጋል? ባለሥልጣን ስለሆነ የሚናገረውና የሚደፍረው የለም፣ ሁሉም ወገኑ ነው ። ከባለጊዜ ጋር ማን ተጋፍቶ ይችላል? ቤት እየመጣ እናት አባቴና ወንድሞቼ ፊት ይደበድበኝ ነበር ። ወንወንድሞቼ እሳት የላሱ ጎረምሶች ቢሆኑም ምንም ሊያደርጉት አይችሉም ነበር ። ቢናገሩትና ቢደበድቡት ምናልባት ጸረ አብዮትና ጸረ አንድነት ናቸው ተብለው ሰምበል ይገባሉ ። ይህን ውርደት ማየት ጠልተው በመጨረሻ አንዱ አበደ ፣ ሌላው አዲስ አበባ ሔዶ የት እንዳለ አይታወቅም ፣ ቤታችን ላይ የደረሰ ርግማን ሆኘ ቀረሁ ። ነው ደግሞም ። በገዛ ራሴ ያመጣሁባቸው ውርደት ነው ። ሲያዝኑብኝ ይኖራሉ ።

«እኔ መውጣት የምወደው ሚስት ካላቸው ወንዶች ጋር ነው ብዬህ ነበር ። ታስታውሳለህ? ከሴትም ጋር አልክ መግባት ደስ ይለኛል ። ግን ዋናው ምክንያት ሚስት ያለው ወንድ ጧት ማታ

አያስቸግረኝም ፤ እንደ ልቤ ለመሆን እችላለሁ በማለት ነበር ። አሁን ሚስት ያላቸውንም ወንዶች መሸሽ ጀምሬአለሁ ። አንዳንዶቹ ከወንደላጤዎች ይበልጥ ያስቸግራሉ ፤ ይሉኝታ አያውቁም ። ከሚስቶቻቸው ጋር በተጣሉ ቁጥር መጥተው ያስቸግራሉ። በር ይደበድባሉ ። በስካሩ ቁጥር አያስቀምጡም ፤ አያስተኙም ፤ ሰው ምን ይለኛል አይሉም ። መጥኔ ለሚስቶቻቸው! ይህን እያየሁ እንዴት ባል ላገባ እችላለሁ? እንዴት ልወስን እችላለሁ?

«ከአዲስ አበባ የመጣ አንድ አባወራ ያደረገኝን ልንገርህ ። ግን ለምንድነው የምናዘዝልህ? እዚህ አገር የተመደበ ባለሥልጣን ነው ። ስሙ ምንም አያደርግልህም ። አዲስ አበባ ቆንጆ ሚስትና አበባ የመሰሉ ልጆች አሉት ። ባለሥልጣንም ባለትዳርም ስለሆነ አያስቸግረኝም ብዬ እንደልማዴ አጠመድኩት ። ሊሰቀኝ መስለህ! ኩርፊያው ፤ ዱላው ፤ ጭቅጭቁ አላስቆም አላስቀምጥ አለኝ ። መግቢያ መውጫ አሳጣኝ ። የተፈጠርኩበትን ቀን አስረገመኝ ። እንዴት ልገላገለው ብዬ ሳስበው ስጨነቅ አንድ ሌላ ባለሥልጣን አጋጠመኝ ። እብድ ነው ። ጨርሶ የለየለት እብድ ነው ። ይኸኛውም የባሰ መኸገር ሆነብኝ ። ምሳና ራቴ ጥፊ ሆነ ። ከመጥበሻ ወደ እሳት እንዲሉ ፤ ከበፊተኛው ሰውዬ ተገላገልኩ ስል የባሰ አጋጠመኝ ። ነፍስና ሥጋዬ ተሰበሰበ ። ሰበሰበኝ ፤ አቃጠለኝ ፤ መኝታው እሳት ሆነብኝ ። ስለዚህ ሰውዬ ኋላ አጫውትሀለሁ ። ግን አሁን ልነግርህ የምፈልገው ሌላ ነገር ነው ።

«ይህ ሁሉ ችግር የሚደርስብኝ ለምን መሰለህ? ግፍ ውያለሁ ። አንድ ሰውዬ ነበር ። ቤቱ ሲወስደኝ ልጃገረድ ነኝ ብዬ አለቀስኩበት ። ውሽቴን ነበር ። ለምን እንዲህ እንዳልኩት አላውቅም ። በውሸቴ ጸናሁ ። አመነኝ ። ሁለት ዓመት ሙሉ አብረን ወጣን ፤ ያበላኛል ፤ ያጠጣኛል ፤ ያስጌጠኛል ፤ ያንሸራሽረኛል ። አንድ ቀን እንዳጋጣሚ በኮምቢሽታቶ በእግሩ ሲዘዋወር ካንድ ፎቶ ቤት በቬሎ የተነሳሁትን የሠርጌን ፎቶግራፍ አየ ። ይገርምሃል ምንም አላለኝም ። በራሱ ሞኝነት ሲስቅ ቆየና «ምናለ በይኝ ፤ የዋልሽብኝ ግፍ ደም ሲያስለቅስሽ ይኖራል» ብሎኝ ሔደ ። እውነትም ደም ሳለቅስ እኖራለሁ ። ወንዶች ላይ የምዘረጋው ወጥመድ እኔን መልሶ ያጠምደኛል ፤ ያስቃየኛል ። ግን ለምንድነው እንዲህ የምሆነው? ምን ዓይነት ሴት ነኝ?

«ማን አባቴ ይሙት ፤ ለምንድነው ክብራቸውን የሚጠብቁ ፤ ያልሆኑትን ሆነው መታየት የማይፈልጉ ፤ ሲወዷቸው የሚወዱ ፤ ሲጠሏቸው የሚተው ፤ በየመጠጥ ቤቱ የማይዞሩ ፤ ሥራቸውን አክብረው የሚያስከብሩ ፤ ትግሬ ሲባል ሁሉም ወንበዴ ነው ብለው የማያምኑ ፤ በአነጋገራቸውና በተግባራቸው እንደ ምሳሌነት የሚታዩ ፤ አጉል ኩራት ፤ ትዕቢትና ጉራ የማያጠቃቸው ፤ አስተዋይና ትሁት የሆኑ ምርጥ ፤ ምርጥ ሰዎች እዚህ የማይመደቡት? ጥሩ ነበር አባቴ ይሙት ። እኔ የፖለቲካ ሥራ ነው የምለው ይህን ነው ። ፍትወት ፤ ፍቅረንዋይ ፤ ጉራ ፤ አጉል ትዕቢትና የሥልጣን ጉጉት የሚያጠቃቸውን ሰዎች ሥልጣን ላይ ማስቀመጥ ፖለቲካ ያበላሻል ። ቀይ ኮከብ ዘመቻ ነገሩን ቢያስብበት ጥሩ ይመስለኛል ። እኔ ፖለቲካ አላውቅም ። ማወቅም አልፈልግም፤ እኔ የማውቀው ፍቅር ብቻ ነው ። ቢሆንም የፖለቲካ ሥራ በመሠረቱ አመራር ላይ ያሉ ሰዎች ያላቸው ጥንካሬና በሕዝብ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነትና እምነት ይመስለኛል ። አንዳንዶቹ ደግሞ ከጸሐይ በታች ያለውን ነገር ሁሉ ቃል ይገባሉ ። ሥራ አስገባሻለሁ ፤ ደሞወዝ አስጨምርልሻለሁ ፤ ውጭ አገር እልክሻለሁ ፤ የታሰረውን ወንድምሽን ወይም ዘመድሽን አስፈታልሻለሁ ወዘተ... የማይገቡት ቃል የለም ። አንዳንዶቹ ያደርጉታል ። ይህ ምን ፍትሕ ይባላል አባቴ ይሙት ። ደህና ባለሥልጣን የያዘች ሴት የፈለገችውን ስታደርግ ሌሎቹ ምን ያድርጉ? ምን ይበሉ? ምን ይሥሩ?

«ምርጥ ምርጥ ሰዎች ሥልጣን ላይ እንዲቀመጡ ቢደረግ የአሥመራ ሴቶችም ያርፉ ነበር አባቴ ይሙት ። ፍትሕም ይገኝ ነበር ። አሁን የአሥመራ ሴቶች ከኔ ጀምሮ ፤ የመሐል አገር ወንዶች ለሴት ሟች ስለሆኑ በቀላሉ ይሞኛሉ ፤ ይታለላሉ ፤ ይራገፋሉ ፤ በቀላሉ ለሴት ተገዢ ይሆናሉ የሚል እምነት አለን ። ደግሞም እውነት ነው ። ከመሐል አገር የሚመጡት ወንዶች ልክ እንደ ጣልያን ናቸው ። ሴቶችን ማክበርና መንከባከብ ይወዳሉ ። ያሏቸውን ያደርጋሉ ። ጉራ አላቸው ። የትግሬ ወንድ ረግጦ ነው ሴቶችን የሚገዛው ። ለሴት ደንታ የለውም ፤ ክብር አይሰጣትም ። ከፈለገ ሚስቱን አስቀምጦ ሌላ ያገባል ። እና በዚህ እምነት የተነሳ የመሐል አገር ወንዶችን ሆን ብለው አሳደው የሚይዙ ፤ የሚቀበሉና የሚሸኙ ልዩ ሴቶች እሥመራ ውስጥ ተፈጥረዋል ። በጣም ብልጦች ናቸው ። ዓላማቸው አማርሶ ቶሎ ዞር ማለት ነው ። አንዳንድ መጥፎ መኸገር ካላጋጠ

ማቸው በስተቀር ለምን? ከመሐል አገር የመጣው ወንድ ባለ ትዳር መሆኑንና ለትዳርና ለነገር የማያፈልጋቸው መሆኑን ያውቃሉ ። ገንዘብ እንዳለው ያውቃሉ ፡ አብዛኞዎቹ ፍትወተ ሥጋ የሚያጠቃቸው መሆናቸውንም ያውቃሉ ። ወንዱ ሊጠቀምባቸው ይፈልጋል ፤ እነሱም ይጠቀሙበታል ። ይረባረቡበታል ። የምትግጠውና የምታራግፈው የሚያወጣት ቤት ብቻ አይደለለችም ። ጓደኞቿንም ጭምር ትጋብዛለች ። የመሐል አገር ሰው ጉረኛ ነውና ታከተኝ ፤ ደከመኝ አይልም ። ገንዘቡን ይከሰክሳል ፤ ማታ ማታ ሠርግና ምላሽ ይሆናል ። እንደ መዥገር ተጣብቀው በት ደሙን መጠው ሳይጨርሱ አይለቁትም ። ሂ... የሥመራ ቤተ ሳጤዎች ደም ውስጥ ለመግባት ጊዜ አይፈጅባቸውም ። ከደባበሱትና የወደዱት መስለው ከታዩት የመሐል አገር ወንድ በሬ ነው ፤ ቶሎ ልቡ ይማረካል ። በመሐል አገር ወንዶች ጉዳይ ከኔ የበለጠች ኤክስፐርት በአሥመራ ከተማ አትገኝም ። ብዙ ተቀብያለሁ ፤ ብዙ ሸኝቻለሁ ። ብዙ ተምሬአለሁ ። ታሳታውስ እንደሆን እንደተዋወቅን ሰሞን እኔም ጓደኞቼን እየጠራሁ ላማርስህ ተነስቼ ነበር ። ግን አሳዘንከኝ ። አንተ እንደሌሎቹ ወንዶች የራስክን ጊዜያዊ ደስታ ብቻ የምትፈልግና የምትሞኝ ሰው አይደለህም ፤ ወይም አትመስለኝም ። የምታደርገው ነገር ሁሉ ከንጹህ ፍቅርና ከቀና አስተሳሰብ ስለሚመነጭ ነው መሰለኝ ፤ ፍቅርህንና ግብዣህን ፤ ስጦታህንና ደግነትህን ማራከስ ይከብዳል ። ሌሎች ወንዶች ግን በገንዘብ ወይም በማታለል ወይም በጉልበት ጊዜያዊ ስሜታቸውን ብቻ ለማርካት ስለሚፈልጉ ፤ ደማቸውን መምጠጥ ቀርቶ አጥንታቸውንም ቢግጡ አይቆጭም፤ አያሳዝንም ። ብዙዎቹ ከሚስቱ ጋር የምኖርም አይመስለኝም ሲሉ የከረሙ አዲስ አበባ በገቡ ማግስት መፈጠሬን ጭምር የረሱ ብዙ ወንዶች አውቃለሁ ። አብዛኛዎቻቸሁ ርካሾች ናችሁ ። ግን እኔ እንደ አሥመራ ቤቶች ፍቅር ቶሎ አይዘኝም፤ አባቴ ይሙት ። የአሥመራ ቤቶች ይግረምህና ፍቅር ቶሎ ይገድላቸዋል ፤ ባንድ ጊዜ ሙትት ይላሉ ፤ ባንድ ጊዜ ነው ሙትት ፤ ፍርክርክ ፤ ብትንትን የሚሉት ። በተለይማ የሚያከብራቸውን ፤ የሚወዳቸውንና የሚንከባከባቸውን ወንድ ካገኙ በቃ ልባቸው እንደ ቅቤ ይቀልጣል ። የመሐል ሀገር ወንዶችን የሚወዱት ለምን መሰለህ? ፍቅር ያውቃሉ ፤ ሴቶች ያከብራሉ ስለሚሉ ነው ። ደብረ ዘይት ብትሄድ የአየር ኃይል የመኰንኖች ሚስቶች መሳ ለመሳ የአሥመራ ሴቶች ናቸው ። ከባሕር ኃይሎችም ጋር

በብዛት ተጋብተናል ። ከመሐል ሀገር የመጣው መለዮ ለባሽና ሚሊሺያ ፣ አባት ጦሮችም ሳይቀሩ አንዳንድ እየያዙ በመመለስ ላይ ናቸው ። ጥሩ ምልክት ነው አባቴ ይሙት ። ጥቂት ወንዶ ቻችን እንገንጠል ቢሉም ፣ ሴቶቻችን አንድነትን እያጠበቁ ናቸው ። የአንድነት መሠረቱ ፍቅር ነው ፣ አይመስልህም? እኔ ግን የመሐል ሀገር ሰዎችን አልወድም ነበር ። ከቱሪስቶች ጋር ፍቅር መውደቅ ምን ያደርጋል? ብዙዎቻችሁ ቱሪስቶች ናችሁ። ጊዜው ሲደርስ ሾንጣችሁን እንጠልጥላችሁ ፈትለክ ከማለት ሌላ ምን ታደርጋላችሁ? ስትሔዱ እንኳን ደህና ሁኑ አትሉም ። አንተም ያው እንደሌሎቹ ቱሪስት ነህ ፣ አይደለህም? ቢሆንም ካንተ ጋር ፍቅር ይዞኛል ። ለምንድነው ግን? ምን ዓይነት ሴት ነኝ? እስቲ ንገረኝ ባባትህ? ይህን እዚህ ላይ ላቁምና ስለኔ ላጫ ውትህ ።

«አታውቅም እንጂ በጣም ቀናተኛ ነኝ።አይገርምህም!ባንድ በኩል ከአንድ ወንድ ጋር ብዙ ጊዜ መቆየት አልወድም ፣ በግድ ካልሆነ በቀር ። ይሁን እንጂ የማልወደው ወንድ ቢሆንም ከሌላ ሴት ጋር ሲወጣ ካየሁ ደግሞ ቅናት ይይዘኛል ፣ እታመ ማለሁ ፣ እስቃለሁ ፣ ልቤ የኃዘን ሙዚቃ ሲዘፍን ይውላል ፣ አንጀቴ ይቃጠላል ። ያንን ወንድ ካላገኘሁው ይለኛል ሆዴ ። እና እሱን ማሳደድ እጀምራለሁ ። ካላገኘሁት አላርፍም ። በእው ነት የሸርሙጣ ልብ ነው ያለኝ ። ግን ለምንድነው? እንዴት ልበ ልህ ? ወንዶች እንደ ውሻ ሲናከሱብኝና ሲጣሉብኝ በቃ ደስ ይለ ኛል ። እሷን ወደው ተጣሉባት ሲባል አቤት ደስታዬ! በወንዶች መጫወት ደስታ ይሰጠኛል ። ለራሴ ጥቅምና ውስጣዊ ፍላጎት ስል እጫወትባቸዋለሁ ። ግን እንዲህ ዓይነቱ ግንኙነት አንዳ ንዴ በመጨረሻ ያሳዝነኛል ። ያሰቃየኛል ። አንዳንድ ጊዜ በውድም ሆነ በግድ ፍቅር ይይዘኛል ። ግን መወሰን አይሆን ልኝም ። ሸርሙጣ ልብ እንዴት ሊወስን ይችላል ። ይገረምሀና የሚለማመጠኝን ወንድ ብዙውን ጊዜ አልወድም ። ኮስተር ሲል ብኝ ይስበኛል ። አልፎ አልፎም ዱላ አልጠላም ። ኃይለኛ ወንድ እወዳለሁ ። ብዙ ሴቶች ወንድ ይወዳሉ ። ምናልባት ተፈ ጥሮአችንን ስለሚያካክስ ይሆናል ። አይገርምህም? ለኃጢአቴ የምከፍለው ዋጋ ስለሆነ ነው መሰለኝ ።

«ምን ልነግርህ ፈልጌ ነበር? ረሳሁት ልጄ....... አዎን ፣ ወንዶች እንደውሻ ሲጣሉብኝ ደስ ይለኛል ብየሀለሁ ። እኔና

አንተ በፍቅር መተሳሰር የጀመርን ሰሞን ፣ ያ በገባሁበት እየገባ ደብድቦና አሰቃይቶ ይወስደኝ የነበረው ሰውዬ እዚህ መጥቶ ነበር ። ስሙን አልነግርህም ። የአሥመራ ሴቶች ወንድ ሁሉ የኔ ነው ፣ ወይም ነበር ማለት ይወዳሉ ። ለማንኛውም ነገር ሰውዬው እብድ ነው ። ከመምጣቱ በፊት ደወለልኝ ። እዚህም ከደረሰ በኋላ ቢሮና ቤት እየደወለ ከዛቻ ጭምር ያስፈራራኝ ጀመር ። አንተ ስላለህ ከእሱ ጋር ፈጽሞ ለመውጣት አልፈለኩም ። ባንድ ፊት ደግሞ እይው ፣ እይው የሚል በሽታ መጣብኝ ። እዚህ መጥቶ እኔ እያለሁ እንዴት ከሌላ ሴት ጋር ይሄዳል? የሚል ቁጭትና ቅናት አደረብኝ ። እሱ እዚህ መጥቶ ከሌላ ሴት ጋር መሔዱ ውርደት መስሎ ታየኝ ። በአሥመራ ከተማ የኔንና የሱን ታሪክ የማያውቅ መቸም የለም ። አንቀዠቀዠኝ ፣ ሆዴ ተቃጠለ ። በቃ ሳየው ፈለኩ ። አልገባህም እንጂ አንተ'ን ይገፎ እሱን ፍለጋ ያልዞርኩበት ቦታ የለም ። ከተማው ውስጥ ያለውን ቡና ቤት ሁሉ እየዞርክ ካላሰየኸኝ ብዬ ያስቸገርኩህ ምሽት ትዝ ይልሃል? ደደብ ፣ ግን አንተ አልገባህም ። ምንም አይገባ ህም ። ደደብ የምልህ ለዚህ ነው ። ከዚያ በኋላ የሆነውን ነገር አልነግርህም ። ብቻ ይቅር በለኝ ። ምን ላድርግ? ሸርሙጣ ልቤ ነው እንዲህ የሚያደርገኝ ። አንተ ሰው ታምናለህ ። ቅናት አታ ውቅም ። በእልክ አታምንም ። ማንኛውንም ነገር በውይይትና በመግባባት ለመፍታት ከልብ ትጥራለህ ። መግባባት ከሌለ ቀራጥ ርምጃ ለመውሰድ የምትችል ሰው ትመስለኛለህ ። በአጠ ቃላይ ንጹህ ልብ ቀና ስሜትና አስተሳሰብ ያለህ ሠላማዊ ሰው ነህ ። በጉልበቱ የሚመካ ኃይለኛ አይደለህም ። ግን ጉልበትና ኃይል የሚበግርህ ፍጡር እንዳልሆንክ ደግሞ አውቃለሁ ። ፍር ሀት የሚባል ነገር አታውቅም ። ምናልባት ደደብ ስለሆንክ ይሆናል ፣ አላውቅም ። ግን የተለየ ኃይል አለህ ። ግን ለምንድነው የወደድኩህ? ከሥልጣን ሥልጣን ፣ ከገንዘብ ገንዘብ የለህም ፣ መልክም ቢሆን ይህን ያህል አይደለህም።ያለህ ነገር ቢኖር ምላስ ብቻ ነው ፣ ለዚያውም ቢሆን ቲፎ ላይ ካልሆነ ዝግ ነህ ። ጨዋታ አታውቅም ። ድንግል ነህ ። ምናልባት ለዚህ ይሆናል የወደድ ኩህ ። ከነክብርናዋ የተገኘች ልጃገረድ ትወደድ የለ? እንደሱ ነህ አንተ ለኔ ። እንዲህ ባይሆንማኖሮ ይህን ጊዜ ሁለት ቀንድ አስ በቅልህ ነበር አባቴ ይሙት ። ግን ምን ያደርጋል? አሁን ነገሩ ሁሉ አልፎአል ።

«አሁን ይህ ሁሉ ምንም አይደለም ። ሌላም ያልነገርኩህ ነገር አለኝ ። እየተለወጥኩ መሔዴን አይተህ ምን ሆነሻል? እያልክ ብዙ ጊዜ ጠይቀኸኛል ። በጊዜው እንዳልነግርህ ለሕይወቴ ፈራሁ ። መወሰንም ተሳነኝ ። መወሰን አይሆንልኝም አባቴ ይሙት ። አሁን ግን ወሰኛለሁ ። ለምን? ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ? አሁን ምክንያቱን ልንገርህ ።

«ከጥቂት ሳምንታት በፊት አንድ ሰው ቤቴ መጥቶ ከጸጋዬ ኃይለማርያም ወይም ካንቺ ሕይወት አንዱን ምረጭ አለኝ ። ምን እንዳደርግ ነው የምትፈልገው? አልኩት ። ሰውዬው የሚፈልገው ነገር ግልጽ ነበር ። አንተን ከተፈለገበት ቦታ በተወሰነ ሰዓት ይዤ እንድመጣ ነበር የፈለገው ። ቦታውንና ቀኑን ወደፊት እነግርሻለሁ ብሎኝ ሔደ ። ሰውዬው ማን እንደሆነና የት እንደሚሠራ ደርሼበታለሁ ። የሚሠራው አርሚ አቪዬሽን ነው ። ስሙ ሁቼገይ ሲላ ይባላል ። እንዳልነግርህ ፈራሁ ። እንደሚገድለኝ እርግጠኛ ነበርኩ ። ነፍሴ ክፉኛ መጨነቅ ጀመረች ። ካንተ ወይም ከራሴ አንዳችንን መምረጥ ነበረብኝ ። በተጠየቅሁት መሠረት አሳልፌ ከሰጠሁህ ምንም ችግር ሳይገጥመኝ ካርቱም እንደሚያደርሱኝና ከዚያም ወደፈለኩበት እንድሔድ እንደሚያደርጉልኝ ቃል ተገብቶልኛል ።

«እንዳጋጣሚ ሆኖ ጊዜውንና ቦታውን ሳይነግሩኝ አንተ ተነስተህ ወደ ጦር ግንባር ሔድክ ። ለጊዜው ከጭንቀትና ከመከራ ተገላገልኩ ። አንተ ከመመለስህ በፊት ተነስቼ ለመጥፋት ፈልጌ ነበር ። አልሆነልኝም ፤ መወሰን አልቻልም ። በሔድኩበት ቦታ ሁሉ እንደሚከተሉኝ ይሰማኛል ። የማላውቃቸው ሰዎች እንደጥላ ይከተሉኛል ። በየጊዜው ቤቱና ቢሮዬ እየደወሉ መኖር እስመኖሬን ያረጋግጣሉ ። ሠላም አይሰጡኝም ። እንቅልፍ ካጣሁ ቆይቻለሁ ።

«እና በመሀሉ እሬኛህ መምጣቷን ሰማሁ ። መምጣቷን የነገረኝና ወስዶ እሷን ያሳየኝ አንድ የማላውቀው ሰው ነው ። አንድ ጠቅት ላይ ለኔ ካልሆነ ለማን እባክ ይሆናል? ከሕይወቴ የሚበልጥብኝ ምን ነገር አለ? አሳልፌ ሰጥቼው ለምን አልኖርም? ከሚል አሳብ ላይ ደረስኩ ። በዚሁ አሳብ ጸንቼ ሳለሁ ዛሬ አንድ ሰው ደውሎ መምጣትህን ነገረኝ ። ታስታውስ እንደሆነ ከአምስት

ደቂቃ በኋላ እደውልልሀለሁ ብዬህ ነበር ። በዚያ ጊዜ ውስጥ የተሰጠኝን ስልክ ቁጥር ተጠቅሜ ደወልኩ ። አንድ ሰዓት ላይ ወደ አይሮፕላን ማረፊያ እንዳመጣህ ታዘዝኩ ። የማደርገው ነገር ጠፋኝ ። መቁረጥ አቃተኝ ። አንድ የማላውቀው ሰው እንግዳ መስሎ መጥቶ ቢሮዬ ቁጭ አለ ። ምን እንደማደርግ ለመከታተል የመጣ ሰው መሆኑ ገባኝ ። እና የመሥሪያ ቤቱን ሥራ የምሠራ አስመስዬ ይህን ደብዳቤ ከመጻፍ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም ። ይህንኑ ደብዳቤ ስጽፍ ነው የዋልኩት ። ከልብ የሚጽፉት ነገር አያስቸግርም አባቴ ይሙት ። ደብዳቤውን እንዴት እንዳወጣሁት ይገርምሀል ። የሚጠብቀኝ ሰውዬ እንዳ ያየኝ በምሳ ሣህኔ ውስጥ አድርጌ ነው ያወጣሁት ። ምን ያህል እንደምወድህ የገባኝ ዛሬ ነው ። እወድሀለሁ አባቴ ይሙት ። ደደብ ። ግን ምን ዓይነት ሴት ነኝ፣ አንድ ነገር በሕይወቴ ወስኜ አላውቅም ። እርሜን ዛሬ አንድ ነገር ብወስን ይኸውና ችግር ላይ ወደቅሁ ።

«ለምን ለፖሊስ አትነግሪም ነበር፣ ትለኝ ይሆናል ። እስ ቤው ነበር ። ግን እንዳልኩህ ሰው እጠገቤ ነበር ። ይህን ሳልነግ ርህ ብሞት አንተም አትተርፍም ። የነበረኝ አማራጭ ይህን ደብ ዳቤ ጽፌ በሰው መላክ ነበር ። ይህ ደብዳቤ ይደርስሀል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ። ከዚህ በኋላ ምን ታደርጊያለሽ፣ ትለኝ ይሆናል ። በእውነት አላውቅም ። ተማፅኖብኛል ። ምንም እንደማልሆን ተስፋ አደርጋለሁ ። እንደገና እንገናኛለን፣ አይመስለኝም ። አገ ኘሁህ ፣ አጣሁህ ። ቻው እምበእር...... ጺጋዬ ።»

ወደ ኮሎኔል በትሩ ቢሮ ደወልኩ ።

ጸሐፊው ፣ «መጥተዋል ። ላገናኝዎት ፈልጌ አጣሆዎት ። ቢሮም ቤትም አልነበሩም» አለኝ ።

«እሺ አሁን አገናኝኝ.....»

«ቤት ደርሼ እመለሳለሁ ብለው አሁን ወጡ ። እሳቸውም በጣም ነው የሚፈልጉዎት .........»

«እሺ የቤቱን ቁጥር ስጠኝ ።»

የቤቱን ስልክ ቁጥር ሰጠኝ ። ቤቱ ደወልኩ ። አሁን ወጡ ተባልኩ ።

ጊዜ አላጠፋሁም ። ተነስቼ ወደ ማይተማናይ እንደ እብድ በረርኩ ። አሳቤ ፥ ቶሎ ደርሼ በሕዝብ ደኅንነት ሰዎች ጥበቃ ሥር ለጊዜው እንድትቆይ ለማድረግ ነበር ። ማይተማናይ ተናውጦቆየኝ ። የሠፈሩ ሕዝብ ይራወጣል ፥ ጩኸት በርክቷል ። እንዴትና የት እንዳቆምኩ አላውቅም ። ብቻ እንደሮጥኩ ሔጄ ፈያሜታ ቤት ጥልቅ አልኩ ። ግቢው በሚጮሁ ሰዎች ተሞልቷል ። አልጋዋ ላይ አጋድመዋታል ።

«ፈያሜታ! ፈያሜታ! ጸጋዬ ነኝ።ትሰሚኛለሽ? ፈያሜታ!» ቤቱ ላንዳፍታ ጸጥ አለ ።

«ደብዳቤው ደረሰህ?» አለች በተዳከመ ድምጽ ።
ልብሷ በደም ተበክሏል ።

«አዎን ፈያሜታ ። አይዞሽ ። አሁን ደህና ትሆኛለሽ.....»
«እሞታለሁ?»
«ኖኖ .......... ፈያሜታ አትሞችም...........»
«ግን ለምንድነው የምሞተው? ምን አጠፋሁ? እግዜር ለምንድነው የሚገድለኝ? ምን አደረኩት?»
«አይዞሽ ፥ ምንም አትሆኝም.....»
«ታስታውሰኛለህወይ?»
«እባክሽን ፈያሜታ ዝም በይ...........»
«አዎን ፥ አዎን ፈያሜታ...........»
«ሁልጊዜ?»

«ሁልጊዜ..... ኖኖ ፈያሜታ ። እባክሽን በርቺ........... ማነው የሚያግዘኝ? ሰዎች ለምን ዝም ትላላችሁ? ወደ ሆስፒታል እን ውሰዳት እንጂ...........»
«የሰጠሁህን መረጃ ቶሎ ተጠቀምበት ። ሰዎቹ አደገኞች ናቸው.....»
«እሺ...........»
«እኔም የቀይ ኮከብ ዘመቻ አባል ነኝ ፥ አይደለሁም? ፍቅር የቀይ ኮከብ ዘመቻ አካል አደረገኝ ። አንተ ደደብ...........»
«ፈያሜቴ! ፈያሜታ!»
ቆንጆ ፈገግታ ብቻ ከቆንጆ ፊቷ ላይ ቀርቶ ነበር ። ትንፏ ነበልባል ጠፋች ።

# አ ሮ ማ ይ

ዶራሲው ነኝ እንደገና ። ጺጋዬ ኃይለማርያም ከእንግዲህ በራሱ ቃላትና ስሜት ታሪኩን ለመግለጽ አይችልም ። ከባድ ኃዘን በድን አድርጎታል ። ምንም ነገር አያይም ፣ አይሰማም ። ምንም ነገር አይሰማውም ። ኃዘኑ ከአቅሙ በላይ ሆኖበታል ። ደራሲ ኃዘን አይሰማውም? ስለሰው ልጅ ያዝናል ። የራሱ ኃዘን ግን የለውም።እግዜር ሰውን በራሱ አምሳል ፈጠረ ይባላል። ግን ስለሰው ልጅ ያዝናል ። አይገርምም፣ ይገርማል ። ደራሲም እንደዚሁ ነው ። ግን ስለእግዚርም ሆነ ስለደራሲ ማን ደንታ አለው? አሁን ስለእሱ ግድ የለም ። ወደ ጺጋዬ እንመለስ ።

ፊያሚታ ጠፍታለች ። ይህ ሕይወት ባንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያስኬድ መንገድ ነው ። ከእንግዲህ ተመልሳ አትመጣም ። ሕይወት እንቆቅልሽ ሆነበት — ለጺጋዬ ኃይለማርያም ። ለጥል የፈለጋት ቤት ሕይወቷን ለእሱ ብላ አሳልፋ ሰጠች ። የእሷ ሞት ለእሱ ሕይወት ሆኗል — የብድር ሕይወት ። ሞቷ ከልቡ ውስጥ የበጠሰው ነገር የመኖሩን ያህል የሰወጠውም ነገር ነበር ። አዲስ እምነት አግኝቷል ። በሰው ልጅ ላይ አዲስ እምነት እንዲኖረው አድርገዋለች ። ኰሎኔል በትሩ ቢሮ ደወለ ።

ወደ ኰሎኔል በትሩ ቢሮ ሔዶ ስለ ሥዕላይ ያገኘውን መረጃ ሰጠውና ፣ «በጊዜ ባገኝህ ኖሮ ይህ ሁሉ አይደርስም ነበር» በማለት እድሉን አማረረ ።

ኰሎኔል በትሩ መልስ እስኪሰጠው ድረስ አልጠበቀውም ። በተጨማሪ «ስለ ፓራዲዞ ቡና ቤት ጠቃሚ የሆነ መረጃ ሰጥቼህ ነበር ። እስካሁን ርምጃ ያልተወሰደበት ምክንያት ምንድ ነው? በእናንተ ቸልተኛነት ምክንያት ነው የዚች ልጅ ሕይወት የጠፋው ። በእውነት አዝናለሁ» በማለት ሞኘበት ።

ኰሎኔል በትሩ ስለ ሥዕላይ ያገኘውን መረጃ ትኩር ብሎ ሲመረምር ከቆየ በኋላ ከወንበሩ ላይ ተነስቶ ቆመ ። ፊቱ ላይ የድል ስሜት ይነበብ ነበር — «ጓድ ጸጋዬ» አለ — «ቸል ያልን በት ጊዜ የለም ። ፓራዲዞን ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ በዓይነ ቁራኛ ስንጠብቅ ነው የከረምነው ። ሰብሮ መግባት ቀላል ነገር ነው ። ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብን ። ያልሆነ ሥራ ሠርተን ሌሎቹ እንዲነቁ ምክንያት መሆን ትርፉ ድካም ነው ። የምንወስደው ርምጃ ካለ የእነሱን የስለላ ድርጅት የጀርባ አጥንት የሚሰብር መሆን አለበት ። ብዙ «ሴሎች» እንዳሏቸው ይገመታል ። ዋና ሴላቸውን ካልሰበርን ጥቃቅኖቹን መስበር ጥቅም የለውም ። አንዱ ሴል ስለሌላው አያውቅም ። ዋናውን ሴል ከሰበርን ግን ሌሎቹን መስበር ቀላል ነው ። እርግጠኞች መሆን ነበረብን ። አሁን እርግጠኛ የሆንኩ ይመስለኛል ። አሁን የሚያጠራጥር ነገር የለም ። ፓራዲዞ ። ሥዕላይ ። ዋናው የእርማይ ሴል ።»

ፊቱ ላይ የሚታየው ፈገግታ ብሩህ እየሆነ ይሔድ ነበር ። ስልኩን አንስቶ ተኽላይን ጠራው ። ተኽላይ እንደልማዱ ሽክ ብሎአል ።

«ሰዎችህ ዝግጁ ናቸው?»
«ዝግጁ ነን ጓድ ኰሎኔል ። የምንሠራው ሥራ አለ?»
ተኽላይ ድርጊት የጠማው ይመስላል ።
«ስለፓራዲዞ ቡና ቤት አዲስ ወይም ተጨማሪ መረጃ አለህ?
«እስካሁን ምንም የለንም!»

«እሺ ። ቡና ቤቱ እንዲሰበር እፈልጋለሁ ። አሁን! እዚያ ውስጥ የሚሠሩትን ሰዎች አንዳቸውም እንዲያመልጡ አልፈልግም ። ግልጽ ነኝ ። እና ሥዕላይን ከነሕይወቱ ነው የምፈልገው ። ጊዜ የለንም!» አለው ።

ተኽላይ ፊት ላይ ይነበብ የነበረው ደስታ ልዩ ነበር ። ወጥቶ ሔደ ።

ከምሽቱ አራት ሰዓት ከአርባ ደቂቃ ሲሆን የፓራዲዞ ቡና ቤት ባሬስታ ቡና ቤቱን ዘግቶ ሲወጣ ተያዘ ። ተኽላይ ዘድንገል ለሰውዬው ጊዜም ሆነ እድል አልሰጠውም ። ኩላሊቱን እንዴ

በመርገጥ አናገረው ፡፡ ሰውዬው ወደ ተክስተ ገብራይ መራው ፡፡ ተክስተ ዓለም ጤና ነው ብሎ ቤቱ ተኝቶ ነበር ፡፡ ተኽላይ ቤቱ ዘው ብሎ ገብቶ ከተኛበት ድንገት ያዘው ፡፡ ተከስተ ራቁቱን ነበር፡፡ እጭኖቹ መሐል በጉልበቱ መታው ፡፡ በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃ ዎች እቁባይ ሲላ ከሁለት ሌሎች ሰዎች ጋር ቤቱ መጠጥ እየ ጠጣ ሲጫወት ተኽላይ ዘድንገልና ረዳቶቹ እንደመብረቅ ወረ ዱበት ፡፡ ሦስቱም ሰዎች ሰክረው ነበር ፡፡ ከእቁባይ ጋር የነበሩት ሁለት ሰዎች ያን ምሽት በመረዳዳት ፊያሜታ ጊላይን በሯ ላይ ጠብቀው በጥይት የመቷት ፣ አጥፍተው ለመጥፋት የተሰለፉ ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ነበሩ ፡፡ ወዲያውኑ ሰፈለፉ ፡፡

ፊያሜታ ጊላይን ሲከታተሉ ነበር የዋሉት ፡፡ እንደነገረቻ ቸው ወደ ኒያላ በመሔድ ፊንታ ወደ ቤቷ በታክሲ ሔደች ፡፡ በመኪና ተከተሏት ፡፡ ቀድመው በሯ ላይ ጠበቋትና ከውጭ በር ላይ መንገድ ዘግተው ያዟት ፡፡

«ምንድነው?» አለች ፡፡
«እንደተነገረሽ ለምን አላደረግሽም?»
«አላደርግም ፡፡»
«አንቺ የመንግሥት ሰላይ!»
«አይደለሁም......»

በሁለት ጥይት ልቧ ላይ መተዋት ሮጡ ፡፡ ተኽላይ ራሱን ለመቆጣጠር አልቻለም ፡፡ ረዳቶቹ ባይዙት ኖሮ እዚያው ሊጨር ሳቸው ፈልጎ ነበር ፡፡

«ወዲበራኺ ተያዘ አይደለም?» አለ ዕቁባይ ደሙን ከፉ ላይ እየጠረገ ፡፡
«ሥዕላይ ማለትህ ነው!? አለ ተኽላይ ፡፡»
«ድሮውኑም እሱ ላይ እምነት አልነበረኝ! የውሻ ልጅ!» አለ ፡፡

፦

ተኽላይ ተነሰቶ ወደ ቻው ሆቴል በረረ ፡፡ ሰዓት ቢያልፍም የሆቴል ቤቱ ባር ገና አልተዘጋም ፡፡ ሥዕላይ በራኺ ከቀይ ኮከብ ዘማቾች ጋር ተዝናንቶ እያወራ ቢራ ይጠጣ ነበር ፡፡ ተኸላይ መጥቶ እጉኑ በርጋታ ቁጭ ካለ በኋላ ቢራ አዘዘ ፡፡ ጠምቶታል ፡፡ ጉሮሮው ተቃጥሏል ፡፡

ሥዕላይ «ዛሬ እደኑ እንዴት ነው?» ብሎ ተኽላይን በቀልድ ጠየቀው ።

«ዛሬ ሴቶች ሁሉ በጊዜ ተኝተዋል ። እግዜር ይይላቸውና!» ብሎ መለሰለት ።

ተኽላይ ቀስ ብሎ ቢራውን ጨለጠና ፣ «ፊያሜታ ጊላይ የሆነችውን ሰምተሀል?» አለው ።

«ምን ሆነች?»

«የሆነችውን የምታውቅ መሰሎኝ ነበር?»

«ምን ለማለት ፈልገህ ነው?»

«ሞታለች ። እና መሞቷን ታውቃለህ አይደለም? እንደሷ ያለች ቆንጆ ልጅ አሁን ጨካኖ ማን ይገድላል? ታውቀዋለህ ፣ እኔም አውቃለሁ ። ሁሊታችንም እናውቀዋለን......»

«እንዴት አውቃለሁ?»

«አርማይ የማያውቀው ምን ነገር አለ?»

ሥዕላይ አልተደናገጠም ። ተኽላይን ላንዳፍታ አተኩሮ ተመለከተው ።ዞር ፣ ዞር ብሎ ቡና ቤቱን በዓይኑ ቃኘ ። የሚያውቃቸው አንዳንድ የሕዝብ ደኅንነት ሰዎች ነበሩ ። ነገሩ ገባው ። እ'ንን ወደ ኪሱ ሊከት ሲል ተኽላይ አንቆ ያዘው ። ሌሎች የሕዝብ ደኅንነት ሰዎችም ተረባረቡበት ። ሥዕላይ ኪስ ውስጥ ከሳይናይድ መርዝ ሌላ ምንም ነገር አልተገኘም ።

«ተከሰተን ያዛችሁት? እሱ መሆን አለበት ወደኔ የመራችሁ ።»

«እንሒድ?» አለው ተኽላይ ።

«ምን ምርጫ ይኖረኛል? ሳልቀድምህ ቀደምከኝ አይደለም?»

«ምን ይጠቅመኛል?» አለ ተኽላይ ጥርሱን ነክሶ ።

«እንዴት? ራስ...ን እንኳን ደስ ያለህ ማለት አለብህ......»

«አዎ ፣ በእጄ ብገድልህ ኖሮ ራሴን አመሰግን ነበር ። ግን ምን ያደርጋል? እድለኛ አይደለሁም» አለው ።

«አሁን ጸጋዬ የት ነው?»

«ጋዘን ላይ ነው ። ምነው?»

«የሱ ጦስ ሳይሆን አይቀርም ለዚህ ያበቃን ፡፡ እና ደግሞ ያቺ ሸርሙጣ!»

ተኽላይ ዘድንግል እየተቆጨ ሥዕላይ በራኺን ይዞ ወጣ ፡፡ የቃናሽ ወንድሙ ምስል እየመጣበት በለው ፣ በለው ይለው ነበር ፡፡ ግን ሥዕላይ እድል አልሰጠውም ፡፡ እንደ በግ እየተነዳ ሔደ ፡፡ በሚቀጥለው አንድ ሰዓት ውስጥ ፓራዲዞ ቡና ቤት ሥር የሚገኝ «ሴል» ተከፈተ፡፡ኩሎኔል በትሩ ተሰማ ራሱ በቦታው ላይ ተገኝቶ ነበር ፡፡ እንቅልፉን ጠግቦ ገና የነቃ ወጣት መስሏል ፡፡ ጥርጣሬው ልክ ሆኖ በመገኘቱ በጣም ደስ ብሎታል ፡፡ በሌላ በኩል የጠላቶቹን ዝግጅትና ድርጅት በልቡ እያደነቀ ባንድ ፊት ደግሞ ይህ ሁሉ አፍንጫው ሥር ሲሠራ በመቆየቱ ውስጥ ውስጡን ይበሽቅ ነበር ፡፡

በሰለላና በግድያ ተግባር ላይ የተሰማሩ ፣ በቁጥር ከአምስት መቶ በላይ የሆኑ የሰዎች ስም ዝርዝርና እንዲሁም ለግድያ የሚፈለጉ የሲቪልና ወታደራዊ ባለሥልጣኖችና ኃላፊዎች ፣ የሕዝባዊ ድርጅቶች ተወካዮች ስም እንዳለ ተገኘ ፡፡ የኦሮማይን ተልእኮ በቅጥረኛነት የሚያስፈጽሙ ሰዎችም ስም ነበር ፡፡ ኩሎኔል በትሩ የሻለቃ ቃደሰ ቆሪቾን ስም ሲያይ ራሱን ይዞ ቀረ ፡፡ ይህ የመጨረሻ እንዳልሆነ ያውቃል ፡፡ ሥራው ገና መጀመሩ ነበር ፡፡ ክትትሉ ወዴት እንደሚያመራው ላንዳፍታ አሳሰበው ፡፡ እስከምን ድረስ ወደ ላይ ይሔድ ይሆን? የት ይሆን ነገሩ የሚቆመው?» የሚሉ ጥያቄዎች አእምሮው ላይ ተመላለሱበት ፡፡

የሥዕላይን ርጋታና ድፍረት በሆዱ እያደነቀ ፣ «ታዲያስ ሚስተር ኦሮማይ?» አለው ፡፡

«አለና.....» የሚል ነበር መልሱ
«እንደምትተባበረን ተስፋ አደርጋለሁ......»
«በምን?»
«ቢሮክራሲ ማነው?»

ሥዕላይ በራኺ መተባበር ነበረበት ፡፡ ሞቱን ቢመርጥም የሚገድለው ሰው አልነበረም ፡፡ መሰቃየት ደግሞ አልፈለገም ፡፡ በጀብሐ እሥር ቤት ያየው መከራና ፍዳ በቅቶታል ፡፡ በሚቀጥ

ለው ሰዓት ውስጥ ከተከላይ ዘድንግል ጋር በልዩ አይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ እንዲበር ተደረገ ። በዚያኑ ወቅት ምናልባት ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ኢንተሌጀንስ አገልግሎት ታሪክ ው ስጥ ታይቶ የማይታወቅ ፣ ሰዎችን በያሉበት አድኖ የመያዝ ሥራ ተጀምሮ ነበር ። ኰሎኔል በትሩ ምቹ ወንበሩ ላይ ወደኋላ ተለጥጦ ተቀመጠ ። ሲጠብቀው የነበረ ሽልማት ደረሰለት ። ግን፣ ከትትሉ ወዴት ያመራ ይሆን ? የሚለው ጥያቄ ከአእምሮው ላይ አልጠፋም ። ለጸጋዬ ኃይለማርያም የከፈለው ሦስት መቶ ብር በከንቱ አልነበረም ፣ የተፈለገውን ትርፍ አስገኝቷል ። ምስጋናውን ሁሉ ለራሱ አድርጎ ፈገግ አለ ። ንጋቱም ፈገግ ማለት ጀምሮአል ። ዓይኖቹን ሊከድን ሲል የስልክ ጥሪ መጣለት።

«ጸጋዬ ነኝ»
«እሺ ጸጋዬ ። የት ነህ?»
«ፊያሚታ ቤት ነኝ ። የምትረዳኝ ነገር አለኝ......»
«ደስ እያለኝ ። ምን ኖሮአል?»
«የሬሣ ሣጥን እፈልጋለሁ ።»

«ያውም በጣም ግሩም የሆነ ሣጥን ነው የምልክልህ ። ከዚህ የበለጠ ነገር በተገባት ነበር ። የጀግና ሰው ቀብር ። ገዳዮ ቿም ተይዘዋል ። አይዞህ» አለው ።

ከጧቱ ሦስት ሰዓት ገደማ ግሩም የሆነ የሬሣ ሣጥንና አራት ትላልቅ ጉንጉን አበባዎች ተጭነው ከኃዘኑ ቤት ደረሱ ። ጸጋዬ ደረቱ ላይ የሰካውን ቀይ ኮከብ አውጥቶ ፊያሚታ ጊላይ ደረት ላይ አደረገላት ። በአገር ልብስ አሸብርቃ የመላክ ሞት ውብ ሙሽራ በመምሰል ጸጥ ብላ ተኝታለች ።

የፊያሚታ ጊላይ ቀብር ከቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት ተፈ ጸመ ። ኰሎኔል በትሩ ፣ ሰለሞን በትረና ሌሎችም ከፍተኛ ሰዎች ቀብሩ ላይ ተገኝተው ነበር ።

«አይዞህ» አለው ሰለሞን ።
«ደስታና ሕይወት ገንዘቦቼ ነበሩ......»

«በ'ውነት መጽናናት አለብህ ፡፡ ሁላችንም በእቧ ሞት መጽ ናናት ይኖርብናል ፡፡ እንዱ ለሌላው ደስታና ሕይወት ራሱን አሳ ልፎ ሲሰጥ ማየት አያሳዝንም ፣ ያበረታታል እንጂ ፡፡ ለሌሎች ጥፋት ሳይሆን ለሌሎች ደስታና ሕይወት ብዙዎቻችን መስዋእት የምንሆንበት ቀን ሲመጣ ይታየኛል ፡፡ ጥሩ ምሳሌ ትታልን ነው የሔደችው ፡፡ ጥሩ አጀማመር ነው» አለው ፡፡

ቀጥሎ ያነጋገረው ኰሎኔል በትሩ ነበር ፡፡
«እንዲህ ዓይነቱ ነገር ሲደርስ ብርታት ይጠይቃል» አለው፡፡
«ስለማጥኑ አመሰግናለሁ» አለ ጸጋዬ ፡፡

«እንዳልኩት ሌላም ይገባት ነበር ፡፡ የእቧ ሞት ለብዙዎች ሕይወት ሆኗል ፡፡ ብዙ ነገር ከብዙ ጥፋት አድኗል ፡፡ ያንተንም ጥንቃቄ አደንቃለሁ......»

«ኦፕሬሽኑ እንዴት እየተካሔደ ነው? » ብሎ ጠየቀው ፡፡

«በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው ፡፡ ያሥመራን ሴል ሰብረ ናል ፡፡ ያዲሳባ ሴላቸውንም ዛሬ ወይም ነገ እንሰብረዋለን ፡፡ ለጊ ዜው ቢሮክራሲ አምልጦናል ፡፡ ግን የጊዜ ጉዳይ ነው ፡፡ ድሬዳዋ መሆኑን ፍንጭ አግኝተናል ፡፡ የገባበት ገብተን እንይዘዋለን ፡፡ በሕዝባዊ አሠራር ላይ እምነት ማሳደር ይኸውልህ ጥሩ ነው — ይከፍላል» ብሎ ቀጠለና ፣ «ቀደም ብላ ብትነግረን ኖሮ ሕይ ወቷ አይጠፋም ነበር ፡፡ ያሳዝናል» አለው ፡፡

«መወሰን አልቻለችም ፡፡ ድሮውንም ውሣኔ ማድረግ ያስ ቸግራታል ፡፡ ቃመነታለች ፡፡ ምናልባት በሕይወቷ ያደረገችው ትልቅ ውሣኔ ቢኖር እኔን አሳልፋ ላለመስጠት ያደረገችው ው ሣኔ ይሆናል ፡፡ እና ለሞቷ ምክንያት ሆነ» ብሎ ዝም አለ ፡፡

ሰው ሁሉ ሔዷል፡፡ ትቢያ ፡፡ ዐፈር ፡፡ ጥርኝ ዐፈር-ሕይወት ፡፡ ጸጋዬ ኃይለማርያም ብቻውን ወደኋላ ቀረ ፡፡ የሚያደርገው ነገር አልነበረውም ፡፡ ግን ፊያሜታ ጊላይን እዚያ ብቻዋን ጥሎአት መሔድ አንጀቱ እምቢ አለው ፡፡

ከላይ እስከ ታች ጥቁር በጥቁር የለበሰች አንድ ሴትም እን ዲሁ ወደኋላ ቀርታ ነበር ። እንዲያውም ከሴት ኃዘንተኞች ውስጥ ጥቁር በጥቁር የለበሰች እሷ ብቻ ነበረች ። የሐማሴን ሴቶች ለኃዘን ጥቁር የመልበስ ልማድ የላቸውም ።

ወደ ቀብር ሲሔዱ ነጭ በነጭ ለብሰው ነው ። ልቅሶ ቤት ሲደርሱ ያሸርጣሉ ፣ ወጣ እንዳሉ ሽርጡን ይፈታሉ ። ጌጣ ጌጥም አይቀራቸውም ። አጊጠው ሙታንን ይሸኛሉ ። ታዲያ ምን ይሁን? የሞተ ሞቷል ፣ የቀረው መኖር አለበት ። ሕይወት መቀጠል ይኖርባታል ። ሕይወት አጭር ናት ። ከሰው ረጅም ነገር ምንድነው? ምናልባት ጥላው ብቻ ነው ። ጸጋዬ ዞር ሲል አያት ። ሮማን ኅለተወርቅ ነበረች ። ወደ እሷ ሔደና ፣ «ማታ ብዙ ፈለኩሽ የት ጠፋሽ» አላት ።

ለጥያቄው መልስ ሳትሰጠው ፣ «እግዜር ያጥናህ» አለችው ። የሚለው ነገር አልነበረውም ። ዝም አለ ።

«ልብህ ወደ መቃብሯ አብርሐት ወርዶአል አይደለም?» አለች ። እንደገና ሊከዳት አልሞከረም ወይም አልፈለገም ። ታስታውሰኛለህ?...... አዎን በለኝ...... ሁልጊዜ?...... ምን ዓይነት ሴት ነኝ፣ እስቲ ባባትህ ንገረኝ...... ደደብ...... አባቴ ይሙት ደደብ ነህ...... የፈያሚታ ጊላይ ቃላት ትዝ አሉት ።

«ቀለበት መለዋወጥ ምንድነው? ባታውቀው ነው እንጂ እኔ ሕይወቴን ልለውጥልህ ነው...... ብላ በደብዳቤዋ ላይ ያስፈ ረችው ቃል ባሳቡ ተነበበው ።

«ካልሽ ፣ አዎን» አላት ።
«እና ሁልጊዜ ስታስታውሳት ትኖራለህ አይደለም?»

«ሮሚ ፣ ሕይወቷን የሰጠችኝ ልጅ መሆኗን አትርሺ ። አዎን አስታውሳታለሁ ። አሳቤ ውስጥ ትኖራለች ። ሌላ ምን ላደርግላት እችላለሁ? አብሬአት ወደ መቃብር አልወርድ ነገር......»

«ግን ልብህ ወደ መቃብሯ ወርዷል ። ከመቃብር በታችና በላይ የሆነ ልብ ምን ያደርጋል!» ካለች በኋላ ፣ የቃል ኪዳናች

ውን ቀለበት ከጣቷ ላይ አውልቃ እግሩ ሥር ወረወረችለት ። ወርቅ ። ዐፈር ። ዐፈርና ወርቅ ። ሕይወት ።

«ፍርድሽ ይህ ነው?» አላት ።

«ይኸው ነው» ብላ ለጠቀችና ፣ «መጥፎ እድል እቴ!» አለች ።

«ምን?»

«የምወዳቸው ወንዶች ለምን እንደሚከዱኝ አላውቅም! አገኝቼ ማጣት ያርባ ቀን እድሌ ነው መሰለኝ ። ቻው» ብላው እቀመበት ጥላው ሔደች ።

ሮማን ከፊቱ ፣ የፊያሜታ ጊላይ መቃብር ከኋላው ፣ በመካከላቸው ቆሞ ቀረ ። በመጨረሻ ሰው ብቻውን ነው ፣ብቸኛ ነው ። ብቸኛነት ተሰማው ። ልቡ የኃዘን እንጉርጉሮ አንጎራጎረ ። ልቡ የኃዘን እንጉርጉሮ የማያንጎራጉር ሰው አለ ይሆን? ግን ልናዳምጠው አንፈልግም ። ለምን ? ደስተኞች መሆን እንፈልጋለን ። ተስፋ ከመቁረጥ ተስፋ ማድረግ ይሻላልና ባናገኘውም ቅሉ ዘላለም እንሻዋለን ። ዘላለማዊ ተስፋ ፣ የኃዘንና የእንጉርጉሮ። ሰው ያለተስፋ ምንድነው? ተስፋ በልባችን ማሳደር አለብን ፣ ተስፋ በሌለበት ቦታም ቢሆን ።

እንባ እንባ ይለኛል
ይተናነቀኛል
ግን እንባ ከየት አባቱ!
ደርቋል ከረጢቱ
ሳቅ ሳቅም ይለኛል
ስቆ ላይስቅ ጥርሴ
ሲቃ እያለቀሰች
መከረኛ ነፍሴ ።

ጆምበሯ ለመጥለቅ አቆልቁላለች ። አድማሱ ቀልቷል ። ቀለበቷን በማማው ረግጦ ለጋት ። እንደ እውነቱ ከሆነ ቀለበቷን አልነበረም በማማው ረግጦ የለጋው ፣ የገዛ ሕይወቱን ነበር እንጂ ። ቻው ፊያሜታ አለ በልቡ ። መቃብሯ ጸጥ ብሎአል ።

ከመቃብር ጸጥታ ባሻገር የናቅፋ ተኩስ ተሰማው ፣ የጀግኖችን ደምጨኸት  እየሰማ ልቡ ወደዚያ ሔደ ። ሁሉን ትወዳለህ ፣ በመጨረሻም ሁሉን ታጣለህ ። ሴ ላ ቪ ! እሮማይ ።



. . . . ባሬስታው ከፊት መታጠቢያው ማህን ሥር ያለውን የውሀ ቧንቧ መዘውር ሔዶ ጫን ሲለው . . . በኮንክሪት የተቀበረ መስሎ ይታይ የነበረው ትልቅ ባኞ ተነስቶ ቆመ ፡፡ ሥዕላይ ባኞው አርፎበት የነበረበትን ጉድጓድ ተመለከተ ፡፡ የኤሌክትሪክ ብርሃን ኩሬ ጉድጓዱን ሞልቶታል ፡፡ ወደ ውስጥ የሚወስዱ ከብረት የተሠሩ ደረጃዎች ይታያሉ ፡፡ ሥዕላይ ወደ ውስጥ ዘለቀ ፡፡ ባኞው ቦታው ተመለሰ . . .

. . . «የመረጃ ሥራ የመረጃ ሰዎች ብቻ የሥራ ክልል አይደለም፤ ባሁኑ ጊዜ ሕዝባዊ ባሕርይና መሠረት ሊኖረው ይገባል ፡፡ ሁሉም ለአብዮቱና ላገሩ አንድነት ሰላይ መሆን አለበት ፡፡ አብዮተኛ ነኝ ማለት አይበቃም . . . ጓድ ፣ መለኪያው ተግባር ነው» . . .

. . . ካሌብ ካዶሊስ የቀይ ባሕርን ሞገድ ሲገዛ ፣ ልብነ ድንግል በዱር ሲንከራተት ፣ ዮሐንስ መተማ ላይ አንገቱን ለሠይፍ ሲሰጥ ፣ አሉላ አባነጋ ፣ «ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ ተፈጥሮ በር ነው» እያለ ዶጋሊ ላይ ቆሞ በለው ሲል ፣ ቴዎድሮስ ፣ «የቱ ወንድ ክንዴን ይይዛል!» ብሎ መቅደላ ላይ የመጨረሻ ጥይቱን ሲጠጣ፤ ምኒልክና ጣይቱ አድዋ ላይ «ድሉ ያንተ ነው ያገሬ ጀግና!»ሲሉ . . .

. . .ሳመችኝ ፡፡ ትንፋሿ እንደ ዱር ጽጌረዳ ሁልጊዜ ደስ ይላል ፡፡ እየተነጫነጨች የግዷን ተነሳች ፡፡ ለመልበስ ጊዜ አልፈጀባትም ፡፡ በቀላሉ የማጌጥና የመዋብ ችሎታ አላት ፡፡ ወይም የወጣትነት ዕድሜዋ ይሆናል የሚረዳት ፡፡ መኳኳል አታበዛም ፡፡ . . .

ከመጽሐፉ ውስጥ የተወሰዱ ፡፡

ዋጋው ብር 10·